ያልታበሱ ዕንባዎች



ዘጠነኛ ዕትም

አሰፋ በቀለ ገ/የሱስ

"መጽሐፉ ሰው የመሆንን ነገር ብቻ ሳይሆን
ዜጋ የመሆንንም ጉዳይ ይፈትሻል!"
(ገምጋሚዎች)

ያልታበሱ ዕንባዎች

(ወጥ ታሪክ በልዩ አተራረክ)

እርስዎ እንደምንም ይጀምሩት፣
ጨብጦ ይዞ ራሱ ያስጨርስዎታል።

ከ

አሰፋ በቀለ ገ/የሱስ

መጀመሪያ ጥቅምት 2002 ዓ.ም ታተመ
እንደገና ሚያዝያ 2002 ታተመ
እንደገና መስከረም 2003 ታተመ
እንደገና ጥር 2004 ታተመ
እንደገና ሚያዝያ 2004 ታተመ
እንደገና ሀምሌ 2005 ታተመ
እንደገና ህዳር 2006 ታተመ

የደራሲው መብት በህግ የተጠበቀ ነው።

ይህን መጽሐፍ ያለደራሲው ፈቃድ በማናቸውም መንገድ ማባዛት፣ ማተምና ወደ ሌላ ቋንቋ መተርጎም በህግ ያስጠይቃል።

ምስጋና

ይህ መጽሐፍ እዚህ ደረጃ ይደረስ ዘንድ ረቂቁን በማንበብ ገንቢ አስተያየት ከመስጠት ጀምሮ በኮምፒውተር ታይፕ ሥራ፣ ፕሪንት በማድረግና በሌሎችም ሁኔታዎች ድጋፍና ዕርዳታ ላደረጋችሁልኝ ሁሉ የከበረ ምስጋናዬ በያላችሁበት ይድረሳችሁ!!

ደራሲው
አሰፋ በቀለ ገብረየሱስ

መታሰቢያ

ይህ መጽሐፍ ኢትዮጵያን በተፈራረቁበት የግፍና የጭካኔ አገዛዝ ዘመናት ሁሉ በሀሳብ ልዩነታቸው ብቻ ህይወታቸውን ላጡ፣ ለተጋዙ፣ በእስር ለማቀቁ፣ ከሀገር ለተሰደዱ፣ የአካልና የአዕምሮ ጉዳት ለደረሰባቸውና ኑሮአቸው ተጎሳቁሎ ህይወታቸው ለተበላሸ ኢትዮጵያዊያን ወገኖቼ ሁሉ መታሰቢያ ይሁንልኝ።

ደራሲው

አሰፋ በቀለ ገብረየሱስ

ምዕራፍ አንድ

የታላቁ ምሥራቅ አፍሪቃ ስምጥ ሸለቆ አካል በሆነ ተራተራማ ቦታ ላይ በተቆረቆረችው ዲላ ከተማ ውስጥ መኖር ከጀመረ ሰባት ዓመት ሞላው። ነገር ግን በብርዳማነቷ በምትታወቀው መሀል ሜዳ ከተማ ተወልዶ ያደገ በመሆኑ የዲላ ከተማን ሙቀት በቅጡ ሊላመደው አልቻለም። በተለይ ከረፋዱ አራት ሰዓት ጀምሮ እስከ ቀኑ አስር ሰዓት ድረስ የሚወርደው የፀሀይ ንዳድ መላ ሰውነቱን እንደ ሰም እያቀለጠ ያቅበጠብጠዋል። እንደ መፍትሄ የሚጠቀምበት ዘዴ አካላቱን በቀዝቃዛ ውሃ መለቃለቅ ብቻ ነው።

ነርስ አስቻለው ፍስሀ ዛሬም ከሚሰራበት ዲላ ሆስፒታል ወደ ዜሮ አምስት ቀበሌ የሚገሰግሰው ከቤቱ ደርሶ አካላቱን ቀዝቃዛ ባለ ውሃ እስከሚለቃለቅ ድረስ እየቸኮለ ነው። ወሩ ታህሳስ፣ ሰዓቱ ደግሞ ዘጠኝ አካባቢ በመሆኑ ሙቀቱ ወደር አልነበረውም። ጥቁር ቆዳ ጃኬቱን ትከሻው ላይ በማንጠልጠል በጥቁር ቡኒ ሱሪው ላይ ነጭ ሸሚዝ ለብሶ ክሩቱ እያንቦገቦገ በመገስገስ ደርሶ ተዘግቶ የዋለ ቤቱን ሲከፍተው ግን የትኩሳና የድካሙን ያህል በደስታ አልተቀበለውም።

«ጉ! ምን ጉድ ነው ባካችሁ!?» አለ በሩን ከፊት አድርጎ እጁታውን እንደያዘ። ወደ ውስጥ መልከት ሲል ወለሉ አስጠላው። ትናንት ማታ የቅርብ ጓደኞቹ የሆኑት በልሁ ተገኔና መርዕድ አሹቱ ጫት ሲቅሙበት አምሽተዋል። የቢያ ውጤት የሆኑ የጫት ገራባ፣ የከሰል ማንደጃ ከነአመዱ፣ የሻይ ማፊያ በራድ፣ መጠጫ ብርጭቆዎች ሁሉ በወለሉ ላይ ብትንትን፣ ዝርክርክ እንዳሉ ናቸው። የወንደ ላጤ አልጋው እንኳ አልተነጠፈም፣ አንሶላና ብርድ ልብሱ ምስቅልቅል ብለው የአልጋ ልብሱም በአንድ ወገን ተንዘርፏል። «ብቻ የኔ ነገር እንዲህ ሆኖ ይቅር!?» አለና በር ላይ ቆሞ ለረጂም ጊዜ ተመለከተው።

«አየ ትርፌ!» አለ እንደገና ወደ ውስጥ ገባ እያለ። በአንድ እጁ ጃኬቱን በሌላው ሸንጡን ያዝ አድርጎ መሀል ወለሉ ላይ በመቆም «አጉል ልማድ ካስለመድሽኝ በኋላ ጥለሽኝ ጠፍተሽ እንዲህ ታዘበራርቂኝ?» ሲል ከበርካታ ወራት በፊት ድንገትና በማያውቀው ምክንያት የጠፋችበትን የቤት ሰራተኛውን አማረራት። ጃኬቱን ወንበር ላይ ጣል አድርጎ ያንን ቤት ለማስተካከል ቃጣ። ግን ደግሞ በጣም ስለደከመው ትንሽ ለማረፍ ፈልጎ ወደ አልጋው አለፈ። የተንዘረፈፈውን የአልጋ ልብስ ብቻ ሰብሰብ አድርጎ ጫማውንም ሳያወልቅ እግሩን በጎን በኩል አንጠልጥሎ በጀርባው ጋለል አለ። ትርፌን አሁንም አሰባት። በእሷ አለመኖር ኑሮው ከመመሰቃቀሉም በላይ አጠፋፏ ድንገት ስለነበረ የደህንነቷም ነገር ያሳስበው ጀመር።

በትርፌ አለመኖር በቤት ውስጥ የተከሰተበትን አለመመቸት ሲያስብ ቆይቶ የመስሪያ ቤቱም ሁኔታ ድንገት ከፊቱ ድቅን አለበት። አስቻለው በዲላ ሆስፒታል ውስጥ ሰላም የለውም፣ የሰው ተባይ እየነከሰው ተቸግሯል። በቢያው ልክ የስራ ሞራሉ እየወደቀና እየተሸረሸረ ሄዶበታል።

ለዚህ ሁኔታ ዋና መነሻ የሆነው ከስምንት ዓመታት በፊት በዲላና አካባቢዋ ተከስቶ የነበረው የማጅራት ገትር ወረርሽኝ በሽታ ነበር። በተለይ በከተማዋ በርካታ

ህጻናት እየሞቱ በየቀኑ ቀብር ሆኖ በየቤታቸው ድንኳን እየተተከለ ህዝቡ አልቃሽና ለቀስተኛ ሆኖ ዲላ ከተማ መዓት የወረደባት መስላ ነበር::

ዘመኑ ደግሞ በራሱ በሽተኛ፣ አምባገነኖች ዘውድ ሳይጭኑ የነገሱበት፣ አውር ድንብራቸውን ሀገር የሚመሩበት፣ ሳያውቁ የሚፈላሰፉበትና በተለይ ኣድሬዎቻቸው በዕስት ዓይነት ቀለም ካኪ ልብስ ራሳቸውን እየጀቡኑ ምርጥ ዜማዎቻቸውን በይፋ ያወጁበት ወቅት ነበር:: በዚያው መጠን ዜጎች በሞትና በስደት፣ እንግልትና ውክቢያ፣ አበሳ የሚያዩበትና መላ ሀገሪቱ በመጤ ፖለቲካ ወረርሽኝ የምትታመስበት የቅስፈት ዘመን ነው:: ከማጅራት ገትር ወረርሽኝ ጋር ተያይዞ በዲላ ሆስፒታል ሰራተኞች ላይ የሥነ ልቦና ቀውስ ያስከተለ መመሪያም ተላልፏል:: «...የህክምናም ሆነ የክትባት አገልግሎት ቅድሚያ ለጓዶችና ለቤተሰቦቻቸው ይሰጥ» የሚል::

ነርስ አስቻለው ፍሰሀ ቀድሞም ቢሆን በካኪ ለባሾች ላይ ጥሩ አመለካከት አልነበረውም:: ከዓመታት በፊት በገንዘብ ይረዳው የነበረውን ወንድሙን ገድለውበት ተቸግሮ እንዲማር አድርገውታል:: ከዚያም በላይ አልፍ አዕላፍን እንደ ገደሉ ልቦናው ያውቃልና ፖለቲካዊ መሠረታቸውም በመግደልና በማስገደል ላይ የተገነባ መሆኑን ይረዳል:: ራስ ወዳድ መሆናቸውን በውል ተገንዝቦታል:: በዚያ ሰሞን ያስተላለፉት መመሪያም የዚሁ ማንነታቸው መገለጫ ነውና አስቻለው በሁኔታው እንጀቱ ተቃጥሏል:: አንድ ቀን ጠዋት ደግሞ አስቻለው በበሽታው የተያዙ ሰዎችን ተራ በተራ እየጠራ የህክምና ዕርዳታ ይሰጥ በነበረበት ክፍል ውስጥ አንዲት ኑሮ ደልቷት የወፈረች፣ ጉንጯ ሊፈነዳ የደረሰ፣ ቀላ ያለች ሴት ክፍሉን ከፍታ ገባች:: በአንገቷ ላይ የተጋደመው የወርቅ ሀብልና በጣቶቿ ላይ የተደረደሩት የአልማዝ ጌጣጌጦች እንደ ፀሐይ ያበራሉ::

አስቻለው በኢጋጣሚ የሴትዮዋን ቤተሰባዊ መሰረት ያውቃል:: አመጣጧ የዚያ መመሪያ ውጤት መሆኑ ስለገባው ሰውነቱ በንዴት ተለዋውጦ በዚሁ ንዴት ውስጥ ሆኖ «ማን ጠራዎት?» ሲል አፈጠጠባት::

ሴትዮዋ ለአስቻለው ቁጣ ቦታ አልሰጠችውም፣ እንዲያውም ኩራ ብላ ወደ አስቻለው ጠጋ በማለት አንዲት ወረቀት ዘረጋችለት:: ወረቀቷን የንጥቂያ ያህል ከእጇ ወስዶ ሲያነባት የዘጠኝ ሰዎች ስም ተዘርዝሮ ቅድሚያ የክትባት አገልግሎት እንዲሰጣቸው የታዘዘበት ማስታወሻ ሆና አገኛት:: ወረቀቷን ለሴትዮዋ መልሶ በመዘርጋት «ይቅርታ የኔ እመቤት፣ በቅድሚያ በበሽታው ተይዘው የሚሰቃዩትን ልርዳና የእርስዎን በኋላ! ውጭ ይጠብቁኝ::» አላት::

ወይዘሮዋ በቁጣ ስሜት ግንባሯ ቋጥርጥር አለ:: ለጠጥ ብላ ወረቀቷን ከአስቻለው እጅ እየተቀበለች «ጓድ ባርናባስን ልጥራቸው እንዴ?» ስትል ጠየቀችው::

«ሰኔ አያስፈልገኝም:: የሚረዳዎት ነገር ካለ እዚያው ጨርሱ!» አለና ፊቱን ከሴትዮዋ ላይ መልሶ ስራውን ቀጠለ:: ወይዘሮዋ ከክፍሉ ወጣች:: ከትንሽ ደቂቃዎች በኋላ ግን ያቺ ሴትና ባርናባስ የአስቻለውን ቢሮ ከፍተው ተከታትለው ነው:: ባርናባስ ብጭጭ ያለ ቀይ ነው፤ ዕድሜው ወደ ሃምሳ አምስት የሚጠጋ ቀጭን ረጅም:: ደማቁን ሰማያዊ ካኪ ለብሶ ወርቃማ ቀለም ያላት ጠበብ ያለች

መነፅር አድርጓል:: የሆስፒታሉ የአስተዳደር አገልግሎት ሃላፊና የፓርቲ መሠረታዊ ድርጅት አንደኛ ፀሃፊ ነው::

«አቶ አስቻለው!» ሲል ጠራው ባርናባስ ኩራ ባለ አነጋገር::

«አቤት» አለው አስቻለው በንቀት ስሜት::

«የወይዘሮ ጥበቧን ማንነት አታውቅም እንዴ?»

«በትክክል አላውቅም»

«የአውራጃችን ፓርቲ ኮሚቴ የድርጅት ጉዳይ ሃላፊ የሆነው የጓድ ሙሉነህ ባለቤት ናት እኮ!»

«ታዲያ ይኼ የምንነት እንጂ የማንነት መገለጫ ነው እንዴ?»

«ምን?» አለ ባርናባስ ድንገት ኩም ብሎ:: መነፅሩን አውልቆ አስቻለውን በሌጣ ዓይኑ እየተመለከተ «ምንድነው ልዩነቱ?» ሲልም እንደገና ጠየቀው::

«አሁን ምን ልርዳችሁ? ክትባቱን ቢተመለከተ ከሆነ ለወይዘሮዋ ነግሬያቸዋለሁ::» አለ አስቻለው ዓይኑን በሁለቱም ላይ ሰካ ነቀል እያደረገ::

«መመሪያ አትቀበልም ማለት ነው?»

«በበኩሌ ‹ቅድሚያ ህይወት ማዳን› የሚለውን የህክምና መርህና ሥነ-ምግባር ማክበሬ ነው::»

ባርናባስ ከዚያ በኋላ ምንም አላለም:: ስስ ከንፈሮቹን እንደ እንሽላሊት ጅራት ወዲያ ወዲህ እያንቀሳቀሰ ቀጫጭን ዓይኖቹን በአስቻለው ላይ ሰክቶ ለአፍታ ያህል ከተመለከተው በኋላ ሴትዮዋን አስከትሎ ከክፍሉ ወጣ::

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አስቻለውና ባርናባስ አይጥና ድመት ሆነው ይኖራሉ:: በሆስፒታሉ ቅጥር ግቢ ባርናባስ ስልጣኑን በመጠቀም አስቻለውን ብዙ ጎድቶታል:: በሆስፒታሉ ቅጥር ግቢ ውስጥ ለሠራተኞች መኖሪያ ተብለው ከተሰሩ ቤቶች እንዳያገኝ እንኳ በሰበብ አስባብ ተራውን ብዙ ጊዜ አሳልፎበታል:: አጫጭር የሥልጠና ኮርሶችን እንዳይካፈልም አድርጎታል:: የአጭር ጊዜ ፈቃድ ፈጽሞ አይሰጠውም:: ብዛግይተህ ሥራ ገባህ፣ ቀድመህ ከሥራ ወጣህ...ወዘተ› በሚል ሰበብ ፋይሉን በጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ሞልቶበታል:: የዚያች ዕለት መዘዝ አልለት ብሎት ከችግሩ ጋር አብሮ ይኖራል::

አስቻለው ዛሬም አልጋው ላይ ጋለል እንዳለ በዚህ አስቀያሚ የሥራ ሁኔታው ዙሪያ ሲያስብና ሲያሰላስል ቆይቶ በቁጭት ስሜት በረጅሙ ተነፈሰና እንደገና ወደ ግል ህይወቱ ተመለሰ:: በቅርቡ ደስ በሚል የፍቅር ህይወት ውስጥ ገብቷል:: በቁልምጫ ‹ሔዪ› የሚላት ፍቅረኛው ሔዋን ተስፋዬ በአዕምሮው ውስጥ ድንገት ብቅ አለችበትና ሳያውቀው ፈገግ አለ:: ግን ደግሞ ለፍቅራቸው ውጋት የሆነ ሃሳብ ስላለ በዚያ ጉዳይ ላይ ያስብ ጀመር:: ሆኖም ብዙም ሳይቆይ የቤቱ በር ድንገት ተንኳኳ::

«ማነው?» አለ ከሀሳቡ ብንን በማለት:: ደነገጠ:: የቤቱ ሁኔታ አሳፈረው:: ከተንጋለለበት ቀና ብሎ እንደ አዲስ ወለሉን በዓይኑ ሲቃኝ እንግዳዋ ደግሞ ወደ ውስጥ ገባች፤ መምህርት ታፈሡ እንግዳሰው::

«ታፈሥ ነሽ እንዴ?» አለና ከአልጋው ላይ ወርዶ መሬት ላይ ቆመ:: የቤቱ ሁኔታ በፈጠረበት የሀፍረት ስሜት ውስጥ ሆኖ ታፈሡን መልከት አላት::

ታፈሡ ቀይ ቆንጆ! ቁመቷ መለሎ! ሰውነቷ ደልደል ያለ! ዕድሜዋ ከለላ ዘለል ያለ የምትመስል ሴት ወይዘሮ ናት:: ስልክክ ያለ አፍንጫዋ ቅርፃቸው አሞራ ቅድ ከሆነው ትልልቅ ዓይኖቿ ጋር ሲታይ የተለየ የሴትነት ውበት

እንናጅቷታል። በጉሯ ረጅምና የጥቁር ዞማ ነው። ጉንጯ ሳይወፍር ሳይቀጥን ደልደል ያለ ሆኖ ከቅላቷ ጋር ጥሬቱ እንደ ፀሀይ ያበራል። በስሱቱ ደመቅ ያለ ቡኒ ቀለም ያለው ኮትና ጉርድ ቀሚስ ለብሳለች። ቦርሳዋን እንግታ የማስተማሪያ ቁሳቁሶቿን በግራ እጇ ይዛለች። ገና የቤቱን ደፍ እንደረገጠች መጀመሪያ ያየችው ያን ዝርክርክ ያለ የአስቻለውን ቤት ወለል ነው። ፊቷን ጭምድድ አድርጋ ጉንጯን በቀኝ እጇ መዳፍ በማስደገፍ «ውይይ...! አስቻለው ምን ነካህ?» አለችው።

«እንዚሪያ በልሁና መርዕድ ናቸው እኮ እንዲህ የሚሰሩኝ!» አላት በሀፍረት ስሜት ጉንጩ ጭምድድ፣ ዓይኖቹ ጥብብ እያሉ።

«ታዲያ ሲያበቁ አይጠራርጉትም እንዴ?»

«ሌላ ጊዜ ሲቅሙ ሲሉ ነው ትገዝ የሚላቸው።»

«ሌዲያ! አሁንስ አበዛችሁት!» አለችና ወደ አስቻለው ጠጋ ብላ ሳመችውና የማስተማሪያ ቁሳቁሶቿን ጠረጴዛ ላይ አስቀምጣ መጥረጊያ አነሳች።

«ታፈሶ! አንቺ ልትጠርጊ?» አላት አስቻለው እንደ ማፈር እያለ።

«ምን ላርግ ታዲያ! አንተ እንደሆንክ ትርፌ በጋሸው ከሄዶች ወዲህ መላው ጠፍቶሃል። ወይ እንግዲህ አግብተህ ይለይልህ!» አለችው አጎንብሳ ፈገግ እያለች።

«ይቀራል ብለሽ ነው ታፈሶ?»

«እንዲያውም አንተና ሔዩ ጉዳችሁ ፈልቷል፣ ቶሎ ተጠቃለሉ።» አለችው ታፈሡ አሁንም አጎንብሳ ሳቅ እያለች።

«ጉዳችሁ?» አለ አስቻለው ድንግጥ ብሎ።

«አዎ፣ ጉዳችሁ! መምህርት ሸዋዬ ማን እንደነገራት አላውቅም፣ ዛሬ ትምህርት ቤት ውስጥ ስትጨፍርብኝ ዋለች። አሁንም የመጣሁት ‹አገር አማን› ብለህ ወደዚያ ቤት እንዳትሄድ ልነግርህ ነው።»

«ትቀልጂለሽ እንዴ ታፈሶ?» አለ አስቻለው አሁንም በድንጋጤ ስሜት መላ ሰውነቱ እየተወረረ።

«የምሬን ነው። ‹እህቴን ለአበ-ልጅሽ አቃጠርሽ› አለችኝ።»

«ምን አልሻት ታዲያ?»

«አበጀሁ! ገና እጋባቸዋለሁ አልኳታ!»

«እንዲሁ ብለሽ?»

«ምን ላድርግ ታዲያ? ብታይ እኮ መሬት ካልሰነጠኩ፣ ሰማይ ካልሰበርኩ ነው ያለችው። ያወረደችብኝ ስድብ ቀላል መሰለህ?»

«እስከዚህ ድረስ?»

«ብታይ ተቃጥላለች።» አለችና ታፈሡ መጥረጊያዋን ደገፍ ብላ በመቆም አስቻለውን እየተመለከተች «ቆይ ግን፣ ለመሆኑ አንተስ ብትሆን የአንተና የሔዩ ጉዳይ ከሸዋዬ ተደብቆ ይኖራል ብለህ ታስባለህ?» ስትል ጠየቀችው።

«እሱማ እንዴት ይሆናል? ለጊዜው የሔዋን ሁኔታ አስቸገረኝ እንጂ!» አላት ጭንቅ ጥብብ እያለው።

«ያ ችግር እንዳለ እኔም አውቃለሁ። ሔዩ በጣም ስሱ ናት፣ ሽቁጥቁጥ። ያም ሆኖ ከእንግዲህ እንዴት መያዝ ነው ያለባችሁ።» አለችው።

አስቻለው ሰማይና መሬት የተደበላለቀበት መሰለው። በታፈሡ የተገለጸለት የሸዋዬ ሁኔታና የሔዋን ተፈጥሮአዊ ባህሪ ፈጽሞ አይጣጣምም። ሔዋንን የገባችበት

መከራ በሀሳቡ ታየውና መንፈሱ በጭንቀት ተወጠረ። ከዚያ በኋላ ምንም ቃል ሳይተነፍስ ጸጥ እንዳለ ታፈሡ ቤቱን ጠርጋ ጨረሰች። እሷም ወደ ቤቷ እሱም ከጓደኞቹ ጋር እራት ወደሚበሉበት ‹ዋርካው ምግብ ቤት› ተብሎ ወደሚታወቀው ሆቴል ለመሄድ ተነሳና አብረው ከቤት ወጡ። በዚሁ ጉዳይ ዙሪያ እየተነጋገሩ አብረው ጥቂት ተጓዙና ታፈሡ ወደ ቤቷ ገባች። እሱም ወደ ዋርካው ምግብ ቤት አመራ።

ገና አሥራ አንድ ሰዓት አካባቢ ስለሆነ በዚያ ሰዓት ጓደኞቹ ለእራት እንደማይመጡ ያውቃል። እሱ ግን ከምግብ ቤቱ ደረሰና ጥግ ሥር ፊንጠር ብሎ በምትገኝ ጠረጴዛና ወንበር ላይ ቁጭ በማለት ስለ ሔዋንና ሸዋዬ ፍጥጫ ማሰብ ጀመረ። በዚያውም የእሱንና የሔዋንን ፍቅር አጀማመርና ሂደት ወደ ኋላ እያጠነጠነ በዓይነ ህሊናው ይዳስሰው ጀመር።

ቀድሞ ነገር መጀመሪያ የሚተዋወቁት አስቻለውና ሸዋዬ ነበሩ፣ ባለፈው ሰኔ ወር በአንድ መኪና ላይ ተሳፍረው ከአዋሳ ወደ ዲላ በመጓዝ ላይ በነበሩበት ቀን። ያ ጊዜ ደግሞ ‹ሁሉም ነገር ወደ ጦር ግንባር› የሚል መፈክር ተግባር ላይ የዋለበት ወቅት ስለነበር በህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ዕጥረት የትራንስፖርት ችግር ህዝብን የሚያተራምስበት ወቅት ነው። አስቻለውና ሸዋዬም የዚሁ ችግር ሰለባ ሆነው በአዋሳ የአውቶብስ መናኸሪያ ውስጥ ሲንገላቱ ውለዋል።

ከቀኑ ስምንት ሰዓት አካባቢ አንድ የህዝብ ማመላለሻ ሊዮንቺን ወደ መናኸሪያው ትገባና ረዳቱ ‹ዲላ! ዲላ!› ሲል ይጮሃል። የዲላ ተጓዦች ወደ መኪናዋ ይሮጣሉ። ‹ሰልፍ! ሰልፍ! ሰልፍ!› ረዳቱ። ሰልፍ ቢጤ ይያዛል። አስቻለው ከፊት፣ ሸዋዬ ከኋላው ሆነው ይሰለፋሉ። የመኪናው በር ሲከፈት ቀድሞ ለመግባት ሲባል የሚፈጠረውን ግፊያ ከወዲሁ የፈራችው ሸዋዬ አስቻለውን ትንተል አድርጋ «እባክህ የኔ ወንድም፣ ቀድመህ ከገባህ ቦታ ብትይዝልኝ!» ስትል በልመና ዓይነት ጠየቀችው።

«ከቻልኩ እሺ» አላት አስቻለው።

የመኪናዋ በር ሲከፈት ግፊያው ጦፈ። ጉልበት ያለው ሲገባ የሌለው ቀረ። በእርግጥም ሸዋዬ እንደፈራችው ተገፍትራ ቀረች። ኋላ ላይ ግን መኪናዋ ልትንቀሳቀስ ስትል ‹የኔ እህት! የእኔ እህት!› የሚል ድምጽ ሰማች። ዞር ስትል አስቻለው ነው። እንገቱን በመስኮት አውጥቶ ሲጠቅሳት አየችው። የደመነፍሷን ወደ መኪናው ሮጣ ገባች። አስቻለው በያዘላት ወንበር ላይ ከጎኑ ቁጭ ብላ ጉዞው ወደ ዲላ ተጀመረ።

ሸዋዬ መኪና እንግኝታ በመሳፈሯ የተደሰተችውን ያህል የዕለቱ ጉዞዋ ግን ወትሮ ከምታደርገው ለየት ብሎባት ትገረማለች። እንደ አስቻለው ያሉ ዕድሜአቸው ከሃያ ስድስት እስከ ሃያ ሰባት ዓመት የሚሆናቸው ወጣቶች አብረዋት ከተቀመጡ በአንድ ወይም በሌላ ሰበብ ጎንተል ሳያደርጓት ቀርተው አያውቁም። ‹የት ነሽ? ከየት ነህ...› በሚል ሰበብ ጨዋታ ይጀመርና በዚያው ትውውቅ፣ በዚያው መግባባትና

መቀራረብ እየተፈጠረ ሰላም ሰላም ይከተል ነበር። አስቻለው ግን ምንም አላላትም። አይኑን በአንዲት መጽሀፍ ላይ ተክሎ እያነበበ ዝም ብሎ ይጓጓል። መሲናዋ ብዙ ተጉዛ ይርጋለም አካባቢ ስትደርስ ራሷ ሸዋዬ ወሬ ጀመረች።

«ይቅርታ የኔ ወንድም፤ ዲላ ነው የምትኖረው?»

«አዎ» አላት አስቻለው።

«ሰው ብጠይቅህ ታውቅ ይሆን?»

«ማን የሚባል?»

«ታፈሡ እንግዳሰው?»

«ምን ዓይነት ናት?» ሲል ጠየቃት የሚያውቃት ታፈሡ ልትሆን እንደምትችል ልቦናው እያወቀ።

ሸዋዬ ጥብቅ ባለ አነጋገር «ቀይ ቆንጆ!» አለችና «መምህርት ናት፤ ባለቤቷ ደግሞ የማዘጋጃ ቤት መሐንዲስ።» አለችው።

«ሳላውቃት አልቀርም፤ ግን ምንሽ ናት?»

«የትምህርት ቤት ጓደኛዬ ነበረች። ኮተቤ መምህራን ኮሌጅ ስንማር አንድ መኝታ ክፍል ውስጥ ነበርን። ከምረቃ በኋላ ግን እኔ ወደ ያቤሎ ተመድቤ ስሄድ እሷ በትዳር ምክንያት ዲላ ቀረች። አሁን ግን እኔም ወደ ዲላ ተዛውሬ ሪፖርት ላደርግ እየሄድኩ ነው። እማርፈው እሷ ጋር ነው።» ካለች በኋላ «ግን ቤቷን ታውቀዋለህ?» ስትል ጠየቀችው።

«ይህን ያህል የምትቀራረቡ ከሆናችሁማ አደርስሻለሁ» አላት ፈገግ ብሎ እየተ እያደረጋት።

«እንዴ! እኔና ታፈ! እንኳን እኔ፤ በዚያ ዘመን አብሮን የተማረ ሁሉ እሷን የማያውቅ የለም፤ እንዲያውም በቅፅል ስም ነበር የምንጠራት።»

«ማን ትሏት ነበር?»

«እቴጌ እትደፈር»

አስቻለው ፈገግ ብሎ ሸዋዬን እያየ «እንዴት አወጣችሁላት?» ሲል ጠየቃት።

«ያን ለመሰለ ቁንጅናዋ፤ ያን ለመሰለ ውብትና ቁመናዋ የማይረግፍላት ወንድ አልነበረም። ታፈ ግን ፊት አትሰጥም። የቆንጆ ኩስታራ ናት። በዚህ ምክንያት ነው።» ስትለው አስቻለው በመገረም ዓይነት ሸዋዬን መልከት እያለ ሀሆዱ ደግሞ እውነትም በደንብ ታውቃታለች፣ እያለ ዓይኑን ወደ መጽሐፉ መለሰ።

«ባለቤቷስ ደህና ነው?» ስትል ሸዋዬ እንደገና ጠየቀችው።

«ደህና ነው። ለጊዜው ግን ወደ ውጭ ሄዷል»

«የት? መቼ?»

«ወደ ስዊድን ከሄደ ጥቂት ወራት አለፉት።»

«ይመለሳል ወይስ...?»

«ዛሬ ጊዜ ወደ ውጭ የሄደ ይመለሳል ብለሽ ነው? ለነገሩ ለትምህርት ነው የተላከው፤ ነገር ግን ሲመቸው ቤተሰቡን ይወስድ እንደሆን እንጂ ይመለስ እንኳ አይመስለኝም።»

«ውይይ...» ብላ ሸዋዬ ትንሽ ከቆየች በኋላ አሁንም ጨዋታ ጀመረች።

«እንደው ምን ዓይነት መጽሐፍ ብትይዝ ነው ይህን ያህል ቀልብህን የያዘው?» ስትል ጠየቀችው።

አስቻለው የመጽሐፉን ርዕስ እያሳየ «ይኸው» አላት። የመጽሐፉ ርዕስ 'ስመመን' የሚል ነበር።

«አሃ...ለካ ስመመን ውስጥ ገብተህ ነው!» አለችና «ኪኪኪኪ...» ብላ ሳቀች።

«እኔ እንኳ አልገባሁም፤ የዘውትን እያየሁ ነው።»

«እኮ! በዚያውም የራስህን እያስላሰልክ! ኪም ኪም- ኪም- ኪም...»

«እስከ አሁን አልገባሁም!» አላት አስቻለው ፈገግ ብሎ እየተ እያፈረጋት።

«እስከ አሁን ያልሞከርህ ከሆነማ ወዮልህ! ከእንግዲህ ወዲያ የሚጀምረው ጭራሽ ጨርቅህን ያስጥልሃል! ኪኪኪኪ...»

በዚህ ጊዜ አስቻለውም ከት ብሎ ሳቀ። በሸዋዬ ሁኔታ እንደ መገረም ብሎ እግረ መንገዱን ተክለ ሰውነቷን ሰለል ሲያደርገው መልኳ የቀይ ዳማ ቢጤ ሆና በጉሯ ግን አጭር፤ ፊቷ እነስ ያለች ናት። ዓይኖቿ ትንንሽ፤ አፍንጫዋ መካከለኛና ክትክሻዋ ሽጣጣ ሆና ከዚያ በታች እስከ ጉልበቷ ድረስ ወፈር ብላ እግሮቿ ግን ቀጫጭን ናቸው። አፏ ጠበብ ያለ ቢሆንም ምላሷ ግን እንደ እንዝርት የሚሾር ግልብልብ ናት። ዕድሜዋ ወደ ሰላሳዎቹ መጀመሪያ የደረሰ ይመስላል።

አስቻለው ለሰኮንዶች ያህል ሸዋዬን ቃኘት አድርጎ ወደ መጽሐፉ ሲመለስ ሸዋዬ ግን በሙሉ ነጻነት የአስቻለውን ተፈጥሮ በነይፏ ሙሉ ስትቃኘው አስቻለው እሳ የመሰለ ጠይም ነው። የፊቱ ወዝ ይቀዳ ይመስላል። ፊቱ ወሰል ያለ፤ ዓይኑም ትልልቅ ሆኖ አቀማመጡም የሚያምር፤ ትክሻው ደልደል፤ አፍንጫው መካከለኛ፤ ከጭንቅላቱም ከበድ ያለና ግርማ ሞገስ የተላበሰ መልክ መልካም ወጣት ነው። በዕለቱ ሙሉ ሰማያዊ ራንገለር ሱሪና ጃኬት በአረንጓዴ ሸሚዝ ለብሷል።

ይህ ትውውቅ በተከናወነ ከሁለት ወራት በኋላ የተፈጠረ አጋጣሚ ነው ለባሬ የአስቻለው ጭንቀት መነሻ የሆነው። በዚያው በጥርነው ምግብ ቤት ቁጭ ብሎ ያንን ሁኔታ በዓይነ ህሊናው ይመለከተው ጀመር።

ትዝ ይለዋል፤ በነሐሴ ወር አጋማሽ በዕለተ እሁድ ነበር። አስቻለው ቤቱ ውስጥ አረፋፍዶ ወደ ምሳ ሲሄድ እግረ መንገዱን ከታፈሡ ቤት ጎራ ይላል። ከቤት ሲገባ ታፈሡና አንዲት እንግዳ ልጅ ሶፋ ላይ ቁጭ ብለው ሲጨዋወቱ ያገኛቸዋል። እሱ ሲገባ ሁለቱም ብድግ ብለው ተቀበሉት። ታፈሡ ወደ እንግዳዋ ልጅ እያመለከተች፦

«ተዋወቃት እስቲ የሸዋዬ እህት ናት» አለችው።

«አስቻለው ፍሰሀ — ሒዋን ተስፋዬ» ተባብለው ስም በመለዋወጥ ተጨባበጡ። አስቻለው ለአፍታ ቆይታ አብሮአቸው ሶፋ ላይ ተቀመጠ።

«ሸዋዬን አውቅሃት አይደል?» አለችው ታፈሡ።

«ባለፈው ከአዋሳ አብረን የመጣነው መሰለችኝ»

«አዎ፤ የክረምቱን ዕረፍት ቤተሰቦቿ ጋር ክብረ መንግስት አሳልፋ ትናንት መጣች።»

«ያታለች ታዲያ?»

«እዚያ ስምንተኛ መንገድ ላይ ወይዘሮ ዘነቡ እስግድ ከሚባሉ ሴት ግቢ ውስጥ ሁለት ክፍሎች ያሉት ሰርቢስ ቤት አግኝቼላት ስለ ኪራይ ልትነጋገር ሄዳ ነው:: እንዴት ያሉ ዕድት ያሉ ክፍሎች መሰሉህ፣ ስፋታቸውም በቂ ነው» አለችና ታፈሡ ወደ ሔዋን ዞር ብላ ፈገግ እያለች «እደብቃችሁም የኔ ቆንጆ?» ስትል ጠየቀቻት::

«ኧረ ይበቃል::» አለች ሔዋንም ኀንበስ ብላ ፈገግ በማለት::

«እህቷ ጋ ሆና ልትማር ነው የመጣችው:: የአሥራ ሁለተኛ ክፍል ተማሪ ናት» አለች ታፈሡ አሁንም::

«ጨርሳለች!» አለ እስቻለውም ሔዋንን በዓይኑ ቃኘት እያደረገ::

ሔዋን ዕድሜዋ ወደ አሥራ ዘጠኝ ዓመት ይጠጋል:: መልኳ ድምቅ ያለ ቀይ ነው:: እንደ ጨረቃ ክብ በሆነ ፊቷ ላይ ዓይኖቿ እንደ ኮከብ ያበራሉ:: የጥቁር ዞማ ፀጉሯን ለሁለት ክፍላ በመጎንጎን ያለ ጡት መያዣ ጉብ ጉብ ባሉ ጡቶቿ ላይ ለቃቸዋለች:: ደረቷ ሙልት ያለ፣ እፍንጫዋ ሰልከክ ብሎ የወረደና ቀዳዳዎቹ ሰፋ ሰፋ ያሉ ናቸው:: ጥርስና ከንፈሮቿ የውብት ጡድድር የያዙ ይመስል ዓይን በየትኛው ላይ ማረፍ እንደሚችል ያስቸግራ ° ያምራሉ፣ ሁሉም ያሳሳሉ:: በእለቱ ጥቁር ጉርድ ክፋይ ቀሚስና ነጣ ያለ ሰማያዊ ስስ ሸሚዝ ለብሳለች:: በመካከለኛ ቁመት ደልደል ያለ ሰውነቷ ዓይን እየጎተተ የግድ እዩኝ እዩኝ ይላል::

‹ስታምር!› አለ እስቻለው በሆዱ:: ከፊቷ ቁጭ ብሎ በጨዋታ መሀል ዓይኑን ጣል እያደረገ የሰለለው የሔዋን ውበት ለብዙ ቀናት ከልቡ አልጠፋ ብሎት ትዝ ባለችው ቁጥር ደግሞ ደጋግሞ ‹እንዴት ቆንጆ ልጅ ናት!› በማለት ከራሱ ጋር እየተነጋገረ በልቡም ሲያደንቃት ሰነበተ:: ውሎ እያደረም ለፍቅር ይመኛትና ያስባት ጀመር::

ሸዋዬ የተከራየችውን ቤት አጸዳድታ የገባችበት ዕለት ለማስመረቂያ ለአዘጋጀቺው ምሳና ለአፈላችው ቡና እንዱ ተጋባዥ እስቻለው ነበር:: ጥሪውን አክብሮ ተገኝቷል:: ግን ከበላው የጣፈጠ ወጥና ከጠጣው ወፍራም ቡና ይልቅ በጣም ያስደሰተው በዚያ ሰበብ የሸዋዬን ቤት ማየት ነው፤ የሔዋንን አድራሻ ማወቁ በልቡ ለያዘው እቅድ መፈጸሚያ የመጀመሪያ ርምጃ ነውና:: በእርግጥም ከዚያ በኋላ ያንን ቤት በሰበብ አስባቡ ይመላለስበት ጀመር:: ሸዋዬም የቂስ እንግዳ እያደረገች ሽር ጉድ ስትልለት እየሞቀውና እየተመቸው ሄደ:: ከሔዋንም ጋር እየተቀራረቡ ሲሄዱ እሷም ከዓይን እፋርነት ወጣ በማለት እየተላመደችው ሄደች:: እስቻለውም በቀረባት መጠን ከማራኪ አካላዊ ገጽታዋ ይበልጥ ውስጣዊ ውበቷም ስሜቱን ይገዛው ጀመር::

እስቻለው ዛሬ በዋርካው ምግብ ቤት ውስጥ ቁጭ ብሎ ስለዚሁ ጉዳይ ሲያሰላስል በተለይ ሁለት አጋጣሚዎች ትዝ ብለውት ሳያውቀው ፈገግ አለ::

ትዝ አለው፤ ዕለቱ ዓርብ ነበር፣ የጥቅምት ወር የመጀመሪያ ሳምንት:: በዕለቱ የከሰዓት ፈረቃ ስራ ገቢ ነበር:: በጠዋቱ ፈረቃ የመምህራን ጠቅላላ ስብሰባ እንደነበርና ትምህርት እንደሌለ፣ በዚህም ምክንያት ሸዋዬ ስብሰባ ላይ እንደምትሆንና ሔዋን ደግሞ ቤቷ ውስጥ ብቻዋን እንደምትገኝ ቀደም ብሎ ያውቃል:: ፍቅሩን ለሔዋን ሊገልጽበት የሚችል ጥሩ አጋጣሚ ሆኖ ታየው:: በዚሁ ጉዳይ ላይ ሌሊቱን ሙሉ ሲያስብና ሲያሰላስል አድሮ ልክ ከረፋዱ አራት ሰዓት

አካባቢ ወደ ሔዋን ለመሄድ ቆርጦ ተነሳ:: ልቡ እየፈራ፣ ሰውነቱ እየተንቀጠቀጠ፣ ከንፈሩ በፍርሃት ሲደርቅበት በምላሱ እያራሰ፣ ጉሮሮውን እየሳለና ላብ ላብ እያለው ከሸዋዬ ቤት ደረሰ:: በዚያ ሰዓት ሔዋን መኝታዋም መቀመጫዋም በሆነች ከሸዋዬ ታጣፊ አልጋ ግርጌ በተነጠፈች ፍራሽ ላይ ቁጭ ብላ ስታጠና አገኛት::

«እንዴት አደራችሁ?» አለ የሸዋዬን አለመኖር እንደማያቅ ሆኖ::

«እንዴ እስቻለው! ዛሬ እንዴት በዚህ ሰዓት?» አለችው ሔዋን ብድግ ብላ እየተቀበለችው:: ለውትሮው የሚመጣው ማታ ማታ ስለነበር አመጣጡ ያልተለመደ ሆኖባታል::

«አንዳንዴ እንኳ በፀሐይ ልምጣ ብዬ::» እያለ ዱካ ላይ ቁጭ አለ::

«ሥራ አልነበረህም?»

«የከሠዓት ፈረቃ ገቢ ስለሆንኩ ነው::» ካለ በኋላ «ሸዋዬስ?» ሲል ጠየቃት አሁንም እንደማያውቅ ሆኖ::

«ስብሰባ አላቸው»

«እስከ ስንት ሠዓት ይቆያሉ?»

«ምናልባት እስከ ስድስት ወይም እስከ ሰባት::» አለችና ሔዋን «እንዲያውም እት-አበባ ሐታፈሡ ጋር እንመጣለን፤ ቡና አፍልተሽ ጠብቂን ስላለች ልቆላ ስል ነው የመጣኸው::» አለችው::

«ሥራ ካላበሸማ ልመለስ»

«እየሰራሁ መጫወት አንችልም?» ሔዋን ቃየቀለች:: አንዳንዴ ጣሪያ እስቻለው ልቡ ፈርቷልና ሲቅበጠበጥ ጣሪያ! ሌላ ጊዜ ውጭ ውጭ ሲያይ ትመለከተዋለች:: ከንፈሩንም ደጋግሞ በምላሱ ሲያርስ ይገርማታል:: ያልተለመደ ስሜት ታነበበታለች::

«ምነው እስቻለው? ችግር አለ እንዴ?» አለችው::

«ቢኖር ትፈቺያለሽ?»

«የምችለው ከሆነ!»

«ከማንም በላይ ላንቺ የሚቀል::»

«ምንድነው እሱ?»

እስቻለው ጉዳዩን በቃል ሊነግራት አልፈለገም፤ ከተቀመጠበት ብድግ በማለት ወደ ሔዋን ጠጋ አለና «እስቲ እንዴ ቆም በይ!» ሲል ጠየቃት::

ሔዋን የእስቻለው ሁኔታ አሁንም እየገረማት ብድግ አለች:: በድንጋጤ አስተያየት ዓይን ዓይኑንም ስትመለከተው እስቻለው አሁንም የበለጠ ጠጋ በማለት በሁለት እጆቹ ትከሻና ትከሻዋን ይዞ «ስሚ ሔዋን» አላት::

«እ- እቤት!» አለችው ሔዋን በድንጋጤ ድምጿ እየተቆራረጠ::

«እነሆ ከአየሁሽ_ድፍን ሁለት ወር አለፈኝ:: አንቺን በማየት የገባሁትን ዕዳ ብቻዬን ልወጣው አልቻልኩም::»

«የምን ዕዳ?» ሔዋን ዓይኖቿ በዓይኖቹ ላይ ስኩት አሉ::

«የፍቅር ዕዳ! ፍቅርሽን ብቻዬን አልቻልኩትም::»

«አ! ምነው እስቼ?» አለችው ሔዋን የባሰ እየደነገጠች:: ስለ ፈራች ይተዋት ዘንድ አቆላመጠችው::

አስቻለው ግን አልለቀቃትም፤ እንገቷን እቅፍ አድርጎ ደረቱ ላይ ከለጠፋት በኋላ «ሔዋ! ከእንግዲህ አንቺም አስቼ በይኝ፤ እኔም ሔዩ ልበልሽ።»

ሔዋን ከመደንገጧ የተነሳ ምን እያላት እንደሆነ አልታወቃትም። በሁለት እጆቿ የአስቻለውን የቶዳ ጃኬት ጫፎች እንቅ አድርጋ በመያዝ፦

«በእናትህ አስቻለው፤ ልቀቀኝ» አለችው።

«አንድ ቃል ተናገሪልኝና!»

«ም - ምን ብዬ?»

«እወድሃለሁ በይኝ»

«እሺ እወድሃለሁ። በል ልቀቀኝ!» አለችው። በእሷ ሀሳብ እንዲለቃት መለማመጧ ነው።

አስቻለው በቀኝ እጁ እንገቷን እቅፍ እንዳደረገ በግራ እጁ አገጯን ይዞ ቀና አደረጋትና ከንፈሮቿን ሶስት ጊዜ ሳም ሳም አድርጎ ለቀቃት።

ሔዋን ልክ አስቻለው እንደለቀቃት ፍራሿ ላይ ወጥታ ግድግዳ ተደግፋ በመቆም በድንጋጤ ጭብጥ ብላ በፍርሃት ዓይን ታየው ጀመር። ሰውነቷ በላብ ተነክሮ መላ አካላቷ ይንቀጠቀጣል።

«አይዞሽ!» አላት አስቻለው በስስት ዓይን ፍዝዝ ብሎ እየተመለከታት።

«እነ እት-አበባ ሳይመጡ ቶሎ ሂድ!» አለችው የተሳሙ ከንፈሮቿን በምላሷ ላስ ላስ እያደረገች። የአስቻለው ከንፈሮች ከንፈሯ ላይ የቀሩ ይመስላታል።

«ተመልሼ መቼ ልምጣ?» አላት እንደ ቀልድ ፈገግ ብሎ እያያት፤፤

«በእናትህ! ሁለተኛ እንዳትመጣ!»

አስቻለው ዛሬ ከምርካው ምግብ ቤት ቁጭ ብሎ ይህን ሁሉ ሲያስታውሰው ለራሱ ገርሞት ብቻውን ሳቀ። ራሱን ወዝወዝ አደረገና ማስቡን ቀጠለ። እንዲያውም ሌላውና በተለይ ለዛሬው ጭንቀቱ ዋና ምክንያት የሆነው አጋጣሚ በሀሳብ ፊቱ ላይ ድቅን አለበት። ፍቅሩን ለሔዋን ከገለጸ በኋላ ወደ ሸዋዬ ቤት የሚሄድበት ወቅትና ሰዓት ተቀይሮ እንደ ነበር አስታወሰ። ቀደም ሲል ወደዚያ ቤት የሚሄደው ለሳቅ ለጨዋታ ስለሆነ የሸዋዬን ቤት ውስጥ መኖር ይፈልገው ነበር። በኋላ ግን የሰው ዓይን የሚፈራ የተለየ ጉዳይ አለውና በአብዛኛው ሔዋን በዚያ ቤት ውስጥ ብቻዋን የምትገኝበትን ጊዜ ይመርጣል። ሸዋዬ በአለችበት የሚሄደው አልፎ አልፎ ለዚያውም ጥርጣሬ እንዳያስከትል ለማደናገር ብቻ ነበር።

ሔዋን ደግሞ ከዕለት ወደ ዕለት እየተመቸችው ሄዳለች። ለሁለተኛው እና ለሶስተኛ ምናልባት እስከ አራተኛው ጊዜ ልክ እንደ መጀመሪያው ቀን እየተጨነቀች ታስቸግረው የነበረ ቢሆንም እያደር ግን መለወጥ ጀምራለች። ያዝ ሲያደርጋት ቁና ቁና መተንፈሷን ትታ በስሜት መስለምለም፣ እንገቷን እቅፍ ሲያደርጋት በወገቡ ላይ ጥምጥም፤ ከንፈር ሲሰጣት የእሷን ማቀበል ተለማምዳለች። ከዚያም በላይ መናፈቅም ጀምራለች።

በዚያው ልክ የአስቻለውም ፍላጎት እያደገ ሄደ። በሳማትና በተሻሻት ቁጥር እንደ ብረት እየጋለ የሚያቅበጠብጠውን ሰውነቱን ‹እፎይ› ሊያሰኘው ፈለገ። ለዚህ የሚመች አጋጣሚና ሁኔታ ለመፍጠር አዕምሮውን ያዘጋጅ ጀመረ። ለዚህ ጉዳይ ደግሞ የራሱን ቤት መረጠ። ሔዋን ወደዚያ ቤት ብቅ ትልለት ዘንድ ሲያባብልም ሰነበተና አንድ ቀን ተሳካለት። ዕለቱ የህዳር ወር የመጨረሻው ማክሰኞ ነው፣

የአስቻለው ከንፈሮች ከሔዋን ከንፈሮች ጋር ከተገናኙ ሃምሳ ሁለተኛ ቀን። ሔዋን ቀጠሮ አክብራ ከተኑ ስምንት ሁዓት ላይ ከአስቻለው ቤት ደረሰች። አስቻለው ሔዋንን ከውስጥ አድርጎ ቤቱን ሲዘጋ ተሰምቶት የነበረ ደስታ አይረሳውም።

በዚያ ዕለት ሔዋንን እንደ እንግዳ ወንበር ላይ ቁጭ በይ አላላትም፤ እንገቷን እቅፍ አድርጎ በቀጥታ ወደ አልጋ ወሰዳት። አልጋ ላይ ቁጭ ብለው ትንሽ ከተሟሟቁ በኋላ ስሜት በራሱ ሀይል ሲገፋቸው አንገት ለአንገት እንደተቃቀፉ፣ ከንፈር ለከንፈር እንደተያያዙ ወደ ኋላ ከንብል አሉ። ጫማዎቻቸውን አወላልቀው ወደ መሀል አልጋው ወጡና ከሰፊው የፍቅር ሜዳ ላይ ሰፈሩ።

ትንፋሽ ገባው ቀጠለ። ከንፈሮች በስራ ተጠመዱ። ዓይኖች ተስለመለሙ። ትንፋሽ በረከተ። ግሊጋይ የማያስፈልገው ትንቅንቅ ተጀመረ። የአስቻለው ቀኝ እጅ የሔዋንን አንገት አቅፎ ግራው ደግሞ ሌላ ሥራ ያዘ። ከሔዋን ፀጉር ጀምሮ ማጅራቷን ይጎበኝና በወገቧ ላይ እየተስለከለከ ወደ ዳሌና ጭኖቿ ይወርዳል። ላይ ላዩን እንደ ወረደ ሁሉ ወስጥ ውስጡን ለመመለስ በማሰብ ቀሚሷን ሰብሰብ እያደረገ ወደ መሀል ጭኖቿ ጎራ ሲል ይቃጣዋል። ነገር ግን የሔዋን ጭኖች ወይ ፍንክች!! እንደገና ከላይ ይጀምራል። ይወርድ ይወርድና በአሰበው መንገድ ለመመለስ ሲሞክር ሔዋን ጭኖች ግን አሁንም ተቃውሞ ይገጥመዋል። ለሶስተኛ ጊዜ ሞከረ። የሔዋን ጭኖች ግን አልበገር አሉ።

በአራተኛው ጊዜ ከንፈሮችም ድንገት ተላቀቁ። ሔዋን ወደ ቀልቧ ተመልሳ ኖሮ ድንገት ፍንጥር ብላ በመነሳት አልጋው ላይ ቁጭ አለች። አስቻለውም አልዘገየ፤ ሔዋን በተነሳችበት ቅፅበት እሱም ፍንጥር ብሎ ጭራሽ ከአልጋው ላይ ወደ መሬት ወረደ። ፊትለፊቷ ቆሞ በነጭ ካኒተራው ላይ ደረቱን እያሻሸ፦

«ስሜቱ አልገባሽም እይደል ሔዩ!?» አላት በስሜት ውስጥ ሆኖ ቅልስልስ እያለ፤፤

«ገብቶኛል»

«ታዲያ ለምን ታስጨንቂኛለሽ?»

«እኔም ስለጨነቀኝ።»

«እንዴት?»

«የእናት አደራና የእህት ማስጠንቀቂያ ስላሉብኝ»

«አልገባኝም ሔዩ!»

«ና ቁጭ በል ልንገርህ»

አስቻለው ፈጥኖ ከአጠገቧ ቁጭ አለ። በመሀል ሔዋን በሀሳብ ጭልጥ ብላ ሄደች። ያኔ በነሐሴ ወር አጋማሽ ላይ ከሸዋዬ ጋር ጠዋት ከኩብረ መንግሥት ወደ ዲላ ሊመጡ ሲሉ ማታ በዝግጅት ላይ በነበሩበት ወቅት ሸዋዬ ሔዋንን እፊቷ ቁጭ አድርጋ ከእናቷ ጋር የተነጋገሩት ነገር።

«ስሚ እማዬ!» ብላ ነበር ሸዋዬ ወሬ የጀመረችው። «ይቺን ሔዋንን ከአሁኑ ምክሪልኝ። ዲላ የቡና አገር ስለሆነ ሁብታም ሁሉ ሰው በገንዘብ መግዛት ይፈልጋል። እሷ ደሞ ቆንጆ ስለሆነች በገንዘብ እያታለሉ ትምህርቷን አስትተው ብልግና ሊያስተምሯት ይችላሉ። ይህ ከሆነ ደግሞ ህይወቷ ሊበላሽ ይችላል። እኔም ብልግና ሊያስተምሯት ይችላሉ... ብሆን እንኳን ብልግና ፈጽማ፤ የወንድ እጅ ጨበጠች ያሉኝ ዕለት ባለጌሽን እምጥቼ አስረክብሻለሁ።» ብላቸው ነበር። እናቷ ከተል አድርገው «እንደኔ እንደኔ፤ የኔ ልጅ

እንዳሁ ዓይነት ብልግና ትፈጥማለች ብዬ አልገምትም፡፡ ያን ያህል ለፍቼ አሳድጌአታለሁና ክብሯን ጠብቃ ወግ ማረግ ታሳየኛለች ብዬ እጠብቃለሁ፡፡ ያ ሳይሆን ቀርቶ ብልግና ፈጥማ አንቺ ወደኔ ብታመጪት እኔም የዚያኑ ዕለት ገደል ገብቼ እሞትና ቀብረሽኝ ትመለሻለሽ፡፡» በማለት ተናግረው ነበር፡፡ ሒዋን ይህን የእናቷን አደራና የእህቷን የማስጠንቀቂያ ቃል በሀሳቧ እያደመጠች በነበረች ወቅት «እስቲ ያስጨነቀሽን ነገር ንገሪኝ» ሲል እስቻለው ከሀሳቧ ቀሰቀሳት፡፡

«ለመሆኑ ገርል መሆኔን ታውቃለህ?» አለችው ድንግል መሆኗን ስትገልፅለት፡፡

«ኤ!» አለ እስቻለው ያላሰበው ነገር ሆኖበት፡፡

«አትጠራጠር፡፡» አለችውና ሒዋን እናቷ የጣሉባትን አደራና እህቷ ሽዋዬ የሰጠቻትን ማስጠንቀቂያ በዝርዝር አስረዳችው፡፡

ያ እንደ ብረት ግሎ የነበረ የእስቻለው ሰውነት ድንገት ትዝትዝ! ብርድ! ስንዝ! አለ፡፡

«አደራ የምልህ እስቹ!» ስትል ቀጠለች ሒዋን፡፡ «ይህን የፍቅር ጉዳያችንን አንድ ቀን እትብባ የሰማች እንደሆነ መግቢያ ቀዳዳ የለኝም፡፡ ስለዚህ ምስጢራችንን ከታፈሡና ከጓደኞችህ በቀር ሌላ ማንም ስለማያውቅ ሁሉም በምስጢር እንዲይዙልን አደራ እንድትላቸው ነው፡፡» አለችው፡፡

እስቻለው በሁኔታው ተገርሞ ግንባሩን ይዞ መሬት መሬት ሲያይ ቆየና ድንገት ብድግ ብሎ ከሒዋን ፊት በመቆም «እስቲ ወደኔ ነይ ሒዩ!» አላት፡፡

ሒዋንም ብድግ ብላ በመቆም የእስቻለውን ዓይኖች ማየት ጀመረች፡፡

እስቻለው በሁለት እጆቹ የሒዋን ትከሻና ትከሻ ያዝ አድርጎ ቁልቁል እየተመለከታት፡ «ቃል ልገባ ነው ሒዩ»

«ምን ብለህ?»

«በሕይወት እስካለሁ ድረስ ፍጹም አልለይሽም፡፡ ከሠርጋችንም በፊት ምንም አላደርግሽም» አላት፡፡

«እሺ» አለችው ሒዋን፡፡

አንገት ለአንገት ተቃቀፉ፡፡ ምናልባት በሁለተኛው የህይወት ምዕራፍ ውስጥ እንደ ገቡ ታውቋቸው ሳይሆን አይቀርም ሆዳቸው ባባቶ ሁለቱም ተላቀሱ፡፡

ይህ ዓይነቱ የፍቅር አመሰራረት! ሂደትና በውስጡ ያለው የሒዋን አደራ ነው ዛሬ እስቻለውን የከበደውና መንፈሱን ወጥሮ ነፍሱን ያስጨነቃት፡፡ እም ተጨነቀ፡፡ ሒዋን በተፈጥሮ ፈሪና ሽቁጥቁጥ መሆኗን ያውቃል፡፡ ዛሬ በሽዋዬ ፊት እንደ ጭብጦ ኩርምትምት ብላ ታየችው፡፡ ችግሩን በምን መላ ሊፈታው እንደሚችል ግራ ገብቶት ፍዝዝ ትክዝ እንዳለ በጥርኘው ምግብ ቤት ለብዙ ጊዜ ቆየ፡፡

የአራት ሠዓት ደርሶ ኖሯል፡፡ ድንገት ጓደኛው በልሁ በበር በኩል ወደ እሱ ሲያመራ አየው፡፡ በልሁ ቁመቱ ዘለግ! ሰውነቱም ፈርጠምጠም ያለ ነው፡፡ ሰፋ ባለ የቀይ ዳማ ፊቱ ላይ በትር መስሎ የተገተረው አፍንጫው ግርማ ሞገስ አላብሶታል፡፡ ዓይኑ ጎላ ጎላ ያለና ፈገግ ሲል ጥርሱ የሚያምር ነው፡፡ ከውጭ ሲመጣ እስቻለው ትክዝ ብሎ በርቶት ዓይቶት ኖሮ ቀረብ ብሎ ሲያጤነውም ስሜቱ መመሰቃቀሉን በመገንዘብ፡

«ምነው ዶክተር? ሰላም አይደለህም እንዴ?» አለና ሰላም ብሎት ከአጠገቡ ቁጭ አለ፡፡ እስቻለው ነርስ ስለሆነ ጓደኞቹ ብዙ ጊዜ ‹ዶክተር› እያሉ በመጥራት ያሾፉበታል፡፡

«ትንሽ ሳያመኝ አይቀርም!» አለው የሚነበብበትን የጭንቀት ስሜት ያስወግደ መስሎት የፊቱን ላብ በእጁ እየጠረገ፡፡

«ሀኪምም ያመዋል እንዴ?»

«ጠንቋይ ለራሱ አያውቅ ይባል የለ!»

ወዲያው ደግሞ መርዕድ ከውጭ ሲመጣ ሁለቱም አዩት፡፡ መርዕድ አጠር ያለ! መልኩ ደግሞ ጥቁር ነው፡፡ ነጣ! ገጠጥ ያሉ ጥርሶቹ ከሩቅ ይታያሉ፡፡ በተፈጥሮው ፈገግተኛ ቢሆንም ሳኩርፍ ቢል እንኳ ጥርሶቹ አይገጠሙለትም፡፡ አፍንጫው አጭርና ደፍጣጣ ናት፡፡ በጥቁር ፊቱ ላይ ቁልጭ ቁልጭ የሚሉት ዓይኖቹ እጥረቷን ያሸፍኑለታል፡፡ ሲቀላቀላቸው ሁለት ወይም ሶስት ርምጃዎች ሲቀሩት በልሁ እንደ ልማዱ በቀልድ ዓይነት፦

«ስማ አንተ! እስከ አሁን ቆይተህ ራት አልቋል ቢባል አንተን ነው የምጎርስህ!» አለው፡፡

«አንተ እኮ የእቶ ተገኔ ልጅና የግብርና ሰራተኛ ባትሆን ኖሮ ሰው አይተርፍህም ነበር!» በማለት መርዕድም የቀልድ ምላሽ እየሰጠ ተጠጋቸውና ሰላም ብሏቸው ከአጠገባቸው ቁጭ አለ፡፡ በልሁና እስቻለው በመርዕድ መልስ ተገርመው እየተያዩ ሲሳሳቁ መርዕድ ቀጠለ፡፡

«ሀሰት ነው?» አለ በተለይ በልሁን ፈገግ ብሎ እያየ፡፡

«መቼም አንተ የምትለው አታጣ! እስተማሪ አይደለህ?» አለና በልሁ በቀልድ ዓይነት ቡጢ ቃጣ አደረገበት፡፡

የመርዕድ ቀልድ መሠረት አለው፡፡ በልሁ የባላባት የልጅ ልጅ ነው፡፡ አባቱ አቶ ተገኔ ክብረት ከደብረ ብርሃን በስተምዕራብ በኩል በግምት በሰላሳ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በሚገኝ ገጠራማ ቀበሌ ይወለዳሉ፡፡ ከአባታቸው የወረሱትን በርካታ ጋሻ መሬት ገና በንጉሡ ጊዜ ሸጠው ሸጠው በደብረ ብርሃን ከተማ ውስጥ በርካታ የንግድ ድርጅቶችን አቋቁመዋል፡፡ ሆቴል! የሸቀጣሸቀጥ መደብር! በርካታ የእህል ወፍጮዎችን ከማደራጀታቸውም በላይ አንድ ከባድ የጭነት መኪናም አላቸው፡፡ የእሳቸውን ያህል አይሁን እንጂ በዕድሜ ከበልሁ በላይ ያሉ አራት ልጆቻቸውንም በንግድ ሥራ አቋቁመዋቸዋል፡፡

በልሁ ለአባትና ለእናቱ የመጨረሻ ልጅ ነው፡፡ በቤተሰቡ ውስጥ እንደ ብርቅ ስለሚታይ በማር በወተት ያደገ ነው፡፡ በቤተሰቡ ውስጥ እስከ ዩኒቨርስቲ ድረስ የተማረው እሱ ብቻ ነው፡፡ ከዓለማያ እርሻ ኮሌጅ በድግሪ ተመርቆ በዲላ ከተማ በእውራጃው ግብርና ጽህፈት ቤት ውስጥ በባለሙያነት ያገለግላል፡፡ በዘመኑ እስከ ዩኒቨርስቲ ደረጃ ተምሮ የመንግስት ስራ አለመያዝ የማይደገፍ በመሆኑ እንጂ እንደ ቤተሰባዊ መሠረቱ ቢሆን ኖሮ ለሥራ ሲል ዲላ ድረስ መሄድ ባላስፈለገው ነበር፡፡ ያም ሆኖ በአስፈለገው ጊዜና መጠን ከቤተሰቡ ገንዘብ ይላክለታል፡፡ ደብረ ብርሃን ብቅ ካለም በገንዘብ ተንበሽብሾ ይመለሳል፡፡ በዚያ ላይ አዘውትሮ ለመስክ ስራ ስለሚወጣ አበል ሳያገኝ አንዲት ወር እንኳ አታልፍም፡፡

መርዕድ ግን በሐረርጌ ክፍለ ሀገር ከደሃ የገበሬ ቤተሰብ የተወለደ ከመሆኑም በተጨማሪ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህር በመሆኑ በአነስተኛ

ዝ. የሚናር ነው። ከደሞዙ ሌላ ምንም አያገኝም። እናም በበልሁ ኑሮ ይጎመዠል። ደግነቱ በልሁ በተፈጥሮው ቸር ከመሆኑም በላይ መርዕድን በጣም ስለሚወደው በቸገረው ሁሉ ይረዳዋል። የኑሮአቸውን ልዩነት ግን የዘወትር መቀላለጃና መሳሳለፊያቸው አድርገውታል።

ሦስቱም ጓደኛሞች ፊታቸውን አዝዘው አጥንት እየተሻሙ በልተው ከጨረሱ በኋላ እስቻለው ኮቦላዳቸው መልሶ ከአንድ ቁም ነገር ውስጥ ከተታቸው።

«ዛሬ እንደ ልጅ ልልካችሁ ነው።» አላቸው ዓይኑን በሁለቱም ላይ ዞር ዞር አድርጎ እያያቸው።

«የት?» ሲል ጠየቀው በልሁ።

«ለሸዋዬ ቤት።»

«ለምን» አለ መርዕድ በተራው።

«ለአንድ ብርቱ ጉዳይ።» አላቸው እስቻለው ፈገግ ብሎ እያያቸው።

በዚህ ጊዜ በልሁ ድንገት «ሃ-ሃ-ሃ-ሃ...» ብሎ ሳቀና «ብቻህን ሮጠህ ሮጠህ ሊሰለችህ ጊዜ ዛሬ ደግሞ ፖስተኛ አስፈለገህ እንዴ?» ሲል ቀለደበት። ሦስቱም ተሳሳቁ። እስቻለው ከሔዋን ጋር ከተዋወቀ ጊዜ ጀምሮ ብዙ ጊዜ ለብቻው ወደ ሸዋዬ ቤት ስለሚሄድና ይለያቸው ስለነበረ ነው የአሁኑ ለበልሁ ቀልድ መሠረቱ።

«አትቀልዱ! ችግር ተፈጥሯል።» አላቸው እስቻለው ኮስተር ብሎ።

«እኮ ምን?» ሲል በልሁ አሁንም እየሳቀ ጠየቀው።

እስቻለው ከታፈሡ ያገኘውን መረጃ ዘርዝሮ አስረዳቸው። ስለ ሔዋን ሁኔታ ያደረበትን ስጋት ገለፀላቸው። ቀጥሎም ‹እስቻለው ጠፋብን፣ እዚህ መጥቶ ከሆነ ብለን ነው› በሚል ሰበብ ሔዋን በምን ሁኔታ ላይ እንዳለች ስለለው መረጃ ይዘውለት እንዲመጡ ጠየቃቸው።

በልሁና መርዕድ የእስቻለውን ማሳሰቢያ በቀላሉ አላዩትም። ሔዋንን የሕሉን ያህል ያውቋታል። በጣምም ይወዷታል። ባህሪዋንም፣ የነበረባትንም ስጋት ሁሉ ያውቃሉ። የተፈጠረው ሁኔታ ከእስቻለው ባልተናነሰ መልኩ አሳሰባቸው። በዚህም ምክንያት እንደ ወትሮው ከአራት በኋላ ሻይ ቡና ማለት አልፈለጉም፤ በቀጥታ ወደ ሸዋዬ ቤት ሊሄዱ ተነሱ። በልሁ ቀልድ ይወዳልና፦

«ችግር ካለ ሔዋን ተሸክመንም ቢሆን ይዘንልህ እንምጣ እንዴ ዶክተር?» ሲል እስቻለውን በፈገግታ እያየ ጠየቀው።

«ያን ካደረጋችሁማ ትሸለማላችሁ።» አለው እስቻለውም እንደ ቀልድ።

«ትሰማለህ መርዕድ!» አለ በልሁ ቀልዱን ለመቀጠል። «ሽልማት ካለው ችግር ኖረ አልኖረ ሔዋን ዝም ብለን አምጥተን እንጣልለትና እንዳረገ ያድርጋት። እኛም ሽልማታችንን እንቀበል።»

«እኔ የለሁበትም!» አለ መርዕድ ሳቅ እያለ።

በልሁና መርዕድ በደህና ቦታ ላይ ተቀላልደው ወደ ምሩ ቦታ ገቡ ጀመሩ፤ ወደ ሸዋዬ ቤት።

* * *

‹ሰው አይችለው የለ› እንዲሉ ሸዋዬ በተለይ ከአንድ ቀን በፊት ጀምሮ በአዕምሮዋ ውስጥ የሚተረማመስ የሃሳብ ብዛት ቢመዝን ክብደቱ፣ ቢለካ ርዝመቱ፣ በዓይን የሚታይ ቢሆን የብዛቱ ነገር የትየለሌ በሆን ነበር። ያላሰበችው ዱብ ዕዳ ወርዶባት ምስቅልቅል ባለ ስሜት ውስጥ ገብታ ትቃትታለች።

የሃሳብና የጭንቀቷ ሥር ያኔ ከአዋሳ ወደ ዲላ ከእስቻለው ጋር እስከተጓዘችበት ቀን ድረስ የተዘረጋ ነው። ትዝ ይላታል የጉዟቸው ሁኔታ። ትዝ ይላታል ከእስቻለው ጋር ያደረጉት ጭውውት። ትዝ ይላታል እስቻለው ያደረገላት ዕርዳታ። ቆጠብ ያለ አነጋገሩ፣ እንዲሁም በጆሮዋ የተንቆረቆረው ማራኪ ድምፁ። በተለይ ዲላ ደርሳ ከታፈሡ ጋር ተገናኝታ ለቀናት ያህል እዚያው በሰነበተችበት ወቅት ታፈሡ በጨዋታ መሀል እያነሳች እስቻለው የልጆቿ ክርስትና አባት መሆኑን ከመግለጽ ጀምሮ ማንነቱን፣ ባህሪውን፣ ሙያውንና አናኗኗሩን ሁሉ በሰፊው አስረድታት ነበር። የዚህ ሁሉ ውጤት የሸዋዬን ልብ በፍቅር ወደ እስቻለው ዘንበል እንዲል አድርጎት ‹ደስ የሚል ወንድ› እስከ ማለት ደርሳ ነበር።

ክብረ መንግስት ሄዳ ለአንድ ወር ያህል ከወላጆቿ ጋር የዕረፍት ጊዜዋን ባሳለፈችበት ጊዜ ሁሉ እስቻለውን ለአንድም ቀን ረስታው አታውቅም። ሁሉም ነገሮቹ በዓይነ-ህሊናዋ ውል ሲሉባት ቆይተዋል። ወደ ዲላ ስትመለስ ምን ዓይነት ዘዴ ፈጥራ ልትቀርበው እንደምትችል ታሰላስል ነበር። እሷ የታፈሡ ጓደኛ፣ እሱ ደግሞ ከጓደኝነትም በላይ የታፈሡ አቡልጅ እንደ መሆኑ ሁሉንም ነገር በታፈሡ ጥላ ሥር ልትሞክር እንደምትችል ይታያት ነበር። ከታፈሡ ቤት አይጠፋምና ነጋ መሽ ልታየውና ልታገኘው እንደምትችል በማመን በፍቅር ቀርባ ልታቀርበው የምትችልበትን መንገድ ስታሰላስል ከርማለች።

በነሐሴ ወር አጋማሽ ላይ ዲላ መጥታ ቤት ተከራይታ የምርቃት ምሣ አዘጋጅታ እስቻለውን የጠራችው ለዚሁ ዓላማዋ አንድ ርምጃ መራመጃ ነበር። ሸር ጉድ ብላም አስተናግዳዋለች። ጠርታው በመምጣቱ ደስ ብሏታል። ከሁሉም በላይ በዚያ አጋጣሚ ቤቷን ማወቁ ለወደፊት ግንኙነታቸው መሠረት ሊጥል እንደሚችልም ተስፋ አድርጋ ነበር።

በእርግጥ እስቻለውም ወደ ቤቷ ብዙ ተመላልሷል። በተለይ ማታ ማታ ብቅ እያለ ሲያጫውታት ከርሟል። አንዳንዴም ወደ ከተማ ይዟት እየወጣ የሆቴል ምግብ አብረው በልተዋል። የመጠጥ ዓይነቶችንም አዝናንቷታል። በርካታ ርዕሶችንም እያነሱ ተጨዋውተዋል። ነገር ግን እስቻለው ወደ ፍቅር ያዘነበለ ስሜት ሳታይበት ወራት አለፉ።

እስቻለው የፍቅር ጥያቄ ሳያቀርብላት ሲቀር እየጨነቃት ‹አንዳንድ ሰው› ትላለች በሃሳቧ ‹የሰውን ሁለመና ሳያጠና ልቡን ለፍቅር አይከፍትም። እንዴ ከከፈተ ደሞ በቀላሉ አይዘጋም። ይህም ሰው ባህሪው እንደዚያ ሆኖ ሊሆን ይችላል።› በማለት የራሷን ምክንያታዊ ግንዛቤ ትፈጥራለች።

ቀን እየረዘመ ሲሄድ ደግሞ ሌላ ሃሳብ። ‹ይኸ ሰው ምናልባት ሰው የማያውቃት ሌላ ሴት ትኖረው ይሆን እንዴ? ወይስ ንቆኝ? መቼም ቆንጆ ባልሆንም ገና አፍላ ነኝ። ሊያገባኝ ባይፈልግ እንኳ ለወዳጅነት ታንሳለች ብሎ አይገምተኝም።› ካለች በኋላ ‹ግን እኮ! ዝምብሎ በእህትነት ሊያየኝ አስቦም ሊሆን ይችላል›

ወደ ደሞ ይሆን ያህል ጊዜ በአሁታዊና ወንድማዊ ግንኙነት ስለቆየን እንደገና ሃሳቡን ለመቀየር ፈርቶ ሊሆን ይችላል፡ በማለት ታስብ ጀመር::

ይኸኛው ሲጋት እያየለባት በመሄዱ ስሞኑን አንድ መላ ፈጥራ ተግባራዊ ለማድረግ ዝግጅት ላይ ነበረች:: ጠቀም ያለ ገንዘብ እጇ ላይ መያዝ፣ አስቻለውን ራሷ ስትጋብዘው ልታመሽ፣ ከአቅሙ በላይ እንዲጠጣ ልታደርገው፣ ከተማ ውስጥ ብዙ ልታስመሽው፣ በኋላም በእሱ ቤት በኩል ወደ ቤታቸው ሊመለሱ፣ ከእሱ ቤት አካባቢ ስትደርስ ‹አልቻልኩም› ብላ ልትዝለፈለፍና ቤትህ አስገብተህ አሳርፈኝ ልትለው፣ ቅር እንደማይለው ታውቃለችና ገብታ በበልሁና በመርዕድ ሚት መቃሚያ ፍራሽ ላይ ልትተኛ፣ ያኔ ስንፈተ ወሲብ ከሌለበት በቀር ጎኗ አልጋው ላይ ተኚ ሌላት እንደሚችል በማሰብ ይህንኑ ልትፈጽም ወስና ቀን መምረጥ ብቻ ነበር የቀራት:: ግን ደግሞ ሳታስበውና ባልጠበቀችው ሁኔታ የስሜት እንቅፋት ተፈጥሮባት እነሆ ዛሬ ውልክፍክፍ ብላለች::

ከታፈሡ ጋር በዕለተ ሰኞ ከመገባቷ አንድ ቀን ቀደም ብሎ በዕለተ እሁድ ከአንድ የሥራ ባልደረባዋ ጋር ስለ ፈተና ዝግጅት ልትነጋገር ከጠዋቱ ሁለት ሰዓት አካባቢ ከቤቷ ወጥታ አረፈደች:: ጉዳይዋን ጨርሳ ስትመለስ ቤቷ ተዘግቶ አገኘችው:: ትዝ ሲላት ሒዋን ወደ ገበያ ሄዳ የወጥ ቅመማ ቅመሞች እንድትገዛ አዛታለች:: ቤቱ የመዘጋቱ ምክንያት የእሷ ወደ ገበያ መሄድ መሆኑን ተገንዝባ ራሷ በያዘችው ቁልፍ ከፍታ ለመግባት ወደ በሩ ስትራመድ ድንገት አንዲት ህጻን ፦

«እት-አበባ» ስትል ጠራቻት:: ሕጻኗ ለሸዋዬ ቤት የአከራዩዋት ወይዘሮ ዘነቡ የሚያሳድጉት የዘመድ ልጅ ናት:: ከአምስት እስከ ስድስት ዓመት ይሆናታል:: ከወይዘሮ ዘነቡ ዚላ ቤት በስተጓሮ በኩል ጥግ ይዛ ዕቃ ዕቃ ትጫወታለች:: ሒዋን ሸዋዬን ‹እት-አበባ› እያለች ስትጠራት እየሰሙ ያቺ ህጻንና የወይዘሮ ዘነቡ ሰራተኛ ሸዋዬን በዚሁ ስም ነው የሚጠሯት::

«ወይ ሚሚዬ!» በማለት ሸዋዬ ለሕጻኗ ጥሪ መልስ ሰጠችና በዚያው ቀጥላ «ቡናሽ ደርሷል?» ስትል በማጫወት ዓይነት ጠየቀቻት:: ሕጻኗ ግን የሸዋዬን ጥያቄ ወደ ጎን ትታ የራሷን ቀጠለች::

«የሒዋን አባት መጥቶ ቤቱ ሲዘጋበት ጊዜ ተመልሶ ሄደ::» አለቻት::

«እ!» አለች ሸዋዬ ምንነቱን ያላወቀችው ስሜት መላ ሰውነቷን ነዘር እያደረጋት:: ቤት መክፈቷን ትታ ወደ ህጻኗ ልጅ በማቅብቀብ «ማነው የሒዋን አባት አንቺ?» ስትልም ጠየቀቻት::

«አስቻለው ነዋ! ሀአ!» አለች ሕጻኗ አጎንብሳ ቆርኪዎቿን እየደረደረች::

«አስቻለው?»

«አዋ! ሀአ!»

ሸዋዬ የባሰ ደነገጠች:: ዓይኗ ከህጻኗ ላይ ሳይነቀል ፍጥጥ ብላ ታያት ጀመር:: እሷም ሒዋንም በሌለበት አስቻለው መጥቶ እንደተመለሰ ገባት:: የቸገራት በዚያች ህጻን አንደበት አስቻለው የሒዋን አባት መባሉ ነው:: በዲላና አካባቢዋ ባለው ህብረተሰብ ውስጥ ባል ‹አባት› ተብሎ እንደሚገለጽ ታውቃለች:: እና አስቻለው የሒዋን ባል? በጣም ግራ የገባት ይኸ ብቻ ነው::

«እንዴ!» አለችና ሸዋዬ አሁንም ህጻኗን ትኩር ብላ እየተመለከተች «አስቻለው የሒዋን አባት መሆኑን ማን ነገረሽ አንቺ?» ስትል ጠየቀቻት::

«ነዋ! እንዴ! ሀአ!» አለች ሕጻኗ አሁንም::

ሸዋዬ የበለጠ ግራ ገባት:: ህጻኗ ያለ አንድ መነሻ ያን ንግግር እንዳልተናገረች ገመተች:: ወይዘሮ ዘነቡንና ሰራተኞቻቸውን አሰበቻቸው:: ለጊዜው ግን «እንዴ! እንዴ! እንዴ!» እያለች ቤቷን ከፍታ ገባች:: አልጋዋ ላይ ቁጭ አለችና «እንዴት ነው ይኸ ነገር?» በማለት ቁና ቁና እየተነፈሰች ለረጅም ጊዜ ቆየች::

ሒዋን የገዛቻቸውን የወጥ ቅመማ ቅመሞች በዘንቢል ይዛ ወደ ቤት ስትገባ የሸዋዬ ዓይን ፈጥጦ አገኘችው:: ሁኔታዋ አላማራትም::-

«እት-አበባ» አለቻት በንዚሷን እንደያዘች ከፊቷ በመቆም:: ሸዋዬ ግን ገልመጥመጥ ከማድረግ በቀር ምላሽ ሳትሰጣት ቀረች::

«ምነው?» አለቻት ሒዋን አሁንም::

«አትተዪኝም?» አለቻት ሸዋዬ ቁጣ በተቀላቀለበት አነጋገር:: ወዲያው ወደ አልጋዋ በመውጣት አንሶላና ብርድ ልብስ ውስጥ ገብታ ሽፍንፍን ብላ ተኛች::

ሒዋን የእህቷ ሁኔታ ግራ አጋባት:: በዚያው ልክ ፈራች:: ድንጋጤም ተሰማት:: ወደ ጓዳ ገብታ ዘንቢሏን ካስቀመጠች በኋላ በጓዳው በር በኩል አንገቷን ብቅ እያረገች የሸዋዬን ሁኔታ ትከታተል ጀመር:: አይታ አይታ ምንም ለውጥ ልታገኝ ባለመቻሏ የምሳ ወጥ ስራዋን ጀመረች::

ሸዋዬ ከተኛች ወዲህ ለመጀመሪያ ጊዜ ቀስቀስ ያለችው የወይዘሮ ዘነቡ የቀትር ቡና ሲጠቀጥ ነው:: ወትሮም ቢሆን በተለይ ቅዳሜና እሁድ ከምሳ በኋላ ለሚጠጣው ቡና ሸዋዬ ወደ ወይዘሮ ዘነቡ ቤት ትጠራ ነበር:: ዛሬ ግን ገና ሳትጠራ ለመሄድ ብድግ አለች:: ያቺ ህጻን በዚያ ቤት ውስጥ ሲወራ ያልሰማችውን ነገር ከየትም አምጥታ ልትነግራት እንዳልቻለች ገምታ የወሬውን ምንጭ ከስሩ ለመጎርጎር ወሰነች:: ፒጃማ ዓይነት ጀወለል ቢጤ የቤት ልብስ እንደለበሰች ነጠላ ጫማ አድርጋ ወደዚያው አመራች፤ በጓሮ በኩል ወደ ሳሎን በሚያስገባው የወይዘሮ ዘነቡ ቤት በር በኩል እየገባች፦

«ደህና ዋላችሁ» አለቻቸው::

ወይዘሮ ዘነቡ ነጭ በነጭ የሆነ የሀገር ልብሳቸውን ለብሰው ሶፋ ላይ ጉብ ብለዋል:: ቀይ ናቸው:: የአንገታቸው ንቅሳት ከቅላታቸው ጋር አለላ መስሎ ይታያል:: የአገጭ ሥር ጅማቶቻቸው ገተር ገተር ማለት የዕድሜያቸውን መግፋት ይናገራሉ:: ነገር ግን ጥቁር መነፅራቸው ከቀይ ፊታቸው ጋር ደምቆ ሲታይ ዕድሜያቸውን ወደ ኋላ ለመመለስ የሚታገል ይመስላል:: ኑሮአቸውን የቤታቸው ሁኔታ ያመለክታል:: በዘመናዊ ዕቃ የተሞላ ነው:: የሳሎኑ ስፋት ፈረስ ያስጋልባል የሚባል ዓይነት ነው:: በቡና ንግድ የናጠጡ ሀብታም የነበሩት ሟቹ ባለቤታቸው ያደራጁላቸው ንብረት ነው::

«ደህና ዋልሽ የኔ ልጅ!» አሉና ወይዘሮ ዘነቡ «ይኸውልሽ፣ የጎረቤት ደንቡ ይኸ ነው:: ጥሪ የሚፈልግ ከሆነ ግን ንፉግነቱን ያመለክታል::» አሏት ሸዋዬ ሳትጠራ በመምጣቷ የተሰማቸውን ደስታ ለመግለጽ::

«አንዳንዴም ቀላዋጭ ያሰኛል!»

«እሱም የስስታም ሰው አባባል ነው:: በእኛ ቤት ደሞ እንደዚያ ብሎ ነገር የለም:: ለወደፊቱም ይልመድብሽ::» ብለው ፊታቸውን ከሶፋው አጠገብ በነጭ

ረከቦት ላይ ወደ ተደረደረው ሲኒ መለስ አደረጉ:: ሰራተኛቸው ፋንትዬ ቡናውን ጀበና ውስጥ እየጨመረች ናት::

«ጉዳይ ስላለኝም ነው ቀድም ብዬ የመጣሁት::» አለች ሽዋዬ በወይዘሮ ዘነቡ ፊትለፊት ሶፋ ላይ ተቀምጣ ዓይን ዓይናቸውን እያየች::

«ምነው? ደህና?» አሏት ወይዘሮ ዘነቡ ፊታቸውን ወደ ሽዋዬ መለስ አድርገው::

«ተቀይሜብዎታለሁ::»

«ውይ የኔ ልጅ! ድንግል ትባርክሽ! ቅያሜሽን ፊትለፊት ተነገርሽኝማ ድንግልም ትወድሻለች::» አሉና «ግን ሳላውቅ ምን አጥፍቼ ይሆን» ሲሉ አንገታቸውን ዘመም አድርገው እያዩ ጠየቋት::

«አንድ ነገር እያወቁ ደብቀውኛል::»

«ምን ይሆን የኔ ልጅ?»

«በኔ ሰበብ ግቢዎት ሲደፈር እያዩ ዝም ማለትም!»

«ምን ያገባው ሰው ነው ግቢዬን የሚደፍረው?»

«ብልግና ከተፈጸመበት ያው ተደፈረ ማለት አይደል?»

«የምን ብልግና?»

«አይቀሽኝ እማማ ዘነብ!»

«ድንግል ትመስክር፣ ምንም የምቀሽው ነገር የለም:: አንቺ ግን ምን ሰምተሽ ነው?» ሲሉ መነፅራቸውን ወለት አድርገው እያዩ ጠየቋት::

«ይቺ የኔ እህት ከዚያ አስቻለው ከሚባል ልጅ ጋር እየባለገች መሆኑን ሳያውቁ ቀርተው ነው?» ስትል ጠየቀቻቸው አንገቷን ጠመም አድርጋ በጎን አስተያየት እየተመለከተቻቸው::

«ውይ! ይኼ ነው እንዴ ነገሩ?» አሉና ወይዘሮ ዘነቡ ቀለል አድርገው «ለመሆኑ አንቺ እስተ ዛሬ ምንም የምታውቂው ነገር አልነበረም?» ሲሉ ጠየቋት::

«ምኑን?» አለች ሽዋዬ እንደ አዲስ:: ነገሩ እርግጥ መሆኑ ሲገባት በድንጋጤ ሰውነቷ ሁሉ ክፍልፍል ያለ መሰላት::

«ስለ ሁለቱ ልጆች ፍቅር ነዋ!»

«ፍቅር?»

«ምናልባት እኩያሞች ስለሆኑ ነው መሰል የእነሱን ፍቅር ልቤ ይወደዋል::»

«እማማ ዘነብ!» ስትል ጮኸች ሽዋዬ ድንገት:: ዓይኗ በወይዘሮ ዘነቡ ላይ ፍጥጥ አለና መላ ሰውነቷንም ያንቀጠቀጣት ጀመር::

«ወይ የኔ ልጅ!»

«ምን እያወሩ እንደሆነ ያውቃሉ?»

«ዘባርቂ ይሆን እንዴ ልጄ?» አሉና ወይዘሮ ዘነቡ እውነትም ድንግጥ ብለው ሽዋዬን ትኩር ብለው ያዩዋት ጀመር::

«ቀላል!»

«ምን አልኩኝ?»

«ሊያጋቧቸው አስበዋል እንዴ?»

«ኧረ ምን ቁርጥ አድርገኝ ልጄ! ቢሆን አይከፋም ማለቴ ነው እንጂ!»

ሽዋዬ ውስጧ ተቃጠለ:: አረረች:: በወይዘሮ ዘነቡ ሀሳብ ከመበሳጨቷ የተነሳ ያን ከሰል ላይ የተጣደ ጀበና ብድግ አድርጋ በመሀል እናታቸው ላይ

ብትከለክለው እየተመኘች «የሚሉት ነገር ሁሉ ሊገባኝ አልቻለም!» አለቻቸው ዓይኗን ፍጥጥ፣ ጥርሷን ግጥጥ አድርጋ እያየቻቸው::

«ግልጥልጥ አድርጌ እየነገርኩሽ! እንዴት አይገባሽም?» አሏት የሽዋዬ የውስጥ ስሜት ያልገባቸው ወይዘሮ ዘነቡ::

«ቆይ ግን» አለችና ሽዋዬ ንዴት ያወላከፈውን ጉሮሮዋን «እህህ» ብላ ሞረደችና «የሁለቱን መፋቀር እንዴት አወቁ?» ስትል ጠየቀቻቸው::

«ድንግል ምስክሬ ናት፤ በበኩሌ ክርና መርፌ ሆነው በዓይኔ አላየሁም:: ግን መቸም ትንሽ ሳይያዝ ብዙ አይወራም ብዬ ነው::» ብለው ፊታቸውን ወደ ረከቦቱ መለስ አደረጉ::

ወይዘሮ ዘነቡ አንድ ነገር በሆዳቸው አሉ:: አንድ ቀን አስቻለውና ሒዋን ተዘናግተው ሳይሆን አይቀርም በሩን መለስ እንኳ ሳያደርጉት ቆመው ሲሳሳሙ ሰራተኛቸው ፋንትዬ በበር በኩል አለፍ ስትል አይታቸው ኖሯል:: ወይዘሮ ዘነቡ በአቅራቢያዋ ስለነበሩ ወደ ጆሮቸአው ጠጋ ብላ በሹክሹክታ ዓይነት «እማማ! ሂዱ ወደ እትአበባ በር አጠገብ! የሚያዩት ነገር አለ» ብላቸው ነበር:: እሳቸውም ሌላ ነገር መስሏቸው ቤቱን ሰላል እያረጉ በበሩ አጠገብ አለፍ ሲሉ ፋንትዬ ያየችውን ያያሉ:: በእርግጥ በወቅቱ በፋንትዬ ድርጊት ተቆጥተው ነበር:: ግን ደግሞ ያዩትን ማመን ችለዋል::

«ለመሆኑ ይህን ወሬ የሚያወራው ማነው?» ስትል ሽዋዬ ጠየቀቻቸው::

«ሠፈር ሙሉ ነዋ! እኔ እንደውም የሰማሁት በወይዘሮ እልፍነሽ ቤት ውስጥ ሲወራ ነው::» አሏት::

«እሳቸውም ያውቃሉ?»

«እንዴ! ቤቷ ውስጥ እየተወራ!?»

ሽዋዬ አንዳች ነገር ሰትስቶ ያስነሳት ይመስል ከሶፋው ላይ ድንገት ብድግ አለችና በጓሮ በር በኩል ወጥታ ወደ ወይዘሮ እልፍነሽ ቤት አመራች::

«ውይ! እንዲህ ያለች ሰው ኖራለች እንዴ ልጄ!?» በማለት ወይዘሮ ዘነቡ በመገረም ሠራተኛቸውን ፋንትዬን መልከት አሏት::

«ኧረ እኔ እንጃ እማማ!» አለቻቸው ዕድሜዋ ወደ ሃያ የሚጠጋት የጥቁር ደማም የሆነችው ፋንትዬ::

ቤቱ ቅርብ በመሆኑ ሽዋዬ ከወይዘሮ እልፍነሽ ግቢ የውጭ በር ደርሳ በር ስታንኳኳ ጊዜ አልፈጀባትም:: ጆላላ የቤት ውስጥ ቀሚሷን በቀኝ እጇ ወደ ጉያዋ ሰብሰብ እንዳረገች ለአንኳኳችው በር ምላሽ ትጠብቅ ጀመር::

«ማነው?» አሏት ወይዘሮ እልፍነሽ ከቤታቸው በረንዳ ላይ ቆመው::

«እንግዳ!»

ወይዘሮ እልፍነሽ ወደ ውጭ በር መጥተው በሩን ከፍተው ሽዋዬን ሲያዩዋት ድንግጥ እንደማለት ብለው «ውይ! የኔው ነሽ እንዴ? ምነው በዚህ በጠሐይ?» አሏት ፍንጭታቸው ከመስፋቱ የተነሳ ከመሀሉ አንድ ጥርስ የወለቀለት የሚመስል ጥርሳቸውን ብልጭ እያረጉ::

«ኑ ወደ ቤት እንግባ! ጉዳይ አለኝ::» አለቻቸው በችኮላ አነጋገር:: በቀጥታ ወደ ቤት እያመራች ወይዘሮ እልፍነሽን በገዛ ቤታቸው ጋበዘቻቸው:: ወይዘሮ እልፍነሽ እጆቻቸውን በወገባቸው ላይ አጣምረው ከኋላ ከኋላ ተከተሏት::

ወይዘሮ እልፍነሽ አጭር ወፍራም ናቸው፤ ከወገባቸው ጎንበስ ያሉ፤ ፀጉራቸውም አጭርና ሽበቱ፤ በባህሪያቸው ‹ወሬኛ› የሚባሉ ናቸው፤ አንዷን ከአስር በላይ የሚያባዙ፤ ለውሸት ልክ የሌላቸው። ከዚሁ ባህሪያቸው በመነጩ የጎረቤት ሰው ሁሉ ‹እልፍነሽ ወሬ አፈሽ› ይላቸዋል።

ሸዋዬ ቤት ውስጥ ገብታ ራሷ ወንበር ሳብ አድርጋ ስትቀመጥ ወይዘሮ እልፍነሽ እጆቻቸውን በወገባቸው ላይ አጣምረው ከፊቷ ቆሙ። ለወሬው በጣም የቸኮሉ ይመስላሉ።

«እንደው ምን አግኝቶሽ ይሆን ልጄ?» ሲሉ ጠየቋት።

«ቱጭ በሏ!» አለቻቸው ሸዋዬ ከንፈሯን በምላሷ እያራሰች። የእጆቿን መዳፎች አጋጥማ በጉልበቶቿ መሀል አጥብቃ ይዛቸዋለች።

ወይዘሮ እልፍነሽ ለወሬው ሰፍ ብለዋል። ጠበብ ካለች አፋቸው ውስጥ ከአራት በላይ የማይታዩ ጥርሶቻቸውን ገለጥ አድርገው ፈገግ እያሉ ተቀመጡና፦

«እስቲ ንገሪኝ ልጄ!» አሏት።

«ጉድ የምትሰሩኝ እኮ እናንተ ጎረቤቶቼ ናችሁ!» አለቻቸው ሸዋዬ ምላሷን በከንፈሮቿ ዳር እና ዳር ግራና ቀኝ ወጣ ገባ እያረገች። ወይዘሮ እልፍነሽ ደረታቸውን በእጃቸው ደሰቅ አረጉና «ውይ በሞትኩት! ምነው? ምን አደረግን?»

«የእህቷ ህይወት ሲበላሽ እያያችሁ ዝም ትሉኛላችሁ?»

«ምነው? ምን አገኛት?»

«አርግዛ ትምህርቷን ብታቋርጥስ?»

«እንዴ!» አሉ ወይዘሮ እልፍነሽ ነገሩን እንደማታለል ዓይነት በሚያስመስል አነጋገር። «እሙኛዋ ባለሙያ አይደል እንዴ! ችግር ቢፈጥር አሽቀንጥሮ ይጥላት የለ!» ካሉ በኋላ አፋቸውን የበለጠ ወደ ሸዋዬ ጠጋ በማድረግ «ከአሁን ቀደምስ ችግሩ ተፈጥሮ ገላገላት ተብሎ—» ብለው ሳይጨርሱ ሸዋዬ ቀደመቻቸው።

«ምን አሉ?» አለች ዓይኗን ፍጥጥ አድርጋ እያየቻቸው። ‹እሙኛዋ› ያሏት ነገር ከተቀመጠችበት አንጥሮ ሊያነሳት ሲል ደም የውርጃ ነገር ጨመሩባትና በአለችበት ኩርምትምት አለች።

«ኧረ ተይኝ እቴ!» ብለው ወይዘሮ እልፍነሽ እንደ መግደርደር ዓይነት ወደ ውጭ እየት ካደረጉ በኋላ እንደገና ወደ ሸዋዬ መለስ በማለት «በአንቺ እህት ስንት ልጃገረዶች እየቀኑባት ደሞ እንዲህ ያለ ሥጋት ይደረብሽ እንዴ? ሆሆይ...»

ሸዋዬ በባሰ ድንጋጤ ሰውነቷ ሽምቅቅ ብሎ መንፈሷ ድክም፣ ልቧም ስንፍ አለና በተራዘመ የቃል አወጣጥ «‹አ ሶ ር ዳ ለ ች› ነው የሚሉኝ» ስትል ጠየቀቻቸው።

«ገላገሏት!»

ሸዋዬ አሁንም ድክም ባለ መንፈስ «አ መ ሰ ግ ና ለ ሁ!» አለቻቸውና ከተቀመጠችበት በተስታ ብድግ አለች። ወይዘሮ እልፍነሽ እውነትም አፍሰው አታሟት።

«ጤሐይ ይብረድልሽ እንጂ!» አሏት ወይዘሮ እልፍነሽ እኚያኑ ጥርሶቻቸውን ገለጥ እያደረጉ።

«ቤቴ ሄጄ ማረፍ እፈልጋለሁ። ደህና ዋሉ!» ብላቸው ወጣች።

ወይዘሮ እልፍነሽ አሁንም እጃቸውን በወገባቸው ላይ አጣምረው እስር እስሯ እየሄዱ በሹክሹክታ ዓይነት «እይው ልጄ፣ እኔ እኮ ቀድሜ ጠርጥሪያለሁ፣

ብታይ አንቺ እግርሽ ወጣ ያለ ጊዜ እሱ ዘሎ ጥልቅ! ትናት ዘሎ ጥልቅ! ዛሬም ዘሎ ጥልቅ ሲል እያየሁ ሆዴ በጣም ይፈራ ነበር።» አሏት።

«ከቤት ይዟት ወጥቶ ያውቃል?»

«ኧረ በገዛ ቤትሽ ውስጥ እቴ! ደሞ የምን ወደ ውጪ! ሆሆይ...?» አሉና «ማናት ይቺ እቴ! ስሟን አምጪልኝ፣ ይቺ የወይዘሮ ዘነቡ ሠራተኛ?»

«ፋንትዬ?»

«እ! እሷ! ቲራቲር ስታይ አይደል እንዴ የምትውለው! እሷን ብትጠይቂያት እኮ ጉድ ትነግርሻለች።»

ሸዋዬ ነገሩ ሁሉ ገባት። ወሬው ሁሉ ከፋንትዬ እንደሚመነጭ ተረዳች። ለነገሩ ይሁንና ብትጠይቃት ደፍራ እውነቱን ላትነግራት እንደምትችል ገመተች። ለነገሩ ወሬ በትቷታል። ከእንግዲህ ታፈሡ ብቻ ቀረቻት፣ በእሷ ግምት አስቻለውና ሔዋንን የምታገናኝ ታፈሡ እንደምትሆን በማመን።

ሸዋዬ በዕለቱ እህል ውሃ አላሰኛትም። ሔዋን ምሳ አዘጋጅታ እየጠበቀቻት ቢሆንም ቤቷ እንደ ደረሰች የሔዋንን ዓይኖች ቀና ብላ እንኳ ሳታይ በቀጥታ አልጋዋ ላይ ወጥታ ጥቅልል ብላ ተኛች። በዚያው መሸ። ቀኑም በለሊት ተተካ፤ ያ ሁሉ ሆኖ ሸዋዬ በዓይኗ ላይ እንቅልፍ አልዞረም። ይልቁንም እንኳን ራሷ ለአልጋዋም አልመቻት ብላ በየደቂቃው በመገላበጥ ስታንቋቋት አደረች።

በማግስቱ ጠዋት ሔዋን ወደ ትምህርት ቤት ስትሄድ ልክ እግሯ ከቤት እንደ ወጣ ሸዋዬ ልታደርግ ስታስብ ከአደረችው እቅድ ውስጥ የመጀመሪያውን መፈፀም ጀመረች። ሔዋንና አስቻለው የተፃፃፉት የፍቅር ደብዳቤ ካለ ብላ ደብተሮቿን መፈተሽ ያዘች፤ ገፅ በገፅ እያገላበጠች፣ የደብተሮቹን መሸፈኛ እየገለጠችና ዘቅዝቃ እያራገፈች በረበረቻቸው። የሔዋን ቅያሬ ልብሶች አልቀሯትም። ኪሶቿን ሁሉ ዳበሰቻቸው። ግን ምንም ነገር ሳታገኝ ቀረች። ግን ደግሞ አንድ ነገር ትዝ አላት። የድካሟ ሲደክማት አልጋዋ ላይ ቁጭ አለች። ግን ደግሞ አንድ ነገር ትዝ አላት። የድካሟ ምክንያት ርሀብ ጭምር ነው። ከትናንት ምሣ ጀምሮ እስከ ዛሬ ቁርስ ሰዓት ድረስ ምንም አልቀመሰችምና ወደ ምግብ አዘነበለች። በእርግጥም ከነውዝፋ አጠቃለለችው። በንዴት ውስጥ ስለነበረች አጎራረሷ እንኳ ጤናማ አልነበረም፤ ቶሎ ቶሎ ጎሰጎሰችው።

ከታፈሡ ጋር የምትገናኝበት ሰዓት በመከራ ደረሰ። ጠዋት ወደ ታፈሡ ቤት መሄድ አልቃጣችም፤ በአንድ በኩል ስጡብ ነው የምትፈልጋት፤ በሌላ በኩ ደግሞ አስቻለውም ቢሆን ከታፈሡ ቤት አይጠፋምና። በሁለተኛው ፈረቃ የዕረፍት ሰዓት ነው ከታፈሡ ጋር የተገናኘችው። በዲላ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ መሀል ላይ በምትገኘው ባንዲራ ሥር ሆና ጠራቻትና አብረው እንደተቀመጡ ሸዋዬ ዓይኗን አፍጣ፣ ጥርሷን አግጣ፦

«ስሚ አንቺ!» አለቻት።

«ወይ» ታፈሡ ድንግጥ በማለት።

«እህቴን ከአበ-ልጅሽ ጋር አቃጥረሽ አበላሽሻት አይደል!?»

«እ?» ታፈሡ ሁለመናዋን ነዘር እያደረጋት።

«አላደረኩም በያ?»

«ጓደኛዬ ምን እያልሽ ነው?»

«ኧረ ጓደኛሽን ወዲያ ፈልጊ!»

«ሐእንቺ የበለጠ ምን ጓደኛ አለኝ?» አለቻት ታፈሡ ነገሩ እየገባት ጊዶ ፈገግ እያለች፡፡
«ጥሩ አቃጣሪ ኖረሻል! ጉድሽ ሁሉ ወጣ!»
«አበዛሽው ሸዋዬ!»
«አቃጣሪ ማለቴ? እንዲያውም ሲያንስሽ ነው!»
«ጨምሪልኝ! ኪም-ኪም-ኪም-ኪም!»
«አሁን ሳቂ! የምታለቅሽበት ጊዜ ይመጣል፡፡»
«አጠብቃለኋ! ኪም-ኪም-ኪም-ኪም...» ታፈሡ አሁንም፡፡
«እንዲህ ስትንከተከች ትንሽም አታፍሪ?» ሸዋዬ ውስጧ ብግን እያለ፡፡
«ምንም አላፍር ሸዋዬ! ምንም በማላውቀው ነገር ይህን ያህል ካልሽኝ ምናልባት ሁለቱ ተዋድደው ከአገኘኋቸው እንዲያውም እንዲያውም አጋባቸዋለሁ፡፡»
«ኣ?» ሸዋዬ ቆሽቷ አረረ፡፡
«በእርግጥ ሁለቱ ተዋደው ከሆነ ወደ ኋላ አልልም፤ ታይኝ የለ!» ብላት ታፈሡ ከሸዋዬ ፊት ዘወር አለች፡፡

ሸዋዬ ግራ ግብት እንዳላት ነበር ከዚያ በኋላ ያለውን ጊዜ ያሳለፈችው፡፡ የታፈሡ ሁኔታ ስለ ሒዋንና አስቻለው ፍቅር ብዙም ፍንጭ አልሰጣትም፡፡ በእርግጥ ስለዚሁ ጉዳይ ባለፈው ለሊት በምታስላስልበት ጊዜ በተለይ ከወይዘሮ አልፍነሽ የሰማችው ወሬ ለጊዜው ቢያናድዳትም በእውነትነቱ ግን ተጠራጥራዋለች፡፡ የሒዋን ማስወረድ ጉዳይ እምብዛም አልተዋጠላትም፡፡ የዚህ ዓይነት ችግር እሷ ራሷ ደጋግሞ ተከስቶባት ያውቃል፡፡ ሴት ልጅ የረጋ ደም ከወረዳት አካላዊም ሆነ ሥነ-ልቦናዊ ምልክት ይታይባታል፡፡ ያንን ግን በሒዋን ላይ አይታባት አታውቅም፡፡ ብቻ ከሁለት ወራት በፊት በከተማው ውስጥ በተከሰተ የጉንፋን በሽታ ብዙ መሰቃየቷን ታስታውሳለች፡፡ በዚያው ምክንያት ለሦስት ቀናት ያህል ከትምህርት ቤት መቅረቷም አይረሳትም፡፡ እሷም ‹እህቴ ታማብኛለች› ብላ ሰፈር ውስጥ ማውራቷ ትዝ ይላታል፡፡ ለወይዘሮ አልፍነሽ ወሬ መነሻው ያ ሊሆን ይችላል ብላም በማሰብ ምናልባት ሁሉም ነገር ከመሬት የታፈሡ አሉባልታ ሊሆን እንደሚችል በመገመት ቀቢፀ ተስፋዋን ስታለመልም ነበር ያደረችው፡፡

የመጨረሻው ጉድ የሚለየው ሒዋንን አፋጥጣ እውነቱን ስትናገር አለያም በሚያሳምን ሁኔታ ‹ፍፁም አላደረኩትም› ያለች እንደሆነ ብቻ መሆኑን በማመን የዚያኑ ዕለት ማታ ልትፈፅመው እየዛተች ከሥራ ቦታ ወደ ቤቷ ተመለሰች፡፡

ልክ በልሁና መርዕድ በአስቻለው ተልከው ወደ ሸዋዬ ቤት ማምራት በጀመሩበት ሰዓት ሸዋዬና ሒዋንም ተፋጥጠዋል፡፡ ሸዋዬ አልጋዋ ላይ ትራሷን በመደገፍ ቀና ብላ ወደ ግርጌዋ ሒዋንን እየተመለከተች፡-
«ስሚ አንቺ!» አለቻት፡፡
ሒዋን ደብተሮቿን ገለጥ ከደን ማድረግ ትታ «አቤት እት አበባ!» አለቻት፡፡
«በሰፈሩ ሁሉ የሚወራው ምንድነው?»
«ምን ተወራ እት አበባ?»
«የሚወራው ስለ አንቺ ስለሆነ ከአንቺ በላይ ማንም ሊያውቅ አይችልም»
«ስለ እኔ?» አለች ሒዋን ድንግጥ ብላ ጣቷን ወደ ራሷ እያመለከተች፡፡
«እውነተኛውን ነገር ልቦናሽ ያውቀው ይመስለኛል፡፡»

«እረ ምንም እት አበባ!» አለች ሒዋን፡፡ ግን ደግሞ ‹ልቦናሽ› ከሚል የሸዋዬ ቃል ጋር በተያያዘ ድንገት የእሷና የአስቻለው ጉዳይ ትዝ አላት፡፡
«መዋሸቱን ትተሽ እውነተኛውን ነገር ንገሪኝና ባይሆን...» ካለች በኋላ ሸዋዬ ነገሯን ጎተት አድርጋ ተወችው፡፡ ዓላማዋ ሒዋንን ለማባበልና እውነቱን ከተናገረች ሰላም ሊገኝ እንደሚችል አንጉታ ልታዋጣት ፈልጋ ነው፡፡

ሒዋን ግን በዚያ ሰዓት ለዚህ ነገር ዝግጁ አልነበረችም፡፡ ነገር ግን ሆዷ ፈራና ላብ ላብ ይላት ጀመር፡፡ ዓይኖቿን እያርገበገበች ከደን ገለጥ አደረገቻቸው፡፡
«ንገሪኛ!» አለቻት ሸዋዬ ቆጣ ብላ፡፡
«ምኑን እት-አበባ?»
«የሆድሽን ሁሉ!»
«በሆዴ ምንም የለም!» አለች ሒዋን አሁንም ጭንቅ ጥብብ እያላት፡፡
«ስሚ!» አለቻት ሸዋዬ ሲባ ጣቷን ቀስራ እያሾረችባት፡፡ «በዚህ ጉዳይ ላይ በቂ መረጃ አግኝቻለሁ፡፡ የእናቴም አደራ ስላለብኝ በቀላሉ የማልፈው እንዳይመስልሽ፡፡ እውነቱን ሳታወጪ አልለቅሽም፤ ዋ!» በማለት አስጠነቀቀቻት፡፡

‹የእናት አደራ› የሚለው የሸዋዬ ቃል የሒዋንን ልብ አነጠረው፡፡ የባሰ ጭንቅ ጥብብ አላትና ዓይኖቿም በእንባ ሞሉ፡፡ አቀርቅራ ዝም አለች፡፡

በዚህ ሰዓት ሸዋዬ በአንድ በኩል ለድል የተቃረበች መስሏት ለሒዋን ምላሽ ጓጓች፡፡ በሌላ በኩል ቁርጡን አውቃው ልታርፍ መሆኑ ተሰማትና ልቧ ድው ድው ማለት ጀመረ፡፡ ለአፍታ ያህል ዝም ብላ ስትመለከታት ቆየችና ጨከን በማለት፡-
«አንቺን እኮ ነው የምጠብቀው?» ስትል ድንገት ጮኸችባት፡፡
«ስለ ምን እንደሆነ እኮ አልገባኝም እት አበባ?» አለች ሒዋን አንገቷን ዘመም አድርጋ በማላዘን ዓይነት ሸዋዬን እያየቻት፡፡
«አስቻለው ስለተባለ ጎረምሳሽ ነዋ!» ስትላት ሒዋን መሬት ተሰንጥቃ ብትውጣት ተመኘች፡፡ ኩርምትምት ብላ ጭብጦ አከለች፡፡
«ጠየቀኝ እንጂ እኔ እኮ እሺ አላልኩትም!» አለቻት ሒዋን አንገቷን ትከሻዋ ውስጥ ቅብር አድርጋ በፍርሃት እያየቻት፡፡
«እ!» የሸዋዬ አፍ ፏ ብሎ ተከፈተ፡፡
«መች እት-አበባ!»
«ሲጠይቅሽ አልሰደብሽውም?» አለች ሸዋዬ ከድጋፏ ቀና ብላ ዓይኗን በሒዋን ላይ በማፍጠጥ፡፡
«ለምን እት አበባ?»

በቃ! አከተመ፡፡ ከእንግዲህ ወዲያ የሸዋዬ ልብ አስቻለውን የሚከጅልበት ሁኔታ የለም፡፡ አንድ ወንድ አንዲትን ሴት ለፍቅር ጠይቆ ‹እምቢ› ብትለው የፍቅር ዓይኑን ወደ እህቷ የመጣሉ ሁኔታ ብዙም የተለመደ አይደለም፡፡ ሸዋዬ በንዴት እርር ድብን ከማለቷ የተነሳ አንዳች ነገር ከወለል ላይ አንስታ በሒዋን ግንባር ላይ ልታላትምባት በዓይኗ በመፈለግ ላይ ሳለች «መጣን ቤቶች» ብለው በልሁና መርዕድ ድንገት በሯ ላይ ከች አሉ፡፡

ሸዋዬ በተለይ የበልሁን ድምጽ ስትሰማ አንዳች የሚውጥ አውሬ የመጣባት መሰላት፡፡ ድንግጥ በማለት ቶሎ ብላ በእንሶላና በብርድ ልብስ ጥቅልል ብላ ተኛች፡፡ ሒዋን ግን እንባዋ ዝርግፍ ብሎ ጉንጯ ሁሉ ረሰረሰ፡፡

«ምን ሆንሽ አንቺ!» አሳት በልሁ እሱም ድንግጥ ብሎ ወለሉ ላይ ቶካ ብሎ በመቆም፡፡

«ምንም በልሁዬ!» አለች ሔዋን፡፡

«አትዋሺ!»

«እናቴ ናፍቃኝ ነው፡፡» አለችው ሔዋን ድንገት አፏ ላይ የመጣላትን፡፡

«አንቺ ሽዋዬ!» አለ በልሁ እንደገና ወደ ሽዋዬ ዞር በማለት፡፡

ሽዋዬ ግን ዝም፡፡

«አንቺን እኮ ነው!» ብሎ በልሁ አንሶላና ብርድ ልብሷን ሊገፍፋት ሲል ሔዋን እየተሸቆጠቆጠች፡-

«ተው በልሁ! አሟት ነው፡፡» አለችው፣ ግን ደግሞ አፏን እየደመደመች፡፡

«ትነሳና ሀኪም ቤት እንውሰዳታ!» በማለት በልሁ ሽዋዬን ጨክኖ ገፈፋት፡፡ «ምንሽን ነው ያመመሽ?» ሲልም ጠየቃት፡፡

«ብርድ ነው፡፡»

«ሃኪም ቤት ሂጂ!»

«እኔ የሃኪም ዘመድ የለኝም!» አለችና ሽዋዬ ደበልጥ ኩርምት ብላ ተኛች፡፡

በዚህ ጊዜ በልሁ የሽዋዬ አሽሙር ገብቶት «ሃሃሃ...» ብሎ ሳቀ፡፡ በዚያው ወደ ሔዋን ዞር ብሎ ሲያያት ‹ውጡ ሂዱ› የሚል ምልክት ታሳያለች፡፡ በልሁ የሔዋን ጭንቀት ገባው፡፡ ነገር ግን የሽዋዬ ሁኔታ እናደደው፡፡ በመሀል አስቻለው የነገራቸው ዘዴ ትዝ አለውና «አስቻለው ጠፍቶብን ነው የመጣነው፣ ዛሬ ወዲህ ብቅ አላለም?» ሲል ጠየቀ በተለይ ሔዋንን እየተመለከተ፡፡

«አልመጣም» አለችው ሔዋን፡፡

በልሁ እንደገና ወደ ሽዋዬ ዞር አለና «አንቺስ ሽዋዬ?» ሲል ጠየቃት፡፡

«ሕሷ ናት የምታውቀው፣ እሷኑ አጥብቃችሁ ጠይቋት፡፡» አለችው፡፡

በልሁና መርዕድ ነገሩ ሁሉ ገባቸው፡፡ የአስቻለው ስጋት ትክክል ኖሯል፡፡ ተልዕኳቸውንም ጨርሰዋልና አስቻለውን እስከሚያገኙት ድረስ እየቸኮሉ ወደ ቤቱ ገሰገሱ፡፡

ምዕራፍ ሁለት

በዲላ ከተማ ዜሮ አምስት ቀበሌ ውስጥ ስምንተኛ መንገድ ላይ ፊቱን ለማታ ፀሃይ ሰጥቶ በተገነባው በወይዘሮ ዘነቡ እሰግድ ግቢ ውስጥ በስተጓሮ በኩል ያለው የሽዋዬና የሔዋን መኖሪያ ቤት ከጣሪያና ግድግዳው በስተቀር በውስጡ ይታይ የነበረ ትዕይንት ሁሉ ዛሬ መልኩን ቀይሯል፡፡ የሁለት የእትማማች ልቦች ጣውንቶች መኖሪያ ሆኖ ደስታ ርቆታል፡፡ በፍቅር ተስፋ ለምልመው የነበሩ ልቦች ዛሬ ተከድነዋል፡፡ በሳቅ ይፍለቀለቁ የነበሩ ጥርሶች ዛሬ ተከድነዋል፡፡ ኩልኩልት ዛሬ የሀዘን ድባብ ጥሎባቸዋል፡፡ ፈ ብለው ይታዩ የነበሩ ፊቶች ዛሬ ግን እኩርፈው እንደ ተንጠልጥለዋል፡፡ የአስቻለው እግሮች ተሰብስበው ቤቱ እንግዳ ናፍቆታል፡፡ የሽዋዬ ግን ይንጉዳሉ፡፡ የሽዋዬ ግን ተንጠልጥለዋል፡፡ የአስቻለው እግሮች ተሰብስበው ቤቱ እንግዳ ናፍቆታል፡፡ የሽዋዬ ግን

ሽዋዬ፣ ሔዋንና አስቻለው በየራሳቸው የሀሳብ ጎዳና ይንጉዳሉ፡፡ የሽዋዬ ግን ከሁሉም በተለየ ሁኔታ እንቅፋት የበዛበት ሆኗል፡፡ የሚቆጫት አስቻለውን ማጣቷ ብቻ አይደለም፤ በእሷ እምነት አስቻለውን የነጠቀቻት እህቷ በመሆኗ ከዚሁ ጋር ተያይዘው ይመጣሉ ብላ የምታስባቸው ማህበራዊ ቀውሶች ከወዲሁ ያስጨንቋት ይዘዋል፡፡ አስቻለውን በማፍቀሯና ከግንኙነታቸው መጥበት የተነሳ ‹የኔ ነው› ብላ ለሌላ ሰው ያወራችም ይመስላታል፡፡ ዛሬ ‹በእህቷ ተነጠቀች› የሚል አሉባልታ የሚነግ እየመሰላት ትሳቀቃለች፡፡ ምናልባት አስቻለውና ሔዋን ወደፊት ቢጋቡ ቤተሰባዊ ግንኙ ትልቋ እያለች ትንሿ፣ ሥራ ያላት እያለች ተማሪዋ አገባች፣ የሚል የዘመድ አገዛዝ ሹክሹክታም ሲነሳባት ይታያታል፡፡ ወደፊት በሚፈጠር ቤተሰባዊ ግንኙነት ሁልጊዜ እያየችው በቅናት እየተቃጠለች ልትኖር ነው፡፡ ዛሬ የገጠማትን የስሜት ሰቀቀን ሁልጊዜ እያስታወሰች እንዴት መኖር እንደምትችል ይቸግራታል፡፡ አዕምሮ ደግሞ ትንሽ የሀሳብ ቀዳዳ ከከፈቱለት ያቺኑ በማስፋት የጭንቅ ተባይ እየፈጠረ ያቅበጠብጣልና የሽዋዬ መንፈስ በስጋት ተወጠረ፡፡ ቀኑን ያለ ዕረፍት ሌሊቱን ያለ እንቅልፍ ታቀያይረው ጀመር፡፡

ከዚህ ሁሉ ጭንቀ የሚገላግላት ብቸኛ መንገድ አስቻለውና ሔዋንን ማለያየት ብቻ መሆኑ ታያት፣ ጨለማ የሆነባት ግን ማለያያው ዘዴ፡፡ አንዳንዴ ሔዋንን ወደ ቤተሰቦቿ መመለስ መፍትሄ የሚሆን መስሎ ይታያታል፡፡ ነገር ግን አስቻለው ሔዋንን፣ ሔዋን ደግሞ አስቻለውን እስካሉ ድረስ ከዚያስ ሄዶ ቢያመጣት? ወይም አስቻለው ከቤቷ ድርሽ እንዳይል ማድረግ ብትሞክርስ? ያም አያዋጣ፡፡ ሔዋን ራሷ ወደ እሱ ቤት ልትሄድ ትችላለች፡፡ እንደ በግ አትዘጋባት፣ እንደ ጥጃ አታስራት፤ ወይ ደግሞ ስራዋን ትታ እሷን ስትጠብቅ አትውል! ሁሉም መንገድ የማይጨበጥ ህልም ሆኖባታል፡፡

ከመዋል ከማደር አንድ የተስፋ ብልጭታ ብቻ ማየት ጀመረች፤ ለዚያውም ይህ ነው ብላ የምትጠብቀው ግልጽ ውጤት ሳይኖር፡፡ ያም ቢሆን ከራሱ ከአስቻለው ያገኘችው ፍንጭ ነው፡፡ ከጥቂት ወራት በፊት አንድ ቀን እሷና አስቻለው በአንድ ቡና ቤት ውስጥ ይዝናናሉ፡፡ የተቀመጡበት ቦታ መስኮት አጠገብ ስለነበረ መንገዱ ይታያቸዋል፡፡ አስቻለው ድንገት ባርናባስን መንገድ ላይ ያየውና ሽዋዬን ጎሸም አድርጎ «ያን ሰውዬ ተመልከች» ይላታል፡፡

«የቱን?»

«ደማቅ ሰማያዊ ካኪ የለበሰውን፡፡»

«እሺ አየሁት»

«ዲላ ሆስፒታል ውስጥ ድርብ ስልጣን ያለው ነው::» ካለ በኋላ በእሱና ባርናባስ መካከል ያለውን ያለመግባባት ከመነሻ ጀምሮ አሁን እስካሉበት ጊዜ ድረስ ያለውን ሁኔታ እንደ ቀልድ ያጫውታታል:: ይህ ነገር በሸዋዬ ልብ ውስጥ እስከ አሁን አለ::

ግን ደግሞ አስቻለው አላወቀም እንጂ ሸዋዬና ባርናባስ በደንብ ይተዋወቃሉ፤ ያውም ከስምንት ዓመታት በፊት ጀምሮ:: ሰበቡ ሸዋዬ ትምህርቷን እንደ ጨረሰች በመምህርነት ተመድባ ወደ ያቤሎ መሄዷና ባርናባስ ደግሞ በወቅቱ የያቤሎ ጤና ጣቢያ የአስተዳደር ክፍል ኃላፊ ሆኖ ይሰራ የነበረ መሆኑ ነው:: ሸዋዬ ያቤሎ ደርሳ ከመኪና እንደ ወረደች ማረፊያ የት እንደምታገኝ ስትጠይቅ የመኪና ተራ ልጆች ወደ አንድ የማረፊያ ቦታ ይወስዷታል:: ቤቱ ሆቴል ቤት አልነበረም፤ ነገር ግን ግቢው ውስጥ በርካታ በእልበርጎ ዓይነት የተሰሩ ክፍሎች አሉት:: ድንገተኛ እንግዳም ያርፍባቸዋል:: ለወር ኮንትራትም ይሰጣል:: ባርናባስም ከእነዚያ ክፍሎች አንዷን በኮንትራት ይዞ ብቻውን ይኖር ነበር::

ሸዋዬ ከእነዚያ ክፍሎች በአንዷ ውስጥ አድራ በማግስቱም እዚያው ትደግማለች:: በሦስተኛ ቀንም እንዲሁ:: በኋላም ከዚያ የተሻለ መኖሪያ እንደማታገኝ ሲገባት ልክ እንደ ባርናባስ ክፍሏን በኮንትራት ይዛ ትቀመጣለች:: ከመዋል ከማደር ከባርናባስ ጋር ይተዋወቃሉ:: ቀስ በቀስ ይቀራረባሉ:: ይግባቡና ይፋቀራሉ:: ባርናባስ መጨረሻ ላይ ልክ እንደ ደባል ሆነው አብረው መኖር ይጀምራሉ:: ባርናባስ በዕድሜው ጠና ያለ ቢሆንም ለሸዋዬ ግን ይመቻታል:: እሷም ለእሱ ትሞቀዋለች:: ያ ሁሉ ሲሆን ባርናባስ ባለ ትዳርና የልጆች አባት መሆኑን እንዲሁም ቤተሰቦቹ ዲላ ከተማ ውስጥ እንደሚኖሩ ሸዋዬ አታውቅም ነበር:: በእርግጥ ወደ ዲላ አዘውትሮ እንደሚሄድ ታውቃለች:: ነገር ግን ‹ለስራ ጉዳይ› እያለ ስለሚያታልላት እሷም አትጠረጥር ነበር::

በዚሁ ሁኔታ ለአንድ ዓመት ያህል ከቆዩ በኋላ ድንገት የባርናባስ የሰባት ወር ህጻን ልጁ ይሞትና ከዲላ መልዕክት የተቀበሉ የመሥሪያ ቤቱ ሠራተኞች መርዶው እንዲደርሰው ያደርጋሉ:: በወቅቱ ሸዋዬ ማመን ቢያቅታትም ነገር ግን ከማግስቱ ጀምሮ ከባርናባስ ቤት ወጥታ ትሄዳለች:: በዚያው ትቀራለች:: ፍቅራቸውም ይቋረጣል::

ባርናባስ ከልጁ መሞት በኋላ በያቤሎ ብዙ አልቆየም:: እድገትና ዝውውር አግኝቶ ዲላ በመግባት ከቤተሰቡ ጋር ይቀላቀላል:: ይሁንና የባርናባስና የሸዋዬ መለያየት የከረረ ጠብ አላስከተለም፤ ቆይቶም ቢሆን ከፍቅር ውጭ ያለ ግንኙነት ማስቀጠል የሚችል እርቅ ፈጽመዋል:: ሸዋዬ ዲላ ከመጣችም ወዲህ ከአለፈ አገደም እየተገናኙ ሰላምታ ይለዋወጣሉ:: አስቻለው ስለ ባርናባስ ያወራት በነበረ ጊዜ ሸዋዬ ይህን ሁሉ በሆዷ ይዛለች፡ እሷ ግን ስለ ባርናባስ ለአስቻለው ትንፍሽ አላለችም::

ምን ሊያደርግላት እንደሚችል በውል ባይታወቃትም ሸዋዬ ለዛሬው ጭንቋ መላ ስታፈላልግ ባርናባስ ትዝ ብሏታል:: የአስቻለው አለቃ ነውና፣ በዚያ ላይ አይስማሙምና፣ ‹ለችግሬ መፍትሄ የሚያመጣ መላ ያፈላልግልኝ ይሆን?› እያለች ለአንድ ወይም ለሌላ ጉዳይ በልቧ ታውጠነጥነው ጀመር::

የሸዋዬ ሀሳብ በዚህ መልኩ ሲነጉድ ሔዋን ግን ስለ ጭንቀቷ እንጂ ችግሯን ስለምታቃልልበት መንገድ የሚታያት አንዳች ነገር የለም:: ሆነም አልሆነ

ነገሩ ይበርድላት ዘንድ መጓጓት ብቻ ነው:: ከዚያ ባለፈ አስቻለው ወደዚያ ግድም ድርሽ እንዳይል የጠበቀ አደራ በታፈሡ በኩል ልካበታለች:: ነገር ግን አደራውን ስለመቀበሉ እርግጠኛ አይደለችም:: ድንገት የመጣ እንደሆን እያለች ከመሳቀቅ አልዳነችም::

አስቻለው ደግሞ ያኮረፈው ወይም የሚያኮርፈው ሰው ስለሌለ ቤቱ ሰላም ይሁን እንጂ አዕምሮው ግን እረፍት አጥቷል:: ዓይኖቹም ከእንቅልፍ ተለያይተዋል:: በአካል አልጋው ላይ ተኝቶ ሀሳቡ ያለው በሸዋዬ ቤት ውስጥ ነው:: በልሁና መርዕድ የነገሩት የሸዋዬና የሔዋን የተበላሸ ግንኙነት የጭንቁ ሁሉ መነሻ ነው:: በዚያ ላይ ወደዚያ ቤት ድርሽ እንዳይል ሔዋን በታፈሡ በኩል ልካበት መልዕክቱ ደርሶታል:: በሁለቱ እህትማማቾች መካከል ስላለው ግንኙነት ለውጥ ሁሉ መኖሩን ወይም ያለመኖሩን ማወቅ እንዳይችል የመገናኛ መንገዶች ሁሉ ተዘግተዋል:: እሱም ቀረ፤ ታፈሡም አትሄድ:: የሔዋን ሁኔታ ጨለማ ሆኖበት በሀሳብና በጭንቀት ይሰቃያል:: በዚህ ሁኔታ ለአንድ ሳምንት ያህል ቆይቶ ጭንቀቱ መተንፈሻ ሲያሳጣው ድንገተኛ ስሜት ወደ ሸዋዬ ቤት ሂድ ሂድ አለው፤ ሩጥ ሩጥ!!

ዕለቱ ዕረቡ ነው፣ በዚያ ዕለት እሱ የዘጠኝ ሰዓት ሥራ ገቢ ነው:: ሔዋን የጠዋት ተማሪ፣ ሸዋዬም የከሰዓት ፈረቃ ሥራ ገቢ መሆናቸውን ያውቃል:: በዚህ አጋጣሚ ለአፍታም ቢሆን ሔዋንን አየት አድርጎት በዚያው ወደ ሥራ ሊሄድ ወስና ከቀኑ ሰባት ሰዓት አካባቢ ሦስተኛ መንገድ ላይ ከሚገኘው ቤቱ ተነስቶ ወደ ሸዋዬ ቤት አመራ:: መንገዱ እስከ አሥር ደቂቃ ይወስድበት የነበረ ቢሆንም በዕለቱ ግን በአምስት ደቂቃ ውስጥ አረምርሞት ከወይዘሮ ዘነቡ ግቢ በር ላይ ደረሰ:: ገርበብ ብሎ በተከፈተው የውጭ በር በኩል አንገቱን ብቅ አድርጎ ወደ ውስጥ ሲመለከት ወይዘሮ ዘነቡ ከቤታቸው በረንዳ ላይ ሆነው አፈር በተሞሉ ጣሳዎች ላይ የተከሏቸውን አበቦች ሲንከባከቡ አያቸው:: ወትሮም አይፈራቸውም ነበርና ሲያያቸው አልደነገጠም:: ትህትና የተሞላበት ሠላምታ አቅርቦላቸው ወደ ጓሮ አለፈ፣ ወደ ሸዋዬ ቤት:: ፊት ለፊት ሲያይ ቤቱ ክፍት ነው:: እንደ ሌባ ግራ ቀኙን ሰሰል እያደረገ በፍጥነት ተራምዶ በሩ ላይ ሲደርስ ሔዋን ፊትለፊት ባለችው ፍራሽ ላይ ቁጭ ብላ እንጀራ በሳህን አትርባ ምሣ ስትበላ አያት:: ፈገግ ብሎ ወደ ውስጥ ገባና ወደ እሷ ጠጋ ሲል ሲል ሔዋን በድንጋጤ ኩርምትምት ስትል አያት::

«አይዞሽ» ብሎ አቅፎ ደግፎ ሲያፅናናት አሁንም ድንገት «አ!» የሚል ድምጽ ተሰማው:: ወደ ግራው ዞር ብሎ ሲያይ ሸዋዬም ከጓዳዋ በር አጠገብ ቁጭ ብላ እንጀራ በሳህን ይዛ ምሣ ትበላለች::

«እንዴ!» አለ አስቻለው ሳያውቀው ጮክ ባለ ድምጽ:: በድንጋጤ ስሜት ውስጥ ሆኖ ሸዋዬን አከታትሎ ሲያያት ‹አ!› ስትል ተከፍቶ በቀረው አፏ ውስጥ የጎረሰችው እንጀራ ከነነፍሱ ታየው::

«ምነው?» አለ አስቻለው የሚለው ጠፍቶበት::

«ና ብላ» አለችው ሸዋዬም የመንተ ዕፍረቷን::

አስቻለው ግብዣውንም አልተቀበለ:: ለሠላምታም እጁን አልዘረጋ:: ወደ ሔዋንም መጠጋት አልቃጣ:: በድንጋጤ ተርገድግዶ የነበረውን ወገቡን ለማሳረፍ ብቻ ዱካ ላይ ቁጭ አለና «ሰላም ናችሁ?» አለ አጎንብሶ ግንባሩን እያሻሸ::

«ክብሩ ይስፋ!» አለችው ሸዋዬ ልቧ ድው ድው እያለና እጇ እንጂራ መቋረስ አቅቶት እየተንቀጠቀጠች::

ለአፍታ ያህል በመሀላቸው ፀጥታ ሰፈነ::

በፀጥታው መሀል አንዳቸው ለላኛቸውን በየትንፋሻቸው ስር ያደምጡ ኖሯል:: ሒዋን የሸዋዬን ሁኔታ ሰለል አድርጋ የማታያት መስሏት በእጅና በዓይን ምልክት እስቻለው ተመልሶ እንዲሄድ ስትጠቁመው ሸዋዬ ድንገት አየቻት:: በሊያቺው ቅጽበት ሸዋዬ በእጇ ይዛው የነበረውን የእንጀራ ሳህን መሬት ላይ ልትጥል አደረገችና:-

«እሱ ለምን ይሄድብሽ! እረ እኔ እወጣልሻለሁ!» ብላት ከመቀመጫዋ ብድግ በማለት ከቤት ምንጥቅ ብላ ወጣች:: እስቻለውና ሒዋን በድንጋጤ ክው ብለው ተፋጠጡ::

«በእናትህ እስቹ ሂድ! ተመለስ!» አለችው ሒዋን እየተሽቆጠቆጠች::

«አልሄድም!» አላት እስቻለው በሰጭት ባለ አነጋገር::

«በእናትህ ለኔ ስትል!» አለች ሒዋን አሁንም እጆቿን እያርገበገበች::

«ምንድነው እህትሽን እንዲህ የሚያደርጋት?» ሲል ፊቱን ኮስተር አድርጎ በብስጭት አነጋገር ሒዋንን ጠየቃት::

«እሷን ተዋት እስቹ! አንተ ብቻ ለኔ ስትል ሂድ! በእናትህ!»

እስቻለው ለጊዜው የሚያደርገውን አጣና ግራ ግብት ብት አለው:: ውስጡ ተጨንቆ ትንበስ ብሎ ግንባሩን ሲያሻሽ ከቆየ በኋላ ድንገት ከተቀመጠበት ብድግ አለና «እስቲ ቆይ እሺ የምትል ከሆን ልመልሳት::» እያለ በፍጥነት ርምጃ ወደ ውጭ ገሰገሰ:: ከግቢ ወጥቶ ግራና ቀኝ ሲመለከት ሸዋዬን በግራ በኩል በርቀት አያት:: ድምጹን ከፍ አድርጎ «ሸዋዬ! ሸዋዬ! ሸዋዬ!» ሲል ተጣራ:: ሸዋዬ ግን ዝም ብላው ርምጃዋን ቀጠለች:: ልትሰማው እንደምትችል ይገምታል፣ ነገር ግን ዝም ስላለችው ተናደደና ወደ ሒዋን ተመለሰ::

«መነብለሷ ነው?» አለ ወደ ቤት እየገባ::

«ሄደች?» አለችው ሒዋንም ጭንቅ ጥብብ ባለ ሁኔታ እስቻለውን እየተመለከተች:: ዓይኖቿንም እንባ እንባ ይላቸው ጀመር::

«ምንም ማድረግ አልችልም:: እየጠራኋት ዝም ብላ ወደ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አቅጣጫ ሄደች::» አላት እዚያቸው ዱካ ላይ ቁጭ ብሎ ግንባሩን እያሻሸ::

«ግን ለምን መጣህ እስቹ?» አለችው ሒዋን::

«ለመሆኑ የክሰዓት ፈረቃ ገቢ አልነበረችም እንዴ? በእሁኑ ሠዓት ቤት ውስጥ አትኖርም ብዬ እንቺን ስለ አሰነባበትሽ ጠይቄ ለመሄድ ነበር የመጣሁት!»

«የሁለቱም ፈረቃ ተማሪ ሥራ ዘመቻ ላይ ስላረፈደ ከሠዓት ትምህርት ስላልነበረ ነው:: አሁንም ሂድ እስቹ! ደሞ ተመልሳ ከመጣች ጉዱ ይፈላል::»

«ሰሞኑን እንዴት ነበራችሁ?»

«ሰላም ነበርን::»

እስቻለው በደረቁ ፈገግ ብሎ እያያት: «ሰላም እስመሆናችሁንማ ይኸው እያየሁት ነው:: ግን የተለየ ሁኔታ ገጥሞሽ ከሆን ብዬ እንጂ!?»

«አንተ የምትረዳኝ ከሆን ወደፊት የተሻለ ሰላም ላገኝ እችላለሁ::»

«ምን ልርዳሽ?»

«ብቻ አንተ ዳግመኛ ወዲህ አትምጣ:: እኔ አንዳንዴ ወደ አንተ ብመጣ ይሻላል::»

«አይመስለኝም::»

«እመነኝ እስቹ፣ አልፎ አልፎም ቢሆን ሲመችኝ እመጣለሁ:: እኔ ወደ አንተ የምመጣው የእት አበባን ሁኔታ አጥንቼ ነው:: አንተ ግን የለችም ብለህ ብትመጣ ልክ እንደ አሁኑ ልንጋለጥ እንችላለን:: ስለዚህ እስቹ፣ እባክህ ዳግመኛ ወደዚህ ላትመጣ ቃል ገብተህልኝ ሂድ::»

እስቻለው የሒዋን ዘዴና ዓላማዋ ገባው:: እሱም በቀላሉ ሊሸከመው የሚችለው አደራ ነው:: በትካዜ እስተያየት ለአፍታ ያህል ሲመለከታት ቆየና ከመቀመጫው ብድግ በማለት «ተቀብያለሁ ሒዶ:: አሁንም ልሂድልሽ:: ግን ሸኚኝ» አላት::

የእስቻለው ‹ሸኚኝ› ቃል ለሒዋን ትርጉሙ እየገባት ሄዷል:: እሷም ከፍራሿ ላይ ብድግ ብላ ወደ እስቻለው ራመድ በማለት ከፍቶ በጠበቃት የእጆቹ እቅፍ ውስጥ ገብታ ደረቱ ላይ ልጥፍ አለች:: በመሳሳም ናፍቆታቸውን ተወጡ::

«የፈለገው ችግር ይምጣ፣ ምንጊዜም ከአንቺ ጋር ነኝ::» አላት እስቻለው አንገቷን እቅፍ አድርጎ ቁልቁል እያያት::

«እኔም እስቹ!»

ሸዋዬ ከቤቷ ስትወጣ የት መሄድ እንደነበረባት እቅዱ አልነበረም:: ሰሞኑን ነገሮች ሁሉ ረገብ ብለው ስታይ ትንሽም ቢሆን ቀዝቀዝ ብላ የነበረ ቢሆንም የዛሬው የእስቻለው ቤቷ ድረስ መምጣት ግን እሳት ለኩሶባት ንዴቷን ቀስቅሶባታል:: ከወጣችም በኋላ ጅው ብላ መሄዷ እስቻለውና ሒዋን ብስጭቷን አይተው ለወደፊቱም እንዲፈሩ ማድረግ ነበር:: ያ ሁሉ ሆኖ አሁንም ጉዞዋን ወደፊት ቀጠለች:: የዲላ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትን ወደ ቀኝ በመተው ሄዳ ሄዳ ወደ ኳስ ሜዳው ደረሰች:: በሜዳው አሻግራ ፊት ለፊት ስትመለከት የዲላ ሆስፒታል ሰፊ ባለ ሜዳ ላይ ተንጣሎ ታያት:: ያኔ ባርናባስ ወየሶ ትዝ አላት:: አሁንም ለራሷ «አሃ» አለች ቀጥ ብላ በመቆም ብቻዋን እየተነጋገረች:: «ለምን ባርኔ ጋ አልሄድም?» አለች:: ባርናባስን ስታቆላምጠው ‹ባርኔ› እያለች ነው::

ሜዳዋንም ለኳስ ሜዳ ተብሎ የተናደውን ገደል ተንደርድራ ወረደችው:: የእስፋልት እቋርጣት አለፈች:: ከዚያም አልፋ ከዲላ ወደ ሞያሌ የሚወስደውን መንገድ ተሻገረች:: ብላ ብላ የቆፈን የኮረንኮች መንገድ ትውረገረግበት ጀመር:: ደግነቱ ከቤቷ የወጣችው ትምህርት ቤት ስትሄድ የለበሰችውን ልብስ እንደለበሰች ስለሆነ አለባበሷ ወደትም ብትሄድ አያሳፍራትም:: ከቦርሳ በስተቀር የሚቀራት ነገር የለም:: አንገቷ ላይ ቀላ ያለ ቡኒ ቀለም ያላት ስከርፍ አጣፍታለች::

ለሆስፒታሉ እንግዳ ናት:: ታማ ልትታከም ወይም ታማሚ ልትጠይቅ እንኳ ገብታበት አታውቅም:: ይሁን እንጂ ሆስፒታሉ አደናጋሪ ሁኔታ የለውም:: ህንፃዎቹ በአንድ አካባቢ ችምችም ብለው የተሰሩ ናቸው:: ቀሪው ደግሞ ወለል ያለ ሜዳ:: ቀጥታ ወደ ህንጻዎቹ ስትጠጋ የተጓዘችበት መንገድ ከድንገተኛ መቀበያ ክፍሎች አካባቢ አደረሳት::

ሰዓቱ ወደ ስምንት ተኩል ገደማ ይሆናል። በርካታ ሀመምተኞች በአግዳሚ ወንበሮች ላይ ተቀምጠው ወረፋቸውን ይጠባበቃሉ። ከሀመምተኞቹ ጀርባ ቆም ብላ ወደ ቀኝ አቅጣጫ ስትመለከት ረጅም የመተላለፊያ ኮሪደር ታያት። ኮርደሩ ልትልበት አስባ ጥቂት ከተራመደች በኋላ አሁንም ወደ ቀኝ ስትመለከት የአስተዳደር አገልግሎት ሃላፊ የሚል የቢሮ መለያ አነበበች።

«አሃ! የባርኔ ቢሮ ይኸ መሆን አለበት» አለችና ቆም ብላ ወደ ቢሮ ስትመለከት ከኋላ በኩል የሰው እጅ ትከሻዋ ላይ ቸብ አደረጋት፣ ባርናባስ ወየሰ። ሸዋዬ ድንግጥ አለች። «እንዴ! አለህ እንዴ?» ስትል ጠየቀችው ምን እያለች እንደሆነ ለራሷም ሳይገባት።

«የሸዋ ዛሬ ከየት ተገኘሽ?» አለና ባርናባስ እጇን ጨብጦ እንደገና ደረት ለደረት ተሳሳሙ። ባርናባስ ሸዋዬን ሲያቀላምጥ ብሸዋ እያለ ነው።

«ጉብኝት መጥቼ።» አለችው ሸዋዬ ሳቅ እያለች።

«ጥሩ ነዋ! የሚጎበኘም ሞልቷል፤ የሚያስጎበኝም አለ።» አላት ባርናባስ እጁን ትከሻዋ ላይ ጣል አድርጎ በረጅም ቁመቱ ቁልቁል እየተመለከታት።

«አለፈልኝ! ኪኪኪኪ ...»

«እኔ ጋ ነው የመጣሽው?» ሲል ጠየቃት እሷንም ቢሮውንም ተራ በተራ እየተመለከተ።

«አይ!» ሸዋዬ ተሽኮረመመች።

«ቢሮዬ አጠገብ ቆመሽ ሳገኝሽ ጊዜ እኮ ነው። ጎራ በያ፣ ሻይ ቡና ልበልሽ»

«በዚህ ሙቀት ሻይ ቡና?»

«ለስላሳም ይኖራል።» አለና ባርናባስ እጇን ይዟት ወደ ቢሮው አመራ።

በሸዋዬ ዓይን የባርናባስ ቢሮ ልዩ ነው። ስፋቱ፣ ጽዳቱ፣ የመስኮቶቹ መጋረጃዎችና የወለሉ ምንጣፍ ዓይን ይማርካሉ። የመጋረጃው ቀለም ነጣ ያለ ብርቱካናማ ነው፤ ለቢሮው ልዩ ብርሃን ሰጥቶታል። የእንግዳ መቀበያው ጠረጴዛ ስፋትና የወንበሮቹ ብዛት አስደነቃት። በቢሮው የግድግዳ ጥግ ዙሪያ ተጨማሪ ወንበሮችም አሉ። ያቤሎ ጤና ጣቢያ ውስጥ በነበረበት ጊዜ በአንድ ጥብብ ባለች ክፍል ውስጥ ከአንድ ሜትር የማትበልጥ ጠረጴዛውንና የሚቀመጥባትን ደረቅ ወንበር አስታውሳ ስታወዳድር አሁን ግን ገነት ውስጥ እንደገባ ቆጠረችው።

«አንተ! ቢሮህ ግን እንዴት ያምራል!?» አለችው የቢሮውን ዙሪያ በዓይኗ እየቃኘች።

«ከዚህ የበለጠ ስንት ዓይነት ቢሮ አለ እባክሽ! ደሞ ይኸ ቢሮ ሆኖ?» አለና ወንበር ሳብ አድርጎ እንድትቀመጥ ጋበዛት።

«ጡር አትናገር!»

ባርናባስ በእንግዳ መቀበያው ጠረጴዛ ላይ ከሸዋዬ ፊትለፊት ቁጭ አለና በደወል ተላላኪ ጠርቶ ለእሱ ቡና ለሸዋዬ ለስላሳ አዘዘ።

«ይኸ ሁሉ ወንበር ምን ያረጋል?» ስትል ጠየቀችው።

«ሀአ! የባለ ስልጣን ቢሮ እኮ ነው፣ ስንት ዓይነት ስብሰባ የሚካሄድበትና ውሳኔ የሚሰጥበት።» አለና ባርናባስ በተቀመጠበት ላይ ፈነስነስ አለ።

«በምን በምን ጉዳይ ላይ ትወስናለህ?»

«በፖለቲካ ብትይ፣ በአስተዳደር ጉዳይ ብትይ፣ በደረጃ ዕድገት፣ በዲስፕሊን...ወዘተ!» አለና ሸዋዬን ፈገግ ብሎ እያየ በቀልድ ዓይነት አነጋገር፦

«በፍቅር ላይ ብቻ ነው መወሰን ያቃተኝ!» አለና «ሃሃሃሃ...» ብሎ ለራሱ ስቆ ሸዋዬንም አሳቃት።

«ስትል?» አለች ሸዋዬ በትንድቢ ስር እያየችው።

«የምወዳት ሴት እንዳትጠላኝ አድርጌ መወሰን! ሃሃሃሃ...»

«ውይ፣ አልቀረብህም!»

«ያን ማድረግ ብችል ኖሮ አንቺ መች ታመልጪኝ ነበር!» አለና እንደ ቁም ነገር አድርጎ «ግን የሸዋ፣ ይህን ያህል ወራት ዱላ ውስጥ ስትኖሪ እንዴት ወደ ቢሮው ሄጄ ልጠይቀው አላልሽም?» ሲል ጠየቃት።

«ሆሆይ! ደሞ የሰው ባል! ለአለፈውም ይቅር ይበለኝ። ያም ቢሆን ሳላውቅ ያደረኩት ስለሆነ ከኀኔው የአንተ ነው።» አለችና የቀረበላትን ሚሪንዳ ጎንጨት አለች።

ባርናባስ በስጨት እንዳለ ዓይነት እጁን ወንጨፍ እያረገ «የሸዋ ደሞ ዝም ብለሽ ነው፣ ይኸን ሚስት፣ድስት፣ ትዳር ምናምን፣ የምትይውን ነገር ለምን አትተይም? ፍቅር በትዳርና በሰማኒያ ይገለጽ መሰለሽ እንዴ?» አላት ቡናውን እያማሰለ።

«ብታርፍ ይሻልሃል»

«በተለይ በአንቺ ነገር መቼም ቢሆን የምቆርጥ አይመስለኝም»

«ግን ባለቤትህ ደህና ናት?»

«ለራሷ ትኖራለች»

«ማለት?»

«እዚህ ገባህ፣ ከዚያ ወጣህ አትለኝም!»

«መረን ለቃሃለቻ!»

«ኧረ ዛሬ ከየት ተገኘሽ የሸዋ? እስቲ ስለ አንቺ እንጨዋወት?» ብሎ ቡናውን ፉት አለ።

«አንተን ልጠይቅ! ኪ-ኪ-ኪ-ኪ...»

«ጎሽ የኔ ወለላ! አንቺ እኮ ዱሮም ቁም ነገኛ ነሽ! ሰውየው እኔ ሆኜ እንጂ ...» ብሎ ነገሩን ተወት ሲያደርገው ሸዋዬ ቀጠላች።

«ባትሆንስ?»

«ልብ ቢኖረኝ ኖሮ እግርሽ ላይ ወድቄ ይቅርታ መጠየቅ ነበረብኝ። ግን ዛሬ ነገ ስል ---» አለና ንግግሩን ቆረጥ አድርጎ አሁንም ቡናውን ፉት አለ።

«ደሞ እንደገና?»

«የቆየ ነገር እኮ ሲታደስ ከበፊቱ ይበልጣል። ሃሃሃሃ...»

«ይልቅስ ስለ መጣሁበት ጉዳይ ልጠይቅህ!»

«ምን ልርዳሽ?»

«አንድ ሴት፣ በተለይ ልጃገረድ ማስወረድ አለማስወረዷን በሀኪም ምርመራ ማወቅ ይቻላል?» ስትል ጠየቀችው።

«ሀኪሞችን አነጋግሮ መረዳት ይቻላል። ግን በዚህ ዙሪያ ምን ችግር ገጠመሽ?» ሲል ጠየቃት።

«በእናትህ ባርኔ ዶክተሮችን ጠይቅና ንገረኝ!»

«ማነጋገር እችላለሁ!»

«ይገርምሃል፤ በአንዲት እህቴ ጉዳይ ተቸግሬአለሁ።»

«አስወርዳ?»

«መሰለኝ!»

«ብአገር ባህል ወይስ በህሊም?»

«እረ የእናንተ ሠራተኛ በሆነ ሰው! ደሞ የምን ባህል አመጣህ! ያማ ሆ[illegible] ራሴ ተከታትዬ ሴሕግ አቀርበው አልነበር? ያስቸገረኝ...» ብላ ሸዋዬ የተበሳጨ[illegible] ለመምሰል ራሷን ወዘወዘች።

«ማነው የኛ ሰው?» ሲል ጠየቃት ባርናባስ ግንባሩን ቋጠር አድርጎ።

«ሀሆይ! ደሞ ያለ በቂ ማስረጃ የሰው ስም ጠርቼ ዕዳ ልግባ» አለችና ዓይኖቿን ወደ ጣሪያ ሰካች ።

«እንዴ! የምታወሪው እኮ ለኔ ነው። ፖሊስ ጣቢያ ወይ ፍርድ ቤት ያለ[illegible] መሰለሽ እንዴ?»

«አንተስ ብትሆን የፖርቲ አባል አይደለህ?»

«ታዲያ እኮ የኛ ዋንኛ መለያ ምስጢር መጠበቅ ነው።»

«ለማንም አታወራ?»

«እንዴ.... የአንቺን ምስጢር!»

ሸዋዬ እንደ ማቅማማት ብላ የላይኛውን ከንፈሯን በጥርሷ ነከስ አድርጋ ወደ ላይ አንጋጣ እያየች ታስብ ጀመር። ወይዘሮ እልፍነሽም ትገ[illegible] አሏት። ከእሳቸው የሰማችው ወሬ ነውና እውነትነቱንም ተጠራጥራ ፍርሀት ተሰማት።

«አትፍራ የሸዋ! እንደውም እንዲህ ያለ ነገር በራሳችን ባለሙያዎች ተሰርቶ ካገኘን ርምጃችን የከፋ ነው።» አላት ተመልሶ ወደ ጠረጴዛው ደገፍ እያለ።

«እኔ እኮ የጨነቀኝ የማስረጃው ጉዳይ ነው።»

«ለዚያ ምን አስጨነቀሽ? ፍንጭ ካገኘን እኛው ራሳችን እየሰረሰርን እንገባበት የለ? ዋናው ጥቆማው ነው።»

«አስቻለው የሚባለውን ነርስ በደንብ ታውቀዋለህ?»

ባርናባስ አንገቱን መዘዝ፣ ዓይኑን ፈጠጥ አድርጎ እንደውም ሾክክ ባለ አነጋገር «እሱ ነው እንዴ?» ሲል ጠየቃት።

ሸዋዬ ከንፈሯቿን አጣብቃ አንገቷን በእውንታ በመነቅነቅ አረጋገጠችለት።

በዚህ ጊዜ ባርናባስ ፈጠን ብሎ በመነሳት ወደ ወንበሩ አለፈ። ወረቀትና እስኪርብቶ አዘጋጀ። የአስቻለውን ስም ጻፈና፦

«ድርጊቱን የፈጸመበትን ወቅት ታውቂዋለሽ?» ሲል ጠየቃት።

«በትክክል አላውቅም።»

«እንደው በግምት?»

«ምናልባት ሁለት ወይም ሦስት ወራት!»

«እንዴ! ይኸማ ትናንትና ነው በይኛ!» በማለት አዳነቀና «የእህትሽ ስም ማን ይባላል?» ሲል ጠየቃት።

«ሔዋን ተስፋዬ።»

«በእሷ በኩል ፍንጭ ማግኘት ይቻል ይሆን?»

«ሀሆይ!» አለች ሸዋዬ ጮክ ብላ። «እሷ ብትጠየቅ ‹አስቻለው የሚባል ሰው አላውቅም› ነው የምትለው። በዚያ በኩል አትልፋ።»

«ቆንጠጥ ብናደርጋትስ?»

«ብትፈንክቷትም! እንዲያውም አንዳች ነገር ሳያስነካት የቀረ አይመስለኝም፤ የእሱ ነገር ሲነሳባት አትወድም።» አለችው በመስኮት በኩል ወደ ውጭ እያየች።

«በቃ ተይው! ይህን ያህል ፍንጭ ከተገኘ የትም አያመልጥም። ቀስ ተብሎ ይመረመራል።» አለና ደስታ ይሁን ንዴት ብቻ የያዘውን ብዕር የምት ያህል ወርውሮ ወረቀቱ ላይ ጣል አደረገው።

«ውጤቱን እንዴት ልከታተል?» አለችው ሸዋዬ የባርናባስ ስሜት ጋል ብሎ ስታይ ዓይን ብላ።

«የት ልንተጣጣ?» አለና «ቤትሽን ባውቀው እኮ እኔው ራሴ እየመጣሁ የደረስኩበትን እገልጽልሽ ነበር።» አላት አንገቱን ጠመም አድርጎ በፈገግታ እያያት።

«ደሞ እንዴ ካጠከው በኋላ ነጋ መሸ እየተመላለስክ ...» ብላ ሸዋዬ ነገሯን ተወት ስታደርግ ባርናባስ ራሱ ቀጠለ።

«ያልተመቸሁሽ ዕለት በቃኝ ትይኛ የለም!» ብሎ «ወይ ስልክ ቁጥር ስጪኝ።» አላት

«የአንተን ስልክ ስጠኝ፣ ቁምነገር ከስራህ ልጠራህም እችላለሁ።»

«ይኸማ ጥሩ!» አለና የስልክ ቁጥሩን ወረቀት ላይ ጽፎ ሰጣት።

ሸዋዬ ሠዓት አየት ስታደርግ ወደ አሥር ተጠግቷል። «በቃ ልሂድ!» ብላ ከተቀመጠችበት ተነሳች።

«ግብዣው እንደማይደገም እተማመናለሁ።» አላት ባርናባስ ፈገግ እያለና ትከሻዋን ቸብ እያረገ።

«ገና ጠላው ተጠምቆ ነዋ! ኪም - ኪም - ኪም - ኪም...»

«ጥሩ እርገሽ ጥመቂው እንጂ ይደርሳል።»

ሸዋዬ ለጊዜውም ቢሆን የንዴትና የብስጭት ሸክሟን በጨዋታ ሰበብ ቀለል አድርጋ ፈገግ እያለች ከባርናባስ ቢሮ ልትወጣ በሩን ከፈት ስታደርግ ጋወን ለብሶ በኮሪደሩ ላይ ከአንድ አትጣጫ ወደ ሌላ በመሄድ ላይ ከነበረው አስቻለው ፍስሀ ጋር ድንገት ዓይን ለዓይን ግጥምጥም አሉ። እሷም ፍጥጥ! እሱም ፍጥጥ!

* * *

ታፈሡ እንግዳሰው በሸዋዬ ሆድ ውስጥ እየነደደ ስላለው የቅናት እሳት ምንም አታውቅም። በአስቻለውና በሔዋን መካከል ከተፈጠረ የፍቅር ግንኙነት ጋር በተያያዘ የሸዋዬን ንዴትና ብስጭት ማንኛዋም ታላቅ እህት ታናሽ እህቷ በፍቅር ተዘናግታ ከትምህርቷ እንዳትስተጓጎል ለመቆጣጠር ከምታደርገው ጥረት ለይታ አልተመለከተችውም። ‹አቃጣሪ› ብላ የሰደበቻትንም ቢሆን ከቁብ አልቆጠረችውም። የታፈሡና የአስቻለው ግንኙነት የጠበቀ እንደመሆኑ ለሁለቱ የፍቅር ግንኙነት በአንድ ወይም በሌላ መንገድ ድጋፍና ርዳታ ያደረገች መስሎ ቢታያት አያስገርምም በማለት የሸዋዬን ግልምጫና ስድብ በቀላሉ አልፋዋለች። ይህ ሁሉ ችግር በእርቅና በመግባባት ሊፈታ እንደሚችል በፅኑ ታምናለች። ሰሞኑን ስታወጣ ስታወርድ የቆየችውም እርቁና መግባባቱ በእንዴት ያለ ሁኔታና አኳኋን መከናወን እንዳለበት ዘዴና ብልሀት ስታፈላልግ ነው።

በእሷ በኩል የታያትን ለዋናው ባለ ጉዳይ ለአስቻለው ፍስሀና ምናልባትም በልሁና መርዕድም ከተገኙ በጋራ ተነጋግረው ከአንድ ውሳኔ ላይ ለመድረስ በማሰብ ታፈሡ በዕለተ ትዳሜ ከሠዓት በኋላ ላይ ወደ አስቻለው ቤት ስትሄድ የአስቻለውን

ቤት በጠበቶቸው ሁኔታ አገኘቸው፡፡ አስቻለውን ጨምሮ በልሁና መርዕድም ቤት ውስጥ አሉ፡፡ በልሁና መርዕድ እንደ ልማዳቸው ሜት ይዘው ፍራሽ ላይ ተቀምጠዋል፡፡ አስቻለው ደግሞ አልጋው ላይ ጋደም ብሎ እነበልሁን ፊት ለፊት እየተመለከተ ይጫወታሉ፡፡ ቤቱ በሰንደል ጭስና በመፍላት ላይ በነበረ የሻይ ሽታ ደስ በሚል መዓዛ ታውዷል፡፡

«እነ አጅሮች! ከአሁኑ ፈርሻችኋል?» አለች ታፈሡ ፏ ባለ ፈገግታ እየዋቻቸው ወደ ውስጥ በመግባት፡፡

«በእናትሽ ታፈሥ! እስቲ ዛሬ እንኳ ተቀላቀይን፡፡» አላት በልሁ፡፡

«ከኔ ይልቅ አስቹ አይቀርባችሁም፤ እሱን አልጋ ላይ አስተኝታችሁ እኔን ከሩቅ የምመጣውን ትጋብዛላችሁ፡፡» እያለች ታፈሡ ሁሉም ወዳሉበት እየተጠጋች ሰላም አለቻቸው፡፡

«ባክሽ ዶክተር ነገር በሆዱ ጉብቶ እየተብሰለሰለ ነው፡፡ ምናለ ከሌት ብልሀት አይጠፋምና አንድ ዘዴ ፈጥረሽ ከበሽታው ብትፈውሽው!» አለ በልሁ ፈገግ ብሎ አስቻለውንም ታፈሡንም እየተመለከተ፡፡

«እኔ እህቴ ሁሉንም ነገር አስተካክልለታለሁ፡፡» አለች ታፈሡ ፍራሿ ላይ ከበልሁ አጠገብ ቁጭ እያለች፡፡

«በእናትሽ ታፈሥ ፍጠኝ! አሁን ደግሞ አንድ አዲስ ነገር ተፈጥሮ በዚሁ ጉዳይ ላይ ስንነጋገር ነው የመጣሽው፡፡» አላት በልሁ አሁንም፡፡

«ደሞ ምን ተፈጠረ?» አለች ታፈሡ ፈገግታዋን ቀነስ በማድረግ በቁም ነገር በልሁንም አስቻለውንም እየተ እየተ እያረገች፡፡

«ሁለቱ ወዳጆቹ ማህበር እየፈጠሩ ስለመሆኑ ተሰማ፡፡»

«ማለት?»

«ሸዋዬን በባርናባስ ቢሮ ውስጥ አየኋት ይለናል፡፡»

«የት ይተዋወቃሉና?»

«የሰው መሄጃው ይታወቃል ብለሽ ነው?»

«አስቻለው!» ስትል ታፈሡ ጠራችውና በተለይ ወደ አስቻለው ዓይኖቿን ተከለች፡፡ «እውነት ነው እንዴ የምሰማው ነገር?»

«ምን እንዳሰቡ አላውቅም፤ ሸዋዬን ግን በእርግጥም በባርናባስ ቢሮ አይቻታለሁ፡፡»

«መቼ?» አለች ታፈሡ እንደ መገረም እያለች፡፡

«ሳምንት ሊሆነው ነው፡፡»

«እንዴ! እንዴት ነው ይኸ ነገር?» አለችና ታፈሡ ሁሉንም በዓይኗ ትቃኛቸው ጀመር፡፡

«ለነገሩ እነሱ የሚያመጡት ነገር የለም፡፡ አሁን አሳሳቢ የሆነብን ግን የሔዋን ጉዳይ ነው፡፡ የእህትማማቾቹ ግንኙነት መልካም እንዳልሆነ ነው የሚሰማው፡፡ በዚህ መሀል የምትሰቃየው ሔዩ ናት፡፡ ታዲያ ምን ቢደረግ ይሻላል ትያለሽ ታፈሥ?» ሲል በልሁ ጠየቃት፡፡

«የእኔም እኮ አመጣጥ ለዚሁ ጉዳይ ነበር፡፡» አለች ታፈሡ በተለይ በልሁን እየተመለከተች፡፡

«ምን አሰብሽ ታፈሥ?»

«ሔዩን ከሸዋዬ እንዲሁም አስቻለውንም ከእሷው ጋር አስታርቀን ሰላም የምንፈጥር ከሆነ ብዬ!»

«ሸዋዬ እሺ ትለን ይሆን ታፈሥ?» በልሁ አሁንም፡፡

«ሸዋዬ እሺ ትለን ይሆን ታፈሥ?» ...
«ምን ትሆናለች? ቁጣዋም እያደር ይበርዳል፡፡ የእስቹና የሔዩን ጉዳይ ቁርጡን እያወቀችው ስትሄድ የግዷን ትቀበላለች፡፡ ለዚህ ደግሞ እኔ ማግባባቱን እተጥላለሁ፡፡»

«ይኸ ጥሩ ነገር ነው ታፈሥ!» አለ በልሁ በእጁ ሜቱን እየቀነጠበና በዓይኑ ግን ታፈሡን እየተመለከተ፡፡

«እስቹ እንዴት ትላለህ?» አለች ታፈሡ ወደ አስቻለው እየተመለከተች፡፡

«ይቻላል ብለሽ ነው ታፈሥ?»

«ይቺ ሸዋዬ የምትባል ሰው ግን እሺ የምትል አይመስለኝም፡፡ የሆነች...» ብሎ መርዕድ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲናገር በልሁ በመሀል አቋረጠው፡፡

«አንተ ደሞ አታሟርት!»

ሁሉም ተሳሳቁ፡፡

«ማሟረት ሳይሆን እንደው ሁኔታዋ ሁሉ ቅፍፍ እያለኝ ነው፡፡»

«ግድየላችሁም፤ ብቻ እናንተም ተባበሩኝ እንጂ ዋናውን ነገር እኔ እፈጽማለሁ፡፡» አለች ታፈሡ አሁንም፡፡

«መቼ እናድርገው ታዲያ?» አለ በልሁ ታፈሡን በቁም ነገር እየተመለከተ፡፡

«እኔ ምን ጊዜም ይመችኛል፡፡ ሳስብበትም ሰንብቻለሁ፡፡ እናንተ ብቻ ተዘጋጅታችሁ ንገሩኝ፡፡»

«በኔ እምነት ባይውል ባያድር ደስ ይለኛል፡፡» አለ በልሁ ታፈሡንም አስቻለውንም እየተመለከተ፡፡

«ዛሬ እናድርገው?» ስትል ጠየቀች ታፈሡ፡፡

«ምን ችግር አለ? ቂስ መነኩሴ እንጠራ! ሸዋዬ እሺ ካለች ጥሩ፤ ካላለችም ሌላ ዘዴ ይቀየሳል፡፡» አለ በልሁ፡፡

ለአፍታ ያህል በመሀላቸው ፀጥታ ሰፍኖ ቆየና ታፈሡ ከተቀመጠችበት ድንገት ብድግ እያለች «እንዲያውም ጥሩ ሀሳብ ነው፡፡ ልብሴን ቀይሬ ልምጣ፡፡ እናንተም ተዘጋጅታችሁ ጠብቁኝ፡፡» ብላቸው ከአስቻለው ቤት ወጥታ በፍጥነት ርምጃ ወደ ቤቷ ገሰገሰች፡፡

ታፈሡ ወደ ቤቷ በምትገሰግስበት ሰዓት በሀሳቧ አንድ ነገር ይመላለሳል፡፡ በሁለት ዓመት የኮሌጅ ቆይታቸው የሸዋዬን ልዩ ባህሪ ጠንቅቃ አውቃዋለች፡፡ ሸዋዬ ከምንም በላይ ራስ ወዳድ መሆኗን፤ እርምጃዋ ሁሉ የጭካኔ፤ ጥላቻዋ ጭፍን፤ ቀናተኛ፤ ነገረኛ፤ አስመሳይና ግብዝ መሆኗን ታውቃለች፡፡ የሔዋንና የአስቻለው የፍቅር ግንኙነት ከልብ ያናደዳትና ያስቆጫት ከሆነም በሁለቱ ተዋዳጆች ላይ የምትሸርበው ተንኮል አደገኛ ሊሆን እንደሚችል ትገምታለች፡፡ በተለይ አስቻለውና ባርናባስ የጎሪጥ የሚተያዩ አለቃና ምንዝር እንደ መሆናቸው ሸዋዬ

አስቻለውን ጠልታ ከባርናባስ ጋር እስከ ገጠመች ድረስ ብዙ ነገር ልታበላሽ እንደምትችልም ይታያታል።

ቤቷ ሄዳ ብዙ አልቆየችም፤ ወትሮም በሰንበት ቀናት ከቤቷ ወጣ ስትል እንደምታደርገው ሁሉ ነጫጭ የሀገር ልብሶቿን ለብሳ፣ ነጭ ጫማ አድርጋ፣ እነስ ያለች ነጭ የእጅ ቦርሳዋን በመያዝ የሀገር ልብስ አሳባሽ ነጭ የአንገት ልብሷን ትከሻዋ ላይ ጣል አድርጋ እፍንጫ የሚሰነፍጥ የፈረንሳይ ሽቶዋን በልብሷ ላይ እርከፍክፍ አድርጋ በተጥታ ወደ አስቻለው ቤት የመልስ ጉዞ ጀመረች።

በልሁና መርዕድም ተዘጋጅተው ጠብቀዋታል። እፋቸውን ተጉመጥምጠው፣ የጫት መቃሚያ ሸርጦቻቸውን አውልቀውና ልብሶቻቸውን ለብሰው አገኘቻቸው።

ታፈሡ ከቤት እንደ ደረሰች መቀመጥ አልፈለገችም፤ ወዲያው ጉዞው ወደ ሸዋዬ ቤት እንዲጀመር የእነበልሁን ፈቃድ ጠየቀች። ሁሉም ተስማሙ። አንድ ሸዋዬ ቤት እንዲጀመር የእነበልሁን ፈቃድ ጠየቀች። ሁሉም ተስማሙ። አንድ ስምምነትም አደረጉ። በእርቁ ጥረት ሂደት ሸዋዬ በንዴት ወይም በብስጭት ምንም ብትል ምን ማንም ላይቀየም፣ ማንም ላይናደድና የቁጣ ቃል ላይናገር ተስማምተው ወደ ሸዋዬ ቤት ልክ ከቀኑ ዘጠኝ ሰዓት ተኩል ላይ ጉዞ ተጀመረ። በልሁና መርዕድ ግራና ቀኝ፣ ታፈሡ ደግሞ ከመሀል ሆነው ሲራመዱ ልዩ ቀጠሮ በተያዘለት የሽር ሽር ቦታ እንጂ ወደዚያ ጨለማ የዋጠው የሸዋዬ ቤት የሚሄዱ አይመስሉም። በዚያ ላይ ቀልድና ጨዋታ ጀመሩ።

«ስማ መርዕድ!» አለ በልሁ መጀመሪያ።

«ወይ»

«አንተ አንድ ቀን እንኳ የሴት እጅ ሳትጨብጥ ይኸው ዛሬ ለአማጭ ረማጭነት በቃህ።» አለው በታፈሡ ላይ አሻግሮ እየተመለከተው።

«በለማመድ ብዬ ነዋ!» አለ መርዕድ በተለይ ታፈሡን አፈር እያለ አጎንብሶ ፈገግ በማለት።

«እንዴት አንተ! ምን ያህል ብትንቀው ነው እንዲህ የምትለው?» አለች ታፈሡ በልሁንም መርዕድንም ተራ በተራ እየተ እየተ እያደረገች።

«እስቲ ሴት ነክቼ አውቃለሁ ይበል!» አለ በልሁ አሁንም በፈገግታ መርዕድን እየተ እያረገ።

«እውነት ነው መርዕድ?» አለች ታፈሡ።

«ተደሞ እሱ ሙች ያሲዛል?» አላት መርዕድ በልሁን በጎን እየተመለከተ።

«ጉድህ ፈላ በልሁ!» ብላ ታፈሡ «ኪም - ኪም - ኪም - ኪም...›

«እሱ ከደፈረ እኔ ለአንድ ዓመት ያህል ሴት በዞረችበት ላልዞር እምላለሁ።» ካለ በኋላ በልሁ «እስቲ በታፈሡ ፊት ‹አደርጋለሁ› ብለህ ቃል ግባ!» አለው መርዕድን በፈገግታ እያየ።

«ገደለህ መርዕድ!» ታፈሡ አሁንም እያሳቀች።

«አንተ እያየሽኝ ነው እንዴ የማደርገው?» አለና መርዕድ ዓይኑን በታፈሡ ላይ አሻግሮ በልሁን ገርመም አደረገው። ይሁንና ሰፍረት የተቀላቀለበት ፈገግታ ከፊቱ ላይ አልጠፋም።

«አሁን ምን እያሰብኩ እንደሆነ ታውቃለህ?» አለ በልሁ።

«መቼም ደህና ነገር አታስብ!»

«አንድ ቀን ቤትህ ውስጥ አንድ ሴት አስገብቼ ቆልፌባችሁ ላድር ነው። ጠዋት ሴትዮዋን ጠይቂ ‹ምንም› ካለች በቃ! ይኸን ሱሪህን አውልቄ ቀሚስ ላለብስህ አስቤአለሁ።» አለውና በልሁ ለራሱ እየሳቀ ታፈሡንም አሳቃት።

መርዕድ በእርግጥም ሴት ይፈራል። የበልሁን የዚህ ዓይነት ቀልድ የለመደው ነው። ነገር ግን የዛሬው በታፈሡ ፊት መሆኑ ይበልጥ አሳፈረውና፦

«የምታወራው አጣህ እንዴ አንተ? የት እየሄድክ መሰለህ? ወደ ሸዋዬ ነው እኮ! እስከሚያትለሸልሽህ ድረስ ታጠጣህ የለ!» አለና ድንገት የሚሄዱበትን ጉዳይ ድባብ ከአእምሮአቸው ውስጥ አስገባው። ለጊዜው ንግግሩ ያሳቃቸው ቢሆንም ከዚያ በኋላ ግን ሀሳባቸው ሁሉ ሸዋዬ ቤት ደርሰው ስለሚያከናውኑት ነገር ብቻ ሆነ። በእህትማማቾች መካከል ኩርፊያና ጥላቻ የነገሰበት ሁኔታ ይታያቸዋል።

የማታ ፀሐይ ግንባር ግንባራቸውን እያላቸው፣ ሙቀቱ ሰውነታቸውን እያቀለጠ በላብ እየነከራቸው፣ በቀልድና ጨዋታ የተሸፈነ ስጋት ውስጥ ውስጣቸውን ወጋ ቆንጠጥ እያረገ ሲያስጨንቃቸው ይዘው የነበሩት ታፈሡ፣ በልሁና መርዕድ ከሸዋዬ ቤት በር ላይ ደርሰው ወደ ውስጥ እየተ ሲያደርጉ ፊትለፊት ያዩት ሁኔታ ግን ያ የገመቱት ጨለማ አልነበረም፤ ቤቱ ሞቅ ደመቅ ብሎ፣ ጥሩ ጥሩ የሚሸት፣ ለእርቅ የተዘጋጀ ቤት መስሏል። በልሁ ከፊት፣ ታፈሡ ከመሀል ቀጥሎ ደግሞ መርዕድ በመሆን ተከታትለው ሲገቡ መጀመሪያ ሔዋንን አዩአት። በነጭ ረከቦት ላይ ነጫጭ ስኒ ደርድራ፣ በሥሩ ቄጠማ ጎዝጉዛ ቡና ለመቁላት በዝግጅት ላይ ናት። የሸዋዬ ታጣፊ አልጋና የሔዋን ፍራሽም ክርክም ብለው ተነጥፈዋል።

«እንዴት ዋላችሁ!» ብሎ በልሁ ቀድሞ ሲገባ ሔዋን ድንገት ድንግጥ ያለች መሠለች። ከተቀመጠችበት ብድግ ብላ ዓይኗን ፍጥጥ በማድረግ ሁሉንም ተመለከተቻቸው። ምናልባት አስቻለውም ሊኖር ይችላል ብላ ሳይሆን አይቀርም፣ ከመርዕድ ኋላ የሚመጣ ሰው የምትፈልግ ይመስል ዓይኖቿ ተንከራተቱ።

«እንዴት ያምርብሻል እባክሽ!» አለና በልሁ ቀድሞ ሳማት። ታፈሡም መርዕድም ተከተሉ።

«ሸዋዬ የለችም እንዴ?» ሲል በልሁ ሁሉም እንደ ቆሙ ሔዋንን ጠየቃት።

«እረ አለች» ብላ ሔዋን ፊቷን ወደ ጓዳ መለስ አድርጋ ስታይ በልሁ የሸዋዬ አድራሻ ገባውና ወደ ጓዳው በር ራመድ በማለት «ሸዋዬ!» ሲል ጠራት ከጓዳው በር ላይ ቆሞ ወደ ውስጥ እያየ።

ሸዋዬ ግን ዝም።

«ሸዋዬ!» በልሁ አሁንም።

አሁንም ምላሽ አጣ። አንገቱን ወደ ጓዳ ብቅ አድርጎ መልከት ሲል ሸዋዬ በድንጋጤ ድርቅ ብላ ቆማ አያት። እጅጌ ጉርድ ነጭ የሀገር ባህል ቀሚስ ለብሳለች። አጭር ሀጉሯን ብን አድርጋ አበጥራለች። እንዲያውም የተኳኳለች ትመስላለች።

«ምነው?» ሲል ጠየቃት በልሁ አቋቋሟን አይቶ እሱም ግራ ገባ እያለው።

«ምንም!»።

«ታዲያ ስጠራሽ ወይ አትይም እንዴ?»

ሸዋዬ ግን አሁንም ዝም።

ታፈሡና መርዕድ መሀል ወለል ላይ ቆመው የበልሁን መጨረሻ ይጠባበቃሉ። ሔዋን ወደ ፍራሿ ወጣ ብላ ግድግዳ ላይ ልጥፍ ብላ በፍርሀት

ተነፋሥታ ቆማለች:: በልሁ ተስፋ አልቆረጠም፤ ቀጥታ ወደ ጓዳ ገባና በግራ እጁ የሸዋዬን ክንድ ያዝ በማድረግ «ኧረ ከእንግዶች ጋር ሳስተዋውቅሽ::» አላት::

«ተወኝ!» አለችው ሸዋዬ በተመናጨቀ አነጋገር::

«ኧረ...እንግዲህ!» አለና በልሁ ሳቅ እያለ የመንተተ ያህል የግድ ወደ ሳሎን ይዟት ወጣ:: ሸዋዬን በግራ እጁ ታፈሡን ደግሞ በቀኝ ክንድና ክንዳቸውን ይዞ በመሃላቸው በመቆም «ድሮ ጓደኞቼ ተተዋወቁ ተቀያይማችሁ መቅረት የለባችሁም:: የፍቅር አምላክ ሳይሆን አይቀርም፤ ዛሬ ደግሞ ሆድ ለሆድ እንገናኛችሁ ኖሮ ሁሌታችሁም የሰላም ምልክት የሆነውን ነጭ ልብስ ለብሳችኋል:: በሉ ያለ ወቀሳ ይቅር ተባባሉና ተሳሳሙ::» አላቸው::

ታፈሡ ፍልቅቅ ባለ ፈገግታ የሸዋዬን አንገት ለማቀፍ እጆቿን ዘርግታ ጠጋ ስትል ሸዋዬ ግን አንዳች አስቀያሚ ነገር ያየች ይመስል ፊቷን ኩስትርትር አድርጋ «እንዳትጠጊኝ!» አለችና ወደ ኋላዋ ፈግፈግ አለች::

«ውይ! ምነው ሸዋዬ?» አለቻት ታፈሡ በልመና አነጋገር::

«ቢቃ! አልፈልግሽም!»

«እኔ ግን እፈልግሻለሁ::»

«ግድ!?» አለች አንገቷን ሰገግ አድርጋ በትንድዷ ስር ታፈሡን እያየች::

«እሺ ልለምንሽ?» አለቻት ታፈሡ ከአንገቷ ገደድ ብላ እያየቻት::

«ነገር አይገባሽም?»

«እንዲህ ስትለምንሽ?» አለ በልሁ በሸዋዬ ሁኔታ ውስጡ የተቃጠለ ቢሆንም ነገር ግን እስከ መጨረሻው ሊታገስ ቃል ገብቷልና ረጋ ባለ አነጋገር::

«እዚያው አለመደችበት ሄዳ ትለምነኝ?» አለች ሸዋዬ አሁንም እነዚያን እንደ ጦስፈ የሚዋጉ ዓይኖቿን በታፈሡ ላይ ትክል አድርጋ::

«ከእንቺ ሌላ ማንን ለምና ታውቃለች?» አላት በልሁ ክንዷን እንደያዘ ገደድ ብሎ ፊት ፊቷን እየተመለከተ::

«ታውቅበት የለ አንዴ በዚያ በዚህ እያለች ማቃጠሩን!»

ታፈሡ ፈገግ ብላ ሸዋዬን ካየቻት በኋላ ወደ በልሁ ቀና በማለት «ተዋት በልሁ:: ነገሩ እየገባት ሲሄድ እንታረቃለን::» አለችው ረጋ ባለ አነጋገር::

«ልቀቀኝ!» አለችው ሸዋዬ በልሁን::

በልሁ ክንዷን ከለቀቀ በኋላ ዝም ብሎ ሲመለከታት ሸዋዬ ራሷ «በህግ አምላክ! ከቤቴ ውጡልኝ!» አለቻቸው በዓይኗ ሁሉንም ተራ በተራ እየተመለከተቻቸው:: ሔዋን ተጨንቃ መግቢያ ቀዳዳ አጥታለች:: ጭንቅ አይችሌው መርዕድም ከዚያ ቤት እግሩ እስኪወጣ ቸኩሏል:: በልሁን ከመካከላቸው አድርገው ታፈሡና ሸዋዬ ቃላት ሲመላለሱ እሱ ግን ውጭ ውጭ ያያል::

«እኛ እኮ ለዘረፋ አልመጣንም::» አላት በልሁ ረጋ ብሎ::

«ለምንም ኑ፣ ግን ውጡልኝ::» ብላቸው ሸዋዬ ወደ ጓዳ ጥልቅ አለች::

ከዚያ በኋላ ምን ማድረግ እንደሚችሉ የሚያውቁት ነገር አልነበረም፤ ግን ሁሉም በየዱካዎች ላይ ቁጭ ቁጭ አሉ:: በዚያ ሠዓት ሔዋን የሁሉንም ትኩረት አገኘች:: ሁኔታዋ ያሳዘናት ታፈሡ ቀድማ-

«ሔዩ ቁጭ በይ!» አለቻት::

«ምን ያስለቅስሻል?» አላት በልሁም:: ሔዋን ግን መልስ አልሰጠችውም:: አንገቷን ደፍታ ፍራሽ ላይ ቁጭ አለች::

ከአፍታ ዝምታ በኋላ በልሁ ፊቱን ወደ ጓዳ መልስ አድርጎ «እንደው ተለምንሽም አታውቂ ሸዋዬ?» ካለ በኋላ «የኛ አመጣጥ እኮ እንቺና ታፈሡን ከአስታረቅን በኋላ ሔዋን...» ብሎ ሳይጨርስ ታፈሡ ጎንተል አድርጋው አፏን ስትደመድም እያትና ዝም አለ::

«ሔዩ!» ስትል ታፈሡ ሔዋንን ጠራቻት:: የሔዋን ጉዳይ የሚነሳ ከሆነ እሷ በሌለችበት እንዲሆን ፈልጋ በሰበብ ወጣ እንድትል ለማድረግ አስባ ነው::

«አቤት!» አለቻት ሔዋን ከአጎነበሰችበት ቀና ብላ::

«እስኪ በዚህ አካባቢ ሱቅ ካለ አስፕሪን ገዝተሽልኝ ነይ:: ብታይ ራስ ምታቱ ተነስቶ ጭንቅላቴ ሊፈነዳ ደርሷል::» አለችና ብር ልትሰጣት ቦርሳዋን ስትከፍት ከወደ ጓዳ በኩል ሸዋዬ በሔዋን ላይ ድንገት አምባረቀች::

«እግርሽን ታነሽና ዋ!»

ሔዋን ልትነሳ የነበረውን ተመልሳ ኩርምት ብላ ተቀመጠች::

በልሁ ንዴትና ብስጭቱ ከቁጥጥሩ በላይ እየሆነበት መጣ:: ግን ደግሞ ያን ሁሉ ዋጥ አድርጎ «እንደው ትንሽ እንኳ ሰው አይከብድሽም?» ሲል ሸዋዬን ረጋ ባለ አነጋገር ጠየቃት::

«ስለ ከበዳችሁኝ አይደል ውጡልኝ ያልኩት!» አለችው ሸዋዬ ጮክ ባለና መንጨቅጨቅ ባለ አነጋገር::

«አ!» አለ በልሁ ድንገት ብልጭ አለበትና «ምናችን ነው የሚከብደው እንቺ? ኧረ ይቺ...» ብሎ ሳይጨርስ ታፈሡ አሁንም ጎንተል አደረገችውና ዝም በል በሚል ዓይነት አፏን ደመደመችበት ::

በልሁ ግን ተቆጣ:: «ተይኝ ታፈሥ! ጭራሽ ልትሰድበን አይደል እንዴ ይቺ ባለጌ!» አለና በተቀመጠበት ቆነጥነጥ አለ::

ሸዋዬ ቀድሞም ቢሆን በራሷ አነጋገር ወዲያው ድንግጥ ብላ ነበር:: በልሁን ደግሞ በጣም ትፈራዋለች፤ ጥሎባት:: ጓዳ ውስጥ ዘው ብሎ ገብቶ የሚያንቃትም መስሏት ሰጋች:: በዚህ ጊዜ ልክ ከተደበቀበት ቦታ ቱር ብሎ እንደሚሸሽ ሌባ በፍጥነት ሮምጃ ከጓዳ ወጣችና በሳሎን በኩል አቋርጣ በመሮጥ ከወይዘሮ ዘነቡ ቤት ጥልቅ ስትል ሁሉም ገረማቸውና እርስ በእርስ ተያዩ::

«ወይኔ የት አባቱ ልግባ!» አለችና ሔዋን ማልቀስ ጀመረች::

ታፈሡ ከዱካዋ ላይ ብድግ ብላ ወደ ሔዋን በመሄድ ፍራሽ ላይ ቁጭ አለች:: የሔዋንን አንገት እቅፍ በማድረግ «አይዞሽ የኔ ቆንጆ!» ብላ ጉንጯ ላይ ሳም አደረገቻት:: በልሁና መርዕድም ሔዋንን በሀዘን ዓይን ይመለከቷት ጀመር::

«ይቺ እህትሽ ፍጥረቷ ምንድነው ሔዩ?» ሲል በልሁ ጠየቃት::

«በልሁዬ፣ በእናትህ ዝም በል:: ደሞ የሰማች እንደሆን...» ብላ ሔዋን እንባዋን እየጠረገች ታለቅስ ጀመር::

«አቦ ይቺ ሰማች አልሰማች!» አለና ወደ ውጭ እየተ እያረገ «ልብ ከሌላት ጆሮ ምን ያደርግላታል?» አለ::

«ቢቃ በልሁ፣ ሔዩን አታስጨንቃት::» ካለች በኋላ ታፈሡ ወደ ሔዋን ዞር በማለት «ሰሞኑን ግን እንዴት ነበራችሁ? ስመሆኑ ታነጋግርሽ ነበር?» ስትል ጠየቀቻት::

«በጣም ደህና ነበርን:: ከአሁን በኋላ ግን ፈራሁ::» አለቻት ሔዋን እንባዋን ከዓይኗም ከፊቷም ላይ እየጠረገች::

«በምን ታረቃችሁ::»

«ቃል አስገብታኝ::»
«ምን የሚል ቃል?»
«ኛም ከአስቻለው ጋር እንዳትገናኚ ብላኝ እኔም እሺ ብያት::»
«እ?» አለ በልሁ ፊትለፊት ፍጥጥ ብሎ እያየት::» «ከልብሽ ነው?» ሲልም ጠየቃት::

«አይደለም በልሁዬ፣ የሆዴን በሆዴ አድርጌ ነው::» አለችው ቀና ብላ ዓይናቿን በበልሁ ላይ እያንከራተተች::

በልሁ በሒዋን አኳኋር ልቡ ተነክቶ አከታትሎ ከተመለከታት በኋላ ዓይኑን ወደ ታፈሡ በማዞር «ጉዳዮችንን አልጨረስንም ታፈሥ?» ሲል ጠየቃት ::

«ጨርሰናል::»

ሶስቱም ከተቀመጡበት እየተነሱ ሒዋንን ስመው ከዚያ ቤት ተከታትለው ወጡ::

ከመይዙር በነሱ ግቢ የውጭ በር አካባቢ ሲደርሱ ባርናባስ ወየሰ ዛሬም ደማቁን ለማያዩ ካኪ ለብሶ፣ ያችኑ ጠበብ ያለች ወርቃማ መነፅሩን አድርጎ፤ እጆቹን በሱሪ ኪሶቹ ውስጥ አስገብቶ ወጠርጠር እያለ ወደ ግቢ ሲገባ በር ላይ ተገናኙ:: እነሱ አውቀውታል:: እሱ ግን አያውቃቸውም:: እነሱን አልፎ በቀጥታ ወደ ሸዋዬ ቤት አቅጣጫ አመራ:: ሁሉም ዞር ዞር ብለው ሲመለከቱት በእርግጥም ስተት ብሎ ከሸዋዬ ቤት ገባ:: የዕለቱ የሸዋዬ የቤት ውስጥ ዝግጅት ምክንያቱ ምን እንደነበረ ገና አሁን ገባቸው::

ምዕራፍ ሶስት

ዲላ ሆስፒታል ውስጥ አንድ አነጋጋሪ የሆነ ክስተት ተፈጠረ:: ሰበቡ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ከየጤና ተቋማቱ ነርሶችን አወዳድሮ ከሚተኮስው የትምህርት ዘመን ጀምሮ በጤና መኮንንነት ለማሰልጠን ባወጣው ማስታወቂያ መሠረት ከዲላ ሆስፒታል የተመረጠውን ነርስ የማወቅ ውጤት ነው:: የመወዳደሪያው ዋነኛ መስፈርት የአገልግሎት ዘመን ሲሆን በማስታወቂያው ላይ የተጠየቀው አነስተኛ መስፈርት የአገልግሎት ዘመን ሲሆን በማስታወቂያው ላይ የተመረጠው ነርስ ግን ሦስት ዓመት የአገልግሎት ዘመን አምስት ዓመት ሆኖ ሳለ የተመረጠው ነርስ ግን ሦስት ዓመት እንኳ ያልሞላው ሆኖ ተገኘ:: ይህ ሁኔታ እንኳንስ መስፈርቱን የሚያሟሉ ነርሶችን የማይመለከታቸውንም የሆስፒታሉ ሠራተኞች ሁሉ ክፉኛ አስቆጫቸው:: በላይ በሆስፒታሉ ውድድሩ ካለማሟላቱም

ተመራጩ ነርስ የውድድሩን መስፈርት ካለማሟላቱም በላይ በሆስፒታሉ ውስጥ የሙያ አገልግሎት የሚሰጥባቸው ቀናት እንኳ እጅግ የተወሰኑ ነበሩ:: በአውራጃው የወጣቶች ማህበር ፅህፈት ቤት ውስጥ የአንድ ዘርፍ ሃላፊ በመሆኑ በመደበኛ ስራው ላይ አዘውትሮ አይገኝም:: ከጤና ባለሙያነቱ ይልቅ ፖለቲከኛነቱ ያመዝናል:: ‹ጆሮ› የሚል ቅጽል ስም ወጥቶለት ሰዎች ሁሉ ይሸሹታል:: እሱ ባለበት ቦታ ወሬ አይሞከርም:: ዛሬ እንዲያውም ወደ ሆስፒታሉ ብቅ ባይል የብዙ ሠራተኞች ፍላጎት ነው:: በዚህ ሰበብ ለከፍተኛ የሙያ ስልጠና የተመረጠበት ሁኔታ ቢያስቆጫቸውም ከመሀላቸው በመውጣቱ የተደሰቱም አይጠፉም::

ለአስቻለው ግን ይህ አይዋጥለትም:: ‹ጆሮ› ለሁለትና ለሦስት ዓመታት ከአካባቢው ገለል ቢልም ኮርሱን ሲጨርስ ይበልጥ አብጦ እና ተከፍቶ መመለሱ እንደማይቀር ይገነዘባል:: የእሱ ጭንቀት ‹ጆሮ› በማይመለከተው ውድድር ውስጥ ገብቶ ጭራሽ አሸናፊ የሆነበት ሁኔታ ነው:: ፍላጎቱም የራሱን መብትና ጥቅም ለማስከበር መንቀሳቀስ ነው:: ይህን ጥረት ለብቻው ከማድረግ ይልቅ እንደ እሱ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ለማስተባበር ሞክሮ ነበር፣ ነገር ግን አልተሳካለትም:: ሁሉም የሰጡት ምላሽ ‹ማን ሊሰማኝ? ምን ለውጥ ሊመጣ? ምን ህግ አለና?... ወዘተ› የሚሉ ተስፋ አስቆራጭ ቃላቶችን ነበር::

ይህ ዓይነቱ የሰዎች አመለካከት የአስቻለው የዘወትር ራስ ምታቱ ነው:: ገገርዎች በህዝብ ላይ ከሚፈጽሙት ግፍና በደል የበለጠ የዜጎች ልበ ሙትነት ያበሳጨዋል:: መብትና ጥቅምን በፈቃደኝነት አሳልፎ የመስጠት ጅልነት ያንገበግበዋል:: አሁን ሲቆጧት ኋላ እንደሚቆረጥሟት እንደማታውቅ ጥሬ መብቱ ሲረገጥ፣ ጥቅሙ ሲጨፈለቅ ዝም ብሎ የሚመለከት ሰው አንጀቱን ያቆስለዋል:: ‹ሰው እንዴት ሰሚ በሌለበት፣ ህግ በማይከበርበት፣ ግፍና በደል በተንሰራፋበት፣ እድሎና ጭቆና በነገሰበት፣ አቤት ቢባል ፍትህ በማይገኝበት ሥርዓት ውስጥ ለመኖር ፈቃደኛ ይሆናል? በዚህ ሁኔታ ውስጥ እየኖረስ እንዴት ሰው ነኝ ብሎ ያስባል?› ይላል ዘወትር:: ምንም እንኳ ሰውን ሁሉ ለዚህ ዓይነቱ የአመለካከትና የአስተሳሰብ ዝቅጠት ያበቃውን ታሪካዊ መነሻ የሚያውቀው ቢሆንም ‹ግን እስከ መቼ?› ለሚል ጥያቄ መልስ እያጣ በእጅጉ ያዝናል፣ ይበሳጫል::

ያም ሆኖ አስቻለው ወትሮም እንደሚያደርገው ሁሉ የበኩሉን ድርሻ ከመወጣት ወደ ኋላ አላለም:: በዕለተ ሐሙስ ከጠዋቱ አንድ ሠዓት ጀምሮ እስከ ቀኑ ዘጠኝ ሠዓት ባለው ፈረቃ ስራውን ሲያከናውን ውሎ ወዲያው ወደ ቤቱ መሄድ አልፈለገም:: በቀጥታ ወደ ሆስፒታሉ የአስተዳደር አገልግሎት ሃላፊ ቢሮ አመራ፤ ወደ ባርናባስ:: በሩን ከፈት አድርጎ ወደ ውስጥ አየት ሲያደርግ ባርናባስ ወየሶ በጠረጴዛው ላይ አጎንብሶ ይጽፋል:: አለባበሱ ያው የተለመደው ነው:: በሩ ሲከፈት ሰምቶ ዞር ሲል አስቻለው የበሩን እጀታ እንደያዘ በር ላይ ቆሞ አየው::

«እቤት!» አለው ዓይኑን በአስቻለው ላይ እንደተከለ::

«ላነጋግርህ ፈልጌ ነበር::»

ባርናባስ ፈጥኖ መልስ አልሰጠውም:: ለአፍታ ያህል መልከት ካለው በኋላ እጅግ በቀዘቀዘ ስሜት «ትችላለህ» አለና በእጁ ወደ እንግዳ ወንበር አመለከተው::

አስቻለው ገባ:: ከእንግዳ ወንበሮች መካከል አንዷን ሳብ አድርጎ ቁጭ አለና ባርናባስን በጥርጣሬ ዓይን ያየው ጀመር::

«ምን ልርዳህ?» ሲል ጠየቀው ባርናባስ መነፅሩን አውልቆ ጠረጴዛ ላይ ቁጭ እያደረገ::

«ለእጩ ጤና መኮንንነት ኮርስ ውድድር ተመዝግቤ ነበር::»

«እህ!» አለው ባርናባስ በሾፍ አነጋገር::

«በውጤቱ አልተደሰትኩም!»

«ምን ጠብቀህ ነበር?»

«እመረጣለሁ ብዬ ነበረ!»

«ሀአ! ዝም ብሎ መመረጥ አለ እንዴ?»

«ዝም ብዬማ አይደለም:: በወጣው ማስታወቂያ መሠረት ከሆነ በአገልግሎት እኔ እበልጣለሁ:: እንዲያውም ሁለት ዓመት ትርፍ አለኝ:: የተመረጠው ነርስ ግን ጭራሽ ከመስፈርቱ አነስተኛ መነሻ እንኳ ለመድረስ ሁለት ዓመት እንደሚቀረው አውቃለሁ:: ታዲያ እንዴት ዝም ብለህ ትለኛለህ?» ሲል ግንባሩን ቋጠር አድርጎ ጠየቀው::

«ለመሆኑ በማስታወቂያው ላይ የተጠየቀው መስፈርት የአገልግሎት ዘመን ብቻ ነው እንዴ?»

«ሌሎችማ አሉ፤ ነገር ግን ዋናው መስፈርት የአገልግሎት ዘመን መሆኑን ማስታወቂያው በግልጽ አስቀምጧል::»

«ሌሎቹ ስትል?» አለና ባርናባስ ዓይኑን ፈጠጥ አደረገ::

«በቃ! ሌሎቹ ማለቴ ነው፤ ለፍርደ ገምድልነት ምክንያት የሚሆኑ እንጂ ዋናውን መስፈርት የማያሽሩ!»

ባርናባስም ዓይኑ ፈጠጠ:: ቀይ ፊቱ የባሰ ደም መምሰል ጀመረ:: አፍንጫው ነፉ ምሽሽ አለ:: ወደ ጠረጴዛው መለስ ብሎ እጆቹን አቆላልፎ ተደገፈና «ጉልህ አብዮታዊ ተሳትፎ ያደረገ የሚለውን መስፈርት ማለትህ ነው?» ሲል አስቻለውን ጠየቀው::

«ያ ይኼ አላልኩም:: ግን ከሙያው ጋር የማይሄዱትን በሙሉ ማለቴ ነው::» አለው አስቻለው እሱም ጠረጴዛውን እየተደገፈ::

ሁለቱም ተፋጠጡ:: ዓይን ማን ይሰበር? ማን ይስበር? በሚል የሚጠባበቁ ይመስላሉ:: ባርናባስ እንደገና ወደ ኋላ ወንበሩን ተደግፎ በረጅሙ ተነፈሰና:-

«ለማንኛውም አንተና የተመረጠው ጓድ በምንም መንገድ አንድ ልትሆኑ አትችሉም::» አለው::

«ምን አገናኘቶን?» አለ አስቻለው ፈርጠም ባለ አነጋገር:: «የኔስ ችግር ይኸ አይደል?» አለና ባርናባስን አከታትሎ ይመለከተው ጀመር::

«ታዲያ ይኸን ካወቅህ ሌላ ምን ፈለክ?»

«እኔ እያለሁ እሱ እንዴት ተመረጠ ብዬ ነዋ!»

«ባላችሁ ልዩነት ምክንያት!»

«ውድድሩ እኮ ለባለሙያነት እንጂ ለካድሬነት አይደለም አቶ ባርናባስ!»

ባርናባስ ድንገት ቁጥት አለና «ጓድ በል! ደሞ የምን ‹አቶ› ነው?» በማለት በአስቻለው ላይ አፈጠጠ::

አስቻለው ሳያስበው ፈገግ አለና ረጋ ስስስ ባለ አነጋገርን "ጓድ" የሚለው ቃል እኮ በዓላማና በተግባራቸው የሚመሳሰሉ ግለሰቦች የሚጠራሩበትና የሚሞካሹበት ቃል ነው:: ታዲያ እኔና አንተ...» ብሎ ሳይጨርስ ባርናባስ አቋረጠው::

«የመጣህበትን ጨርሰሃል?»

«አልጨረስኩም!»

«ምን ቀረህ ደሞ?»

«አመራረጡ ትክክል ስላልሆነ እንደገና ይታይ ነው የምለው!! በዚህ ላይ ያለህን አስተያየት ስጠኝና እንጨርስ::» አለ አስቻለው ፊቱ በብስጭት ልውጥውጥ እያለ::

«በቃ! ጓዱ በአበረከተውና እያበረከተ ባለው አብዮታዊ አስተዋጽኦ ምክንያት ተመርጧል ነው የኔ መልስ::» አለና በርናባስ እንደገና ወደ ኋላው ወንበሩን ተደገፈ::

«በፖለቲካ?»

«አዎ!»

«ታዲያ ወደ ፖለቲካ ትምህርት ቤት ላኩታ! ወደዚያ ቢሄድ ነው እኮ ይበልጥ ስልቶ ይበልጥ ሾሎ የሚመስላችሁ::»

ባርናባስ በቁጣ ስሜቱ ተለዋወጠ:: መናገር ሲያቅተው አስቻለው ራሱ ቀጠለ:: «ሙያ ካስተማራችሁትማ አመስካከቱም ይቀየርና ምላሱንም ይሰበስባል:: መቼም ለእናንተ በኩል እንደ መዋሸት አይችልም:: መቅጠፍ አይሆንለትም:: ያ ከሆነ ደግሞ በእናንተ በኩል እንደ ደነዝ ስለሚታይ ለእናንተም አይጠቅማችሁ:: ለራሱም ነገሩ ሁሉ እየተምታታበት ግራ ይጋባና ይቸግራል::» አለው አሁንም ፈገግ ባለ አስተያየት ባርናባስን እየተመለከተ::

«ኻኻኻኻ ...» ብሎ ባርናባስ ሳቀና «አሁንስ አሳከኝ!» ሲል በቃልም ተናገረው::

«የነገርኩህን በደንብ ተረድተኸኛል ማለት ነው::»

«የኔ ወንድም! ያለ ስራህ የገባህ ይመስለኛል! ይልቅስ የሙያ ሥነ-ምግባርህን አክብረህ መንቀሳቀስ ይበጅሃል:: በማያገባህ ጉዳይ እየገባህ መዘባረቁ ግን—» ብሎ ሳይጨርስ አስቻለው አቋረጠው::

«ትክክል! የሙያ ሥነ-ምግባርን ማክበር ማለት መርሁንም ከሚጥሱት ጋር መታገልን ያጠቃልላል::» ሲለው የባርናባስ ስሜት ግን ድንገት ልውጥውጥ አለ:: ባርናባስ አንድ ነገር ትዝ ብሎት በሀሳብ ጭልጥ ብሎ ሄደ::

ባለፈው ዳላ ከተማ በማጅራት ገትር ወረርሽኝ በተናወጠችበት ወቅት የሆስፒታሉ ሠራተኞች በአንድ ላይ ተሰብስበው በሽታውን የመከላከል ጥረታቸው ምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ ግምገማ ላይ ነበሩ:: ያኔ ባርናባስ ወየሶ በአስተዳደር አገልግሎት ሃላፊነቱና በፖርቲ መሠረታዊ ድርጅት አንደኛ ሀላፊነቱ አስተያየቱን በሚሰጥበት ጊዜ ከሌሎች ሃሳብ በተጨማሪ የተሰማውን ቅሬታ ሲገልጽ «...በአንዳንድ ዓይነት አደጋ ወቅት ከፍተኛ የሆነ ሀገራዊ አደራ ተሸክመው ደፋ ቀና ለሚሉ ጓዶች ቅድሚያ መስጠት አስፈላጊና ተገቢ ቢሆንም አንዳንድ ለአብዮቱና ለአብዮቱ አራማጆች ቀና አመለካከት የሌላቸው ራስ ወዳዶች ግን የበላይ አካል የሰጠውን አመራር ባለመቀበል ሲያንገራግሩ ተስተውለዋል.....» በማለት በስብሰባው ላይ ተናግሮ ነበር:: ይህ አሽሙር በቀጥታ እንደሚመለከተው የገባው አስቻለው ደግሞ፡

«በምንመራበት ፖለቲካዊ ፍልስፍና መሰረት ህዝባዊ አደራ መሸከም ማለት ህዝብ ማገልገል እንደሆነ ራሳቸው አራማጆቹ አስተምረውናል:: በቅድሚያ ስራውን ህዝብ ማገልገል የሚፈልጉትን አልፈጸምንላቸው እንደሆነ እንጂ ዘሊህም መሠረት ምንልባት የሚፈልጉትን አልፈጸምንላቸው እንደሆነ እንጂ የሚነገሩትን ግን ሳናሆን አከናውነናል:: ከዚህም በተጨማሪ ስልጣን በሙያ ስራ ላይ ሲገባ ሙያን ከማራከስም ባሻገር በሂደት ራሱ ስልጣንም ዋጋ እያጣ እንደሚሄድ ስማቱን የመከላከልም ጥሪት አድርገናል::» ካለ በኋላ ንግግሩን ሲያጠቃልል «አንዳንድ ወገኖች ግን የስልጣን ወንበራቸው ከፍ ባለ ቁጥር እየመሰላቸው የተለየ ክብርን ሲሹ አጠቃቀቸውም በዚያው መጠን ያደገ የምንፈልገው ክብርና ሞገስ እንመለከታለን:: ይህ አጋጣሚ ልናስገነዝባቸው የምንፈልገው ከሚቀመጡበት ወንበር ላይ እንደማይመነጭ ከአእምሮአዊ ማንነት እንጂ እንዲረዱልን ብቻ ነው::» በማለት ተናግሮ እንዳበቃ አዳራሹ በጭብጨባና በፉጨት ተናውጦ ነበር:: ያኔ የባርናባስ በድንጋጤና በንዴት ፊቱ በቁጣ ከሰል መስሎ ነበር:: ተናውጦ ነበር:: ያኔ የባርናባስ ፊቱ በቁጣ ተለዋወጠ:: አስቻለው ዛሬም ያንኑ እየደገመ መሆኑ ተሰምቶት ባርናባስ ፊቱ በቁጣ ተለዋወጠ::

«ለማ» አለ ባርናባስ ጣቱን ወደ አስቻለው እየቀሰረ:: «ወሬና ተግባር ለየቅል ናቸው:: ያልተወለደ እየገደልክ የሙያ ሥነ-ምግባር አከብራለሁ ብትል የሚሰማህ የለም» አለው::

«ምን?» አለ አስቻለው ዓይኑን በባርናባስ ላይ ፍጥጥ አድርጎ:: ያልተወለደ መግደል በዚህ ቋንቋ ማስወረድ ማለት መሆኑን ያውቃልና የባርናባስ አነጋገር ከምን የተነሳ እንደሆነ ለማወቅ ፈለገ::

«በደረስን ጥቆማ መሠረት መረጃዎችን እያሰባሰብን ነው:: ከዚያ በኋላ የምንነጋገርበት ይሆናል::» አለና ባርናባስ «አሁን ጨርሻለሁ:: ከቢሮዬ እንድትወጣልኝ በትህትና እጠይቃለሁ::» ብሎት በረጅሙ ተነፈሰ::

«አዲስ ነገር እየጀመርክ ምንን ጨረስከው?» አለ አስቻለው አሁንም ዓይኑን በባርናባስ ላይ እንደተከለ::

«ሌላ ጊዜ በአዲስ መልክ እንጀምረዋለን:: አሁን ከቢሮዬ ውጣልኝ::»

አስቻለው በባርናባስ ጥያቄ ተቻኩሎ ከመቀመጫው ቶሎ አልተነሳም:: እንዲያውም ለአፍታ ያህል ትኩር ብሎ ከተመለከተው በኋላ «‹ያልተወለደ ገዳይ› አልከኝ?» በማለት መልሶ እስኪጠይቀውና «ብቻ! ገላግየዋለሁ፣ ያንን ሳይወለድ ሟች!» አለው ባርናባስ የሚሰጠውን ምላሽ በመጠባበቅ ትኩር ብሎ እያየው::

«በመግደል?»

«ቢወለድ ምን ያደርጋል? ያው አንተን ወይም እኔን ሆኖ መኖር ነው!»

«ስትል?»

«የአንተን ዕድል ቢያገኝ ሲበድል ይኖራል:: የኔ ዕጣ ከደረሰው ደግሞ ሲበደል! አየህ! በዚች አገር ሁለት ዓይነት አሰላለፎች አሉ! በዳይና ተበዳይ:: የቁጥር ልዩነታቸው ግን የትየለሌ! በዳዮች አናሳ! ተበዳዮች ግን እልፍ አዕላፍ! ታዲያ አዲስ መጪው ሰው ከእነዚህ የህዝብ ክፍሎች አንዱን ከመሆን የት ያመልጣል?» ባርናባስ በትድሚያ ስለ ከንፈሮቹን ወዲህ ወዲያ አሾራቸው:: ቀጥሎም መነፅሩን ብድግ አድርጎ ወደ ዓይኑ እያስጠጋ «ፍልስፍናውን ተወት አድርገህ ከቢሮዬ ብትወጣ የሚሻል መስለኝ!» አለው::

አስቻለው ለባርናባስ ማስጠንቀቂያ ብሎ ሳይሆን ጉዳዩንም ጨርሷልና ድንገት ብድግ እያለ «አቶ ባርናባስ! ያልገባህን ሁሉ ከፍልስፍና የምትቆጥር ከሆነ የባሰ ድንቁርናህን ያሳያል:: እየገባህ ያልገባህ ለመምሰል የምትሞክርም ከሆነ ካለ ትቀላለህ:: ቅሌት ሲደጋገም መጨረሻው ሳይነሱ ሆኖ መጥፎችን ያስከትላል::» ካለ በኋላ «በዓይን የሚታይ፣ በእጅ የሚዳሰስ ግልጽ ነገር ልትክድ ነው!?» ብሎት በሩን ከፍቶ ወጣና መልሶ ጓ! አድርጎ ዘግቶት ሄደ::

አስቻለው ከባርናባስ ክፍል እንደ ወጣ በንዴት ፈረስ ወደ አንድ አቅጣጫ እየተራመደ ነበር:: ነገር ግን በዚያው በነበረበት ኮሪደር ውስጥ ድንገት ቀጥ ብሎ ቆመ:: ያልተወለደ ገዳይነቱ ጉዳይ ስሜቱን ቆጣቆጠው:: በዚህ ዙሪያ ለራሱ የሚያውቀው ነገር ባይኖርም ባርናባስ ግን ያለ አንድ ነገር እንዳለነሳው ገመተ:: ብቻ አንድ ነገር ታየው:: ስለ ሁሉም ጉዳይ የሆስፒታሉን ሜዲካል ዳይሬክተር ማነጋገር:: በቀጥታ ወደ ዳይሬክተሩ ቢሮ አመራ::

ዶክተር ደጀኔ አድማሱ ከሆስፒታሉ ሜዲካል ዳይሬክተርነቱ በተጨማሪ የፖርቲ መሠረታዊ ድርጅት ሁለተኛ ፀሃፊ ነው! ከባርናባስ ቀጥሎ ያለ የፖለቲካ ባለ ስልጣን:: ያም ሆኖ በሁሉም የሆስፒታሉ ሠራተኞች ዘንድ የሚወደድና የሚከበር ሰው ነው:: በሰከነ አመለካከቱና በረጋ አነጋገሩ የተመሰገነ ነው:: በዕድሜው ብዙ የገፋ ባይሆንም እንደ አባት የሚታይ ነው:: እንደ አለቃ ሲያዝና ሲቆጣ አይታይም:: ከዶክተር እስከ ዘበኛ ያሉትን የሆስፒታሉ ሠራተኞች በእኩል ዓይን እያየ የማስተናገድ የተለየ ስጦታ ያለው ቅንና አስተዋይ ሰው ነው:: በዚህ የተነሳ የሚያከብረው እንጂ የሚፈራው የለም::

ዶክተር ደጀኔ በተለይ ለአስቻለው ጥሩ አመለካከት አለው:: ሁለቱ በዲላ ሆስፒታል ውስጥ ከአራት ዓመት በላይ አብረው ሰርተዋል:: በዚህ ጊዜ ውስጥ ዶክተር ደጀኔ የአስቻለውን ማንነትና ምንነት እንዲሁም ሙያዊ ስነ-ምግባሩን ይወድለታል:: የአቅሙን ያህል ከቅርብ ርቀት ተከታትሎታል:: ስራውንና አሰራሩን ይወድለታል:: በባህሪውም ትሁት መሆኑን ተረድቶታል:: ሲፍጨረጨር ለብዙ ጊዜ አጢኖታል:: ሃሳቦችን ሲያፈልቅና ደካማ መስለው በታዩት ሙያዊ በሆኑና ባልሆኑ ጉዳዮች ላይ ሲከራከር በቅንነት መሆኑን ተገንዝቧል:: ሀሳቡን ሲሰነዝር የማይፈራና የማይጨኑት ግልፅና ደፋር መሆኑን አጢኗል:: ከሁሉም በላይ ሲዋሽና ሲያስመስል አይቶት ወይም ሰምቶት አያውቅም:: ከዚህም አጠቃላይ ሁኔታ በመነሳት ለአስቻለው ጥሩ ስሜት አለው::

አስቻለው በር አንኳኩቶ ሲገባ ዶክተር ደጀኔ ብድግ ብሎ ተቀበለው። በእለቱ
በላውንጅ ዙሪያ ከውስጥ ለብሶ ከላይ ነጭ ጋውን ደርቧል። ፊቱ አነስ ያለችና ፍክት
ያለ ጠይም ነው። እንዲያውም አብዛኛው ፊቱ በረጂም ጥቁር ጺም የተሞላ በመሆኑ
ዮቹው ትንሽና ጠይም ፊቱ ቦግ ብላ ትታያለች። ፀጉሩ ገባ በማለቱ ግንባሩ ሰፋ
ብሏል። ዓይኖቹ አነስ አነስ ያሉ ሆነው ነገር ግን ቀልጭ ያሉ ናቸው። አፍንጫው
በፊቱ ልክ አጭር ናት። በጥቁር ጺሙ መሀል ብልጭ የሚሉት ጥርሶቹ ነጫጭ
ናቸው። ሁል ጊዜ ፈገግታ አይለየውምና ደስተኛ ይመስላል።

«ፈልገህ ነበር ዶክተር» አለው አስቻለው ተጨባበጠው ከጨረሱ በኋላ።

«ይቻላል። ቁጭ በል!» ሲል ዶክተር ደጀኔ አስቻለው እንዲቀመጥ
ጋበዘው፣ በግራ እጁ ፊትለፊት ግድግዳ ሥር የተቀመጠ ሶፋ እያሳየ።

አስቻለው ሊቀመጥ ወደ ሶፋው ሲያመራ እንኳ ስሜቱ ጥሩ እንዳልሆነ
አረማመዱ ያስታውቃል። ፈጠን ፈጠን ብሎ ከተራመደ በኋላ ሶፋው ላይ ዘፍ
ብሎ በመቀመጥ የፊቱን ላብ በእጁ ይጠርግ ጀመር። ከንፈሩንም ደጋግሞ በምላሱ
ያርሳል። ዓይኖቹም ፍጥጥ ብለዋል። የአስቻለውን የውስጥ ስሜት የተረዳው
ዶክተር ደጀኔ ለአፍታ ያህል ትኩር ብሎ ከተመለከተው በኋላ፦

«ምነው አስቻለው! ሰላም አይደለህም?» ሲል ረጋ ባለ አነጋገር ጠየቀው።

«ፍፁም ደህና አይደለሁም!» አለው አስቻለው ቁጭ ባለበት እየተቁነጠነጠ።

«ምነው ምን ሆንክ?»

«በዚህ ሆስፒታል ውስጥ ምን እየተካሄደ እንደሆነ ሊገባኝ አልቻለም
ዶክተር። በጣም ግራ ተጋባሁ።

«እንዴት?»

«በቃ! አልገባኝም!»

ዶክተር ደጀኔ የአስቻለውን አኳኋን ሲመለከት ቆየና «ስማ አስቻለው!» ሲል
ረጋ ባለ አነጋገር ጠራው።

«አቤት!»

«የዲላ ሆስፒታል ትልቅ ተቋም ነው። ከስልሳ በላይ ሠራተኞች አሉት።
በርካታ ህሙማን ይመላለሱበታል። አስታማሚዎችም እንዲሁ። አልፎ አልፎም
የሥራ ሃላፊዎችና የፖለቲካ ባለ ስልጣኖችም ብቅ ብቅ ይሉበታል። በአጠቃላይ ብዙ
የሰው ዓይነት የሚመጣበትና የሚቀበል ትልቅ መንግስታዊ ተቋም ነው። ታዲያ
የሰው ዓይነት የሚመጣበትና... በእያንዳንዳችን ቤትና ግቢ ውስጥ ምን
ዛሬ በእያንዳንዳችን የግል ህይወት ዙሪያ፣ በእያንዳንዳችን ቤትና ግቢ ውስጥ ምን
እየተካሄደብን እንደሆነ እንኳ በውል የማናውቅበት ጊዜ ላይ ሆነን በዚህ ትልቅ
ተቋም ውስጥ እየተካሄደ ያለውን ነገር መረዳት ቢያቅተን ምን ያስገርማል!» ሲል
ጥያቄ አዘል በሆነ አስተያየት ስሜቱን ገለፀለት።

አስቻለው በዚህ የዶክተር ደጀኔ ንግግር ለአጠቃላይ ችግሩ አጠቃላይ
መፍትሄ ያገኘ ያህል ደስ አለው። እጅግ በጣም ረካ። በንዴትና በብስጭት
ውጥርጥር ብሎ የነበረ ሰውነቱ ላላ ረገብ ሲል ተሰማው። አተነፋፈሱም ወደ
መደበኛ ፍጥነትና መጠን ተመለሰ። ዓይኖቹ ራሳቸው እንደገና ሲደላደሉ ተሰማው።
አቀማመጡንም በአዲስ መልክ አስተካክሎ በረጅሙ ተነፈሰና፦

«ታዲያ ምን ብንሆን፣ ወዴትስ መሄድ ይሻለናል?» ሲል ዶክተር ደጀኔን
በትካዜ ዓይን እያየ ጠየቀው።

«ምን መሆን እንዳለብን መናገር የምችል አይመስለኝም። መሄጃው ግን
ላይገድ ይችላል። ችግሩ የተሻለ ቦታና ሁኔታ ከማግኘቱ ላይ እንደሆነ እንጂ!» አለ
ዶክተር ደጀኔ ሃሳብ ውስጥ የገባ እየመሰለ ጣሪያ ጣሪያ በማየት።

አስቻለው ለችግሩ መፍትሄ ሊፈልግ የገባበት ቢሮ በሌላ ችግረኛ የተያዘ
እስከሚመስለው ድረስ ዶክተር ደጀኔ አሳዘነው። ከፊቱ ላይ የሚያነበበው ትካዜና
ከአነጋገሩ የሚረዳው የውስጥ ስሜት ራሱን መልሶ አስጨነቀው። በዚሁ ስሜት
ውስጥ ሆኖ እያየው ሳለ ዶክተር ደጀኔ ፊቱን ወደ አስቻለው መለስ አደረገና፦

«ግን የዛሬው የተለየ ችግርህ ምን ሆኖ ነው እኔን የፈለከኝ? ስሜትህም
ጥሩ እንዳልሆነ ይሰማኛል።» ሲል ጠየቀው።

«የዚህ የጤና መኮንንነት ኮርስ ውድድር ውጤት አናደደኝ። አንተ ደግሞ
የሆስፒታሉ ሜዲካል ዳይሬክተር ነህና ቢያንስ ቢያንስ ሙያ ነክ በሆኑ ጉዳዮች ላይ
እንዴት የመወሰን ስልጣን እንዳጣህ ሊገባኝ አልቻለም። አመጣጤም ለኔ የማይገባኝ
የተለየ ችግር ካለብህ ብትገልፅልኝና ቁርጡን አውቄው ባርፍ ብዬ ነው። ምናልባት
ተገቢ ያልሆነ ጥያቄ አቅርቤልህ ከሆነ ይቅርታ!» አለው የይቅርታ ጥያቄው ከልብ
የመነጨ መሆኑን በሚገልጽ አስተያየት እያየው።

ዶክተር ደጀኔ የአስቻለው ጥያቄ ተገቢ መሆኑንና የዛሬም አመጣጡ ለዚሁ
ጉዳይ ሊሆን እንደሚችል ገና ሲገባ ጠርጥሮ ስለነበር ሀሳቡ እንግዳ አልሆነበትም።
ብዕሩን ከጠረጴዛው ላይ አንስቶ በጣቶቹ መሀል እያሽከረከረ በረጅሙ ተነፈሰና፦
«ከፋህ አይደል?» አለው አስቻለውን በይቅርታ ዓይን እያየ።

«ተቃጠልኩ! እንዲያውም አመመኝ!»

«አይፈረድብህም አስቻለው!»

ዶክተር ደጀኔ አሁንም በረጅሙ ተነፈሰና
ብሎት በሁለት የእጁ መዳፎች ሙሉ ፊቱን ሸፍኖ ያስብ ጀመር። ዶክተር ደጀኔ አስቻለው

«ዶክተር!» ሲል አስቻለው ከሀሳቡ መለሰው። ዶክተር ደጀኔ አስቻለው
የሚለውን ለመስማት ትኩር ብሎ እያየው ሳለ አስቻለው ቀጠለ። «ይህን ውሳኔ እኮ
እንደማታምንበት ልቤ ይረዳል። እንደሚያስጨንቅህም እገነዘባለሁ። በዚህ ምክንያት
ልወቅስህም አልመጣሁም። የቆጨኝ ግን በዚህ ጉዳይ ላይ ሳነጋግረው ባርናባስ
የሰጠኝ ምላሽ—» ብሎ ሳይጨርስ ዶክተር ደጀኔ ድንገት አቋረጠው።

«አነጋገርከው?» ሲል ቀልጠፍ ብሎ ጠየቀው።

«አዎ።»

«ምን አለህ ታዲያ?»

«ጭራሽ ያልተወለደ ገዳይ ብሎኝ አረፈ።»

ዶክተር ደጀኔ ትስሙ ስብር አለ። የውድድሩን አሸናፊ ለመምረጥና ቃለ
ጉባዔ ለማፅደቅ በተገኘበት የኮሚቴ ስበሰባ ላይ በአንዳንድ ነርሶች የሥነ- ምግባር
ዙሪያ ውይይት ሲደረግ በአስቻለው ላይ እንዲህ ያለ አሉባልታ ሲነገር ሰምቷል።
በወቅቱም ሁኔታው አሳዝኖት ነበር። ለነገሩ በስብሰባም ላይ ጉዳዩ ሲነሳ በአሉባልታ
ደረጃ የተጠቀሰ መሆኑን ቢረዳም አስቻለው ይህን ነገር ቢሰማው ምን ያህል
ሊያሳዝነው እንደሚችል ተሰምቶት ሆዱ ፈርቶ ነበር። ለካ ባርናባስ አንስቶ
የአስቻለውን ስሜት ጎድቶታል።

«ግን በዚህ ነገር የተነሳ ምንም እንዳይሰማህ አስቻለው።» አለ ዶክተር
ደጀኔ አስቻለውን በማፅናናት ዓይነት።

«ያልተመረጥኩት በዚህ ምክንያት ይሆን?»

«በፍጹም!» አለ ዶክተር ደጀኔ እርግጠኛ ስለመሆኑ ለማሳየት ጭንቅላቱን እየወዘወዘ፡፡ «ቀድሞ ነገር ውድድር አልተካሄደም፤ ነገሩ ከላይ ተወስኖ ነው የመጣው!» አለው፡፡

«ከላይ ማለት?» ሲል ጠየቀ አስቻለው፡፡ በእርግጥ የቃሉ ትርጉም ጠፍቶት አልነበረም፡፡ ነገር ግን ከዚያው ከአውራጃው ወይስ ከክፍለ ሀገር አለያም ከማዕከል ለማለት ፈልጎ እንጂ፡፡

«በቃ ከላይ! ሌላው ምን ያደርጋል፡፡» ካለ በኋላ ዶክተር ደጀኔ ድንገት ወደ ሌላ ሃሳብ ውስጥ ገብና መሬት መሬት እያየ ይተክዝ ጀመር፡፡ አስቻለው በበኩሉ በንዴት አንጀቱ ተቃጥሎ በእግሩ መሬቱን መታ መታ ያደርግ ጀመር፡፡

«ግን አስቻለው!» ሲል ዶክተር ደጀኔ ለራሱ ነቃ አለና አስቻለውንም አነቃው፡፡

«አቤት ዶክተር!»፡፡

«ለመሆኑ እዚህ ሆስፒታል ውስጥ ለምን ያህል ጊዜ ሰራህ?»

«ስባት ዓመት አለፈኝ፡፡»

«ዝውውር ሞክረህ አታውቅም?»

«አልሞከርኩም፡፡»

«አሁንስ ለመሞከር አታስብም?»

«ይሳካል ብለህ ነው ዶክተር?»

«እርግጠኛ ነኝ፤ በዚህ ከተማ ውስጥ የምትሰራቸው አሮጊትና ሽማግሌ የሉህም፡፡»

«ምንም» አለ አስቻለው፡፡ ግን ደግሞ ወዲያው ሒሩትን ጨምሮ ታፈሡ፣ በለሀና መርዕድ ትዝ አሉት፡፡ ከእናትና ከአባቱ ባልተናነሰ ሊለያቸው የማይፈልጋቸው የቅርብ ቤተሰቦች ናቸውና፡፡

«አንዳንድ አንዳንድ ከዚህ ሆስፒታል ወደሌላ ብትዛወር የተሻለ ርምጃ መስሎ ይታየኛል፡፡ ለምን መሰለህ አስቻለው!»

«እሺ ዶክተር!»

አስቻለው በጽሞና እያዳመጠው መሆኑን የተረዳው ዶክተር ደጀኔ ሀሳቡን ቀጥር አደረገና «በቅድሚያ አንድ ነገር ልጠይቅህና አንተም ትክክለኛውን ንገረኝ፡፡» ሲል ፈገግ እያለ በማየት አሳሰበው፡፡

«ምንም አልደብቅህም ዶክተር!»

«ለመሆኑ እዚህ ከተማ ውስጥ የቤት ጓደኛ አለችህ?» ሲል አሁንም ፈገግ ብሎ እያየ ጠየቀው፡፡ አስቻለው ድንገት ብሎ ድንገት ስሜቱ ሲለዋወጥ አይቶ ዶክተር ደጀኔ አሁንም ፈገግ እያለ «ምነው ደነገጥክ?» ሲል ደግሞ ጠየቀው፡፡

አስቻለው የምንተ-ሰፍረቱን «እ… …ማለት» አለና እንደ መርበትበት ከአደረገው በኋላ «መኖር አለችኝ፤ ግን ምነው?» ሲል ዶክተር ደጀኔን መልሶ ጠየቀው፡፡

«እስከገባኝ ድረስ ከልጅቷ ጋር አብራችሁ አይደላችሁም፡፡ ልጅቷ የምትኖረው ከእህቷ ጋር ነው፡፡ ልክ ነኝ?»

«እንዴት ሊታወቅ ቻልክ ዶክተር?»

ዶክተር ደጀኔ በሃሳቡ እስኪደርሲቶ ጠረጴዛውን መታ መታ አደረገና እንደገና ወደ አስቻለው ቀና በማለት «ቅድም በቢታችንና በግቢያችን ውስጥ የሚከናወነውን እንኳ አናውቅም ብዬህ ተማምነንስ አልነበረም?» አለው፡፡

«ልጅቷ ገና በልቤ ውስጥ ነች ያለችው!»

ዶክተር ደጀኔ ድንገት «ኪም-ኪም-ኪም-ኪም» ብሎ ሳቀና «እየህ! ግማሽ አካሏ ከውጭ ቀርቶ ጥሯል!» አለና አሁንም «ኪኪኪኪ…»

«የሷን ነገር ለምን አነሳኸው?» አለ አስቻለው ዶክተሩ ሳቁን ሲጨርስ፡፡

«ግን እንደው እርግጠኛ ታውቃለች?»

«በፍጹም ዶክተር! እንዲያውም እታምነኝ እንደሆን እንጂ ልጅቱ ገና ድንግል ናት፡፡»

ዶክተር ደጀኔ እንደ መደነት ብሎ «ድንግል! ድንግል!»

«ከልቤ ነው የምነግርህ ዶክተር!»

ዶክተር ደጀኔ በመገረም ዓይኑን ፍዝዝ ብሎ አስቻለውን ሲመለከት ቆየና ራሱንም ወዘወዘ፡፡ እንደገና ነቃ በማለት «ገና ብር እምባር ስበረልዎ … እንላለን!»

«እዚያ ከደረስን!» አለና አስቻለው «ግን የእሷን ነገር ለምን እንዳነሳህ አልገባኝም ዶክተር» አለ አሁንም ዓይኑን በዶክተር ደጀኔ ላይ እያንከራተተ፡፡

«ምክንያት አለኝ!»

«ምን?»

«ያልተወለደ ገዳይ የሆንከው ከእሷ ጋር በተገናኘ ሁኔታ ነው፡፡ እኔ ግን ነገሩ አሉባልታ ስለመሆኑ በትክክል ገብቶኛል፡፡» አለው፡፡

«ምን ከምን ጋር ተገናኘና»

«ምንም ከምንም!» አለና ዶክተር ደጀኔ በአጭር ቃል መሰለትና ራሱ ቀጠለ፡፡ «እንደሚመስለኝ የአንተና የልጅቷ እህት ግንኙነታችሁ ጥሩ አይደለም፡፡»

«አሁን አሁን እየተበላሸ ነው፡፡»

«የልጅቷ እህትና ባርናባስ እንደሚግባቡስ ታውቃለህ?»

«ለምን ሲደንቀኝ የሰነበተው ይህ ነው፤ ብትነግረኝ ይከብድህ ይሆን?»

«ብዙ የማውቀው ነገር የለም፡፡ አንድ ቀን ግን እኔና ባርናባስ ከተማ ውስጥ አብረን ስንዘዋወር መንገድ ላይ ከአንዲት ሴት ጋር ተነጋግሮ ወደኔ እንደመጣ ያህች ሴት መምህርት ናት፤ ያቤሎ በነበርኩበት ወቅት እሷም እዚያ ስለነበረች እንተዋወቃለን፡፡› ብቻ ነው ያለኝ» አለው ዶክተር ደጀኔ፡፡ አስቻለው የሁለቱን የትውውቅ መሠረት በማወቁ ሳይሆን አይቀርም አንገቱን ደጋግሞ ነቅንቆና

«አሁን ብዙ ነገር ገባኝ ዶክተር፡፡» አለው፡፡

«አዎ አስቻለው! የጓደኛህ እህትና ባርናባስ ከፈጠሩት ግንኙነት በመነጨ ነው ያልተወለደ ገዳይነትህ የተወራብህ፡፡ ይህን ደግሞ የነገረኝ ራሱ ባርናባስ ነው፤ መምህርቷ ነገረችኝ ብሎ፡፡ ግን ደግሞ ይህን ሁሉ የምነግርህ ብዙ ጊዜ አካኼድህ ፈትለፈት ስለሆነ ድንገት ሳታውቀው እንዳትጠለፍ ለጥንቃቄ ይረዳሃል ብዬ ነውና አስብበት፡፡ የዝውውሩንም ጉዳይ ችላ ባትለው መልካም ይመስለኛል፡፡› አለው፡፡

አስቻለው በረጅሙ ተንፍሶ ጥቂት ካሰላሰለ በኋላ «የሰሞኑ እንቆቅልሽ ገና ዛሬ ተፈታልኝ ዶክተር!» ብሎ ከንፈሩን ነክሶ ጣሪያ ጣሪያ እያየ በሀሳብ ጭልጥ ብሎ ሄደ፡፡ የዶክተር ደጀኔን የዝውውር ሃሳብ በቀላሉ አልተመለከተውም፤ እንዲያውም በርካታ ነገሮች በተዘዋዋሪ መንገድ ይህንኑ ጉዳይ ሲያስቡት

ለማስታረቅ ከሞከሩ በኋላ ሰንዘተዋል። በልሁና መርዕድ ታፈሡና ሸዋዬን ለማስታረት ከሞከሩ በኋላ ሸዋዬ ተመልሰው የገለፁለት ነገር «ሔዋን በሃሳብ ምን ጊዜም ከአንተ ጋር ናት። ሸዋዬ ባለችበት አካባቢ ግን እንኳ ...» የሚል ፍሬ ሃሳብ የነበረው ነው። ከዚያም በላይ ፊቷ የእርቅ ሙከራ በተደረገ ሦስተኛ ቀን ረፋዱ ላይ ሔዋን ሳያስባት ለዚያውም በእንባ ረስርሶ ወደ ቤቱ መጥታ ነበር።

«ምነው ሔዩ?» ነበር የአስቻለው ጥያቄ።

«እንካ ይኸን ወረቀት አንብብ» ብላ እንዲት ወረቀት ሰጠችው።

አስቻለው ወረቀቷን ገለጥ አድርጎ ሲያነብ የሚከተለውን መልዕክት አገኘበት።

«ለተከበራችሁ አባትና እናቴ ለአቶ ተስፋዬ ይርጋ እና ለወይዘሮ ስንዱ በላቸው፤ ለጤናችሁ እንደምን አላችሁ። እኔ ግን በጣም ተቸግሬያለሁ። እናንተንም እሷንም ለመርዳት ስል ሔዋን የተባለች ልጃችሁን ወደ ዲላ ይዣት መጥቼ ነበር። እሷ ግን ትምህርቷን እርግፍ አድርጋ ትታ ሥራዋ ወንድ ማባረር ብቻ ሆኗል። እንዲያውም መዘዟ ለኔ ተርፎ ችግር ላይ ወድቄአለሁ። ከመቸገሬ የተነሣ በጥቂት ቀናት ውስጥ ከቤቴ ላባርራት ነው። ምናልባት ልጃችን ባክና መቅረት የለባትም የምትሉ ከሆነ ከሁለት አንዳችሁ መጥታችሁ ውሰዷት። መጥተን አንወስድም ካላችሁ ውርድ ከራሴ።»

ልጃችሁ ሸዋዬ ተስፋዬ

አስቻለው ደብዳቤውን አንብቦ ከጨረሰ በኋላ በንዴት እሳት ለብሶ እሳት ጎርሶ ፈጠን ባለ አነጋገር «ሴትዮዋ ምን እያለች ነው?» ሲል ሔዋንን ጠየቃት።

«እኔ እንጃ አስቼ፣ ግራ ገባኝ» ሔዋን እያለቀሰች።

«የት አገኘሽው?»

«ዛሬ ጠዋት ሥራ ስትሄድ ረስታው መስለኝ አልጋዋ ላይ ተቀምጦ አገኘሁት»

«ቀዳድጂ ልጣለው?»

«ተው አስቼ፣ ነገር ይባባስብኛል። ግን አንድ ነገር ላማክርህ?

«ምን?»

«በቃ/ አንተም ወደዚያ ቤት አትምጣ። እኔም ከዚህ ቤት ልቅር?»

«እስከ መቼ?»

«ጊዜና ቦታ እስኪገጥመን ድረስ?» ብላው ነበር።

አስቻለው ይህን ሁሉ በሃሳቡ ከቃኘ በኋላ «ለመሆኑ ዝውውሩስ በቀላል ይሳካል ብለህ ነው ዶክተር?» በማለት ዶክተር ደጀኔን ጠየቀው።

«መሞከር ጥሩ ነው። አሁን ደግሞ የካቲት እየገባ ነውና የዝውውር ፎርም መሙያው ጊዜ ስለሆነ አታሳልፈው።»

«አንተ ልትረዳኝ የምትችለው ነገር ሊኖር ይችል ይሆን?»

ዶክተር ደጀኔ ለአስቻለው መልስ ከመስጠቱ በፊት ትክዝ ብሎ ያስብ ጀመር። አስኪርቢቶውን በጣቶቹ ውስጥ ይዞ እያሽከረከረ በታችኛው ጥርሱ የላይኛውን ከፈሩን ነክሶ ወደ ጠረጴዛው ያይ ጀመር።

«ይህን ያህልም አትጨነቅ ዶክተር። ምናልባት ዝውውር ብጠይቅ እንኳን በዚሁ ባርናባስ በሚባል ሰው ተንኮል ሊጨናገፍ የሚችል ነገር ቢኖር ልትከላከልልኝ የምትችልበት መንገድ ካለ ብዬ እንጂ የተለየ—» ብሎ አስቻለው ሳይጨርስ ዶክተር ደጀኔ አቋረጠው።

«አንድ ነገር ማድረግ እችል ይመስለኛል።»

«ምን ይሆን ዶክተር?»

«የዋናው መሥሪያ ቤት አስተዳደር አገልግሎት ኃላፊ በቅርብ የማውቀው ሰው ነው። ዝውውሩ ደግሞ በማዕከል ስለሚፈፀም የገጠመህን ማኅበራዊ ችግር ሁሉ ብነግረውና ሥራውን እስካጣበላሽበት ድረስ ሊረዳህ ቢሞክር ደስ ይለኛል። ግን ደግሞ ፈጠን ያልክ እንደሆን ነው።» አለው።

«ፈጠን ማለት?» ሲል ጠየቀ አስቻለው።

«ማለቴ...» አለና ዶክተር ደጀኔ እንደገና አመነታ። ፊቱንም ክፍት እያለው ሲሄድ ውስጥ ውስጡን የሚያስጨንቀው ነገር ያለ ይመስላል። እንደ ምንም ራሱን አረጋግቶ «በቅርቡ ወደ አዲስ አበባ የምትሄድ ከሆነ ማስታወሻ ልጻፍልህና ሰውየውን አግኘው። ምናልባት በሚሰጥህ ምላሽ መሠረት ሌላም አማራጭ እንፈልግ ይሆናል። ፍጠን ያልኩህ ግን ያለ ምክንያት አይደለም፤ በሆዴ አንድ ምስጢር ስላለ ነው። አምንህሁና ብነግርህ ቅር አይለኝም።» አለው በደረቁ ፈገግ እያለ።

«ምን ይሆን ዶክተር?»

«እኔም በበኩሌ እየፈጠንኩ ነው።»

«ማለት?» አለ አስቻለው ለሚሰማው ነገር እየጓጓ።

«አንተን ከዚህ አገር ተዛውረህ ሂድ ስልህ የኔም ልብ ቀድሞ መሸፈቱን ልነግርህ ወደድኩ።»

«ወዴት?» አለ አስቻለው ግራ ገባ እያለው።

«ሩቅ ወዳለ ቦታ።» አለና ዶክተር ደጀኔ ድንገት ዓይኑ በእንባ ሞላ።

«ከሀገር ውጪ?»

«አዎ! ስደት፤ ከሀሊና ቅኝ አገዛዝ ነጻ ለመውጣት!!»

ምዕራፍ አራት

«እባ አበበ.... እባ አበበ!» አለ ዲማሙ የዕለቱን የማለዳ እስላማዊ ስውት ሊያደርስ:: እስቻለው ዛሬ መንገደኛ ስለሆነ ከእንቅልፉ ያነቃው ዘንድ ሲለምነው የነበረ ድምፁ ነው:: ልክ እንደነቃ ከእንቅልፉ ቀና ብሎ ንትንት ሲል እንደ ውትሮው አልተለለውም፤ ከሰውነቱ ልጥፍ ብላ የተኛች ሴት አለች፤ ሒዋን ተሰፋ::

በወርሃ የካቲት ሁለተኛ ሳምንት ላይ ሸዋዬ ዲላ ውስጥ አልነበረችም:: ለአንድ ሳምንት የሚቆይ አጭር የሥራ ላይ ስልጠና ልትካፈል ወደ አዲስ አበባ ሲሄድ ሄዳለች:: በዚያው ሳምንት በዕለተ ሐሙስ እስቻለው ወደ አዲስ አበባ ሊሄድ ተነሳ፤ ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ዋና መሥሪያ ቤት የዝውውር ጥያቄ ሊያቀርብ::

በአስገዳጅ ሁኔታ ግንኙነታቸውን ለጊዜው ለማቋረጥ ወስነው የነበሩት እስቻለውና ሒዋን ለዚያች ዕለት የጋራ ቃላቸውን በጋራ አፍርሰዋል፤ የሸዋዬን አለመኖር ኢጋጣሚ ተጠቅመው አብረው ለማደር:: በዚሁ መሠረት ትናንትና ምሽት ላይ እስቻለውና በልሁ ከቤቷ እምጥተዋት ሒዋን በእስቻለው ቤት፣ በእስቻለው አልጋ ላይ፣ ከእስቻለው ጋር አድራለች::

እስቻለው መብራት አብርቶ የሒዋንን እስተኛኘት እየት ሲያደርገው አላወቀችው:: አንድ እግሯን በጭኖቹ መሀል አስገብታ፣ በግራ እጇ አንገቱን እቅፍ አድርጋው:: አንድ እግሯን በጭኖቹ መሀል አስገብታ፣ በግራ እጇ አንገቱን እቅፍ በቀኝ እጇ ደግሞ ወገቡ ላይ ጥምጥም ብላ ተኝታለች:: ከእንቅልፉ ቀና ብሎ ለአፍታ ያህል ቁልቁል ሲያያት ቆየና ግንባሯ ላይ ሳም አደረጋት:: ምናልባት በእንቅልፍ ስሜት ውስጥ ሆኗ የእስቻለው እንቅስቃሴ ተሰምቷት ሳይሆን አይቀርም ሒዋን ዓይኗን ገለጥ ስታደርግ ሁለቱም ተያዩ::

«ጊጋ እንዴ እስቹ?» ስትል ጠየቀችው::

«እረፍደ!»

ሒዋን ከእንቅልፏ ቀና ብላ ወደ መስኮት እየት ስታደርግ የውጭ ብርሃን የለም:: «ጥሸሁ» ብላ ተመልሳ ተኛች::

«ለኔ ማለቴ እኮ ነው፤ መንገደኛ አይደለሁ!»

«ህልም እያየሁ ነበር እስቹ!»

«ጥሩ ወይስ መጥፎ?»

«የት እንዳለሁ አይታወቀኝም፣ ግን እናትህ ይመስሉኛል:: እፊቴ ቆመው ‹ልጄን ከምታመጭበት አምጪ! የት ነው የደበቅሽው? ኋላ አንድ ነገር ቢሆን ነገ ከእንቺ ራስ ላይ አልወርድም› ይሉኛል::»

«ምን አልሻት ታዲያ?» አላት እስቻለው እንደ መሳቅ እያለ::

«ምንም! ዝም ብዬ ሳያቸው ከእንቅልፌ ነቃሁ::»

«አትዋሺ!» አለና እስቻለው አሁንም በቀልድ ዓይነት «ይኼኔ ‹ልጄን አምጪ› ስትልሽ ‹አልሰጥም› ‹የት ነው የደበቅሽው› ስትልሽ ‹ልቤ ውስጥ› ኋላ ልጄ አንድ ነገር ቢሆን ስትልሽ ደግሞ ‹ግድ የለዎትም እኔ ጋር የተተመጠ ነገር አይደብላሽም› ብለሻት ይሆናል::» አለና ለራሱ እየሳቀ ሒዋንንም አሳቃት::

እስቻለው ሳቁን ከጨረሰ በኋላ ወደ ቁም ነገር በመመለስ «ይኼኔ እናቴ በህይወት ብትኖርልኝማ ኖሮ ብዙ ችግሮቼ በቀላሉ ይፈቱ ነበር:: በተለይ እንቺን የመሰለች ምራት በማግኘቷ እየተደሰተች እንቺን በማለቴ ለተፈጠረብኝ ችግርም መላ ትፈልግልኝ ነበር:: ግን ምን ዋጋ አለው! እኔም እሷም ሳንታደል ቀረንና በልጇ በዘን ተቃጥላ ሞተች::» አላት እውነትም በመጥፎ ትዝታ ፊቱን እየከፋው::

«ልጅ ሞተባቸው ነበር?»

«ያውም የኔ ታላቅ! እሷንም እኔንም በገንዘብ ይረዳ የነበረ፤ እውሮች ‹ለምን እየህ?› ብለው ገደሉት::» አላት::

«እውሮች?» አለች ሒዋን አባባሉ ግራ ገብ ብሏት::

«ዓይን ቢኖራቸውም ማስተዋል የጎደላቸው ህሊና ቢሶች::» አለና ያን አስቃቂ የቀይ ሽብር ዘመን በዓይን ህሊናው ለአፍታ ያህል ዳሰስ አደረገው::

«እየኒጋ ነው ሒዩ» አላት ከሃሳቡ መለስ ሲል::

«ትሄድ እስቹ?»

«በትድሚያ ግን የውጭ በይኝ::» ብሎ ዓይኖቹን ፈገግ አድርጎ ሲመለከታት ምላሹን ሰጠች:: አንገቱን እቅፍ አድርጋ ከንፈሮቿን በከንፈሩ ላይ ጣል አደረገቻቸው:: ጠሰዳት:: ወሰደችው:: ዓይኖቻቸው ተስለመለሙ:: ሰውነታቸው ሞቀ:: ገላቸው ተጣበቀ:: ትንፋሻቸው በረከተ:: በስሜት ባህር ውስጥ ሰጠሙ:: ምድር ላይ ሆነው ገነትን ለአንድ አፍታ ተመላለሱባት::

ከስሜት ገብ መልስ እስቻለው ከአልጋ ላይ ወረደ:: ታጠበ:: አበጠረ:: ለብሶ የመንገድ ሻንጣውን ትከሻው ላይ አንገተና አልጋው ስር ቆሞ ሒዋንን ቁልቁል እየተመለከተ «ከአዲስ አበባ ምን ገዝቼልሽ ልምጣ ሒዩ?» ሲል ጠየቃት::

«ምንም እስቹ!»

«ለምን? ጫማ፣ ልብስ፣ ወይም ሌላ ነገር ብገዛልሽስ»

«ማን ገዛልኝ ብዬ ልለብሰው እስቹ?» አለችው አልጋው ላይ በክንዷ ደገፍ ብላ ከእንቅልፏ ቀና በማለት እየተመለከተችው:: እስቻለው የዘነጋው ነገር ነበር:: እንደ አዲስ ትዝ ብሎት ድንገት ትስሙ ስብር አለና ለአፍታ ያህል በሀዘን አይን ተመለከታት::

«አንተ ብቻ በሰላም ተመለስ::» አለችው ሒዋን ዓይን ዓይኑን እያየች::

«አሜን የኔ ፍቅር» ብሏት ሳም አድርጎ ተሰናበታት::

ሰዓቱ ገና ማለዳ ስለነበር ሒዋን ወዲያው አልተነሳችም:: አልጋው ላይ ጋለል ብላ ጣሪያ ጣሪያ እያየች እስተዳደሯን በትዝታ ታየው ጀመር:: ደስ የሚል ሌሊት ነበር:: ከሁሉም በላይ እስቻለው ቃሉን ማክበሩ አስደስታት:: ለግማሽ ሌሊት ያህል ከንፈሮቻቸው ሳይላቀቁ፣ በመተሻሸት ብዛት በስሜት ሲፈራገጡ ያላደሩትን ያህል እስቻለው ለአንዴ እንኳ ወደ ጭኖቿ መሃል ሳያመራ በማደሩ ከልቧ አደነቀችው:: ከመቸውም ጊዜ በላይ በእሱ ላይ ያላት እምነት የፀና ሆነ:: ያ ሌሊት ሒዋን ሴት እንደመሆኗ ወንድ እንደሚያስፈልጋት በውል የተረዳችበትም ነበር፤ ከሆነም እስቻለው ፍስሀ ብቻ!!

ሒዋን መልካም የፍቅር ተስፋ የምታይበት አዕምሮዋን ስጋትም ጠቅ ያረገው ነበር፤ ከሁሉም በላይ እህቷ ሸዋዬ በሁለቱ ፍቅር ላይ ያላት መጥፎ አመለካከት:: ከዚያ ቀጥሎ ለቤተሰቦቿ የጻፈችባት ደብዳቤ:: ሁለቱም እንደ ትልቅ የፍቅር እንቅፋት ያሰጓታል:: ያስጨንቋታል:: ለመሆኑ እስቻለው የዝውውሩ ጉዳይ

ቢቀናውስ? ወደ ሄደበት ቦታ አብሯው ትሄድ ይሆን? በምን ሁኔታ? ጠፍታ ወደስ በቤተሰቦቿ ፊታድ? የሚታወቅ ነገር የለም:: ይህም አንዱ የሀሳቧ ዘርፍ ነበር::

በዚህና በመሳሰሉት የፍቅር ትዝታ ዙሪያ ስታወጣ ስታወርድ ሳታውቀው ተኩል አካባቢ ተጠግቷል:: የጠዋት እረፍታ ጥሯል፣ በግምት ወደ አንድ ሰዓት ተነሳች:: የእስቻለውን እሊጋ ስምር አድርጋ ፈረቃ ተማሪ ናትና ፈጥና ተነሳች:: በዘመዷናው ላይ የተቀመጠ የእስቻለውን አንጣጠፈች:: ተጣጥፋ በጉሯን ጎነጎነች:: ከዛም ወደ ቤቷ:: ፎቶ ግራፍ ሳም ሳም አድርጋ ቤቱን ቆልፋ ወጣች::

እስቻለው ከሾፌሩ ኋላ ሦስት ሰዎችን በሚያስቀምጠው የመጀመሪያ ወንበር ላይ በሁለት ሰዎች መካከል ተቀምጦ ወደ አዲስ አበባ ይጓዛል:: በግራ በኩል የመስኮት ጥግ ይዘው ዕድሜያቸው ወደ ሀምሳዎቹ የገባ የሚመስል፣ ነገር ግን በምቾት ኑሮ ፊታቸው ደንዛዥዝ ያለ ቀይ መልከ መልካም ሴት ተቀምጠዋል:: ራሳቸውን የጥቁርና ነጭ በራብራ ቀሚስና ባለ ጥለት ነጭ ነጠላ ለብሰዋል:: ከቀኙ በኩል ደግሞ አንዲት ዕድሜዋ በጥቁር ሻሽ ሸክፍ አድርገው አስረዋል:: ከቀኙ በኩል ደግሞ አንዲት ዕድሜዋ ከአሥራ ሰባት ዓመት የማይበልጣት ጠይም ልጃገረድ ተቀምጣለች:: ነጣ ያለ ጉርድ ቀሚስ በቀይ ሹራብ ለብሳለች:: ስልክክ ያለች የጠይም ቆንጆ ናት:: ሦስቱም እየተጨዋወቱ ይጓዛሉ::

ከዲላ እስከ አዲስ አበባ ድረስ ያለውን የሦስት መቶ ስልሳ አምስት ኪሎ ሜትር መንገድ በዘመናዊ አውቶቡሶች ከአራት እስከ አምስት ሰዓት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ተጉዞ መጨረስ በተቻለ ነበር:: ነገር ግን በዚያ መስመር ላይ ከዘጠኝ ያላነሱ የፍተሻ ኬላዎች ትልቅ እንቅፋቶች ስለነበሩ ከአመሻሹ አሥራ አንድ ሰዓት በፊት አዲስ አበባ መድረስ አይታሰብም:: መዛዙ ደግሞ ቡና፣ እህል ሆና ላይበላ፣ ውሃ ሆና ላይጠጣ፣ እንደው ባህላዊ ልማድ በመሆኑ ብቻ:: ህዝብ ደግሞ ቋጠር አድርጎት ከዚህ የተነሳ በየኬላው መንገዱ ይጠዳል:: መንግስት ደግሞ በጥብቅ ይከለክላል:: በፍተሻ የሚባክነው ጊዜ ያን መንገድ ረጅምና አሰልቺ ያደርገዋል::

ከጊዜው መባከንና በመውጣት መውረድ ከሚደርስ እንግልት ይልቅ መንገደኞችን ክፉኛ የሚያማርራቸው የፈታሾች አብራት ነው:: መኪና ልክ ኬላው ላይ እንደ ደረሰ ‹ውረድ!› የሚል ጩኸታቸው፣ ፈትሸው ሲያስገቡ ‹ተሰለፍ!› የሚል ግልምጫቸው፣ ሻንጣ ሲፈትሹ በውስጡ ያለውን ዕቃ ሃላፊነት በጎደለው ሁኔታ ሲመነቃቅሩት፣ እንድም ትሁን ሁለት ኪሎ የምትሆን የቡና ቋጠሮ ካገኙም በባለ ቋጠሮው ተጓዥ ላይ የሚያደርሱት እንግልት፣ በቃ ሁሉም ነገራቸው ያስመርራል:: ያበሳጫል::

እስቻለው የተሳፈረበት አንደኛ በራሪ አውቶቡስ ከዲላ መውጫ ኬላ ጀምሮ በጩኸት፣ በአፖስቶ በአቤላ እና በአዋሳ ጥቁር ውሃ ፍተሻ ጣቢያዎች ላይ ፍዳውን ጨርሶ ከሻሸመኔው ኬላ ላይ ከአረፋዱ አራት ሰዓት አካባቢ ደረሰ:: የማይቀረው ዕዳ ሊከፈል ተጓዥ ሁሉ ከመኪና ላይ ወረደ:: ከእስቻለው አጠገብ በስተግራ በኩል የመስኮት ጥግ ይዘው ተቀምጠው የነበሩት ወይዘሮ ግን አልወረዱም::

ፈታሾች ከመኪናው ዙሪያ እንደ ልማዳቸው ሲጎማለሉ በርካታ ደቂቃዎችን ከአሳለፉ በኋላ ሁለት ፈታሾች ከመኪናው ፊትና ኋላ በር በኩል ገብተው ለመበርበር ተዘጋጁ:: ቀድሞ በፊት በር በኩል የገባው ፈታሽ የመኪና በር መወጣጫ ረግጦ ጠልጠል ሲል እኒያ ሴትዮ መኪና ውስጥ ቁጭ ብለው አገኛቸው::

«ምንድነው?» ሲል ዓይኑን ፈጠጥ አድርጎ ጠየቃቸው:: ፈታሹ አጠር ጠየም ያለ ነው:: የፊቱ ወዝ ያብረቀርቃል:: ፊቱ ጠፍጠፍ ያለና አፍንጫው ደፍጠጥ ያለ ጎረምሳ ቢጤ ነው:: የመለዮውን እጅጌ ሰትስቶት የእጁ ጡንቻ ፍርጥም ብሎ ይታያል:: ስንስለት የሚያህል የወርቅ ሀብል ደረቱ ላይ ተጋድሞ ይንቀለቀላል::

«የኔ ልጅ፣ መውጣት መውረዱ ስለቸት ብሎኛል ና እዚሁ ፈትሸ ሳስ!» አሉት ሴትዮዋ በልመና ዓይነት ፈገግ ብለው ፈታሹን እየተመለከቱት::

«ክክሽ ውረጅ! ምን ትቀልዳለች!?» አለና ፈታሹ ቆጣ ብሎ በዓይኑም ገርመም አደረጋቸው::

ሴትዮዋ ፈገግታቸው ድንገት እልም ብሎ ጠፋና ፊታቸው ኩስትርትር፣ ዓይናቸውም ፍጥጥ አለ:: ተናደዱ:: በተቀመጡበት ወንበር ላይ እንደ መቅበጥበጥ እያሉ «አንቺ አትበለኝ አንተ! ኧረ ይሄ ደፋር!» አሉት::

«እ?» አለ ፈታሹ ወደ ውስጥ ገባ እያለ:: እንደገና «ምን አልሽ አንቺ?» ብሎ ቁልቁል ይመለከታቸው ጀመር::

«አንቺ አትበለኝ አልኩህ!» አሉና «ደሞ ምን ያፈጥብኛል?» ብለው እሳቸውም አፈጠጡበት::

«ቆይ ምንድነሽ አንቺ?» አላቸው ድፍረታቸው ያልተለመደ ሆኖበት::

«ሰው! አውራ እመስላለሁ?»

ፈታሹ ለአፍታ ያህል ፍጥጥ ብሎ ተመለከታቸውና ወደ ውጭ እየተመለሰ «ቢቃ ይሄ መኪና ተገትሮ ይውላታል እንጂ ይቺ አሮጊት ሳትወርድ አይፈተሽም::» ብሎ ከመኪናው ላይ ወረደ:: «እንዳትገባ!» ሲል በኋላ በኩል ሊገባ የነበረውንም ፈታሽ ከለከለው::

ተሳፋሪው ሁኔታውን ይከታተል ነበርና ግራ የመጋባት ስሜት አደረበት:: ሊጉላላ ነው:: ግማሹ ፈታሹን ይለምን ጀመር:: ሌላው ደግሞ ከመኪና ላይ እንዲወርዱ ሴትዮዋን:: ሴትዮዋ ግን ፍንክች አልል አሉ:: ይልቁንም በሚለምናቸው ተሳፋሪ ላይ ወረዱበት:: «መድሐኒዓለም አይለመነኝ ንትንት ላልል!» አሉና «እዳሜ እንዴ ወኔህን አትጨቅጭቀኝ! ወዲያ ሂደህ የምትለምነውን ለምን! መቼም ልብ ሙት ሁሉ! ደሞ እኒንም ይዘኸኝ ሙታ!» አሉ ትንፋሻቸው በርክቶ ተስልበሀ፣ አፍንጫቸው ነፋ ሞሸሽ፣ ነፋ ሞሸሽ እያለ::

በሁሉቱም አቅጣጫ ልመና ያልተሳካለት ተሳፋሪ ያለው አማራጭ አንድ ብቻ ነበር፣ ወደ ኬላው ሃላፊ በመሄድ የተፈጠረውን ሁኔታ ማስታወቅ:: በእርግጥም በርካታ ተሳፋሪ ወደ ሃላፊው ቢሮ ተከታትሎ ሄደና አቤቱታውን ማቅረብ ጀመረ:: በዚህ መሀል ግን ብዙ ጊዜ ባከነ::

ከበርካታ ደቂቃዎች በኋላ የኬላው ሃላፊ ሳይሆን የማይቀር አንድ ፖሊስ የመቶ አለቅነት መለያ ምልክቱን ደርድሮ ከቢሮ ወጣና በለመነው ተሳፋሪ ታጅቦ ወደ መኪናው አመራ:: ቀጠን ያለ ረጅም ነው:: ፊካ ያለ ጠይም ሆና ገተር ባለ

አፍንጫው ላይ ጥቁር መነጽር አድርጓል፡፡ ልክ ከመኪናው የፊት በር አጠገብ ሲደርስ የተጣባቸውን ፈታሽ ጨምሮ ተሳፋሪው ሁሉ የሚፈጠረውን ሁኔታ ለማየት ዙሪያውን አሰፈሰፈ፡፡ አስቻለውም ከህዝቡ ፊት ሆኖ ከፈታሾቹ አጠገብ ቆሟል፡፡ የኬላው ኃላፊ ወደ ውስጥ ሴትዮዋን እያየ «ምንድነው ችግሩ?» ሲል ጠየቃቸው፡፡

«እናንተ እያላችሁ ችግር መች ይጠፋልና? ችግር ለመፍጠር አይደል ዘወትር የተሰለፋችሁት!» አሉ ሴትዮዋ ዓይናቸውን አፍጥጠው ቆንጥንጥ እያሉ፡፡

«መኪናው አይፈተሽ ነው የሚሉት?»

«እኔ አልወጣኝም፡፡ ስትፈልጉ መንታትሩት!፡፡» አሉና ሁለመናቸውን እየገዘሩቸው «ብል! ስንት እንበሳ የመሳሰለ ጀግና ወልጄ ወልጄ ለወግ ማረግ ያደረስኩ ሴትዮ እንድ ጓንጉቸር በመሰለ አሽከርህ ልዋረድ!» አሉና ቀሚሳቸውን ቀልጠፍ እያረጉ «ይሀ ቅሌታም! አያውቅም እንጂ እኔ አቦነሽ ሃይሌ ስንት ኩሩ የሚያከብረኝ ሴትዮ ነኝ፡፡ ይሀ ባለጌ! ባለጌ ያሳደገው!» አሉ በማከታተል፡፡

«አሁንም አታርፊ እንዴ አሮጊት!» አላቸው ያ መጀመሪያ የተጣላቸው ፈታሽ በመቶ አለቃው ትከሻ ላይ አንገቱን ስገግ አድርጎ ወደ ውስጥ እያየ፡፡

ሴትዮዋ አሁንም እየተቅበጠበጡ «አንተ እንደኔ አታረጅ፤ አንት የተረገምክ! ለድሜ እኮ የንጡህና ምልክት ነው፡፡ አዳሜን እያስለቀስክ ዛሬ ደረትህ ቢያብጥ ዘላለም የምትኖር መሰለህ? ዛሬ ሰው ቢያቅተው ነገ አንድዬ ይደፋሃል፡፡ ምናምንቴ! የምናምንቴ ልጅ!» አሉት ወይዘሮ አቦነሽ ሀይሌ፡፡ ምናልባት አፍ አላፊ የተናገሩ መስሏቸው ለማካካስ ሳይሆን አይቀርም ከተቀመጡበት ድንገት ብድግ አሉና ግማሽ ጭናቸው እስከሚታይ ድረስ ቀሚሳቸውን እያራገፉ «ቡና ቋጥራለች ብላችሁ ተሆነ ያው! አቦነሽ ሃይሌ ነኝ!» ብለው ቁጭ እያሉ «ተንገዲህ ወዲያ አዳሜ ዓይንህን ብታፈጥ የምፈራህ እንዳይመስልህ!» አሉ፡፡ እንዳነጋገራቸው የኬላውንም ሀላፊ ነካ እያረጉ ይመስላል፡፡

መቶ አለቃው ቀጥሎ ምን ማድረግ እንዳለበት በማሰብ ላይ ሳለ በሴትዮዋ ቆራጥነትና አነጋገር ልቡ ሲነካ የቆየው አስቻለው ጣልቃ ገባ፡፡ «እኔ እምልህ መቶ አለቃ!» አለው እጆቹን በደረቱ ላይ አቆላልፎ የኬላውን ሃላፊ ዓይን ዓይኑን እያየ፡፡

«አንተ እምትለኝ?» አለው መቶ አለቃው በንቀት ዓይን እያየው፡፡

«የምትፈልጉት ቡና አለማለፉን ወይስ የተሳፋሪውን ከመኪና ላይ መውረድና መውጣት?» ሲል ኮስተር ብሎ ጠየቀው፡፡

«አንተ ምንድን ነህ?» አለው ያ መጀመሪያ ከሴትዮዋ ጋር የተጣላ ፈታሽ ጣልቃ ገብቶ፡፡ ዓይኑንም አፈጠጠበት፡፡

አስቻለው ውስጡ ተቆጣ፡፡ ቀድሞም ቢሆን መቶ አለቃው በንቀት ዓይን ሲያየው በስጨት ብሎ ነበርና አሁን ደግሞ የባሰ በመናደድ «ምንድነህ?» ሲል የፈታሹን ጥያቄ ራሱ ደገመው፡፡

«አዎ ምንድነህ?»

አስቻለው ድንገት ሳያስበው አንድ ነገር በአዕምሮው ብልጭ አለበት፡፡ በሆዱ ‹የመጣው ይምጣ› እያለ «ካኪ አለመልበሴን አይተህ ከሆነ ተሳስተሃል! እኔ ግን ሙሉ የፓርቲ አባል ነኝ!» ብሎ መታወቂያ እንደመፈለግ ዓይነት እጆቹን ከአንድ ኪሱ ወደ ሌላው ያራውጣቸው ጀመር፡፡

«ቆይ ጓድ!» አለ መቶ አለቃው ፈጠን ብሎ፡፡ የአስቻለውንም ሁለት እጆች በሁለት እጆቹ ያዛቸው፡፡

«ደሞ ምንድነህ ይለኛል እንዴ ይሄ!?» በማለት አስቻለው በፈታሹ ላይ ዓይኑን አፈጠጠ፡፡ ያ ፈታሽ በሀፍረትና በፍርሀት ፊቱ ልውጥውጥ አለ፡፡

«የኛ ችግር እኮ — » ብሎ መቶ አለቃው ንግግር ሲጀምር አስቻለው ቶሎ ብሎ አቋረጠው፡፡

«እ! የእናንተ ችግር?»

«እንዱን አስወርደን ሌላውን ስንተው ሕዝቡ አድሎ አደረጋችሁ እያለ—» ብሎ ሳይጨርስ አሁንም አስቻለው አቋረጠው፡፡ ፈጠን ፈጠን ባለ አነጋገር፡-

«ፈጽሞ! ያ የሕዝብ ችግር አይደለም፡፡ ይልቅስ የህዝብ ምሬት እሱ አንድ ወይም ሁለት ኪሎ ቡና ሲከስከል ባለ ስልጣናት ግን በጠፍ ጨረቃ በጭነት መኪና እያስጫኑ ማሳለፍ መቻላቸው ነው፡፡ ይህን ደግሞ እኛም በደንብ እናውቃለን፡፡ አንተስ? ትክዳለህ?» ሲል በመቶ አለቃው ላይ አፈጠጠበት፡፡

«እልፎ እልፎ ይደረጋል፡፡ ግን የበላይ መመሪያ በውስጥ...» ብሎ ሳይጨርስ አሁንም አስቻለው አቋረጠው፡፡

«አውቃለሁ! ባልተጻፈ ህግ እናንተን ያዝዛሉ፤ ለራሳቸው፡፡ የተጻፈውን ደግሞ በሚዲያ ያነባሉ፤ ለሕዝባቸው፡፡» ካለ በኋላ እጁን ወንጨፍ አድርጎ «ችግሩስ ይሄ አይደል?» አለና እጆቹን በኪሱ ውስጥ ከትቶ ጎርደድ እያለ «አሁን ሕዝቡ አይንገላታ! ቶሎ አስፈትሹልንና እንሂድበት፡፡» አለው፡፡

«በቃ ገቢታችሁ ሂዱ!» አለ መቶ አለቃው፡፡ እንደገና ወደ ሕዝቡ ዞሮ ጮክ ባለ ድምጽ «መንገደኞች ግቡ! ግቡ!» ሲል አወጀ፡፡

ሕዝቡ በሁለቱም በሮች ግርር ብሎ መግባት ጀመረ፡፡ መቶ አለቃውና ረዳቶቹ ወደ ቢሮአቸው ማምራት ጀመሩ፡፡ «ምን ዓይነት እሳት የላስ ካድሬ ነው!» በማለት አስቻለውን በየሆዳቸው አሙት፡፡ አስቻለው በስራው ሥራ ራሱ እየተገረመ መኪናው ውስጥ ገብቶ ቁጭ አለ፡፡ ሳቁ እፍን ያደርገዋል፡፡

ያ መኪና ከሻሸመኔ ተነስቶ ብዙ ኪሎ ሜትሮችን ተጉዞ፤ በርካታ ከተሞችን አቋርጦ ቡልቡላ ከተማ እስከሚደርስ ድረስ በተሳፋሪ መካከል ይህ ነው የሚባል ጭውውት አልተደረገም፡፡ ምናልባት ጎን ለጎን የተቀመጡ መንገደኞች በሹክሹክታ ያወሩ እንደሆነ እንጂ ድንበር ያለፈ የጉዞ ላይ ጫጫታ አልተሰማም፡፡ ግን ሁሉም በየሆዱ የሚነጋገርበት ጉዳይ አለ፡፡

ተሳፋሪው በተለይ የወይዘሮ አቦነሽን ድፍረት እንዲሁም ደግሞ አስቻለው በ ካድሬነቱ ያሳየውን ‹ግልጽነት› በግርምት ያሰላስላል፡፡ ሁለቱም ‹አስገራሚዎች› የተቀመጡት ደግሞ ከፊት በኩል በአንድ ወንበር ላይ በመሆኑ ተሳፋሪ ሁሉ ፊትለፊት እያየ በልቡ ያደንቃቸዋል፡፡ የፈታሾቹም ልብ እስከምን ድረስ እንደሆነ አውቆ በሀሳብ ይታዘባቸዋል፡፡

አስቻለውና ወይዘሮ አቦነሽ ሃይሌም በየልባቸው የሚያሰላስሉት ጉዳይ አላቸው፡፡ አስቻለው በሴትዮዋ ቆራጥነት ከመጀመሪያ ጀምሮ እየተደነቀ ሲሆን በተለይ ስለ ራሱም ድርጊት ራሱ ይገረም ይዟል፡፡ ‹ግን ምን ዓይነት ሰይጣን ገፋፍቶኝ ነው በእንዲህ ዓይነት ድፍረት ውስጥ የገባሁት?› እያለ እጁን አፉ ላይ አስደግፎ ያስባል፡፡ ገፋ አድርገው መታወቂያ እንዲያሳያቸው ቢጠይቁት ኖሮ ሊፈጠር ስለሚችለው ነገር እያሰላሰለ ባለፈ ነገር ይሳቀቃል፡፡

ወይዘሮ አቦነሽ በሁኔታቸው ውስጥ ቢያንስ የአስቻለው ካድሬነት፣ በእንግድነት ልባቸው ውስጥ ገዝቶ ያስገርማቸዋል። ሻሸመኔ ከመድረሳቸው በፊት ከአስቻለው ጋር በዚሁ ጉዳይ ላይ ሲነጋገሩ ቆይተዋል። ያን እያሰላሰሉ ካድሬን ሊያስቀይም የሚችል ነገር ተናግሬ ይሆን? በማለት ወደ ኋላ ያስባሉ። ግን ደግሞ የሚያስፈራ ካድሬ አለመሆኑን በፊታቸው ፊት የተናገረውን በማስታወስ ራሳቸውን ያጽናናሉ። በዚህ መሀል ግን በአስቻለው፣ በወይዘሮ አቦነሽና በጠይሟ ልጃገረድ መካከል ምንም ዓይነት ንግግር ሳይደረግ የላንጋኖ ሀይቅ ዳርቻ መንገድ ተጠናቆ የዘዋይ ተጀመረ።

«እነዚያ ሰዎች ምን እያደረጉ ነው?» ስትል ጠይሟ ልጃገረድ በአነሳችው ጥያቄ ነው በመሀላቸው ንግግር የተጀመረው። ለጥያቄዋ መነሻ የሆነው በርካታ ሰዎች በየመንገዱ ዳር እየቆሙ ወደ መኪናው እያሳዩ የበረባሶ ጫማ ሲያወጡ ማየቷ ነበር።

«ስለ ግቡን ማለታቸው ነው።» አላት አስቻለው ወደ ጠይሟ ልጃገረድ ዞር ብሎ እየተመለከታት።

«ታዲያ አጠገባቸው የታል?» ስትል ጠየቀችው።

«ስለሱ ጫካ ውስጥ ነው ደብቀው የሚያስቀምጡት። ፊትለፊት ከአስቀመጡትማ የደንና ዱር አራዊት ባለስልጣን ይነጥቋቸዋል። መኪና ሲቆምላቸው ግን በሩጫ ሄደው ያመጡታል።» አለና አስቻለው ወደ ወይዘሮ አቦነሽ ዘወር ብሎ በፈገግታ እያያቸው «እማማ ቢሆኑ ኖሮ ማንንም ሳይፈሩ በግልጽ ነበር የሚሸጡት። ልንጠቁሽ ብሎ የሚመጣ ቢኖር ያው ነው፤ ደህና አድርገው በነገር ይጠብሱታል!» አለና «አይደል እማማ?» ሲል ፈገግ ብሎ ጠየቃቸው፤ እግረ መንገዱንም ወደ ጨዋታ ሊያስገባቸው አስቦ።

«ሆሆይ! በምን ገመትከኝ ልጄ?» አሉት ወይዘሮ አቦነሽ እሳቸውም ፈገግ ብለው በመስኮት በኩል ውጭ ውጭ እያዩ።

«ደፋር ነዎታ! ቆራጥ። ማን አባቱ ነው እርስዎን የሚደፍርዎት? ተያየን እኮ!» አላቸው አሁንም ፈገግ እያለ።

«ደፋርስ አንተ!» አሉት ወይዘሮ አቦነሽ ወደ ቀኝ ዞር ብለው አስቻለውን እየተመለከቱ።

«እኔ ደሞ ምን ሳደርግ አዩኝ?»

ወይዘሮ አቦነሽ ‹ይህን ስታደርግ› ማለት አልፈለጉም። እስከ አሁን ሲገረሙበት በነበረ ነገር ላይ አተኩሩና «ግን ምናለ ቅዱስ ሚካኤል ፈቃዱ ሆኖ በእነዚህ ማንይሆኔዎች መሀል የአንተ ዓይነቶችን በርከት አድርጎልን ቢሆን?» አሉና ፊታቸውን ወደ መስኮቱ መለስ አደረጉ።

«ምንድናቸው ማንይሆኔዎች?» ሲል አስቻለው ጠየቃቸው።

«እኔ ስማችሁ አይያዘኝ ልጄ፤ ሰፖ ነው ሱፖ የምትባሉት?» አሉና ወዲያው ደግሞ «ቀደም ሲል እንኳ ደርግ ነበር ስማችሁ» አሉት።

አስቻለው ድንገት «ሃ-ሃ-ሃ-ሃ...» ብሎ በረጅሙ ሳቀ። በአሳሳቁ ጠይሟ ልጃገረድ ተገርማ ትኩር ብላ እስከምታየው ድረስ እንደገና «ቂ..ቂ..ቂ..ቂ...»

«አጠፋሁ እንዴ የኔ ልጅ? ምነው ሳቀብኝ?» በማለት ወይዘሮ አቦነሽ ፈገግ እያሉ ጠይሟን ልጃገረድ ጠየቋት ከጨዋታውም ለመቀላቀልም በማሰብ።

«እኔ እንጃ!» ብላ ስትመልስላቸው ራሳቸው ቀጠሉ።

«የልቡን ነግሬው ይሆናል!» አሉ አስቻለውን እየት እያረጉ።

«በጣም እማማ፤ የልቤን ነው የነገሩኝ!» አላቸው አስቻለው አሁንም እየሳቀ።

«ግን ምን ቢያደርጉህ ይሆን እንዲህ በአደባባይ የዘረጠጥኻቸው? ይሄኔ አስቀይመዋቸው እንስም ነካ አድርገውህ ይሆናል።» አሉት በዓይናቸውም እየት እያረጉት።

«ግን የእነሱ አባል ስለመሆኔ እርግጠኛ ነዎት?»

«እንዴ! በአደባባይ እየተናገርከ?»

«እንግዲያውስ ከእንግዲህ ወዲያ ተጠንቀቁ። እኔ ፊት እንዳች እፍ እላፊ ብትናገሩ ዋ!» አሉና አስቻለው አሁንም ሳቀ።

«የመጣችሁትን አምጡ! መቼም እንግዲህ ሆናችኋል! ጨፍሩብን!» ካሉ በኋላ «ግን ግን እርግማን ወርዶባችሁ መሆኑን ማን በነገራችሁ!» አሉት ፊታቸውን ወደ መስኮት መልሰው ፈገግ እያሉ።

ጠይሟ ልጃገረድ በአስቻለው ሁኔታ እየተጠራጠረች መጥታለች። ግን ደግሞ ካድሬ ባይሆን ያን የመሰለ ሥራ እንደማይሰራ ገምታለች። ምንም ይበላት ምንም ብቻ ልትጠይቀው ፈለገች።

«የፓርቲ አባል አይደለህም?» አለችው ቀና ብላ እየተመለከተችው።

አስቻለው ለጠይሟ ልጃገረድ መልስ በመስጠት ፈንታ ወዲያውም ወይዘሮ አቦነሽን በመሰለ ሰው አዕምሮ ውስጥ በወትቱ የፓርቲ አባልነት የእጉል ስብዕና ስዕል እንዳይፈጠርበት እውነቱን ሊነግራቸው እያሰበ ሳለ እነዚያ በረባሶ ጫማ አወዛዋጊ ከሰል ሻጮች በብዛት ታዩና መኪናው ድንገት የመንገድ ዳር ይዞ ቆመ። ሾፌሩና ረዳቱ ወረዱ፤ ከሰል ሊገዙ።

«ጤፉ የምትፈልጉ መውረድ ትችላላችሁ።» አለ ረዳቱ። አስቻለውን «መናፈስ ቀርቶ ጨምሮ በርካታ ተሳፋሪዎች ወረዱ። የአካባቢው አየር ሁኔታ ግን መናፈስ ቀርቶ ለመተንፈስም ያስቸግራል። ሁሩሩ ይርገበገባል። ፀሐዩ እናት ይበሳል። ጭራሽ ሙቀቱ እንደ ስም ያቀልጣል። የንፋስ ሽውታ የለም። ከሰል ሻጮቹ ወደ ሚኪ በመርገጥ የቆዩትን ያህል ጊዜ ቆይተው የከሰል ጆንያቸውን ተሸክመው እየተሸቀዳደሙ ከመኪናው አጠገብ ሲደርሱ ሾፌሩና ረዳቱ የከሰል ምርጫቸውን ጀመሩ። የዋጋ ድርድር ጦፈ። ነገር ግን ገበርና ሻጭ የተስማሙ አይመስሉም።

«ቢቃ ወደ ላይ ከፍ ብለን እንገዛለን።» አለና ሾፌሩ ወደ መኪናው ሲዞር ሲል አንድ ሁኔታውን ይከታተል የነበረ ተሳፋሪ ድንገት፦

«ደሞ እንደገና ሊታገላን?» አለው ቆጣ በማለት። በመሀል ዕድሜ ላይ የሚገኝ ቀይና ፊተ ሰፊ ሰው ነው። ከሙቀቱ የተነሳ ኮቱን አውልቆ ትከሻው ላይ አንጠልጥሏል።

«ምን አገባህ?» አለ ሾፌሩ ቁልፎቹን እያቅጨለጨለ።

«ገንዘቤን አውጥቼ የተሳፈርኩበት መኪና እኮ ነው፤ ለምን አያገባኝም?» አለው ሰውዬው ዓይኑን ፈጠጥ አድርጎ።

«ታዲያ የገዛኸው መሰለህ እንዴ?» አለና ሾፌሩ ዝም ብሎ ወደ መግቢያው በር አመራ።

ሰውየው በጣም ተናደደ፡፡ እሱም ወደ መኪናው ገስግሶ ገባና በተሳፋሪ መሀል በመቆም «ስሙ ጃዝ! ይኼ ሾፌር ይሄን መኪና ለከሰል ማገር እንደገና ቢያቆም እጣላዋለሁ፡፡ ጊዜ በኪ እንዳትፈርዱ፡፡» አለ፡፡

«እንዣ... እንዣ...! መንገድ ላይ ሊያሳድረን! ኧረ እኛ እርቦናል! ይኸማ፣ ይጮማ —» በማለት ተሳፋሪው አጉረመረመ፡፡ ሰዓቱ ወደ ሰባት ተጠግቷል፡፡ ያ ሰዓት ዝዋይ ላይ ምሳ ተበልቶ ማብቂያው ነበር፡፡ የሻሸመኔ ፍተሻ ጣቢያ ጭቅጭቅ ብዙ ጊዜ ስለ ወሰደ ጉዞው ጎታታ ሆኗል፡፡ በዚያው ልክ ተሳፋሪ ሆዱ ተርቦ እህል እህል ይላል፡፡

ሾፌሩ ደንታም አልሰጠው፡፡ ይልቁንም የመኪናውን ሞተር አጠፋና «ና እስቲ ስትነዳው ልይህ!» በማለት ፊቱን ወደዚያ ሰውዬ አዙሮ ይመለከተው ጀመር፡፡

ያ ሰውዬ አላመነታም፤ ብድግ ብሎ ኮቱን አስተመጠና የሸሚዙን እጅጌ ሰትስቶ ከወደ መሀል አቦበ፤ በቀጥታ ወደ ሾፌሩ አመራ፡፡ ማንም ተመሰስ ብሎ አልጋዘዘውም፡፡ ሁሉም ዝም ብሎ ያየው ጀመር፡፡

ወይዘሮ አቦነሽ ግን እስቻለውን ጎንተል አደረጉና «እባክህ ልጄ፣ ይኼ ሰው ይሆን ሾፌር አንድ ነገር ያረገው እንደሆን መንገድ ላይ ማደራችን ነው፤ ተነሳና መላ በል» አሉት፡፡

እስቻለውም ሁኔታው አሳስቦታል፡፡ ተነስቶ ቆመና የዚያን ሰውዬ መንገድ ዘጋ፡፡ «ቆይ የኔ ወንድም፤ ረጋ በል፤ መሪውን የያዘው እሱ ነው፡፡» ካለ በኋላ ወደ ሾፌሩ መለስ ብሎ «ሾፌር፣ ዳግመኛ ከቆምክ ጠብህ ከእሱ ብቻ አይደለም፡፡ ከሁላችንም ጋር ነው፡፡ አሁንም ሂድልን» አለው፡፡

ሾፌሩ ምንም አላለም፤ የመኪናውን ሞተር አስነሳ፡፡ ያም የተቆጣ ሰው ወደ መቀመጫው ተመለሰ፡፡ ጉዞው ቀጠለ፡፡ ያ ተሳፋሪ ሁሉ ሌላ ሦስተኛ ብርቅዬ ሰው በማየቱ የዕለቱን ጉዞ ተዓምረኛ፣ ይለው ጀመር፡፡ ሁሉም በየሆዱ ደፋሮችን ሁሉ አመሰገነ፡፡

ሾፌሩ ያለ ወትሮው ተደፈርኩ በሚል ስሜት ሳይቆጣ አይቀርም፤ ያን መኪና ይረግጠው ጀመር፡፡ ያለ ማቋረጥ ጡሩምባ እያሮጠ አከነፈው፡፡ አንዳንዱ ተሳፋሪ ቶሎ ዝዋይ ደርሶ እህል ውሃ ለማለት ቸኩሎ ስለነበር መንፈሱ ተነቃቃ፡፡ ሌላው ደግሞ አደጋ እንዳይደርስ ሰጋ፡፡ እንዲያውም ‹ኧረ ይኸን ሾፌር አንድ በሉ! ተው ረጋ በል በሉት› ያሉም ነበሩ፡፡ ሾፌሩ ግን ልክ እንደ መኪናው ራሱም ቤንዚን የጠጣ ይመስል በንዴት ስሜት ውስጥ ገብቶ ያን ሽንጠ ረጂም ሰማያዊ መልክ አውቶቡስ ክንፍ አስወጥቶ ያበርረው፣ ያከንፈው ጀመር፡፡

በግምት ለአስር ደቂቃ ያህል ከተጓዙ በኋላ ወይዘሮ አቦነሽ ንግግር ጀመሩ፡፡

«እየሸው አንተ ልጅ!» አሉት እስቻለውን በሁኔታው ተገርመው፡፡ «የአንተ ቃል እንኳን የፍተሻ ኬላ ወሮበላ ‹ሕኒ ነኝ› ያለውን ሾፌሩም ልክ አስገባው፡፡» አሉና ፈገግ እያሉ ተመለከቱት፡፡

«ሥልጣን ነዋ-ህእ!» አለ እስቻለው እየሳቀ፡፡

«ለእንዲህ እንዲህ ዓይነቱማ መዳኒት ናችሁ፡፡» አሉት ወይዘሮ አቦነሽ ፈገግ እያሉ፡፡

«ሃ-ሃ-ሃ-ሃ...» በማለት እስቻለው በረጅሙ ከሳቀ በኋላ በዚያው ቀጥሎ ቲ-ቲ-ቲ...» ሳቁን ሲጨርስ ወደ ወይዘሮ አቦነሽ ዞር ብሎ «እኔ ብሆን እኮ እርስዎም እያትቱኝ ነበር፡፡» አላቸው፡፡

«ከአንተ ዓይነቱ ጋር እኔስ ምን አጣልቶኝ፡፡» አሉና ወይዘሮ አቦነሽ «እኔ እሚገርመኝ ይኸ ኮሜዲ እየተነሳ ደረቴ እበጠ ብሎ የሚፎገላውን ሳይ! በጠባይ ቢጠይቀኝ እኮ መቸስ ትዛዝ ነውና አላስቸግረውም ነበር፡፡» አሉ ወይዘሮ አቦነሽ፡፡

«ግን አንድ እውነት ብነግርዎት ያምኑኝ ይሆን እማማ?» ሲል ጠየቃቸው እስቻለው በቁም ነገር ዓይነት አነጋገር፡፡

«ምን?» አሉት መልከት እያሉት፡፡

«ተናድጄ ድንገት በል በል ብሎኝ ነው እንጂ እኔ እኮ የፓርቲ አባል አይደለሁም፡፡»

«መድሃኒዓለምን በል!»

«እውነት እማማ! ድንጉጦች መሆናቸውን ስለማውቅ ነው ያጭበረበርኳቸው፡፡»

ወይዘሮ አቦነሽ እስቻለውን እንደ አዲስ ይመለከቱት ጀመር፡፡ ውሸት ወይም እውነት እየተናገረ ስለመሆኑ ከፊቱ ላይ የሚያነቡ ይመስላሉ፡፡

«እንዴት ደፈርካቸው ታዲያ?» አሉት አሁንም ትኩር ብለው እያዩት፡፡

«ለእነሱ ሀይልና ጉልበት ምንጩ የኛ ፍርሀት ነው፡፡ የሚያጠቁንም በተናጠል ስለሚያገኙን ነው፡፡ በእርግጥም ጥቅሙን ስለሚያውቁት ነጣጥለውናል፡፡ አንዱ ሲጋፈጥ ሌላው ዝም ስለሚል ብቻ ነው ልባቸው ጎራ እያከለ ሰው የሚንቁት፡፡» ብሎ ሌላ ነገር ሊቀጥል ሲል ወይዘሮ አቦነሽ ቀደሙት፡፡ ጎንበስ ብለው በእስቻለው ሥር ጠይሟን ልጃገረድ እየተመለከቱ፡፡

«እንቺ ቆንጆ! ይኸ ልጅ የሚለኝን ትሰሚያለሽ?» ሲሉ ጠየቋት፡፡

«እኔማ ከተጠራጠርኩ ቆየት አልኩ እማማ፡፡ አሁን ደግሞ በደንብ አመንኩት፡፡» አለቻቸው እሳቸውንም እስቻለውንም ተራ በተራ እየተመለከተች፡፡

«ይኸው! ምስክርም አገኘሁ፡፡» አሉና እስቻለው ወዲያው ደግሞ «እንደውም አሁን ወደ አዲስ አበባ የምሄደው እነሱን ለመሸሽ ነው፡፡ በፈጠሩብኝ ችግር ምክንያት ዲላ መኖር ስላልቻልኩ ወደ ሌላ አገር ዝውውር ጠይቄ ለመሄድ ነው፡፡»

«ለመሆኑ እነሱ የሌሉበት አገር አለ እንዴ?» ሲሉ ጠየቁት አሁንም እስቻለውን ትኩር ብለው እያዩ፡፡

«ምናልባት በአዲስ መንፈስ የተሻለ —» ብሎ እስቻለው ሳይጨርስ ድንገት ጓ! ያለ ድምጽና ሀይለኛ ቅፅበታዊ ብርሃን በሁሉም ተሳፋሪ ላይ ተብለጨለጨ፡፡ የሁሉም ተሳፋሪ ድምፅ በአንዴ ቆመ፡፡ እስቻለውም ያለበት ቦታ ጠፋበት፡፡ ሁሉም ተጠፋፋ፡፡

* * *

ታፈሡ የከሰዓት ፈረቃ ሥራ ገቢ ስለነበረች የዚያን ዕለት ጠዋት ሁለት ሰዓት አካባቢ የቤት ልብሶቿን እንደለበሰች ከልጆቿ ጋር ሶፋ ላይ ቁጭ ብላ ቁርስ ትበላለች፡፡ ልጆቿ ከፊትለፊቷ ቁጭ ብለው ሲበሉ የዳቦ ቁራሽ በመናጠቅ ሰበብ እየተጣሉ ሲናቆሩባት እየገላገለችና እግረ መንገዷንም እያጫወተቻቸው ሳለች

ድንገት ከውጭ በኩል ጷ፣ ጷ፣ ጷ የሚል የሩጫ ድምፅ ከጆሮዋ ጥልቅ አለ:: ጆሮዋን አቅማ ስታዳምጥ ድምፁ እየቀረባት መጣ:: ወዲያው ደግሞ የሰው ድምፅ ተሰማት፣ ለዚያውም የጭንቅ ጩኸት! እንዲያውም የሔዋን ተስፋዬ:: «ታፈሡዬ ደረሽልኝ...!» የሚል

«ወይኔ በምትክትት!» ብላ ልትነርስ ያዘጋጀችውን እንጀራ ትሪ ላይ ጣል አድርጋ ወደ በር ሮጣ ብቅ ስትል ግቢ ውስጥ ከሔዋን ጋር ግጥምጥሞ አሉ::

«ምነው ሔዩዬ/ ምንድነው?» አለቻት ታፈሡ ክፉኛ ደንግጣ ዓይኖቿን በሔዋን ላይ እያንከራተተች::

«ታፈሡዬ አድኚኝ! አት-አበባ ልትገለኝ ነው!» አለችና ሔዋን በታፈሡ ወገብ ላይ ጥምጥም አለች:: በሩጫ ሲቃ እያስከለከች ወደ ውጭም አቀብቂ ትመለከት ጀመር::

«የታለች?» አለች ታፈሡ እሷም ወደ ውጭ በር እየተመለከተች::

«እየመጣች ነው ታፈሡዬ!» አለች ሔዋን አሁንም እየተርገበገበች::

«ምን አድርገሽ ነው?»

«አጥፍቻለሁ ታፈሡዬ! የዛሬን አድኚኝ!»

ታፈሡ ወደ ውጭ በር ብታይ ብታይ ሽዋዬ ብቅ ባለማለቷ ቀሚሷን ከሔዋን እጅ እንደ ምንም አስለቅቃ ራሷ ወደ ውጭ በር ሮጠች:: መንገድ ላይ ወጣ ብላ ግራና ቀኝ አካባቢውን እያየች ስትቃኝ ሽዋዬን ከሩቅ አየቻት:: ወደ ቤቷ ተመልሳ እየሄደች ነው! ለዚያውም በሩጫ! ልክ አመለኛ ከብት ያመለጣት እረኛ ይመስል የያዘችውን ዱላ ወደ ላይ አቁማ ሽምጥ ትሮጣለች::

ታፈሡ የሽዋዬን አድራሻ ካረጋገጠች በኋላ ነገር ግን የእሯሯጧ ሁኔታ «ሕንዴ! ምንድነው ነገሩ?» እያለች ወደ ሔዋን ገሰገሰች:: ሔዋን አስገርሟት በታፈሡ ቤት ሳሎን ውስጥ ወለል ላይ ቆማ ጭብጥ ኩርምት እያለች ታለቅሳለች::

«እሷ ወደ ቤቷ እየተመለሰች ነው ሔዩ! አይዞሽ!» እያለች ታፈሡ ተጠጋቻት::

ሔዋን የሽዋዬን ወደ ቤቷ መመለስ ዜና ስትሰማ ልቧ ረጋ ቢልም ነገር ግን ሆዷ የባሰ ባባና ስቅስቅ ብላ ታለቅስ ጀመር:: ከእንባዋ በብዛት መፍሰስ የተነሳ ፊቷ በውሃ የታጠበ መሰለ::

«አንቺ ሔዩ!» አለቻት ታፈሡ በለበሰችው ስከርፍ የሔዋንን እንባ እየጠረገች::

«እ-አቤት!» አለች ሔዋን ድምጿ እየተቆራረጠ::

«ደሞ ምን ተፈጠረ?»

«እ-አጥፍቻለሁ ታ-ታፈሡዬ!»

«እስቲ ቁጭ በይና ያጠፋሽውን ንገሪኝ!» አለችና ታፈሡ ሔዋንን ወደ ሶፋው ትጎትት ጀመር:: አባብላ አባብላ አስቀመጠቻት:: ሔዋን ግን አሁንም እንጉብሳ ማልቀሷን ቀጠለች::

«ሔዩ!»

«እ-አቤት!»

«ኧረ ምንድነው ችግሩ? ለምን ረጋ ብለሽ አትነግሪኝም?»

«ጥፋቱ የኔ ነው ታፈሡዬ!»

«እኮ ምን አረግሽ?»

«ዛሬ ከእስቻለው ጋ ነው ያደርኩት::»

«ብታድሪስ ታዲያ?»

«በቃ! አት-አበባ አውቀችብኝ:: ከእንግዲህ ከእሷ ጋር መኖር አልችልም:: ወደ እናቴ ጋ እሄዳለሁ:: ታፈሡዬ፣ ባሬውኑ አሳፍሪኝ!» አለቻት::

«ረጋ በይ ታዲያ!»

ሔዋን ግን ልትረጋጋ አልቻለችም፣ እንዲያውም ጮክ ባለና ረዘም ባለ ድምፅ «ወደ እናቴ ጋ ...!!» ስትል ጮኸች::

ታፈሡ ግራ ተጋባች:: በእርግጥ የሔዋንን ከእስቻለው ጋር ማደር ገና አሁን ከራሷ ከሔዋን አንደበት መስማቷ ነው:: በሌላ በኩል ግን ሽዋዬ ኮርስ ልትከታተል ወደ አዲስ አበባ መሄዷንና ነገር ግን የመምጫዋ ቀን ገና እንደነበር ነው የምታውቀው:: እንዴትና መቼ መጥታ የዛሬውን ግጭት ከሔዋን ጋር መፍጠር እንደቻለች ሊገባት አልቻለም:: በዚህ የተምታታ ሀሳብ ውስጥ ሆና የሔዋንን እኒኒን ለአፍታ ያህል ፀጥ ብላ ስትመለከት ቆየችና «እኔ እምልሽ ሔዩ!» አለቻት::

«አቤት!» አለቻት ሔዋን አጎንብሳ እንባዋን እየጠረገች::

«ለመሆኑ ሽዋዬ ከአዲስ አበባ መቼ መጣች?»

«እኔ አላወኩም ታፈሡዬ:: እመጣለሁ ያለችው የፊታችን ቅዳሜ ነበር:: «እስቲ እስቻለው ደሞ ይኼንን ስለሚያውቅና ዛሬ አዲስ አበባ እንደሚሄድ ነግሮኝ፣ እስቲ ዛሬ እንኳ በሽኝት ሰበብ አስተዳድሪኝ› ብሎ ሲለምነኝ እኔም እሺ አልኩት:: ትናንት ዕረቡ ምሽት ላይ ከበልሁ ጋር መጥተው ከቤት ይዘውኝ ወጡ:: በዚያው ወደ እስቻለው ቤት ሄድንና እዚያው አደርኩ:: እኔ ከቤት እስከወጣሁበት እስከ ምሽቱ አንድ ሠዓት ድረስ አት-አበባ አልመጣችም ነበር:: ዛሬ ጠዋት ወደ ቤት ስሄድ ግን በር ላይ ቆማ አገኘኋት:: ልትመታኝ ሮጣ ስትመጣብኝ ወደ ውጭ ሸሸሁ:: ተከትላ ስታባርረኝ ይኸው አንቺ ጋ መጣሁ::» አለቻት ሔዋን ከዓይኗ ተርፎ በጉንጯ ላይ የሚንቆረቆር እንባዋን እየጠረገች::

ታፈሡ በሔዋን ላይ በተፈጠረው መጥፎ አጋጣሚ ከልብ በማዘኗ ራሷን ለረጅም ጊዜ እየነቀነቀች ሔዋንን በሀዘን አስተያየት ትመለከታት ያዘች:: የእሷም ዓይኖች እንባ አቀረሩ::

አዎ! ሔዋን ተጨንቃለች:: ልክ እሷ ራሷ ለታፈሡ እንደገለፀችላት ‹አገር አማን› ብላ ጠዋት ከእስቻለው ቤት ወጥታ ወደ ቤቷ በመሄድ ከቤት ስትደርስ የገጠማት ሁኔታ ያላሰበችው ነበር:: ማታ ቆልፋው የሄደችው ቤት ተከፍቷል:: በሩ ላይ ደግሞ ሽዋዬ መቃን ተደግፋ ቆማለች:: በዚያች ሠዓት፣ በዚያች ደቂቃና ሰኮንድ መሬት ተሰንጥቃ ብትውጣት ሔዋን ምንኛ በተደሰተች ነበር::

ለሽዋዬ ባልታሰበችበት ቀን ከአዲስ አበባ መምጣት ምክንያቱ ልትካፈል የሄደችበት የኮርስ ፕሮግራም መስተጓጎሉ ነበር:: ባለፈው እሁድ ወደ አዲስ አበባ ስትጓዝ ውላ በማግስቱ ሰኞ ለስልጠና ክፍል ሪፖርት ስታደርግ ለእሷም ሆነ ለሌሎች ሰልጣኞች በዕለቱ ስልጠና እንደማይካሄድና በማግስቱ እንዲመለሱ ይነገራቸዋል:: ነገር ግን በማግስቱም የስልጠናው ጉዳይ ሳይሳካ ይቀራል::

የተሰጣቸው ምክንያት ኮርሱን እንዲሰጥ ተመድቦ የነበረው ባለሙያ በግል ችግር ምክንያት መገኘት አለመቻሉ ነበር። በዚሁ ሰበብ በሌላ ፕሮግራም ሲጠሩ እንደሚችሉ ተገልጾላቸው ሁሉም ሰልጣኞች ወደየመጡበት እንዲመለሱ ተነገራቸው ሸዋዬ በዕለተ ዕረቡ ከአዲስ አበባ ወደ ዲላ ስትጓዝ ነው የዋለችው። ነገር ግን የተሳፈረችበት መኪና ቴክኒካዊ ችግር ገጥሞት በየመንገዱ ሲፈታ ሲገጠም ውሎ ዲላ የደረሰው ከምሽቱ አንድ ሠዓት አካባቢ ነበር። ሸዋዬ መናኸሪያ ሳትደርስ መንገድ ላይ ወርዳ ስምንተኛ መንገድ ላይ በመግባት ወደ ቤቷ ስትሄድ ቤቷ ልትደርስ በግምት መቶ ሜትሮች ያህል ሲቀራት ከወይዘሮ ዘነቡ ግቢ የውጭ በር አጠገብ ሁለት ሰዎች ቆመው አየች። ትንሽ ጠጋ ስትል አስቻለውና ሔዋን መሆናቸውን አውቃ «እሃ!» በማለት በአለችበት ላይ ቀጥ ብላ ቆመች። ከትንሽ ቆይታ በኋላ ሔዋን ከግቢ ወጥታ ስትቀላቀላቸውና ሲስሟት አየች።

«እንዴ!» አለች አሁንም። እንዲያዩዋት ወደ ጨለማ ጠጋ ብላ ስትመለከታቸው ሁለቱ ወንዶች ሔዋንን ከመሀል አድርገው እሷ ወዳለችበት አቅጣጫ መራመድ ጀመሩ።

«እንዴ! እንዴት ነው ነገሩ?» አለች ሸዋዬ ለብቻዋ እየተነጋገረች። ዓይኗ ከእነሱ ላይ እንዳይነቀል ፊትለፊት እያየች ወደ ኋላዋ ትራመድ ጀመር። እነሱ ግን ቀኛቸውን ይዘው ወደ አስቻለው ቤት በሚወስደው አቅጣጫ ታጠፉ።

«ጭራሽ?» አለች ሸዋዬ አሁንም። እንደ ንዴትም ጀመራትና የያዘችውን ሻንጣ መሬት ላይ ቁጭ አደረገች። በፍጥነት ከፈተችው። አዲስ አበባ ስትሰነብት ለብርድ መከላከያ ብላ የያዘችውን ጋቢ አወጣችና ንጥልጥል አድርጋ ከእግር እስከ ራሷ ድረስ ተከናነበችው። የአገር ቤት ሰው ለመምሰል ሻንጣዋን በስከርፏ ወገቧ ላይ አዘለች። ከዚያም እነአስቻለው በሄዱበት መንገድ ላይ ገብታ ትከታተላቸው ጀመር። ሲሄዱ ስትከተላቸው፣ ሲሄዱ ስትከተላቸው በተጥታ ሦስቱም ከአስቻለው ቤት ደርሰው ገቡ።

ሸዋዬ በዚያች ሠዓት ጨሂ ጨሂ ብሏት ነበር። ግን በልሁ አለ፤ ትፈራዋለችና ዞር ብሎ የሚያንቃት መሰላት። ውስጧ ጨሰ። ተቃጠለች። ወዲያው አንድ ነገር ትዝ አላት። ሔዋን ወደ ቤቷ ስትመለስ የልቧን ማድረሻ የሚሆኑ መደብደቢያ ነገሮችን ልታዘጋጅ ወደ ቤቷ ገሰገሰች። በእሷ እምነት ሔዋን ጥቂት ቆይታ የምትመለስ መስሏት ነበር። ልክ ቤቷ እንደደረሰች የቤት መወልወያዋን ከሜፉ ላይ ቆረጠችና ዱላ ሰራች። የሚወረወሩ ነገሮችም አዘጋጀች።

ከምሽቱ ሦስት ሠዓት አለፈ። ሔዋን ግን ወይ ብቅ!! ሸዋዬ እሳት ነደደባት። በሀሳቧ በልሁ ወዲያው ወጥቶላቸው አስቻለውና ሔዋን ለእሷ ስሜት የማይመች ነገር ሲሰሩ ታያት፣ ፍቅር። ሔዋን በጣም ስትቆይ ደግሞ ጭራሽ የማደሯ ነገር ታሰባት። የምታደርገውን አጥታ እንደ መቀወስ ዓይነት ሲያደርጋት ወደ አስቻለው ቤት ብረሪ ብረሪ አላት። በእርግጥም ቤቷን ቆልፋ ወጣች። መንገዱን አየት ስታደርገው የሰው ሽታ የለም። ሄደች ወደ አስቻለው ቤት። ቀደም ሲል እዚያ በደረሰችበት ወቅት በየመስኮቱ የብርሀን ጭላጭል ታይቷት ነበር። አሁን ግን ቤቱም ግቢውም ጨለማ። ሁሉም ነገር ዝግትግት ያለ፣ ሁሉም ፀጥ ረጭ። በዚያው መጠን በአእምሮዋ ውስጥ ልዩ ድምጽ አቃጨለ፣ ለስሜት ብቻ የሚሰማ ድምፅ። አዎ በአስቻለው አልጋ ላይ የሚንኮሻኮሽ ነገር። በአገዛ-ልቦናዋ

ስትመለከተው፣ ከንፈሮች ተጋጥመው፣ ጭኖች ተወራርሰው፣ እጅና ወገብ ተሳስረው ታያት። ሸዋዬ ቱስኳን የባሰ አቶሳስላ በራስ ምታት ትኩሳት እየነደደች ምልስ ወደ ቤቷ!!

ያ ሌሊት ለሸዋዬ እንደ ሌሊት አልነበረም፣ ሊቆጠር የማይችል ረጅም ዘመን እንጂ። ልብሷ የሞላችውን ሳታወልቅ፣ መብራት ሳታጠፋ፣ ብርድልብስና አንሶላ ውስጥ ሳትገባ፣ አንዳንዴ በግንባሯ ድፍት፣ ሌላ ጊዜ በጀርባዋ ጋለል፣ እንዲሁም በጎኗ ስትገላበጥና አሥር ዓይነት ሲሰራት አደረ። በእሷ ሀሳብ ሌሊቱን ሙሉ የአስቻለውና የሔዋን ከንፈሮች ለአንዴም አይላቀቁም። አስቻለው ከሔዋን ጭኖች ውስጥ ለአንዴም አይወጣ። እጆቻቸው ከየወገባቸው ላይ ለአንዴም አይነሱ። ሁለቱ አንድ ሰው መስለው ሲታዩዋት አደሩ።

በሸዋዬ እምነት ሔዋን ማታ በጨለማ እንደሄደች ሁሉ ጠዋትም ሰው እንዳያያት ከጨለማው ቅልቅል ማልዳ የምትመጣ ነበር የመሰላት። ጥበቃዋንም ከዚያው ሠዓት ጀመረች። ነገር ግን ሔዋን ብቅ ሳትል ፀሃይ ወጣች። ከዚያም አልፎ አንድ ሰዓት። ቀጠለ፣ አንድ ሰዓት ተኩል። ከመቆም ብዛት እግሮቿ ተንቀጠቀጡ። ወገቧም ተርገደገደ። ለነገሩ በትክክል ማሰብ ተስኗት እንጂ የወይዘሮ ዘነቡ ግቢ የውጭ በር በዚያ ሠዓት ስለማይከፈት ሔዋንን መጠበቋ በከንቱ ነበር።

በግምት ለሁለት ሰዓት ሃያ ጉዳይ አካባቢ ነበር ሸዋዬ በአንዳች የስሜት አፍንጫ የሔዋንን ዱካ ያሸተተችው። ሔዋን የተዘጋ ቤት ከፍታ ደብተሮቿን ብድግ አድርጋ ወደ ትምህርት ቤት ስለ መሄድ ብቻ እያሰበች የወይዘሮ ዘነቡን ቪላ ቤት አልፍ ብላ ወደ ቤቷ ብቅ ስትል አንዳች የሚያስደነግጥ ክስተት አየች። ሸዋዬ የበር መቃን ተደግፋ ቆማለች። ከው ብላ በመደንገጧ በነበረችበት ቦታ ላይ ቀጥ ብላ በመቆም፣ «እ-እት እ-አበባ!» አለች ድምጿ ቁርጥርጥ እያለ።

የሸዋዬ ምላሽ አስፈሪና አስደንጋጭ ነበር። «አበባሽ እርግፍ ይበል አባሽ!» በማለት መዝጊያ ሥር የደበቀቻትን መጥረጊያ ብድግ አድርጋ ወደ ሔዋን ሮጠች። ሔዋን ደግሞ ወደ ውጭ። ሄደች፣ ሸመጠጠች። ሸዋዬም ተከተለች። ሔዋን ‹ሓድኑኝ› አትልም። ሸዋዬም ‹ያዙልኝ› አትልም። ብቻ መሮጥ፣ ብቻ መከተል!!

እድሜና የሰውነት አቋም ልዩነት ፈጥሮ ሊደራረሱ አልቻሉም። ሔዋን ወደፊት እየራቀች ሄደች፣ ሸዋዬ ደግሞ ወደ ኋላ ቀረች። የሔዋን መድረሻ የታፈሡ ቤት ሆነና ሸዋዬ በሩ ላይ ከደረሰች በኋላ ወደኋላዋ ተመለሰች። አሁንም በሩጫ። በዚህ ሁኔታ ላይ ሳለች ነበር ታፈሡ በሯ ላይ ቆማ ሸዋዬን ከርቀት ያየቻት።

የታፈሡና የሔዋን ውይይት ቀጠለ። ታፈሡ የሔዋን ‹ወደ እናቴ ጋ ልሂድ› የሚል ሀሳብ ከብዙ አቅጣጫ አሳሰባትና «እኔ እምልሽ ሔዬ!» አለቻት።

«አቤት!»

«ይኼ ነው በአሁኑ ሠዓት ወደ ኩብረ መንግስት ልሂድ የሚያሰኝሽ?»

«አዎ ታፈሡዬ፣ ከእንግዲህ እኔ እዚህ አገር አልቀመጥም። ከእት-አበባዎ ጋር ዳግመኛ አብሬ አልኖርም። እንደምንም ብለሽ አሳፍሪኝና ልሂድ።»

«የዘነጋሽው ነገር አለ እኮ!»

«ምንም ነገር ማስታወስ አልፈልግም ታፈሡዬ!»

«ትምህርትሽስ?»

«ብቃ ይቅር!»

«ለፍተሽ ለፍተሽ?»

«በቃ አልሆንልኝም ታፈሡዬ! ዛሬ ባይሆንልሽ ነገ እንደምንም አሳፍረሽ እንድትሸኚኝ እለምንሻለሁ»

«ለማትሪክ እኮ ተመዝግበሻል። ፈተናው የቀረው አንድ ወር ብቻ ነው። ለዚች አጭር ጊዜ ብለሽ ነው እንዴ እቋርጠሽ የምትሄጂው?»

«የመከራ ቀን ከሆነ አንዱም ቢሆን ከዓመት ይረዝማል።»

«አይደለም የኔ ቆንጆ! ይቺን አንድ ወር እኔ ጋር ሆነሽ ፈተናሽን ትወስጂለሽ። እስቻለውም ይምጣና ስለ ሁኔታው እንመካከርበታለን። አሁን ተረጋጊ።»

«ታፈሡዬ፣ እምቢ! እኔ እናቴ ጋ መሄድ እፈልጋለሁ። ከነ እንዳታሳልፊኝ። እኔ ጨንቆኛል ታፈሡዬ!» ካለች በኋላ ሒዋን እንደ አዲስ ሆዷ ባብቶ፣ እንደ አዲስ እንባ እየተናነቃት ሙክ ባለ ድምፅ «እማይዬ...!» ስትል እናቷን በርቀት ተጣራች።

የታፈሡም ሆድ ተንቦጫቦጨ። የሒዋን የውስጥ ስሜት ቁስል እስከምን ድረስ እንደቆጠቆጣት እሷንም ተሰማትና ልክ እንደ ሒዋን የእሷም ዓይኖች እንባ ያረግፉ ጀመር። ከተቀመጠችበት ሶፋ ላይ ብድግ ብላ ከሒዋን አጠገብ ሄዳ ቁጭ አለች። አንገቷን አቅፍ አደረገችና «እሺ የኔ ወርቅ፣ እሺ የኔ ቆንጆ! መሄድሽ የግድ ከሆነ ነገውኑ አሳፍሬ እሸኝሻለሁ። ምናልባት ወደ ማታ ላይ በልሁና መርዕድ ከመጡም ተመካክረን እንሸኝሻለን።» አለቻት።

ሒዋን ግን በተለይ የበልሁ ስም ሲነሳ ሰውነቷ ሽምቅቅ አለ። ፊቷን ወደ ታፈሡ መለስ አድርጋ «ታፈሡዬ፣ ይህንንማ በልሁ አትንገሪው። እንደምታውቂው እሱም እትብባን አይወዳትም። እሷም ተፈራዋለች። ታዲያ ይህንን ነገር ከሰማ በንዴት ውስጥ ይገባና እትብባን ካልገደልኩ ያለ እንደሆንስ? ችግር አይፈጠርም ታፈሡዬ? ስለዚህ አደራ ለበልሁ አትንገሪው።» ስትል ተማፀነቻት።

«እሺ የኔ ወርቅ! በቃ አልነግረውም። ባይሆን እኔና አንቺ በጉዳዩ ላይ በሰፊው እንነጋገርና ለአንቺ የተመቸሽን ሁሉ አደርጋለሁ። አሁን ዝም በይ። አታልቅሺ። እሺ የኔ ቆንጆ!» አለቻት ታፈሡ።

«እሺ» አለቻት ሒዋንም። ማልቀሰዋን ቆም አደረገችና በእስከ አሁኑ እንባዋ የረሰረሰውን ፊቷን ትጠራርግ ጀመር።

አንፃራዊ መረጋጋት ተፈጠረ። ታፈሡ ሒዋንን ትታ ከሶፋ ላይ ተነሳችና የሚበላ ነገር መሥራት ጀመረች። እንዲሁ እንዲሁ እያለ ሰዓቱም ሄደ። የታፈሡም ሥራ መግቢያ ደረሰ። የሰራችውን ምግብ ከሒዋን ጋር ቀማመሱና

«ሒዩ» አለቻት ታፈሡ።

«አቤት»

«እኔ የስራ ሰዓት ስለደረሰብኝ ልሂድ። አንቺ ደግሞ ሶፋው ላይ ጋደም በይና መንፈስሽን አረጋጊ። እሺ የኔ ቆንጆ!» አለቻት በማባበል ዓይነት።

«እሺ»

ታፈሡ ወደ ጓዳ ገባችና ትራስና ጋቢ ይዛ ተመለሰች። ትራሱን በሶፋው ላይ ከአመቻቸች በኋላ «ነይ የኔ ወርቅ» በማለት ሒዋን ወደ ትልቁ ሶፋ እንድታልፍ ጋበዘቻት። ሒዋንም ወደዚያው አልፋ ተቀመጠች።

«ጋደም በይ!»

ሒዋን በተመቻቸላት ትራስ ላይ ጋደም ስትል ታፈሡ ጋቢ ደረበችላትና ልክ እንደ ህፃን ልጅ ሽፍንፍን አድርጋት ወደ ሥራዋ ሄደች።

* * *

ከተኙ ዘጠኝ ሠዓት አካባቢ መርዕድ ከአንድ የሥራ ባልደረባው ጋር በመሆን በቀድሞው የዲላ ከተማ አውቶቡስ መናኸሪያ ፊትለፊት ጥቂት ሜትሮች ወረድ ብሎ ከሚገኘ ‹አባይ ፏፏቴ› ተብሎ በሚታወቅ ሆቴል በረንዳ ላይ ቁጭ ብለው ሻይ ይጠጣሉ። ፊታቸውን ወደ መናኸሪያው አድርገው ስለተቀመጡ የመናኸሪያው አካባቢ ወለል ብሎ ይታያቸዋል። በጨዋታቸው መሀል ዓይንና ቀልባቸውን ወደ መናኸሪያው ወርወር ሲያደርጉ በአካባቢው ለየት ያለ ሁኔታ እየተፈጠረ መሄዱን ሁለቱም በየግላቸው ያጤኑ ኖሯል፣ ሰው በርከትከት እያለ መሄዱን፣ ወንዶች ጋቢ፣ ሴቶች ደግሞ ነጠላ እየለበሱ እጀብ እጀብ እያሉ መቆማቸውን ያያሉ።

«ዛሬ ምን ችግር አለ?» ሲል የመርዕድ ጓደኛ ጠየቀ።

«እኔ እንጃ! ምናልባት ከሌላ አገር የሚመጣ አስክሬን ይኖር እንደሆን።» አለ መርዕድ ወደ መናኸሪያው እየተመለከተ።

ከትንሽ ቆይታ በኋላ ከርቀት የሚሰማ የለቅሶ ድምፅ ከጆሮአቸው ጥልቅ አለ። የድምጹ አቅጣጫ ከተቀመጡበት ሆቴል በስተጀርባ ነው። መርዕድ ከተቀመጠበት ብድግ ብሎ የለቅሶ ድምጽ ወደተሰማበት መንገድ ወጣ በማለት ቁልቁል ሲመለከት አንዲት ሴት በሌሎች በርካታ ሰዎች ታጅባ ክንፏን ዘርግታ እያለቀሰች ወደ ላይ ወደ መናኸሪያው ስትገሰግስ አያት።«ወንድሜ! ወንድሜ! እኔ አፈር ልብላ! ወንድሜ እኔ ልደፋ! ወንድሜ...!» ስትል ይሰማዋል።

«ኸረ ወደዚህ ወደ መናኸሪያው እየመጣች ነው!» ሲል መርዕድ ያየውን ሁኔታ ለጓደኛው ገለጸለት።

ሴትዮዋ ብዙም ሳትቆይ እነመርዕድ የነበሩበትን ሆቴል አልፋ ወደ መናኸሪያው ተጠጋች። በአካባቢው የነበሩ ሰዎችም እየተላቀሱ ሲቀበሏት መርዕድና ጓደኛው ተመለከቱ። «እስቲ ጠጋ ብለን እንጠይቅ!» ተባባሉና መርዕድና ጓደኛው ወደ መናኸሪያው አቀኑ። የመርዕድ ጓደኛ ወደ አንድ ትክዝ ብሎ ቆሞ የነበረ ሰው ጠጋ በማለት «ችግር አለ እንዴ የኔ ወንድም?» ሲል ጠየቀው።

«ሰው አለቀ ይላሉ።» አለው ሰውየው እዝን ባለ አነጋገር።

«ምን ሆኖ?»

«በመኪና አደጋ።»

«የት?»

«ዝዋይ የሚዳ በረሃ ላይ።» አለና «ከዚህ ከዲላ ወደ አዲስ አበባ ይሄድ የነበረ አንደኛ በራሪ አውቶቡስ ከሌላ መኪና ጋር ተጋጭቶ ነው አሉ።» አለ ጉንጩን በመዳፉ ደገፍ ዘመም በማለት።

«እንዴ!» አለ መርዕድ። ጓደኛው ዞር ብሎ መልከት ሲያደርገው የመርዕድ ፊት ልውጥውጥ ብሏል።

«የሄደ ዘመድ አለህ እንዴ?» ሲል ጠየቀው።

«አንድ ጓደኛዬ ሄዷል።»

«በአንደኛው በራሪ?»

«እሱን እንኳ አላወቅሁም፣ ጠዋት የሸኘው ሌላው ጓደኛችን ነው።» አለና መርዕድ «እንዴት ይሻለኛል?» ሲል ጠየቀ ለጊዜው ምላሽ ባይጠብቅም።

«ጠዋት የሸኘውን ጓደኛህን ጠይቀዋ!» አለው ጓደኛው።

«ለመስክ ሥራ እንደሚሄድ ማታ ነግሮኛል። አሁን ከተማ ውስጥ አይኖርም።» አለ መርዕድ። ትናንት ምሽት ላይ የአስቻለውንም የበልሁንም የወጪ ግብግቦ ጠጥቷልና በልሁ ከተማ ውስጥ እንደማይኖር ያውቃል።

አካባቢው በፍጥነት እየተለዋወጠ ሄደ። ከዲላ ከተማ አራቱም ማዕዘን ወደ መናኸሪያው ሰው ይጎርፍ ጀመር። የዚያኑ ያህል አልቃሹ በዛና ጩኸት በረከተ። ድብልቅልቁ ወጣ። አንዳንዶቹ የዘመዶቻቸውን ሰጣ ፊንታ አውቀው አስከሬን ለማምጣት የኮንትራት መኪና ፍለጋ ይሯሯጡ ጀመር። አብዛኛው ግን ከአዲስ አበባ ወደ ዲላ በሚመጣው አውቶቡስ የሚመጣውን ሰው ይጠባበቃል፣ ሁኔታውን አይቶ ወይም አውቆ ከሆነ ብሎ መረጃ ለማግኘት።

ወደ አስር ሠዓት አካባቢ ድንገት የአውቶብስ ጡሩምባ ከሩቅ ተሰማ። ልክ 'አልቅሱ' የሚል ፊሽካ የተነፋ ይመስል ያ ሁሉ ሰው በአንዴ ጮኸ። እሪታና ኡኡታው ቀለጠ። በዚያ አላበቃም፣ ወደ አውቶብሱ መምጫ መንገድ ሩጫና እሽቅድምድም ተጀመረ። አውቶብሱ ከታች ከአዲስ አበባ መግቢያ በሆነው አስፋልት መንገድ ላይ ገስግሶ ወደ መናኸሪያ መታጠፊያ በሆነችው አደባባይ ላይ ሲደርስ በህዝብ ተከበበ። መሄጃ አጥቶ ቆመ። በተሳፋሪና በጠባቂው ህዝብ መካከል መጯጯህ ተጀመረ። መኪና ውስጥ ያለው አንገቱን በመስኮት እያወጣ «ምነው? ምንድነው?» ይላል። ከውጭ ያለው ደግሞ «እንዴት ነው? ሰው ተርፏል ወይ!... ወዘተ» እያለ ይጮሀል። መስማማትም መግባባትም አልተቻለም። እንደ ምንም መግባባት ሲጀመር ደግሞ ለካ መኪኖቹ ተሳልፈው ኖሮ ከአዲስ አበባ የመጣው መንገደኛ ስለ አደጋው ምንም አልሰማም። እንደውም ከአውቶቡሱ ላይ እየወረደ ቀድሞ ከነበረው መረጃ ፈላጊ ሕዝብ ጋር እየተቀላቀለ አብሮ ወሰሌ ይል ጀመር። ቀጣዩ አማራጭ በእለታ ወንዶ በኩል የሚመጣውን ሁለተኛ በራሪ መጠበቅ ብቻ ሆነ።

መርዕድ በዚያ ጭንቀት ውስጥ ሆኖ መቆየት አልቻለም። ይህን ሁኔታ ለታፈሡ መንገር እንዳለበት አሰበ። ጊዜ አላጠፋም፣ ወዲያው ወደ ቤቷ በረረ። በሩጫው ወቅት ከቤቷ ስለ መድረሱ እንጂ ታፈሡ ትኑር ወይም አትኑር ምንም የሚያስበው ነገር አልነበረም። ብቻ ሲደርስ ምን ብሎ እንደሚነግራት ያስባል። ከታፈሡ ቤት ሲደርስ ልክ አሥር ሠዓት ሆኗል። ያገኛት ግን ታፈሡን ሳይሆን ያላሰባትን ሔዋንን ነው።

«ታፈሡ የለችም እንዴ?» ሲል እያለከለከ ሔዋንን ጠየቃት።

«ምነው?» አለችው ሔዋን ከሶፋ ላይ ብድግ ብላ። የመርዕድ ሁኔታ አስደንግጧታል። ከማለክለኩም በተጨማሪ ፊቱን አልቦታል። ዓይኑም ፈጥጧል።

«እይ...ብቻ ... ደህና ነኝ።» አለና መርዕድ ሶፋው ላይ ቁጭ አለ።

«አትመስለኝም መርዕድ!»

«ግን አንቺ በአሁኑ ሠዓት እንዴት እዚህ ልትገኚ ቻልሽ?» ሲል ጠየቃት መርዕድ እሱም በበኩሉ የሔዋንን ሁኔታ ሰሰል እያደረገ። ሲያያት ሁኔታዋ ሁሉ አላማረውም። ስታለቅስ እንደ ዋለች ሁሉ ዓይኖቿ ቀልተው እንዲያውም ያበጡ ይመስላሉ። ከፊቷም ላይ ደስታ አይነበብም።! 'ይቺ ልጅ ስለ አስቻለው ምን ሰምታ ይሆን?' እያለ በልቡ ያስብ ጀመር።

«ድንገት መጥቼ ነው።» አለችው ሔዋን። ለጊዜው በዚያ ሠዓት እዚያ ቤት የተገኘችበትን ሁኔታ መዘርዘር አልፈለገችም።

«ታፈሡ ስራ ሄዳ ነው?» ሲል ጠየቃት።

«አዎ።» አለችና ሔዋን «ግን ደህና አትመስለኝም መርዕድ!» ስትል ሁኔታውን ሁሉ በዓይኗ እየሰለለች ጠየቀችው።

መርዕድም ልክ እንደ ሔዋን የሆዱን ምስጢር መዘርዘር አልፈለገም፤ የቻለውን ያህል ራሱን እያረጋጋ «ደህና ነኝ ስልሽ!» አለና ዝምብሎ ጣሪያ ጣሪያ ይመለከት ጀመር። በመሀላቸው ፀጥታ ሰፈነ። በየሆዳቸው ግን የየግላቸውን ጉዳይ ያሰላስላሉ።

በመሀል ከውጭ በኩል የሰው ኮቴ ተሰማቸው። ሁለቱም ጆሮአቸውን አቁመው ሲያዳምጡ ኮቴው እየቀረባቸው መጣ። አሁንም እርስ በእርስ እየተያዩ ሲያዳምጡ ታፈሡ ከቤት ውስጥ ዘው ብላ ገባች። የቸኮለችና የተጣደፈች ትመስላለች። ያ ብርቱካን የመሰለ ቀይ ፊቷ የባሰ ደም መስሏል። ዓይኗም ፈጧል። ትንፋሿ ቁርጥ ቁርጥ ይላል። በዚሁ ስሜት ውስጥ ሆና ሳታስበው መርዕድን በዚያ ሠዓት እዚያ ቤት ውስጥ ማግኘቷ የበለጠ አስደነገጣትና፡-

«አንተ መርዕድ!» አለችው ጮክ ባለ ድምጽ።

«ወይ» መርዕድም ደንግጦ ብድግ አለ።

«ምንድነው ከተማ ውስጥ የሚወራው?»

«አደጋ ደረሰ ይላሉ። አንቺም ሰማሽ እንዴ?» አላት በድንጋጤ አስተያየት ትኩር ብሎ እያያት።

«የተለየ ነገር ሰምተሃል?»

«ምንም!»

ታፈሡ ፈጠን ፈጠን ባለ ሁኔታ ቦርሳዋንና የማስተማሪያ ቁሳቁሶቿን ሳሎን ውስጥ በሚገኝ ብፌ ላይ ውርውር እያደረገች «ለጉድ ያውጣን ብቻ!» ብላ ወደ ጓዳ ገባች።

«ምንድነው መርዕድ?» አለችው ሔዋን እንደገና ድንግጥ ብላ።

«አደጋ ደርሷል ነው የሚሉት። ግን በግልጽ የተረጋገጠ ነገር የለም።» ብሎ በሀፍረትም በፍርሀትም ውጭ ውጭ ማየት ሲጀመር ሔዋን ከአስቻለው የተያያዘ ችግር መሆኑ ገብቷት የበለጠ በመደንገጧ፡-

«አንቺ ታፈሡዬ!» ስትል ወደ ጓዳ ተጣራች።

«እስቲ እኔና መርዕድ ወደ ከተማ እንሂድና ሁኔታውን አጣርተን እንመጣለን።» አለቻት ታፈሡ እዚያው ጓዳ ውስጥ ሆኗ ነጠላ እየለበሰች።

«እኔስ ታፈሡዬ?» ሔዋን ግራ ገባትና ዓይኖቿ ወደ መርዕድም ወ... ታፈሡም ክርትት ክርትት ይሉ ጀመር::

«እህትሽ ውጭ ያገኘችሽ እንደሆን ደሞ ችግር ልፍጠር ... ልናደድ እችላለሁ:: አንቺ እዚሁ ቆይን::» አለቻት ታፈሡ ምናልባት ... ነገር አስደንጋጭ ሁኔታ ካስከተለ ብላ በመፍራት:: ቀጠል አደረገችና ... መርዕድ!» ብላ ከቤት ወጣች:: መርዕድ ተከተላት:: ሔዋን ግን ጭንቅ ... ላይ ኩርምት ብላ ተቀመጠች:: ሆዷ ፈራ::

ታፈሡና መርዕድ መናኸሪያ ሲደርሱ ከምሽቱ አሥራ አንድ ሰዓት እየተጠጋ ነው:: ሁኔታው ግን የበለጠ ተባብሷል:: እንዲያውም ሁለተኛው ... አውቶብስ ገብቶ ነገር ግን አሁንም ተሳልፈው ኖራልና የተጠበቀው መረጃ ባለመገ... ቱ ህዝቡ ግራ ተጋብቶ ወለሌ ይላል:: ይተረማመሳል:: ይላቀሳል::

ታፈሡ በሕዝቡ መሀል ከወዲያ ወዲህ እየተሯሯጠች «እህ እንዴት ነው? ምን ሰማችሁ? እንዴት ሰማችሁ! ሰው ተርፎ ይሆን?» በማለት ስትርበተበ... አኳኋኗን ይመለከት የነበረ አንድ ቀደም ብሎ ያውቃት የነበረ ሰው እጇን ያ... አደረገና፣ «ወይዘሮ ታፈሡ፣ እንቺም ሰው ሸኝተሽ ኖሯል?» ሲል ጠየቃት።

«አዎ ጋሽ ዓለሙ፣ ወንድሜን::» አለችው እጆቿን እያርገበገበች::

«እግዜር ይጠብቅልሽ እንጂ የጉዳቱ መጠን እንኳ በጣም አሳሳቢ ሳይሆን አይቀርም:: ይኸው እስከ አሁን እንኳ የሰባት ሰው መርዶ ደረሰ::»

ታፈሡ ወዲያው እጆቿን ወደ ላይ ዘርግታ «ወየው! ወየው! ወየው! ...» እያለች ልክ መርዶ የደረሳት ያህል ለይቶላት ታለቅስ ጀመር:: እንባዋ በጉንጯ ላይ ቦይ ሰርቶ ይንቆረቆር ጀመር:: ጭንቅ ጥብብ፣ ብክን ክርትት ስትል የሚያያት ሁሉ ልክ እንደ እሷው እንባውን ያዘራው ጀመር:: በከተማው ውስጥ ታዋቂ እንደ መሆኗ ሴት ወንዱ ዙሪያዋን እየከበበ ሊያጽናናት ቢሞክርም እሷ ግን እንጀቷ እየተንሰፈሰፈ አልረጋጋ ብላ አስቸገረች::

ጀምበር ጠልቃ ለዓይን መያዝ ጀምሯል:: ቀሪው የዚያ ቦታ ትርዒት ስለ ነገው አስከሬን ፍለጋ ጉዞ መነጋገር ብቻ ሆነ:: አንዱ ከሌላው ጋር ይመካከር ጀመር:: ታፈሡና መርዕድም ሲሄዱ በጋራ ወሰኑ::

ታፈሡና መርዕድ ወደ መናኸሪያ ከሄዱበት ሰዓት ጀምሮ ሔዋን ቢያንስ አሥር ጊዜ ከቤት እደጅ ወጣ ገባ ስትል ቆይታለች:: ሲጋት እያቁነጠነጣት ከተቀመጠችበት ይልቅ ስትቆም ስትራመድ ያሳለፈችው ጊዜ ይበልጣል:: መርዶ ይሁን ብሥራት የሚመጣላትን አታውቀውም:: እነሱ ደግሞ ለእሷ ምንም ዓይነት ፍንጭ ሳለመስጠት እየተዘጋጁ ናቸው:: ሁለቱም ወደ ቤት እየተመለሱ በእሉበት ሰዓት ታፈሡ ያለቀሰችበትን ዓይኗን ጭምቅ፣ ፊቷን ጥርግርግ አረገች:: እንዲሁም ስለ ሁለት ሠዓት ዜና አለማግም ተመካከሩ:: በታፈሡ ቤት ሬዲዮ ላይከፈት፣ በዚያ ምትክ መርዕድ ቴፕ ሊከፍት፣ ታፈሡ ወደ ጎረቤት ሄዳ ዜና ሰምታ ልትመለስ:: የጠዋቱን ጉዞ በተመለከተ ታፈሡ ከባለቤቷ መልዕክት ተልኮላት ያን ልትቀበል ወደ አዲስ አበባ ልትሄድ መሆኗንና መርዕድ ጠዋት ይሸኛት ዘንድ እሷው ቤት ሊያድር ሆኖ የሔዋንን ጥርጣሬ ለመቀነስ ተዘጋጅተዋል::

ከምሽቱ አንድ ሠዓት ላይ ታፈሡና መርዕድ ከቤት ሲደርሱ ሔዋን በር ላይ ቆማ ስትጠብቃቸው አዩዋት:: ታፈሡ የመጀመሪያውን ሔዋንን ማረጋጊያ ዘዴ ወዲያው ፈጠረችና «ሔዩ! ቡና አላፈላችሁ ይሆን? ብታይ የረባ ወሬ ላይገኝ ነገር

ወዲያ ወዲህ ስንከራተት ስለ ቆየን ራሴን እንዴት ቀስፎ ይዞኛል መሰለሽ» አለቻት ወደ በር እየተራመደች:: መርዕድ እንንብሶ ከኋላዋ ይከተላል::

«ምንም የለም?» አለች ሔዋን የበሩን መቃን ደገፍ ብላ እንደቆመች::

«ወሬማ ሞልቷል፣ ግን እርስ በእርሱ ይጋጫል!»

«ምን ምን ይባላል ታፈሡዬ?»

«ጭራሽ የትኛው መኪና እንደተጋጨ እንኳ አልታወቀም::»

ሦስቱም ወደ ቤት ገቡ:: ሔዋንና መርዕድ ሶፋ ላይ ሲቀመጡ ታፈሡ ወደ ጓዳ ገባች:: ሠራተኛዋ የእራት ወጥ እያሰራች ነበርና «ቶሎ በይና ቡና አፍይልኝ::» አለቻት ድምጿ ወደ ሳሎን እንዲሰማ አድርጋ ጮክ በማለት:: ልብሷን ቀያይራ ወደ ሳሎን እየተመለሰች ሳለች መርዕድን «አዲስ አበባ የምትልከኝ ነገር ካለ አሁኑ ተዘጋጅ መርዕድ!» እያለችው ወደ ሶፋ ሄዳ ከሔዋን ጎን ተቀመጠች::

«መቼ ልትሄጂ?» አለቻት ሔዋን አዲስ ወሬ ሆኖባት በርገግ ብላ::

«ባለቤቴ ከርሞ ከርሞ ከውጭ ሀገር የሆነ ነገር ሳይልክ አይቀርም፣ አዲስ አበባ መጥተሽ ውሰጂ ብለው ዛሬ በትምህርት ቤት በኩል ስልክ ደወሉልኝ::»

«እና ነገ ልትሄጂ?» አለች ሔዋን አሁንም ጭንቅ ጥብብ እያላት::

«አዎ፣ ግን በጠዋት እንድትቀሰቅሱኝ:: መርዕድም እንዲሸኝኝ ብዬ እዚሁ ላሳድረው ነው ይገፍው የመጣሁት::» አለቻት ወደ መርዕድ እየት እያደረገች::

«የኔስ ነገር ታፈሡዬ?»

«የአስቻለው ቁርጥ ሳይታወቅ ትሄጃለሽ እንዴ?» አለችና ታፈሡ «እኔም እኮ ነገ ሄጄ ከነገ ወዲያ እመጣለሁ:: እስከዚያው እዚሁ እኔ ቤት ሆነሽ ጠብቂኝ::» አለቻት::

ሔዋን ነገሮች ሁሉ ተምታቱባት:: ቀደም ሲል ያየችባቸው አስደንጋጭ ሁኔታና የአሁኑ እርጋታቸው ፈጽሞ ሊጣጣምላት አልቻለም:: ጭራሽ የአስቻለውም ነገር ማንሳት የነገር ደባል መፍጠር ሊመስልባት እንደሚችል እስከ መስጋት ደረሰች:: ግን ደግሞ ሆድ ሆዷን በላትና «በዚያው ስለ አደጋውም ትሰሚያለሽ» ስትል ታፈሡን ጠየቀቻት::

«የሆነ ነገር ካለማ ማየቴም አይቀርም::» አለችና ታፈሡ በተለይ ወደ መርዕድ እየት እያደረገች:: «ግን እንደው ወሬው ሁሉ የማይጨበጥ ሆነና ግራ ሊገባን እንጂ!» አለች::

«ሰው ደሞ ዝምብሎ ማዳነት ይወዳል::» አለ መርዕድም ጣሪያ ጣሪያ እያየ:: የመንተ አፍረቱን ወዲያው ብድግ አለና ወደ ብፌው በመሄድ ሙዚቃ ከፈተ:: «ሲሌስህ ማን አለ እደጅህ - ኪስህ ነው የቅርብ ወዳጅ» የሚለው ዜማ መሰማት ጀመረ::

እራት በልተው ሲጨርሱ ሁለት ሠዓት ሊሆን ተቃርቧል:: የታፈሡ ሠራተኛ ቡና እያፈላች ሳለች ታፈሡ በጉጉት የምትጠብቀው የዜና ሠዓት ደረሰና «መጣሁ» ብላ ከቤት ውልቅ አለች:: ከጎረቤቶቿ ቤት ስትደርስ ሬዲዮ ተከፍቶ የዜና ንባብ ተጀምሯል:: ታፈሡ በዚያ ቤት የተከበረች እንግዳ ናትና ከቤት ስትገባ ቤተሰቡ በሙሉ ተነስቶ ተቀበላት:: ከሰላምታ በኋላ ሬዲዮው ሥር ቁጭ አለች:: ዜና ንባቡ ቀጠለ:: ዋና ዋና ዜናዎች ከአለቁ በኋላ «በመጨረሻም» አለ ዜና አንባቢው ጋዜጠኛ::

«ሣሪ ከዲላ ወደ አዲስ አበባ ይጓዝ የነበረ የሕዝብ ማመላለሻ አውቶቡስ ከሞጆ ወደ ሻሸመኔ ይጓዝ ከነበረ መለስተኛ የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ጋር ተጋጭቶ በደረሰ አደጋ በተገኙ ሠላሣ ሁለት ሰዎች ሲሞቱ አርባ ስምንት ተሳፋሪዎች ከባድና ቀላል ጉዳት ደርሶባቸው በናዝሬት ሀይለ ማርያም ማሞ ሆስፒታል የህክምና እርዳታ እየተደረገላቸው መሆኑን የዝዋይ ከተማ ትራፊክ ፖሊስ ጽህፈት ቤት ገለፀ። ጽፈህት ቤቱ እንዳለው—» ብሎ ሳይጨርስ ታፈሡ የገን ቤት በጩኸት አደበላለቀችው።

«እየየ እኔ... እየየ እኔ... እየየ እኔ...!» እያለች በወለሉ ላይ ድፍት አለች።

ከዜናው ይልቅ በታፈሡ ሁኔታ የደነገጠው የዚያ ቤት ቤተሰብ በመደ ተረባርቦ ከተደፋችበት ቀና እድርጎ አስቀመጣት። «ምነው? ምነው?...» እያለ ሁሉም ሰው በማከታተል። ታፈሡ ምላሽ መስጠት የሚያስችል ፋታ አላገኘችም፤ ስቅስቅ ብላ ታለቅስ ጀመር። «እስቹ አርፈኸዋል! ተገላግለሃል ወንድሜ! የኔ ግልቱ! የኔ ብስጩ! ወይኔ ! ወይኔ ! ወይኔ!!» አለች በማከታተል።

«ምነው ወይዘሮ ታፈሡ ገና በግምት?» አሏት የቤቱ አባወራ ቀድም ብለው። «ምንሽ ነው ወይዘሮ ታፈሡ?» ሲሉ የቤቱ እማወራ ቀጠሉ።

ታፈሡ ግን ወደ ዝርዝር መግባት አልቻለችም። «ተዉኝ፣ ተዉኝ ተዉኝ፣ በቃ ሌላ ሰው አይስማብኝ!» አለችና «እደራ ጎረቤቶቼ! ነገ እኔ እዚህ አልውልም፤ ወደ ናዝሬት እሄዳለሁ። ግን እዚህ እኔ ቤት ውስጥ ይኸን ጉድ መስማት የሌለባት ልጅ አለችና አደራ! የአሁኑን አኳኋኔን ለሠራተኛዬ እንኳ እንዳትነግሩብኝ» አለቻቸውና እያለቀሰች ተሰናብታቸው ወደ ቤቷ ተመለሰች።

ቡናው ፈልቷል፤ ተቀዳና መጠጣት ተጀመረ። ለታፈሡ ግን ቡና ይሁን ኮሶ ሳይታወቃት ትኩሱን አቦል ላፍ አደረገችና የጠዋት መንገደኛነቷን ሰበብ አድርጋ «ሁለተኛው ይቅር። መንገደኛ ስለሆንኩ እንተኛ።» አለቻቸው ቶሎ ተኝታ መብራት በማጥፋት ስሜቷን ጨለማ ውስጥ ለመደበቅ ቸኩላ።

ማንም የተቃወመ የለም። የቡና ዕቃ ተነሳሳ። ሌላውም ዕቃ ተስተረ። ቤት ተጠራረገና ሁሉም ተኙ። መብራትም ጠፋ። ግን ግን ሁሉም ደፈጡ እንጂ አልተኙም። በተለይ ታፈሡ ከሰላሳ ሁለት ሟቾች መሀል የእስቻለውን አስከሬን በመፈለግ በሀሳብ ትለፋለች። በጨለማ ውስጥ ታነባለች።

ከሌሊቱ ልክ ስድስት ሰዓት ላይ የታፈሡ ቤት በር ተንኳኳ። ማንም ተኝቶ እንዳልነበረ በዚህ ጊዜ ታወቀ። ሁሉም እየበረገገ «ማነው? ማነው? ማነው?» አሉ በአንድ ላይ። በተለይ ታፈሡ ከአልጋዋ ተስፈንጥራ በመነሳት ከበሩ አጠገብ ስትደርስ ማንም አልቀደማትም። ሶፋ ላይ ተኝቶ የነበረው መርዕድ እንኳ ገና ይርበተበታል።

«ማነው?» አለች ታፈሡ በሩ ሥር ከውስጥ በኩል ቆማ።

« በልሁ ነኝ ታፈሥ!»

«በልሁ! በልሁ!» አሉ በተለይ ታፈሡና ሔዋን በተከታታይ። በሩ ሲከፈት በልሁ ሦስት ሰው ተሰልፎ አየ፤ ታፈሡ ሔዋን እንዲሁም መርዕድ።

«ምን ሰበሰባችሁ?» ሲል ጠየቀ በልሁ ወገቡን በሁለቱ እጆቹ ደገፍ አድርጎ ዓይኑን በሁሉም ላይ እየማተረ።

«እስቲ መጀመሪያ ግባ!» አለችና ታፈሡ በሩን ለቀቅ አረገችለት።

እራቱም ሶፋ ላይ ቁጭ እሉና ተፋጠጡ። ሦስቱም በልሁን፣ እሱ ደግሞ ሦስቱንም ተራ በተራ ያያቸው ጀመር። ግን ተድሞ ነገር ይጀምር፣ ተፈራሩ፣ እንዱ ከሌላው መርዶ ይጠብቃል። ቆየት ብሎ ግን በልሁ የገዱን ፀጥታውን ሰበረ።

«የሰማችሁት ነገር አለ?» ሲል ጠየቀ በመደዳ።

«ምንም በልሁ! ግን የመኪና አደጋ ደረሰ እየተባለ ይወራል።» እለችውና «አንተስ በልሁ?» ስትልም ጠየቀችው።

«እኔም የሰማሁት አደጋ ስለ መድረሱ ብቻ ነው።» አላትና መሬት መሬት ያይ ጀመር። መሬቱንም በእግሩ መታ መታ አደረገው።

«እንዴት ሰማህ ግን?» ሲል መርዕድ ጠየቀው።

«እሰማማሜማ ...» ብሎ በልሁ ወደ ኮርኒስ በማንጋጠጥ የእሰማመን ሁኔታ በዓይነ ህሊናው እያየ ያስታውስ ጀመር።

ለሦስት ሰዓት ሩብ ጉዳይ አካባቢ ነበር። ፍስሀ ፕትሮ ተብላ በምትጠራው ከተማ በአንድ ቡና ቤት ውስጥ ከአንድ ሰው ጋር ባልኪ ተደግፈው ቢራ ይጠጣሉ። ድንገት አንድ ሌላ ሰው መጥቶ ይቀላቀላቸዋል። ያ ሰውዬ ለካ ዲላ እምሽቶ የዲላን እመሻሽ አይቶ ኖሯልና ለበልሁና አብሮት ለነበረው ሰውዬ ሁሉንም ነገር ይነግራቸዋል! የተጋጨው አንደኛ በራሪው አውቶብስ መሆኑን ጭምር።

«እ!» ይላል በልሁ በድንጋጤ።

«ሰው ሸኝተሃል?» ይለዋል ያ መጀመሪያ አብሮት የነበረ ሰውዬ።

«ወንድሜን?»

«ታዲያ ተረጋጋ እንጂ!»

በልሁ ራሱን ይዞ «ኡ-ኡ-ኡ-ኡ ...!» ይላል።

«እስቲ ቆይ ረጋ በል፤ ሦስት ሰዓት ስለሆነ ዜና እንስማ!» ብሎ ሰውየው ቴፑን አዞግቶ ራዲዮ ያስከፍታል። ዜናው ይሰማል። መልዕክቱ ደግሞ ያ ታፈሡም የሰማችው።

በልሁ እንደ እብደት እንደ ስካር ያደርገዋል። ‹ኡ ኡ መኪና ፈልጉልኝ› ብሎ ያስቸግራል። እደርና ጠዋት ሂድ ቢባል እንኳ እምቢ!! ከሀገረ ማርያም ወደ ዲላ አትጣዉ የሚጓዝ መኪና ተጠብቆ በአሳር በመከራ አንድ የጭነት መኪና ይገኛል። በብርቱ ልመና ይሳፈራል። ተጉዞ ተጉዞ ልክ ከምሽቱ አምስት ሰዓት ላይ ዲላ ይደርሳል። ዲላ እንደ ደረሰ የከተማው ሁኔታ ያስገርማል። ነዋሪው ከወዲያ ወዲህ ይሯሯጣል። በርካታ ድንኳን በየቦታው ተተክሏል። ጩኸትና ጫጫታ በርክቷል። ለቅሶውም እንዲሁ። በቀጥታ ወደ ታፈሡ ቤት መሄድ አልፈለገም። ጠዋት እስቻለውን ሲሸኝ ያቺ እስቻለው አጠገብ ተቀምጣ የነበረችው ጠይሟ ልጃገረድ በአባቷ ስትሸኝ አይቷል። አባቷ ደግሞ የእነሱ መሥሪያ ቤት ዘበኛ ነው። በልሁ ቤቱን ያውቀዋልና የእስቻለውን ዕጣ ፈንታ በሷ ሁኔታ ለመገመት ወደዚያ ይሄዳል። ከቤቱ ሲደርስ ከርቀት ለቅሶ ይሰማል። ሲጠጋ ድንኳን ተጥሏል። በልሁ ተስፋ በቆረጠ ሁኔታ ወደ ውስጥ ገብቶ የልጅቷን አባት ፍለጋ ይጀምራል። ግን ደግሞ ያጣዋል። ‹የት ሄደ?› ብሎ ሲጠይቅ የልጁን አስከሬን ሊያመጣ ወደ ናዝሬት ሃይለ ማርያም ማሞ ሆስፒታል መሄዱ ይነገረዋል። በልሁ ስለ እስቻለው እዚያው እርሙን ያወጣል።

የአስቻለውን መርዶ እንታፈሡ ይስሙ አይስሙ እያውቅም:: ነገር ግን ‹ሕልሰሙ ከሆነ› ብሎ ያለ ሠዓት ላያስለቅሳቸው ስሜቱን ታገለ:: ግን ደግሞ ሆዱ አልችል አለ:: በአንድ በኩል ለአስቻለው እያለቀሰ ከዓይኑ ላይ እንባው ይንቀረቀራል:: በሌላ በኩል የእንታፈሡ ሁኔታ አስጨንቀው:: ‹ሰምተው ከሆነ ልሂድና አብሬ ላልቅስ:: አልሰሙ ከሆነ እንግዲህ የሆነ ሆኗልና ልቤን አደንድኜ ስሜቴን ቀጥ አድርጌ ከእነሱ ጋር አብሬ ልጨነቅ::› በማለት ጨክኖ ወደ ታፈሡ ቤት ያመራል:: ቤት ሲደርስ ሁሉም ነገር ፀጥ ረጭ ያለ:: አሁንም ልቡን በትግል አደንድኖ ነበር የታፈሡን ቤት በር ያንኳኳውና የተከፈተለት::

በልሁ ከሀሳቡ መለስ አለና «ግን ግን አሁን ምን አስባችኋል?» ሲል ጠየቃቸው ሁሉንም እየተመለከተ::

«እኔና መርዕድ ነገ ወደ ናዝሬት ልንሄድ ነው::» አለችው ታፈሡ::

«ታፈሥዬ! ምን እያልሽ ነው? ለ– ለካ የአስቻለውን አስከሬን ልታመጪ ኖሯል እንዴ አዲስ አበባ እሄዳለሁ ብለሽ የነበረው?» አለችና ሒዋን ልክ እንደ ልጅነቷ ክንዷን በግንባሯ ላይ አስደግፋ «ይ-ይ-ይ-ይ...» በማለት ማልቀስ ጀመረች::

«ሒዩ ምን ነካሽ?» አለች ታፈሡ እፍር ድንግጥ ብላ:: ለካ ቀደም ሲል ሒዋንን ለማረጋጋት ስትል የዋሸችውን ረስታዋለች::

«ተይ እንጂ አንቺ!» ሲል በልሁም ተቆጣት::

ሒዋን ግን አጎንብሳ ለትሶዋን ቀጠለች:: ከትንሽ ቆይታ በኋላ በበልሁ ቁጣና በታፈሡ ማባበል ብዛት ሒዋን በረድ ስትል በልሁ ንግግር ጀመረ::

«እኔ ብሔድ ይሻላል ታፈሥ! እናንተ ቅሩ:: ማን ያውቃል ወይ ክፉ ነገር ይኖርና ዝግጅት ሊያስፈልግ ይችላል::» ብሎ ሳያስበው እንባው በጉንጮቹ ላይ ኮለል አለ::

ይህ የበልሁ ሁኔታ በተለይ ለሒዋን የመርዶ ያህል ነበር:: ወዲያው «በቃ! አስቻለው ሞቷል!» አለችና ከታፈሡ ጭን ላይ ድፍት ብላ ምርር ብላ አለቀሰች:: ከሁሉም ዓይን እንባ ይንቆረቆር ጀመር::

* * *

በማግስቱ ጠዋት በመድ ወዳጁን ሞት የነጠቀው፣ የቆሰለበትና ገና የሆነውን ነገር በውል ያላወቀ የዲላ ነዋሪ ሁሉ ማልዶ ተነሳ:: ማልዶ ወደ ሁሪያ ባሉ መዳረሻዎች ይሰሩ የነበሩ በርካታ ተሽከርካሪዎች ሁሉ ስዕለቱ አስቸኳይ ጉዞ ተመድበዋል:: መሄድ የፈለገ ሁሉ ተሳፍሯል:: ሽንቱ በለትሶ የተደበላለቀ ነበር:: በልሁም አንዱ ተጓዥ ነበርና በታፈሡ በሒዋንና በመርዕድ እየየ እና ጨኸት ተሸኝ::

ጉዞው ከወትሮው ፍፁም የተለየ ነበር:: ሁሉም አዘንተኛ በመሆኑ የተኳረፈ ይመስል ፀጥ ረጭ ባለ ሁኔታ ይጓዛል:: አብዛኛው ሰው ጋቢና ነጠላ እንዲሁም ጥቁር ልብስ ለብሷል:: የፍተሻ ኬላዎችም ረግበዋል:: በየመኪናው ውስጥ ገብ ብለው ወጣ ከማለት ውጭ ተጓዡን ከመኪና ላይ አስወርደው ሁሉን ነገር

በመበርበር ያጠፉት ጊዜ አልነበረም:: ሾፌሮችም የጫኑትን ሕዝብ የውስጥ ስሜት የውቱ ነበርና ለከሰል ግኝ የትም ቦታ አልቆሙም:: እየተከታተሉ አንዳንዴም እየተሽቀዳደሙ በመብረር ከአረፋዱ አራት ሠዓት ተኩል ላይ ከዚያ አደጋ ከደረሰበት ቦታ ደረሱ፤ ከዝዋይ ከተማ በስተደቡብ በአሥራ አምስት ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ::

ያ ቦታ ለአየው ሁሉ ይሰቀጥጣል:: ወጭ ወራጅ ሁሉ ከሚጓዝበት መኪና ላይ እየወረደ ያለቅስበታል:: የተጋጩት መኪኖች ራሳቸው እንደ ሰው ያሳዝናሉ:: ከሞጆ ወደ ሻሸመኔ ስትበር የነበረችው ሲኖትራክ ለዓመታት ስትረገጥ የኖረች ጣሳ መስላ ተጨራምታለች:: ሁሉም ወንበሮቿ ሜዳ ላይ እንደ ቆሎ ተበትነዋል:: ከዲላ ወደ አዲስ አበባ ይሄድ የነበረው አውቶቡስ ደግሞ ፊትለፊቱ ተቦድሶ ከግራ በኩል ያለው ጎኑ እስከ ኋላ ድረስ ከውጭ ወደ ውስጥ ተጠርምሷል:: ከሲኖትራኳ በአጠቃላይ፣ እንዲሁም በአውቶቡሱ ግራ በኩል ከተቀመጠ ተሳፋሪ መሀል ሰው ይተርፋል ብሎ ለመገመት እጅግ ያስቸግራል::

መኪኖቹን ተወት አድርጎ የተጋጩበትን አካባቢ መሬት ሲያዩት ደግሞ የባሰ አንጀት ያላውሳል:: የአደጋ ሰለባዎች ደም በይ ስርቶ ተንኳሎበታል:: ከፈረሱ ጭንቅላቶች የተበተነ አንጎል በያለበት ተረጭቶ ዝንቦች ሰፍረውበታል:: የተለያየ ትርጃ፣ ቀለምና መጠን ያላቸው የወንዶችም የሴቶችም ጫማዎች ሜዳው ላይ ተበታትነዋል:: ደም የተጠረገባቸው ጨርቆችና ስስ ወረቀቶች በየቦታው ተልከስክሰዋል:: በዚያ ላይ ያ የዲላ ተሳፋሪ ሁሉ ከቦታው ደርሶ ከየመኪናው እየወረደ እንባ ሲራጭበት ያ ቦታ የባሰውኑ መዓት ወረደበት::

በልሁ ትናንት ጠዋት አስቻለውን ሲሸኝ የተቀመጠበትን ቦታ አይቷልና ከመኪና እንደ ወረደ በቀጥታ በፊት በር በኩል ወደ አውቶቡሱ ሮጠ:: በዚያ ቦታ ላይ ያየው ሁኔታ መሬት ላይ ካለው የባሰ ነው፤ ደም ተጋግሮበታል:: የሞተሩ ክዳን ወደ ኋላ ተጨራምቶ ወደ ወንበሩ መደገፊያ በመጠጋቱ ከዚያ ውስጥ ሰው ከነነፍሱ ሊወጣ ይችላል ብሎ መገመት ያስቸግራል:: በልሁ በሁለት እጆቹ ራሱን ይዞ በለቅሶ ሲንሰቀሰቅ ከቆየ በኋላ ድንገት የአስቻለውን የእካል ቁራጭ የሚያገኝ መስሎት ጎንበስ ብሎ በተጨራመተው የሞተር ክዳን ሥር ሲመለከት የአስቻለውን የቀኝ እግር ቢጫ ጫማ አየ::

ድምጹን ከፍ አድርጎ «ወየው ወየው..... ወየው ወየው...!» ካለ በኋላ በመኪናው በር በኩል አንገቱን ወጣ አድርጎ «ጎበዝ! ጎበዝ! ጎበዝ! ድረሱልኝ! ጎበዝ! ድረሱልኝ!» ሲል ዕርዳታ ጥሪ ጩኸት አሰማ:: በአካባቢው የነበሩ ሰዎች ሰምተውት ኖር ጠጋ ጠጋ ብለው «ምነው? ምነው?» ሲሉት በልሁ እያለቀሰ «የወንድሜ እግር እዚህ ቀርቷል! ኑ አውጡልኝ! ቶሎ በሉልኝ!» አላቸው::

ሰዎቹ ወደመኪናው ውስጥ ገብተው በልሁ ወደ ጠቆማቸው ቦታ ጎንበስ እያሉ ሲያዩ እውነትም ቢጫ ነገር ታያቸው:: ያን የሞተር ክዳን እንደ ምንም ተረዳድተው ወደ ፊት ከመለሱ በኋላ ከመኪና ስፖንዳ ጋር ተጣብቆ የነበረችውን ጫማ ፈልቅቀው በማውጣት ለበልሁ ሰጡት::

በልሁ ያቺን ቢጫ ጫማ ይዞ ከመኪናው ላይ ወረደና ጫማዋን ወደ ላይ ከፍ አድርጎ ለሕዝብ እያሳየ «እዩት ወገኖቼ! እዩዋት የወንድሜን ጫማ! የሆነውን ነገር በዚህ ገምቱ! ወንድሜ ሞቷል! ወንድሜ ሞቷል! ...» እያለ ይጮህ ጀመር:: አስቻለውን የማያውቅ ሁሉ የሆነውን ነገር እየገመተ እንባውን አፈሰሰ::

ወዲያው ደግሞ ጥቂት ሰዎች በስቴሽን ዋገን ቶዮታ መኪና አስክሬን ጭነው ከቦታው ደረሱ፣ የጠይሟ ልጃገረድ አስክሬን ኖሯል። ህዝቡ ሁሉ ግርር ብሎ ወደ መኪናዋ ሲሮጥ በልሁም አብሮ ተጠጋ። ሌላው ሰው ከኋላ ከተሳፈሩት ሰዎች ጋር ሲነጋገር በልሁ ግን የልጅቷን አባት ጋቢና ውስጥ ሆኖ ሲያለቅስ አየውና ጠጋ ብሎ፦

«አቶ ዘመድኩን!» ሲል ጠራው እንባውን በጉንጩ ላይ እያፈሰሰ።

«እንዲህ ሆንኩልህ በልሁ! የድሃ ልጅን ጉድ ተሰራሁ! ስንት ሆኜ ያሳደኳትን የበኩር ልጄን! ወይኔ ወይኔ ...» በማለት እያለቀሰ ሀዘኑን ለበልሁ ገለፀ።

«አስክሬን የት አገኘህ?» ሲል ጠየቀው በልሁ አሁንም እያለቀሰ።

«ናዝሬት ሆስፒታል ነው የሰጡኝ በልሁ።»

«ምናልባት የልጅህን አስክሬን ስታወጣ ልብ ያልከው ነገር ይኖር ይሆን?» ሲል በልሁ ጠየቀው። ዘመድኩን የበልሁ ፍላጎት ገብቶታል።

«ምን ይለያል ብለህ በልሁ? የሬሣ መዓት ተከምሯል። በያ ላይ አንዳንዱ ምንም ምንም አያስታውቅ፤ ሰውነቱ ሁሉ ፈራርሷል። ብታይ እኮ ጉድ ነው የሚታየው።» አለው ፊቱን በመሀረብ ሙዥቅ አድርጎ እየጠረገ።

በልሁ አንጀቱ ብጥስ ያለ መሰለው። መቆም አቃተውና ከመኪናዋ ራቅ ብሎ ሜዳው ላይ ቁጭ አለ። ያቺን የአስቻለውን ጫማ ከፊቱ አስቀምጦ በእግሮቹ መሀል አጎንብሶ እያየ ያለቅስ ጀመር።

የጠይሟን ልጃገረድ አስክሬን የጫነችው መኪና ወደ ዲላ ጉዞ ስትጀምር ወደ ናዝሬት የሚሄዱ አዘንተኞችን የጫኑ መኪኖች ሾፌሮችም ሕዝቡ ወደየመኪናው እንዲገባና ጉዞው እንዲቀጥል ይለምኑ ጀመር። በዚያ ሰዓት ስለ አደጋው ያጠኑ የነበሩ የትራፊክ ፖሊሶችም መንገድ በማስለቀቅ ሰበብ ሕዝቡ እንዲሳፈር ወደ መኪናው መግፋት ጀመሩ። በልሁንም ደጋግፈው በማንሳት ወደ መቀመጫው ወስደው አስቀመጡት።

ጉዞው ተጀመረ። ማታ እራት በወጉ፣ ጠዋትም ቁርስ ያልበላ አዘንተኛ ሁሉ ዝዋይ ሲደርስ እህል ልቅመስ አላለም። ሾፌሮቹ እንኳ አልከጀሉም። ዝም ብለው አለፉ። መቂና አለም ጤና እንዲሁም ቆቃ ከተሞች ታለፉ። ህዝቡ ደግሞ አደጋው በደረሰበት ቦታ ላይ አልቅሶ አልቅሶ ደክሞት ስለነበር ጉዞውም ፀጥ ረጭ ያለ ሆነ። በአብዛኛው የተሳፋሪ እምነት የናዝሬት ሃይለ ማርያም ማሞ ሆስፒታል የአስክሬን መልቀሚያ ወይም የቁስለኛ መገኛ ነውና ሁኔታዎች መቀየር የጀመሩት ሞጆ ከተማ ታልፋ ወደ ናዝሬት ማቆልቆል ሲጀምር ነው። በተለይ ከናዝሬት መዳረሻ የመጨረሻዋ ዳገት ላይ ሲደርስ ለጥ ባለ ሜዳ ላይ የተቆረቆረችውን የናዝሬት ከተማ ሲያይ ሁሉም ተሳፋሪ ያለቅስ ጀመር። ከተማ ውስጥ ሲገባ ደግሞ ጫጫታና ኡኡታ። ሆስፒታሉ በር ላይ ሲደርስ ደግሞ አገር ቀለጠ።

ሕዝቡ ከየመኪናዎቹ ላይ እየተሽቀዳደመ በመውረድ እያለቀሰና እየጮኸ ከሆስፒታሉ ቅጥር ግቢ ውስጥ ሲገባ ወዴት አቅጣጫ መሄድ እንደነበረበት አያውቅም። የወገኖቻቸውን ሞት የተረዱ የሬሣ ክፍል የት እንደሆነ በመጠየቅ ይዋከቡ ጀመር። ሌላው ደግሞ ፊትለፊት ወደሚገኘው የድንገተኛ መቀበያ ክፍል ገሰገሰ። የድብልቅልቁ መጠን ለማስተናገድም እስከ ማስቸገር ደረሰ።

በልሁ የሮጠው ወደዚሁ ድንገተኛ መቀበያ ክፍል ነው። በቦታው በርካታ ነርሶችና ጤና ረዳቶች አሉ። ከነርሶቹ መካከል አንዷ በልሁ ጠጋ ብሎ እንዲያነጋግራት ጠራችውና የያዛትን ጫማ አየት እያደረገች፦

«በእጅህ የያዝከው ምንድነው?» ስትል ጠየቀችው።

በልሁ ያለ ምክንያት እንዳልጠየቀችው ገባው። ፍዝዝ ድክም ባለ አነጋገር «ሌላዋ ያለችበትን ቦታ አውቀሽ ከሆነ ንገሪኝ።» አላት ዓይኑ በእንባ ጢም ብሎ ሞልቶ በጉንጩ ላይ እየተንቆረቆረ።

«ተጎጂው ማን ይባላል?»

«አስቻለው ፍሰሀ።»

«ምናልባት አዲስ አበባ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ልታገኘው ትችል ይሆናል።» አለችው ነርሷ በፊቷ ላይ ሀዘን እየተነበበ።

«ምን ወስዷት?» አለ በልሁ ልቡ ድው ድው እያለ።

«ትናትናው እሱንና ሌሎች ተጎጂዎችንም በሆስፒታል አምቡላስ ለከፍተኛ ህክምና እዚያ አድርሰናቸው መጥተናል።»

«አንቺ ራስሽ?»

«ሌሎችም የሥራ ባልደረቦቼ ነበሩ።»

«አስቻለው መናገር ይችላል?» ሲል ጠየቃት በልሁ አስቻለው ያለበትን ሁኔታ የምትገልጽለት መስሎት።

ነርሷ ራሷን ወደ ቀኝ ወደ ግራ ዘንበል ቀና አድርጋ ፈራ ተባ ባለ ስሜት ከአቅማማች በኋላ «እሱን እንኳ አታስዋሽኝ!» አለችው።

በልሁ ለጊዜው ወደ ሬሣ ክፍል መሮጥ እንደማያስፈልገው ቢያረጋግጥም የነርሷ ንግግር እንደገና ተስፋ አስቆረጠው። ከንፈሩን ነክሶ ወደ ሰማይ አንጋጠጠና እንደገና ፊቱን ወደ ነርሷ መለስ በማድረግ፦

«ግን ይተርፍ ይመስልሻል የኔ እህት?» ሲል ጠየቃት።

«ብዙ ደም ፈስሶታል።»

«አመሰግናለሁ» አላትና በልሁ ፊቱን ምልስ አድርጎ ከሆስፒታል መውጫ በር አቅጣጫ ገሰገሰ። ከግቢ ወጥቶ በኮንትራት ታክሲ ወደ ናዝሬት የአውቶቡስ መናኸሪያ በረረ።

ከዲላ እስከ ናዝሬት ያለው የሁለት መቶ አርባ አምስት ኪሎ ሜትር መንገድ ከናዝሬት እስከ አዲስ አበባ ያለውን የአንድ መቶ ኪሎ ሜትር መንገድ ያህል አላሰለቸውም ነበር። ከናዝሬት እስከ ቃሊቲ ያለውን ጉዞ ከአንድ ሠዓት ብዙም ባልበለጠ ጊዜ ቢያጠቃልለውም ከቃሊቲ እስከ ጥቁር አንበሳ ያለው ግን ካለው የትራፊክ መጨናነቅ የተነሳ የተሳፈረበት መኪና ፍንክች ሊልለት አልቻለም። ትንሽ ሄዶ መቆም፣ ፈቅ ብሎ መገተር። ጭራሽ መንገድ ላይ ያሳደረው መሰለው። አሁንም ያው። ቆይቶም ያው። በመኪና እንደ ተጓዘ ሳይሆን በልቡ እየዳኸ በሚመስል ስሜት ታጥቶ ታጥቶ ልክ ከምሽቱ አሥራ አንድ ሠዓት ላይ ከጥቁር አንበሳ ሆስፒታል መግቢያ በር ላይ ደረሰ።

የሆስፒታሉ መግቢያ በር ስፍር ቁጥር በሌለው ሕዝብ ተጨናንቋል። የሕዝብ ‹እንግባ› የዘበኞች ‹አናስገባም› ጭቅጭቅ ጦፏል። አንዳንዶች ብቻ ቁራጭ ወረቀት እያሳዩ ይገባሉ፤ የአስታማሚ ወረቀት መሆኗ ነው። በልሁ በመግቢያ

ጠረቀት ምትክ የአስቻለውን ቢጫ ጫማ ሊጠቀምባት ፈለገ:: በሩ ላይ የተኮለኮለውን ህዝብ እየገፈታተረ መሀሉን ሰንጥቆ በሩ ላይ ደረሰና ከአንድ ዘበኛ ጋር ተፋጠጠ::

«ወዴት ነው?» ሲል ዘበኛው ፈጠጥ ብሎ እያየ ጠየቀው::

«የትናንቱን የመኪና አደጋ ሰምተሃል?» አለው በልሁ::

«እናስ?»

በልሁ ጫማዋን እያሳየ «ይቺ ጫማ አደጋው ከደረሰበት ሰው እግር ላይ ወድቃ የተገኘች ናት:: ተጎጂው ወንድሜ ነው:: በዚህ ሆስፒታል ውስጥ ስለ መተኛቱ መረጃ አለኝ:: ልገባ እፈልጋለሁ::» አለው::

«የእስታማሚ ጠረቀት ይዘሃል» አለው ዘበኛው::

«ከየት አምጥቼ?» በልሁ ሳያውቀው ዓይኑን ፈጠጥ አድርጎ አያየው::

«ከሌለህ አትገባማ!»

«ችግሩን እየነገርኩህ!?»

«መመሪያ ነዋ!»

«እንዴት?» አለና በልሁ በግርምት አስተያየት ዘበኛውን ያየው ጀመር:: ዘበኛው ከዚያም አልፎ «መተላለፊያ ልቀቃ!» አለው::

በልሁ የበለጠ ተናደደና መተላለፊያ ልቀቅ በመባሉን ሰበብ አድርጎ ወደ ኋላ ከመመለስ ይልቅ ወደ ፊት ተራምዶ ከአጥሩ ግቢ ውስጥ ገብቶ ዳር ይዞ ቆመ::

«ምን መሆንህ ነው?» ሲል ዘበኛው በቁጣ ዓይን እያየ ጠየቀው::

«መተላለፊያ ልቀቅ አልከኝ!»

«ውጣ ወደ ውጭ!»

«አልወጣም!» አለና በልሁ የያዛትን ጫማ ወደ እግሩ ሥር ጣል አደረጋት:: እልሁ መጣና ትንፋሹ በርክቶ ደረቱ ወጣ ገባ ይል ጀመር::

«ጤና የለህም?» አለ ዘበኛው በልሁን ትኩር ብሎ እያየው::

«ጤና የሌለህስ አንተ!»

በመሀል ሁኔታውን ይከታተል የነበረ ሌላ ዘበኛ ወደ ሁለቱም ጠጋ በማለት «ምንድነው?» አለ ሁለቱንም ተራ በተራ እየተመለከተ::

በልሁ ሁኔታውን እጠር አድርጎ አስረዳው::

ሁለተኛው ዘበኛ የመጀመሪያውን ለአፍታ ያህል ከተመለከተ በኋላ፡ «ገባ ብሎ ይውጣ?» ሲል ፈቃዱን ጠየቀ::

«ሃላፊነቱ የራስህ ነው::» አለና የመጀመሪያው ዘበኛ በሩ ላይ ወደሚገኝ ህመማን ጠያቂ ፊቱን አዞረ:: ከበልሁ ፍጥጫ በመገላገሉ ውስጥ ውስጡን ሳይደሰት አይቀርም:: አያያዙን ፈርቶት ነበር::

ሁለተኛው ዘበኛ በዓይኑ ጠቀስ ሲያደርገው በልሁ መሬት ላይ ጣል አድርጓት የነበረችውን የአስቻለውን ጫማ ብድግ አድርጎ ወደ ውስጥ ገሰገሰ:: መጀመሪያ ያገኘው የድንገተኛ መቀበያ ክፍሉን ነው:: በአካባቢው ነጫጭ ጋውን የለበሱ ሰራተኞች በብዛት ይርመሰመሳሉ::

«ወንድሜ!» አለው በልሁ በቅርብ ያገኘውን የሆስፒታል ሠራተኛ::

«አቤት!»

«ትናንት በመኪና አደጋ ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች እዚህ ሆስፒታል መግባታቸውን ሰምቼ ወንድሜን ፍለጋ ከሲዳሞ መጥቼ ነው:: የተኛበትን ክፍል አገኘው ዘንድ ልትረዳኝ ትችላለህ?» ሲል በትህትና ጠየቀው::

ሠራተኛው በልሁን መልከት አለና ቦታውን ሊነግረው ሲል ድንገት በልሁ በሚፈልገው ክፍል ውስጥ ምድብተኛ የሆነችው ነርስ ከድንገተኛ ክፍሉ ስትወጣ አያት:: ቀይ! ረጅም፣ ልጅ እግር ቢጤ ናት::

«ሲስተር!» ሲል ጠራት::

«አቤት!»

«ከትናትና የአደጋ ሰለባዎች ውስጥ አንደኛው ዘመድ ሳያገኝ አይቀርም፣ ይዘሽው ብትሄጂ!» አላት በዓይኑ በልሁን እየጠቆመ እያረገ::

«የማ ዘመድ ነህ?» ስትል ነርሷ በልሁን ጠየቀችው::

«የአስቻለው ፍሰሀ::»

«አ፣ የዚያ የነርሱ?» አለችው:: ለካ አስቻለው ኪሉ ውስጥ በተገኘ መታወቂያ ነርስ መሆኑ ታውቆ ኖሯል::

«አዎ ሲስተር::» አላት በልሁ:: የአስቻለው ነርስ መሆኑ መታወቅ ምናልባት ለሚደረግለት ርዳታ ትኩረትን የሚያገኝ መስሎት በየዋህነትም ቢሆን ደስ እያለው::

«ና ተከተለኝ::» አለችውና ነርሷ ርምጃ ቀጠለች:: በልሁም ተከተላት:: አንድ ፎቅ ወጣች:: በልሁም ወጣ:: ሌላ ደገመች:: በልሁም ደገመ:: ሦስተኛውን ጨርሳ አራተኛው ላይ ስትደርስ ወደ ቀኝ ታጠፈች:: በልሁም ታጠፈ:: ሁለት በሮችን አልፋ ከሦስተኛው ስትደርስ በልሁን ዞር ብላ አይታ ይከተላት ዘንድ ጠቀስ አድርጋው በር ከፍታ ገባች::

በልሁ ተከትሏት ሲገባ በክፍሉ ውስጥ ከአሥር ያላነሱ ህመምተኞች ተኝተዋል:: በርካታዎች ቀና ቀና ብለው ከጠያቂዎቻቸው ጋር ይነጋገራሉ:: ዓይኑን ወደ ነርሷ ሲመልስ ወደ ክፍሉ የመጨረሻ ጥግ ስትራመድ አያት:: ከአንድ ህመምተኛ አልጋ አጠገብ ስትደርስ በዓይኗ ጠቀሰችው:: ህመምተኛው ቀኝ እጁ እና እግሩ በጀሶ ታስሯል:: ከዓይኑ እና ከአፍንጫው ቀዳዳዎች በቀር ሙሉ ፊቱም በፋሻ ተሸፍኗል:: በክንዱ ላይ ግሉኮስ ተሰክቶለታል:: ነርሷ የህመምተኛውን ስም በልሁ ያየው ዘንድ ከአልጋው ራስጌ ግድግዳ ላይ የተሰቀለውን ካርድ አውርዳ ጠጋ አድርጋ አሳየችው::

«ነርስ አስቻለው ፍሰሀ»

ምዕራፍ አምስት

ሻሞት ተጎዱ እንዲሉ ከአደጋው መድረስ በኋላ ሳምንት እንኳን ሳይሞላ ሀዘን በረድ፤ ቀዝቀዝ እያለ ሄደ። ድንኳኖች ሁሉ ተነቃቅለው ወደ መጋዘን ተመለሱ። ሀዘንተኛ ሁሉ ወደ ሥራ ገባ። ከሩቅ የመጣ ሁሉ ወደየመጣበት ተመለሰ። እንባ ቆሞ በከንፈር መምጠጥ ተተካ። መብረድ ቀርቶ ይባስ እየተቀጣጠለ የሚሄደው በሸዋዬ ቤት ውስጥ የተነሳው እሳት ብቻ! አስቻለውን በተመለከተ

ሔዋን ስደት ላይ ነች፤ በታፈሡ ቤት። አስቻለውን በተመለከተ የተፈጠረባት ጭንቀትና ሥጋት በልሁ ከወደ አዲስ አበባ የስልክ መልዕክት ካስተላለፈበት ጊዜ ጀምሮ ቀለል ያለላት ቢሆንም የወደፊት አኗኗሯ ግን ጨለማ ሆኖባታል። አስቻለው በደረሰበት አደጋ ምክንያት ወደ ክብረ መንግስት ያስበችውን ጉዞ ለጊዜው ትተዋለች። ግን ደግሞ ወደ ሸዋዬ ቤት መመለሻው መንገድ ይጨንቃታል። ሸዋዬ ለቤተሰቦቿ የሃፈችባት ደብዳቤም የጎን ውጋት ሆኖባታል። በስጋት እንቅልፍ አጥታ ተቸግራለች። መንፈሷም ዕረፍት አጥቷል።

ሸዋዬ በበኩሏ በተምታቱ ሀሳቦች ውስጥ ገብታ ራሷም ተምታቶባታል። በአስቻለው መትረፍ ባትከፋም ከመትረፉ ጋር ተያይዞ የሚመጣባትን አደጋ ስታስበው እንደ ገደል ፈርተዋለች። ሔዋን አስቻለው ቤት በማደሯ ምክንያት የወሰደችባትን ርምጃ ሲመለስ መስማቱ አይቀርምና ምናልባት አስቻለውም በዚህ አጋጣሚ ቢጠቃለስስ? ሸዋዬ ተናድዶ፤ ሔዋንም ወደ ቤቷ ለመመለስ ፈርታ ቀውስ በአቋራጭ ከች ከቅናት በተጨማሪ ያ የምትፈራው የማህበራዊ ህይወት ቀውስ በአቋራጭ ከች ሲልባት ነው። ከዚህ አደጋ ማምለጫዋ መንገድ አንድ ብቻ ሆኗል፤ አስቻለው ህክምናውን ጨርሶ ሳይመለስ ሔዋንን በዚያም በዚህም ብላ ወደ ቤቷ መመለስና በእጇ ማስገባት። ምንም እንኳ ቀልቧ የጠላቸው ቢሆንም ሔዋንን ከታፈሡ ቤት አምጥተው ለማስታረቅ የሚችሉ ወይዘሮ ዘነቡ ብቻ መሆናቸውን በማመን ተስፋዋን በእሳቸው ላይ ጣለች። ልክ አደጋው በደረሰ ሳምንት በዕለተ ሐሙስ ዓይኗን በጨው አጥባ ወደ ቤታቸው ጎራ በማለት

«እማማ ዘነብ!» አለቻቸው።

«ወይ የኔ ልጅ?»

«መቼም የሰሞኑን ጉዱን ሳይሰሙት አይቀሩም»

«የምን ጉድ?» አሏት ሆዳቸው እየጠረጠረ ነገር ግን እሷው ትዘርዝረው በሚል ሐሳብ።

«እህቴን ከቤት እንዳባረርኩ አልሰሙም?»

«መስማቱን ሰማሁ ልጄ! ግን ምን አድርጋ ይሆን?» አሉና ጉንጫቸውን በእጃቸው መዳፍ ደገፍ አድርገው ያዩዋት ጀመር።

«በጣም በጣም ባለገችብኝ።»

«እንዴት?»

ሸዋዬ የነበረውን ሁኔታ ሁሉ ዝርዝር አድርጋ ከነገረቻቸው በኋላ «ታዲያ ይኸ አያናድድም እማማ ዘነብ?» ስትል ጠየቀቻቸው።

ወይዘሮ ዘነቡ ለሸዋዬ ጥያቄ መልስ ከመስጠት ይልቅ በውስጣቸው ይጉላላ ለነበረው ሀሳብ መልስ ለማግኘት ሲሉ «አሁን ታዲያ የት ነው ያለችው?» ሲሉ ጠየቋት።

«አንድ ታፈሡ የምትባል መርዝ አለች። እሷ ጋር ሳትሆን አትቀርም።»

ወይዘሮ ዘነቡ በሸዋዬ አነጋገር ውስጣቸው ትደም አሉ። ታፈሡን ያውቋታልና የመርዘኛነት ባህሪ እንደሌላት ያውቃሉ። ይልቁንም ሲያዩዋትም ሆነ ሲያነጋግሯት ደስ ትላቸዋለች። የተዋወቋትም እዚያው ሸዋዬ ጋ ስትመጣ በነበረበት ወቅት ነው። አሁንም የሆዳቸውን በሆዳቸው አድርገው፦

«ያቺ ደርባባ ጓደኛሽ?» ሲሉ ጠየቋት።

«እንዳች ያንደርባትና ሲያዩዋትማ ትመስላለች።» አለችና ሸዋዬ ከንፈሯን ንክስ አድርጋ ወደ ሰማይ አንጋጣ ማየት ጀመረች። ወይዘሮ ዘነቡ ግን ታፈሡን «...ደርባባ የምትመስለው» በማለት ብቻ ሊረኩ አልቻሉም። «እንደው ጥሎብኝ እወዳታለሁ ልጄ! ከመልክ ቢሉ መልክ፣ ከጠባይ ቢሉ ጠባይ፣ ትትናውንም ሁሉ አስተካክሎ አንድዬ የሰጣት እመቤት» በማለት ለታፈሡ ያላቸውን ትክክለኛ ስሜት ከገለፁ በኋላ «ከእንቺስ ጋር ሰላም አልነበራችሁም ነበር እንዴ?» ሲሉ ጠየቋት።

«በዚችው በእህቴ የተነሳ ተጣላን።» አለቻቸው ወይዘሮ ዘነቡ ስለ ታፈሡ የሰጡት አስተያየት ሆድ ሆዷን እየቆጫት። «እሷ አይደለች እህቴን እንደ ዓይን እልም አድርጋ ያጠፋችብኝ» ብላ ፊቷን ወደ ወይዘሮ ዘነቡ መለስ በማድረግ «አሁን ሽማግሌ ሁኑኝ!» አለቻቸው።

«የምን ሽምግልና?»

«ይቺት እህቴን ከተወሸቀችበት ጎትተው ቢያወጡልኝ ብዬ ነዋ! ያለበለዚያማ ትምህርቷም መቋረጡ ነው።»

ወይዘሮ ዘነቡ አሁንም ጉንጫቸውን በመዳፋቸው ደገፍ አድርገው ረጋ ባለ አነጋገር «ሰማሽ ልጄ!» አሏት ከአንገታቸው ዘንበል ብለው እያዩዋት።

«እ»

«ከእንቺም በኩል ጥፋት አየሁ።»

«ምን አደረኩ?» አለቻቸው ሸዋዬ ፊቷን ኩስትርትር በማድረግ እያየቻቸው።

«መቼም ሁላችንም ልጅ ሆነን አድገናል። ልጅነት ደግሞ የተስፋ ዘመን ነው። ልጆች ሁሉን ነገር የሚያዩት በበጎ ነው። መስሎ የታያቸውን ነገር ከመፈጸም አይመለሱም። በተለይ ሴት ልጅ እንዴ እግሯ ከወጣ የልቧን ሳታደርስ አትመለስም። ስለዚህ ዘመድ ነኝ የሚል ሰው ከፊት ከፊቷ እየቀደመ መንገዷን ቢያመቻችላት ይሻላል እንጂ ተመለሽ ብሎ ከእሷ ጋር እልህ መያያዝ... » ብለው ሳይጨርሱ ሸዋዬ አቋረጠቻቸው።

«አልገባኝም!» አለች ቆጣ ባለ አነጋገር።

«ትዳር ሳትይዝ እንዳትጠንስ መላ መላውን መንገር፣ የወደደ ቢጠላት ተበሳጭታ አንድ ነገር እንዳትሆን ማጥናናትና —» ብለው ሳይጨርሱ ሸዋዬ አሁንም ቀደመቻቸው።

«ቁም ነገሩን ብናወራስ እማማ!»

«የማወራሽ ቁም ነገር መስሎኝ!» አሏት እሳቸውም መነፅራቸውን ወለቅ አድርገው እየት እያረጓት።

«ያ ሁሉ የሚሆነው በእጅ ስትገባ አይደል!?» አለቻቸው እስተያየታቸው የንዴት መስሏት ደንገጥ እያለች።

«ቁም ነገሩ በእጅ ማስገባቱ ብቻ አይደለም፣ ተመልሳ እንዳትወጣ ማድረጉ ነው። ለነገሩ እህትሽም ዕድለኛ ሳትሆን አትቀርም፤ ከእጅሽ ብትወጣም መውደቂያዋ ያማረ። ያ ልጅ ደግሞ ባለሙያና ረጋ ያለ የልጅ አዋቂ ነው። እንዳይለያዩ ድንግል ትርዳቸው እንጂ ሁለቱም መልካም ልጆች ናቸው።» አሏት።

ሸዋዬ የበለጠ ውስጧ ጨሰ። በሆዷ ‹ይቺ ፈልፈላ አሮጊት› አለቻቸው በወይዘሮ ዘነቡ ላይ ዓይኗን ስከት አድርጋ።

«ለመሆኑ የዚያች የጓደኛሽ ቤት የት ይሆን?» ሲሉ ወይዘሮ ዘነቡ በመሀል ጠየቋት። በዚህ ጊዜ ሸዋዬ ወደ ዋናው ቁምነገር የተመለሰላት መስሏት ልቧ ትንሽ ተንፈስ አለና «እኔ ወስጄ ከሩቅ አሳይዎትና እመለሳለሁ።» አለቻቸው ትንፋሿ በርከት አፍንጫዋ ሳብ ረገብ እያለ።

«ተሀን ደግ ልጄ፣ ትንሽ፣ ጠሐዩ በረድ ይበልና ሄጄ እሞክራለሁ።»

«እንደ ምንም ብለው ይዘዋት ይምጡ፣ እደራ!»

የዚያን ዕለት ከአመሻሹ አሥር ሰዓት አካባቢ ሸዋዬ ወይዘሮ ዘነቡን ከታፈሡ ቤት አካባቢ አድርሳቸው ወደ ቤቷ ተመለሰች። ነገር ግን የወይዘሮ ዘነቡ አመለካከት ትፍፍ አላት። ሔዋንን በእጇ የማስገባት ዓላማዋ ቢሰናከል ችግሩ የከፋ እንዳይሆን ፈርታ እንጂ ሽምግልናቸውም ቢቀርባት በወደደች ነበር።

ወይዘሮ ዘነቡ ከታፈሡ ቤት ሲደርሱ ከቀኑ አሥር ሠዓት አለፍ ብሏል። ታፈሡና ሔዋን ሶፋ ላይ ቁጭ ብለው እንጀራ በትሪ አትርበው ሲበሉ አገኟቸው። እስቻለውን ለመጠየቅ አዲስ አበባ ስንብተው ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት ነው ከቤታቸው የደረሱት። ቡናም እየተፈላ ነው።

«እራት ነው ምሣ የምትበሉት?» እያሉ ወይዘሮ ዘነቡ ወደ ቤት ገቡ።

«ውይ እማማ ዘነብ» አለችና ታፈሡ የቆረሰችውን እንጀራ ትሪው ላይ ትውት አድርጋ ተነስታ ተቀበለቻቸው። ሔዋንም ብድግ አለች። ግን ሸዋዬ ተከትላቸው የምትገባ መስሏት ቀልቧ ግፍፍ አለ። ደነገጠች።

ሦስቱም ተሳሳሙ። ወይዘሮ ዘነቡ ከላይ እስከ ታች ጥቁር ለብሰው ስለነበር «ምነው እማማ ዘነብ ጠቋቁሩ?» ስትል ታፈሡ ጠየቀቻቸው። ሔዋንም ትኩር ብላ ታያቸዋለች።

«የስምንት መዓት ያልወረደበት ማን አለ ብለሽ ነው የኔ ልጅ!»

«ምነው? ዘመድ ሞተብዎት?»

«ከዘመድ የምትበልጥ ጓደኛዬን አሳጣኝ ልጄ! ያውም አብሮ አደጌን።» ካሉ በኋላ «ምናልባት በስም ታውቂያት ተሆን ወይዘሮ አቦነሽ ሀይሌ ትባል ነበር፣ እዚሁ ዜሮ ሰባት ቀበሌ ውስጥ የታወቀች ጠጅ ጣይ!» አሉና በለበሱት ጥቁር ነጠላ ዓይንና አፍንጫቸውን ጠረግ አደረጉ።

«ውይ...ውይ...» አሉ ታፈሡና ሔዋን። የወይዘሮ ዘነቡ አለቃቀስ አሳዘናቸው። ሟቿ ያኔ ከእስቻለው ግራ ጎን ቁጭ ብለው የነበሩ የሴት ጀግና መሆናቸውን ቢያቁማ ኖሮ ምን ያህል እንጀታቸው በተንሰፈሰፈ ነበር።

ታፈሡ ወይዘሮ ዘነቡን ጋብዛ ሶፋ ላይ ከአስቀመጠቻቸው በኋላ ፊቷን ወደ ጓዳ መለስ አድርጋ ለወይዘሮ ዘነቡ የእጅ ውሀ ታመጣ ዘንድ ሠራተኛዋን አዘዘች። እሳቸው ግን ጠንክረው ተቃወሙ። ጭውውቱ ብቻ ቀጠለ።

«የእኛንስ ጉድ ሰምተው ይሆን እማማ ዘነብ!» ስትል ታፈሡ ጠየቀቻቸው።

«ምን ሆናችሁ?»

«ሸዋዬ አልነገረችዎትም?»

«ኧረ ድንግል ትመስክርብኝ! ምንም አልነገረችኝ።»

«ከአደጋው ወዲህ አልተገናኛችሁም?»

«እንዴ! አብረን እየኖርን!» አሉና «አሁንስ ቢሆን እዚህ አንቺ ደጃፍ ያደረሰችኝ እሷ አይደለች እንዴ?» አሉ እንደ መገረምም እያሉ።

ታፈሡ በመናደድ ዓይነት ራሷን እየወዘወዘች «ብጣም የምትገርም ሰው ናት። እጅግ በጣም።» አለች።

«ግን እናንተ ማን ተጎዳባችሁ?» ሲሉ ጠየቁ ወይዘሮ ዘነቡ።

«እስቻለው ነዋ!»

«አ!» አሉ ወይዘሮ ዘነቡ ድንግጥ ብለው «እስቻለው የእናንተ?» እንደገና።

«ህይወቱ ለጥቂት ተረፈች እማማ ዘነብ።»

«ውይ በሞትኩት! ውይ በሞትኩት! ውይ በሞትኩት!» አሉና ወይዘሮ ዘነቡ ደጋግመው ደረታቸውንም በቡጢ ደለቅ ደለቅ አድርገው «አሁን ታዲያ እንዴት ነው?» ሲሉ ጠየቋት።

«ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ውስጥ ህክምና እየተደረገለት ነው።»

«ውይ ልጄን! ውይ ልጄን! ውይ ልጄን! እኔ መች ሰማሁ ልጄ፣ እኔ ምን ቁቤ!» አሉና «ለመሆኑ ሸዋዬም አልሰማች ይሆን እንዴ?» ሲሉ ጠየቋት።

«በደንብ ሰምታለች!»

«ምን ነካት ልጄ? ታዲያ እንዴት አልነገረችኝም?» አሉና «እውነትም ሆዷ ክፉ ነው ልበል!» እንደገና።

«ጥሩ ሰው ብትሆንማ ኖሮ እንኳንስ ለእርስዎ መንገር አዲስ አበባ ድረስ ሄዳም ልትጠይቀው በተገባት ነበር።»

«አቤት! አቤት! አቤት!» አሉና ወይዘሮ ዘነቡ «አሁንስ ታዘብኳት ልጄ! በጣምም አዘንኩባት። ይህን ሆዷን ባውቅ ኖሮ ወደዚህ የመጣሁበትን ጉዳይ እንኳ እሺ ብዬ አልቀበላትም ነበር።» በማለት ተፀፁ።

«እሷ ናት እንዴ የላከችዎት?» ስትል ታፈሡ ጠየቀቻቸው።

«ጓላስ ልጄ! ይቺን ልጅ አምጥተሽ አስታርቂኝ ብላ!» አሉና ሔዋንንም አየት አደረጓት።

«እንኳን ለዚህ አበቃሽ ሔዬ፣ ልትሸመገይ ነው።» አለችና ታፈሡ ሔዋንን እያየች ሳቅ አለች።

«የኔ ደማማ! አትሸመገይኝ ይሆን?» ሲሉ ወይዘሮ ዘነቡ ሔዋንን ጠየቋት። ሔዋን ግን በሀፍረትም በድንጋጤም አቀርቅራ መሬት መሬት ታይ ጀመር።

«ምን ቁርጥ አድርጓት!» አለች ታፈሡ ፈገግ ብላ ሔዋንን እየተመለከተቻት። «አይደል የኔ ቆንጆ?» እንደገና።

«እዎ! የኔ ልጅ እምቢታ አይወጣትም።» አሉ ወይዘሮ ዘነቡ ወደ ኋላቸው ሶፋውን ደገፍ እያሉ።

«ለመሆኑ ለምን አባረርኳት አለችዎት እማማ ዘነብ?» ስትል ታፈሡ ፈገግ እያለች ጠየቀቻቸው።

«ልጄ! አሁን አሁን ሳያት ይቺ ሽዋዬ የምትባል ሰው ቅጥ ያጣት ሴ… ልለመስል አለችኝ። እንደው ምኗም ምኗም አላማረኝ፤ አትታዘቡኝ እንጂ!» ብለው ዓይናቸውን በታፈሡና በሔዋን ላይ ጣል ነቀል አደረጉት።

«ገራ ገብቶናል እማማ፤ አባክዎትን ምክሩልን።» አለቻቸው ታፈሡ።

«ኤዲያ!» አሉና ወይዘሮ ዘነቡ እጃቸውን መንጨር አደረጉ። «ተመክሮ ልብ…አለ! ቢመክሯትስ መች የምትሰማ ሆነች?» አሉና ታፈሡን አየት አደረጉት። ለአፍታ ያህል ፀጥታ ሰፈነ።

«ታዲያ እንግዲህ አንዴ መጥቻለሁ፤ ይገርሽ ልሂድና ሳስታርቃችኋ የኔ አበባ!» በማለት ወይዘሮ ዘነቡ ፀጥታውን ሰበሩት። እሳቸው ሔዋንን ፈገግ ብለው ሲያዩዋት እሷ ግን መሬት መሬት ትመለከት ጀመር። ልቧም ፈራ።

«ማስታረቁን ያስታርቋታል እማማ ዘነብ፤ ነገር ግን የሚሆንልዎ ከሆነ መጀመሪያ እኔና ሽዋዬን ያስታርቁን። ከዚያ በፊት ሔዩ ከዚች ቤት ንቅንቅ አትልም።» አለቻቸው ታፈሡ ቀድማ። ቀጠል አድርጋም «በዚህ ጉዳይ ላይ ሰሞኑን ሔዩም ባለችበት ከበልሁ ጋር የተነጋገርነው ነገር አለ» ቸለችና «በልሁን ያውቁት የለ?» ስትል ጠየቀቻቸው።

«የዚሁ ልጅ ጓደኛ መሆኑ ነው?»

«አዎ። አሁንም ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ውስጥ እያስታመመው ያለው እሱ ነው። የሰሞኑን የሔዩን ሁኔታ ነግረነው እጅግ በጣም ተቆጭቶ እንደውም እሱ ሳይመጣ ሔዩ ከዚህ ቤት ወዴትም እንዳትሄድ አደራ ብሎኛል። ሆኖም አያያዙ ስላስፈራኝ እሱ ሳይመጣ ሔዩ ከእህቷ ጋር ብትታረቅ ደስ ይለኛል። ባይሆን እሱን ይቅርታ እጠይቃለሁ።»

ወይዘሮ ዘነቡ በታፈሡ ቅንነትና ግልፅነት ደስ እያላቸው «ሀሳብሽ መልካም ነው የኔ ልጅ! ልብሽም እንደ መልክሽ የጠዳ! ድንግል ትባርክሽ።» አሉና «መቼ እናድርገው ታዲያ?» ሲሉ ጠየቋት።

«መሽ እንጂ ዛሬም ይቻል ነበር። ነገ ከተመቸዎት እኔ ዝግጁ ነኝ።»

«ጥሩ የኔ ልጅ! ግን አደራ ወቀሳ እንዳይበዛ!» አሏት።

«የምን ወቀሳ እማማ ዘነብ! ኧረ ከቶ ትምጣልኝ እንጂ እግሯ ላይ ወድቄ ማሪኝ ነው የምላት! ያጠፋሁትን ግን እሷ ትወቀው። አጠፋሁ አላጠፋሁ እሷን ይቅርታ በመጠየቄ የትኛው ክብሬ ሊቀነስ?»

«ክብርና ሞገስማ ያንቺ ነው የኔ ልጅ! ሰው ለሰላም ሲል ባልሰራው ጥፋት ይቅርታ ከመጠየቅ በላይ ምን ሊያስከብረው ይችላል? ይብላኝ ለልበ ክፉዎች እንጂ!» አሉና «ድንግል ትባርክሽ ልጄ!» ብለው በረጅሙ ተነፈሱና እንደገና ወደ ሔዋን ዞር ብለው «አይዞሽ የኔ ልጅ፣ ማንም በልጅነቱ ሳያጠፋ ያለፈ የለም። ልብሽ አይፍራ። ጥፋተኛ ቢኖር አንቺን ለምን አጠፋሽ ብሎ ሰማይ ካልሰበርኩ የሚል ብቻ ነው። አይዞሽ የኔ አበባ። ባይሆን ለነገ ተረጋግተሽ ጠብቂኝ።» አሏት።

ወ/ሮ ዘነቡ ቡናቸውን ጠጥተው ወደ ቤታቸው ለመሄድ ሲዘጋጁ «ነገ ወደ ማታ ላይ ብመጣ አይሻልም?» ሲሉ ስለ ነገው ቀጠሮ ጠየቋት።

«ልክ ዛሬ በመጠብት ሰዓት!»

የወይዘሮ ዘነቡና የታፈሡ ውይይት በዚህ መልኩ እየተካሄደ ባለበት ሰዓት ሽዋዬ አልጋዋ ላይ ቁጭ ብላ በሁለት እጆቿ ጆሮ ግንዶቿን ጠፍራ በመያዝ አቀርቅራ በማሰብ ላይ ናት። ታፈሡንና ወይዘሮ ዘነቡን እያሰበች ልክ በመሀላቸው ቁጭ ብላ እንደምታዳምጣቸው ዓይነት ስለ እሷ ሲያወሩ በሀሳቧ ይሰሟታል፤ «ጉድ ነው እኮ ተቃጥላ! ሰው እንዴት በእህቱ ይቀናል? ኧረ የሷ የብቻው ነው? አስቻለውን እንደሆን አታገኘው፤ ምን ያሰፋታል?» የሚሏት ይመስላታል። ወይዘሮ ዘነቡ ታፈሡን ሲያሞካሹ፣ ለአስቻለውና ለሔዋን ፍቅር መልካም ሲመኙ፣ እሷ በአላቸው ፊት የምታሳየውን ድንጋጤና የብስጭት ስሜት ለታፈሡ ዝርዝር አድርገው ሲያወሩባት ሁሉ ይታያታል። በዚያው ልክ ትጥል ንድድ ትላለች።

ወይዘሮ ዘነቡ ግቢያቸው ውስጥ እንደገቡ ወደ ቤታቸው ጎራ ሳይሉ በቀጥታ ወደ ጓሮ ዞረው ወደ ሽዋዬ ቤት አመሩ። ሽዋዬ ድንገት የሰው ኮቴ ሰምታ ከአጎነበሰችበት ቀና ስትል ወይዘሮ ዘነቡ ብቻቸውን ሲመጡ አየቻቸው። ወደ ጓዳቸው ዓይኗን ስታማትር ሔዋን የለችም። «እንዴ!» አለችና «እማማ ዘነቡ» ስትል ጠራቻቸው ገና ከሩቅ ሳሉ።

«ወይ»

«አልተሳካልዎትም?»

ወይዘሮ ዘነቡ ዝም ብለዋት ወደ ቤት ገቡና ዱካ ላይ ቁጭ ካሉ በኋላ «ትሰሚያለሽ የኔ ልጅ!» አሏት ቀልብና ስሜቷን ሰብስብ ለማድረግ።

«እሺ!» አለቻቸው በጉጉትና በፍርሀት ስሜት ተውጣ።

«ጓደኛሽም እህትሽም መልካም ሰዎች ናቸው። እህትሽ ጥፋቷን አምናለች። ጓደኛሽም ተቆጥታለች። አንቺ የፈለግሽውን እርቅ እነሱ የበለጠ ፈልገውታል። እውነተኛ እርቅ ደግሞ አፍን ሳይሆን ልብን ከፍቶ ስለሆነ፣ ለዚህ ብርቱ ጉዳይ አንቺም ስትዘጋጂ እደሪና ነገ ሁለታችንም አብረን እንሂድና አንቺንም ከጓደኛሽ፣ እህትሽንም ከአንቺ በማስታረቅ ሁሉንም ነገር ፈጥመን እንመጣለን። ከዚያ በኋላ እህትሽንም ይዘናት እንመጣለን።» ከማለት ውጭ ሌላ ምንም ሳይጨምሩ ከተቀመጡበት ብድግ ብለው «ብይ ደህና እደሪ!» ብለዋት ውልቅ አሉ።

ሽዋዬ ድንግጥ አለች። ‹እንዴ!› አለች በሆዷ። በዓይኗ ወይዘሮ ዘነቡን እየተከተለች ‹ይቺ አሮጊትና ያቺ ታፈሡ የምትባል መናጢ ምን ተማክረው ይሆን?› በማለት ብቻዋን ታወራ ጀመር። ሄደች በሀሳብ አሁንም ‹ታፈሡ ከኔ ጋር ታርቃ ሰላ እያለች ወደ ቤቴ በመምጣት የጀመረችውን ልትጨርስ!? እኔ ሳላውቅ ከዚች አሮጊት ጋር ገጥማ ውስጥ ለውስጥ ሊያርዱኝ!? በፍጹም! ይህ የማይሆን ነው። ከታፈሡ ጋር እርቅ ብሎ ነገር የለም። ብቻ ያቺ ሰላቢ እህቴ እንደምንም ብላ በእጄ ትግባልኝ። ይህ እንዲሆን የግድ ከታፈሡ ጋር ታረቂ ብባልም ለዚያች ቀን ብቻ! በማግስቱ ግን አፈርሰዋለሁ። በቃ!»

ሽዋዬ ምሽቱን ሁሉ ስለዚሁ ስታስብ ቆይታ ሌሊቱንም ሳትረሳው መልሳ መላልሳ ስታመነዥገው አደረች። ፍላጎቷ አንድ፤ ሔዋንን በእጇ ማስገባት፤ ተከራዋም አንድ፤ ከታፈሡ ጋር ፈጽሞ ከልብ ላለመታረቅ። ሀሳቧ ሁሉ ከዚሁ ሳያልፍ ሌቱ ነግቶ በጠዋቱ ፈረቃ ስራ ገባች።

ከሰዓት በኋላ በታፈሡ ቤት የተያዘው የቀጠሮ ሠዓት ደረሰና ከወይዘሮ ዘነቡ ጋር ወደ ታፈሡ ቤት ጉዞ ጀመሩ::

«እማማ ዘነብ!» ስትል ጠራቻቸው ከጎናቸው ሆና እየተራመደች::

«ወይ»

«ለመሆኑ ታፈሡ እኔን ምን አደረገችኝ አለችዎት?»

«ኧረ እሷ እቴ! ምንም ያለችው ነገር የለም::»

«ታዲያ ከእሷ ጋር መታረቁ ለምን አስፈለገ?»

«በእንቺ ሆድ ውስጥ ያለ ነገር ሊኖር ይችላል ብዬ ነዋ!»

«እስማ ብዙ አለ:: ግን ዝም ነው የምለው::»

«የማ ቂመኝነት ነው:: የነገር ብዛት ባይጠቅምም የቂም ቋጠሮ ከልተፈታ እርቅ አይኖርምና ቅር ያለሽን ነገር አጠር አርገሽ መግለጥ ይኖርብሻል::»

«እኔና እሷን ያቀያየመን እኮ ይኸው የእህቴ ጉዳይ ነው::»

ወይዘሮ ዘነቡ ድንገት ቁጥት አሉ:: «የእህትሽ ጉዳይ የአንቺና የእሷ ጉዳይ አይደለም፣ የራሷ ብቻ ነው:: በእሷ አታሳቢ፣ ተዋት!!» አሉ ጠበቅ ባለ አነጋገር::

«እንዴት እማማ ዘነብ? እኔማ የእህቴ ጉዳይ ያገባኛል::»

«ስለምታብያትና ስለምታጠጫት ተሆነ ተሳስተሻል:: ሆድ የትም ይሞላል:: ቍንቅላት ግን ነጣነት የሚያገኝበትን መንገድ ይፈልጋል:: አትሞኚ!»

«መሬን ልተቂየት ነው የሚሉኝ!»

«ተይ አንቺ ልጅ! ኋላ እንዳልጠላሽ! እህትሽን እንኳን አንቺ እኔ አውቋታለሁ:: ምንስራት ያላት ጨዋ ናት:: የሆዷን አይታ ድንግል ያን የመሰለ ጨዋ ልጅ ስጥታታለች:: እንደኔ ቢሆን በእነሱ መሀል ባትገቢ ጥሩ ይመስለኛል:: እሷት ፈርጠም ባለ አነጋገር::

ሸዋዬ ወይዘሮ ዘነቡን ክፉኛ ጠላቻቸው:: ዛሬ ሔዋንን በእጇ የማስገባት ዓላማ ባይኖርባት ኖሮ በዚያ ሠዓት ወደ ቤቷ ምልስ ብትል በወደደች ነበር:: ከዚያ በኋላ ፀጥ እንዳለች ከታፈሡ ቤት በር ላይ ደረሱ::

የታፈሡ ቤት እንግዳ ሊቀበል ተዘጋጅቷል:: ወለሉ ተወልውሎ ፏ ብሏል:: ከሰል ተያይዞ የቡና ሰቃዎች ተርበዋል:: ታፈሡም እምር ብላለች:: ቀላ ያለ ጉርድ ቀሚስ በነጭ ሸሚዝ ለብሳ ሁብሏ በደረቷ ላይ እንደ ፀሐይ ያበራል:: ያን ረጅም የጥቁር ዞማ ፀጉሯን ጎንጉና በጀርባዋ ላይ ለቃዋለች:: ወይዘሮ ዘነቡ ሸዋዬን አስከትለው ወደ ቤት ራመድ ሲሉ ፈልተቅ ባለ ፈገግታ ተቀበለቻቸው:: በዚያ ሠዓት ሔዋን ድንግጥ ብላ ወደ ጓዳ ስትሮጥ ወይዘሮ ዘነቡ ተመልክተዋት ኖሯል::

«ዛሬ ፈርቶ መደበቅ፣ አኮርፎ መንጋደድ የለም::» አሉና መሀል ወለል ላይ ቆመው «በሉ እናንተ ተድማችሁ በይትርባይነት ያለ ወቀሳ ተሳሳሙ::» አሏቸው ታፈሡና ሸዋዬን ግራና ቀኝ እየተ እየተ እያረጉ::

ታፈሡ ሁለት እጆቿን ዘርግታ ወደ ሸዋዬ ጠጋ በማለት «ሸዋዬ! ከአጠፋሁ ይቅርታ!» ብላ አንገቷን አትፍ አድርጋ በመሳም ጨመጨመቻት::

ወይዘሮ ዘነቡ ታፈሡ በዚያ ዓይነት ፈገግታ እየሳመቻት ሳለች የሸዋዬ ፊት ግን ፈታ አለማለቱ እያናደዳቸው ነገር ግን የጀመሩትን ለመጨረስ ሲሉ፡ «በይ ወይዘሮ ዘነቡ አሁንም ሆዳቸው ቢገኝ:: ሔዋን ያን ያህል በእግሯ ላይ ...

ያቺንም አበባ ጥረልኝ:: በእህቷ እግር ላይ ትውደት» ብለው ሔዋን ወዳለችበት ጓዳ ዓይናቸውን ወረወሩ::

«አንቺ ሔዩ!» ስትል ታፈሡ ተጣራችና ተጥላም «ነይ እማማ ዘነብ ይፈልጉሻል» ስትላት ሔዋን ሽቍጥቍጥ እያለች ከወደ ጓዳ ብቅ አለች:: ለአንደም ቀና ሳትል አቀርቅራ በመራመድ ከመሀላቸው ደረሰችና ከሸዋዬ እግር ላይ ወደቀች:: ወይዘሮ ዘነቡና ታፈሡም «እልል...እልል...» በማለት ዕርቁን አጸመቁት::

ወይዘሮ ዘነቡ አሁንም ሆዳቸው በግኝ:: ሔዋን ያን ያህል በእግሯ ላይ ስትደፋ ሸዋዬ ግን ለመግደርደር ስትል እንኳ ቀና እንድትል አልጋበዘቻትም:: በሆዳቸው ‹ምኗ ድንጋይ ናት በማሪያም› አሉ::

የእርቁ ሥነ ሥርዓት በዚህ ሁኔታ ተጠናቆ ሔዋን ብቻ ወደ ጓዳ ፈጥና ስትመለስ ሦስቱም ሶፋ ላይ ቁጭ አሉ:: የታፈሡ ሠራተኛ ቡና መቁላት ጀምራለች::

«ሰላም ነሽ ሸዋዬ!» አለቻት ታፈሡ ቀድማ ፈገግ ብላ እያየቻት::

«እግዜርን አይነሱ፡ው::»

«ስሞኑን እንደተበሳጨሽ ይገባኛል፣ ሔዩ አጥፍታለች» አለቻት ታፈሡ የሆዷን በሆዷ አድርጋ ግን ደግሞ ፈገግ እያለች::

ሸዋዬ በረጅሙ ተነፈሰችና «ቀድሞ የተባላሽ ነገር ምን መላ አለው፣ ስልጠንተት ቀርቼ...» ብላ ነገሯን ተውት ስታደርግ ታፈሡ ቀጠለች::

«ሁለተኛ ላትደግም ቃል ገብታለች::» አለችና «እኔና አንቺ ግን ስለ ወደፊቱ ትንሽ ብንነጋገርና ከተቻለም ተግምገን ብንስማማ ደስ ይለኛል::» አለቻት::

«ስለ እሷ ከሆነ የሚያነጋግረን ነገር የለም::» አለች ሸዋዬ ኮስተር ብላ::

«ብንነጋገር የሚከፋ አይመስለኝም ሸዋዬ:: ሔዋን እኮ እህትሽ ናት:: እኔን ያገኘችኝ በአንቺ ላይ ነው:: ስለዚህ ለእሷ ማሰብ ያለብሽ ከኔ በላይ አንቺ ነሽ::»

«ይጠቅመኛል ያለችውንማ ይዛለች» አለች ሸዋዬ አፏን ጠመም አድርጋ::

«በኔና በአንቺ ዕድሜ እኮ ከሙያችንም አንጻር በስል ያለ አመለካከት ይጠበቃል ሸዋዬ?» ስትል ታፈሡ አሁንም ረጋ ብላ አስተያየቷን ሰጠቻት::

«ታዲያ ሸዋዬ ምን ጎደላት አሉሽ?»

«ቢያንስ ቢያንስ በሔዋን ዙሪያ የያዝሽው አቋም ትክክል አይመስለኝም:: ነገሩ ሳያስፈልገኝ ራሴ እያየሁት ነው::»

«ተወት አድርጊኝ!»

«እውነቱን እኮ ነው ሸዋዬ! ለመሆኑ ሔዩን ለጥፋት ያነሳሳት ነገር ምን እንደሆነ ታውቂያለሽ?» ስትል ጠየቀቻት::

«አንቺ ነሽ በይኛ!» አለች ሸዋዬ አሁንም ታፈሡን በመገላመጥ:: ታፈሡ እም፣ አንቺ ነሽ ልትላት ስሜቷ ገፋፍቷት ነበር:: ነገር ግን እርጋታና ትዕግስትን የሚጠይቅ ጉዳይ በልቧ አለና ስሜቷን ገታ አድርጋ «ማንም ይሁን ማ፣ ነገር ግን እስራ ስምንት ዓመት ባለፋት ልጃገረድ ላይ ዱላ ማንሳት አልነበረብሽም::» አለቻት::

ሸዋዬ ወደ ወይዘሮ ዘነቡ ፊቷን መለስ በማድረግ «እማማ ዘነብ ለዚህ ነው እንዴ ያመጡኝ?» ስትል ዓይኗን ፈጠጥ አድርጋ ጠየቀቻቸው::

«እስቲ እኮ ቆይ አስጨርሻት!» አሉ ወ/ሮ ዘነቡ እረጋ ብለው::

«ገዛም በላሽ ተመልክቻት አያለችኝ እኮ ነው።»
«እኔ እኮ ቁም ነገር ነው የማወራው ሽዋዬ» ታሪኩ አሁንም።
«ለእናቴ ይመስልሽ ይሆናል።»
በዚህ ጊዜ ታሪኩ የበለጠ ተናደዶ ዳኛነት የፈለጉት ይመስል ወይዘሮ ዘነቡን መልሰት አለቻቸው። በእርግጥ አላቸውም በመሀል ገቡ።
«ምነው ልጆቹ! ፈገ ብላችሁ በተጉና ብትነጋገሩ» አሉ በተለይ ሽዋዬን አየት አያረጉ።
ሽዋዬ ፊቷን ወደ ወይዘሮ ዘነቡ መለስ አድርጋ ቀጣ ባለ አነጋገር «እንዴት አትገዘብኝ! እዚ ያደፈረሰችውን ቤቴ ላይ ሰማትሰል ስትፈልግ አያዩኝም!» አለች። እግሬ መንገዷን ታሪኩን በዓይኗ ገርመም አድርጋት ውጭ ውጭ ጎዳይ ጀመር። ታሪኩ ድገነት «ኪም - ኪም - ኪም - ኪም ...» ብላ ሳቀች።
«ተይ አይሆንም አንቺ ልጅ! ሰው የሚልሽን ተቀበይ! እንዲህ ያለውን ነገር ድንገልም አትወደው! ጊዳ አይሆንም» አሉና ወይዘሮ ዘነቡ ዓይናቸውን ወደ ቡና ሥነ-ሥርዓቱ አዞሩ።
«የመንግስት ጉዳይ ተረስቶ ለሌ መዘዝ ሲመዘዝ ምን ሳድርግ?» አለች ሽዋዬ በተለይ ወይዘሮ ዘነቡን እያየች።
«ምን አደረሰ ሽዋዬ? እኔ እኮ እንነጋገር ነው ያልኩት» አለች ታሪኩ።
«ያደረግሽውንማ አድርገሻል!»
«እስቲ ምን?»
«ለቀጣሪው አረዱት ይሆነብኛል!»
ታሪኩ አሁንም «ኪም-ኪም-ኪም ...» ብላ ሳቀችና፡ «እስቲ አንድ ነገር ልጠይቅሽ።» አለቻት ፈገግ ብላ። ሽዋዬ በዓይኗ ገርመም አድርጋት እንደገና ፊቷን ወደ ውጭ ስታዞር ታሪኩ ቀጠለች። «አንቺ በታላቅነትሽ አህትሽን ድረሽ እስከ ለዘን ማሰረግ ማቢያት አትችይም? አይገባሽም?» ስትል ጠየቀቻት።
«አስተምሮ እንዴ ዳራ ኪይ አልተባለኩም።»
«ምንድ መታዘዝ የለብሽም። ሁኔታዎች ቢያስገድዱሽስ?»
«ማን አባቱ ነው የሚያስገድደኝ?»
ታሪኩ የሽዋዬን ምላሽ ፍፃል ወዲያ ትዝምዝም ወዲሁ ብላ ከታዘበች በኋላ «አልገባሽም እንጂ ጉዳዩ እንደዛሁ ዓይኑን አፍጥጦ መጥቶብሻል።»
«እ!» አለች ሽዋዬ ድንገት በመገረም። ታሪኩንም ፍጥጥ ብላ ትመለከታት ጀመር።
«አንቺ የማይሆንልሽ ከሆነ እኔና በልሁ ልንፈፅመው ወሰንናል።»
«እንዴት አድርጋችሁ?»
«በጣም ቀላል ነው፤ ወደፊት ሀምሌና ነሐሴ ትምህርት ቤት ሲዘጋ እኔና በልሁ ክብረ መንግስት እንሄድና የሔዩን አባትና እናት እናስፈቅዳለን። ከዚያ በኋላ የኔና ያቺን ድርሻ ድል ያለ ሰርግ ደግሰን እሰቱና ሔዩን ማጋባት ነው በቃ!» ካለቻት በኋላ «ክብረ መንግስት ለመሄድም ያሰብነው የሔዩን ችግር አይተን እንጂ ራሳቸው እሰቱና ሔዩ ብቻ የሚፈፅሙት ጉዳይ ነበር።» አለችና ታሪኩ እንደገና ጥብቅ ባለ አነጋገር "ምን ቁርጥ ያረገው ሰው ይከለክላቸዋል?» አለች ፏ ብላ በፈገግታ በመሞላት።

«እሚማ ዘነበ» አለች ሽዋዬ የታሪኩን ሀሳብ የሰሰሙላት ይመስል።
«ወይ»
«እንዳመመውን በሰላም አይመልሱኝም» አለቻቸው ከንፈሯን በምላሷ እያፈሰች።
«ዝም ወዲያ ምን በላም አለ የኔ ልጅ! አንቺም እኮ አሳፊነቱ አያመረዳሽ ነው።» አሉና፣ «እንዲያውም ወደ ክብረ መንግስት በሚያደርገው ጉዞ እኔም በሀዋሳ የሉ ይሰኛል።» እሷት ይጠመቃት ብለው።
«ሽ... እሚማ ዘነበ» ብላ ታሪኩ «ኪም ኪም ኪም...» ብላ ሳቀች።
«ተማሪዎችኑሀሉ» ሽዋዬ በንዴት።
«ማይድታን ስይቀበለው ይገናኛሉ» ሲባል አልሰማሽም? በዚያውም ልብ ያለው ልብ ያርገው ማለቱ ነው።» ካሉ በኋላ ወይዘሮ ዘነቡ «ይኸን ቡና ቶሎ ቶሎ በይው አንቺ ልጅ!» አሉ ወደ ጀበናው እየተመለከቱ። በእርግጥ ቡናው ደርሶ ነበርና መቀዳት ጀመረ።
«ሽዋዬ ቅር አይበልሽ!» አለቻት ታሪኩ አሁንም ፈገግ ብላ እያየቻት።
«ሽዋዬ ነገሮች ሁሉ ከቁጥጥሯ ውጭ እንደሆኑ ተገነዘበች። በዚያችው ቅፅበት ሽዋዬ ብርዓበስ ትዝ አላት። ሰሞኑን ይነጋገሩበት የነበረ አንድ ጉዳይ እሱና ላንተድም ዓይነን ባርኔሁ አለች በሆዷ።
ቡናው ተጠጥቶ ሲያልቅ ለሰሉቱ ሔዋን ከእህቷ ጋር ወደ ቤቷ ተመለሰች። በተህዳላት ጠዋቱን ውስጥ ትገባ አትግባ ገና የሚታወቅ ነገር የለም። እሷ ግን መጠመዱን እንኳ አታውቅም።

ምዕራፍ ስድስት

አንድ ወር ተኩል አለፈ። እስቻለው ከደረሰበት የመኪና አደጋ ጉዳት አገግሞ ዲላ ከተመለሰ አስር ቀን ሆኖታል። የወዳጆቹን የእንኳን አተረፈህ የመልካም ምኞት መግለጫ ተቀብሎ ጨርሷል። ዲላ በገባ ሶስተኛ ቀን ላይ ከሒዋንም ጋር ተገናኝተው የስቀቀን እንባቸውን እፍሰሰዋል። የእስቻለው የእግሩን ስብራትና በቆዳው ላይ ተከስተው የነበሩ ቁስሎቶች ፈጥነው የሻሩ ቢሆንም በተለይ በተኝ እግሩ ጣቶችና በማንባሩ አካበቢ የደረሰበት ጉዳት ጠባሳቸው ባለመጥፋቱ የሒዋንን አንጀት አላውሰውታል። በእጇ እየዳበሰቻቸው በመሳቀቅ ያወረደችው እንባ ከእስቻለው አዕምሮ ምንጊዜም አይጠፋም። እሱም ቢሆን ባለፈው ጊዜ ከእሱ ጋር በማይረ ምክንያት ተፈጥሮባት የነበረውን ችግር ሰምቶ ሁኔታው ክፉኛ አሳዝኖታል።

ዛሬም ሊገናኙ ቀጠሮ ነበራቸው፤ በሚያዚያ ወር ሁለተኛ ሳምንት ላይ በዕለተ ሰኞ። እስቻለው በሀኪም ዕረፍት ላይ ስለሆን ስራ አይገባም። ዕለቱ ደግሞ ለአስራ ሁለተኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ወሳጆች የፈተና አስራር ማብራሪያ የሚሰጥበት በመሆኑ ሒዋን ከማብራሪያው በኋላ ወደ ቤቱ ብቅ ብላ ልታየው ቃል ገብታለት ነበር። ነገር ግን ትናንት ምሽት ላይ በልሁና መርዕድ በእስቻለው ቤት ጫት እየቃሙ ሳሉ ታፈሡ ድንገት ብቅ ብላ «እስቹ» ብላው ነበር።

«ወይ»

«ነገ ከሒዩ ጋር ልትገናኙ ቀጠሮ ነበራችሁ አይደል!?»

«እዎ»

«ቅድም መንገድ ላይ አግኝቻት ‹ስላልተመቸኝ አልመጣምና እንዳትጠብቀኝ› ብላሀለች» በማለት መልዕክት አድርሳለታለች። እስቻለው ዛሬ ስለ ቀጠሮው ማሰብ ትቶ ማርፈጃውን ሁሉ አልጋው ላይ ጋለል ብሎ ያስቸገረው የደረሰበት የመኪና አደጋ ነው። በአደጋው የተጎዳ ሰውነቱ በሰላም ስርቶ በሰላም ውሎ ማደር ሲችል ነገር ግን በእሱ አመለካከት ለምንም ነገር በማይበጁ፤ ለክፋትና ለተንኮል ብቻ በተፈጠሩ እብሪተኞች እስተዳደራዊ ተፅዕኖ በመማረር አካባቢውን ለቆ ለመሄድ ለዝውውር ጥያቄ ሲጓዝ ያን የመሰለ አስቃቂ አደጋ ደርሶበት ለጥቂት መትረፉ ትዝ ባለው ቁጥር ዝግንን ይለዋል። ሁል ጊዜ ንዴት እየተናነቀው መንፈሱ ውጥርጥር፣ ውስጡ እርር ድብን እያለ ከንፈሩን እያስከከሰ ራሱን ያስወዘውዘዋል። የእስቻለው ችግር ይህ ብቻ አይደለም፤ ያለፈውን እንዳለፈ ቆጥሮ መጽናናት እንዳይችል እንኳ ሌላም አደጋ ከፊቱ እንደተደቀነበት ያወቀው ገና ህክምናውን ጨርሶ ዲላ በገባ ማግስት ነበር።

በመሰረቱ የዶክተር ደጀኔ አሜሪካ መግባት እርግጥ ሆኗል። በእሱ እግር የተተካው የዲላ ሆስፒታል ሜዲካል ዳይሬክተር ደግሞ ከመልካቸው በስተቀር

በአስተሳሰብ ከባርናባስ ወየሶ ጋር የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው። እንዲያውም በመላ የሆስፒታሉ ሰራተኞች አፈራረጅ ከባርናባስ የባሰ አገር አጥፊ የተባለ ሰው ነው። ለእስቻለውማ ጭራሽ ሰው የሚበላ የሰው አውሬ!!

አዲሱ ሹመኛ በሙያው ዶክተር ቢሆንም በባህሪው ግን ወትሮም ካድሬ ካድሬ የሚሸት ነበር። በሚናገርበት መድረክ ላይ ሁሉ የሚሰነዝረው ሃሳብና ሀሳቡን የሚገልፅባቸው ቃላት ስልጣን መስመኛ ይመስላሉ። እንዳንዴ ሲፈላሰፍም የሚታጣው ነው። ነገር ግን ከባዶነቱ የተነሳ የጀመረውን ዐረፍተ ነገር እንኳ በግስ መዝጋት የማይችል ግብዝና ዘባራቂ ዓይነት ሰው ነው። ዛሬ ደግሞ ስልጣን አግኝቷል፤ ተናግሮ ማሳመን ባይችል ተናጋሪዎችን ዝም ፀጥ የሚያሰኝ በትር!! እዎ ስልጣን! በእብሪተኞች ጎራ በተሰለፉ ደንቆሮዎች እጅ በገባ ቁጥር የሩቅ አሳቢ አስተዋዮችን አንገት የሚቀላ ሰይፍ!!

እስቻለው በዚህና በዚሁ ዙሪያ ሲያስብ ሲያሰላስል ቆይቶ የተሰማው ንዴትና ቁጭት አዕምሮው ሊሸከመው ከሚችለው በላይ ሲሆንበት ትንሽ የሚቀለው መስለውና ከመኝታው ሊነሳ እንሶላና ብርድ ልብሱን ከላዩ ላይ አሽቀጥሮ ጣለው። ሱሪና ጫማውን እንዲሁም ሸሚዙን ለባበሰ። ጥርሶቹ ግን ከንፈሩን ንክስ እንዳደረጉ ናቸው። ጭንቅላቱን ደጋግሞ እየወዘወዘ ፊቱን ሲታጠብ ውሃ ይዞ ወደ በረንዳ ወጣ።

ሰዓቱ ከሶስት አለፍ ብሏል። እስቻለው ቃጥፉና አበጥሮ ከጨረሰም በኋላ ወዴትም መሄድ አልፈለገም። የቁርስ ሰዓት አልፏል። ቀድሞ ነገር ሆዱም እህል አላሰኘውም። ወንበር ይዞ ከቤት ወጣና ጀርባውን ለፀሐይ ሰጥቶ ግቢው ውስጥ ቁጭ አለ።

ፀጥ ረጭ ብሎ የዲላ ህይወቱን ሲያሰላስለው በአንድ ወይም በሌላ መንገድ ምቾት እንደማይሰጠው ተሰማው። ቢሆንም ባይሆንም አንዲት ተስፋ ብቻ ታየችው። ዶክተር ደጀኔ በገባለት ቃል መሰረት የአዲስ አበባውን ባለስልጣን አነጋግሮለት ኖሯል። እስቻለው ከሆስፒታል እንደ ወጣ ወደ ፅህፈት ቤቱ በመሄድ ያን ባለስልጣን አግኝቶታል። እሱም ዶክተር ደጀኔ በገለፀለት መሰረት የእስቻለውን ችግር እንደተረዳለትና ሊያዛውረው እንደሚችል ቃል ገብቶለታል። ግን ደግሞ ይህን ተስፋ የሚያጨልሙ ሁኔታዎች ከእስቻለው አዕምሮ ውስጥ ድቅን ይላሉ።

ከአሁን በፊት ስለ ዝውውር ጉዳይ ከዶክተር ደጀኔ ጋር ሲነጋገር ‹...የት ቢሔድ ይሻላል?› ባለው ጊዜ ዶክተር ደጀኔ ‹... መሄጃው ላይገድ ይችላል፤ ችግሩ የተሻለ ሁኔታ ከማግኘቱ ላይ እንደሆነ እንጂ› ብሎት ነበር። እንዲሁም ለዝውውር ጥያቄ ወደ አዲስ አበባ በሚሄድበት ጊዜ በመኪና ጉዞ ላይ ከሚቿ ከወይዘሮ አቦነሽ ሐይሉ ጋር ሲነጋገር ወይዘሮ አቦነሽም ‹ሰመሆኑ እነሱ የሌሉበት አገር አለ እንዴ?› ብለውት እንደነበር አስታወሰ። በዚሁ አጋጣሚ የወይዘሮ አቦነሽ ሐይሉ እና የጠይሟ ልጃገረድ ሞት ትዝ አለውና አሟሟታቸው አሳዝኖት በሀዘን ስሜት ከንፈሩን መጥጦ ራሱን ወዘወዘና ወደ ንዴቱና ብስጭቱ ተመለሰ።

«ቆይ ግን!» አለ ድንገት ጮክ ባለ ድምፅና በሐልህ አነጋገር። ምናልባት በሐዩም በዘቶበት ሊሆን ይችላል፤ ከተቀመጠበት ወንበርም ላይ ፍንጥር ብሎ ተነሳ። አንገቱን ደፋ አድርጎ በዚያው በግቢው ውስጥ ጎርደድ እያለ «ሰው በገዛ

ሀገሩ በሰላም ሰርቶ በሰላም መኖር ላይችል!?» አለና መልስ የሚጠብቅ ይመስል ፀጥ ብሎ በመቆም አተርቻሮ መሬት መሬት ያይ ጀመር:: ብስጭቱ ጨመረ፣ «ቀድሞ ነገር ንጹሑስ ለምን? ብስጭትስ ለምን? በምሬት የተነሳ የገጠመር ጥያቄ ለምን? ይህ ሁሉ ጣጣ የመጣው ስዎች በሌላ ሰው ኑሮና ህይወት ላይ ይወስኑ ዘንድ ገደብ የሌለው ስልጣን ስለ ተሰጣቸው አይደል!» አለ በንዴት ስሜት እጆቹን ጥብቅ አድርጎ በመጨበጥ ሰውነቱንም በእልህ እያጠነከረ:: ከዚሁ ጋር ተያይዞ ሰፊዋ ሀገር ኢትዮጵያ እንደ ኳስ ተድቦልቡላ አዕምሮው ውስጥ ድንገት ዘው ብላ ገባች፤ በሀሳቡ:: እንደ እሱ በበደልና በእንግልት ቁም ስቅላቸውን እጥተው የሚስቃዩና የሚያለቅሱ ዜጎቿ አብረው ገቡበት:: ገገርምችና እጫፋሪዎቻቸውም አልቀሩ! ከነድንፋታቸው፣ ከነጭካኔያቸውና ከነትጥፈታቸው እየገቡ ታጨቁበት:: በሆድና በህሊና ጎራ ለሁለት የተከፈሉ የአንድ ሀገር ዜጎች በአዕምሮው ውስጥ ገብተው እየተንጫጩ ተርመሰመሱበት:: በዚህ አስጨናቂ ስሜት ውስጥ ሲገባ ከመንፈሱም በላይ የአካል ድካም ተሰማው:: ወገቡ ተንተጠተጠ:: መቆምም አቃተው:: ያን በሐይ ላይ የነበረ ወንበር ወደ ጥላ ቦታ ወሰደና ቁጭ አለ:: የሀሳብ ሸክሙን ያቀለለ መስሎት «እሁሁ ...» ብሎ በረጅሙ ተነፈሰ::

«አንቺ ኢትዮጵያ!» አለ ትንሽ ቆይቶ:: ሀገሩን ሲወቅሳት ይሁን ሲያለቅስላት ገና ሃሳቡን አላዘጋጀም:: ብቻ ከንፈሩን ንክስ አድርጎ ራሱን ወዘወዘ::

ከትንሽ ቆይታ በኋላ ግን ከራሱ ጋር መነጋገሩን ቀጠለ:: የሚያደምጠው ቢኖር እስከ ውጭ ድረስ በሚሰማ ድምፅ «አንቺ አገር! አንቺ ኢትዮጵያ፣ እስከ መቼ ይሆን ጥቂቶች ሲፈነጩብሽ፣ ብዙሃን ሲያለቅሱብሽ፣ እብሪት እንደነገሰብሽ፣ ፍትህ እንደጎደለብሽ የምትኖረው? ከቶ መቼ ይሆን ደም ያልተቃባ መንግስትና ሕዝብ የሚኖሩብሽ? እኮ እስከ መቼ!?» ካለ በኋላ አሁንም ትንሽ ተንፈስ ብሎ «በእርግጥ እብሪት ለማስተዋል፣ ተንኮል ለግልጽነት፣ ውሸትና ቅጥፈት ለሀቅና ለእውነት ቦታቸውን ለቀው የሰላምና የነፃነት አየር የሚተነፍስብሽ ሀገር ለመሆን ያቢቃሽ ይሆን? በእርግጥ የእናትነት እቅፍሽ ለሁሉም ዜጎችሽ እኩል የሚሞቅበት ጊዜና ዘመን ይመጣ ይሆን!?» አለና ላነሳቸው ጥያቄዎች ሁሉ መልስ የሚጠብቅ ይመስል ዝም ፀጥ፣ ፍዝዝ ትክዝ እንዳለ ለደቂቃዎች ያህል ቆየ:: በሀሳቡ ግን ሌላ ዓይነት በደረቱ ፊገግ እያለ:: በዚህ ጊዜ ትዝ ያለው ገገርዎች ከመጋረጃ ጀርባ ያላቸውን ድብቅ አጀንዳ ይበልጥ ለመሸፈንና የአኮረፈ ሕዝብ ለመደለል ሲሉ በቁጥጥራቸው ስር በአደረጉት ሬዲዮና ቴሌቪዥን አዘውትረው የሚወሻክቱት ባዶ ተስፋ ነው:: እናም ይህንኑ በራሱ ቃል ይናገረው ጀመር:: «‹ኢትዮጵያ አገራችን፣ የአሥራ ሦስት ወር ፀጋ!› ይሏታል፤ ደሞ የመከራ ቀን ሲያራዝሙ! ‹አገራችን ኢትዮጵያ፣ የሰው ዘር መገኛ!› ይሏታል፤ ነገር ግን ኑሮውን አንሳቅለው፣ አስተሳሰቡን አዛብተው፣ አመለካከቱን አሳሽተው በሁሉም ነገር ከዓለም ህዝብ ሁሉ ወደ ኋላ የቀረ ሕዝብ የሚኖርባትን ሀገር! ‹ለምለሟ ኢትዮጵያ!› ይሏታል፤ ድርቅና ረሀብ መለያዋ ሆኖ ዓለም በሚያውቀው መዝገብ ላይ በምሳሌነት ስሟ እንዲመዘገብ ያደረጓትን ያልታደለች ሀገር! ‹የነፃነት ተምሳሌት› ይሏታል፤ ነገር ግን ላይናገር የታፈነ፣ ላያይ ዓይኑ የተጋረደ፣ ላይላወስ እግር ከወርች የታሰረ ሕዝብ

የሚኖርባትን የሲኦል እምባ!!» አለና ለአፍታ ያህል ፀጥ ብሎ ሀሳቡን ሲያዳምጥ ቆየና ድንገት «ኢዲያ!» በማለት እጁን እወናጭፎ ከወንበሩ ብድግ አለ:: ሁለት እጆቹን በሁለት የሱሪ ኪሶቹ ውስጥ ከትቶ በዚያው አካባቢ እንጎብስ ኀርደድ እያለ «ላይኖሩብሽ የሚፈጠሩብሽ አገር!» አለ አሁንም::

ሀሳቡ ሁሉ ከዚሁ ጉዳይ ሳይርቅ አንዳንዴ መሬት መሬት ሌላ ጊዜ ሰማይ ሰማይ እያየ እንደገና ራመድ ኀርደድ ሲል ደቂቃዎችን አሳለፈ:: እልፍ እልፍም በልቡ እያጠራ ከንፈሮቹ ይንቀሳቀሳሉ:: በዚህ ጊዜ ብሶቱን መግለጫ የሚሆኑ አንዳንድ ቃሎችና ሐረጎች ውስጥ ውስጡን ይንገዋለሉበት ጀመር:: በልቡ እመላለሳቸው:: እያደር ነፍስ እየዘሩ ይጎዱበት ጀመር:: እሱም ስጋ ሲያለብሳቸው ፈለገ፤ እዎ በጽሁፍ ሊያስቀምጣቸው::

ድንገት ከሃሳቡ እንደመባነን አለና ፈጠን ቀልጠፍ ብሎ ወንበሩን ይዞ ወደ ቤት ገባ:: ጠረጴዛ ላይ ቁጭ አለና ብዕርና ወረቀት አዘጋጀ:: መሞነጫጨር ጀመረ:: በትድሚያ የህሊናው ጭማቂ የሆኑ ቃላትና ሀረጎችን እንደመጡለት ወረቀት ላይ አሰፈራቸው:: ቀጥሎ ደግሞ ማያያዣ ቃሎችን እያሰበ እነዚያንም ይፅፋቸው ጀመር:: ስንኞችን ለመቋጠር ሞከረ:: ሞካከረ:: በእርግጥም ሃሳቡን የሚገልፁ ስንኞች ተቋጠሩለት:: በመጨረሻም የሀሳብ ቅደም ተከተላቸውን አስተካክሎ በግጥም መልክ አስቀመጣቸው:: ከዚያም ለራሱ ያነባቸው ጀመር::

«ህሊና ታሥረ ከወህኒ ወረደ:-
አዕምሮን ተክቶ ሆድ እየፈረደ::
ሲያለቅስ አገኘሁት ህግ ተንሰቅስቆ:-
መክሰስም መፍረድም ለአንድ ሰው ተለቆ::
ጊዜ በቅሎህን ጫን ገስግስ በፈረስ:-
እውነት ዳኛ ትሁን ተራዋ ይድረስ::
ይኸ ለሊት ይንጋ እንደ ያ ቀን መጥቶ:-
ሁሉም እንደ ስራው እንዲበላ እንጉቶ::
ዝምታ ወርቅ ነው ያለው ሰው ይሙት:-

አገር ይዞ ጠፍቷል ሁሉን ፀጥ አርጎት::
እርጥብ ደረቅ በልተህ የጠገብክ መስሎህል:-
ወገኔ ልንገርህ እውነት ተርበሀል::
ምነዋ ሰው ሆዬ ሰው መሆንን ተውከው:-
ቁንጫ ትኋኑ ሲበላህ ዝም አልከው::
መኖር ስቃይ ሲሆን መከራ ጎራ አክሎ:-
ሞትም ጀግንነት ነው እምቢ አልኖርም ብሎ::»

እስቻለው የራሱ ስንኞች ለራሱ ደስ አሉት:: እንዲያውም አንዳንዶቹ ቃሎችና ሀረጎች ልክ እንደ እሱ ሲያለቅሱ ተሰሙት:: ሌሎቹ ደግሞ ሲጣሩ፤ ለዚያውም ከፍ ባለ ድምፅ:: ስንኞቹ የራሱ ናቸውና እሱን እሱን ሸተቱት::

«ለካ!» አለ አስቻለው አሁንም ለራሱ በመናገር። «ሰው ብዕርና ወረቀት የሚያነሳው ወዶ አይደለም፣ የሀሳብ እጭታት አዕምሮውን ሲወጥረው ቀንበ እድርን ለመተንፈስ ነው። አሊያም ሀሳብ በገዛ ሀይሉ ሞልቶ ሲፈስበት ሀሳቡ ሳይፈስ ሽክፍ፣ ክርክርም አድርጎ ለማስቀመጥ ሲፈልግ ነው።» አለና ምናልባት የጸሐፊ ኢጋጣሚ የደራሲ ህይወት በትንሹም ቢሆን ገብቶት ሲሆን ይችላል «የደራሲ ነገር ሕይወት እንዴት ነው!? ሁል ጊዜ መጨነቅ? ሁልጊዜ መጠበብ? ...ይገርማል!» እያለ ራሱን ደጋግሞ ወዘወዘ።

ሰዓቱ ወደ ስድስት ተጠጋ። የአስቻለው አንጀት እህል እህል ማለት ጀመረ። ምሳ ትዝ አለው። በእርግጥ መንፈሱንም ማሳረፍ ፈለገ። ያቺን ግጥም የጻፈበትን ወረቀት በስነ-ስርዓት አስቀመጠና ከጠንበር ላይ ብድግ ብሎ ጃኬቱን ደረበ። ቤቱን ቆላልፎ ቀጥታ ወደ ዋርካው ምግብ ቤት አመራ።

ወትሮም ቢሆን አስቻለውና ጓደኞች ለምሳ አይጠባበቁም፣ እንደየ ስራቸው ባህሪ የስራ መግቢያና መውጫ ሰዓታቸው ስለሚለያይ ሁሉም በየደረሱበት ሰዓትና ደስ ባላቸው ምግብ ቤት ነው የሚበሉት። አስቻለውም ማንንም ሳይጠብቅ ቁርሱንና ምሳውን በአንዴ በላ። ቀዝቀዝ ያለ ውሃ ጠጥቶ ቡና ሲጨምርበት መንፈሱም ተረጋጋ።

በዚያው ምግብ ቤት ውስጥ ትንሽ ለመቆየት ፈልጎ ነበር፣ ነገር ግን በተለይ ዛሬ ማርፈጃውን እንደ ዱቄት ሲፈጨው ከነበረ ሀሳብ ጋር የማይጣጣሙ ሁኔታዎች ተከሰቱበት። በርካታ ሀሳብ የለሽ የሆኑ ወጣቶችና ጎልማሶች በሆነ ባልሆነ ወሬ ሲያጠኩበት ለስሜቱ አልመች አለው። አንዳንዶቹ ይሿርቃሉ፣ በሳቅ ይንከተከታሉ፣ በቀን በጠራራ ክሲት ጋር ይላፋሉ፣ ይዳራሉ። በዚያ ላይ ንፋሱ፣ አባራው፣ የሻይ ማሽን ሿሿታ፣ የራዲዮ፣ የቴፕ፣... ወዘተ ጫጫታ፣ ብቻ ሁሉም ነገር የአዕምሮ እረፍት አሳጣው። ከዚህ ሁሉ ግርግር የሚገላገለውን ቦታ መረጠ፣ የገዛ ቤቱን። ብድግ አለና በቀጥታ ወደ ቤቱ ሄደ። የተለመደ የዲላ ቀትር ፀሐይ እናት አናቱን እያለው ደረሰና ቤቱን ከፍቶ ገባ። ከዚያም ወደ አልጋው። የተንዘረፈፈ አንሶላና ብርድ ልብሱን ሰብስብ አድርጎ ጫማውን ብቻ አወለቀና በጀርባው ጋለል አለ። ደካከመው። እንደ እንቅልፍም ይሞካክረው ጀመር።

ባርናባስ የሒዋንን ሁለት እጆች ግጥም አድርጎ ይዟል። ሸዋዬ የአገኘችውን ነገር ሁሉ እያነሳች ትደበድባታለች። ሒዋን ‹ኡኡ ድረሱልኝ› እያለች ትጮሀለች። እጆቿን ከባርናባስ ለማስለቀቅ ትታገላለች። እሱ ደግሞ እንዳታመልጠው ጥርሱን ንክስ እያረገ ሀይሉን ያጠነክራል። ሸዋዬ አሁንም ትደበድባታለች። ሒዋንም ትጮሀለች። ይህ ሁሉ ሲሆን በርካታ ሰው ዙሪያውን ከብቦ ይመለከታል። ግን ማንም ሊገላግል አያስብም። አስቻለው ሊገላግል እየፈለገ ግን ደግሞ መሮጥ ያቅተዋል። ይለፋል ግን አይችልም። ከያዘው ነገር ራሱን እንድምንም አላቅቆ ወደ ድብድቡ ቦታ ሊሮጥ ሲል ድንገት ከእንቅልፉ ብንን አለ። «በስመ አብ ወወልድ መንፈስ ቅዱስ...» ብሎ ከተንጋለለበት ቀና በማለት ፊቱን በሁለት እጆቹ ሸፍን

አድርጎ ወደፊት ወደ እግሮቹ ድፍት አለ። ዝግንን አለው። ድርጊቱን ያየው በቅዠት እንዳልሆነ ሁሉ ሒዋን አሁንም በዚያው ሁኔታ ውስጥ ሆና ትታየው ጀመር። አሳዘነችው። ከዚያ በኋላ መተኛት አልፈለገም። ከአልጋው ላይ ፈጠን ብሎ ወረደና ልብሱን ለባበሰ።

ምን ሊያደርግ እንደሆነ ሳይታወቀው በቀጥታ ወደ ሸዋዬ ቤት መሄድ ፈለገ። ቤቱን ቆላልፎ ከግቢ ወጥቶ ቁልቁል ወደ ሸዋዬ ቤት አቅጣጫ ወረደ። ልክ በሸዋዬ ቤት አቅጣጫ በምንተኛ መንገድ ላይ ሲደርስ መንገድ ላይ ቆም ብሎ ቆመና በቀኝ አቅጣጫ ያለውን የወይዘሮ ዘነቡን ግቢ በርቀት ይመለከተው ጀመር። በሃሳቡ በቀን ከሸዋዬ ቤት ገባ። ሸዋዬና ባርናባስ ፍራሽ ላይ ቁጭ ብለው ጫት ሲቅሙ፣ ሒዋን ደግሞ በከሰል ላይ ጀበና ጥዳ የሁለቱ ቡና አፍይ ሆና፣ ሁሉም በአንድ ላይ እንደ ስዕል ታዩት። ልቡ ወደዚያው ቤት ሄድ ሄድ አለው። ነገር ግን ድንገት ዘሎ ቢል ሊፈጠር የሚችለው ሁኔታ ታየው። ከሁሉም በላይ ሒዋን ትሳቀቅበታለች። ስጋ። በዚያ ምትክ ከንፈሩን ንክስ አድርጎ ራሱን በቁጭት ወዘወዘው።

በዚሁ ሁኔታ ጥቂት ቆየና ሳይወድ በግድ ሃሳቡን ለወጠ። በቃ ወደ ሸዋዬ ቤት መግባት አልፈለገም። ግን ደግሞ ወዴት እንደሚሄድ ጨነቀው። ቤቱም ሰለቸው። ወደ አንድ ቡና ቤት አይሄድ ነገር እዚያ ሄዶ የሚገጥመው ነገር ለመንፈሱ አይመችውም። ግራ ሲገባው ቁልቁል ወደ ከተማዋ ዳርቻ ይራመድ ጀመር። ቁርጥ ያለ አድራሻ የለውም። ብቻ መሄድ፣ ብቻ መራመድ። ብሎ ብሎ ከከተማውም ወጣና ወደ አርሬሳ ገበሬ ማህበር አዋሳኝ ላይ ደረሰ። እያደር ደግሞ የገጠሩ ሽታ አማለለው። አሁንም ወደፊት ሲራመድ ወሰነና ርምጃውን ቀጠለ።

በዚያ መንገድ ላይ በርካታ የገጠር ነዋሪዎች ወደ ከተማ ያመራሉ። ከከተማም ወደ ገጠር ይሄዳሉ። አስቻለውም ርምጃውን ዝም ብሎ ወደ ፊቱ ቀጠለ። በልቡ ግን አንድ ነገር ያስላስላል፣ ወደፊት ሐምሌ ላይ የሚጠብቀውን ዝውውርና ከሒዋን ጋር ስለሚኖረው ግንኙነት። ‹ለመሆኑ› ይላል በሀሳቡ። ‹ዝውውሬ የሒዋን ጉዳይ እንዴት ሊሆን ነው? ይዣት ልሄድ ወይስ ትቻት?› ይልና እንደገና [illegible] የበልሁ ወደ ክብረ መንግስት የመሄድ ዕቅድ ይመጣበታል። ‹ሄደውስ [illegible] ይሆን? ወይስ የሒዋ እናትና አባት ሸዋዬ በነፈትላቸው [illegible] ይሆን? [illegible] ያንገራግሩ ይሆን? እሺ ቢሉም ሰርግ ድግስ [illegible] ሁኔታው [illegible] ያ እስከሚሆን ጊዜ ይፈጃል። ዞሮ ዞሮ ሳልተወሰነ ጊዜ [illegible] ሊሉ ይችላሉ። [illegible] ጋር መራራቁ አይቀርም።› በማለት ራሱን እንደማረጋጋት ዓይነት ‹እንግዲህ የሆነው ይሁን! ብቻ ሰላምና ጤና ትሁንልኝ።› እያለ አምላኩን ይማፀናል።

ሳያውቀው ብዙ ተጉዟል። በለየለት ገጠር ውስጥ ገብቶ ከዲላ ከተማ በግምት ሁለት ኪሎ ሜትር ያህል ርቋል። ከሀሳቡ ብንን በማለት ባለበት ቦታ ላይ ቆሞ ዓይኑን ወደ ቀኝ አቅጣጫ ጣል ሲያደርግ ዙሪያዋን በረጃጅም ዛፎች የተከበበችና፣ ሰፋ ያለች ደስ የምትል ገላጣ ሜዳ ታየችው። ከግጦሽ ከፍ ያለ የሰጋት ደረጃ ላይ በደረሰ ለምለም ሳር ተሸፍናለች። በውስጧ አልፎ አልፎ የደረቁ ጉቶዎች ጉብ ጉብ ብለው ይታያሉ። ወደዚያው ታጠፈና ሜዳዋ መሀል ገብቶ ከአንድ ጉቶ ላይ ቁጭ አለ። ዙሪያውን ሲመለከት ጥቅጥቅ ያለ ጫካ ነው። ዛፎቹ ደግሞ ረጃጅም። ወደ መሬት ሲያይ ያ ለምለም ሳር። በአፍንጫው የሚገባው

አየር በራሱ የተለየ መዓዛ ያለው። መንፈስ የሚያድስ። እጆቹን በደረቱ ላይ አቆላልፎ ወደ ዛፎቹ ሲያይ ከአንዱ ወደ ሌላው እየተዘዋወሩ የሚንጫጩ ወፎች ቀልቡን ሳቡት። ከወፎቹ የሚጫጫታ ድግግሞሽ የተነሳ የወፍ ድምጽ ጌጡ ሳይሆን ሴኮንድ አታልፍም። የድምፃቸው ልዩነት ውበትና ህብሩ በጭንት በጥብ ከተቀመረ ዘመናዊ ሙዚቃ የበለጠ ስሜት ይማርካል።

«እናንተ ወፎች!» አለ እስቻለው ሁኔታቸው ሁሉ ግርም ብሎት። «ሁሉ የሁላችሁ! ለኑ ብቻ ባይ ስግብግብ በመሆናችሁ የለ፤ አዛኝ የላችሁ ገልማጭ ጠላት የላችሁ ምቀኛ፤ ኑሮአችሁ በራሳችሁ፤ ውሸት አታውቁ ቅጥፈት፤ አትሰሙ ክፉ አትናገሩ፤ አትቀየሙ አታስቀይሙ፤ ጨኸታችሁ ከጫጫታችሁ አይመዘገብ፤ ቂም አታውቁ በቀል፤ በእናንተ ዘንድ ዛቻ የለ ማስፈራራት፤ ፍርሀት የለ ጭንቀት፤ በዚች ምድር ሰላም ልትኖሩ የተፈጠራችሁ ሰላማዊ ፍጡሮች!» በማለት ብቻውን ሲነጋገር ከቆየ በኋላ ሀሳቡን ወደ ሰው ልጅ ባህሪና አኗኗር መለስ ሲያደርገው ጭራሽ አስጠላው።

«ያልታደለ ፍጡር» አለ በስጨት ባለ አነጋገር። ታየው የሰው ልጅ ክፋቱና ተንኮሉ፤ ቂምና በቀሉ፤ ሸርና ምቀኝነቱ፤ ጠብና ጭቅጭቁ፤ ከሁሉም በላይ እብሪቱና ጭካኔው። በቃሉም ይገልፀው ጀመር «የአሳር ሸክም የተጫነ መከረኛ ፍጡር፤ ሰው! የቱንም ያህል ቢማር ቢመራመር ከራሱ ጋር መታረቅ ያቃተው ደካማ ፍጡር፤ ሰው! ፈጣሪው ራሱ እሱን በመፍጠሩ የተፀፀተበት ብቸኛ እንስሳ፤ ሰው!!» ካለ በኋላ ራሱን ወዘወዘ አድርጎ ወደ መሬት ጎንበስ አለና ያን የለመለመ ሳር ልብ ብሎ ይመለከተው ጀመር። ከሩቅ ሲያዩት ልምላሜው ያምራል። ስሩ ሲታይ ግን ብዙ ጥቃንጥት አለበት። የደረቁ ቅጠሎችና ጭራሮዎች እንዲሁም ልዩ ልዩ በርካታ ነገሮች ስር ስሩን ትብትብ አድርገው ይዘውታል። ይህ ሁኔታ ሔዋንን አስታወሰው።

«አንተ ለምለም ሳርና የኔዋ ሔዋን አንድ ናችሁ። ከሩቅ ሲያዩአችሁ ውብ ናችሁ። ፍጹም የደላችሁ ትመስላላችሁ። ሥር ሥራችሁንና ውስጥ ውስጣችሁን ግን ብዙ ችግር አለባችሁ። ሳትጠሩት የመጣባችሁ፤ ሳትፈልጉት የተዳበላችሁ፤ አቁሳይ ጥገኛ አለባችሁ። አንተን የጭራሮና የቅጠል ርጋፊዎች ሥርህን ተብትበው እንደ ያዙህ ሁሉ የኔዋ ሔዋንም የአፈቀረ ልቧን የሚወጋ የስሜት እሾህ አለባት። ለመውደድና ለመወደድ የተፈጠረች ቆንጆ ነበረች። ግን እሾሁ ጋረጣው በዛብትና መንፈሷ ቆሰለ። በእፈቀረች ተሰቃየች። ማልቀስና መተከዝ ዕጣ ፋንታዋ ሆነ።» እያለ ሲያሰብ በዚያው ያ በቅዠት ውስጥ ያየው ሁኔታዋ ትዝ አለው። ድንግጥ ብሎ እንደ መደንበር አረገውና ከተቀመጠበት ጉቶ ላይ ብድግ አለ። ሳያስበው በዚያ በለመለመ ሳር ላይ ይዘዋወር ጀመር።

እጆቹን በጆርባው ላይ አጣምሮ ጎንበስ በማለት በግምት ከአስር እስከ አስራ አምስት ርምጃዎችን ከተራመደ በኋላ በግራ በኩል ወደ መንገዱ ቦር ብሎ ሲያይ አንድ ለየት ያለ ነገር አየ። በመንገዱ ላይ ስዎች አሁንም ወደ ላይም ወደ ታችም አቅጣጫ ይጓዳሉ። ነገር ግን ከመንገደኞቹ ለየት ባለ አኳኋን አንዲት በጆርባዋ ዓዝ የያዘች ሴት ቆማ እሱን እሱን ስትመለከት አያት። ‹ያኔኳ እብድ መሰያት ያሆናል› አለና ዝም ብሎ ርምጃውን ቀጠለ። ደግሞ ሲያያት አሁንም ታየዋለች። ሰራሱ

ገርሞት ቀና ጎንበስ እያለ ሲያያት ሴትዮዋ ንቅንቅ አትልም። ድንገት ደግሞ ድምጽ ሰማ «ጋሽ እስቻለው...» የሚል የጥሪ ድምጽ።

«እንዴ!» አለና እስቻለው እንደ መገረም ብሎ ጆሮውን ጣል አድርጎ ሲያዳምጥ አሁንም «ጋሽ እስቻለው» ስትል ተጣራች ሴትዮዋ።

«ምንድነው ነገሩ?» በማለት ከራሱ ጋር እየተነጋገረ ቆም ብሎ ወደ ሴትዮዋ ሲመለከት አሁንም «ጋሽ እስቻለው አይደለህም እንዴ?» ስትለው ሰማ።

«በዚህ መንገድ የምታልፍ የገጠር ሴት እንዴት ልታውቀኝ ቻለች?» በማለት እየተገረመ «አዎ ነኝ። አንቺ ግን ማነሽ?» ሲል ከርቀት ጠየቃት።

ሴትዮዋ ‹እኔ እንጃ?› ከማለት ይልቅ ጓዟን ከጆርባዋ ላይ አውርዳ ቁጭ አለች። ከሩቅ ሲያያት የምታለቅስም መሰለችው። አሁንም ግራ እያገባው «ማነሽ አንቺ?» እያለ ተጠጋት። በተጠጋት ቁጥር እያለቀሰች መሆኗ በደንብ ታየው። አሁንም ተጠጋት። «ምን ሆንሽ ነው ሴትዮ?» ሲል ሽንጥና ሽንጡን ይዞ አጠገቧ በመቆም ጠየቃት።

«አላወቅከኝም?» አለችው ሴትዮዋ።

«ማን ብዬ ልወቅሽ?»

«ትርፌ ቢጋሻው ነኝ።» አለችና እንባዋ በጉንጯ ላይ ድንገት ብሎ ወረደ።

«እ?» አለ እስቻለው በድንጋጤ አፉን ከፍቶና ዓይኑን በሴትዮዋ ላይ አፍጥጦ «የኔ ትርፌ ቢጋሻው?» እንደገና።

«አዎ»

ያቺ ለሦስት ዓመታት ያህል ቤቱን ቅልጥፍጥፍ አድርጋ በመያዝ ምቹ የወንደ ላጤ ህይወት እስለምዳው ነገር ግን ድንገትና በማያውቀው ምክንያት ከአንድ ዓመት በፊት ጥላው የጠፋችው የቤት ሰራተኛው ናት።

«እንዴት ሊሆን ይችላል?» አለ እስቻለው በሁለት እጆቹ ጉንጮቹን ይዞ።

«ሆን ጋሽ እስቻለው።» አሁንም እያለቀሰች።

እስቻለው ለጊዜው ልክ ያን ቀደም ሲል ያየውን የቀን ቅዠት ዓይነት ስሜት ተሰማውና ለሴኮንዶች ያህል ተጠራጠረ። ግን ደግሞ ወዲያው ወደ ትርፌ ጠጋ በማለት እቅፍ አድርጎ ሳማትና «ከየት እየመጣሽ ነው?» ሲል ጠየቃት።

«ከባላገር?» አለች ትርፌ አጎንብሳ አሁንም እያለቀሰች።

«ለምን ሄድሽ?»

«ቀን ጎድሎብኝ።»

ትርፌ ቀን የጎደለባት ስለመሆኗ ገጽታዋ ያስታውቃል። ቀይ የነበረው ፊቷ ማድያት አልብሶት ተኰርኩሯል። የለበሰቻቸው ቀሚስና ነጠላ ውሃ ነክቷቸው የሚያውቁ አይመስሉም። ፀጉሯ እብቅ የነሰነሰበት ይመስላል። ዓይኖቿም ጎድጉደዋል። የጉንጮቿ አጥንቶች በጎይኗ ሥር ሸሎዋል። አንገቷ ላይ የሚታየው የሰውነት ስሯ ጎዶ ሰርቷል። በቃ! የድሮዋ ትርፌ አይደለችም፤ ተቀይራለች። እስቻለው የሆነ ሁሉ ሁኔታዋን ዓይቶ ሆዱ አዘነና ከንፈሩን መጠጥ አድርጎ «አሁን ታዲያ ከተማዉሽ ወዴት ነው?» ሲል ጠየቃት።

«በቃ! እግሬ እንዳደረሰኝ።»

እስቻለው የባሰ አዘነ። ከመጎሳቆሏ በተጨማሪ የተስፋ መቁረጥ ንግግሯ አንጀቱን በላው። ጓዟን አሳዘላትና እጇን ይዞ ወደ ከተማ መንገድ ጀመሩ። ብዙ ተጉዘው ወደ ከተማዋ ጫፍ ሲደርሱ ሲሉ ትርፌ ከእስቻለው ግንባር ላይ ተፈጥሮ

የነበረውን ጠባሳ በዓይኗ ሰለል ስታደርግ ቆይታ ኖሯልና «ግንባርህን ምን ሆነህ ነው ጋሽ አስቻለው? ሰው መታህ?» ስትል ጠየቀችው::

«የጉልበተኛ ዘመን አይደል፤ ተደባዳቢ ምን ይጠፋል ብለሽ?» አለና «እስቲ ቆይ ቤት ስንደርስ እናወራዋለን::» ብሏት አሁንም ገሰገሰ ወደ ከተማ:: አስቻለው ትርፌን ይዞ ከቤቱ ሲገባ ከቀኑ አስራ አንድ ሠዓት ሆኗል::

ልክ እንደ ቀድሞው አተማመጣቸው አስቻለው ጠረጴዛና ወንበር ላይ፣ ትርፌ ደግሞ ከእሱ ፊትለፊት ጓሏን እንዳዘለች ዱካ ላይ ቁጭ አሉ:: አስቻለው የትርፌን መልክ በዘዘን ዓይን ሲመለከት ትርፌ ደግሞ ድሮ ትጠቀምባቸው የነበሩ የአስቻለውን የቤት ቁሳቁሶች በዓይኗ ሰለል ታደርጋቸዋለች:: አብዛኞቹ እሷ እንዳስተመጠቻቸው ናቸው:: በአቧራ ቁሽሽ ብለዋል:: ሸረሪት ያደረባቸው ይመስላሉ:: እሷ ከሄደች ወዲህ የተነኩ ወይም የተገላበጡ አይመስሉም:: በልሁና መርዕድ ጫት ሲቅሙ የሚጠቀሙባቸው ብርጭቆዎች ብቻ ያብለጨልጫሉ::

«ሚስት አላገባህም ጋሽ አስቻለው?» ስትል ትርፌ ጠየቀችው::

«ችግር መች ፈታችኝና ሚስት ልደርብባት ብለሽ ነው ትርፌ::» ካለ በኋላ «ለምን ጓዝሽን አታወርጂውም?» አላት ጉንጩን ደገፍ አድርጎ እየተመለከታት::

ትርፌ የነጠላዋን ቋጠሮ ፈትታ ጓዟን አወረደች:: ከአጠገቧ ቁጭ አድርጋው መሬት መሬት ታይ ጀመር:: ሀፍረትና መሳቀቅ የተሰማት ትመስላለች::

«ግን እንደው ትርፌ!» አላት አስቻለው ረጋ ባለ አነጋገር:: «ምን በደልኩሽና ድንገት እልም ብለሽ ጠፋሽ?» ሲል በትህትና ጠየቃት::

«ምንም ጋሽ አስቻለው?»

«አንድ ነገርማ መኖር አለበት::»

«ቢኖርም ከኔ እንጂ ከአንተ አልነበረም::»

«እስቲ እሱንም ቢሆን ንገሪኝ::»

«ተታለልኩ::»

«ማነው ያታለለሽ?»

«ያኔ አንተም የምትመገብበት፣ እኔም እሰራበት የነበረ ውቴል ውስጥ ከጎረቤት እየመጡ ከውቴሉ ባለቤት ጋር ቁጭ የሚሉ ወፍራም ሴት አልነበሩም?»

«አዎ»

«ገና እዚያው ውቴል ቤቱ ውስጥ እያለሁ እንደ ቀልድ እያረጉ ‹ይቺን ሰራተኛሽን ስጪኝና ለወንድሜ ልጅ ልዳራት› እያሉ የውቴሉን ባለቤት ይጠይቋቸው ነበር::»

«እሺ!» አለና አስቻለው ፈገግ እያለ ያያት ጀመር:: የትርፌ ወሬ ወዴት እንደሚያመራ ከወዲሁ ገባው::

«አንተ ጋ ከገባሁ በኋላም ባገኙኝ ቁጥር ይጨቀጭቁኝ ነበር»

«ምን እያሉ?»

«‹ወንድሜ አንድ ብቻ ወልዶ ሞቶብኛል:: ልጁ የአባቱን ሀብት ብቻውን ወርሶ ሀብታም ሆኗል:: ሚስት የለውም:: እኔ የምፈልጋትን ሴት ሊያገባ ቃል ገብቶልኛል:: እኔ ደሞ ለእሱ የምመኘው አንቺን ነው:: አንቺም የሰው አገር ሰው ስለሆንሽ ሁነኛ ሰው ያስፈልግሻል:: ልጅ ወልደሽ ዓይንሽን በዓይንሽ ማየት ይኖርብሻል:: የሰው ቤት ኑሮስ እስከ መቼ ይዘለቃል?› እያሉ::»

«ብቃ! እሺ አልሻቸው ማለት ነው?»

«መስሎኝ ተታለልኩ::» አለችና ትርፌ አሁንም እንደቀረቀረች ዓይንና አፍንጫዋን በለበሰችት ቁሽሽ ያለች ነጠላ ትጠርግ ጀመር::

«ከየት ወሰዱሽ ታዲያ?»

«ከገበያ ላይ::»

አስቻለው በመገረም ዓይነት ራሱን እየወዘወዘ ለአፍታ ያህል ሲመለከታት ቆየና «ታዲያ ሀብታሙ ገበሬ እንዴት አድርጎ ቢይዝሽ ነው እንዲህ ያማረብሽ» ሲል በምፀት አነጋገር ጠየቃት::

«ምንም አልተጠቀምኩም ጋሽ አስቻለው!»

«ሀብት የለውም?»

«ሙልጭ ያለ ድሀ ነው»

አስቻለው ድንገት «ቲ-ቲ-ቲ-ቲ» ብሎ ሳቀና «እንዴት?» ሲል ጠየቃት::

«ቀድሞ ነገር የእሱ የሆነ ምንም ነገር አልነበረውም:: ላሞች ቢኖሩም የእናቱ ናቸው:: እሳቸው ‹እነዚህን ላሞች በደንብ ተንከባከቢ፤ እንዷ ስትወልድ ጥጃዋን ለአንቺና ለባልሽ እሰጣችኋለሁ› ይሉኝ ጀመር፤ ላም ወልዳ ጥጃው አድጎ ልጠቀም!»

«ታዲያ ወዲያው ጥለሽው አትመለሽም ነበር?»

«ምስጢሩ እስከሚገባኝ ድረስ ለካ እርግዝና ኖሯል:: መሄጃው ጨነቀኝ::»

አስቻለው ድንግጥ አለና «ብቃ ወልደሻላ?»

«ግን ገና በአንድ ወሩ ሞተብኝ::»

«በስመ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ......!ህዘንተኛ ነሽ?»

«እማገባነው ግን ለራሱ ነው፤ ልጁማ ተገላገለ::»

«አይዞሽ!» አላት አስቻለው:: ከመቀመጫው ብድግ አለና ወደ ትርፌ ጠጋ በማለት «ቢያንስ አይርብሽም:: ፈቃደኛ ከሆንሽ ከኔው ጋር ትኖሪያለሽ::» አላትና እንደገናም «ቅር ይልሻል?» ሲል ጠየቃት::

ትርፌ ዓይኖቿን በእንባ ሰማይ አስመስላ ወደ አስቻለው ቀና በማለት «እታምነኛማ ጋሽ አስቻለው?» አለችው ሽቁጥቁጥ እያለች::

«ዘርፈሽኝ አልሄድሽም እኮ! አይዞሽ አትፍሪ::» አላትና ወደ መቀመጫው ተመልሶ ቁጭ አለ:: ግንባሩን ወደ ጠረጴዛ ደፍቶ ያስብ ጀመር::

ሰዓቱ ወደ አስራ አንድ ተኩል ተጠጋ:: አስቻለው የራት ነገር ትዝ ሲለው በትድሚያ ለእሷ በሳህን ሊያመጣላት አሰበ:: ከቤት ወጣ ሊል ሲል «እስቲ የሚበላ ነገር ላምጣልሽ፤ እስከዚያው ገላሽን ተጣጥበሽ ጠብቂኝ» አላት::

«ምግብ ይገኛለሁ እኮ!» አለችው ትርፌ ቀና ብላ እያየችው::

«እስቲ ምን ይዘሻል?»

ትርፌ ጓሏን ፍትት አደረገችና በሌላ እርጌ ጨርቅ የተቋጠረች ነገር አወጣች:: ያቺንም ፈታታችና ከውስጧ በቁጥር አምስት የሚሆኑ ድርቅ ያሉ ቂጣ የሚመስሉ ነገሮች እያሳየችው «ይኸው!» አለችው::

አስቻለው አሁንም ሆዱ አዘነና «እሱን ነገ ትበይዋለሽ፤ ለዛሬ ግን መንገድ ላይ ውስሽ አንጀትሽ ስለ ታጠፈ ለስለስ ያለ ነገር ላምጣልሽ::» ብሏት ወጣ::

በግምት ከግማሽ ሰዓት በኋላ በዳንቴል የተሸፈነ ሳህን ይዞ ሲመለስ ትርፌ እነዚያን የቆሸሹ የአስቻለውን የቤት ዕቃዎች ሁሉ አውጥታ ግቢ ውስጥ ስታጣጥብ

አገኛት:: ደንግጦም ገርሞትም ቀጥ ብሎ በመቆም «ምነው ትርፌ? ምን ነካሽ? ከ ከነገ ወዲያ አይደርስም እንዴ?» በማለት ቆጣ ባለ ንግግር ተናገራት::

«ለምን ጋሽ አስቻለው? በጣም ነው እኮ የቆሸሸው:: እኔ ደግሞ አልደከመኝም::» አለችና ወደ እሱ ጠጋ በማለት በሹክሹክታ አነጋገር «ወዲያው አንተ እንደወጣህ አንዲት ልጅ መጥታ ቤት ውስጥ እየጠበቀችህ ነው::» አለችው::

«ምን ዓይነት ልጅ?» ሲል ጠየቃት ሆዱ እየጠረጠረ::

«ቆንጆ! በጣ...ም የምታምር!» አለችው ትርፌ ጥብቅ ባለ አነጋገር::

አስቻለው የልጅቷ ማንነት በትክክል ገባውና ትርፌን በፈገግታ እያት አድርጎት ወደ ቤት ሲገባ ሔዋንም በፈገግታ ተቀበለችው::

«ታዲያስ ሔዩ!» እያለ ሳህኑን ጠረጴዛ ላይ ከአስቀመጠ በኋላ «አዘናግተሽ መምጣት ጀመርሽ!» እያላት ሁለቱም በፈገግታ ተሞልተው ተሳሳሙ::

«ትርፌ!» ሲል አስቻለው ወደ ውጭ ተጣራ::

«አቤት!»

«ነይ እንጂ::»

ትርፌ የእጇን ውሃ እያራገፈች ወደ ቤት ስትገባ አስቻለው የሔዋንን አንገት አቅፎ፣ ሔዋን ደግሞ ወገቡን ያዝ አድርጋ ፎቶ እንደሚነሱ ሙሽሮች ፈገግ ብለው ቆመው ጠበቋት:: «ቅድም ስለሚስት ያነሳሽብኝ ነገር አልነበር፤ ይቻት እሙናዬ! ነይ ተዋወቂ::» አላት አስቻለው::

«ሔዋን - ትርፌ::» ተባብለው ተጨባበጡ::

«ያቺ የምወዳትና የማምናት ሰራተኛዬ እያልኩ ስነግርሽ የነበረችው ትርፌ በጋሻው ማለት ይቺ ናት ሔዩ!» በማለት ለሔዋን ከገለፀላት በኋላ ትርፌን ደግሞ «ስም አውጭላታ!» አላት ፈገግ ብሎ እያያት::

«እታለም ብያታለሁ::» አለች ትርፌ እንደ ማፈር እያለች::

«አመሰግናለሁ::» አለች ሔዋንም ሳቅ እያለች::

ሦስቱም ተሳሳቁ::

ትርፌ ወደ ስራዋ ስትመለስ አስቻለውና ሔዋን ወንበር ላይ ቁጭ አሉና «ቆየሽ እንዴ ከመጣሽ!» አላት አስቻለው::

«አም! እንዲያውም ልመለስ ስል ነው የመጣኸው::»

«ጠዋት ግን ለምን ቀረሽ?»

«ስላልተመቸኝ:: ግን ይኼው አካክስኩ አይደል!»

«አመሰግናለሁ:: ከቸኮልሽ ሂጂ ልሸኝሽ::» አለና አስቻለው ብድግ አለ:: ሔዋንም ብድግ ስትል ከንፈሮቿን ሳም ሳም አደረጋቸው::

አስቻለውና ሔዋን ልክ ከግቢ እንደወጡ በቀኝ በኩል እየት ሲያደርጉ በልሁና መርዕድ ጫት ይዘው ሲመጡ አዩአቸው:: ከዕራት በፊት ጫታቸውን እስተምጠው መቀመጫቸውን ሲያዘገጃጁ ነው::

በልሁ ከርቀት ሔዋንን መናገር ጀመረ:: «ትናንት አልመጣም ብለሽ ከላክሽ በኋላ አሁን የመጣሽበትን ምስጢር ሳታወጪ የሚለቅሽ የለም::» እያለ ሔዋንን ቀለደባት:: በልሁና መርዕድ ከአስቻለውና ሔዋን ጋር ደረሱና ተሳስመው ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ «ግን ትናንት ለምን አልመጣም ብለሽ ላክሽ? ምናልባት ያቺ እህትሽ የተለመደ መጥረጊያዋን አንስታብሽ ይሆን እንዴ?» ሲል ጠየቃት በልሁ ኮስተር ብሎ::

«ያ እንኳ አይደለም::» አለች ሔዋን መሬት መሬት እያየች::

«ሌላውስ?» አላት በልሁ በሔዋን ሁኔታ ተጠራጥሮ::

«ብቻ...» ብላ እንደ ማቅማማት ስትል በልሁ አሁንም አጥብቆ ጠየቃት::

«ንገሪኝ! እኔና እሷ መቸም...» ብሎ ሳይጨርስ ሔዋን ቸኩል ብላ አቋረጠችው:: ሸዋዬ በልሁን እንደምትፈራ በልሁም እንደማይወዳት ታውቃለችና የሁለቱን የባሰ መራራቅ ለማስቀረት ስትል ወደ አላሰበችው ነገር አመራች::

«እንግዶች ይመጣሉና የትም እንዳትሄጂ ብላኝ ነው።»

«ከየት የሚመጡ?» አላት አስቻለው::

«የዚሁ ከተማ ናቸው:: ባርናባስ የሚባሉት ሰውዬና የእሳቸው ጓደኛ ነው መሰል አንድ በድሉ አሸናፊ የሚባል ነው::» አለች በተለይ በልሁን እያየች::

«በድሉ አሸናፊ?» ሲል ጠየቃት በልሁ ግንባሩን ቋጠር አድርጎ::

«አዎ»

«መቼ ጀምሮ ነው እሱ ደግሞ ወደዚያ ቤት መምጣት የጀመረው?»

«ከአሁን በፊት ሁለት ጊዜ መጥቶ ከባርናባስ ጋር ጫት ቅመዋል::

በድሉ አሸናፊን አስቻለው፤ በልሁና መርዕድም ያውቁታልና እርስ በርስ ተያዩ:: በከተማ ውስጥ አሉ የተባሉ የህዝብ ተሽከርካሪዎች ባለ ንብረት የሆኑ ሰው ልጅ ነው:: ራሱም ባለ ሽራ ቶዮታ ይይዛል::

«ምን ብለው ከእንቺ ጋ አስተዋወቁሽ?» አላት አስቻለው ልቡ ተጠራጥሮ ለምትሰጠው መልስ እየጓጓ::

«ሀብታም፤ የሀብታም ልጅ ምናምን አሉኝ::»

«እሺ. ከዚያስ?»

«ዛሬ ደሞ ሁሉም ጫት ሲቅሙ ውለው የማታ ማታ ላይ ባርናባስና እት-አበባ እኔና ሰውየውን ‹ተጫወቱ› ብለውን ወደ ከተማ ወጡ:: ልክ እነሱ ሲወጡ ጀምሮ ሰውየው ‹ነይ አጠገቤ ቁጭ በይ› እያለ ይጨቀጭቀኝ ጀመር:: እምቢ ስለው እጄን ይዞ በመጎተት ፍራሽ ላይ ሊያስቀምጠኝ ሲሞክር አምልጨው ሮጬ እማማ ዘነብ ቤት ገባሁ::»

«ከዚያስ?» አላት በልሁ ጥርሱን ነከስ እያረገ::

«እዚያው ስቆይበት የቤቱን በር መለስ አድርጎት ወጣና ውጭ አቁሟት የነበረች መኪናውን አስነስቶ ሄደ:: እኔም እት-አበባና ባርናባስ አብረው ከወጡ እሷ ቶሎ እንደማትመለስ ስለማውቅ በዚች ቀዳዳ ብቅ ብዬ ልመለስ በማለት ወደዚህ መጣሁ::» አለች ሔዋን ዓይኗን በሁሉም ላይ እያንከራተተች::

አስቻለው፤ በልሁና መርዕድ አሁንም እርስ በእርስ ተያዩ:: በሸዋዬ ቤት ውስጥ ምን እየተካሄደ እንደሆን ሳይነጋገሩ፤ ነገር ግን በደንብ ተግባቡ::

ምዕራፍ ሰባት

ሳትታሰብ የተገኘችው ትርፌ በጋሻው ሰብዙዎች አስገኝታለች። ከሁሉም በላይ አስቻለው ተመችቶታል። ቤቱ ተዘግቶ አይውልም፣ አይዝረከረክም፣ አይመስቃቀልም፣ ትርፌ ሽክፍ አድርጋ ይዛዋለች። የሆቴል ምግብ ትቶ ቤቱ ውስጥ መመገብ ጀምሯል። እንጀራዊ የሆነ የመንፈስ መረጋጋት አግኝቷል። በልሁና መርዕድ እንኳ እንደ ወትሮው ፍራሽ በማንጠፍ፣ ከሰል በማያያዝና ሻይ ወይም ቡና በማፍላት ተራ መጨቃጨቃቸውን ትተዋል። ሒታቸውን ብቻ ገዝተው በተነጠፈና በተበጃጀ ፍራሽ ላይ እግራቸውን መዘርጋት ነው። ቀሪውን ስራ ትርፌ ታቀለጣጥፈው ይዛለች።

የትርፌ በአስቻለው ቤት ተመልሳ መግባት ለሒዋንም የዐጋ ያህል ሆኗል። ሒዋን የአስራ ሁለተኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ከወሰደች በኋላ በወቅቱ ግዴታ በነበረው የመሰረተ ትምህርት ዘመቻ ሥራ በመጀመሯ በከፊልም ቢሆን ከሽዋዬ ቁጥጥር ውጭ ሆናለች። አጋጣሚ ሆኖ የተመደበችው ደግሞ በዚያው በዲላ ከተማ በዜሮ ስምንት ቀበሌ ውስጥ በመሆኑ ከቤት ወደ ስራ፣ ከስራ ወደ ቤት የምትመላለሰው በአስቻለው ቤት በር ላይ ነው። እናም ስታልፍ ስታገድም ጎራ ትልበታለች። ትርፌ ስላለች ዘወትር ክፍት ነውና አትቸገርም። ይህ ሁኔታ በእሷና በትርፌ መካከል ያለውን ግንኙነት ይበልጥ አጠናክሮት መነፋፈቅም ጀምረዋል።

አንድ ቀን ደግሞ ሁለቱን ለረጅም ሰዓት አብሮ የሚያቆይ አጋጣሚ ተፈጠረ። የግንቦት ወር መጨረሻ አካባቢ ነው፣ ሒዋን መሰረተ ትምህርት በምታስተምርበት ጣቢያ አካባቢ አንዲት ሴት ሞተው በለቅሶው ምክንያት በዕለቱ ማስተማር እንደማትችል ከጣቢያ ሃላፊው ይነገራታል። ከጠዋቱ ሦስት ሠዓት አካባቢ ወደ ቤቷ ስትመለስ እግረ መንገዷን ወደ አስቻለው ቤት ጎራ ትላለች። ጊዜ ነበራትና ተረጋግታ ቁጭ በማለት ከትርፌ ጋራ ጭውውት ይጀምራሉ። ሒዋን በአስቻለው አልጋ ላይ ትራስ ደገፍ ብላ፣ ትርፌ ደግሞ በአልጋው ትይዩ በተነጠፈችው ፍራሽ ላይ ሆና ፊትለፊት እየተያዩ ይጫወታሉ።

«ትርፍዬ!» ስትል ጠራቻት ሒዋን።

«ወይ እታለም።»

«አገርሽ የት ነው?»

«ውይይ... እታለምዬ! በጣም ሩቅ ነው፤ ቢጠሩት እንኳ አይሰማም።»

ትርፌ የገጠር ኑሮዋ ባያጎሳቁላት ኖሮ ቀይና ስልክክ ያለች፣ ዓይንና ጥርሶቿ እዩኝ እዩኝ የሚሉ መልከ ቀና የነበረች ልጅ ትመስላለች። ያም ሆኖ አሁን ወደ አስቻለው ቤት ከተመለሰች ወዲህ ወዘናዋ እየተመለሰ መጥቷል።

«የት ቢሆን ነው ትርፍዬ?» ስትል ሒዋን ደግማ ጠየቀቻት የትርፌን ሁለመና እየት ሰለል እያደረገች።

«ወሎዬ ነኝ።»

«ውይይ... ከዚያ እዚህ ድረስ እንዴት መጣሽ?»

«ታሪኩ ብዙ ነው እታለም። ደግሞም ያሳዝናል።»

«እንዴት ትርፌ?»

«ቤቶ ያሳዝናል።»

«ከመጣሽ ግን ምን ያህል ጊዜ ሆነሽ?»

«ወደ አስር ዓመት ሊሆነኝ ነው።»

«ውይይ...» አለችና ሒዋን አሁንም «ግን እንዴት መጣሽ?» ስትል ጠየቀቻት።

«ተጣጥዬ»

«ማለት?»

«የወሎ ድርቅ ሲባል ሰምተሽ ታውቂያለሽ?»

«አዎ!»

«በድርቁ ዘመን እኔ ህጻን ልጅ ነበርኩ። የተወለድኩትም ውጫሌ እሚባል ቦታ ነው። ያኔ በድርቁ ጊዜ በአገሩ ላይ የሚበላም የሚጠጣም ጠፋ። የአገሩ ሰው ሁሉ ተንቀሳቀሰ ተሰደደ። አባቴ በድርቁ ምክንያት ቀደም ብሎ ሞቶ ስለነበር እኔና እናቴም ሕዝቡ ሲሰደድ አብረን ተሰደድን።»

«ወደ ሲዳሞ?»

«ወደዚሁ ደሴ ወደሚባል ከተማ ነው።»

«አይደለም፣ እዚያ የሚበላና የሚጠጣ አገኛችሁ?»

«ታዲያ እዚያ የሚበላና የሚጠጣ አገኛችሁ?»

«ታዲያ እታለም! ምን ይገኛል ብለሽ? ጣጣው ብዙ ነበር።» አለችና ትርፌ «እየየ... እታለም! ባህር ውስጥ ገባች። ያን በልጅነት አዕምሮዋ የተቀረፀ የርሀብ አሁንም በትካዜ ባህር ውስጥ ገባች። ያን በልጅነት አዕምሮዋ የተቀረፀ የርሀብ ሁኔታ የቻለችውን ያህል ለማስታወስ ትሞክር ጀመር። ትርፌ በዚያን ጊዜ ገና የስድስት ወይም ሰባት ዓመት ህጻን ስለነበረች ሁሉን ነገር አታውቀውም እንጂ ሁኔታው እጅግን አሳዛኝ ነበር።

አዎ፣ እንደ ሰው ጨክኗል፣ የወሎ ሰማይ። ከዝናብ ሰጪ ደመናዎች ጋር ላይታረቅ የተጣላ ይመስል ቁልጭ ጥርት እንዳለ ድፍን ሶስት ዓመታት አለፉ። በሐይና ጨረቃ ስእንዶ እንኳ በደመና ውስጥ ብቅ ጥልቅ እያሉ የእየሁሽ ጨዋታ ሳይጫወቱ በጠራው ሰማይ ላይ ተንቀሳቀሱበት። በተለይ ፀሐይ በየቀኑ እሥራ ሁለት ሰዓት ሙሉ እየነደደች የወሎን ምድር ታነደውና ታቃጥለው ጀመር። ወንዞች ነጠፉ። ሳር ቅጠሉ ደረቀ። ዛፎች ወደ ጭራሮነት ተቀየሩ። ቢመጣ ንፋስ፣ ቢነሳ አቧራ ብቻ ሆነ።

የወሎ ገበሬ የመጀመሪያውን የድርቅ ዓመት ቀድሞ የነበረውን ጥሪት ተጠቅሞ ሳይደናገጥ ተወጥቶት ነበር። የሁለተኛው ግን ወገቡን ሰበረው። ሶስተኛው ደግሞ ከሥሩ ነቀለው። እንኳን ለራሱ ለሰንጋ ፈረሱ የእህል ዓይነት ይመርጥ እንዳልነበረ ሁሉ እንኳን ያቀምሰው የሚቀምሰውም አጣ። በሰንጋ ፈረስ ይጋልብ የነበረ የወሎ መኳንንት፣ በሲናር በቅሎ ስትፈስ የነበረች የወሎ ወይዛዝርት ሁሉ እርካባቸው ወለቀ። ግላሳቸው ተጠቀለለ። በቅሎና ፈረሶቻቸው የአውሬና የአዕዋፍ ሲሳይ ሆኑ። አጥንቶቻቸው ሜዳ ሙሉ ተረጩ። የረገመው ሳይታወቅ ወሎ ምዕዓት ወረደበት። የረሀብ እሳት ያቃጥለው ጀመር። በቸነፈር ተመታ።

በዚያን ጊዜ፣ በዚያን ዘመን፣ የወሎ ሕዝብ ምርጫው አንድ ብቻ ነበር፣ ስደት። አቅጣጫው ደግሞ ወደ ደሴ ከተማ። ይህም ምክንያት ነበረው። የወቅቱ

ንጉሥ ለጉብኝት ደሴ ከተማ እንደሚገቡ ተወርቶ ነበር። እሳቸው ደግሞ በዚህ ሁሉ ለልጆች ከረሜላ በመርጨታቸው ብቻ የቸርነት ዝናን ያተረፉ ነበሩና የወሎ ርሀብተኛ ወደ ‹ቸሩ› ንጉሥ በመሄድ የልመና እጆቹን ለመዘርጋት ጓር ከደር ተንጋግሮ ወደ ደሴ መንገዘ መትመም ጀመረ።

ከሰሜን አቅጣጫ የራያና የየጁ ሕዝብ በርሀብ የመነመነ ሰውነቱን በእርዛ ብጥቅጣቂ ጨርቅ እየሸፈነ ሰንሰለት ሰርቶ ወደ ደሴ ሲግተለተል የአምባሰል ተራሮች ቁልቁል እየተመለከቱ ይታዘቡ ነበር። ከምዕራብና ከሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ የቦረና፣ የወረሂመኖ፣ የሳስታና የወገልጤና ሕዝብ ተንቅንቆ ወደ ደሴ ሲጓዝ በመሀል እየደመከው በገራዶና በቦሩ ሜዳ ላይ ሲፈስ የጦሳ ተራራ መሀል ላይ ቆሞ ግራና ቀኝ እየተመለከተ ያለቅስ ነበር። ከምስራቅና ከደቡብ ምሥራቅ ደግሞ የአውሳ፣ የቃሉ፣ የእንቻሮና የከሚሴ ሕዝብ በበረሃ አሰባበስ ዘይቤው ከወገቡ በታች ሸርጥ መሳይ አገልድሞ ከወገቡ በላይ ሲያዩት ግጠው ግጠው የጣሉት አጥንት መስሎ ወደ ደሴ ሲተምም የቦርከና ወንዝ ‹እናንተስ ወደ ንጉሳችሁ ሄዳችሁ፣ የእኔንስ ችግር ለአባይና ለተከዜ ማን ይንገርልኝ› እያለ የሚያገነ ይመስል ነበር። በጋ ከክረምት የውሃ ፈረሰኛ ሲያጓራበት እንዳልነበረ ሁሉ ያኔ ግን ከው ብሎ ደርቋልና በውስጡ የነበሩ ቋጥኞች ጨዉ መስለው የፀሐይ ንዳድ እየፈኳቸከታቸው ነበር።

ያ ሁሉ የወሎ ርሀብተኛ በዚህ መልክ ተጉዞ ተጉዞ ደሴ ከተማ ሲደርስ ያሰበው አልሆነለትም። እንዲያውም ወደ መሀል ደሴ ከተማ መግባት እንኳ ሳይፈቀድለት ቀረ። የንጉሡ ፊጥኖ ደራሽ ፖሊሶች በየመግቢያው አቅጣጫ ተሰልፈው ጠበቁት። ከሰሜን በኩል የመጣውን በሮቢት ገበያ ላይ፣ ከምዕራብ በኩል የመጣውን በሰኞ ገበያ ላይ፣ እንዲሁም ከምስራቅና ከደቡብ ምስራቅ አቅጣጫ የመጣውን ርሀብተኛ ሀረጎ አፋፍ ላይ በተሰራ የእንጨት አጥር ውስጥ አያስገቡ አጎሩት። በቀን አንዳንድ ዳቦ ለእያንዳንዱ ርሀብተኛ እንደ ውሻ ይጥሉለት ጀመር። እንዳይንቀሳቀስ ይጠብቁትም ጀመር።

ንጉሡ ደሴ ከተማ ገቡ። ከጦሳ ተራራ በስተ ደቡብ ምሥራቅ በኩል በምትገኝ ጎራ ላይ ተሰርቶ፣ ከስፋቱና የገባ ቢገባበት በቃኝ የማይል ከመሆኑ የተነሳ ‹አይጠግቤ› ተብሎ በሚታወቀው አዳራሽ ውስጥ በተመቻቸ መድረክ ላይ በተዘጋጀ ዙፋናቸው ላይ ተሰየሙ። ቤተሰባቸውና የቅርብ ዘመዶቻቸው ግራና ቀኝ ከጎናቸውና ከኋላቸው ተኮለኮሉ። መሳፍንቶቻቸው ደግሞ እንደየማዕረጋቸው ቅደም ተከተል ከፊትለፊታቸው ተደረደሩ። የንቁ የበቁ አስተናጋጆች ነጠላቸውን አሸርጠው ያጋፍሩ ጀመር። እየተበላ እየተጠጣ ይሸለል ይፎከር ጀመር። ምድር ቀውጢ ሆና የሚዘለልባትን ያህል እሷም ተንተጠቀጠች።

በዚህ ጊዜ ደሴ ከተማ ሁለት ተቃራኒ ትዕይንቶች በተመሳሳይ ሰዓት የሚከናወኑባት አንድ መድረክ ሆነች። በአንድ በኩል አፍንጫ ከሚቆርጥ ቂይና አልጫ ወጥ በተጨማሪ ጮማ እየተቆረጠ፣ ከጠጅ እስከ ውስኪ እየተጠጣና ሻምፓኝ እየተረጨ በፌንጠዚያ ጮቤ የሚረገጥባት ምድራዊ ገነት፤ በሌላ በኩል ደግሞ የቀን ሀሩር እያቃጠለው፣ የሌሊት ቁር እየጠበሰው እንደ ከብት በበረት ውስጥ ታጉሮ በርሀብ አለንጋ በመገረፍ ላይ ካለ ሕዝብ የስቃይ ጩኸት የሚሰማባት

ሲኦል!! ደሴ ከተማ አበነች። ለጉሮ አመቺ ከመሆኗ የተነሳ ሕናት ከተማ፣ ተብላ የምትታወቀው ደሴ እውነትም በሕዝቧ የስቃይ ጩኸት የእናትነት ሆዷ ተንሰፍስፎና እንደ ሰው አለቀሰች።

የአያጠየፉ ትዕይንት አስተላለትም ሌላው የወቅቱ አስገራሚና አሳዛኝ ክስተት ነበር። ንጉሡ ባላምባራሱን ግራ አዝማች፣ ግራዝማቹን ቀኝ አዝማች፣ ቀኝ አዝማቹን ፊታውራሪ፣ ፊታውራሪውን ደጃዝማች፣ ደጃዝማቹን ራስ… ወዘተ እያሉ ከሹመት ከሽልሙ በኋላ በሚያደርጉት አጭር የመዝጊያ ንግግር መሀል የወሎን ርሀብ ጉዳይ አንስተው አንድ ነገር ሊሉ እንደሚችሉ ተጠብቀው ነበር። እሳቸው ግን ወደ ትጉናሽ!! ይልቁንም ያኔ በማይጨው ጦርነት ጊዜ ተሸንፈው ወደ አዲስ አበባ በሚሸሹበት ወቅት የወሎ ሕዝብ ‹እኛን ለጥቃት፣ አገርህን ለጠላት ሰጥተህ ወዴት?› በማለት መንገድ ዘግቶ አሳልፍ ብሏቸው የነበረ ከመሆኑም በላይ ጥሰው ለማለፍ ሲሞክሩ ተዋግቷቸውም እንደነበረ በማስታወስ ሳይሆን አይቀርም ‹ወሎን በድጉም በክፉውም ቀን እናውቀዋለን› በማለት ተሳልቀውበት ነበር በማግስቱ ወደ ዙፋን ማዕከላቸው ወደ አዲስ አበባ የተመለሱት።

ወሎ ተከዳ። አዎ ወሎ፣ ምርቱን በጉድጓድ፣ ዱቄቱን በጎተራ ይከት የነበረ! በሩህሩህነቱና በቸርነቱ ይታወቅ የነበረ ወሎ አባ መስጠት! ከፋትና ተገክል! ሸርና ምቀኝነት የማያውቀው፤ በገርነቱና በየዋህነቱ ታውቆ ‹ወሎ መጆን› እየተባለ ሲመጀንበት የሚኖር አገር ወሎ! እንኳን አዛውንቱ እረኛው ትንቢት የሚናገርበት የነቢያት አገር ወሎ! የግሸን ቁሳውስት እንዲሁም የሳስታ፣ የእንቻሮ ኢማሞች እንዲሁም የቃሉ አብረው የሚኖሩበት፣ የፍቅርና የመቻቻል አገር፣ አብሮ የመኖር ተምሳሌት ወሎ! ሰውም አምላኩም በአንድነት ከዱት። በመከራው ጊዜ ደራሽ አጥቶ የሰው ልጅ እንደ ቅጠል ረገፈ፣ በርሀብ!!

ትርፌ ግን ይህን ሁሉ ሁኔታ በዝርዝር አታውቀውም። ግን ደግሞ የችግሩ ወላፈን ጠብሷት ነበርና የምታውቀውንና የምታስታውሰውን ያህል ለሔዋን ለማጫወት እስባ ከትካዜዋ ብንን አለች።

«ምን መሰለሽ እታለምዬ!» ስትል ቀጠለች። «እኔና እናቴ ከሕዝቡ ጋር መጥተን ደሴ እንደ ደረስን ሮቢት በሚባል የገበያ ቦታ ላይ በእንጨት በታጠረ ግቢ ውስጥ እንድንገባ ተደረግን። ከዚያም ትንንሽ ዳቦ በቀን አንዴ ይታደለን ጀመር። እናቴ ግን ያቺን የድርሻዋን ዳቦ ብዙ ጊዜ ለኔ ነበር የምትሰጠኝ፣ ለኔ በግል የምትደርሰኝን ‹አታጠግብሽም› በማለት።» አለችና ትርፌ እንባዋ በዓይኗ ላይ አቀረረ። ንግግሯን ግን ቀጠለች።

«ከጥቂት ቀናት በኋላ ደግሞ እናቴ ደከመችና መላወስም እያቃታት ሄደ። አንድ ቀን ጠዋት ከእንቅልፌ ስነቃ እሷ ተኝታ ቀረችብኝ። በመሀል ዳቦ የሚያድሉት ሰዎች መጡና ለእሷም ለኔም ትቀበልልኝ ዘንድ ልቀሰቅሳት ብሞክር አለሰማ አለችኝ። ሰውነቷን ገፋ ገፋ ሳደርጋት መላ ሰውነቷ አብሮ ይንቃነቅ ጀመር። በጩኸት ስጠራት የሰማ አንድ ሰው ጠጋ ብሎ እናቴን ካያት በኋላ ‹ቢቃ ተያት እሷ፣ ተገላግላለች› አለኝ። ለካስ እናቴ ሞታ ኖሯል።» አለችና ትርፌ ድንገት «እማይዬ…!» ብላ ጮኸች።

ሔዋን በእስከ አሁኑ የትርፌ አተራረክና በዓይኗ እንባ ማቅረር ምክንያት አንጀቷ እየተላወሰና እሷንም እንባ እንባ ሲላት እንደነበረ ሁሉ እንደገና ስትሮጥ ድንግጥ ብላ ከአልጋው ላይ ተስፈንጥራ ተነሳችና ወደ ትርፌ እየተራመደች

«ተይ ትርፍዬ!» አለቻት። ነገር ግን በልመናዋ አልገፋችበትም፣ ራሷ የእናት ነገር ጥናዋ ነውና በትርፌ እናት ላይ የደረሰው ሁሉ ልክ በእሷ እናት ላይ የደረሰ ያህል ተሰምቷት የትርፌን አንገት አንቅ አድርጋ ይዛ አብረው ይላቀሱ ጀመር።

ትንሽ ቆይተው ተላቀቁ። ሔዋን በትርፌ አጠገብ ቁጭ ብላ ልታፅናናት ሞከረች። ትርፌ ግን እንባዋን እያፈሰሰች ትረካዋን ቀጠለች።

«ከዚያ በኋላ እታለምዬ! ምን ሆነልሽ መሰለሽ፣ ረፋዱ ላይ አንድ መኪና መጣ። የእናቴን አስከሬን ጭነው ወሰዱት። እኔም ያለ እናት ቀረሁ። ከጥቂት ቀናት በኋላ ከዚያ ግቢ አውጥተው ወሰዱኝ። እሄድኩበት ቦታ ብዙ ህፃናቶች ነበሩ። ከእነሱ ተቀላቀልኩና እንጀራ በወጥ መብላት ጀመርኩ።» አለችና ዓይኗንም አፍንጫዋንም ትጠራርግ ጀመር።

«እዚያው አሳደጉሽ?» ስትል ሔዋን ጠየቀቻት።

«አንዳንድ ሰዎች ወደ ህፃናቱ እየመጡ ደስ ያላቸውን እየመረጡ ይወስዱ ነበር። እኔም በዚያ ቦታ ላይ ጥቂት እንደ ቆየሁ አንድ ቀን አንዲት ሴትዮ መጣችና በልጆቹ መሀል ስትዘዋወር ቆይታ ወደኔ ጋ ስትደርስ ‹ይቺን ልጅ ልውሰዳት?› በማለት ህፃናት ጠባቂዎቹን ጠየቀቻቸው። ፈቀዱላትና ወደ ቤቷ ወሰደችኝ። እሷ ዘንድ ለአምስት ዓመታት ቆየሁ።»

«ከዚያስ?» ስትል ሔዋን አሁንም ጠየቀቻት። የትርፌ ታሪክና አኳኋን እያሳዘናት ከአንገቷ ገደድ ብላ በሀዘን ስሜት ትመለከታታለች።

«ከዚያ በኋላ ደግሞ ተማሪዎች በጠበጡ። እየተገደሉም በየመንገዱ ተዘርረው መዋል ጀመሩ።» አለች ትርፌ የወቅቱን የተማሪዎች የተቃውሞ ንቅናቄና የተፈፀመባቸውን የጭካኔ ግድያ በራሷ አመለካከትና ግንዛቤ መጠን ስትገልፀው። «ከተማሪዎች ጋር አንዳንድ ሰው እየተጃለፈ ይገደል ስለነበር አንድ ቀን የዚያች ታሳድገኝ የነበረችው ሴትዮ ባለቤትም ሞቶ ተገኘ። የዚያች ሴትዮ እህት እዚህ ዲላ ውስጥ ትኖር ኖሯል፣ ለለቅሶ መጥታ ደሴ ሰነበተች። ከአሳዳጊዬ ጋር ተመካክረው ኖሮ ስትመለስ ‹ተነሽ እንሂድ› ብላ እዚህ ዲላ ይዛኝ መጣችና የቤት ሰራተኛዋ አደረገችኝ።» አለች ትርፌ አሁንም እንባ እየተናነቃት።

«አይዞሽ ትርፌ!» አለቻት ሔዋን የትርፌ ሁኔታና ታሪክ እያሳዘናት።

ትርፌ ትረካዋን ቀጠለች። «በዚህ ሁኔታ ጥቂት ዓመታት ከቆየሁ በኋላ እኔም አደግሁ መሰለኝ፣ የሴትዮዋ ባል ባለፍኩ ባገደምኩ ቁጥር ይጎነትለኝ ጀመር። አንድ ቀን ደግሞ ሲተናነቀኝ ባለቤቱ ደረሰችና አየችው። ከዚያም እኔን አስወጥታ በአንድ ውቴል ቤት በእንጀራ ጋጋሪነት አስቀጠረችኝ። ከጋሽ እስቻለውም ጋር የተዋወቅኩት እዚያው ውቴል ውስጥ ስሰራ ነው። ጠባዩ ጥሩ ስለሆነ እወደው ነበር። እሱም እኔን እንደ ገረድ ሳይቆጥረኝ በትትና ነበር የሚያነጋግረኝ። በዚያ ቤት ትንሽ እንደሰራሁ አሁንም ከአሰሪዬ ጋር ሳልስማማ ቀረሁና ወጣሁ። ጋሽ እስቻለውን ስራ እንዲያስገባኝ ጠየኩት። ‹እሺ እፈልግልሻለሁ› ብሎ ቃል አደር ካለ በኋላ ‹እኔ ጋር

ብትሆኚበት› አለኝ። ‹ምን ገዶኝ!› አልኩት። ቢቃ! በተነጋገርን ከሁለተኛው ቀን ጀምሮ ከጋሽ እስቻለው ጋር መኖር ጀመርኩ።»

ሔዋን ከንፈሯን መጠጥ አድርጋ «ዲላ ውስጥ ምንም ዘመድ የለሽም?» ስትል ጠየቀቻት።

«ምንም እታለምዬ! የኔ ዘመድ ጋሼ እስቻለው ብቻ ነው፣ ምናልባት ከእንግዲህ ወዲያ አንቺ ትጨመሪልኝ እንደሆን እንጂ!» አለቻት።

ሔዋን ድንገት የትርፌን አንገት አንቅ አድርጋ በመያዝ ጉንጯ ላይ ሳም አደረገችና «ምንም አትጠራጠሪ ትርፍዬ፣ እህት እሆንሻለሁ።» አለቻት።

ትርፌ አሳዛኝ ታሪኳን ስትተርክ፣ ሔዋንም በአንክሮ ስታዳምጥ፣ ሳያውቁት ሰዓቱ ሄዶ ኖሯል፣ ልክ ከቀኑ ስድስት ሠዓት። ያ ሰዓት ደግሞ እንደ ወትሮው ቢሆን ሔዋን ከቤቷ መድረሻዋ፣ ትርፌ ደግሞ ከቀኑ ዘጠኝ ሠዓት ከስራ ወጥቶ ወደ ቤት ለሚመጣው እስቻለው የምሳ ዝግጅት ማጣደጃዋ ነበር። የሰዓቱን መድረስ ሁለቱም ሲያውቁ ድንገት ስሜታቸውን ቀየሩ፣ ሔዋን ወደ ቤቷ ለመሄድ፣ ትርፌ የምሳ ዝግጅት ለመጀመር ከተቀመጡበት ብድግ ብድግ አሉ። ሔዋን ትርፌን ተሰናብታ ከቤት ልትወጣ ስትል ትርፌ እናገረቻት።

«ዛሬ የኔን ታሪክ ሰምተሻል እታለም። ሌላ ጊዜ ደግሞ አንቺና ጋሼ እስቻለው እንዴት እንደተገናኛችሁና እንደተዋወቃችሁ ተራሽን ታወሪልኛለሽ እሺ!» አለቻት ፈገግ ብላ በዓይኗ እየተከተለቻት።

«እስከ አሁን አስቹ አልነገረሽም?» አለቻት ሔዋንም ዞር ብላ ትርፌን በፈገግታ አየት እያረገቻት።

«ምንም እታለምዬ! እኔ የማውቀው እያየሁት ያለውን ነገር ብቻ ነው፣ አለችና «ግን አንቺና ጋሼ እስቻለው መቼ ይሆን የምትጋቡት?» ስትልም እንደ ቀልድ ጠየቀቻት።

በዚያች ቅፅበት እስቻለው በር ላይ ደርሶ ኖሯል። ትርፌ ለሔዋን ያቀረበችውንም ጥያቄ ሰምቷል። ሔዋን ከመናገሯ በፊት ፈጠን ቀልጠፍ ብሎ «በቅርቡ ትርፌ! በጣም በቅርቡ። ግፋ ቢል ከሁለት ወይም ከሶስት ወራት በኋላ» እያለ ወደ ቤት ገባ። ትርፌና ሔዋን ፍጹም ያላሰቡት አጋጣሚ ስለነበር ሁለቱም ድንግጥ ድንግጥ አሉ።

ሔዋን ወዲያው «እንዴ አስቹ! በአሁኑ ሰዓት እንዴት መጣህ?» አለችው ፏ ብላ ፈገግ በማለት እየተመለከተችው።

«የአንቺን ቤቴ ውስጥ መኖር ቀልቤ ነግሮኝ» አላት እየቀለደ። ጠጋ አለና እንደ ቆመች አንገቷን አቅፍ አድርጎ ከንፈሮቿን ሳም አደረጋቸው። በእጁ ዳጎስ ያለ የጤ. ፖስታ ይዟል።

ለእስቻለው በዚያ ሰዓት መምጣት ሰበቡ ሔዋንን ከመሰረተ ትምህርት ስራ ያቋረጠ ለቅሶ ነው። ሚጂ የስራ ባልደረባው እናት ኖረዋል። ለስድስት ሠዓት ቀብር መጥቶ ነው። ከዚያ በኋላ ላለው አጭር የስራ ሠዓት ሲል ዲላ ሆስፒታል ድረስ ላለመሄድ ወስኖ ነው።

«ምነው ሔዬ በር ላይ ቆምሽ?» ሲል ጠየቃት።

«ብዙ ስለቆየሁ ወደ ቤቱ ልሄድ ተነስቼ ነው።» አስቻው በእጆቿ ደረቱን እየደባበሰችና ቀና ብላ ዓይኖቹን በዓይኖቿ እየተመለከተች።

«ለሌዩ ምን አደረግሽላት ትርፌ?» አለ አስቻለው ወደ ትርፌ ዞር ብሎ።

«ምንም ጋሼ አስቻለው፣ ጠራ ብቻ!»

«ምሳ በልተሽ ሂጂያ ሐዩ!»

«በፍጹም አስቹ፣ እትአበባ ከስራ መምጫዋ ስለሆነ ብሄድ ይሻላል።»

«ስሞት!»

«አይሆንም አስቹ! በአጋጣሚ መገናኘታችን በራሱ በቂ ነው።»

አስቻለው አሁንም ከንፈሮቿን ሳም ከአደረገ በኋላ «ብይ እሺ ከችኮልሽ ሂጂ!» አለና እስከ ውጭ በር ሸኝቶ ተሰናብቷት ወደ ቤቱ ተመልሶ ገባ።

አልጋው ላይ ቁጭ አለና ያን በእጁ ይዞት የነበረውን ካኪ ፖስታ በጥድፊያ ይከፍት ጀመር። ከአሜሪካ ካሊፎኒያ ግዛት ከዶክተር ደጀኔ አድማሱ የተላከለት ደብዳቤ ነው። አስቻለው ጫማውን አውልቆ አልጋው ላይ ወጣና ትራሶቹን አነባብሮ ከእንገቱ ቀና ብሎ በጀርባው ጋለል በማለት ደብዳቤውን ማንበብ ጀመረ።

«የምወድህና የማከብርህ እንዲሁም የምናፍቅህ ውድ ወንድሜ ኀርስ አስቻለው ፍስሀ! ከቶ ለጤናህ እንደምን አለህ? ፈጣሪ አምላክ ይመስገን እኔ በጣም ደህና ነኝ።

«የምወድህ አስቻለው፦ የመኪና አደጋ ደርሶብህ እንደነበር አውቃለሁ። አደጋው በደረሰ በስተኛ ቀን በተኛህበት ሆስፒታል ተገኝቼ ልጠይቅህም ሞክሬ ነበር። በወቅቱ ራስህን አታውቅም ነበርና፣ እኔ ደግሞ የበረራ ፕሮግራሜ በማግስቱ ስለነበር ሆዴ እያዘነ ትቼህ ሄጃለሁ። ይሁንና ከኢትዮጵያ አየር ክልል ወጥቼ፣ በሱዳንና በግብጽ እንዲሁም በሜድትራኒያን ባህር፣ ከዚያም በአውሮፓ ሰማይ ላይ ተንሳፍፌ በበረራ ላይ በነበርኩበት ጊዜ ሁሉ ስለ አንተ እያሰላሰልኩ ነበር። አሜሪካም ከገባሁ በኋላ የአንተ ነገር ከአዕምሮዬ አልወጣ ብሎኝ ለቀናት ያህል ተሰቃይቻለሁ። የኋላ ኋላ ግን ከአደጋው ሙሉ በሙሉ አገግመህ ወደ ስራህ የመመለስህን ዜና ስሰማ አምላኬን ከልብ አመሰግኜለሁ። ወደፊትም ፈጣሪህ ከሁሉም ነገር እንዲጠብቅህ እፀልያለሁ።

«ውድ ወንድሜ አስቻለው፦ መቸም ደብዳቤዬ እንደ ደረሰህ መጀመሪያ የሚታሰብህ ምን ዓይነት ኑሮ እየኖርኩ ስለመሆኔ የምገልጽልህ ነገር ይመስለኛል። መሰደዬ የመከፋት ውጤት ነውና አሜሪካ ውስጥ ምን ያህል እንደደላኝ ወይም እንዳልደላኝ ለማወቅ ትጓጓ ይሆናል። በኔ በኩል ‹ደላኝ› ወይም ‹ከፋኝ› ብዬ ልነግርህ አልፈልግም። እኗኗሬን ልግለጽልህና ምደባውን ራስህ ፈርጀው።

«አሜሪካ ውስጥ በእየዕለቱ ያገኘሁትን ሁሉ ስራ እሠራለሁ። ስራዬን ሳጠናቅቅ ለስራው የተመደበው ገንዘብ በሙሉ ይከፈለኛል። ዛሬ አንዱ ጋር ስሰራ ውዬ ነገ ወደ ሌላው ብሄድ መልቀቂያ አልጠየቅም። በስራ ዘመቻ ሰበብ የጉልበቴን ዋጋ ማንም አይነጥቀኝም። በሰላም ስሰራ ውዬ የሰላም እንቅልፍ እተኛለሁ። ‹እገሌ ስለኔ ምን ይላል? ነገ ምን ያደርገኝ ወይም ያስደርገኝ ይሆን?› ብዬ አልጨነቅም። በሰራሁት መጠን ተከፍለኝ ክፍያ ስለምቀበል የገንዘብ ችግር አይገጥመኝም። የሌደታ ዕለት ደምገ ወስጄ እስከ ቀጣዩ ልደታ በቃኝ አልበቃኝ ብዬ ስጨነቅ አልሰነብትም።

አለታዊ አምሳዊና የሆዴ ነገር ይሆን ይመስላል። የመንፈስህስ ነገር ካልከኝ ግን ጣጣው ብዙ ነው። በመሰረቱ ማንም ሰው በሀገሩ ውስጥ ተከፍቶ በተሰደደበት አገር ደስ ይለዋል ማለት ዘበት ነው፤ ምናልባት ‹ከመሞት መሰንበት› ለሚለው የሀገራችን ብሂል ምላሽ ይሆን እንደሆን እንጂ። ስደት ደግሞ የመንፈስ ርሀብ ውጤት ነው። መንፈሱ የተራበ ሰው የቱንም ያህል የጣፈጠና የበዛ ምግብ ቢበላ ሁለንተናው ውስጥ ባዶ ነው። እኔም እንዲሁ ባዶዬን እኖራለሁ።

«አሜሪካ ደግሞ የጭፍን ፖለቲካ ሰለባ ሆነው ለተሰደዱባት ሁሉ የባሰ የመንፈስ ርሀብ የምትለቅ አገር ነች። የዚች ደብዳቤዬም ዋነኛ ይዘት በዚሁ ዙሪያ የሚያጠነጥን ነውና በሰጥና አንብበልኝ። በዚያው ውስጤንም ትረዳዋለህ።

«አየህ አስቻለው፦ አሜሪካኖች ወደ ስልጣን ሲወጡ መንገዳቸው በህዝብ መሀል ነው። ለስልጣን የሚደረግ ትልቅ ጦርነት አለ። መሳሪያው ግን መድፍና መትረየስ አይደለም፣ የጠራና የነጠረ ሀሳብ፣ በሩቅ የሚታይ ራዕይ፣ ከራዕዩ ጋር የሚደርስ የፖለቲካ አመለካከትና አሰራር ቅደም ተከተል ወይም ፕሮግራም እንጂ። ፉክክሩ የሰላ ምላስና ርቱዕ አንደበት ነው። የጦርነቱ ቦታ ክብ ጠረጴዛ ነው። የውጊያ መድረኩም አልፍ አእላፍን የሚይዙ ሰፋፊ አዳራሾች ናቸው። በዚህ የትግል ሜዳ አሸንፎ ስልጣን ላይ የወጣ ሁሉ ስራውን የሚያከናውነው በሕዝብ ይሁንታ በወደቀ ህገ መንግስት መሰረት ነው። ማንም የስልጣን ክልሉን አልፎ ቢገኝ ያለ ቀጠሮ በሕዝብ ጩኸት ስልጣኑን ይለቃል። ስለሆነም አሜሪካ ባለ ስልጣን ሕዝብን ፈርቶ የሚኖርባት እንጂ ሕዝብ ባለ ስልጣንን እየፈራ የሚኖርባት ሀገር አይደለችም። እንዴት ደ...ስ የምትል ሀገር መሰለችህ!!

«የምወድህ አስቻለው፦ እዚህ አሜሪካ ውስጥ በአገኘሁት ብርሃን የሀገሬን ጨለማ እሻግሬ ሳየው እቤት ማስፈራራቱ! እቤት ማስጠላቱ! እቤት ማስጨነቁ! የመንፈስ ርሀብ የሚለትብኝም ይህ ሁኔታ ነው። በእውነት ያንቀጠቅጣል! በእውነት ያዘገንናል! በእውነት ያንገፈግፋል! የዚህ ሁሉ ድምር ውጤት እንቅልፍ እያሳጣ እኔንም ሁል ጊዜ ያስለቅሰኛል።

«የሀገራችን አምባገነኖች ከየትም ይነሱ፣ በየትም ይምጡ፣ መቸም ይድረሱ፣ ነገር ግን አንድ የጋራ መለያ ባህሪ አላቸው፣ ይህም በፊትለፊት በህዝባቸው ስም እየማሉ በስውር ግን የገዛ ሕዝባቸውን በጠላትነት የመፈረጅ መሰሪነታቸው ነው። መሠረታዊ ምክንያቱ ደግሞ ስልጣን ላይ የሚወጡት በሀይል እንጂ የህዝብ ይሁንታ አግኝተው ስላልሆነ ነው። ግን ደግሞ ስልጣኑን ይፈልጉታል። በድሀ ሀገር ስልጣን የሀብት ምንጭ ነውና ከያዙትም በኋላ ሙጭኝ ይሉበታል። ይቆዩበት ዘንድ ‹ጠላታችን› የሚሉትን ሕዝብ ያተረማምሱታል። ቢያንስ በሁለት አንዳንዴም ከዚያ በላይ በሆነ እመዳደብ ይከፋፍሉታል። አንዱን ወገን ወዳጅ አድርገው ሌላውን በጠላትነት ይፈርጁታል። የጠሉትን ወገን የተለያየ ስም እየለጠፉ ይበልጥ እንዲጠላ አውርተው ያስወሩበታል። በዚህም የጠላታቸውን የእርስ በእርስ ጠላትነት ይፈጥራሉ። ሕዝብና ሕዝብ የጎሪጥ እንዲተያይ ያደርጉና ጥላቻና ጥርጣሬን ያነግሱበታል። በዚህ ጊዜ የራሳቸውን የስልጣን ኮርቻ ያደላድላሉ፣ የችሎታ ሳይሆን የብልጠት አካሄድ!!

«በመሠረቱ የግጭቶች ሁሉ፣ የጦርነቶች ሁሉ፣የችግሮቻችን መሠረታዊ ምክንያት ኢኮኖሚ ነው፣ በሌላ አነጋገር ጥቅም!! ፖለቲካ የሚባለው ነገር የዚሁ ፍላጎት ለባሜ ነው:: በተለይ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ የሚበለጡ አምባገነኖች ከስልጣን ላይ የሚወጡት ይህንን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ደህ አገርን ለመቆጣጠር ነው፤ ሁሉን ነገር በመዳፋቸው ውስጥ ማስገባት የአምባገነኖች ልዩ ባህሪ ነውና::

በዚህ አያበቁም፤ የስልጣን ጊዜአቸው እስከ መቼ ድረስ መሆኑን ስለማያውቁት ሰፋ ቀን ቢመጣ እያሉ በተለያየ መንገድ መዘጋጀት ይጀምራሉ:: ልጆቻቸውን ያሏቸውን ዘርቶቻን እያስመለሱ ከአባይ በኋላ ወደ ምዕራባውያን ሀገሮች እየላኩ ምርጥና ድንቅ በሆኑ የትምህርት ተቋማት በማስተማር በሙያ ከሁሉት ያስታጥቃሉ:: የሀገር አንጡራ ሀብት እያሟጠጡ በመዝረፍ በራሳቸውና በልጆቻቸው ስም በውጭ ባንኮች ያስቀምጣሉ::

«የምወድህ አስቻለው፦ እውነት እልሀለሁ! በዚህ ዙሪያ በአስከፊና በአስላሳለኩ ቁጥር በአንድ ወይም በሌላ መንገድ ተጉዞ ተጉዞ የሚመጣ ታላቅ አገራዊ አደጋ ወለል ብሎ ይታየኛል:: በሀገር ሀብትና ንብረት የተለያዩ ሙያ በመስክ ላይ ያሉት የጥቂት የገዥ መደብና የቅርብ ወገኖቻቸው ልጆች የተካኑትን ሙያና በውጭ ባንኮች የተቀመጠላቸውን ገንዘብ በዚያው ይዘውት ቢቀሩ ሀገራዊ ኪሳራው የትየለሌ:: ምናልባት ይዘውት ወደ ሀገር ቢመለሱም አደጋው ከዚያ የሚያንስና እንዲያውም የከፋ የሚሆንበት ሁኔታም ሊኖር እንደሚችል አንዳንዴ በአእምሮዬ ውስጥ ድቅን እያለ ያሳስበኛል::

«መቸም ‹ሰባቱ ለበደለ ልጁ ይቀጣ› የሚል የህግ አንቀጽ የለም:: እነዚህ ቀድሰኛ ልጆች በአባቶቻቸው ተዘርፎ የተሰጣቸውን ሀብትና የተካኑትን ሙያ ይዘው በአንድ ወቅት ወደ አገር ቤት ቢመለሱ ውጤቱ ምን ይሆናል ከተባለ ነገሩ ከግምት ያለፈ ግዘድ ነው:: እነዚህ ወገኖች ታላላቅ ኢንዱስትሪዎችን ያቋቁሙና፣ በየከተማው ምርጥ ቦታዎች ላይ ሰማይ ጠቀስ ፎቆችን ይገነቡና፣ ግዙፍ የአገልግሎት መስጫ ተቋማትን በየቦታው ይከፍቱና የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ሙሉ በሙሉ መቆጣጠራቸው አይቀርም:: ይህ ከሆነ ትርፉ የሚያስገኙ የኢኮኖሚ ተቋማት በሙሉ በጥቂቶች እጅ ጥቅልል ብሎ ገባ ማለት ነው:: የዚህ ውጤት በአንድ ሀገር ውስጥ ሁለት የተራራቁ መደቦችን መፍጠሩ አይቀርም:: በአንድ በኩል ሁሉን ነገር በእጃቸው ካስገቡ ወገኖች የሚመሰረት ‹ፖለቲካ ፈጠር› የከበርቴ መደብ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ሁሉን ነገር ተነጥቆ ያጣ የነጣ ከዕልፍ አዕላፍ የሚመሰረት የድሀ መደብ::

«የምፈራው አደጋ ከዚህ ይመነጫል:: ከጥቂት ወገኖች የተውጣጣ ‹ፖለቲካ ፈጠር› የከበርቴ መደብና ዓይኑ እያየ፣ ጆሮው እየሰማ ደሙን የተመጠጠ፣ ስጋውን የተጋጠ ድሀ ሕዝብ አብረው ከሚኖሩበት አገር ይልቅ አይጥና ድመት በአንድ ላይ በሚያድሩበት ጎታ ውስጥ የተሻለ ሰላም አለ:: ኋለኞቹ አንዱ በሌላው ተበልቶ በይው ወገን ተጠቃሚ ይሆናል:: የፊተኞቹ ዕጣ ፈንታ ግን ከዚህ በእጅጉ ይለያል:: ከበርቴዎቹም በእጃቸው ያስገቡትን ገንዘብ ከየት እንዳመጡት ልባቸው ያውቃልና፤ ድሀውም መዘረፉንና መነጠቁን ፍፁም አይረሳምና በሰላም ጊዜ እንኳ ቢሆን በእነዚህ ሁለት ወገኖች መካከል እውነተኛ ሰላም ሊኖር አይችልም:: ሁልጊዜ

ተፋጠው ትር ነው፤ ድሀ ጊዜ በመጠበቅ፣ ሀብታም በመሸማቀቅ!! ምናልባት በአንድ ወቅት ተፈጥሮም ይከፋና የሚላስ የሚቀመስ ጠፍቶ ድሀ ጠሙን ያደረ ዕለት ፈጠር የሚችለውን አደጋ ማን ይመልሰው ይሆን? እኔ እንደሚታየኝ ያ አደጋ የተከሰተ እንደሆነ የሚጠፋ ነገር ሁሉ ሳያልቅ የሚያጠፉ እጆች ያቀጣ አይመለስም:: በእርግጥም ይህ ዓይነቱ አደጋ ከተፈጠረ ሀገራችን ኢትዮጵያ እጅግ ሊያስ አንድ የጨለማ ዘመን ታሪክ ለመዝገብ ማለፍ ግድ የሚላት መሰሉ እየተገኘ በአውነት ሰትሰት ብዙ አስትሳለሁ:: ለነገሩማ አንድ ሀገር ሰተራዘመ ጊዜ በአምባገነኖች የጭቃና ቀንበር ሥር ወድቃ ከቆየች መጨረሻዋ ጥፋትና ውድቀት ሊሆን እንደሚችል ከማን ሊሰወር!

«በእርግጥ ይህን መሰሉ አደጋ በሀገሩ ላይ ይደርስ ዘንድ ምናልባት ‹እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል› እንዳለችው እንስሳ ማስተዋል ከጎደላቸው አምባገነኖች ይጠበቅ እንደሆነ እንጂ ማንም ጤነኛ አእምሮ ያለው ኢትዮጵያዊ የሚፈልገው አይደለም:: ዳሩ ግን ቀምነገሩ ያለመፈለጉ ብቻ አልነበረም፤ ችግሩ እንዳይፈጠር ቀርበኛ አድም መውሰድን ይጠይቃል እንጂ:: መፍትሔው ደግሞ የችግሩን ምንጭ ወንጅ ከማወቅ ይጀምራል:: ችግሮቻችን አምባገነኖች ናቸው:: መፍትሄውም አምባገነኖችን ከህዝብ ትከሻ ላይ አሽቀንጥሮ መጣል ነው:: መሳሪያው ደግሞ የተቀናጀ ሕዝባዊ አመፅ ብቻ!

«ውድ ወንድሜ አስቻለው፦ ‹አመፅ› ሲባል ሰብዙዎቻችን የሚገባን ጠመንጃ አንስቶ ጫካ መግባት ብቻ ነው:: ለኔ ግን የአመፅ ትርጉም ይህ ብቻ አይደለም:: በአሁኑ ሰዓት በየሀገራችን ዳርና ዳር የሚጎሰሙ የጦርነት ነጋሪቶችም ሀገራችንንና ሕዝባችንን ነጻ አውጥተው የሰላም ድባብ ይጥላሉ ብዬ ተስፋ አላደርግም:: ቀድሞ ነገር ከጠመንጃ አፈ-ሙዝ የተገኘ ነጻነት ያለ ሳሙና የታጠበ ጨርቅ ነው፤ ለጊዜው ጠረኑ ይቀየር እንደሆን እንጂ እድፉ ግን የማይለቅ፣ ውሉ አርሮ የሚሸት፣ ሲለንብት የሚከረፋ::

«የጠመንጃ ነጻነት ሌላም ችግር አለው:: በመሠረቱ ድሉ የሀይል እንጂ የሀሳብና የአመለካከት ብልጫ አይደለም:: የድሉ ባለቤቶች ጦረኞች እንጂ ሕዝቡ አይደለም:: ጦረኞች በጫካ ውስጥ ቆይታቸው የሚማሩት የውጊያ ስልት እንጂ የአመራር ጥበብ አይደለም:: ቢያሸንፉ እንኳ ስልጣን ሲይዙ ግራ መጋባታቸው አይቀርም:: በዚህ ውጤት ፍትህ ይጓደላል:: ሕዝብም ይማረራል:: ሰውጥ በመፈለግ ስሜት ሕዝቡ ድንገት ነቅንቅ ያለ እንደሆን የድሉ ባለቤቶች ያኔ ጫካ ውስጥ ሳሉ ‹ተነስ ለነጻነትህ!› እንዳሉት ሁሉ በኋላ ግን ‹አርፍ ለሕይወትህ!› ቢሉትስ? ይህም ሌላ ብልሽት::

«ጦረኞች ከጫካ እስከ ቤተመንግስት እስኪደርሱ ድረስ እያንዳንዱ ርምጃቸው በደም የጨቀየ ነው:: እየሞቱ ቢሆንም ይበልጥ እየገደሉ ነው የሚመጡት:: በዚህ ምክንያት በቀልን ይፈራሉና ስልጣን ከያዙም በኋላ ጠመንጃቸውን አይጥሉም:: ጠመንጃ ተሸክመው በስነብቱ ቁጥር በዚያው ልክ ልባቸውም ይደነቁራል:: ደንቆሮ ደግሞ የራሱን እንጂ የሰው አይሰማም:: ሀይለኛ የህዝብ ጩኸት ቢያውካቸው እንኳ ፀጥ ማሰኛቸው ያው ጠመንጃ ነው፣ ከምንም በላይ እሱን የመጠቀም ልምድ አካብተዋልና::

«ሌላም አይቀሬ ችግር አለ። ጦረኞች ከጫካ ውስጥ ከጠመንጃ በቀር ሌላ ምንም ነገር ይዘው አይመጡም። ስልጣን ከያዙ በኋላ ግን መከበራቸውም አይቀርም። ፖለቲካኛ ከበረ ከተባለ ነግዶ አተረፈ፤ ወይም እርስ አመረተ ሊባል አይችልም። የሀብት ምንጫቸው ያው የሀገርና ሕዝብ ሀብትና ንብረት ነው። ታዲያ ሀገርና ሕዝብ ከጠመንጃ ነፃነት ምን ያተርፋሉ? ወደ እውነተኛ ፍትህና ነፃነት የሚያመራው መንገድ ግን ወዲህ ነው፤ የተቀናጀና የተባበረ ህዝባዊ አመጽ። በእያንዳንዱ የነጻነት ቀናዒ ስሜት ውስጥ የሚፈጠር የልብ አመጽ!

«በእውነት እልሀለሁ አስቻለው፦ የእያንዳንዱ ሰው ነጻነት በራሱ ልብ ውስጥ በሚፈጠር የአመጽ ስሜት ውስጥ ትጸንሳለች። ጥይትን ጫካ ውስጥ የመሸገ ማንም ፈሪ ሊተኩሳት ይችላል። ነገር ግን ክብርና ነጻነቱን ለሚሻ እውነተኛ ጀግና ሁሉ ያለ ምንም ወጪ ደጋግሞ የሚተኩሳት፤ ግፈኞችን መርዝ ሆና የምታቃጥል አንድ ጥይት በገዛ አንደበቱ ውስጥ አለች ‹እምቢ አሻፈረኝ!› የምትለን የአመጽ ቃል።

«የሀገራችን ህዝብ መሠረታዊ ችግር የሚያስፈራ ነገር በሌለበት መፍራት ነው። እንዲሁም አደር ባይነትና በሌላው ትከሻ ላይ ነጻነትን የማግኘት አጉል ምኞት ነው። ይህ ሁሉ እንዲለጠቀመ ከእኛ ከኢትዮጵያውያን የተሻለ ምስክር የለም። የሰው ልጅ የወደፊት ችግሩ ዛሬ ላይ ሆኖ በሚያስበውና በሚፈጽመው ተግባር ውስጥ ይፈጠራል። የዛሬው ዝምታችን የወደፊት ዋይታችንን ከማስከተሉ በፊት ሁላችንም በየፊናችን መንቀሳቀስ ይጠበቅብናል። ራሳችን ያመጣነውን የፍርሀት፤ የአድርባይነትና ነጻነትን ከሌሎች የመጠበቅ በሽታ ራሳችን ፈውሰን በአምባገነኖችና አቀንቃኞቻቸው ላይ ፈጥነን ልናምጽ ይገባል። አዎ ፍጥነት! ፍጥነት!! ፍጥነት!!! ቀድሞስ ቢሆን እየተከፋ የማያምጽ ልብ ምንድነው? እያረረ እየተከነ የማይቆርጥ አንጀት ምንድነው? ኢያወቀስ የማይወስን አእምሮ ምንድነው? አንዲት ሀገር ታላቅ ለመሆን ታላቅ ሕዝብ ሊኖራት ይገባል። ታላላቅ መሪዎች ከታላቅ ሕዝብ መሀል ይወጣሉ እንጂ በራሳቸው ታላቅ ሕዝብ መፍጠር ከቶ አይቻላቸውም። የሕዝብ ታላቅነት መለኪያ ደግሞ ለራሱ ክብርና ነፃነት እንዲሁም ሀገሩ የምትጠይቀውን መስዋዕትነት ሁሉ ለመክፈል ያለው ዝግጁነት ነው። መስዋዕትነትን ሲሸሹ የሚዝዙበት መንገድ ሁሉ የሚያደርሰው ከውርደት ጫፍ ነው። በሁሉ ነገር እጅ ሰጥቶ እንገቱን ከደፋ ህዝብ መሀል የሚወጡ መሪዎችም ከራሱ ከሕዝብ የባሱ ናቸው፤ ቢያስቡ ለሆዳቸው፤ ቢጨነቁ ለስልጣናቸው። ያኔ ሕዝብም ሀገርም ወደ ታች! ጀውው...ጭል...ጥ ወደ ገደል! እል...ም ሰም...ጥ ወደ አረንቋ!!

«ሀገራችን ታላቅ ነበረች። ታላቅ ሕዝብና ታላላቅ መሪዎችም ነበሯት። ዝናዋ በዓለም ዙሪያ ሲሰማ ኖሯል። ዛሬስ? ዛሬማ... ዛሬማ... መልሱ በእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ልብ ውስጥ ይገኛል። ሲጋት! ፍርሃት ጭንቀት!! የታላቅነት ዝናና ታሪክ ያለው ሕዝብ ወደ ታላቅነቱ ለመመለስ አቋራጩ መንገድ፤ እያንዳንዱ ዜጋ የየራሱን ልብ እየመረመረ ወደ ሀሊናው መመለስና አዕምሮውን ከፍቶ፤ ዓይኑን ገልጦ ማየት መቻል ነው። ምንም ሳይቆይ የውርደቱን መንስዔዎች ያገኛቸዋል፤ ከአምባገነኖች ይበልጥ በእነሱ ዙሪያ ተሰልፈው የሚያጨበጭቡ ሆድ አደር

ሹማምንቶችና ፍርፋሪ ናፋቂ ጆሮ አደሮች ናቸው። የእነዚህ ዓይነቶቹ ሰዎች ወትሮውም ጊዜና ሀገር ውስጥ አይጠፉም። በሀገራችንማ እንደ አሸን ፈልተዋል። እንዲያውም አምባገነኖች በሕዝብ ጫንቃ ላይ እንዲፈናጠጡ መጠጣጫ እርካብ የሆኗቸው እነሱ ናቸው። ስብዕናቸው በጥቂት ሀረጎች ይገለጻል፤ ራሳቸውን የከዱ ሀሊና ቢሶች፤ የሚበሉትን እንጂ የሚሰሩትን የማያውቁ አሳማዎች፤ እንኳን ለሰው ሊያስረዱ ለራሳቸውም ባልገባቸው የአምባገነኖች ፍልስፍና ህዝብን ለማደንቆር የሚጮሁ ጡሩምባዎች ናቸው!! ሕዝባዊ የልብ አመጽም በዚህ ጊዜና በእነዚህ ሰዎች ላይ ሊጀመር ይገባል።

«በአምባገነኖች ጉዳይ ፈጻሚዎች ላይ የሚደረግ የሕዝብ አመጽ ውጤቱ ፈጣን ነው። እነዚህ ወገኖች ቀድሞም ቢሆን ለሆዳቸው ሲሉ እንጂ እምነውበት ስላልሆነ የአመጽ እሳት አይችሉም፤ ወዲያውኑ ይሸሻሉ። ውለው ሳያድሩ መንገዳቸውን ይቀይራሉ። ራሳቸውን ከአደጋ ለማዳን ሲሉ ፈጥነው ወደ ሕዝብ ይቀላቀላሉ።

«ሕዝባዊ አመጽ በባህሪው የሰደድ እሳት ነው። ትንንሾቹን አቃጥሎ በመከከለኞቹ ላይ በመረማመድ ከታላላቆቹ ሆድ አደር ሹማምንቶች ጋር ለመድረስ ጊዜ አይፈጅበትም። እነሱም ቢሆኑ እግሮቻቸው መቆራረጣቸውን ሲያውቁ ይዝረከረካሉ። ሳይውሉ ሳያድሩ ልባቸው ይርዳል፤ ይሸበራሉ። ምርጫቸው አንድ ወይም ሁለት ብቻ ነው፤ ሀገር ጥሎ መሸሽ! አለያም ይቅርታ ጠይቀው ከሕዝባቸው መቀላቀል። ከሁለቱም ካልሆነ ካብ አይገባ ድንጋይ ሆነው ይቀራሉ። ዘሪያ በኋላ ከእውራ ገገርዎች ጋር ፍልሚያ አያስፈልግም፤ ስር የሌላቸው ዛፎች ይሆናሉና በንፋስ ይወድቃሉ። የቆሙበት የፖለቲካ ማማ ይደረመሳል። ይለምጣሉ። ብንን ብትንን ይላሉ። ቢፈልጓቸው እንኳ አይገኙም። ቦታ የሉም!!

«በዚህ ዓይነት የሕዝብ አመጽ የተገኘ ነጻነት ድሉ በአስተማማኝ የሕዝብ ነው። መሪዎቹንም በራሱ ምርጫ ይወስናል። እነሱም ከልቡ ይወጣሉና የልቡን ያደርሱለታል። ያኔ ጉዞው ሁሉ ወደፊት! መንገዱም ሁሉ ቀና ይሆናል። ኢትዮጵያም የሁሉም ዜጎቿ ትሆናለች። እውነተኛዋ ኢትዮጵያም ትፈጠራለች፤ የተስፋዋ ምድር ኢትዮጵያ! የቃል ኪዳኗ አገር ኢትዮጵያ!!

«ወንድሜ አስቻለው፦ ስለ ሀገራችን ሁኔታ ይህችን ያህል ካልኩ እስኪ ስለንተ ኑሮና ሁኔታ ጥቂት ልበልህ። ከድንቁርና በመነጨ እብሪትና ተንኮል የተሞሉ አምባገነኖች ስልጣን በያዙበት ጊዜና ቦታ ሁሉ አውቆ መገኘትን ያህል የሚያድን በሽታ የለም። መሰሪ አካሄዳቸው በገባህ ቁጥር ልብህ ይደማል። ሲዋሹና ሲቀጥፉ በሰማህ ቁጥር አንጀትህ ይቆስላል። የሚፈጽሙት የጭካኔ ተግባር ሁሉ ውስጥህን ይኮሰኩሰዋል። በዚህም ጊዜ መንፈስህ እየቆሰለ ጤና ታጣለህ። ስለሆነም እስቲ ይህን ሁሉ የዘመኑ እውነታ አድርገህ ውሰደው። ሁል ጊዜ አትጨነቅ፤ ሁልጊዜ አትብሰልሰል። የነፃነት ፍላጎት ስሜትህ ሳይቀዘቅዝ ነገር ግን ሁሉን ነገር በእርጋታና በትዕግስት ተከታተለው።

«በአምባገነኖች ዘመን ህግ እለ ብለህ ህጋዊ የመብት ክርክር አታንሳ። ህጉን የሚያወጡት ራሳቸውና ለራሳቸው ብቻ ስለሆነ ያልጠቀማቸው ዕለት በማግስቱ ይሽሩታል። እንዲያውም ዛሬ የተከራከርክበት የህግ አንቀጽ ነገ በወንጀል

ሊያስጠይቅህ ይችላል:: ዕድለኛ ከሆንክ ወህኒ ትወርዳለህ:: ነገሩ ከጠናም ግን ያውቃል፣ እነ-ኢጆሮች የልባቸውን ሰርተው ‹ተሰውሯል› ቢሉህስ? ዘርፈ ብዙ በሆኑ ችግሮች በተተበተበች ሀገር ውስጥ ሲኖሩ ህልውናን ለማቆየት ጥበብ ያስፈልጋልና ወንድሜ ጥበበኛ ብትሆን!! ጊዜያዊ እፎይታን እንኳ ማግኘት ትችል ዘንድ ከዲላ ወደ ሌላ አገር ብትዛወር ብዬ ወንድማዊ ምክሬን አስከትላለሁ::

«በተረፈ ፈጣሪ አምላክ እኔንም ወደ ሀገሬ እንዲመልሰኝ፣ ለሀገሬ ሕዝብም ልቦና ሰጥቶት ከእንቅልፉ ይነቃ ዘንድ እንዲሁም ሀገሬ ኢትዮጵያን ከጥፋት ይጠብቃት ዘንድ ዘወትር በፀሎት እተጋለሁ::

ያንተው ደጀኔ አድማሱ(ዶ/ር)

እስቻለው ይህን ደብዳቤ ሲያነብ ፀጥ ረጭ ብሎ፣ ትንፋሹን ዋጥ አድርጎ በስሜትና በተመስጦ ነበር:: አንብቦ እንደ ጨረሰ ግን አንዳች ስሜት ሰውነቱን ወረረው:: ተሸበረ:: ጭንቅ ጭንቅ አለው:: እራሱን እንደ ማዞር፣ ልቡንም እንደ ማጥወልወል አለውና ከዚህ ስሜት ያመለጠ መስሎት ያን ደብዳቤ ከእጠገቡ ራቅ አድርጎ እልጋው ላይ በማስቀመጥ ሁለት ዓይኖቹን ጨምሮ ሙሉ ፊቱን በሁለት እጆቹ ሸፍኖ አደረገና እልጋው ላይ ተደፋ:: በዚሁ ሁኔታ ለረጅም ጊዜ ቆየ:: ትርፌ ምሳውን አድርሳ ኖሮ ልታስታጥበው ውሃና ማስታጠቢያ ይዛ ወደ አልጋው ቀረብ በማለት፡

«ጋሼ እስቻለው!» ስትል ጠራችው:: እስቻለው ግን ሰምቶ እንዳልሰማ ዝም አላት::

«እንቅልፍ ወሰደህ እንዴ?» እንደገና:: እስቻለው ፈጠን ብሎ ብድግ በማለት ዓይኖቹን ጭፍን እንዳደረገ «አየ ትርፌ! የእንቅልፍን ነገር ተይው፤ ከእንግዲህ እንኳን ለቀኑ ለሌሊቱም ሰጋሁ::» እያለ ሊታጠብ አንድ እጁን ዘረጋ::

ምዕራፍ ስምንት

የሰኔ ወር ገብቶ እንዲያውም ተጋመሰ:: አዲስ የበጀት ዓመት መቃረቡን ተከትሎ የመንግስት ሠራተኞች የዝውውር ጥያቄ መልስ መስጫው ጊዜም ተዳረሰ:: ከዝውውር ጠያቂዎች አንዱ የሆነው እስቻለው ያን ወቅት በጉጉት ሲጠብቀው ቆይቷልና ከጊዜው መቃረብ የተነሳ ህሳቡ ሁሉ ስለ ዝውውርና ከዚያ ጋር ተያያዥ ስለሆኑ ነገሮች ብቻ ሆኖ ሰንብቷል:: ብዙ ነገሮች ያሳስቡታል:: ከዲላ መዛወር የፈለገው ወዶ አይደለም፣ ተችግሮ ነው:: ግን በሚዛወርበት ቦታ ዲላ የገጠሙት ችግሮች አይኖሩ ይሆን? ዲላ የተፈጠሩበት ችግሮች መነሻቸው የግልፅነቱና የተናጋሪነቱ ውጤቶች ናቸው:: ወደ አዲሱ ቦታ ሄዶ ዝም ይል ይሆን? ተናጋሪነቱ የተፈጥሮ ባህሪው ነው:: የሰው ልጅ ደግሞ የተለያዩ አመሎችን መተው ይችል እንደሆነ እንጂ የተፈጥሮ ባህሪውን ግን እንዴት?

ዲላ ከተማ ለእስቻለው በሥራ ሕይወት የኖረባት የመጀመሪያዋ ከተማ ናት:: ጣፋጭ ማህበራዊ ሕይወት የጀመረው በዚያችው ከተማ ነው:: ዕድሉ ሆኖ ጥሩና ዕድሜ ልኩን የማይረሳቸው የባዕድ ወገኖች አግኝቶባታል፣ ታፈሡን በልሁና መርዕድን:: ከእነሱ ተለይቶ መሄዱ ያስጨንቀዋል:: ዝውውር የጠየቀው ወደ ሸዋ ክፍለ ሀገር ቢሆንም የሚመደብበትን የጤና ተቋም ግን አያውቅም:: ከነታፈሡ በልሁና መርዕድ ጋር በቀላሉ መገናኘት በሚያስቸግር ቦታ ቢሄድስ? ልቡ ይፈራል:: ድንገት ትዝ ሲለው ሆዱን ባር ባር ይለዋል::

የሔዋን ጉዳይስ? በወላጆቿ ፈቃድና እውቅና ለፍቅራቸው እልባት ለማግኘት የሚሞከረው ገና ወደፊት ባሉት ወራት ነው፣ ሐምሌ ወይም ነሐሴ:: በእርግጥ በጉዳዩ ላይ ታፈሡና በልሁ አስበውበታል፣ ምናልባት ወይዘሮ ዘነቡም ይጨመራሉ:: ግን ይሳካ ይሆን? ወደሚዛወርበት ቦታ ሔዋንን ይዞ መሄድ ይችል ይሆን? ይህ ጉዳይ ዛሬ ሌሊትም እንቅልፍ ነስቶት አድሯል፤ እሁድ ለሰኞ አጥቢያ:: ሲነጋጋ ሲል ግን ድብን ያለ እንቅልፍ ወስዶት ኖሯል:: ተኝቶ አረፈደ::

እስቻለው የጠዋት ፈረቃ ሥራ ገቢ መሆኑን የምታውቀው ትርፌ በሁኔታው ግራ ተጋባች:: ለወትሮው ወደ ሥራ ለመሄድ ቀስቃሽ አያስፈልገውም ነበር:: ዛሬ ግን ሁኔታው ተለየባት:: ልትቀሰቅሰው እያሰበች ፈራ ተባ ስትል ቆየችና መጨረሻ ላይ ግን ልታነቃው ወሰነች::

«ጋሼ እስቻለው!» አለችው ወደ አልጋው ቀረብ ብላ:: እስቻለው ግን በእንዴ አልሰማትም:: «ጋሼ እስቻለው!» አሁንም ደገመች::

እስቻለው ብንን አለ:: ፊቱን ከብርድ ልብስና አንሶላ ሽፋን ገለጥ አድርጎ ከእንገቱም ቀና በማለት «ወይ» አላት::

«ዛሬ ሥራ የለህም እንዴ?»

«አረፈድ?» በማለት የእጁን ሠዓት አየት ሲያደርግ ከጠዋቱ ሁለት ሠዓት ከአምስት ደቂቃ ሆኗል:: «እንዴ!» ብሎ በድንጋጤ ዓይን ትርፌን ፍጥጥ ብሎ ተመለከታት::

«እኔ እኮ ሥራ የማትገባ መሰለኝ!» አለችው ትርፌ ሳትቀሰቅሰው በመቅረቷ ቅር ያሰው መስሏት አፈር እያለች::

«ምን ነካኝ አጣችሁ!?» አለና አንሶላና ብርድ ልብሱን ጣል አድርጎ ከአልጋው ላይ እየተነሳ «ውሃ ውሃ!» አላት በችኮላ አነጋገር።

«በረንዳ ላይ አውጥቼልሀለሁ።»

አስቻለው በጥድፊያ ልብሱን ለባበሰና ሊታጠብ ወደ በረንዳ ወጣ። ፊቱ ታጥቦ አበጣጠረና ወንበር ላይ የሰቀላትን የቆዳ ጃኬት ብድግ አደረገ።

«ቁርስ ሳትበላ?» አለች ትርፌ እንቅስቃሴውን እየተከታተለች።

«ረፍዷል ትርፌ፣ ቻው!» ብሏት በፍጥነት ርምጃ ከቤት ወጥቶ ሄደ።

መንገድ ላይ ሳለ በልቡ አንድ ነገር ያሰላስላል። ከአሁን በፊት ሰባት ጊዜ እንደተከታተለው የሠራተኞች የሰዓት መቆጣጠሪያ መፈረሚያ ጠዋትም ይሁን ከሰዓት ከቦታው የሚነሳበት ወቅት ከእሱ መፈረም ወይም ያለ መፈረም ጋር ሲያያዝ አይቷል። እሱ በጠዋት ወይም በጊዜ ገብቶ ከፈረመ ያ የሰዓት መቆጣጠሪያ መፈረሚያ ለሩብ ሰዓት ያህል በአለበት ቦታ ሊቆይ ይችላል። እሱ ለደቂቃዎች ያህል ከዘገየ ግን ለአፍታ እንኳ ሳይቆይ ወደ ቢሮው ይገባል። ዓላማው እሱ በአርፋጅነት የሚመዘገብበትን ቀናት ለማበርከት እንደሆነ ይጠረጥራል። ስለዚህም በጣም ይጠነቀቅ ነበር። ለዛሬው ግን አልተሳካለትም። ብዙ ባያስጨንቀውም ነገር ግን ባርናባስ ወየሶን በመጥፎ ስሜት እያስታወሰ በፍጥነት ርምጃ ግስጋሴውን ቀጠለ።

ከሆስፒታሉ ቅጥር ግቢ ሲደርስ ሁለት ሰዓት ተኩል ሆኗል። ያ ሰዓት ደግሞ የፈረቃው ጊዜ የሆኑ የነርሶችና ባለሙያዎች ከሥራ በፊት የተለመደ አጭር ስብሰባ ሊያጠናቅቁ የሚደርሱበት ጊዜ ነው። ባለቀ ሰዓት ወደ ስብሰባው መግባት አልፈለገም። ዝምብሎ ወደ መልበሻ ክፍል አመራና ጋወኑን ለበሰ። ቀጥሎም የሰዓት መፈረሚያው ወደሚገኝበት የባርናባስ ወየሶ ፀሐፊ ቢሮ ሄዶ አንኳኩቶ ገባ።

«ዛሬ እንኳ አረፈድኩ አይባልም፣ ውያለሁ እንጂ!» አለ አስቻለው ፈገግ ብሎ የባርናባስ ወየሶ ፀሐፊ የሆነችውን ሠርክዓለምን እየተመለከተ።

«የአንድ ቀን ደሞዝ ቀለጠች።» አለችው ሠርክዓለም እሷም እንደ አስቻለው ፈገግ ብላ እየተለደች። ሠርክዓለም የሚያምር ፈገግታ ያላትና ቀጠን ያለች ቀይ ዳማ ቢጤ ናት። በዕለቱ ጥቁር ኮትና ጉርድ ቀሚስ ለብሳለች። ዕድሜዋ እስከ ሰላሳ ሊደርስ የሚችል ይመስላል።

«ግድየለም፣ ሌላ ጊዜ ካልደገምኩ ለዚህ ወር የሃያ ዘጠኙ ቀን ደሞዜ ይበቃኛል።» አለና አስቻለው በቀይ እስኪርቢቶ የጥያቄ ምልክት ከተደረገበት ጎን ፊርማውን አስቀመጠ።

«ዛሬ ግን ያለ ወትሮህ አርፍደሃል፣ በሰላም ነው?» አለችው ሠርክዓለም አንድ በውስጧ የምታውቀውና የአስጨናቂት ጉዳይ ያለ ስለመሆኑ በሚያጠራጥር ስሜት አስቻለውን እያየችው።

«የሆነ ሀሳብ ገብቶኝ ያለ እንቅልፍ አደርኩና ከነጋ በኋላ ድብን አድርጎ ወሰደኝ። ሌላ እንኳ ችግር አልነበረብኝም።»

«ምነው? ምን አሳሰበህ?»

«ሀሳብ ይጠፋል ብለሽ ነው!» አለና አስቻለው ወደ ውጭ ሊራመድ ሲል ሠርክዓለም ንግግሯን ቀጠለች።

«ፈልጌህ ነበር አስቻለው።»

«በደህና?»

«እስቲ ቁጭ በል።»

አስቻለው የሠርክዓለም ስሜት ጥሩ እንዳልሆነ ገመተ። ደብዳቤ ሊያነበው እየተፍጨረጨረ ዓይኖቹን በዓይኖቿ ላይ ሰክቶ ከሠርክዓለም ጠረጴዛ አጠገብ በምትገኝ የእንግዳ ወንበር ላይ አረፍ አለና «ሰላም አይደለሽም?» ሲል ጠየቃት።

«እኔ እንኳ ደህና ነኝ!»

«ታዲያ ሌላው ምን ሆነ?»

«ዓርብ ዕለት ከሰዓት በኋላ ለአንተ አንድ ደብዳቤ ስጪ ብለውኝ ቅዳሜና እሁድን በጭንቀት ነው ያሳለፍኩት። ከዛሬ ስለማያልፍ ልሰጥህ ብዬ ነው።» አለችው ሠርክዓለም መንፈሷ ጭንቅ ጥብብ እያለ።

«የምን ደብዳቤ? ዝውውር!?» አላት አስቻለው በድንጋጤ ዓይኖቹ ጉልጉል ብለው በሠርክዓለም ላይ በማፍጠጥ። ትንፋሹም በርክትክት፣ ፈጠን ፈጠን አለ።

«አይደለም። ነገሩ ብዙም ችግር ያለው ሆኖ አይደለም፤ ምናልባት ግን አንተ የማትቀበለው ከሆነ በመሀል ችግር እንዳይፈጥርብህ አስቤ ነው።»

«ማን የጻፈው ደብዳቤ ነው?»

ሠርክዓለም የጻፈውን ሰው ‹እገሌ› ብላ መግለጽ አልፈለገችም። ደብዳቤውን ከመሳቢያ ውስጥ አውጥታ ሰጠችው።

አስቻለው ደብዳቤውን ተቀብሎ ገጹን በሙሉ ቃኘት ሲያደርገው ሙሉ ፕሮቶኮል የጨበጠ ነው። የፈረመበት ባርናባስ ወየሶ ነው። የደብዳቤውን አድራሻ ሲመለከት፡ ‹ለጓድ አስቻለው ፍሰሃ› ይላል።

«አ!» አለ አስቻለው ድንገት ሳያስበው። ቀና ብሎ ሠርክዓለምን አየት ካደረገ በኋላ ወደ ደብዳቤው ተመለሰና ማንበብ ጀመረ። ሲጨርስ «ምን?» አለ በድንጋጤና በቁጣ ስሜት ጮክ ብሎ። ሕልም ሕልም መሰለውና እንደገና አነበበው። መልዕክቱ ግን አልተቀየረም! ያው መጀመሪያ እንዳነበበው ነው።

«አልገባኝም ሠርኬ ይኸ ነገር!» አላት ወደ ሠርክዓለም ዞር ብሎ።

«ለማንኛውም ረጋ በል አስቻለው!» አለችው ሠርክዓለም በማረጋጋት ዓይነት እሷም ቀለስለስ እያለች።

«ባርናባስ አሁን ቢሮ ውስጥ አለ?»

«ይኖራሉ። ግን አሁን አትግባ! ባይሆን ነገ ተነገ ወዲያ ይሻላል።»

አስቻለው ለአፍታ ያህል ሠርክዓለምን መልከት ካለ በኋላ ከወንበሩ ላይ ብድግ ብሎ ከቢሮ ወጣ። ያን ደብዳቤ እንደ ያዘ በቀጥታ ወደ ባርናባስ ቢሮ አመራ። ሳያንኳኳ በሩን በርግዶት ገባ።

ባርናባስ በተለመደው አለባበሱ ሆኖ ጠረጴዛው ላይ አጎንብሶ ይፅፋል። ወደ በሩ ቀና ሲል አስቻለውን አየው። የአስቻለው ስሜት መለዋወጡን አይቶ ለሰላም እንዳልመጣ በመገመት ልቡ ደንገጥ አለና «እቤት!» አለው መነፅሩን ወለቅ እያደረገ።

«ምንድነው ይኼ?» አለና አስቻለው ያን ደብዳቤ በባርናባስ ፊት ጠረጴዛው ላይ ወርወር አደረገው። ጋወኑን ወደ ኋላው ሰብሰብ በማድረግ ሽንጥና ሽንጡን ያዘ ቁና ቁና እየተነፈሰ በባርናባስ ፊት ቆመና ቁልቁል ይመለከተው ጀመር።

ባርናባስ ይህን የአስቻለውን ሁኔታ ቀድሞም አስቦት ነበር። ይሁንና አሁን በትክክል ሲከሰት ቀድሞ ከገመተው በላይ ፍርሀት አደረበት። በሙሉ ቀልቡ

የእስቻለውን እንቅስቃሴ እየተከታተለ ለይምሰል ያህል ወደ ደብዳቤው መልከት እያለ «የበላይ አካል ውሳኔ እኮ ነው::» አለው::

«ምን ዓይነት ውሳኔ?» አለ እስቻለው ድንገት አፉ ላይ የመጣለትን:: ዓይኑ ከመፍጠጡም በላይ ትንፋሹ በርክቶ ደረቱ ሞላ ሞሸሸ፣ ሞላ ሞሸሸ ይላል::

«በቃ! ውሳኔ ነዋ!» አለ ባርናባስ ከአሁን አሁን ዘሎ አንቀኝ በማለት እስቻለውን እየፈራ::

«በእርግጥ እናት ሀገሬ ናት የጠራችኝ ወይስ እናንተ ናችሁ ያዘዛችሁኝ» ሲል ጠየቀው እስቻለው የፊቱን ላብ በእጁ እየጠረገ::

«ሁለቱም ተያያዥ ናቸው::»

«ግን ደግሞ ሁለታችሁ መለያየት አለባችሁ:: የጊዜ ጉዳይ ነው እንጂ መለያየታችሁም አይቀርም:: እኔም የሀገሬን ጥሪ በደስታ የምቀበለው ሁለታችሁን ለማለያየት የኩተት ጥሪ ነጋሪት የተጎሰመ እንደሆነ ብቻ ነው:: ይኸኛውን ግን አልቀበለውም::» አለ ዓይኑን በባርናባስ ላይ ፍጥጥ እንዳደረገ::

«መቀበል ያለ መቀበሉ ጉዳይ የአንተ ነው:: ነገር ግን ደብዳቤው በአድራሻ የተጻፈና የመዝገብ ቁጥር የያዘ ስለሆነ አንተው ጋር ይቀመጥ::» አለና ባርናባስ ደብዳቤውን መልሶ ወደ እስቻለው ዘረጋ::

እስቻለው ደብዳቤውን የንጥቂያ ያህል ከባርናባስ እጅ ላይ ምንጭቶ እያረገ «አምጣው! ለታሪክ ይቀመጣል::» ብሎት ወደ ኋላው ተመልሶ ከቢሮው ወጣና በሩን ድርግም አድርጎ ዘግቶ እዚያው በኮሪደሩ ላይ በመቆም ያንኑ ደብዳቤ እንደገና ያነበበው ጀመር:: ግን የደብዳቤው መልዕክት አሁንም ያው ነው:: እስቻለው በንዴት ስሜቱ ተለዋወጠና ለጊዜው ምን ማድረግ እንዳለበት ቅጡ ጠፋው:: ግን በስተቀኝ አቅጣጫ በሚገኘው የኮርደሩ መውጫ በኩል ጅው ብሎ ሄደና ከህንጻው ውስጥ ወጣ:: በዚያው በመውጫው ዳር የግድግዳ ጥግ ተደግፎ እንደገና ያነበበው ጀመር:: በዚህ ጊዜ ግን «ኪኪኪኪ ....» ብሎ ሳቀ:: የንዴት ሳቅ! አሁንም «ኪኪኪኪ ...!»

በዚያችው ቅፅበት እዚያችው ቦታ ላይ እንደ ቆመ በሀሳብ ከብዙ ቦታ ረገጠ:: ሔዋንን አስታወሳት:: ሸዋዬንም እንዲሁ:: የሸዋዬንና የባርናባስን ግንኙነት እንዲሁም ከሁለቱ ጋር ተለጥፎ ሔዋንን በማስቸገር ላይ ያለው በድሉ አሸናፊ ጭምር ታዩት:: በእጁ የያዘው ደብዳቤ ይዘትም ከእነዚህ ሰዎች ግንኙነትና ፍላጎት የመነጨ ስለመሆኑ ሳይጠራጠር አመነበት::

ወዲያው አንድ ነገር ብቻ ማድረግ ታየው:: በዚያ ሆስፒታል ውስጥ ያስቀመጠው ልብስም ሆነ ማስታወሻ ምንም ሳይታሰበው፣ ጋወን ስለ መልበሱ እንኳ ሳይታወቀው ከዚያ ሆስፒታል ግቢ ውስጥ ለመውጣት ወሰነ:: በልቡ ውስጥ ያለው መድረሻ ደግሞ የአውራጃው ግብርና ፅህፈት ቤት::

ከዲላ ሆስፒታል እስከ ግብርና ጽህፈት ቤት በአማካይ ሠላሳ ደቂቃ የሚወስደው የእግር መንገድ ለእስቻለው ሃያ ደቂቃ እንኳ አልፈጀበትም:: የቆፌን ኮረኮንች መንገድ እየነጠረ ተረማምዶ፣ ዲላ ከተማን ለምስራቅና ለምዕራብ ለሁለት በሚሰነጥቃት አስፋልት መንገድ ላይ ገስግሶ ወደ ዲላ ሰሜናዊ ጫፍ አቅራቢያ ሲደርስ ቀኙን በመያዝ ጥቂት ዳገታማ የሆነውን አባሯማ መንገድ ረምርሞ ከበልሁ ቢሮ በር አጠገብ ደረሰ:-

«ኳ- ኳ- ኳ-ኳ ...»

«እንዴ ይጠብቁኝ» አለ በልሁ ከውስጥ:: በዚያ ሰዓት ከሁለት ባለ ጉዳዮች ጋር እየተነጋገረ ነበር:: እስቻለው ዓራስ አላስቻለውም:: በሩን በርግዶት ገባና የበሩን እጀታ እንደ ያዘ በልሁን በተቀመጠበት አሻግሮ ተመለከተው::

በልሁ እስቻለው መሆኑን ሲያውቅና አጠቃላይ የፊቱን ገፅታ ሲመለከት በድንጋጤ ፊቱ ኩምትርትር አለና «እንዴ! ምነው እስቻለው?» አለው ፍጥጥ ብሎ እየተመለከተው:: እስቻለው መልስ አልሰጠውም:: ዝም ብሎ ወደ ውስጥ ገብቶ ሳይጋበዝ በእንግዳ ወንበር ላይ ቁጭ አለ:: በረጅም በረጅሙ እየተነፈሰ ጣሪያ ጣሪያ ያይ ጀመር:: በእስቻለው ሁኔታ የተገረሙና ምናልባትም ደንገጥ ያሉ የበልሁ እንግዶች በልሁን አየት አየት አደረጉት::

«እስቲ ወንድሞቼ፣ እንዴ ውጭ ሆናችሁ ጠብቁኝ» ሲል በልሁ በትህትና ጠየቃቸው:: ሰዎቹ አላመነቱም፣ ወዲያው ብድግ ብለው ተከታትለው ወጡ::

«እስቻለው!» ሲል ጠራው በልሁ በሁኔታው መሰዋወጥ ሆዱ እያዘነ::

«ወይ» አለው እስቻለው አሁንም ዓይኑን ከኮርኒስ ላይ ሳይነቅል::

«ምነው? ምን ሆንክ?»

እስቻለው የሆነውን ነገር ከመናገር ይልቅ ያን የያዘውን ደብዳቤ ለበልሁ እየዘረጋ «እንካ አንብበው» አለና ሰጠው::

በልሁም ልክ እንደ እስቻለው ቶሎ ወደ ሀሳቡ አልገባም:: የደብዳቤውን ቅርጽ በቅድሚያ ቃኘው:: ፕሮቶኮል የጨበጠ ደብዳቤ ነው:: ፊርማው ባርናባስ፣ ቲተሩም የእሱ:: ከዚያ በኋላ ወደ ዝርዝር ሀሳቡ ገብቶ አንብቦ ከጨረሰ በኋላ ደንግጥ ባለ አኳኋን «ከየት አመጣኸው?» ሲል ጠየቀው::

«ሰጡኝ! እኔማ ከየት አመጣዋለሁ?» አለና እስቻለው ጉንጮቹን ነፋ አድርጎ «ኡሁሁ...» ብሎ በረጅሙ ተነፈሰና አንገቱን ወደ መሬት ደፋ::

በልሁ ለጊዜው ምንም ማለት አልቻለም:: እስቻለውን ግን አከታትሎ ተመለከተው:: የደብዳቤው ይዘትና መልዕክት በውስጡ ሊፈጥርበት የሚችለውን ስሜት ያውቃልና እሱም ሆዱ እያዘነ «እስቲ ወጣ እንበልና ሻይ እየጠጣን እንነጋገር» አለ በልሁ የእስቻለውን ምላሽ በዓይኑም በጆሮውም እየጠበቀ:: እስቻለው እሺ ወይም እምቢ ብሎ ቃል አልተናገረም፤ ብቻ ዝም ብሎ ብድግ አለና ተከታትለው ወጡ::

ለበልሁ መሥሪያ ቤት ሠራተኞች የሻይ ፍላጎት አማራጮች ሁለት ነው:: በዚያው በመስሪያ ቤቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ በምትገኝ የሻይ ክበብ በከሰል የተፈላ ሻይ ቡና መጠጣት፣ አለበለዚያም ከግቢ ወጥቶ በአንደኛ መንገድ ላይ ከሚገኙ ሆቴሎች ድረስ በመሄድ የማሽን ሻይ ቡና መጠቀም:: በዚያን ዕለት ግን በልሁ ስለ እስቻለው ጉዳይ ጊዜ ወስዶ መነጋገር ስለ አሰበ በቀጥታ ወደ ከተማ ወረዱ:: ወደ አንደኛ መንገድ ከተዳረሱ በኋላ እስቻለው አንድ ሀሳብ አመጣ::

«ለምን ወደ ታፈሡ ጋ አንሄድም?» አለና በልሁን አየት አደረገው:: በእርግጥ በልሁም ትዝ ስላላለው ነው እንጂ ያ ጉዳይ ወደ ታፈሡ ቤት የሚያሮጥ ነውና ሀሳቡን ተቀበለው::

ከበልሁ መስሪያ ቤት እስከ ታፈሡ ቤት ድረስ እስከ አሥራ አምስት ደቂቃ የሚወስደውን መንገድ በዝምታ ጨርሰው በሯ ላይ ሲደርሱ ታፈሡ የቤት ልብሷን እንደለበሰች አገኟት::

«እለሽ ታፈሥ?» አላት በልሁ ቀድሞ::

«እንዴ! ምን ዓይነት አመጣጥ ነው?» አለች ታፈሡ ደንገጥ ብላ። ከመንገ አትልክት በተጨማሪ የአስቻለው ጋውን መልበስ ግራ አጋባት። አስቻለውና በልሁ ፊታቸውን ክፍት እንዳላቸው ሰላም እያሏት ወደ ሶፋ አለፍ እያሉ ተቀመጡ።

«እናንተ!» አለች ታፈሡ አሁንም ዓይኗን በሁለቱም ላይ እያንከራተተች።

«እስቲ ቁጭ በይ ታፈሥ!» አሳት በልሁ በተዳከመ ስሜት።

ታፈሡ ቁጭ አለችና «ምን ሆናችኋል?» ስትል ጠየቀቻቸው። በልሁ የያዛትንም ወረቀት ከርቀት አተኩረችባት።

«አይዞሽ፣ ብዙም አትደንግጭ!» አሳት በልሁ።

«ትንሽም ቢሆን ንገሩኝ!»

«መምህርት ሸዋዬ ገና ዛሬ ሳታሸንፈን አልቀረችም።» አሳት በልሁ በደረቁ ፈገግ ብሎ እያያት።

«እንዴት አድርጋ?»

«ያን ባርናባስ የተባለ ሽማግሌዋን ተጠቅማ።»

«ማለት?»

«እንቺ ይኸን ወረቀት አንብቢው።» አለና በልሁ ደብዳቤውን ለታፈሡ ዘረጋላት። ታፈሡ ያን ደብዳቤ ከበልሁ እጅ ላይ በችኮላ ተቀብላ ሁለመናውን አየችው። ቀንና ቁጥር፣ የራስጌና የግርጌ ማህተም እንዲሁም የባርናባስ ወየሰ ፊርማና ቲተር ያለበት ደብዳቤ ነው። ማንበብ ጀመረች።

«ለጓድ አስቻለው ፍሰሀ
ዲላ

ጉዳዩ ፡- <u>የእናት ሀገር ጥሪን ይመለከታል</u>፣

«እንደሚታወቀው ሁሉ በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ጥቂት ተገንጣይ ቡድኖችና ሌሎች ጎጠኞች በመተባበር የሀገራችንን ሉዓላዊነት በመፈታተን ላይ ናቸው። የእነዚሁኑ ተገንጣይ ቡድኖችና የውጭ ደጋፊዎቻቸውን ቅስም ለመስበር ጀግናው ሠራዊታችን ከውጭና ከውስጥ ጠላቶቻችን ጋር አንገት ለአንገት በመተናነቅ ላይ ይገኛል። በመሆኑም አብዮታዊት እናት ሀገራችን በአሁኑ ሰዓት የቁርጥ ቀን ልጆቿን አብዮታዊ ተሳትፎ የምትሻበት ወቅት ነው።

«በዚሁ መሠረት እርስዎም በጦር ግንባር ተሰልፎ በመዋደቅ ላይ ለሚገኘው ጀግናው አብዮታዊ ሠራዊታችን በሙያዎ የህክምና አገልግሎት ይሰጡ ዘንድ አብዮታዊ ጥሪዋን ያስተላለፈችልዎት በመሆኑ ወደ አስመራ በመሄድ ለስድስት ወራት ያህል የሙያ አገልግሎት እንዲሰጡ ተመርጠዋል።

ስለሆነም ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች እንደ እርስዎ ወደ ተጠቀሰው አካባቢ የሚንቀሳቀሱ ስላሉ ለትራንስፖርትና ለሌሎችም ዝግጅቶች ያመች ዘንድ ይህ ደብዳቤ በደረሰዎት በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ አዲስ አበባ በመድረስ ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ሪፖርት እንዲያደርጉ በጥብቅ እናሳስባለን።

ባርናባስ ወየሶ

«እ!» አለች ታፈሡ ደብዳቤውን ጨርሳ ዓይኗን ወደ በልሁና ወደ አስቻለው ተራ በተራ በማቀያየር እየተመለከተች።

«እየሽ አካሄዳቸውን ታፈሥ!» አሳት በልሁ አንገቱን ዘመም አድርጎ በትካዜ እያያት።

«አንተ አስቻለው!» አለች ታፈሡ በዚያ ደብዳቤ ይዘት ምን ያህል መንፈሱ ሊጎዳ እንደሚችል አውቃ ስሜቱን ለመመርመር።

«እኔ ግን ፈጽሞ አልቀበላቸውም! በፍፁም አልሄድም!» አለ አስቻለው አሁንም ዓይኑን በኮርኒስ ላይ ሰክቶ።

ታፈሡና በልሁ እርስ በእርስ ተያዩ። እንደገና ሁለቱም ወደ አስቻለው ዞር በማለት ተመለከቱት። ዓይኑ ፍጥጥ ብሎ ከንፈሩን ነክሷል። በሀሳብም ጭልጥ ብሎ ሄዷል።

«ከውሳኔ በፊት ግን ምክክር ያስፈልገዋል።» አለና በልሁ እንደገና ወደ ታፈሡ ዞር በማለት «አይመስልሽም ታፈሥ?» ሲል ጠየቃት።

ታፈሡ ግን ዓይኖቿ በእንባ ሞልተው በሁለት እጆቿ ግንባሯን ደግፋ ወደ መሬት አቀረቀረች።

* * *

«አስቻለው!» አለችው ሔዋን፣ የዘመቻ ጥሪ ደብዳቤ በደረሰው አምስተኛ ቀን ላይ በዕለተ ዓርብ ከጠዋቱ ሦስት ሠዓት አካባቢ ከቤቱ በመገኘት።

«ወይ!» አሳት አስቻለው አልጋው ላይ ጋለል ብሎ ተኝቶ ከነት ቁጭ ያለችውን ሔዋንን ቀና ብሎ እየተመለከታት።

«ሰሞኑን የምሰማው ወሬ ምንድነው?» ስትል ዓይን ዓይኑን እያየች ጠየቀችው።

«ምን ሰማሽ?»

«ጥሩ ያልሆነ ወሬ።»

«ንገሪኝ!» አሳት አስቻለው ፈገግ ብሎ እያያት።

«ሳታውቀው ቀርተህ ነው?»

«ብዙ ይወራ የለ! የትኛውን ማለቴ ነው።»

«በመሥሪያ ቤትህ በኩል ለስድስት ወር ያህል ዘመቻ ሂድ ተብለህ እምቢ ማለትህን ሰማሁ።» አለችው በፍርሀት እስተያየት እያየችው።

«አዎ፣ አልሄድም ብያለሁ። አሁንም አልሄድም።»

«ግን ለምን?»

«እንደማልሄድ የነገሩሽ ሰዎች ምክንያቱንም ሳይነግሩሽ የቀሩ አልመሰለኝም። አንቺም አትደብቂኝ።» አሳት የሔዋንን ግራ እጅ ይዞ እየደባበሳት።

«ነግረውኛል። ግን ሆዴ በጣም ፈራ!»

«ለምን ብለሽ?»

«ግዳጅ ላለመቀበልህ ምክንያቷ እኔ የምሆን ስለመሰለኝ።» አለችና ሔዋን ዓይኖቿ ላይ ያቀረረ እንባዋን በለበሰችው ስከርፍ ጥርግ አደረገች።

«አይዞሽ ሔዩ፣ አትፍሪ! ምንም አይመጣም።»

«ተው አስቹ! ምንም አይመጣም አትበል:: ኑሮህ ሁሉ ይበላሻል:: ለኔና ኑሮ መበላሸት እኔ ምክንያት መሆን የለብኝም:: የአንተ ከተበላሸ የኔም ይበላሻል» አለችና እንባዋን አሁንም በጉንጫ ላይ ታወርደው ጀመር::

«አታልቅሺ የኔ ፍቅር:: የኔ ሕይወት የሚበላሸው አንቺን ካጣሁ ነው:: ዘመቻ ከሄድኩ ደግሞ አንቺን ላጣሽ እችላለሁ:: ስለዚህ አልሄድም::» ብሎ

«አንተ ዘመቻ ብትሄድ እኔ የት እሄድብሃለሁ?»

«እህትሽ እና ባርናባስ እየሰሩልሽ ያለውን መንገድ አጣሽውና ነው! ወይስ አልገባሽ ይሆን?»

«አውቃለሁ:: ገብቶኛል::»

«ታዲያ የኔ ዘመቻ መሄድ እንዴት አንቺን እያሳጣኝም ብለሽ ትገምቻለሽ?»

«ፈጽሞ አስቻለው! ፈጽሞ አያለያየንም»

«እንዴት?»

«እኔም ላጣህ አልፈልግምና!»

«ወደሽ ሳይሆን ያስገድዱሻል»

«ፈጽሞ አይችሉም»

«አንድ ነገር `አትርሺ ሒዩ! ያለሽው በእህትሽ ቤት፣ የምትጠጪው የእሷን፣ በዚያ ላይ ባርናባስን የሚያህል የፖለቲካ ስልጣን ያለው ወዳጅ አላት:: በዚሁ ላይ ያቀረቡልሽ ወዳጅ በከተማው ውስጥ ‹እሱ› የተባለ ሀብታም በድሉ አሸናፊ:: የባርናባስ ስልጣንና የበድሉ ገንዘብ ከተባበሩ እንዴት እኔና አንቺን መለያየት ያቅታቸዋል?» አለ አስቻለው ከተንጋለለበት ቀና ብሎ ሒዋንን ፊትለፊት እያያት::

«ይህን ሁሉ ግን የታመነ ልብ ያሸንፈዋል::» አለችው ሒዋን የአስቻለውን ደረት እየደባበሰች::

«ፈጽሞ! በበኩሌ ማመን ያስቸግረኛል::»

«ስማ አስቻለው!»

«ወይ የኔ ፍቅር!»

«እኔንም አንተንም ለአደጋ የሚያጋልጥ አጋጣሚ የሚፈጠረው አንተ ዘመቻ አልሄድም ብለህ የቀረህ እንደሆን ነው::»

«እንዴት?»

«ዘመቻ ካልሄድክ ከሥራ ያስወጡሃል! ወይም ያስሩሃል:: ምናልባት ሊገድሉህ ወይም ሊያስገድሉህ ይችላሉ:: አየህ አስቹ! ሥራ ከሌለህ ገንዘብ አይኖርህም:: ገንዘብ ከሌለህ ደግሞ ችግር ያበሳጭህና ለችግርህ ምክንያት በሆኑ ሰዎች ላይ አደጋ አድርሰህ በሌላ የከፋ ችግር ውስጥ ልትገባ ትችላለህ:: ያኔ ልብህ ለጭካኔ እንጂ ለፍቅር ቦታ አይኖረውም:: ዞሮ ዞሮ ለኔ አልሆንከኝም:: ታስረህ ማየቱም ለአዕምሮዬ አይመቸውም:: ብትሞትም ሀዘኔ መራርና የዕድሜ ልክ ነው:: ግን ይህ ሁሉ ይጠገድ ዘንድ ግዳጁን ተቀብለህ መሄድ ስትችል ለምን ሁለታችንም እንቸገራለን?» አለችው በትካዜ ውስጥ ሆና ዓይን ዓይኑን እያየች::

«ሒዩ የኔ ችግር አልገባሽም::»

«ገብቶኛል:: ግን እሱም ቢሆን መላ አለው::»

«ምን ታየሽ?»

«በቃ! እኔ ከእትብት-አበባ ቤት እወጣና አንተ በምትቆርጥልኝ ገንዘብ ከትርፍዬ ጋር በአንተ ቤት ውስጥ እኖራለሁ:: ግዳጅህን ፈጽመህ ስትመለስ እኔና አንተ

ራሳችን በምንደግሰው ሰርግ ተጋብተን አብረን መኖራችንን እንቀጥላለን:: ለኔና ለአንተ ፍቅር የሚበጀው ይኸ ብቻ ነው::» ከዚህ በኋላ ሁለቱም ትካዜ ውስጥ ገቡ:: ሁለቱም በየሙላቸው ያስቡ ጀመር! በየልባቸው ያለውን ነገር በማስታወስ::

እሷ አላወቀችም እንጂ ዛሬ ሒዋን ያቀረበችው ሀሳብ አስቻለው ራሱ በተካረለበት ጉባዔ ላይ የተቀየሰ አቅጣጫ ነበር:: እርግጥ ነው የአስቻለው የዘመቻውን ግዳጅ ያለመቀበል ውሳኔው እጅግ ጠንካራ ነበር:: ነገር ግን ታፈሡና በልሁ መርዕድን ጨምሮ ሀሳቡን እንዲቀይር ብዙ ታግለውታል:: የስድስት ወር ጊዜ እጥር መሆኗን፣ ዘመቻውን ባለ መቀበሉ ከሥራ መባረር፣ ምናልባትም እስር፣ ከዚያም ያለፈ ክፉ ነገር ሊመጣ እንደሚችል እየጠቀሱ ሊያግባቡት ሞክረዋል:: በዚያው በራሱ ቤት መርዕድና በልሁ ጫት እየቃሙ፣ ታፈሡ ራሷ እስከ ውድቀት ሌሊት ድረስ አብራቸው በመቆየት በዚህ ጉዳይ ላይ ከአስቻለው ጋር የተፋጨት ገና ደብዳቤው በደረሰው ማግስት ጀምሮ ነበር:: በአስቻለው ግዳጅ የመቀበልና ያለመቀበል ውይይት ወቅት ጉልህ ሥፍራ ተሰጥቶት የነበረው የአስቻለውና የሒዋን ፍቅር ጉዳይ ነበር::

ለአስቻለው ለግዳጅ መመልመል የባርናባስ ሚና ወሳኝ ሊሆን እንደሚችል ሁሉም አምነውበታል:: እሱ ደግሞ ከራሱ ፍላጎት በተጨማሪ ሸዋዬ የምትጥልበትን አደራ ለመወጣት ጭምር አስቦና ተገፋፍቶ የፈጸመው ስለመሆኑ አይጠራጠሩም:: ሁሉቱ ሰዎች የአስቻለውን እስመኖር ተጠቅመው ሊፈጽሙት ያቀዱት ነገር በሁሉም አዕምሮ ውስጥ አለ:: ሒዋንን ከበድሉ አሸናፊ ጋር ሊያላምዱ ነው:: ይህ ደግሞ በአስቻለውና በሒዋን ፍቅር ላይ ጥላውን ሊያጠላ ነው::

ይህን አደጋ ለመከላከል ይቻል ዘንድ መላ መልምለዋል:: በአንድ ወይም በሌላ መንገድ ሒዋንን ከሸዋዬና ከባርናባስ መዳፍ ውስጥ ፈልቅቀው ማውጣት፣ ዋሽቶም ለምኖም ሒዋንን የችግሩ ፈቺ አንድ አካል ማድረግ:: በዚህ ጉዳይ አስቻለውን ጨምሮ ሁሉም ተስማምተዋል:: ሒዋንን የማሳመን ጉዳይ ለታፈሡ እንግዳሰው ተሰጥቶ እሷም የተጣለባትን ሃላፊነት ለመወጣት አልዘገየችም:: ለአስቻለው የዘመቻ ትዕዛዝ በደረሰው አራተኛ ቀን ላይ ነበር፣ ሒዋንን ከመሠረተ ትምህርት ሥራዋ ስትመለስ ወደ ቤቷ ጎራ እንድትል የጠየቀቻት:: ሒዋንም ጥያቄውን ተቀብላ ከታፈሡ ቤት ተገኘች::

«ሒዩ ተቸግረናል» ነበር ያለቻት ታፈሡ ሒዋንን ሶፋ ላይ አስቀምጣ እሷም ከፊትለፊቷ በመቀመጥ::

«ምን ሆናችሁ?»

«አስቻለው በመሥሪያ ቤቱ በኩል ዘመቻ ታዝዞ ነበር ግን አልሄድም በማለቱ እኔም በልሁና መርዕድም ተጨንቀናል::»

«ዘመቻ?»

«አዎ፣ ለስድስት ወር ብቻ ለሚቆይ የሙያ ዘመቻ ወደ ኤርትራ እንዲሄድ በደብዳቤ ታዟል። እሱ ግን ሔዋንን በሸዋዬ ቤት ውስጥ ትቷ አልሄድም እያለ አስቸግሮናል።»

«ኤርትራ ማለት የጦርነቱ አገር አይደል?»

«አዎ፣ እሱ ግን የሚሄደው ሊዋጋ አይደለም፣ በጦርነቱ ለሚጎዱ ቁስለኞች የህክምና አገልግሎት ሊሰጥ ነው።»

«ታዲያ እንዴት ይሻላል?»

«ችግሩ ያለ አንቺ አይፈታም?»

«ምን አድርጌ እፈታዋለሁ?»

«አስቹ የሚለው ወደዚህ ዘመቻ እንድሄድ ያደረጉኝ ሸዋዬና ባርናባስ ናቸው። ዓላማቸውም ሔዋንን ለበድሉ አሸናፊ ሊድሩ አስበው ነው። ስለዚህ ፍቅሬን ከማጣት እነሱ ላይ አደጋ አድርሼ እስር ቤት ብገባ ይሻለኛል እያለ ድርቅ አለብን።»

«ያን ያህል ታፈሀዩ!»

«አዎ ሐዩ፣ ስሜቱ ተለዋውጦብናል።»

«ምን አድርጊ ትይኛለሽ ታዲያ?»

«አንቺ ከሸዋዬ ቤት ውጭና በአስቻለው ደሞዝ ከትርፌ ጋር አስቻለው ቤት ኑሪ።»

«አይከብድም ታፈሀዩ?»

«ለፍቅር ሲባል ከዚህም በላይ መስዋዕትነት ይከፈላል። ይህን ካላደረግሽ የአስቻለው ህይወት መበላሸቱ ነው። አንቺም ታጭዋለሽ። እሱም ያጣሻል። ዘመቻ ካልሄደ ከሥራ ያባርሩታል። ያኔ ይቸገራል። ከተቸገረ ይበሳጫል። ከተበሳጨ አደገኛ የሆነ የህይወት ርምጃ ይወስዳል። ኢላማዎቹ ደግሞ ሸዋዬና ባርናባስ ናቸው። አስጨናቂው ነገር ይህ ነው። ይህ ደግሞ በአንቺ ቆራጥ ውሳኔ ሰላማዊ መፍትሄ ያገኛል።»

«እኔ ቢሳካልኝ እሱ ግን ዘመቻውን እሺ ብሎ ይቀበላል?»

«አያወላውልም።»

ይህ ነበር ከዛሬው የአስቻለውና የሔዋን ውይይት በስተጀርባ የነበረው ክንውን።

«አስጨነቅሽኝ ሔዋን!» አላት አስቻለው የሆዱን በሆዱ አድርጎ። ሔዋን ብታውቀው ኖሮ በዕለቱ አልጋ ላይ ተኝቶ ይጠባበቅ የነበረው እንኳ ይህንኑ ሀሳብ ልታተርብለት እንደምትመጣ ስለሚያውቅ ነበር።

«ቢጨንቀኝ ነዋ አስቹ!»

«ግን ከልብሽ አምነሽበታል?»

«አሁን አሁን ሲገባኝ እንዲያውም የዘገየሁ እየመሰለኝ መጥቷል። ራሴ እየተጨነኩ አንተንም ሳስጨንቅ መቆየት አልነበረብኝም። አንተ ጋር ሆኜ የሚመጣውን ችግር ሁሉ በአንተ ከለላ ልከላከለው ወስኛለሁ።»

አስቻለው ከተንጋለሰበት ብድግ ብሎ ሔዋንን ሳማት። እሷም ሳመችው። ግን ደግሞ ሁለቱም ሆዳቸው ባባና ተላቀሱ።

ተጣዮቹ ቀናት የአስቻለው የጉዞ ዝግጅት ጊዜ ሆኑ። ከሁሉ በፊት የደመወዙን ውክልና ለበልሁ ሰጡ። ቀጥሎም ሔዋንና ትርፌን አስቀምጦበት የሚሄደው ቤት ከግለሰብ የተከራየው በመሆኑ እሱ በሌለበት ችግር እንዳይፈጠርባቸው ከባለቤቱ ጋር የቃልም ሆነ የጽሁፍ ውል ማሰር ነበረበትና ጥረቱን ጀመረ።

የቤቱ ባለቤት አቶ ከድር አህመድ በቀበሌ ዜሮ ሰባት ውስጥ ይኖራሉ። የሚኖሩባት ቤት ከመጥበሟ የተነሳ ከአንድ ፍራሽ የተረፈችው የሳሎን ቦታ ሌላ ፍራሽ አታዘረጋም። ከሜት መቃሚያ ፍራሻቸው ፊትለፊት ሁለት ወይም ሶስት የዱካ መቀመጫዎች ብቻ ተደርድረዋል። አስቻለውና ሔዋን በተወያዩ በሶስተኛው ቀን ከምሽቱ አሥራ አንድ ሠዓት አካባቢ አስቻለውና በልሁ አብረው ሄዱ። ከአቶ ከድር ቤት ሲገቡ ከባለቤታቸው ጋር ፍራሽ ላይ ጎን ለጎን ቁጭ ብለው ጫት ሲቅሙ አገኟቸው።

«ምን እግር ጣላችሁ ዛሬ ልጆች?» ሲሉ አቶ ከድር አስቻለውና በልሁን ጠየቋቸው። አቶ ከድር በጣም ጥቁር ከመሆናቸው የተነሳ ነጭ ጥርሳቸውን ገለጥ ሲያደርጉት የሰው ዝንጉርጉር መስለው ይታያሉ። በዚያ ላይ ስፌድ የሚያህል የአይታ መነጽራቸው ግማሽ ፊታቸውን ሸፍኖት ሲታዩ ሁኔታቸው ያስፈራራል። ዕድሜያቸው ወደ ሰባ ዓመት የሚጠጋ ሲሆን ሰውነታቸውም መጨማደድ ጀምሯል።

«ስለ ቤት ጉዳይ ላነጋግርዎት ነበር።» አላቸው አስቻለው ከፊትለፊታቸው ባለች ዱካ ላይ ከበልሁ ጎን ተቀምጦ።

«ልትለቅ ነው?»

«አይ! አይደለም።»

«እንግድያማ ኪራይ ልትጨምር ማሰብህን ልትነግረኝ ነው የመጣኸው!» ሲሉ አቶ ከድር ቀለዱ። ጎንበስ ብለው ፈገግ በማለት ጫት ይቀነጣጥባሉ።

«ቢሆንስ ምን ችግር አለው?» አለ አስቻለው በፈገግታ እየተመለከታቸው።

«ጎሽ የኔ ምሁር፣ አፍክን በዳቦ!» በዚህ ጊዜ ባለቤታቸው ወይዘሮ ሰሚራ አሊ ጭምር በቤቱ ውስጥ ያሉት በሙሉ ሳቁ።

«ለአንድ ስድስት ወር ያህል ወደ ሌላ አገር በጊዜያዊነት ልሄድ ስለሆነ ቤቱ ውስጥ አስቀምጫቸው ስለምሄደው ሰዎች ጉዳይ እንድንነጋገር ብዬ ነው የመጣሁት።» አላቸው አስቻለው ወደ ቁም ነገሩ በመመለስ።

«የት ልትሄድ ነው?»

«ወደ ኤርትራ ነው፣ ዘመቻ!»

«አኪምነቱን ትተህ ወታደር ሆንክ እንዴ?» አሉ አቶ ከድር በዚያ መነፅራቸው ውስጥ ቀና ብለው እያዩት። አስቻለው የአስተሳሰባቸው አቅጣጫ እንደ መገረም ብሎት በልሁን እያየ ፈገግ ካለ በኋላ-

«አይ ለሌላ ሥራ ነው።» አላቸው።

«ወደዚያ የሚኬደው ለጦርነት ስለሆነ ብዬ ነዋ!» ካሉት በኋላ «ታዲያ ማንን ልታስቀምጥበት ፈለግህ?» ሲሉ ጠየቁት።

«ስራተኛዬንና አሙኖዬን!»

«ሁለቱም ቤቶች?»

«አዎ» አለና እስቻለው ወደ በልሁ እያመለከተ «ይሄ ወንድሜ የወር ኪራዩን አቤትም ድረስ እያመጣ ይከፍልዎታል።»

«እዶ...!» አሉና እንደ ማቅማማት አሉ። ወደ ባለቤታቸው ዞር በማለት «ይገን ነገር እንዴት ታደያለሽ ስሚራ?» ሲሉ ጠየቋቸው።

እርጅና ወደት ያለባቸውና ቀይ ፊታቸው ጨምደድ ማለት የጀመረው ወይዘሮ ስሚራ ሙሉ ሰውነታቸውን በሰፊና ረጅም ቀሚሳቸው ሸፍነው በቀይ ነጭ ቡራቡሬ ንፍታ አንገትና ጭንቅላታቸውን ተከናንበው በመቀመጥ ዓይን ይትማሉ። ደበናና የሲኒ ረከቦት ከፊታቸው ደርድረዋል።

«እኔ ደሞ ምን አውቄ!» አሏቸው አቶ ከድርን ማየት ትተው ከፊታቸው ያለውን የገስል እሳት ቆስቆስ እያረጉ።

«ችግር እኮ የለውም አባ ከድር!» አላቸው እስቻለው የባልና ሚስቱ ምልልስ ትንሽም ቢሆን ወደ ስጋት ስሜት ወስዶ አደረገውና ለማስተማመን።

«ስማ የኔ ልጅ!» አሉ አቶ ከድር እንንብሰው ጫታቸውን እየቀነጣጠቡ።

«አቤት!»

«የሴት ነገር ያው የሴት ነው። በዚያ ላይ ደግሞ አንተ የምትሄደው ወደ ጦር ሜዳ ነው። ድንገት መጃለፍም ሊኖር ይችላል። በመሀል ታዲያ ችግር የተፈጠረ እንደሆን ሰዶ ማሳደድ አይሆንም ብለህ ነው?» ሲሉ ጥያቄ አዘል አስተያየት ሰጡና ቀና ብለው ተመለከቱት።

በዚህ ጊዜ በልሁ ንድድ ብሎት በሆዱ ‹ምን ዓይነት ፊልፊላ ሽማግሌ ነው› አለና «የሆነው ቢሆን በእርስዎ ቤት ላይ ምን ይመጣል ብለው ፈሩ?» ሲል ኮስተር ብሎ ጠየቃቸው።

«አይደለም! አይደለም! መፍራት ጥሩ ነው።» ባይሆን ስሞኑን ከሰሚራ ጋር ተነጋግረን የደረሰበትን ሁኔታ እንገልጥላችሁ እንዲሆን እንጂ...» ብለው ነገራቸው፤ ንተት ሲያደርጉት በልሁ ድንገት ከተቀመጠበት ብድግ አለና፦

«ቢቃ ጌታዬ! ምንም አያስፈልግዎ፣ ነገ መጥተው ቤትዎን ይረከቡ።» አለና ወደ እስቻለው ዞር ብሎ «ተነስ እንሂድ!» ብሎት ቀድሞ ከቤት ወጣ።

እስቻለው በአቶ ከድር ሁኔታ ሆዱ እየበሸቀ ነገር ግን በልሁ ምን አስቦ እንደሆነ ግራ እየገባው ብድግ ብሎ ተከተለው። ከደረሰበትም በኋላ ምንም የተለየ እማራጭ አልነገረውም። ብቻ «ና ወደ ታፈሁ ጋ ሄደን በጋራ እንነጋገርበታለን።» ብሎት ሁለቱም ዝም ብለው ወደ ታፈሁ ቤት አመሩ።

በልሁ ገና ሔዋን ከሸዋዬ ቤት መውጣት እንዳለባት ሀሳብ ከቀረበ ጀምሮ ምናልባት እሺ ብላ ከወጣች በማለት ስለምትኖርበት ቤት አንድ ነገር ሲያሰላስል ቆይቷል። በእሱ እምነት የሸዋዬና የእስቻለው ቤት ተቀራራቢ በመሆኑ ሸዋዬ ነጋ መሸ እየተመላለሰች ሰላም ልትነሳት ትችላለች። የእሱ ቤት ደግሞ በዜሮ ሁለት ቀበሌ ውስጥ ለዚያውም ዙሪያው በግንብ የታጠረና የተከበረ የትልቅ ሰው ግቢ ነው። ለርቀቱም ለፀጥታውም ምቹ ስለሆነ ሔዋንን ከትርፌ ጋር እዚያ አስገብቶ እሱ በእስቻለው ቤት ውስጥ የመኖር ሀሳብ ነበረው። አቶ ከድር ግን እቅዱን አበላሹበት።

በልሁ ይህንኑ እያሰበ ከእስቻለው ጋር ተጉዞ ከታፈሡ ቤት ደረሱ። ሁለቱም ገብተው ከታፈሁ ጋር ቁጭ ሲሉ በልሁ አንድ ነገር ብቻ ለሁለቱም ነገራቸው።

«ስለ ቤት ጉዳይ ምንም አታስቡ። ቢቻል ነገ፣ ካልሆነ ግን ከነገ ወዲያ ሔዋን ኳኒን ጠቅልላ ከሸዋዬ ቤት የምትወጣበትን ሁኔታ ብቻ አስቡ። ሌላውን ነገር ለኔ ተውት!» አላቸው።

የሆነውም ይኸው ነበር። በልሁ ያሉትን ልብሶችና የመጽሐፍ መደርደሪያ ይዞ ከአንድ ሆቴል ውስጥ የኮንትራት አልጋ ይዞ ገባ። ሔዋንም እንኳንስ ጫማ እና ልብሶቿ፣ የእለቱ የእስክሪብቶ ቀፎ እንኳ ሳይቀራት ኳኒን ጠቅልላ በሚቀጥለው ቀን ወደ ታፈሡ ቤት መጣች። በዚያ ቀን ማግስት ምሽት ላይ ደግሞ ከትርፌ ጋር በበልሁ ቤት ውስጥ ቤት ለእንቦሳ ብለው ገቡ።

የዚያን ዕለት ለእስቻለው አጠር ያለ ሽኝት ተዘጋጀ። አዎ፣ ስንቁ ጥሩ ምግብ ተበላ፣ መጠጦች በያይነቱ ተጠጡ። ነገር ግን መከፈሪያ ኖሮት የሚሉ ቢሆን ኖሮ በሽኝቱ ዕለት ሲወርድ ያመሸው እንባ ምን ያህል ከመያገኘው ተርፎ በፈሰስ ነበር። ሔዋን በሰቀቀን "እየየ" ስትል እስቻለው በቁጭት "እህህ" ሲል እዕናንና ጋብገሮቹ ታፈሡ፣ በልሁና መርዕድም ከእጃቸው ላይ መሀረብ ሳይለዩ ለሲቱ ወሰል ብሎ ነጋ።

እስቻለው በጠዋት በማለዳ ተነስቶ ወደ አዲስ አበባ ሲጓዝ ዋለና በስተኛው ቀን ቀትር ላይ ደግሞ በአይሮፕላን ወደ አስመራ።

በተሳፈረበት አይሮፕላን ውስጥ አየር ላይ ተንሳፎ ሳለ ሁለት ሀሳቦች ተፈራረቁበት። በአንድ በኩል የሽኝቱ ዕለት ማታ ሔዋን ስትሆን ያመሸችው እና ጠዋት ከዲላ አውቶቡስ መናኸሪያ ወደ አዲስ አበባ ስትሸኘው መላ ሰውነቷ በለቅሶ እየተንሰቀሰቀ፣ ሙሉ ፊቷ በእንባ እንደ ረሰረሰ፣ ባልተለመደ ሁኔታ ማንቁርቱ ላይ ተጣብቃ "ክፉ አይንካህ እስቹ"! ያለችው ትዝ ብሎት ሆዱ ባባና ከፋኛ አለቀሰ። በሌላ በኩል ግፈኞች ለራሳቸው ህልውና ሲሉ በቀሰቀሱት እና እሱ በማያምንበት ጦርነት በተፅዕኖ ተሳታፊ እንዲሆን የመደረጉ ቁጭት እንገበገበው። ከንፈሩን እየነከሰ ራሱን እንደ ወዘወዘ፣ አይሮፕላን ውስጥ ስለመሆኑ ለአንዴም ሳይታወቀው፣ በሀሳብ እንደዋለለ ከአንድ ሰዓት ተኩል በረራ በኋላ ልክ ዘጠኝ ሰዓት ላይ አስመራ ከተማ ደረሰ፤ ኤርትራ!!

ምዕራፍ ዘጠኝ

«ሄሎ! ሄሎ! አስደሳች ዜና ለዲላና አካባቢዋ ነዋሪዎች በሙሉ! ታዋቂውና ዝነኛው የፖሊስ ኦርኬስትራ የሙዚቃ ቡድን የተለያዩ አዝናኝና አስደሳች ጣዕመ ዜማዎችን ይዞ እነሆ በመካከላችሁ ተገኝቷል!! ቦታ በዲላ የሕዝብ መሰብሰቢያ አዳራሽ! ሰዓት ከምሽቱ አስራ ሁለት ጀምሮ! የመግቢያ ዋጋ አሥር ብር—ር ብቻ» ይላል አንድ የሙዚቃ ቡድኑ አስተዋዋቂ በፖሊስ መርሴዲስ መኪና በከተማዋ ዋና ዋና መንገዶች ላይ እየተዘዋወረ። አስተዋዋቂው ተናግሮ ሲያበቃ ጆሮ የሚስብ ሙዚቃ በድምጽ ማጉያ ይለቀቃል።

የከተማዋ ነዋሪ ለማስታወቂያው የተለያየ ምላሽ ይሰጣል። እንዳንዱ በዓመት ከአንድ ወይም ከሁለት ላልበለጠ ጊዜ የማይገኝ ዕድል በመሆኑ እንዲመልካም አጋጣሚ እየቆጠረው ‹ኦ! ብራቮ!› ይላል። ሌላው ደግሞ የመግቢያ ዋጋው ለእሱ አቅም የማይተመስ እየሆነበት ‹እምበላው ባገኝሁ እንኳን ለአንተ አስር ብር ላወጣ!› ሲል ‹የአብዮት ዘፈን በሬዲዮም ሰልችቶኛል› የሚልም ነበር።

ዕለቱ የሥራ ቀን ነበርና የመንግስት ሰራተኞች ማስታወቂያውን የሰሙት ከሥራ ሲወጡ ነው። በልሁ ከአንድ የሥራ ባልደረባው ጋር ወደ ዋናው የከተማዋ መንገድ ሲያመራ መኪናው የመንገድ ዳር ይዞ በመቆም ቲኬት ሲሸጥ አዩት።

«ለእንዲህ ዓይነት ነገር ባለቤቴ በጣም ትጓጓለች፣ እንደ ምንም ብዬ ይገርት መግባት አሰብኩ።» አለ የበልሁ የሥራ ባልደረባ።

«እኔስ ማንን ይዤ ልግባ?» አለ በልሁ ፈገግ ብሎ የሥራ ባልደረባውን እየተመለከተ።

«እንደ ፈረደብህ ብቻህን ተንለታ!» አለው ሰውዬው ሳቅ እያለ።

ግን ሁለቱም ቲኬት ወደሚሸጥበት ቦታና መኪና አመሩ። የበልሁ የሥራ ባልደረባ ሃያ ብር አውጥቶ ሁለት ቲኬት ሲገዛ በልሁም «ለኔም ሁለት!» ሲል የሰማው የሥራ ባልደረባው በልሁን ሳቅ ብሎ አየት እያደረገው:-

«ማምሽህን ልታገባ!» ሲል በነገር ወረፍ አደረገው።

«ማን ያውቃል! ትንታና ፍቅር ድንገት አይደል፣ ምናልባት አንዷን ቢያጋጥመኝስ!» አለ በልሁም ፈገግ እያለ።

በልሁ እንዲህና እንዲያ እያለ ከሰውየው ጋር ይቀልድ እንጂ በሆዱ ግን ሒዋንና ትርፌን የዕለቱ የሙዚቃ ታዳሚዎች አድርጎ ሊያዝናናቸው እያሰበ ነበር። ሒዋንና ትርፌን በሙዚቃ የማዝናናት ሀሳብ ለእነሱ ካለው ፍቅርና ከቸርነቱ ብቻ የፈለቀ አልነበረም። በሆዱ ሌላም ብዙ ብዙ የሀሳብ ጓዝ አለ።

እነሆ ልጓም አልባው ጊዜ የራሱን ጉደት ተከትሎ ሄዷል፣ ተምዘግዝጓል። አስቻለው ወደ አስመራ ከሄደበት ካለፈው ሰኔ ወር ቀጥሎ የነበሩት ሐምሌና ነሐሴ ሽው እልም ብለዋል። ቀጣዩቹ መስከረምና ጥቅምትም በፍጥነት ጥቅልል ብለዋል። ህዳርና ታህሳስም እንዲሁ ሳይመለሱ ተሸኝተው ወርሃ ጥር ከች ብሎ ራሱም ተጋምሷል። የፖሊስ ኦርኬስትራ የሙዚቃ ቡድን ወደ ዲላ ብቅ ያለው በዚሁ ወር ሦስተኛ ሳምንት ላይ ነው።

ይህ ሁሉ ጊዜ ሲያልፍ አስቻለውን የበላ ጅብ ለእንዷም ጮሆ አያውቅም፣ ቢደመጥ ቢደመጥ፣ ቢጠበቅ ቢጠበቅ ትንፍሽ አልል ብሎ ድራሹን እጥፍቷል። ለስድስት ወር ተብሎ የሄደው አስቻለው እንኳን መመለስ ድምፁ እንኳ ሳይሰማ ድፍን ሰባት ወራት አልፈዋል። ይህ ሁኔታ በዲላ የፍቅር ቤተሰቦቹ ላይ ስጋትና ጭንቀት ፈጥሮ ያተረማምሳቸው ይዟል፤ ከሁሉም በላይ ደግሞ ሒዋንን።

አስቻለው ወደ አስመራ ሲሄድ ለዲላ የፍቅር ቤተሰቦቹ የገባው ቃል ነበር፤ ቶሎ ቶሎ ደብዳቤ ሊፅፍ፣ ሁኔታዎች በፈቀዱለት መጠን ስልክም ሊደውል። ለነገሩ አንዲት ደብዳቤ ፅፏል። ያቺም ብትሆን ገና አስመራ በገባ ሦስተኛ ቀን ላይ ድንገት ወደ አዲስ አበባ የሚመለስ ሰው አግኝቶ ኖሮ ደህና መድረሱን የገለፀባት እንጂ ዝርዝር የናፍቆት ሀሳብና የተሟላ አድራሻውን የያዘች አልነበረችም። በዚያች ደብዳቤ ላይ የገለፀው ነገር ቢኖር ወደፊት ቋሚ አድራሻውን ሲያውቅ ሌላ ደብዳቤ እንደሚፅፍና ምናልባት ከአዲስ አበባ ወደ አስመራ በአይሮፕላን በረራ ላይ በነበረበት ወቅት ከሒዋን በመለየቱ ምክንያት ሆዱ ባቡቶ በናፍቆት ስሜት ውስጥ ሆኖ የቋጠራቸው እንደሆኑ የሚገመቱ ጥቂት የግጥም ስንኞችን ብቻ ነበር። ያቺ ደብዳቤ ዲላ የደረሰችውም ስትጣጣል ስንብታ ከተጻፈች ከአንድ ወር በኋላ ነበር። ቢቀ ሌላ የለም።

ሒዋን በልቧ ከአንድ ድምዳሜ ላይ ደርሳለች፣ ‹አስቻለው ደህና ባይሆን ነው› ከሚል። የአስቻለውን ደህና አለመሆን ባሰበች ቁጥር ሁለት ነገሮች በሁለት ቦይ እየፈሰሱ በሀሳብ ይወስዷታል። በአንድ በኩል የአስቻለው ደህና አለመሆን ፍቅሯን ሊያሳጣት ነው፤ የዕድሜ ልክ የመንፈስ ስብራት። በሌላ በኩል ስለ እሷ ‹ብልግና› ሸዋዬ ለቤተሰቦቿ የጻፈችባትን ደብዳቤ ታስታውሳለች። ያ ደግሞ የቤተሰቦቿን በተለይም የእናቷን ሆድ እንዳሻከረባት ትገምታለች። ይህን ሁኔታ ማስተየር ያስችላል ብላ የምትገምተው የአስቻለውን መልካም ሰውነት ነበር። እናትና አባቷ አንድ ቀን አስቻለውን ሲያውቁትና መልካም ሰውነቱን ሲረዱት ምርጫዋ ትክክል እንደሆነ በመረዳት የሻከረ ሆዳቸው ይሽርልኛል ብላ ትጓጓ ነበር። አስቻለው ደህና ካልሆነና ምናልባትም ያልተመለሰ እንደሆነ ግን ከሁለት ዛፍ የወደቀች ልትሆን ነው። ጭንቀትና ፍርሀቷም ከዚሁ ስጋት ይመነጫል።

ታፈሡ፣ በልሁና መርዕድ የሒዋንን ጭንቀት በብዙ መንገድ ይጋሩታል። የአስቻለው ደብዳቤ አለመጻፍ፣ ስልክ አለመደወልና የመምጫው ጊዜም በአንድ ወር ማለፉ እነሱንም በከፍተኛ ጥርጣሬ ውስጥ አስገብቷቸዋል። ይሁንና አንዳንድ የዘመኑን እውነታዎች በራሳቸው መንገድ እየተረጎሙ ራሳቸውንም ሆነ ሒዋንን ከማፅናናት አልቦዘኑም። ወትሮም እንደሚያደርጉት ሁሉ ሚት በመቃም ሰበብ ቀደም ሲል በልሁ፣ አሁን ደግሞ ሒዋንና ትርፌ በሚኖሩበት ቤት እየተሰበሰቡ መዋልና ማምሸታቸውን ቀጥለዋል። በዚያው ሂደት በበርካታ ጉዳዮች ላይ ይጎገመው ይነጋገራሉ። የአስቻለውን ደብዳቤ አለመጻፍ ጉዳይ ያነሱና ከወቅቱ ሁኔታ ጋር ለማገናዘብ ይሞክራሉ። በዚያን ወቅት መንግስት በፖስታ ቅብብሎሽ ላይ ከፍተኛ ቁጥጥር ያደርግ ነበር። ተቃዋሚዎች ከደጋፊዎቻቸው ጋር ምስጢር ይለዋወጣሉ በሚል ስጋት በተለይ የተጠርጣሪ ሰዎችን ፖስታ እየቀደደ መንገድ ላይ ያስቀር እንደነበር በሰፊው ይታወቃል። በተለይ ከኤርትራ ወደ ሌሎች

የሀገሪቱ አካባቢዎች የሚላኩ ደብዳቤዎች ለተላኩላቸው ሰዎች የመድረሳቸው ዕድል አስተማማኝ አልነበረም:: ምናልባት አስቻለውም የሚጽፈው ደብዳቤ መንገድ ላይ ተቀድዶ አየቀረ ይሆናል:: እሱ ደግሞ የተከፋ ብሶተኛ ነውና ይህንኑ በሚገኙ በደብዳቤው ላይ አስፍሮ ከተገኘ የባሰ ይጠረጠርና ሁለተኛውም ሦስተኛውም ደብዳቤዎቹ የዚሁ ሰለባ እየሆኑ ቀርተው ሊሆን ይችላል፣ በማለት ግምትና ጥርጣሬዎቸውን ይገልጻሉ:: ስልክ ያለመደወሉንም ጉዳይ ከዚሁ ከወቅቱ እውነታ ለይተው አያዩትም:: በወቅቱ ከአዲስ አበባም ሆነ ከሌሎች የሀገሪቱ አካባቢዎች አስመራን በሽቦ የሚያገናኝ ስልክ አልነበረም፣ በዓመታት ጦርነት ተበጣጥሰው አልቀዋልና:: አማራጭ የመገናኛ መንገዶች ሬዲዮና ቴሌ ግራም እሲያም ገመድ አልባ የማይክሮ ዌቭ ስልክ ናቸው:: ሬዲዮና ቴሌ ግራም ደግሞ ለአብዛኛው ሰው እንደ ልብ አይገኙም:: የማይክሮ ዌቭ ስልክም ገና በጅምር የቴክኖሎጂ ደረጃ ላይ ነው:: ከሚሰራበት ጊዜ የማይሰራበት ጊዜ ይበልጣል:: በሚሰራበትም ወቅት ወረፋው አሰልቺ ነው:: የእነታፈሡ ግምት ታዲያ ‹አስቻለው በዚህም ቢል በዚያ አልሆንለት እያለ ተቸግሮ ነው› በሚል ሀሳብ ይደመድማል:: የአስቻለው የመመለሻ ጊዜ ማለፉንም ካነሱ ‹ምናልባት የአይሮፕላን ጉዞ ወረፋ አልደርስ ብሎት ይሆናል› ከሚል ግምት አያልፍም::

ይህ ሁሉ ምክንያታዊ ትንተና ግን ለሔዋን አይገባትም:: ትሰማቸዋለች እንጂ አታዳምጣቸውም:: ለእሷ አንድ ነገር ብቻ ግልፅ ነው፤ በቃ አስቻለው እስካሁን አልመጣም፤ ድምፁም አልተሰማም፤ ምክንያቱ ደግሞ ደህና ያለ መሆኑ ነው:: የሚያስጨንቃት የእሱ ደህና አለመሆንና ምናልባትም ያልመጣ እንደሆነ የሚፈጠርባት የመንፈስ ቁስል ነው:: የዚህ ሁሉ አጠቃላይ ውጤት ታዲያ ራሷ ተጨንቃ እነታፈሡንም ማስጨነቋ ነው:: ሁኔታዋ ሁሉ ያሳዝናቸው ይዟል:: በልሁ ታዲያ ይህንን ችግር ለአንድ ቀንም ቢሆን የቀረፈ መስሎት ነው በሙዚቃ ዘና ትልለት ዘንድ የመግቢያ ትኬት መግዛቱ::

በልሁ ትኬቶቹን ይዞ በቀጥታ ያመራው ቀድሞ የእሱ፣ ዛሬ ደግሞ የሔዋንና የትርፌ መኖሪያ ወደ ሆነው ቤት አቅጣጫ ነበር:: ነገር ግን ከአንደኛ መንገድ ብዙም ሳይርቅ መርዕድ ከታች በኩል አስፋልቱን ይዞ ወደ ላይ ሲመጣ አገኘውና «ትኬት ገዝተሃል?» ሲል በቅድሚያ ጠየቀው::

«የምን ትኬት?» አለ መርዕድ በርገግ ብሎ::

«ዛሬ እኮ የፖሊስ ኦርኬስትራ መጥቷል::»

«ባክህ ተው! ለአንድ ቀን ምሽት አሥር ብር ከማወጣ በቋሚነት የምሰማው አንድ ካሴት ብገዛ አይሻልም?» አለው::

«እስቲ በልጅ እግርህ ወደነ ሔዋን ልላክህ!»

«ለምን?»

በልሁ ቲኬቶቹን ከኪሱ አውጥቶ እያሳየው «ሔዩና ትርፌ ዛሬ እንኳ ይዝናኑ ብዬ ትኬት ገዝቼላቸዋለሁ:: ስጣቸውና ሰዓቱ ሲደርስ አዳራሹ ድረስ እንዲመጡ ንገራቸው:: እነሱን አስገብተን እኛ ወደየጉዳያችን እንሄዳለን» አለው:: መርዕድ አላቅማማም፤ ቲኬቶቹን ተቀበለውና ሲመለስ የት እንደሚገናኙ ቀጠሮ ይዘው ወደ ሔዋንና ትርፌ ቤት ገሰገሰ::

የሙዚቃ ድግሱ ማስታወቂያ በድምጽ ማጉያ ይነገር በነበረበት ወቅት ብዙዎች ያለ መታደም አገምግሚያ የሚያመለክት አስተያየት ይሰጡ የነበረ ቢሆንም በወቅቱ እስከ ሰላሳ ሺህ ህዝብ ከሚኖርባት ዲላ ከተማ ውስጥ ከአንድ ሺ በላይ የማይዘውን የህዝብ መሰብሰቢያ አዳራሽ የሚሞላ የሙዚቃ አፍቃሪ አልጠፋም:: ሠዓት ደርሶ ሔዋንን እና ትርፌን ቦታ ለማስያዝ በልሁና መርዕድ ወደ ቦታው ብቅ ሲሉ በርካታ ሰው ወደ አዳራሹ እየገባ ነው:: በልሁና መርዕድ ሔዋንና ትርፌን በተጠሩበት ቦታ አግኝተዋቸው ወደ አዳራሹ ይዘዋቸው በመግባት ቦታ ሊያሲዟቸው ቢሞክሩም እነሱ ቲኬት ስላልያዙ ወደ አዳራሹ ለመግባት ተከለከሉ:: በሊያ ምትክ ትዕይንቱ እንዳይርቃቸው ወደፊት ሄደው መቀመጥ እንዲሰጣቸው መከሯቸውና እነሱ ወደ ውጭ ተመለሱ::

ሔዋን እና ትርፌ ግን አገባቡ ጭንቅ አላቸው:: በዚህ ዓይነት ዝግጅትና አዳራሽ ውስጥ ታዳሚ ሆነው አያውቁም:: የዝግጅቱ ተካፋይ ለመሆን የጓጉ ቢሆንም ሌላ ሰው እንደሚያደርገው ቦታ መርጠው ለመቀመጥ ድፍረቱን አጡ:: እንዲያውም ድብልቅልቁ አስፈራራቸው:: አዳራሹ ውስጥ ገብተው በመተላለፊያው ኮሪደር ላይ እንደ ቆሙ በርካታ ሰው ከኋላቸው እየመጣ አልፏቸው ቦታ ሲይዝ ተመለከቱ:: እንደ ምንም ጨክነውና በአዳራሹ መሀል አካባቢ ከቆሙበት የመተላለፊያ ኮሪደር በስተቀኝ በኩል በርካታ ባዶ ወንበሮች መኖራቸውን በማየታቸው ወደዚያው ለማለፍ ወሰኑ:: ሔዋን ከፊት እየመራች ትርፌ ከኋላ እየተከተለች በሰው እግር ስር እየተሹለከለኩ በሚያልፉበት ወቅት ሔዋን ድንገት ተወላከፈች::

«ውይ ይቅርታ!» ብላ ወደ ተወላከፈችበት ሰው ቀና ብላ ስትመለከት ክው ብላ ደነገጠች:: ያወላከፋት ሰው ከአሁን በፊት የምታውቀው ነው፣ በድሉ አሸናፊ::

«አይተሽ አትራመጅም እንዴ?» አላት በድሉ እንደ መንሽ የገጠጡ ጥርሶቹን ገለጥ አድርጎ በሀፍረት ፈገግታ ዓይነት እያያት::

ሔዋን ግን ስትራመድ በነበረችበት ወቅት ታደርግ የነበረውን ጥንቃቄ አስታውሳ ያ ሰው ሆን ብሎ እንዳወላከፋት ገብቷት እየተናደደች ዝም ብላው ወደ ባዶዎቹ ወንበሮች አለፈች:: ከትርፌ ጋር ፊንጠር ብለው ሰብቻቸው ተቀመጡና እንደ ማንኛውም ሰው የሙዚቃውን መጀመር ይጠባበቁ ጀመር::

ዝግጅቱ ደግሞ በጣም ተጓተተ:: ለአስራ ሁለት ሠዓት ጥሪ የተደረገ ቢሆንም ነገር ግን ከአንድ ሠዓትም አለፈ:: በዚያው መጠን ታዳሚው ‹ጀምሩ› በሚል የድምጽ ጥሪ ያፏጫል:: አንዳንዱም ያጨበጭባል:: አልፎ አልፎም የትረመርማል:: በዚህ መሀል ሔዋን ከአንዴም ሁለት ጊዜ ወደ በድሉ አሸናፊ ገልመጥ ባለችበት ወቅት እሱም አከታትሎ እንደሚያያት ተገንዝባለች::

ልክ ከምሽቱ አንድ ሠዓት ተኩል ሲሆን በመድረኩ ላይ ለየት ያለ ነገር መታየት ጀመረ:: መጋረጃ ሙሉ በሙሉ ተገለጠ:: የሙዚቃ መሣሪያ ተጫዋቾች ከነመሳሪያዎቻቸው ለተመልካች ዓይን ገጭ አሉ::

ተጨበጨበላቸው::

ወዲያው ከወደ ጀርባ በኩል አንድ ቀላ ረዘም ያለ ልጅ እግር ሰው ብቅ አለና በቋሚ ብረት ላይ ተሰክቶ የነበረ የድምጽ ማጉያ ነቅሎ ያዘና እጅ ነሳ::

ለእሱም ተጨበጨበለት::

«አመሰግናለሁ!» አለና ቀልድ ቢጤ ጣል አድርጎ ቀጣይ የሙዚቃ ዓይነቶቹንና ዘፋኞቹን አስተዋወቀ። ምስጋናውን ተቀብሎ ወደ ጆርባ ክፍል ገባ። የ ተከትሎ ሦስት መሢቃዎች በተከታታይ ተሰሙ።

ያ አስተዋዋቂ እንደገና ብቅ አለ። ድምጽ ማጉያውን ይዞ «ሕፃ ያንሳል! እ ያንሳል!» አለ።

ተጨበጨበለት።

«እስቲ እንደገና!»

አሁንም ተጨበጨበለት።

የሙዚቃ ድግሱ ገና ያልተነካ መሆኑን አበሰረና አሁንም ሦስት ሙዚቀኞች እንደሚቀርቡ አስተዋውቆ ተመለሰ። ወዲያው አንድ ጠየም! ስልክክ ያለ ድምጻዊ ብቅ አለና የድምጽ ማጉያውን ከተሰቀለበት ቋሚ ብረት ላይ አነሳ። ሙዚቀኞቹ አስቀድመው መሳሪያቸውን መጫወት ጀምረዋል። ድምጻዊው ማዜም ጀመረ።

«አስታውሽኝ አስታውሽኝ
አስታውሽኝ አስታውሽኝ
ያለ አንቺ ማን አለኝ።»

ብሎ ገና የዘፈኑን አዝማች ግጥሞች ሲጀምር ሒዋንን አንዳች የትዝታ ማዕበል ልቧን አናወጠው። ከቱጥጥሯ ውጭ በሆነ ስሜት «ትርፍዬ!» ብላ ከጭኗ ላይ ወድቅ አለች። በዚያው ድፍት እንዳለች ሆዷ እስከሚቦጫጨቅ፣ ጣቧ እስከሚርገፈገፍ ድረስ ስቅስቅ ብላ ታለቅስ ጀመር።

«ምነው እታለምዬ? ምነው?» አለች ትርፌ ለራሷም ድንግጥ በማለት። ከጭኗም ላይ ልታነሳት ሞከረች። ሒዋን ግን በጀ አላለችም። ይልቁንም በትርፌ ጭን ላይ መሽጎጫ የምትፈልግ ይመስል የባሰ ትጣበትባት ጀመር።

የሒዋን ድንገተኛ የትዝታ ማዕበል የተነሳው አስቻለው ጽፎላት ከነበረ ደብዳቤ ነው። ከሰባት ወራት በፊት የጻፉት ብቸኛ ደብዳቤ ከሒዋን አዕምሮ ሊወጣ የማይችል መልዕክት ይዛ ነበር። ደህና መድረሱንና ወደፊት ቋሚ አድራሻውን ሲያውቅ ሁሉንም ነገር አጠቃልሎ እንደሚገልጽላት ከጠቆመ በኋላ በስተ መጨረሻ ላይ የትዝታ ግጥሞችን ጣል አድርጎባት ነበር።

«መች እሰብከት ነበር መሄድ ከሲዳሞ፣
ከአንቺ ዓይን መራቁን መለየቱን ደሞ፤
ወይ ዕድሌ ጠሞ ወይ ሰዎች ጨክነው፣
አወጡኝ ከመንገድ ዕትዬን አምክነው።
ማስተዋልን ባው ይብላኝ ለእነሱ እንጂ፣
ለኔስ አንቺ አለሽኝ የልቤ ወዳጅ፣
አንቺ የዘላለሚ የኔ ፍቅር መውደድ፣
ምንጊዜም አትርሺኝ አስታውሽኝ የኔ ሆድ።»

ሒዋን ያቺን ደብዳቤ የሬት መስታወቷ አድርጋት ጠዋት ማታ ስታያት ቆይታለች። አስቻለው በዚያች ደብዳቤ ላይ ስጋና ደሙ ያለ እስኪመስላት ድረስ አምልካታለች። እያባባቻትም ታስለቅሳት ነበር። ዛሬ ታዲያ ድምጻዊው በመረዋ

ድምጹ፣ በሚያሳዝን ዜማ 'አስታውሽኝ አስታውሽኝ'፣ ሲል በመስማቷ አስቻለው ትዝ ብሏት ነው የሚልቀሷ ምክንያት።

«ወደ ቤታችን እንሂድ!» አለቻት ትርፌ ግራ ሲገባት።

«እሺ ተነሽ!» አለችና ሒዋን እንባዋን እየጠረገች ፊጥና ቀና አለች።

ዝግጅቱን አቋርጠው መውጣት ይፈቀድ አይፈቀድ የሚያውቁት ነገር አልነበረም፣ ግን ጨክነው ተነሱ። ከአሁን አሁን 'ቁጭ በሉ! አትነሱ!' የሚል ድምጽ የሚሰሙ እየመሰላቸው በመጨነቅ ርምጃቸውን ቀጠሉ። በአዳራሹ የቀኝ ግድግዳ ግማ ባለው መተላለፊያ መንገድ ላይ ተከታትለው ወደ መውጫው በር አቀኑ። ብዙ በተራመዱ ቁጥር ከልካይ እንደሌለ እየገባቸው ሄደና በመጠኑም ቢሆን ዘና አሉ። ከአዳራሹም ወጡና ቁልቁል ወደ ቤታቸው የሚወስደውን መንገድ ተያያዙት።

ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ተኩል አካባቢ ሆኗል። በርካታ ህዝብ ወደ አዳራሹ ስለ ገባ የከተማዋ መንገዶች ጭር ብለዋል። ግራና ቀኝ መንገድ ዳር ባሉ ቡና ቤቶች የቴፕ ጩኸትና የሰካራሞች ጫጫታ ጎልቶ በሚሰማበት ሁኔታ የሁለቱ ብቻ መንገድ ላይ መታየት እጅግ ያስፈራ ነበር። ሁለቱ ጆሮ ለጆሮ ገጥመው ግራና ቀኝ ገልመጥ እያሉ ሲራመዱ ከቆዩ በኋላ ንብረትነቱ የዲላ ማዘጋጃ ቤት ከሆነው የህዝብ መድሀኒት ቤት አካባቢ ሲደርሱ ከኋላቸው አንዲት ቶዮታ መኪና መጣችና እነሱን አልፋ እንደ መሄድ ካለች በኋላ እንደገና ወደ ኋላዋ ትሽከረከር ጀመር፣ ወደ እነሱ። እነሱ ደግሞ በቀኝ በኩል ታጥፈው ዜሮ ሁለት ቀበሌ ውስጥ 'ግሪን ፓርክ' ተብሎ ከሚጠራው መዝናኛ በታች ወደሚገኘው ቤታቸው ሊያመሩ ሲሉ ሾፌሩ ከመኪናዋ ላይ ወርዶ ወደ እነሱ ሲራመድ አዩት። ደንገጥ ደንገጥ ብለው እያዩት ሳሉ ከአጠገባቸው ደረሰ።

«ምነው በምሽት ብቻችሁን?» አላቸው ለሰላምታ እጁን በተለይ ወደ ሒዋን እየዘረጋ።

ሒዋን የሰውየውን ማንነት ወዲያው አወቀችው፤ በድሉ አሸናፊ ነው። እጇን መዘርጋት ትታ ወደ ትርፌ ደገፍ አለች። ዓይኖቿ ግን በበድሉ ላይ ስከት አሉ።

በድሉ አጭር ወፍራም ነው። ከአንገቱ ማጠር የተነሳ ጭንቅላቱ ትከሻው ላይ ቁጭ ያለ ይመስላል። መልኩ ጠቆር ያለ ጠይም ነው። እራት የፊት ጥርሶቹ ወጣ ብለው ገጠጥ ያሉና ዓይኖቹ ትናንሽና ድፍርስርስ ያሉ ናቸው። በዕለቱ ጥቁር ቆዳ ጃኬት በነጭ ቲሸርትና ነጣ ያለ ሱሪ ለብሷል።

«የእግዚአብሔር ሰላምታም ልነፈግ እንዴ?» አላት በድሉ የዘረጋውን እጁን ወደ ክንዷ አዙሮ ያዝ እያደረጋት።

«ልቀቀኝ!» አለችው ሒዋን በጨለማው ውስጥ ፊቷን ጭምድድ አድርጋ እያየችው።

«የማነጋግርሽ ጉዳይ አለኝ።» አላት ክንዷን ጠበቅ አድርጎ በመያዝ።

«ስለምን ጉዳይ?»

«ቅድም አዳራሽ ውስጥ ያስቀስሽው እኔ ስላወሳከፍኩሽ ከሆነ ይቅርታ ልጠይቅ እፈልጋለሁ»

«አይ! በእሱ አይደለም»

«ታዲያ ምን ሆነሽ ነው?»

«ዝምብዬ!»

«ዝምብሎማ ለትሶ የለም፤ የሆንሽው ነገር ካለ ንገሪኝ፤ ምናልባት ልረዳሽ እችላለሁ»

«አይ አይ! ምንም ዕርዳታ አልፈልግም። ልቀቀኝና እንሂድ፤ መሽቶብናል።» አለችው ሔዋን አሁንም ክንዷን ለማስለቀቅ እየታገለች።

«በመኪና አደርሳችኋለሁ»

«አያስፈልገንም፤ ቤታችን ቅርብ ነው»

«ቅርብ ከሆነ ታዲያ ምን አስቸኮለሽ?»

ሔዋንን ንድድ አላት። ክንዷን ደግሞ ጥብቅ አድርጎ ነው የያዛት። አሁንም እየታገለች «ልቀቀኝ! አለበለዚያ እጮሀለሁ!» አለችው።

«እጮሀለሁ?» ሲል በድሉ የሔዋንን ቃል ደገመው።

«አዎ፤ እንዳልጮህ ከፈለክ ልቀቀኝ»

«እኔም እጮሀለሁ» አለች ትርፌም። እስከ አሁን ድረስ ከአሁን አሁን የሚለቃት መስሏት ዝም ብትልም አሁን ግን የበድሉ አያያዝ አላምር አላት።

«አሃ! እንደ ከዚህ ቀደሙ ልታስደበድቢኝ ነዋ!» አላት በድሉ በተለይ ሔዋንን እያት እያረገ።

«መቼ አስደብድቤህ አውቃለሁ?»

«ረሳሽው?»

ሔዋን በድሉ ምን እያለ እንደሆነ ሊገባት አልቻለም። በእርግጥም ‹ጨዋ ጨዋ› የሚል ስሜት መጣባት። ነገር ግን በዚያ ጭር ባለ ቦታና ሰዓት ማን ሊደርስላት እንደሚችል አታውቅም።

«በእናትህ ልቀቀኝ!» አለች አዝና እንዲለቃት ለመለማመጥ።

«በልሁ ለሚባለው ሰውዬ ስለኔ ምን ብለሽ ነግረሽው ነው ሊደበድበኝ የተነሳው?»

«እሱ ሰው አይደባደብም»

«የተሞከረብኝ እኮ እኔ ነኝ»

«ምን አደረክ ብሎ ይደበድብሃል?» በማለት ትኩር ብላ ስትመለከተው በድሉ የታችኛውን ከንፈሩን ነክሶ መሬት መሬት እያየ ያስብ ጀመር።

ያስታውሳል፤ በድሉ ሔዋንን በሸዋዬ ቤት ውስጥ እጇን ጎትቶ ፍራሽ ላይ ሊያስቀምጣት በሞከረበት ሳምንት ውስጥ ነበር። ከአንድ ቡና ቤት ውስጥ ብቻውን ቁጭ ብሎ በሚጠጣበት ወቅት በልሁ በዚያ ቡና ቤት ውስጥ ገባ ሲል ሁለቱ ይተያያሉ። በልሁ ጠጋ ብሎ ሰላም ካለው በኋላ አጠገቡ ቁጭ ይላል። ወዲያው ያናግረዋል።

«ይቅርታ የኔ ወንድም፣ መቸም በዓይን እንተዋወቃለን»

«አዎ።» ይለዋል በድሉ ፈዘዝ ብሎ ከነበረበት ስሜት ነቃ እያለ።

«ላነጋግርህ የምፈልገው አንድ ጉዳይ ነበር»

«ምን ዓይነት ጉዳይ?»

«ሸዋዬ የምትባል መምህርት ታውቃለህ?» ሲል ይጠይቀዋል።

«አዎ»

«አልፎ አልፎም ቢሆን ወደ እሷ ቤት የምትሄድ መሰለኝ»

«ምነው?»

«ሔዋን ከምትባል እህቷ ጋር የተለየ ጉዳይ አለህ? ወይ ደሞ ሊኖርህ የምትፈልገው ነገር ይኖር ይሆን?»

«አልገባኝም የኔ ወንድም» ካለ በኋላ በድሉ በደረቁ ፈገግ ብሎ በልሁን እያየ

«እርግጠኛ ነኝ፤ ፖሊስ አይደለህም»

«ትክክል። ፖሊስ አይደለሁም። ልነግርህ የምፈልገው ግን ያቺ ልጅ እሙኛ አላት። ስለዚህ ላትጠቅምህ ነገር አንተም ባትለፋ እሷንም ባታስቸግራት ልልህ ፈልጌ ነው። ቅር ይልህል?»

«ይህንንም ለመግለፅ ራሷ ልጅቷ ትበቃለች። የአንተ ጣልቃ መግባት ያስፈልግ አልመሰለኝም» ይላል በድሉ ፊቱን ኮስተር አድርጎ።

«ጣልቃ መግባት አይደለም በድሉ፤ ጣልቃ ገቦችን ማስጠንቀቅ ፈልጌ ነው። ሳታውቅ ሳደረከው ነገር ይቅርታ ይደረግልሀል። ከእንግዲህ ወዲያ ብትሞክር ግን ሰው እየተዳፈርክ መሆኑን አውቀህ ብታስብበት ብዬ ነው»

«ብታስብበት?» በማለት በድሉ ቃሉን ይደጋግማል።

«ጨርሻለሁ» ብሎ በልሁ ትቶት ይወጣል።

ይህ ብቻ አልነበረም በወቅቱ በድሉን ትዝ ያለው ነገር። አንድ ዕቅዱም እንደከሸፈበት አስታወሰ። ሔዋን ጓሏን ጠቅልላ ከቤቷ በወጣች ዕለት ሸዋዬ ያሳበችው ዱብ ዕዳ ሆኖባት የምታደርገውን አጥታ ተሸብራ ነበር። ሔዋን ከታፈሡ ቤት የገባች መስሏት ዓይኗን በጨው አጥባ ከታፈሡ ቤት በመግባት ታፈሡን ራሷን ጠይቃት ነበር። ታፈሡ የሰጠቻት መልስ ደግሞ ‹ሔዋን እኔ ቤት ልትኖር አትችልም። የራሷን መኖሪያ አግኝታለች። ከእንግዲህ አታገኚያትምና ባትለፊ ጥሩ ነው› የሚል ነበር። የታፈሡ መልስ እና የሔዋን ድራሽ መጥፋት የበለጠ ሲያሳብዳት አድራ በማግስቱ ደሞ ሔዋን መሠረተ ትምህርት ወደምታስተምርበት ጣቢያ ሄዳ አግኝታት «የት ነው የሄድሽው እንቺ?» ስትል ነበር ዓይኗን አፍጥጣ ጥርሷን አግጥጣ የጠየቀቻት።

«እዚሁ ዲላ ውስጥ ነኝ»

«ወደ ቤትሽ ትመለሻለሽ ወይስ አትመለሽም?»

«ፈጽሞ አልመለስም»

አስደንጋጭ አቋም ነበር ለሸዋዬ። ለአንድ ሳምንት ያህል ስትብከነከን ቆይታ መጨረሻ ላይ በተለይ ከባርናባስና ከበድሉ ጋር በመሆን የቀቢፀ ተስፋ ምክክር አድርገው ስምምነት ላይ የደረሱበትም ዕቅድ ነበር። ሸዋዬ ያለ አስታራቂ ሔዋንን ለምናም ቢሆን ልትታረቃት፣ ‹እናታችን ጠርታናለችና ክብረ መንግስት ደርሰን እንምጣ› ብላ ልታታልላት፣ ሔዋን ‹ስራዬስ?› ያለቻት እንደሆነ ‹በአንድ ቀን አድርሶ የሚመልሰን ሰው አለ› ልትላት፣ እሺ ካለች በድሉ አለታ ወንዶ ድረስ ይዟቸው ሊሄድና እዚያው አለታ ወንዶ ከተማ ውስጥ ‹መኪናዬ ተበላሸች› ብሎ እየጎረጎረ ሊያስመሽቸው፣ ከዚያም ማረፊያ ሆቴል ይዘው ሊያድሩና በድሉ ሔዋንን ሊደፍራት። ከዚያም እዚያው አለታ ወንዶ ስነባብተው ሔዋንን ሊያባብሉና ሊያለማምዱ አስበው ነበር።

በእርግጥም ሸዋዬ ሔዋንን ለማታለል ብዙ ጥራ ነበር። ሔዋን ግን ፍንክች አላለችም። የእናቷ ጥሪ ትንሽ አሳስቧት በማማከር ዓይነት ሸዋዬ ያለቻትን ሁሉ ለታፈሡ፣ ለበልሁና ለመርዕድም ነግራቻው ነበር። በተለይ በልሁ ‹በአንድ ቀን አድርሶ የሚመልሰን ሰው አለ› የሚለው ነገር ገብቶት በጣም ይናደዳል። አንድ ቀን

መርዕድን አስከትሎ ወደ ሸዋዬ ቤት ይሄዳል። በአጋጣሚ ሸዋዬና በድሉ ፍሬሽ ላይ ቆሞ በስጦ ሞቶ ሲቅሙ ያገኛቸዋል። ቁጭ ሳይል በቁሙ።

«ሰሚ አንቺ!» ብሏት ነበር ሸዋዬን።

«አቤት!» ሸዋዬ በድንጋጤ ኩርምትምት አለች።

«አየሰራሽ ያለሽው ነገር ያልታወቀ እንዳይመስልሽ ደግሞ መደምትሰራበት ቦታ ብቻ ትደና ወጥልሽ ሔዋን እንኳን በአንድ የከረከሰች ሔዋን አደርገዋን ብታተርቢላት እስቻለው ሳይመጣ ክብሪ መንግስት አትሄድም። ገባሽ።» ካለ በኋላ በልሁ ቀጠል አድርጎም «ይህ ለአንቺም ሆነ ለባለ መኪናው የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ነው።» በማለት አገሬ መንገዱን በድሉንም ወረፍ አድርጎት ነበር። ድንገቱ በድሉ ምንም አልተናገረም እንጂ አንዲት ቃል ተንፍሶ ቢሆን ኖሮ በልሁ እቢያው ሊደፍቀው ከጅል አድርጎት ነበር።

«ሉ-እሺ!» ነበር ያለችው ሸዋዬ በድንጋጤ ድምጿ እየተቆራረጠ።

በድሉ አሸናፊ ታዲያ ይህን ሁሉ ውርደት ተሸክሞ ሊኖር ጠላቱ አድርጎ የሚያየውት ሔዋንን ነው። ዛሬ ያ ሁሉ ሙገር ስሜት መጣበትና «ግን በአንቺ የተነሳ ሲደነፉብኝ የምኖር ይመስልሻል?» ሲል ክንዷን ጠበቅ አያረገ ጠየቃት።

«ምን አድርጊ ነው የምትሉኝ?» አለችው ሔዋን ሙሉ ቁጣ ባለ አነጋገር።

«የምትሰሚ ከሆነ አንድ ነገር ልንገርሽ እፈልጋለሁ።»

«ሌላ ጊዜ ትንገረኛለህ»

«ለላው ጊዜማ የምንገርሽ ነገር እውነት መሆኑን የምታረጋግጪበት ነው።» ብሎ በድሉ ክንዷን ነትሮ እያረጋገጠ «ምን አትሁኚ! ኤርትራ የሄደ ሰው ይመለሳል ብለሽ ወርቃማ ጊዜሽን በከንቱ አታሳልፊ።» አላት።

ሔዋን ድንገት «ም.....ን!» ብላ በረጅሙ ጮኸች።

የመጨረሻ ምክንያት ቀድሞ እንዳሰበችው በድሉ እንዲሉቃት ብላ አልነበረም፤ የእስቻለውን ከኤርትራ ያለ መመለስ ጉዳይ ከተለያዩ ነገሮች ጋር አያይዛው እውነትም ሊተር እንደሚችል ድንገት ታይቷት ደንግጣና ተስፋ ነው። እስቻለው ከመዘግየቱ በተጨማሪ አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ስለ ሰው ሲያወሩ «እገሌ ኤርትራ ዘምቶ ነበር፤ ነገር ግን አለ አይባል፤ ሞተ አይባል፣ ይኸው ደብዛው ጠፍቶ» ሲባል ደጋግማ ሰምታለች። የበድሉ አስተያየት ከዚህ የመነጨና እውነትም እስቻለው በዚያው የሚቀር መሰሏት እንደቷ ተቆርጦ ነው። በድሉም ጩኸቷ አስደንግጦት ወዲያው ለተቃዋሚ ወደ መኪናው በመሮጥ አስነስቶ ተፈተለከ። ሔዋንም እያለቀሰች በትርፊ ድጋፍ ወደ ቤቷ አመራች።

በልሁና መርዕድ የትርፊንና የሔዋንን የሙዚቃ ምሽት ቆይታ ሊጠይቁና በዚያውም ትንሽ ሊያጨዋውቷቸው በማሰብ ከምሽቱ አራት ሰዓት አካባቢ ሄደው ከቤት ሲገቡ የሔዋንን ስሜት ለውጥው ብሉ አገኙት። ያለቀሰችበት ዓይኗ ሁሉ አባብሟል። አንዲት ወረቀት በእጇ ጭብጥ አድርጋ ደብ ትካዝ ብላ ተቀምጣለች።

«ምነው ሔዩ! ሙዚቃው አስለቀሽ ነበር እንዴ?» ሲል በልሁ ፈትለፈቷ እንደ ቆመ ጠየቃት።

«አይ» አለችና ሔዋን እንባዋ በዓይኗ ላይ ግጥም ሲልባት ወደ መሬት አቀረቀረች።

«ምንድነው ችግሩ?» በማለት በልሁ ያያዘችውን ወረቀት ተጠራጠረና ከእጇ ላይ ነጥቆ አድርጎ ሲያያት ያቺው የእስቻለው የመጀመሪያም የመጨረሻም ደብዳቤ ሆና አገኛት።

«ዛሬም እዚያው ነሽ?» አላት ቆጣ ብሎ።

መርዕድ ደግሞ ወደ ትርፊ ዞር አለና «ምን ሆናለች?» ሲል ጠይቋት መልሷን በጉጉት ሲጠብቅ ሔዋን ድንገት ቀደመቻቸው።

«በልሁዬ፤ አታስቡኝ! ኤርትራ የሄደ ሰው አይመለስም። በቃ እስቼ አገሬን ቀርቷል።» አለችው ቀና ብላ ዓይን ዓይኑን እያየች። ዓይኖቿ በእንባ የራሰው ሰማይ መሰሉ።

«ምን?» አለ በልሁ ክው ብሎ በመደንገጥ።

«በቃ! እሱን ነገሩ ሁሉ ገብቶኛል። እስቻለው ከኤርትራ አይመጣም።» ብላ ጉልበቷን በተለበተቿ ላይ አስደግፋ ስቅስቅ ብላ ታለቅስ ጀመር።

በልሁ አንድ ነገር ወለል ብሎ ታየው፤ የእስቻለው ሁኔታ በዚህ ከቀጠለና ምናልባትም መመለስ ባይችል በሔዋን አእምሮ ውስጥ ሊፈጠር የሚችለው አደጋ!!

ምዕራፍ አሥር

የሰሜን ኢትዮጵያ የእርስ በርስ ጦርነት ድምፁ እየበረከተ ሄደ። ተፋላሚ ወገኖች ዜናቸው ሁሉ የሞት ሆነ። ለጠደፊቷ ኢትዮጵያ ገኘነት መወደደሪያው በገደሉት ሰው ቁጥር እንዲሆን የተወሰነ ይመስል፤ የአንዱ ወገን ሬድዮ 'አንድ ሺ ገደልኩ' ካለ ሌላው ወገን ማታ ላይ 'ሁለት ሺ ገደልኩ' ይላል። ጦቅት እንዲሁ ይቀጥላል። የሚገለፀው የሟች ቁጥሩ ከዕለት ወደ ዕለት እየበዛ ሄደ። በየቀኑ 'መንግስት በሁለት ግንባር ሰርጐ ገቦችን ደመሰስኩ' ሲል አማፂያን ደግሞ 'አራት ቦታዎችን ከፋሽስት የጭቆና አገዛዝ ነፃ አወጣን' ይላሉ። በየቀኑ ተመሳሳይ ወሬ፣ ሀገሪቱ ምድሯ ብቻ ሳይሆን አየሯም በደም ተለወሰ። በመግደል ውድድር፤ በመገዳደል ዜና፤ በመጨራረስ አባዜ።

የሀገራቸውን እውነተኛ ዜና መዋዕል በራሳቸው ሀገር የዜና አውታሮች ለመስማት ያልታደሉ ኢትዮጵያውያን ሁለቱንም ወገኖች አያምኑም፤ የውጭ ራዲዮዎችን መኮርኮር ግድ ብሏቸዋል። እነዚያም ቢሆኑ አንዳንዴ 'መንግስት እንዲህ ይላል፤ አማፂያን ደግሞ እንዲያ... ነገር ግን በገለልተኛ ወገን አልተረጋገጠም' ይሉና የሕዝብ ልብ ያንጠለጥላሉ።

አንድ ነገር ብቻ ግልጽ ነው፤ በሰሜናዊ የሐገሪቱ ክፍል በየቀኑ ጦርነት አለ። በየቀኑ መድፍና መትረየስ ይተኮሳል። በየቀኑ ሰው ይሞታል። በየቀኑ ሀገር ትደማለች። በየቀኑ ንብረት ይወድማል። ከቀን ወደ ቀን እንጡራ ሐብቷ ይቀንሳል። በየቀኑ የህዝብ ስቃይ አለ። በየቀኑ ዋይታና ጩኸት አለ።

የአስቻለው ትዝታ ለዲላ የፍቅር ቤተሰቦቹ የሚደርሰው በዚሁ የሰቆቃ ሽታ እየተለወሰ መሆን ከጀመረ ሰነበተ። ስጋትና ፍርሀት በሁሉም ልብ ማደር ጀመረ። የጦርነት ወይም የሞት ዜና በተሰማ ቁጥር አስቻለው በሁሉም አዕምሮ ውስጥ ብቅ ድቅን ማለቱን ቀጠለ። ይፈሩ ጀመር። ይጨነቁ ጀመር።

ችግሩ በሔዋን ላይ ጠነከረ። ሳትወድ በግድ ሬድዮ ጉርጓሪ ሆነች። የምትሰማው ዜና ሁሉ ያስደነብራት ጀመር። በሆነ ቁጥር ሰው ሞተ ከተባለ አንዱ አስቻለው እንደሆነ ታስብ ጀመር። ለእሷ አስቻለው ትናንት ሞቷል። ዛሬም ይሞታል። ነገም እንዲሁ። ልቧ በፍርሀትና በስጋት ቆሰለ። አንጀቷ በሀዘን ይታጠፍ ጀመር። ዓይኗ እንባ አላቋርጥ አለ። በሀሳብ ብዛት የቀን ዕረፍትና የሌሊት እንቅልፍ አጣች። ለራሷ ሰላም አጥታ ሌሎችንም ሰላም ነሳች። በሁሉም ዘንድ ወለሌ ሆነ።

'በእንቅርት ላይ ... እንዲሉ ልክ ሚያዚያ ወር መጨረሻ ላይ ከዲላ ሆስፒታል አካባቢ አስደንጋጭ ወሬ ተሰማ። የአስቻለው ደሞዝ ተቋረጠ። በልሁ በውክልናው መሰረት አስቻለው ኤርትራ ከሄደ ጀምሮ ሲቆጠር የአስረኛ ወር ደመወዙን ሊቀበል ሲሄድ ገንዘብ በእጁ ሳይሆን ለጆሮው መጥፎ ዜና ሰጥተው መለሱት፤ '...በተላለፈልን ሰርኩላር መሰረት ደሞዙ እንዳይከፈል ተብሏል' የሚል። በልሁ ምክንያቱን ለማወቅ አጥብቆ ጠይቆ ነበር፤ ነገር ግን የተሰጠው ምላሽ የመጀመሪያው ደብዳቤ ከአስመራ ሊሆን እንደሚችልና ከዚያ ለዋናው መስሪያ ቤት፣ ቀጥሎ ለሲዳሞ ክፍለ ሀገር እንደገና ለአውራጃው ከዚያም ለዲላ ሆስፒታል

ሲተላለፍ አንዱ በሌላው ላይ ተመስርቶ ሲጽፍ ሲፃፍ የታገደበት ምክንያት አንዱ ጋር ተዘንግቶ ሊሆን እንደሚችል ግምታቸውን ከመግለፅ በቀር እቅጩን አልነገሩትም። አንድ ነገር ብቻ በግልጽ ነገሩት፣ ከእንግዲህ በአስቻለው ስም ደመወዝ ወጪ ሊደረግ እንደማይችል!! በልሁ መርዶውን ይዞ ተመለሰ። ዜናው ከታፈሡም ከመርዕድም ጆሮ ደረሰ። የአስቻለው ነገር ከዕለት ዕለት እየራቀ ሄደ። ይህን ዜና ለሔዋን እንዴት አድርገው ይንገሯት? ዝም አይሏት ነገር የአስቻለው ደመወዝ የሕልውናዋ መሰረት ነው። አይነግሯት ነገር ትሳቀቃለች ብለው ፈሩ። በእርግጥም እንደ ቁስል ፈሯት። የዚያኑ ያህል ታሳዝናቸው ጀመር። ለቀናት ያህል በሀሳብ ሲታመሱ ሰንብተው 'ሁሉም ለበጐ ነው' የሚለውን ኢትዮጵያዊ ብሂል ለመጠቀም ወሰኑ። 'ደስ ብሎናል ደስ ይበልሽ፤ የአስቻለው ደሞዝ ተቋረጠ። ይህ የሚያመለክተው የአስቻለውን በሕይወት መኖር ነው። ነገር ግን የመንግስት ሥራ ለቋል ማለት ነው። በሕይወት ባይኖር ኖሮ ጡረታ ወይም ዳረጐት ውሰዱ ይባል ነበር። አስቻለው ዱሮም የከፋው ሰው ነበርና በአሰብ ወይም በምፅዋ በኩል ሀገር ጥሎ ጠፍቶ ይሆናል፤ ይኸኔ ጀርመን ወይም ጣሊያን አገር ገብቷል። ደብዳቤውም በቅርቡ እንደሚደርሰን እናምናለን። ማን ያውቃል? አንቺንም ሊወስድሽ ይችላል።' እያሉ ሊያጽናኗት ተመካከሩ። 'ቀና ሲታጣ...' እንዲሉ ምርጫቸው ይኸው ብቻ ሆነ። ይህን ለመፈጸም በግንቦት ወር የመጀመሪያ ሳምንት ላይ ቅዳሜን መረጡ፤ ሁሉም ተሰብስበው በሔዋን ቤት ጫት እየቃሙ ለመዋልና እየተረዳዱ የሔዋንን ልብ ሊያደንቁሩ!!

በዕለቱ ታፈሡ ከሁሉም ቀድማ ከሔዋን ቤት ስትደርስ ከቀኑ ሰባት ሰዓት ተኩል አካባቢ ሆኗል። በትልቅ ሳህን ለሁሉም የሚበቃ ምግብ ይዛለች። ለራሷ የነጭና የጥቁር ቡራቡሬ ድሪያዋን ለብሳ፣ አዝነ አትለው አክፋይ ለሔዋን ደግሞ ሰዮት ያለች ስከርፍ ገዝታለች፤ ለስጦታ።

ቀጥሎ የደረሰው መርዕድ ነው፤ አውሎ ሊያስመሽ የሚችል ምርጥ የጫት ቅጠል ይዞ። የሐረሩ ልጅ መርዕድ የጫት ሥነ ስርዓቱን ያውቅበታልና ሁሉን ነገር ወዲያው አመቻቸው። በእሱ አመራር ሰጪነት ሰንደሉ ተለኮሰ። እጣኑ ተጨሰ። ቡናውም በብረት ምጣድ ላይ ይንቸሰቸስ ጀመር። የቤቱ መዓዛ ሙሉ በሙሉ ተለወጠ። ሥነ ሥርዓቱን ለመጀመር የበልሁ መድረስ ብቻ ይጠብቅ ጀመር። የጫት መቃም ልምድም ሆነ ሱስ የሌላት ታፈሡ ያለ ወትሮዋ በመሀል ፍራሽ ላይ ሙሽራ መስላ በመቀመጥ ቤቱን በቀልድና በጨዋታ ሞልታ በሳቅ እያፍለቀለቀቻቸው ሳለች ድንገት ከውጭ በኩል የሰው ድምጽ ተሰማ። የሴት ልጅ ጥሪ ይመስላል። ሔዋን ቡና እየቆላች ስለነበር ትርፌ ወደ ውጭ ወጣ አለች። ከውጭው በር ላይ አንዲት የአሥራ ሁለት ወይም የአስራ ሶስት ዓመት ዕድሜ ያላት ልጅ ቆማ አየችና ወደ እሷ ተጠጋች። ከልጅቷ አጠገብ ደርሳ አንገቷን ከውጭ በር ወጣ አድርጋ ስትለመለከት ደግሞ ከልጅቷ ጋር አንዲት በዕድሜ ጠና ያሉ ሴት ቆመው አየች። ሴትዮዋ ጠይም ናቸው። የባላገር ሴት ይመስላሉ። የነጭና አረንጓዴ ቡራቡሬ ቀሚስ በነጭ ነጠላ ለብሰዋል። ሳሳ ያለች ሸራ ጫማ አድርገዋል። ፀጉራቸውን በነጭ ሻሽ ግጥም አድርገው አስረዋል። እጆቻቸውን በነጠላቸው ውስጥ አድርገው ወገባቸው ላይ አጣምረው ቆመዋል።

«ምነው? ማንን ፈለጋችሁ?» ስትል ትርፌ ልጅቷንም ሴትዮዋንም ተራ በተራ እያየች ጠየቀቻቸው።

«ሔዋን የምትባል ልጅ እዚህ ቤት ውስጥ ናት?» ስትል ልጅቷ ትርፌን ጠየቀቻት።

«አዎ! ግን ምነው?» አለች ትርፌ ደንገጥ እንደ ማለት እያለች።

«እስቲ ብቅ በይ በያት»

ትርፌ ግራ ገባ እየላትም ቢሆን ወደ ቤት ተመለሰችና «እታለም! እንዲት ልጅና አንድ ተለቅ ያሉ ሴት ይፈልጉሻል።» አለቻት። ሔዋን ደንገጥ ብላ «ማን በማለት ትርፌን በመመልከት ላይ ሳለች ታፈሡ ቀድማ «ምን ዓይነት ሴት እማማ ዘነብ ይሆኑ እንዴ?» ስትልም ጠየቀች።

«እኔ እንጃ!» ብላ ሔዋን ወደ ውጭ አመራች።

ወዲያውኑ ልብ የሚሰነጥቅ ጩኸት ተሰማ። የሔዋን ድምጽ ስለመሆኑ ሁሉም አልተጠራጠሩም። ታፈሡ መርድና ትርፌም በትጽበት በመነሳት ወደ ውጭ ሮጡ። ሔዋን የሆነችውን ነገር ሳያውቁ ነገር ግን «ሔዩ አይዞሽ! ሔዩ አይዞሽ» እያሉ በመጯጯህ አጠገቧ ደረሱ። ከመደናገጣቸው የተነሳ ከግቢ ወጥተው በሩ ላይ ከደረሱ በኋላ እንኳ እየተከናወነ ያለውን ነገር በቶሎ ለመለየት ተሳናቸው። ሔዋን በሴትዮዋ እግር ላይ ወድቃ እየተንፈራፈረች «እማ...! እማዬ...! እማይዬ...!» በማለት ትጮሀለች። ሴትዮዋም በሔዋን ጀርባ ላይ እንገታቸውን አንተርሰው «ልጄ! እሙዬ!» ይላሉ። የእናትና ልጅ ናፍቆት የፈጠረው ድንገተኛ ትርምስ ኖሯል። ታፈሡ ፈጥና ወደ ትንቅንቁ በመግባት «ኧረ ምንድነው? ኧረ እባካችሁ!» እያለች የሔዋንን እናት ከሔዋን ጀርባ ላይ ለማንሳት ስትታገል መርዕድ ደግሞ ሔዋንን ከእናቷ እግር ላይ ለማንሳት ይፍጨረጨር ጀመር። ትርፌ ግራ ገብቷት ቆማ ታለቅሳለች።

«እናቷ ነኝ ልጆች! እስቲ እሷን አንሱልኝ! ኧረ እስቲ በርቱልኝ!» አሉ ሴትዮዋ እንባቸውን እያዘሩ። ሔዋን በእግራቸው ላይ ተጠምጥማ ስትጮህ ታፈሡና መርዕድ ቀና ሊያደርጓት ሲሞክሩ በልሁ ድንገት ደረሰ።

«ምንድነው ታፈሥ? ምንድነው መርዕድ?» አላቸው ድንገጥ ብሎ ዓይኑን ወዲያ ወዲህ እያማተረ።

«ሔዋንን አንሳልን በልሁ። እናቷ ናቸው። ቶሎ በል!» አለችው ታፈሡ ሔዋንን ከእናቷ እግር ለማንሳት እየታገለች።

አጅሬ በልሁ ታፈሡንም መርዕድንም ገፈታትሮ ብቻውን ጐንበስ በማለት ሔዋንን ከእናቷ እግር ላይ ፈልቅቆ አነሳት። ሔዋን ግን ወዲያው ቀሚሳቸውን ሙጭኝ አለች። አሁንም «እማ! እማዬ! እማይዬ! በማለት ማልቀሷን ቀጠለች። እናቷም «አይዞሽ ልጄ! አይዞሽ እሙዬ!» እያሉ እንደ ልጃቸው ያለቅሱ ጀመር።

ሔዋንና እናቷ እንደተነፋፈቁ እናትና ልጅ ሳይሆን በሙጫ እንደተጣበቁ ወረቀቶች ተያያዘው በበልሁና በታፈሡ ግፊት ወደ ቤት ገቡ። ፍራሽ ላይ ከተቀመጡም በኋላ እንገት ለአንገት ተያይዘው በለቅሶ ይንፈቀፈቁ ጀመር። ታፈሡ በልሁና መርዕድ ከፊትለፊታቸው ቆመው ቢለምኗቸውም ቶሎ እሺ አላሉም። በርካታ ደቂቃዎች አለፉ። ልጅ እናቱን መውደድ፣ እናት ለልጅዋ መሳሳት እንኳንስ በሰው ልጅ በእንስሳትም ዘንድ የታወቀ ነው፤ የሔዋንና የእናቷ ሁኔታ

... ከተሰመደው መጠን በላይ ሆኖ ሲታይ እጅግ ያሳዝን ነበር። ታፈሡ ወዲያው ወደ ፍራሽ ጉንበስ አለችና መርዕድ በላስቲክ ጠቅልሎ ለትምሽ ያዘጋጀውን ጫት ጥትልል አድርጋ በማንሳት ወደ ጓዳ ይዛው ገባች። ጫቱን አስቀምጣ እንደገና ምልስ አለችና በልሁና መርዕድን በዓይኗ እየጠቀሰች ወደ ውጭ ወጣች። እነሱም ተከተሏት።

«ምን እናድርግ?» ስትል ጠየቀቻቸው።

በልሁም መርዕድም «ምን ይሻላል? እንዴት እናድርግ?» የሚል ጥያቄ አስታተሉ። የመጨረሻ ውሳኔያቸው ለሔዋን እናት መስተንግዶ መጣደፍ ነበር። በዚሁ መሰረት በልሁና መርዕድ ሥጋ እና የመጠጥ ዓይነቶችን ሊገዙ ወደ ከተማ ሮጡ። ታፈሡ ወደ ቤት በመመለስ፦

«ትርፌ» ስትል ጠራቻት።

«አቤት»

«በርከት አድርገሽ ቡና ቁይ!» አለቻትና ከሔዋን አጠገብ ፍራሿ ላይ ቁጭ አለች። በዚያ ሰዓት ሔዋንና እናቷ ከለቅሷቸው ትንሽ በረድ እያሉ ናቸው። እንባቸው ከዓይናቸው ላይ መፍሰሱን ባያቆምም ከመርገብገቡ ተገቱቀዝ እያሉ ሄዱ።

ታፈሡ በጨዋታ አሳብባ ስሜታቸውን ለመቀየር አስባ «እንደው ሳይታሰብ ከየት ብቅ አሉ የእኔ እናት?» ስትል የሔዋንን እናት ጠየቀቻቸው።

«ምን ላድርግ ብለሽ ነው የእኔ ልጅ፣ ባጸምጥ ባጸምጥ የልጆቼ ድምጥ ጥፍት አለብኝ። ባለፈው ክረምት ይመጣሉ ብዬ ስጡብቅ ቅርት አሉ። በጋውም ይኸው አለቀ። ሆዴ አልችል ቢለኝ መጣሁ!» አሏት በነጠላቸው ጫፍ ዓይንና አፍንጫቸውን እየጠራረጉ።

«ሸዋዬ ደብዳቤ አትጽፍም ነበር?»

«ኧረ እሷ እቴ!»

«አንድ ጊዜ እንኳ?»

«በፍጡም!» አሉ የሔዋን እናት። በዚህ ጊዜ ‹ሔዋን ባልጋለች› በማለት ሸዋዬ የፃፈችው ደብዳቤ ትዝ ብሏቸው ሳይሆን አይቀርም ታፈሡና ሔዋን ተያዩ።

«ለመሆኑ መቼ መጡ?» ስትል ታፈሡ እንደገና ጠየቀቻቸው።

«ትናንት ማታ» አሉና «አንድ አስተማሪ ነኝ ያለ የተባረከ ልጅ የሸዋዬን ቤት አሳይቶኝ እሷ ጋር አደርኩ።»

«እዚህስ ማን አደረሰዎት?»

የሔዋን እናት እንዳገነበሱ በረጅሙ ተነፈሱና «እንደ አደራረሴ ደረስኩ የኔ ልጅ፤ አይደረስ የለም።» አሏት እዝን ትክዝ ባለ አነጋገር።

ታፈሡ አኳኋናቸውን ልብ ብላ ስታጤን ቆየችና የሔዋን እናት አንድ ደስ የማይል ስሜት በውስጣቸው እንዳለ ተረዳች። ከሔዋን ዙሪያ የማያልፍ መሆኑን በመገንዘብ ቆረቆራት። ጠይቃ ለመረዳት ስትል «ሔዩን ከሸዋዬ ቤት ሲያጧት ምን ተሰማዎት እማማ?» ስትል ፈገግ ብላ እያየች ጠየቀቻቸው። በዚያው ሔዋንንም ሰላል አደረገቻት። ሔዋን አሁንም በእናቷ ላይ ልጥፍ ብላ እንባዋን ታንቆረቁራለች።

«የእሷንማ ነገር እዚያው አገሬ ሆኜ ሆዱ ነግሮኝ የለ ልጄ፣ ቀድሞም ተረድቸዋለሁ።» አሉና አገጫቸውን በመዳፋቸው ደግፈው ትክዝ አሉ። ትናንት

ማታ ከሸዋዬ ቤት ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ ዛሬ ሒዋን ከአለችበት ቦታ እስከ ደረሰበት ጊዜ ድረስ የነበረውን ሁኔታ በዓይነ-ሕሊናቸው ይቃኙት ጀመር::

ልክ እንደ ሒዋን የእናቷ መምጣት ለሸዋዬም ዱብ ዕዳ ነበር የሆነባት:: ስታያቸው ደንግጣ እትፍ አድርጋ በመሳም በናፍቆት ነበር የተቀበለቻቸው:: በአክብሮት ጋብዛ ነበር ያስቀመጠቻቸው:: ነገር መበላሸት የጀመረው ግን እናቷ ስለ ሒዋን መጠየቅ ሲጀምሩ ነበር::

«እሙዬስ የሸዋ?» ሲሉ ነበር የጠየቋት ወዲያውኑ እንደተቀመጡ:: «እሙዬ» የሒዋን የቤት ስሟ ነው ቶሸዋ ደግሞ የሸዋዬ የቁልምጫ መጠሪያ::

«ትመጣለች::» አለቻቸው ሸዋዬ ነገሩን ቀለል አድርጋ::

የሒዋን እናት ከሸዋዬ ቤት የደረሱት ከአመሻሹ አሥር ሰዓት አካባቢ ነው:: ሒዋን ገና እየተማረች መስሏቸው የተማሪዎችን መውጫ ሰዓት ሲጠባበቁ ቆዩ:: ነገር ግን እየመሸ ሄደ:: ሒዋን ደግሞ ብት አልል አለች:: የሒዋን እናት አሁንም...

«ይቺ ልጅ ምነው ቀረች የሸዋ?» ሲሉ ጠየቋት::

«ትመጣለች አልኩሽ እኮ!» የሸዋዬ አነጋገር ግልምጫ ጭምር ነበር::

አሁንም በጣም መሸ:: ለዓይን ያዘና መብራት በራ:: ሸዋዬ ለእናቷ እንግድነት ቶሎ ቶሎ የሰራችው ወጥ እንደ ደረሰ ራት ልታቀርብ የእጅ ማስታጠቢያ ይዛ ወደ እናቷ ቀረበች::

«እሙዬ ሳትመጣ የሸዋ?»

«ያደረች እንደሆን ጾምሽን ታድሪያለሽ?»

«ርቃ ነው እንዴ የሄደችው?»

«ማን ያውቃል? እሷ ለራሷ እንደ ልቧ አዳሪ!»

የሒዋን እናት ግራ እየገባቸው ሄደ:: እንጀራው ራት ራት እያላቸው ራታቸውን በሉ:: ልባቸው ግን ለሒዋን ተሰቀለ:: የሆነችውን ማወቅ አልቻሉምና ናፍቆቱ፣ ስጋቱ፣ ጭንቀቱ ሁሉ መንፈሳቸውን አመሰቃቀሰው:: ቆየት ብሎ መኝታ ሲነጣጠፍላቸው አዩ:: ቢያንስ ለዛሬ ሒዋንን ሊያዩዋት እንደማይችሉ አውቀው ግን ደግሞ እንደው ለምናልባቱ በማለት፡-

«እሙዬ ማደሯ ነው የሸዋ?» ሲሉ ሸዋዬን ጠየቋት»

«ጠዋት እንፈልጋታለን::»

የሒዋን እናት ሆዳቸው ቅይም አለ:: ንዴትም ተሰማቸው:: ግን መታገስ ነበረባቸውና የሆዳቸውን በሆዳቸው አድርገው ለስለስ ባለ አነጋገር፡-

«ምናለ የሸዋ፣ ልጄ የሆነችው ነገር ታለ ንገሪሽኝ ቁርጤን ባውቀው!» አሏት ዓይናቸውን በሸዋዬ ላይ እያንከራተቱ::

«ምን ትሆናለች ብለሽ ሰጋሽ አንቺ?»

«ለምን አልሰጋ ልጄ፣ ኧረ ጭንቅ አለኝ የሸዋ!»

«ቁርጡን ልንገርሽ! እሷ እናት፣ እህት፣ ወንድም... የሚባል ነገር ትታለች:: ሕይወቷን በአሻት መንገድ እየመራች ነው:: ነገ አለችበት ድረስ ትሄጃለሽ:: እስከዚያ ድረስ አትጨቅጭቂኝ:: በቃ!!» አለቻቸው ሸዋዬ ምንጭቅጭቅ እያለች::

የሒዋን እናት አንጀታቸው የባሰውኑ ቁርጥ አለ:: ቢያንስ ቢያንስ ሁለቱ ልጆቻቸው እንደተጣሉ ገባቸው:: ልባቸው ተከፋ:: በተዘጋጀላቸው መኝታ ላይ ልክ እንዳኮረፈ ሰው ኩርምት ብለው ተኙ:: የረባ እንቅልፍ ሳይወስዳቸው በየመሀሉ

እየባነኑ ያ ለሊት አልቆ በቀን ተተካና ሰማይና ምድር ተላቀቀ:: እየረፈደ ሄደ:: ቀንም ተፋረሰ:: ስለ ሒዋን መጠየቃቸውን አቁመዉ የሸዋዬን እንቅስቃሴ ብቻ ሲጠባበቁ ቆዩ::

ወደ ሰባት ሰዓት ተኩል አካባቢ ሸዋዬ ከቤት ወጣ ብላ ጥቂት ከቆየች በኋላ አንዲት ኮረዳ ቢጤ ይዛ ተመለሰች:: ልጅቷን ይዛ ከፊትለፊታቸው በመቆም «ከዚች ልጅ ጋር ሂዱ፣ የልጅሽን ቤት ታሳይሻለች::» አለቻቸው::

የሒዋን እናት «ጉሽ ልጄ! እሰይ!» በማለት ሸዋዬን እያመሰገኑ ብድግ አሉ:: ሒዋንን እስከዚያ ሰዓት ድረስ ማየት ባለመቻላቸው ግን አንጀታቸው አርሯል:: ከዚያ በኋላ ልጅቷ እፊት እፊት እየመራች ወደ ሒዋን ቤት ወሰደቻቸው ነው ልክ የልጃቸውን ያህል የኦሳቸውም ሆድ ባብቶ ያን ያህል ያነቡት::

ይህ ሁሉ ስሜት አሁንም በፊታቸው ላይ ይነበባልና ታፈሡ «ምነው እማዬ? ደስ ያለዎት አይመስሉኝም:: የተተየመብት ነገር ያለ ይመስላል?» ስትል ጠየቀቻቸው::

የሒዋን እናት አሁንም እጉንብሰው ግንባራቸውን እያሻሹ «ቢከፋኝስ፣ ብተየምስ የት ልደርስ ብለሽ የኔ ልጅ! ብቻ እንኳን ልጄን አግኝቼ ዓይኗን ያየሁት!!» አሉና ወደ ሒዋን ዞር ብለው እያዩዋት «እሙ! ደግሞ በአንቺ ሆድ ምን ይኖር ይሆን?» አሉና «እደራ! የወላድ መካን እንዳታደርጊኝ!» አሏትና ድንገት እንባቸው ድንቡት ብሎ ወረደ::

ሒዋንም በዚያው ሁኔታ ተከተለቻቸው:: ታፈሡ በእናትና ልጅቱ ሁኔታ የእሷም ሆድ እየተንቦጫቦጨ ትንሽ ካለቀሰች በኋላ እንደገና ሁለቱን ማባበሏን ተያያዘችው:: ኩበዙ ልመና በኋላ ትንሽ በረድ ብለውላት በህዘንና በትካዜ ዓይን እየተያዩ ስታያቸው ሳለች በልሁና መርዕድ ድንገት ከተፍ አሉ:: በሁለት ፌስታል ዕቃ ይዘዋል:: ታፈሡ ተቀበለቻቸውና ወደ ጓዳ ገባች:: ወዲያው የመመገቢያ ትሪና ያን ከቤቷ ይዛ የመጣችውን ምግብ ይዛ በመመለስ ማቅረብ ጀመረች:: በቀይ የሥጋ ወጥ የተፈተፈተ የነጭ ጤፍ እንጀራ ነው:: ትሪው ላይ ዘርግፋ ሒዋንና እናቷን ጨምሮ ሁሉም ቀርበው እንዲበሉ አደረገች:: በልሁና መርዕድ ካመጡት ለስላሳ እየከፈተች ማደሏን ቀጠለች:: በርሂራዋ ታፈሡ በማስተናገድ ሽር-ጉድ ያንን ቤት ሞላችው::

ከምሳ ግብዣው መጠናቀቅ በኋላ ትርፌ ያፈላችው ቡና ተከተለ:: ታፈሡ ፍራሽ ላይ ከሒዋን አጠገብ፣ በልሁና መርዕድ ደግሞ ከፊትለፊታቸው የግድግዳ ጥግ ይዘው ወንበር ላይ ተኮለኮሉ:: ቡናው ሊቀዳ ሲል ሒዋን እናቷ ከመጡ ወዲህ ለመጀመሪያ ጊዜ ተናገረች::

«ጫቱን ተዋችሁት እንዴ በልሁዬ?»

«እማማን ፈርተው ይሆናል::» አለች ታፈሡ ፈገግ ብላ ሁሉንም እያየች::

«ውይ! ለምን ልጆቼ! ሲዳሞ ውስጥ እየኖርኩ ጫት ትጠላለች ብላችሁ ነው? የራሴ ልጆችስ ምድጃዬን ክብብ አድርገው እይደል ሲቀጨቅጩት የሚያመሹት! እኔንማ አትፍሩ:: እንደውም ቤቱ ሲሚሚስ ደስ ይለኛል::» አሉ::

«ይደብርዎት እንደሆን ብለን እኮ ነው::» አለ በልሁ ፈገግ ብሎ::

«ኧረ በፍጡም! ለምን ልጄ?»

«እምጡት እንግዲያው!» አለች ታፈሡም በልሁና መርዕድን በፈገግታ ዓይን እያየቻቸው።

መርዕድ አልዘገየም፣ የመቃሚያውንም ቦታ በአዲስ መልክ አበጃጀው። ጫቱን ከጓዳ ውስጥ አወጣ። ያ ቤት እንደገና ነፍስ ዘራ። የጫቱ መጀመር በተለይ በታፈሡና በሐዋን እናት መካከል ተጨማሪ ውይይት እንዲፈጠር ምክንያት ሆነ።

«በልሁ» ስትል ታፈሡ መጀመሪያ ጠራቻቸው።

«አቤት»

«የሐዩ እናት ትናንት ከሸዋዬ ቤት እንዳደሩ ነገሩኝ። ነገር ግን ደስ ያላቸው አልመሰለኝም።» አለች በተለይ የሐዋንን እናት አየት እያደረገች።

«ከፋዎት እንዴ እማማ?» ሲል ጠየቃቸው በልሁ።

«ቢከፋኝስ የት አደርሰዋለሁ ብለህ የኔ ልጅ?» አሉ የሐዋንን እናት ጉንበስ ብለው መሬት መሬት እያዩ።

«ቀድሞ ነገር በልጅዎ ቤት ለምን ይከፋዎታል?» አለ በልሁ አሁንም።

«ምኑን አወቁት ብለህ የኔ ልጅ! እንግዲህ አያድር ሳውቀው ይገባኛ እንደሆን እንጂ እስታሁንስ ነገሩ ሁሉ ግራ ግብት ነው ያለኝ» አሉ የሐዋን እናት።

ታፈሡ ወደ ሐዋን አየት እያረገች «ሐዩ፣ ለእማማ ሁሉንም ነገር ልንገራቸው ነው፣ ከፋሽ አልከፋሽ የራስሽ ጉዳይ» አለቻት በመቀለድ ዓይነት።

ሐዋን አንገቷን ወደ መሬት ቀበረች። እናቷ ሳይቀሩ በልሁ፣ መርዕድና ታፈሡም ያዩዋት ጀመር። በዚህ ግዜ እናቷ፣

«ነውር የሆነ ነገር ሰራሽ እንዴ እመቤ?» ሲሉ ጠየቋት።

«የእርስዎ ልጅ ነውር ልትሰራ አልተፈጠረችም።» አለች ታፈሡ። እንደገና ወደ በልሁና መርዕድ ዞር ብላ «ያ ሲያስጨንቀን የነበረ ሸዋዬ ስለ ሐዩ ለወላጆቿ የፃፈችው ደብዳቤ እኮ አልተላከልንም አሉ» አለቻቸው ሁለቱንም አየት አየት እያረገቻቸው።

«ሙት በይኝ» አለ በልሁ።

«እያችሁ! ሐዩም ስትጨነቅ፣ አስቻለውም እኛም ስንታመስ የኖርነው እንዲሁ በከንቱ ኖሯል» አለችና የተፃፈው ደብዳቤ ይዘት ምን እንደነበረ ዘርዘር አድርጋ ለሐዋን እናት አስረዳቻቸው። ሸዋዬ ያን ደብዳቤ ሐዋንን ለማስፈራራትና ለማስደንገጥ እንጂ ልትልከው አስባ እንዳልነበር እንደ አዲስ ታሰባቸው።

የሐዋን እናት የደብዳቤውን ይዘት ከታፈሡ ገለፃ ከተረዱ በኋላ «ይህን ነገር እመቤ ፈጥማው ነው ወይስ ...» ብለው ታፈሡንም ሐዋንንም ሲመለከቱ ታፈሡ ረዷ ቀጠለች።

«እዩ እማማ! መቼም ሐዩም ሸዋዬም ልጆችዎ ናቸው። በእርስዎ ፊት አንዷን ወግነን ሌላዋን ብናማ ትዝብት እንደሆን እንጂ ሌላ እንደማናተርፍ እናውቃለን። ግን ደግሞ እውነቱን ግልጥልጥ አድርገን ልንነግርዎት እንፈልጋለን።» አለቻቸው አንድ የጫት እግር ይዛ ወዝወዝ ወዝወዝ እያደረገች።

«በጄ» አሏት የሐዋን እናት ለነገሩ እየጓጉ።

«ሐዩና ሸዋዬ በማይጣላ ነገር ተጣልተው ለማስታረቅ ብዙ ጥረን ነገር ግን በሸዋዬ እምቢተኝነት ሳይሳካልን ቀረ።»

«ምን አጣላቸው የኔ ልጅ?»

ታፈሡ ነገሩን ከሥሩ ጀመረችላቸው። በትድማያ እሷና ሸዋዬ የትና እንዴት እንደሚተዋወቁ፣ ሸዋዬ ከያቤሎ ወደ ዲላ ስትመጣ ያደረገችላትን አምበሳ፣ ተጥላም የአስቻለውን ምንነትና ማንነት፣ ከእሷ ጋር የነበረውን ግንኙነትም እንዲሁ ገለፀችላቸው። በመጨረሻም የአስቻለውንና የሐዋንን ጉዳይ ከእጮኝነቱ እስከ የመጻፊት ዓላማቸው ድረስ አስረዳቻቸውና ለዚህ ነገር የሸዋዬ እጅ ምን ይመስል እንደነበረ፣ ችግሩን ለመፍታት የተደረገውንና ሊደረግ የነበረውን ጥረት ሁሉ ዘረዘረችላቸው።

የሐዋን እናት በነገሩ ከመመሰጣቸው የተነሳ በጠሬው መሀል ቢጠሯቸው እንኳ ወይ የሚሉ አይመስሉም። እንዲያውም እንባቸው እየመጣ በሰበሱት ነጠላ ዓይናቸውን ጨመት ያደርጋሉ። ሐዋንንም ዞር እያሉ ስሚቷን ሲስሉ እንባዋ በጉንጯ ላይ ሲፈስ ያያሉ። በዚያው ልክ ሆዳቸው ይንቦጫቦጫል። የእሳቸው ሁኔታ የሁሉንም ቀልብ ስቦ ሁሉም በትካዜ አስተያየት ያዩአቸዋል።

ታፈሡ አሁንም የሐዋንና የሸዋዬን ለየብቻ የመኖር ምክንያት ለትጠቀማቸው ፈልጋ ሸዋዬ ሐዋንና አስቻለውን ለማለያየት ያደረገችውን ጥረትና ሐዋንን በማትፈልገው ሰው ልታስደፍራት መሞከሯን ጭምር ነገረቻቸው።

የሐዋንን እናት ነገሩ ሁሉ ግርም አላቸውና «እንዴት ነው ይኼ ነገር እመቤ?» ሲሉ በተለይ ሐዋንን እያዩ ጠየቋት። ምናልባት እሷም በሆዷ ውስጥ ያለ ነገር ካለ ብለው ብትነግራቸው ፈለጉ።

«ሐዩ፣ አይዞሽ ንገሪያቸው!» አለች ታፈሡ በልጃቸው አንደበት ቢሰሙ የበለጠ ሊያምኑ እንደሚችሉ በመገመት።

ሐዋን ግን አልቻለችም። ለትሶ ቀደማትና በእናቷ ጭን ላይ ድፍት ብላ ትንሰቀሰቅ ጀመር። እናቷም ታፈሡም ቢያባብሏት ዝም ልትል አልቻለችም። በመሀል በልሁ ተቆጣት።

«አንቺ ሐዩ» አለና ከመቀመጫው ብድግ አለ። «ቀና ብለሽ ቁጭ በይ። ለምን የእናትሽን ሆድ ታባቢያለሽ?» አለና አንገቷን ደገፍ አድርጎ ቀና አደረጋት። «እናትሽ የጠየቁሽን መልሽላቸው!።» አላት እንደገና።

«እ- አንቺ ን- ንገሪያት ታፈሡዬ!» አለች ሐዋን ድምጿ እየተቆራረጠ።

ታፈሡ ቀጠለች። «በመሀል ደሞ አንድ ችግር ተፈጠረብን እማማ። ይህ አስቻለው ያልኩዎት ወንድማችን ሳያስበው በዘመቻ ስም በግዳጅ ወደ ኤርትራ መሄድ ግድ ሆነበት። ይህም አጋጣሚ የተፈጠረው በሸዋዬ አማካይነት ልጁንና ሐዋንን ለመነጣጠል የተዶለተ ሴራ መስሎ ታየንና ሐዩም ያለ ፍላጎቷ ከመደፈሯ በፊት ማሸሽ ፈለግን። ልጁም ደሞዙን ለእሷ መተዳደሪያ እንዲሆን አድርጎ ስለነበረ ከሸዋዬ ቤት ወጥታ እዚህ ቤት እንድትኖር አደረግን። በቃ! ሐዩ ከሸዋዬ ቤት የወጣችበት ምስጢሩ ይህ ነው የኔ እናት» አለቻቸውና ምላሻቸውን በመጠበቅ ዓይኗን በዓይኖቻቸው ላይ ስክት አደረገቻቸው።

«ለልጁ መዝመት መዘዘኛዋ ያቺው የእኔ ልጅ ናት በይኝ!» አሉና የሐዋን እናት ታፈሡን ያዩዋት ጀመር።

«እውነተኛውን ነገር እግዜር ይወቅ እማማ! በኛ በኩል ግን እንደዚያ ገመትን።» አለችና ታፈሡ እጆቿን ጨብጣ አገጯን በማስደገፍ የሐዋንን እናት እየተመለከተች «አስቻለው ከመስሪያ ቤት አለቃው ጋር አይስማማም ነበር። ሸዋዬ

ደግሞ ከዚያ ሰው ጋር ጥብቅ የሆነ ግንኙነት ፈጠረች። እኛም በዚህ ጉዳይ የተነጋገርበትና ቢጋራ የፈጠሩት መሳ ሊሆን እንደሚችል ጠረጠርን።» አሳቻቸው።

የሔዋን እናት ያላሰቡት ስሜት ተፈጠረባቸው፤ በግራ እጅ መዳፋቸው ጉንጫቸውን ደገፍ አድርገው «እየየ እኔ! እየየ እኔ! እየየ እኔ! ...» በማለት የተሰማቸውን ሀዘን ሲገልጹ እንባቸውም ከዓይናቸው ላይ ድንገት ብሎ ወረደ። በዚህ ጊዜ በልሁ ብድግ ብሎ ወደ ጓዳ ገባና ቀድሞ የአስቻለው አሁን ደግሞ የሔዋን ከሆነው አልጋ የራስጌ ኮመዲኖ ላይ ሁለት ትላልቅ ፎቶግራፎች ይዞ ተመለሰ። አንዱ አስቻለው ለብቻው የተነሳው ሌላው ደግሞ ወደ ኤርትራ ከመሄዱ አንድ ቀን በፊት ከሔዋን ጋር በመሆን በቀም የተነሱት ነበር። ሁለቱንም ፎቶግራፎች ለሔዋን እናት እየሰጠ «እቤት እማማ! ልጅም ይህ ነበር» አላቸው።

የሔዋን እናት ፎቶግራፎቹን በጭናቸው ላይ አስቀምጠው ልክ እንደ ፊት መስታወት እየየ፤ በቀኝ እጃቸው በጣቢ ደረታቸውን ደስት ደስት እያደረጉ «እ - እ» ካሉ በኋላ «ዓይኔ ይፍሰስ! ዓይኔ ይፍሰስ! ዓይኔ ይፍሰስ» አሉና «ምነው ይኸን ጉድ ሳልሰማ ሞቼ አርፌው ቢሆን!» በማለት አሁንም ዓይንና አፍንጫቸውን በነጠላቸው ይጠርጉ ጀመር።

«አይቀየሙኝና» አለ በልሁ «ሔዩና ሸዋዬ ከአንድ እናት ማህፀን የወጡ አይመስሉኝም እማማ፤ ቅር ይልዎት ይሆን?» ሲል ጠየቃቸው።

«የእናት ሆድ ዥንጉርጉር የተባለው ስለዚህ አይደል የኔ ልጅ! አንተም ባትል በኔም ሆድ ብዙ አለ።» አሉና ድንገት በሀሳብና በትካዜ ውስጥ ጭልጥ ብለው ገቡ። የሸዋዬን የልጅነት አስተዳደግ እያስታወሱ ነው። ሸዋዬ በህፃንነቷ ገና በእቅፋቸው ውስጥ ሆና ጡታቸውን ጠብታ ጠብታ ስትጠግብ እንዴት አድርጋ ትንከሳቸው እንደነበር ትዝ አላቸው። ጠንከር ብላ ወደ ውጭ መውጣት ስትጀምር ደግሞ ከጎረቤት ልጆች ጋር ባለመስማማት ወይ አልቅሳ አለያም አስለቅሳ በመመለስ የምታመጣባቸውን ስሞታ ሁሉ አስታወሱ። በቤት ውስጥ ደግሞ እጥፊ፣ አውዳሚ፤ ምንም ነገር፤ የትም ቦታ ቢደበቅ የማያመልጣት ሰርሳሪ! በዚያ ላይ ደግሞ ሰባቂ፤ የእናቷን ሚስጢር ለአባቷ፤ የአባቷን ደግሞ ለእናቷ እየነገረች የምታሳጣቸው ሰላም እንኳ አልቀራቸውም። ‹ይቺ መሄጃዋ የማይታወቅ መዘዘኛ፣ እያሉ ገና በልጅነቷ ይማረሩባት የነበረው ሁሉ ትዝ አላቸው።

ለአፍታ ያህል ፀጥታ ሰፈነና ከቆይታ በኋላ ግን የፀጥታውን ድባብ ራሳቸው የሔዋን እናት ቀድመው ሰበሩት። «ለመሆኑ ልጄ መቼ ይሆን የሚመለሰው?» ሲሉ ጠየቋቸው።

ታፈሡና በልሁ ድንገት ድንግጥ ድንግጥ አሉና እርስ በርስ ተያዩ። መርዕድ ግን ከእነሱ በባሰ ሁኔታ ደንግጦ ውጭ ውጭ ያይ ጀመር።

«ግራ ገብቶናል እማማ።» አለች ታፈሡ እሷም ብትሆን ቀጥላ የምትለው ነገር አስፈርቷት መሬት መሬት እያየች።

«እንዴት የኔ ልጅ?»

«የሄደው ለስድስት ወር ተብሎ ነበር፤ ትሁን ግን ይኸው ዓመት ሊሞላው ነው። ግን እልም ብሎ ጠፍቶብን በሀሳብ ላይ ነው ያለነው።» አለችና ወደ በልሁ ዞር ብላ «ምናልባት ግን ሰሞኑን አንድ ነገር ሰምተናልና የተስፋ ጭላንጭል ነው

ብለን የምንተናል።» ብላ በልሁን ‹ተናገር› በሚል ስሜት በዓይኗ ጠቀስ አደረገችው። ተግባብተዋልና በልሁ ቀጠለ።

«ይኸን ነገር ለሔዩም ልንነግራት ነበር ዛሬ የተሰባሰብነው።» ሲል ጀመረ። «ደሞዙን ከመስሪያ ቤቱ እያመጣሁ ለሔዩ የምሰጣት እኔ ነበርኩ። ከጥቂት ቀናት በፊት ሄጄ ስጠይቅ ግን ‹ደሞዙ ተቋርጧል› የሚል ወሬ ሰማሁ።» አለና ቀና ብሎ ሔዋንና እናቷን እየተመለከተ ያን ቀደም ሲል ከእንታፈሡ ጋር ሆነው የፈጠሩትን ሔዋንን የማረጋጊያ ‹ዘዴ› መተረክ ጀመረ። አስቻለው በምጽዋ በኩል ወደ ውጭ ሄዶ ሊሆን እንደሚችል፤ ጀርመን ወይም ጣሊያን ሀገር ገብቶ ሊሆን እንደሚችል፤ ደብዳቤው በቅርቡ ሊመጣ እንደሚችል ...ወዘተ። በልሁ በዚሁ ዙሪያ ብዙ ብዙ ተናገረ።

በዚህ ትረካ ምናልባት የሔዋን እናት ተታልለው ሊሆን ይችላል፤ ሔዋን ግን የአስቻለውን ደመወዝ መቋረጥ ስትሰማ አይኖቿ ወደ ዳር ወጥተው ተገለጡ። ትንፋሽዋም በርከት በርከት፤ ፈጠን ፈጠን ማለት ጀመረ። ታፈሡና በልሁ ስሜቷ ገብቷቸው በፍርሀት እስተያዩ። ሲመለከቷት ሔዋን ድንገት ተናገረች።

«ምን እያልክ ነው በልሁዬ?» ስትል ጠየቀችው።

«አትጠራጠሪ ሔዩ፤ ይሄ ነገር ለበጐ ነው።» አላት ምላሽ የምትሰጥ ከሆነ ብሎ ዓይን ዓይኗን እያየ።

የሔዋን ሁኔታ የበለጠ እያስፈራራ ሄደ። ዓይኖቿ እንደፈጠጡ ቀሩ። ታፈሡና በበልሁ እንዲሁም በመርዕድ ላይ አከታትላ ታኩራራቸው ጀመር። ወዲያው ደግሞ በረጅሙ ተነፈሰችና ወደ መሬት አጎነበሰች። ‹ኤርትራ የሄደ ይመለሳል ብለሽ...› የሚለው የበድሉ አነጋገርም ድንገት ፊቷ ላይ ድቅን አለባት። የሔዋን እናት ልጆቻቸውና ጓደኞቿ የተግባቡት ነገር እንዳለ ገባቸው። ሁሉንም ተራ በተራ አየት አየት ሲያደርጉ ከቆዩ በኋላ፦

«ለመሆኑ እናቱ በሕይወት አሉ?» ሲሉ ጠየቁ።

«እናትም አባትም የለውም፤ ሁለቱም ሞተውበታል።» አለች ታፈሡ።

የሔዋን እናት ከንፈራቸውን መጥጠው ዝም አሉ። አገጫቸውን በመደገፍ ወደ መሬት አጎነበሱ። ለአፍታ ያህል አሁንም ፀጥታ ሰፈነ። በመሀል ታፈሡ አንድ ነገር ትዝ አላት። ወዲያውም ማደናገሪያ ይሆናል ብላ በማሰብ ሳይሆን አይቀርም በልሁና መርዕድ የገዙትን ሥጋ ከጓዳ ወደ ሳሎን አመጣችና የእራት ወጥ ለመስራት መክተፍ ጀመረች። ፀጥታው ግን አሁንም ቀጠለ።

«ተጫወቱ እማማ» አለ በልሁ ከብዙ ቆይታ በኋላ።

«ልጆቼ» ሲሉ የሔዋን እናት ሁሉንም በአንዴ ጠሯቸው።

«አቤት እማማ?» አለች ታፈሡ ቀድማ። ግን ሁሉም ቀና ቀና ብለው ያዩዋቸው ጀመር።

«ታዲያ የእሙዬን ነገር እንዴት ባደርግ ይሻላል?» ሲሉ ጠየቁ።

«እንዴት?» አላቸው በልሁ።

«የልጄ መምጫ ቀን አልታወቀም አላችሁ። በያ ላይ ደሞዙ ተቋረጠ ነው የምትሉኝ። ታዲያ ወይ ይዣት ልሂድ?» ሲሉ ፈራ ተባ እያሉ ጠየቁ።

ሁሉም ደነገጡና ዝም ዝም አሉ። ግን ደግሞ እርስ በእርስ ተያዩ።

«አይሻልም ብላችሁ ነው ልጆቼ? ወይስ ቅር ይላችሁ ይሆን?»
«ሔዩ» ስትል ታፈሡ ጠራቻት። ከመደንገጧ የተነሳ እንጂ ወደ ብትሳት ቀጥላ የምትናገረውን ነገር ታፈሡ አላዘጋጀችም።
«እሄዳለሁ» አለች ሔዋን ድንገት ሳትታሰብ።
«እ?» አለ በልሁም ድንገቶ ብሎ።
«አዎ! ከእማዬ ጋር ወደ አገሬ እሄዳለሁ።» አለች ሔዋን አሁንም ድርቅ ባለ ስሜትና ጠንከር ባለ አነጋገር። ዓይኖቿ ግን አሁንም እንደተጉለጎሉ ናቸው። አንዳች ሸብር ውስጧን ያናወጠባት ትመስላለች።
በዚህ ጊዜ ያልታሰበ ድምጽ፣ ባልታሰበ አኳኋን፣ ካልታሰበ ሰው ተሰማ፤ ትርፌ «እኔስ አታስምጹ» ብላ ልክ እንደ ልጅነቷ ግንባሯን በክንዷ ሸፍና «አይይይ...» ብላ አለቀሰች።
«ተይ እንጂ! ምን ነካሽ? እኛ እያለን! እኛ እያለን!» በማለት ታፈሡም በልሁም መርዕድም አከታትለው ተንጫጩባት።»
እሷ ግን ዝም አላለችም። እንዲያውም በለቅሶዋ መሀል ልክ ቤት ውስጥ ሆና ከውጭ እንደምትጠራው አይነት «ጋሽ አስቻለው...!» ስትል በርቀትና በጩኸት ድምጽ ተጣራች። አስቻለው ወደ አስመራ፣ ሔዋን ወደ ክብረ መንግስት ተንጣጥለው ሲሄዱ እሷ ጭር ባለ በረሃ ውስጥ ብቻዋን የቀረች መሰላት። ሆዷም ባባና ስቅስቅ ብላ አለቀሰች።
«ታፈሡዬ» አለች ሔዋን በመሀል አሁንም በዚያው ድርቅ ባለ ስሜት ውስጥ ሆና።
«ወይ የኔ ቆንጆ»
ሔዋን ግን ጥሪዋን ቀጠለች። «በልሁዬ! መርዕድ!» አለች በማከታተል።
«ወይ! አቤት» አሏት ሁለቱም።
«ለአስቹ በልዩለት። ትርፍዬን ደግሞ አደራ!!» አለቻቸው።

ምዕራፍ አሥራ አንድ

አንዳንዴ የጊዜ ማጠርና መርዘም በሰዎች የውስጥ ስሜት የሚለካ ይመስላል። ለተጨነቀ ልብና መንፈስ አንዱ ዓመት በአሥራ ቤት የሚቆጠር ሲመስል ለተደሰተ ደግሞ የአንድ ቀን ያህል አጭር ይሆናል። እሱ ግን አሁንም አይቶን ሲያዛባ እየሄደ ነው። እየነጎደ ነው። የቀንና ለሊትን ፍርርቅ መሠረት አድርጎ ሰምንቱን በሳምንት፣ ወሩንም በወር እየተካ ተምዘገዘገ። ብሎ ብሎ አንድ አመት አለቀና ሌላው ተጋመሰ። እነሆ አስቻለው አስመራ ከሄደ ሁለት ዓመት ከሰባት ወሩ፤ ሔዋን ክብረ መንግስት ከሄደች እንኳ አንድ ዓመት ከአራት ወር ሞላት። ሔዋን በክብረ መንግስት፣ ታፈሡ፣ በልሁና መርዕድ ዲላ ውስጥ እየኖሩ ይህ ጊዜ ከአስቻለው ትዝታና ናፍቆት ጋር በተያያዘ በተመሳሳይ የስሜት አቆጣጠር አያሰቡት በመከራና በስቃይ ነው ያሳለፉት። አዝግሞ፣ ተጎትቶና ተንፏቆ ነው እዚህ የደረሰው። የአንድ ክፍለ ዘመን ያህል ርቀባቸዋል። ለመምህርት ሸዋዬ ደግሞ ሚያስገርም ሁኔታ እጅግ አጭር ነበር።
ሸዋዬ በአስቻለውና በሔዋን መለያየት ቀድሞ የነበረባት የመንፈስ ቁስል ወደ መገረን ተቀይሮ ከቅናት ስቃይ እፎይ ብላለች። ዛሬ የሁለቱ ፍቅር የዕለት ከለት ሀሳብና ጭንቋ አይደለም፤ ፀሎቷ በዚሁ እንዲቀጥል ብቻ ነው። በሰላም የህይወት አጋጣሚ ውስጥ ገብታለች። ኑሮዋ እየተለወጠ ነው። ቤቷ ሞቅ ደመቅ እያለ ነው። ማህበራዊ ግንኙነቷም እየተሻሻለ ነው። ነቃ ነቃ ብላለች። የመንፈስ መረጋጋትም ይታይባታል። የእሁኑ ደስታዋ በስቴታ እንዲኖረው ደፋ ቀና ማለቷን ተያይዛዋለች።
ለዚህ ሁሉ ሰበቡ የእናቷ ከክብረ መንግስት መምጣትና በአጭር ጊዜ ውስጥ ሔዋንን ይዘው ወደ ሀገራቸው መመለሳቸው ነበር። ያ አጋጣሚ በወቅቱ የእግር እሳት ሆኖ እንገብግቧት የነበረ ቢሆንም ለዛሬው ህይወቷ መሰረት ጥሎላት ያለፈ በመሆኑ ግን በመልካም አጋጣሚነቱ እያስታወሰችው ትኖራለች።
የሔዋን እናት በሸዋዬ ቤት አድረው በነጋታው ወደ ሔዋን ጋ ከሄዱ በኋላ ከሸዋዬ ጋር ዳግም ሳይገናኙ ነበር ወደ ክብረ መንግስት የተመለሱት። በእርግጥ መሄዱ ነውና ደህና ሁኚ ሊሏት ከመሄዳቸው አንድ ቀን በፊት ወደ ቤቷ ጎራ ብለው ነበር። ግን አላገኟትም። ዕለቱ ባርናባስ ወየሰ በአንድ የሶሻሊስት አገር የውጭ ትምህርት ዕድል አግኝቶ ሊሄድ ሞቅ ደመቅ ባለ ድግስ የሚሸኝበት ቀን ነበርና ሸዋዬም የድግሱ ታዳሚ በመሆን ከድግሱ ቦታ አምሽታለች። የሔዋን እናት ግሎ የምትመለስ መስሏቸው ከወይዘሮ ዘነቡ ጋር እያወሩና እየተጫወቱ ሲጠብቋት ቢቆዩም እሷ ግን እስከ ምሽት ድረስ ስለቆየችባቸው መልዕክቱ በወይዘሮ ዘነቡ በኩል እንዲደርሳት አድርገው ተመልሰዋል።
ሸዋዬ የእናቷን ፈጥነው ወደ ክብረ መንግስት የመመለስ ጉዳይ ፈጽሞ ያሰበችው አልነበረም። በእሷ ግምት የሚሰነባብቱና በዚያም አጋጣሚ የእሷንና የሔዋንን ለየብቻ የመኖር ምክንያት ዋሽታም ቢሆን ቀጥፋ እውነታውን በመሸፈን ልታጠራላቸውና ራሷን ከተጠያቂነት ለማዳን የሚያስችሉ ብዙ መንገዶችን ፈጥራ ነበር። ግን ያ ካለመሆኑም በተጨማሪ እናቷ ከታፈሡ ጋር ውለው አድረው

እንዲሁም ከወይዘሮ ዘነቡ ጋር ብዙ ተጫውተው የመመለሳቸው ነገር ከፉኛ ያስደነግጣት ነበር። እነዚህ ሁለት ሰዎች የእስቻለውንና የሒዋንን ግንኙነት እንዲሁም እሷ በሁለቱ ፍቅረኞች ላይ የነበራትን አቋም እንዴት አድርገው ለእናቷ እንደሚገልፁላቸው ታውቃለችና በተፈጠረባት ‹መጥፎ› አጋጣሚ ተበሳጭታም ተናድዳም ነበር።

የእናቷን ወደ ክብረ መንግስት መመለስ ጉዳይ በሰማችበት ወቅት የነበራት ምርጫ አንድ ብቻ ነበር። የገዟቸውን ሁኔታ ታውቃለች። ከዲላ ተነስተው በአለታ ወንዶ በኩል ነው የሚጓዙት። አለታ ወንዶ ሲደርሱ ከዲላ መኪና ላይ ወርደው ከአዲስ አበባ ወደ ክብረ መንግስት የሚሄደውን አውቶብስ መጠበቅ አለባቸው። በመሀል ቢያንስ ለሁለት ወይም ለሶስት ሰዓት ያህል አለታ ወንዶ ከተማ ይቆያሉ። እናም ጠዋት ከዲላ ከተማ ተነስታ አብራቸው በመጓዝ አለታ ወንዶ እስከሚደርሱበት ጊዜና በአለታ ወንዶ ከተማ በሚያደርጉት የቆይታ ጊዜ ውስጥ በወሬ ስትተከትካቸው ለመቆየት አስባ ይህንኑ ለመፈጸም ወስና አደረች።

በማግስቱ በጠዋት ተነሳች። እናቷን መሸኘያ የሚሆን ጥቂት ገንዘብ ቋጠረች። ወደ መናኸሪያው ገሰገሰች። ከእናቷ በፊት ቀድማ ከቦታው ደረሰች። ሒዋን ከምትኖርበት አቅጣጫ ወደ መናኸሪያው በሚያመጣው መንገድ ስትመለከት ስድስት ሰዎች ሲመጡ ታዩዋት። እየቀረቧት ሲሄዱ ማንነታቸውን ለየች። እናቷ፣ ታፈሡ፣ በልሁ፣ መርዕድ፣ ሒዋንና ትርፌ ናቸው። ዘንግታው እንጂ! ለካ እናቷ መሸኘት ነበረባቸው። ከተሸኙም በእነዚሁ ሰዎች ነው። ተበሳጨች። ከእናቷ ጋር በአንድ መኪና የመሳፈር ዕቅዷን ሰርዛ በተከታዩ ሲዮንትን ልትጓዝና እናቷን በአለታ ወንዶ ልትደርስባቸው፣ እዚያ በሚያደርጉት የቆይታ ጊዜ ብቻ ልታነጋግራቸውም ወሰነች። ለጊዜው በመናኸሪያው ውስጥ እንዳትታይ ወደ አንድ ሰዋራ ቦታ በመቆም የእናቷንና የሸኝዎቻቸውን እንቅስቃሴ መከታተል ጀመረች።

አሁንም የአሳሰበችው ሁኔታ ተከሰተ። እሷ የምትጠብቀው የእናቷን መሄድ ብቻ ነበር። ግን ደግሞ ሒዋንም መኪና ላይ ወጥታ በመስኮት አንገትና እጆቿን አውጥታ አፏን ፂ አድርጋ ከፍታ ምርር ብላ ስታለቅስና እጆቿን እያርገበገበች እነ ታፈሡን ስትሰናበት አየች። እነሱም አስከሬን ወደ ቀብር ቦታ ሸኝተው የሚመለሱ ሀዘንተኞችን ያህል ምርር ብለው ሲያለቅሱና እጆቻቸውን እያርገበገቡ ሲሰናበቷት አየች።

«እንዴ! እሷም ልትሄድ!» አለች ሸዋዬ ለብቻዋ እየተነጋገረች። ገረማትም፤ ደነቃትም። ግን ለዕለቱ እቅዷ ምንም ዓይነት እንቅፋት እንደማይፈጥርባት ገመተች፤ እሷ ለእናቷ ስለሆነ ነገር ብታወራ በትዝብት ታዳምጥ እንደሆን እንጂ ሒዋን ደፍራ ክርክር እንደማትገጥማት ታውቃታለችና።

ሒዋንና እናቷ በአለታ ወንዶ በኩል በሚሄደው አውቶብስ ተሳፍረው ከሄዱና ሸኝዎቻቸውም ከመናኸሪያው ወጥተው ወደየአቅጣጫቸው ከተበታተኑ በኋላ ሸዋዬ በቀጣይ ወደ አለታ ወንዶ የሚሄደውን መኪና ፍለጋ ጀመረች። በእርግጥም አንድ የመኪና ላይ ሰራተኛ የአንዲት አነስተኛ የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ በር ከፍቶ «ወንዶ! ወንዶ! አለታ ወንዶ!» የሚል ጥሪ አሰማ። ሸዋዬ ወደ መኪናዋ ሮጣ በመግባት የጋቢና ወንበር ይዛ ቁጭ አለች።

ከአንድ ሰዓት አለፍ አለ። ያቺ መኪና ግን ቶሎ አልሞላ አለች። በዚያው ሸዋዬ ተበሳጨች፣ ቸኩላ። ጋቢና ውስጥ ቁጭ ብላ ፊትለፊት ስትመለከት በርካታ መንገደኛ ወደ መናኸሪያው ሲገባ ታያለች። ግን እሷ ወደሄደችባት መኪና የሚገባው ሰው ከቁጥር አይገባም። ረዳቱ አሁንም «ወንዶ ወንዶ» እያለ መንገደኛ ይጠራል። ሸዋዬ ወደ ኋላ ዞር ብላ ስታይ ግን በርካታ ወንበሮች ክፍት ሆነው ተመለከተች። በዚያው ልክ ቀልቧ እየቆመ ትቁነጠነጥ ጀመር።

ከመኪናዋ ወንበሮች ግማሽ ያህሉ በሰው ከተያዙ በኋላ ሾፌሩ ወደ መኪናዋ ገብቶ ሞተር አስነሳ። ነገር ግን ጥቅ ጥቅ ከአደረገ በኋላ ተመልሶ ሲወርድ ሲዘጋጅ ሸዋዬ አየችውና «በእናትህ ሾፌር፣ መንገድ ላይ ትሞላለህ፣ እንሂድ!» አለችው።

«እንሄዳለን።» አላትና ከመኪናው ላይ ወረደ። ቁልፎቹን እያቅጨለጨለ ከመኪናዋ አካባቢ ይንጎራደድ ጀመር።

ሾፌሩ ጥቁርና ጠብሰቅ ያለ ሰውነት ያለው ነው። ቁመቱም ዘለግ ያለና እድሜው በሰላሳዎቹ አጋማሽ ላይ የሚገኝ እፍላ ጎልማሳ ነው። የሰማያዊ ቀለም እጅጌ ጉርድ ሸሚዝ ለብሶ ጨፌታ የሚያህል እጁ ሲታይ ጡንቻው ያስፈራራል። እልፍ እልፍ ከመኪና ላይ ሰራተኞች ጋር እየተላፋ በዚያ ክንዱ ጥምዝዝ አድርጎ ሲያስጨንቃቸው እያየች ሸዋዬ በልሁ ተገኜ ትዝ ይላታል፣ ከመልካቸው በቀር የሰውነታቸው አቋም ተመሳሳይ ነውና።

ሰዓቱ ወደ አንድ ተኩል ሲጠጋ እንደ ምንም ጉዞ ተጀመረ። ያ ሰዓት ሒዋንና እናቷ ወደ አለታ ወንዶ መዳረሻቸው ነው። ያ መንገድ ደግሞ የትራፊክ ቁጥጥር ስለሌለበት በተለይ አነስተኛ ተሽከርካሪዎች ሰው በሰው ላይ እየጫኑ ሲንገራገሩ፣ ተፈሪ ኬላ፣ ቀባዶ በተባሉና በሌሎችም ትንንሽ ከተሞች ሲደርሱ ተሳፋሪ ለማውጣት በማውረድ ጊዜ ያባክናሉ። አታካችና አሰልቺ መንገድ ነው። ሸዋዬ የተሳፈረችባት መኪናም ይህን ድርጊት ዘልላው አላለፈችም። ትቆም ትንተር ጀመር። ሸዋዬ በወጪ ወራጅ ጭቅጭቅ ጊዜው እያለፈባት ስትበሽቅ ስትናደድ ልቧ ሊፈነዳ ደርሶ እያስከለከች ልክ ከጠዋቱ አራት ሰዓት አካባቢ በአለታ ወንዶ መናኸሪያ ውስጥ ደረሰች። ወዲያው ዓይኗን በመናኸሪያው ዙሪያ ብታንከራትት ሒዋንና እናቷ በአካባቢው የሉም። በእርግጥ ከአዲስ አበባ ወደ ክብረ መንግስት የሚሄደው አውቶብስ እዚያ መድረሻው ሰዓት ገና ነው። በዚህ አጋጣሚ ሒዋንና እናቷ ሻይ ቡና ለማለት ሄደው ሊሆን እንደሚችል ገምታ በመናኸሪያው አካባቢ የሚገኙትን ቡና ቤቶች በሙሉ ማሰስ ጀመረች። ነገር ግን እናቷና ሒዋን አላገኘችም። አሁንም እየተናደደች ፍለጋዋን ቀጠለች። ቢቸግራት እሷ በየቡና ቤቱ ስትሯሯጥ እናቷና ሒዋን በሌላ መንገድ ወደ መናኸሪያው ተመልሰው ይሆናል ብላ በማሰብ እንደገና ወደ መናኸሪያው ሮጠች። ወደ ውስጥ ገብታ የመናኸሪያውን ዙሪያ በዓይኗ ስትቃኝ በነበረችበት ወቅት ከበስተ ግራዋ በኩል የአንድ ወንድና ሴት ጭቅጭቅ ድንገት ከጆሮዋ ጥልቅ አለ።

«አንቺ ባትዘገይብኝ ኖሮ እኮ እስካሁን ሄደን ነበር።» በማለት ወንዱ በሴትዮዋ ላይ ይጮሃል።

«ከአሁን በፊት ክብረ መንግስት የሚሄድ መኪና ይገኛል ብዬ እንዴት ልገምት?» አለች ሴትዮዋ።

«አንዴ!» አለች ሸዋዬ እንደ መደንገጥ ብላ። ወደ ሰውየው ጠጋ በማለት «ብትርበ ወደ ክብረ መንግስት የሄደ መኪና ነበር እንዴ?» ስትል ጠየቀችው።

«ሰው አጥቶ ሲጮህ ቆይቶ ከዲላ የመጣው አውቶቡስ የሰው መጉላላት ሲበረግፍለት ጊዜ ጥቅጥቅ አድርጎ ጭኖ ሄደ።» አላት ሰውየው አግረ መንገዱን ቀጭቱን ቀድሞ ለሚያነጋግራት ሴትዮ በመግለጽ ዓይነት።

«እ?» አለች ሸዋዬ ድንግጥ ብላ።

«ሙች ስልሽ!» ሰውየው አሁንም።

ሸዋዬ አንጀቷ ቁርጥ አለ። ከንፈሯን ንክስ አድርጋ በቁጭት ስሜት ራሷን ወዘወዘች። ቢቃ! እናቷ ወይዘሮ ዘነቡና ታፈሡ የነገሯቸውን ሁሉ ተሸክመው ክብረ መንግስት ገብተዋል። የብስጭቷ ብዛት ወገቧን አርገድግዶ ከአጥር ጥግ ድንጋይ ላይ አስቀመጣት። ራሷን በሁለት እጆቿ በመያዝ ወደ መሬት አቀረቀረች። ሀሳብ አወጣች አወረደች። ግን ምንም ማድረግ አልቻለችም።

በዚያው ቦታ ላይ እንደተቀመጠች ሳታውቀው ሰዓቱ ሄዶ ኖሯል። ወደ ስድስት ሰዓት አካባቢ ከአዲስ አበባ ወደ ክብረ መንግስት የሚሄደው አውቶቡስ ደረሰና ጡሩንባውን እየነፋ ወደ መናኸሪያው ገባ። እንደው ለምናልባቱ ብላ ወደ መናኸሪያው በር ብትመለከትም ሔዋንና እናቷ ብቅ አላሉም። አውቶቡሱ የሚያወርደውን አውርዶ የሚጭነውን ጭኖ ወደ ክብረ መንግስት ጉዞውን ቀጠለ። የሸዋዬ ተስፋም ተሟጠጠ። ወደ ቤቷ ከመመለስ በቀር ምርጫ አልነበራትም።

ወደ ዲላ ስለ መመለሷ ማሰብ ስትጀምር ቀደም ሲል ይታያት የነበረ ቢሆንም ነገር ግን ትኩረት ወዳልሰጠችው አትጣጫ አተኮረች። ያቺ ከዲላ ይዛት የመጣች ሊዮንችን እንደገና ወደ ዲላ ስትጭን ተመለከተች። ጠጋ ብላ ስትመለከት በመኪናዋ ውስጥ ሰው በሰው ላይ ተነባብሯል። የቆመው ከተቀመጠው ተሳፋሪ አይተናነስም። ጨነቃት። ድንገት ወደ መናኸሪያው በር ዞር ብላ ስትመለከት ያን ጠጠምሻ ሾፌር አየችው። አሁንም ቁልፎቹን እያቅጨለጨለ ከውጭ ወደ ውስጥ ይገባል። መኪናዋ አጠገብ እስከሚደርስ ጠበቀችና፦

«የኔ ወንድም!» ስትል ጠራችው እንደ መሽኮርመም እያለች።

«አቤት!» አላት በጥቁር ፊቱ ላይ ወተት መስለው የሚታዩ ጥርሶቹን ፈገግ እያረገ።

«መኪናህ በጣም ሞልቷል። እንዴት ይሻለኛል?» አለችው በመለማመጥ ዓይነት።

«የመጣሽበት ጉዳይ አለቀ እንዴ?»

«ጨርሼ ነበር። መመለሻው ግን ጨነቀኝ።»

«እንደ ምንም ትሄጃለሽ!» አለና ሾፌሩ ወደ ረዳቱ ፊቱን መለስ አድርጎ «እንዴት ነው፣ ሞላ?» ሲል ረዳቱን ጠየቀው።

«እየሞላ ነው።» አለው ረዳቱ የሚገባ ከተገኘ አሁንም ለመጫን የሚፈልግ መሆኑን በሚያመለክት አነጋገር።

ሾፌሩ ሸዋዬንም ረዳቱንም ተውት አድርጎ ወደ ሌሎች ሰዎች ጠጋ ብሎ ያወራ ጀመር። ረዳቱ «ዲላ ዲላ!» ማለቱን ቀጠለ። ሸዋዬ ግን ምናልባት ሾፌሩ ወንበር ፈልጎ ያስቀምጠኝ ይሆናል በማለት ቆማ ትጠባበቀው ጀመር። ከትንሽ ቆይታ በኋላ ረዳቱ ሾፌሩን ተጣራ። «ማንዴ! ማንዴ! ግባና እንሂድ!» አለ።

ሾፌሩ የረዳቱን ጥሪ በመቀበል ያዋራቸው የነበሩትን ሰዎች ተሰናብቶ መግቢያው በር በኩል ወደ መኪናው ሲያመራ ሸዋዬ ከኋላ አለችና «ማንዴ፣ እንዴት አረፈኝ ታዲያ?» ስትል እንደ ማፈር እያለች ጠየቀችው። የሾፌሩን ስም ከረዳቱ ጥሪ የወሰደችው ነው።

«አልገባሽም እንዴ?» አላት ሾፌሩ የራሱን መግቢያ በር ከፍቶ በእጁ ያዝ እንዳደረገ።

«መግቢያው ጨንቆኝ።»

ሾፌሩ ከመኪናው ላይ ወጥቶ ከተቀመጠ በኋላ ወደ ኋላው ዞሮ ሲመለከት እሱንትም መኪናው ሞልቶ ተጨናንቋል። መተንፈሻ የለም። ግን አንድ ነገር ትዝ አለው። ሞተሩ ላይ ተቀምጠው ወደ ነበሩት ሰዎች እየተመለከተ «እናንተ ተነሱ! ሞተር ላይ መቀመጥ ክልክል ነው! ወደ ኋላ! ወደ ኋላ! ዳይ! ዳይ!» አላቸው። ሾፌር መሆ ይህ የሚናገረው ሁሉ በተለይ በተቸገረ ተሳፋሪ ዘንድ ተተባይነት አለውና ሰዎቹ እየተጉተመተሙም ቢሆን ተነሱ። ወደኋላ እየተጋፋ ተሸጋሽገው መቀመጫቸውን ካስረጋገጠ በኋላ ሾፌሩ ከመኪና ወርዶ ሸዋዬ በራሱ በር በኩል እንድትገባና ሞተር ላይ እንድትቀመጥ አደረጋት። ሸዋዬ ገባችና ፊቷን ወደ ሾፌሩ አድርጋ እግሮቿን በማርሹ አጠገብ ኮርምታ በመቀመጥ ጉዞው ተጀመረ።

«አስቸገርኩህ አይደል!» አለችው ሸዋዬ ሾፌሩ ማርሽ ሲቀይር ሲል እግሯ እያስነሳት የነበረ አጋጣሚን መነሻ በማድረግ።

«ምን ሳድርግ፣ በሴት ልጅ አይጨከንም ብዬ ነዋ!» አላት ሾፌሩ ቀና ብሎ በፈገግታ እያያት።

«ሁሉም እንዳተ በሆነ!» አለች ሸዋዬ በመኪናው የፊት መስታወት ወደፊት እያየችና ፈገግ እያለች። በዕለቱ ነጣ ያለ ሰማያዊ ኮትና ጉርድ ቀሚስ ለብሳለች። ከትልቢቷ ጀምሮ እስከ ጡቷ ድረስ ሞላ ያለ ሰውነቷ በቀሚሷ ተወጥሮ ቅርፁ ይታያል። በዚያ ላይ አፍንጫ የሚሰነፍጥ ልዩ መዓዛ ያለው ሽቶ ተቀብታለች።

«እንዴት?» አላት ሾፌሩ ሳቅ ብሎ አየት እያደረጋት።

«ለሴት ልጅ ማዘንህ ነዋ!»

«ግን እኮ እናንተ ሴቶች ለወንድ ልጅ አታዝኑም።»

«የሚታዘንለትም አለ።»

«ምን ዓይነት ወንድ ሲሆን ነው የሚታዘንለት?» ሲል እየሳቀ ጠየቃት።

«ልክ እንደ አንተ ተባባሪ ሲሆን ነዋ!» አለችና ሸዋዬ «ኪም-ኪም-ኪም» ብላ ሳቀች።

«አ! ወደሽኛላ!»

«መውደድ ሲሉህ ታዲያ...»

«በቃ ገብቶኛል፣ ውድድድ! አደረኩህ ማለት ነው» በማለት ለራሱ ስቆ ሸዋዬንም አሳቃት።

«ተጫዋች ቢጤ ሳትሆን አትቀርም!»

«በተለይ አጫዋች ካገኘሁማ!»

«እ!»

«ማጫወትም እችልበታለሁ።»

ሁለቱም ሳቁ። ፈገግታቸው ከፊታቸው ላይ ሳይጠፋ ለአፍታ ያህል ዝም ዝም ካሉ በኋላ ሾፌሩ ቀጠለ። «ለምን መጥተሽ ነው?» ሲል ጠየቃት።

«ሰምቶ ፈልጌ ነበር። ግን አጥቻቸው ተመለስኩ። ሥራዬንም ትቼ በከንቱ ለፋሁ።» አለችና ያ ቀጭኗ እንደገና ትዝ ብሏት ሳታውቀው ከንፈሯን ነከሰች።
«የት ነው የምትሰራው?»
«መምህር ነኝ።»
«አ! ምሁር ነሽ!»
«መባሉ ይሆን? ኪም-ኪም-ኪም-ኪም…»
«ከአስተማሪ በላይ ምሁር አለ እንዴ» አለና «እኛ ባለመማራችን አይዳል የሰው መኪና ስንገፋ የምንኖረው!» አላት።
«ታዲያ የምትጠፍሩት እናንተ!» አለችው ሸዋዬ ያን መሪ የያዘ ጠብደል እጁን እያተመለከተች።
«ስርቀን ስለምንበላ እኮ ነው። አየሽ፣ እንዲህ እንደ አሁኑ ትርፍ ሰው ስንጭን ቦጨቅ የምናደርጋትን ገንዘብ አንሳሳትም፣ ወዲያው ጉርስ ነው። አለበለዚያማ ይንቃብን ይመስለናል።»
«ለሚስቶቻችሁ ብትሰጧቸው እኮ…» ብላ ሳትጨርስ ሾፌሩ ቀደማት።
«ልብ ያላት ሴት የለችማ!»
«ባለቤትህ ገንዘብ መያዝ አትችልም?»
«እሷማ ገንዘቡን ብቻ ሳይሆን እሷም አብራ ጠፋች።»
«ማለት?»
«ነገሩ ብዙ ነው የኔ እህት! አሁን አውርቼ አልጨርሰውም።» አላትና ሾፌሩ ለአፍታ ያህል ወደ ትካዜ ውስጥ ገባ። ሾፌሩ ባለ ትዳርና የአንድ ልጅ አባት ነበር። በስራው ፀባይ ከቦታ ወደ ቦታ አዘውትሮ ሲዘዋዋር በመሀል ሚስቱ ከሌላ ወንድ ጋር ስትማግጥ ቆይታ የኋላ ኋላ እንዲያውም ጭራሽ ከድታው ተሰውራ ትቆያለች። ውላ አድራ ያንኑ ያማገጣትን ሰውዬ አግብታ ትኖራለች። ሾፌሩ ከዚያ ወዲህ በወንደላጤነት ብቻውን ይኖራል። ይህን ታሪክ ለሸዋዬ ነገራትና «አያሳዝንም?» ሲል ጠየቃት።
«በእውነት በጣም ያሳዝናል!»
«ይኸውልሽ ያልተማረ ሰው ትርፉ ይኸ ብቻ ነው።»
«መማር ብቻ አይምሰልህ፣ ልብም ይጠይቃል።»
«ጎሽ!» በማለት ሾፌሩ ሸዋዬን አደነቀና «አየሽ፣ ይህን እንኳ ማለትሽ የመማርሽ ውጤት ነው።» አላት ፈገግ ብሎ አየት እያረጋት።
«ሀሳቤን ወደድከው?»
«በእውነት አሁንስ አንቺንም ወደድኩሽ»
«ተዋደድና!»
«ነገሩ ሞቶ!»
በራሳቸው ወሬና ንግግር ሁለቱም ተሳሳቁና ለአፍታ ያህል በዝምታ ተጓዙ። ቆየት ብሎ ግን ሾፌሩ ወሬውን ቀጠለ።
«የኔስ ታሪክ ተዘከዘከ፤ ያንቺስ?» ሲል ጠየቃት ሸዋዬን በማሽኮርመም ዓይነት ፈገግ ብሎ በቅንድቡ ሥር አየት እያረጋት።
«ምን ይመስልሃል?» አለችው በመሽኮርመም ዓይነት አየት እያደረገችው።
«ልጆች ያሉሽ ይመስለኛል።»
ሸዋዬ አንገቷን በመነቅነቅ፡ ‹የለኝም› የሚል መልስ ሰጠችው።
«እንዴ! እስከ አሁን ምን ትጠብቂያለሽ?»

«ባል» አለችና ሸዋዬ «ኪም-ኪም-ኪም-ኪም…» ብላ ለራሷ ሳቀች።
«እስከ አሁን አላገባሽም?»
«ዘገየሁ? ኪም-ኪም-ኪም-ኪም…»
«ለነገሩ ይደርሳል።» አለና «ምናልባት ግራ አብሮ ያዋለን ጌታ አብሮ ሊያሳድረን ይሆን እንዴ?» ብሎ ፈገግ እያለ ፊት ለፊት ያየት ጀመር።
«ጭራሽ! ኪም- ኪም - ኪም -ኪም…»
«ማን ያውቃል ቢያጋባንስ?»
«ሾፌርና አስተማሪ ተጋቡ ብሎ የዓለም ጋዜጠኛ ሁሉ ይሰብሰብ! ኪም-ኪም- ኪም -ኪም…»
«ምን አገባን?»
ሾፌሩና ሸዋዬ እንዲህና እንዲያ እየተባባሉ ሲጫወቱ ሳያውቁት ዲላ መዳረሻ ከሆነችው የመጨረሻ ጎራ ላይ ደረሱ። መኪናዋ በመንገድ ላይ ባሉ የተለያዩ ትንንሽ ከተሞች እየቆመች ተሳፋሪ ስትጭን ስታወርድ ቆይታለች። ሾፌሩ ግን ‹ሆም› ሲባል መቆም ‹ሂድ› ሲባል መሄድ እንጂ ስንት እንደወረደ፣ ስንት እንደተሳፈረ አያስታውስም። ቀልቡ ሁሉ ከሸዋዬና ከጫዋታቸው ጋር ብቻ ነበር።
«እንዴ! ዲላ ደረስን እኮ አንቺ!» አላት ዲላ ከተማን ቁልቁል እየተመለከተ።
«አልታወቀህም አይደል?»
«እረ ስም ሳንለዋወጥ እንዳንለያይ!» አለና ዞር ብሎ በፈገግታ እያያት «እኔ ማንደፍሮ ጌጤነህ እባላለሁ። ሲያቆላምጡኝ ደግሞ ማንዴ፣ ማንድዬ፣ ማንድይዬ!» አለና «አንቺስ?» ሲል ጠየቃት።
«ስምህ አልበዛም? ኪም - ኪም - ኪም-ኪም…»
«ማን ያውቃል ገና አንቺ ትጨምሪልኝ ይሆናል።»
«በዚሁ ላይ?»
«በይ ንገሪኝ!»
ሸዋዬ ትንሽ ስትሽኮረመም ቆየችና ስሟን በአንዴ ጥቅልል አድርጋ ሳይሆን እየቆራረጠችና እንደ ዜማ መነሻ የመኪናውን ስፖንዳ በእግሯ እየመታች፡-
«መምህርት–ሸዋዬ–ተስፋዬ– እባላለሁ!» አለችው።
«እኔ ደግሞ ‹የሸዋ› እልሻለሁ።»
«እንዴ!» አለች ሸዋዬ በሆዷ። ባርናባስ ወየሶም ለመጀመሪያ ጊዜ ሊተዋወቃት በዚሁ ሁኔታና ስም አወጣጥ ነበር። በሆዷ ‹ባርኔ፣ ማንዴን ተክተህ ልትሄድ ይሆን እንዴ?› አለች። ትናንት የሸኘቱን ድግስ በልታለችና ከእንግዲህ ባርባናስ ላልተወሰነ ጊዜ ትዝታ ሆኖ እንደሚቀር ታውቃለችና።
«ይመችሻል?» ሲል ማንደፍሮ ስለ ስም ቁልምጫው ጠየቃት።
«ድሮም እጠራበት የነበረ ነው።» አለችው ሳቅ እያለች።
«ከእንግዲህ ተወርሳችኋል ብለሽ ንገሪያቸው።» ብሎ ማንደፍሮ ለራሱ ስቆ ሸዋዬንም አሳቃት።
መኪናዋ ከዲላ መናኸሪያ ውስጥ ገባች። በየመንገዱ ታጭቆ የነበረ ተሳፋሪ ሁሉ መውረድ ጀመረ። ሸዋዬ ሞተር ላይ ስለነበረች መተላለፊያ ስላልነበራት መጠበቅ ነበረባትና ለአፍታ ያህል በዚያው በተቀመጠችበት ላይ ተቀምጣ ሳለች ማንደፍሮ አናገራት።
«ቢታ መውረድሽ ነው?» አላት እጇን ያዝ አድርጎ።

«መኪናህ ታዲያ መኝታም አለው እንዴ? ኪም-ኪም-ኪም-ኪም...»
«ባይኖረውም መኝታ ካለበት ቦታ ያደርሳል፡፡»
«ሽሬ ከዚህ እንዲታሳድረኝ ፈራሁ፣ ልቀቀኝ!» አለችው እየሳቀች፡፡
«ቢያንስ አድራሻሽን፡፡»
«ምን ያደርግልሃል?»
«አንቺን ፈልጌ አገኝቢታለሁ፡፡»
«ሌላ ጊዜ፡፡»
«ሌላው ጊዜ ሌላ ይሰራብታል፡፡ አድራሻ ግን ዛሬ ማለት አለበት፡፡» አለና ማንደፍሮ ጠበቅ ሲያደርጋት ሾዋዬ ተረታች፡፡
«እሺ ስልኬን ያዘው፡፡»
ማንደፍሮ ደስ እያለው ወረቀትና እስኪርቢቶ ከኪሱ እያወጣ «የቤት ነው የስራ ቦታ?» ሲል ጠየቃት፡፡
«የመምሪያ ቤት፡፡»
ማንደፍሮ ሾዋዬን ከመኪና አውርዶ ከሸኛት በኋላ ወዲያው ወደ ስልክ መደወያ ቦታ አመራ፡፡ ገና ሾዋዬ ከዓይኑ ሳትጠፋ በሰጠችው ስልክ ደውሎ «መምህርት ሾዋዬን ፈልጌ ነበር» ብሎ ሲጠይቅ «ዛሬ ስራ አልገባችም» የሚል ምላሽ ተሰጠው፡፡ የሾዋዬን አድራሻ በትክክል ማግኘቱን አረጋገጠ፡፡ ብዙ አልቆየም፣ በዚያው ሰሞን ሾዋዬን በስልክ አግኝቶ ቀጠሮ አሲያዛት፡፡ በቀጠሮ ሠዓትና ቦታ ተገናኙ፡፡ በሉ ጠጡ፡፡ ተጫወቱ፡፡ ማንደፍሮ የማሳረጊያ ጥያቄ ሲያቀርብ በሾዋዬ ተቃውሞ ለሌላ ቀን ተላለፈበት፡፡ ያም ቀን ደረሰ፡፡ ደግመው ተገናኙ፡፡ ሾዋዬ ማንደፍሮን በቤቷ አስተናገደችው፡፡ ደገሙ፡፡ ደጋገሙ፡፡ ሾዋዬ ማንደፍሮን ወደደች! ማንደፍሮም በዚያው ልምድ!! ቋሚ መኖሪያው አዋሳ ቢሆንም ወደ ዲላ ብቅ ባለ ቁጥር አድራሻው የሾዋዬ ቤት ሆነ፡፡ ውል ያልያዘው ባልና ሚስትነት ተጀመረ፡፡ እነሆ ከዓመት በላይ ሆኗቸዋል፡፡

በድሉ አሸናፊና ማንደፍሮ ጌጤነህ ቀድሞም ይተዋወቁ ነበር፡፡ መነሻው በድሉ የተሽከርካሪ ባለ ንብረት፣ ማንደፍሮ ሾፌር ስለሆነ ከህዝብ ማመላለስ ስራ ጋር በተያያዘ በአንድ ወይም በሌላ መንገድ ስለሚገናኙ ነበር፡፡ ከትርብ ቀናት ወዲህ ደግሞ የተለየ ግንኙነት ፈጥረው ሰንብተዋል፣ ማንደፍሮ ቀድሞ ይዞት የነበረውን ተሽከርካሪ ትቶ በሌላ መኪና ላይ ለመቀጠር ሲፈልግ፣ በድሉ ደግሞ የአንድ ተሽከርካሪን ነባር ሾፌር አባርሮ ሌላ ለመቅጠር በነበረው ፍላጎት መሰረት በመጣየየታቸው ነው፡፡ በመጨረሻም ሁለቱ በቀጣሪና በተቀጣሪነት ስምምነት ላይ ደርሰው ውል የተፈራረሙ ዕለት እማኝ ምስክሮቻቸውን ሲጋብዙ በዋሉበት ቀን ወደ ማታ ላይ ደግሞ ብቻቸውን ከአንድ ቡና ቤት ውስጥ ቁጭ ብለው ይጫወታሉ፡፡ በመሀል የደመወዝ ነገር ተነስቶ ቀድሞም ቢሆን ቅር ብሎት የነበረው ማንደፍሮ ስሜቱን ለበድሉ ማካፈል ጀመረ፡፡
«የምትከፍለኝ ደመወዝ ከስራውና ከጣልክብኝ አደራ ጋር በፍጹም አይጣጣምም፡፡» አለው በድሉን፡፡

«ለዚህም እኔ ስለሆንኩ ነው፣ አባቴ ቢሆን ‹ኡኡ› ነው የሚለው፣ ቀድሞ ስራው የታለና ከዚህ በላይ ደመወዝ ይከፈላል፡፡» ሲል በድሉ መለሰለት፡፡
«እውነቱን ነው በድሉ፣ እኔ ወደ ዲላ ጢጋ ለማለት የፈለኩበት ጉዳይ ባይኖረኝ ኖሮ በዚህ ደመወዝ ... » ብሎ ሳይጨርስ በድሉ ቀጸመው፡፡
«ተጠቃለህ ብትገባማ ጥሩ!»
«የሚቀር አልመሰለኝም፡፡»
«ቤት ልትሰራ አስብክ?»
«መሰረቱን ጥያለሁ፡፡» አለ ማንደፍሮ ሳቅ እያለ በድሉን በማየት፡፡
«የት ቀበሌ?»
«እዚህ ቤር አምስት ቀበሌ ስምንተኛ መንገድ አካባቢ፡፡»
«እዚያ አካባቢ ክፍት ቦታ የታለና?» አለና በድሉ የት ጋ ሊሆን እንደሚችል ሲያሰላስል «ሒስ ቦታ አግኝቼ፡፡» በማለት ማንደፍሮ አሁንም ፈገግ እያለ በድሉን ያየው ጀመር፡፡ በውስጡ ሌላ ምስጢር እንዳለ ከፊቱ ላይ ይነበባል፡፡
«እኔ እንጃ!» አለና በድሉ ቢራውን ሊጎነጭ ብድግ እያረገ «ግዢቱህ እንደሆን እንጂ በምሬት የሚሰጥ ቦታ እዚያ አካባቢ ስለመኖሩ ተጠራጠርኩ፡፡» አለው፡፡
«ለመሆኑ ያን አካባቢ በደንብ ታውቀዋለህ እንዴ?»
«ዲላ ውስጥ የማላውቀው ሰውና ቦታ የለም፡፡» አለና በድሉ ቢራውን እየተጎነጨ «ማነቴ አይደል?» በማለት ቀለደ፡፡
«እዚያ አካባቢ ማን ማን ታውቃለህ?»
«እኔ ከምዘረዝር አንተ ‹እገሌ› በለኝ!»
«እንዴት መምህር ታውቃለህ?»
በድሉ ሾዋዬ ትገዝ አለችው፡፡ ፈገግ ብሎ ማንደፍሮን ትኩር ብሎ ከተመለከተ በኋላ «ሾዋዬን እንዳይሆን?» አለው፡፡
ማንደፍሮ እንደገና ድንግጥ አለና «እንዴ! እውነትም ታውቃታለህ እንዴ?» ሲል ጠየቀው፡፡
ሁለቱም በፈገግታ ተያዩና በተለይ በድሉ «ሃሃሃ ...» ብሎ እየሳቀ «በደንብ አውቃታለሁ፡፡» አለው፡፡
«በምን ሁኔታ?» አለ ማንደፍሮም የባሰ እየደነገጠ፡፡
«አይዞህ! ጉዳይ ካለህም አትደንግጥ፡፡ አንተ የጣልከውን መሰረት በማያናጋት ሁኔታ ነው የማውቃት፡፡»
ሁለቱም ተሳሳቁ፡፡
«ለመሆኑ መቼ ጀምረህ ነው የምታውቃት?» ሲል በድሉ ማንደፍሮን ጠየቀው፡፡
«ከዓመት አለፈኝ»
በድሉ ባርናባስ ወደ ውጭ የሄደበትን ጊዜ አሰላስልና እሱ ከሄደ በኋላ፣ ግን ደግሞ ወዲያው እንደሄደ ሊሆን እንደሚችል ገምቶ በመገረም ዓይነት ራሱን ወዘወዘ፡፡
«ምነው በድሉ? ተደርቤ ይሆን ወይስ...» ብሎ ማንደፍሮ በድሉን ትኩር ብሎ ሲያየው በድሉ ቀጠለ፡፡
«አይ አይ! እሱንማ ነገርኩህ! እኔ የማውቀው ሌላ ነገር ስላለ ያ ትዝ ብሎኝ ነው፡፡» አለው አሁንም ቢራውን እየተጎነጨ፡፡
«መጥፎ ነገር ካለ ንገረኝ፡፡»

«ምንም! እንዲያውም ለኔም ለአንተም ጥሩ አጋጣሚ ሳይሆን አይቀርም።»
«ልቤን እንጠለጠልከው።»
«እንዲያውም እንዲህ አድርግ» አለ በድሉ ፈገግ ብሎ እያየው።
«እንዴት?»
«የኔና የእንተን ግንኙነት ሳትነግራት፤ አንድ ቀን ብሰው ጋር አስተዋውቅሽለሁና ተዘጋጂ፣ ብለህ የእሷንም ልብ አንጠልጥለው። አብረን እንሄድና የሚሆነውን ታያለህ።»
«ተው አንተ ሰው... ደሞ ከገባህ በኋላ አልወጣም ያልክ እንደሆንስ» በማለት ማንደፍሮ ራሱ ስቆ በድሉንም አሳቀው።
እንዲህ እንዲህ እያሉ ሲጨዋወቱ አመሹ። በድሉ ግን ለማንደፍሮ እንዳቸም ምስጢር አውጥቶ አልነገረውም። በባርናባስ ምትክ ማንደፍሮ በሸዋዬ ቤት መግባቱ ለበድሉ ጉዳዩ አልነበረም። ምክንያቱ ባርናባስ ባለ ትዳር መሆንና ከአንድ ዓመት በላይ ለሆነ ጊዜ ሲቆይ መቻሉ ሌላው ነው። ከዚያም በላይ ቀድሞ ነገር በድሉና ባርናባስ ለረጅም ጊዜ የሚተዋወቁ የአንድ ከተማ ነዋሪዎች ከመሆናቸው በቀር የተለየ ግንኙነት አልነበራቸውም። ስለዚህም ከማንደፍሮ ጋር በሸዋዬ ቤት መገኘቱ ለእሱም ሆነ ለእሷ የሚጎረብጣቸው ነገር እንደሌለ ያውቃል።
ማንደፍሮ የበድሉና የሸዋዬ መተዋወቅ መሰረቱ ምን ሊሆን እንደሚችል ለማወቅ ሲጓጓ ሰንብቶ አንድ ቀን ከሄደበት አገር ዶሮ፣ ሽንኩርትና ቅቤ ገዝቶ በመምጣት ለሸዋዬ እያስረከበ «በነገው ዕለት ትልቅ እንግዳ ጠርቻለሁ። ከእንግዳም ጋር አስተዋውቃችኋለሁ። ሲትነትሽ ይታይበታልና አስማምሪው።» አላት።
ማግስቱ ቅዳሜ ነው። ወደ አሥር ሠዓት አካባቢ ሸዋዬ በሁሉም ነገር ተዘጋጅታ የማንደፍሮንና የትልቁን እንግዳ መምጣት ስትጠባበቅ ማንደፍሮ ከዲላ ይርጋለም የነበረውን የደርሶ መልስ ምድብ ስራውን አጠናቆ ከበድሉ ጋር ለማምሻ የሚበቃ ጫት ገዝተው ከሸዋዬ ቤት ከች አሉ።
«እንዴ!» አለች ሸዋዬ ደስታ አይሉት ድንጋጤ እንዳች የማታውቀው ስሜት መንፈሷን ልውጥውጥ እያረገው። ቀጥላም «አንተ ነህ እንዴ ትልቁ እንግዳ!» አለችው በድሉን ልትስመው ጠጋ እያለች።
«በአንድ ወቅት ትልቅ ነበርን። እያደር ግን...» ብሎ በድሉ ሳቅ እያለ ሸዋዬን ሲስም ማንድፍሮ ጣልቃ ገባ።
«እንተዋወቅ ነበር እንዴትሉ!»
«በእንተ ቤት ገና ማስተዋወቅህ ነው!» አለችና ሸዋዬ ሁለቱም ቁጭ እንዲሉ ጋበዘቻቸው።
«ተሸውደሀል ማንዴ።» አለው በድሉ ከተነጠፈው ፍራሽ ላይ ቁጭ እያለ።
«እንዴት?» አለ ማንደፍሮ የተገረመ በመምሰል።
«ቁጭ በልና በእርጋታ ይነገርሃል።» አለው በድሉ።
«ጉድ ሳይሰሙ መስከረም አይጠባም አሉ!» እያለ ማንደፍሮም ወደ ፍራሿ አለፍ ብሎ ተቀመጠና «የሸዋ፤ በይ ከጫት በፊት የሚበላ ነገር ቶሎ በይ!» አላት።
ሸዋዬም ግርምቷን ደጋግማ እየገለጸች ምግብ የማቅረብ ስራዋን ተያያዘችው።
በድሉ ከዚያ ቤት ከቀረ ከዓመት በላይ ሆኖታል። በሸዋዬ ቤት ያየው ለውጥ አስገረመው። የሸዋዬ ታጣፊ አልጋ ልዩ በሆነ ሞዝቦልድ አልጋ ተተክታለች፤ ለብቻ ቢተኙበት ‹የሰው ያለህ› የሚያሰኝ። ከፊትለፊቱ ባለ መስታወት

ፊሬ የግድግዳ ጥግ ይዞ ተሰይሟል። የጓዳው በር እንኳ መጋረጃው ጎዶን ይለባል። ቁቁ በሆሄ ቀለም ተቀብቶ ፍክት ብሏል። ሁሉም ነገር ደስ ይላል። ይህን ሁሉ ሲያዩ ቆይቶ የሸዋዬን ጓዳ ውስጥ መሆን አጋጣሚ በመጠቀም ወደ ማንደፍሮ ዞር ብሎ በማለት በሹክሹክታ አነጋገር «ምን መሰረት ጥያለሁ ትላለህ! የዚህ ሁሉንም አቀመሃል እንጂ!» አለና ለራሱ እየሳቀ ማንደፍሮንም አሳቀው።
ሸዋዬ እንጀራና ወጡን ለበድሉና ለማንደፍሮ አቅርባ እየጋበዘች እሷ ግን ቡና ማፍላቱን ስራ ቀጠለች። ግን ከእነሱ ይበልጥ እሷ ነበረች የምትበላው፤ ሁለቱም እየተፈራረቁ በሚያጎርሷት ጉርሻ ጉንጫ እየሞላ። ስራ ያለ ማቋረጧ ደግሞ ለቡናው ቶሎ መድረስና ለጫት ቅሞሹ መጀመር አስተዋጽኦ አደረገ።
«ማንዴ!» ሲል ጠራው በድሉ ጫቱን እንጉብሶ እየቀነጣጠበ።
«ወይ»
«አንተ እዚህ ቤት አባወራ ከመሆንህ በፊት እኔ ደግሞ እማች ነበርኩ።»
«ማንን አግብተህ?» አለ ማንደፍሮ በድሉንም ሸዋዬንም ተራ በተራ እየተመለከተ። ከዚህ በኋላ ለሚወራው ሁሉ ማንደፍሮ አዲስ ስለሆነ ቀልቡ ይጓጓ ጀመር።
«ቀሪውን ሸዋዬ ትንገርህ።»
«ትልጥፍና ጎድሎህ ያጣኸውን ዕድል አሁን ለምን ታነሳሳለህ?» አለች ሸዋዬ ፈገግ ብላ በድሉንም ማንደፍሮንም እያየች።
«እኔ በድሉ!?»
«እኔ ሸዋዬ ነኝ!»
«እኔ ጨዋታ ልሰማ ነው።» አለ ማንደፍሮ ሁለቱንም እያየ።
«አረፍ ዋጋ አለው፤ በጠራ ቀረ።» ብሎ በድሉ በቁጭት ዓይነት ራሱን «ምን ዋጋ ማንደፍሮ ቀጠለ። «እንዴት? ለምን?»
ወዘወዘ ሲያደርግ
«ቢቃ! አቃተው፤ ቀረ።» አለች ሸዋዬ።
«ልጃገረድ ነበረች?» ሲል ማንደፍሮ ጠየቀ በተለይ ሸዋዬን እየተመለከተ።
«ተድሞ ማን ወንድ ሆኖ እዚያ ቦታ ደረሰና!» አለችና ሸዋዬ «ኪም ኪም ኪም....» ብላ ሳቀች።
«ወንድሜ ጉድ ሆንሃል!» በማለት ማንደፍሮ በድሉን ቀለደበት።
«ዝም በላት ትቀልድ፤ ቀስ እያልክ ምስጢሩን ታገኘው የለ!» አለና በድሉ የተነጠበውን ጫት አፉ አደረገ።
«ልጅቱ አሁን የት ናት?» ሲል ጠየቀ ማንደፍሮ።
«እህቷ ናትና እሷ ናት የምታውቀው።»
«እንዴ!» ብሎ እንደ መደንገጥ አለና ማንደፍሮ «ለዚያውም እህትሽ?» ሲል፣ በተለይ ሸዋዬን ጠየቃት።
«ባለ ጉዳይ ይፈልጋት እንጂ እኔ ምን አገባኝ።»
«እቦ ልቤን አታንጠልጥሉት!» አለና ማንደፍሮ እንደ መናደድ ብሎ «ትነግሩኝ እንደሆን ንገሩኝ!» ብሎ ቀነጣጥቦ እጁ ላይ ያጠራቀመውን ጫት ቃመው።
«ሩቅ አገር ነው ያለችው።» አለችው ሸዋዬ።
«መኪና አይገባውም?»
«ሄደህ ልታመጣለት? ኪም-ኪም-ኪም-ኪም ...»
«ምን ችግር አለ? የምነዳው የአባቱን መኪና!»

«ለመቼ ጀምሮ?» አለች ሸዋዬ በቁም ነገር። ማንደፍሮ መኪና መቀየሩን አልሰማችም! ማንደፍሮ ያልነገራት በድሉ ባሳሰበው መሰረት ነው። ፆም የሆነው የዛሬውን የሸዋዬን ግርምት ለመፍጠር በማሰብ ነበር።

«ለነገሩ እንኳ ከሳምንት በላይ አይሆንም።» አላት ማንደፍሮ በመጠነኛም ቢሆን እንደ አፍረት እየተሰማው።

«እንዴ!» አለች ሸዋዬ እውነትም ነገሩ ዱብ ዕዳ ሆኖባት። ሁለቱ ሳምንት እሷ የማታውቀው ምስጢር ይኖራቸው እንደሆን ብላም ተጠራጠረችና ተራ በተራ ታያቸው ጀመር። ሁኔታዋ የገባቸው በድሉና ማንደፍሮ የተገናኙበትን አጋጣሚ ዝርዝር አድርገው ሲያስረዷት ወደ ማመኑ አዘነበለች። የተጀመረው ጨዋታ ቀጠለ።

«እውነት ግን ልጅቷ መምጣት አትችልም?» ሲል ማንደፍሮ ጠየቃቸው ሁለቱንም ተራ በተራ እየተመለከታቸው።

«ሸዋዬ ከአሰበችበት ከባድ አይሆንም።» አለ በድሉ አሁንም ሸዋዬን እየተመለከተ።

«እንዴት ነው የሸዋ ይኸ ነገር» አላት ማንደፍሮም ሸዋዬን እየተመለከተ።

«ይሆን አይመስለኝም» አለች ሸዋዬ። ግን ደግሞ ድንገት ፍንዝዝ ትክዝ መሰለች። ሸዋዬ እውነትም ጭልጥ ብላ ከሀሳብ በማለት ከሃሳብ ውስጥ ገባች። እንኳን በውኗ በህልሟ እንኳ ታይቷት የማያውቅ አዲስ ሀሳብ በአዕምሮዋ ተፈጠረ። እውነት ሔዋን በዚህ አጋጣሚ ወደ ዲላ ብትመጣስ የሚል ሀሳብ በውስጧ ተመላለሰ። መንገዱ እንደሆን ክፍት ሆኗል፣ እስቻለው ከዘመቻ አልተመለሰም። ወደፊት ቢመጣ እንኳ ሁኔታዎች ሁሉ ከመሠረታቸው ከተለወጡ ምን ሊፈጠር ይችላል? እስከ ዛሬ ሔዋንም ስለ እስቻለው ተስፋ ቆርጣ ሊሆን ይችላል። እንዲያውም ሔዋንን ከበድሉ ጋር የማቀራረት ምኞቷ ተሳክቶ የሔዋን ህይወት የተሻለ ቢሆን ‹ይኸው! የኔም ዓላማ ይኸ ነበር› እያለች ለመፎከርና በተለይ ከእናቷ ጋር የሻከረባት ግንኙነት ሊስተካከል እንደሚችል ይታያት ጀመር። ምናልባት የሔዋንና የበድሉ ግንኙነት እሷም ከማንደፍሮ ጋር ያላትን ግንኙነት መሰረቱን እያጠበቀው ሊሄድ ይችላል። ሸዋዬ ደስ ደስ የሚል ስሜት ይሰማት ጀመር። ድንገት አፍን የሚያደርጋት ግን ሔዋንን የምታገኝበት መንገድ! በእርግጥ ሔዋን እሷን ተማምና ወደ ዲላ ትመጣ ይሆን? እናቷስ እሷን አምነው ሔዋን ከክብረ መንግስት ትመጣ ዘንድ ይፈቅዱ ይሆን? አሳሳቢና አስጨናቂ ጉዳይ!

«አንድ ነገር በይ እንጂ የሸዋ ምነው ዝም አልሽ?» ሲል ማንደፍሮ ከሃሳቧ ቀሰቀሳት።

«እስቲ እየዋልን እያደርን»

ምዕራፍ አሥራ ሁለት

ኑሮ በክብረ መንግስት ለሔዋን አልተመቻትም። በእናት በአባቷ ቤት ደባል ሆናለች። ተጠልዳ ባደገችበት አገር ባይተዋር ሆናለች። ቡሪያዋን ብዙ ሰው እያለ ብቸኛ ሆናለች። በሃሳብና በጭንቀት ብዛት ራሷን ረስታለች። ብትበላ ብትጠጣ ሆዷ ይመገብ እንደሆነ እንጂ! መንፈሷ ግን ርሀብተኛ ሆኗል።

ባህሪዋም ተለውጧል። ደስተኛ የነበረች ሔዋን ብስጩ ሆናለች። ፍልቅልቋ ሔዋን አኩራፊ ሆናለች። ታዛዥና ትሁት የነበረች ሔዋን ነጭናጫ ሆናለች። ተጨዋቿ ሔዋን በትካዜ ተውጣ በጭንቀት ተወርሳለች። ጤንነቷም ተጓደለ። ዘወትር 'ሰዉን' ማለት አበዛች። ከመቆም ይልቅ መቀመጥን፣ ከመቀመጥም መተኛትን አዘወተረች። የምግብ ፍላጎት አጣች። ከምትበላው ምግብ ይልቅ የምትጠጣው ውሃ ያምራት ጀመር። ከቶም 'ብይ' ባትባል ደስታዋ ሆነ። የግድ ብትበላም ብዙ አይስማማትም። እሷ ተቸግራ ቤተሰቦቿንም አስቸገረች። የህመሟ ጉዳይ ቤተሰቦቿ በተለይ በአባትና እናቷ ዘንድ ሌላ ስጋት ፈጠረ። 'ያ የልጅነት ህመሟ ሊነሳባት ነው' እያሉ ይጨነቁ ጀመር።

ስጋታቸው መነሻ አለው። ሔዋን በህጻንነቷ እስከ ሁለት ዓመቷ ድረስ ፍፍት፣ ድንቡሽቡሽ ያለችና ፍልቅልቅ ነበረች። ከዚያ በኋላ ግን ምንነቱ ባልታወቀ በሽታ ሁለመናዋ ተለዋወጠ። ሰውነቷ እየከሳ ቆዳዋ እስከ መሸብሸብና እየጠቆረች መልኳ እስከ መቀየር ደረሰ። በእግሯ መሄድ ከጀመረች በኋላ ወደ መዳህ! ቀጥሎም ቁጭ ብላ ቀረች። ለቅሶ የማታውቀው ሔዋን መነጫነጭ አብዝታ አልቃሻ ሆነች። ወላጅ አባትና እናቷ ትሞትብናለች እያሉም መስጋት ጀመሩ።

የእሷን ህይወት ለማትረፍ ያልተደረገ ጥረት አልነበረም። በተለይ እናቷ ያልተሳለሉበት ቤተክርስቲያን፣ ያልሄዱበት ጠበልና ያልጠየቁት ጠንቋይ አልነበረም። ዘመናዊ ህክምናም እንዲሁ። የሔዋን ጤንነት ግን እንዳችም መሻሻል ሳያሳይ ድፍን ስድስት ዓመት ሞላት። እናቷ ሲፈጩም ሲጋግሩም፣ ሲያነፍሱም ሲቀቅሉም፣ ገበያ ሲሄዱም እንኳ ልጃቸውን አቅፈው ወይ አዝለው መንከራተት ግድ ሆነባቸው።

የሔዋን እናት በዚሁ ሁኔታ በመልፋት ላይ ሳሉ አንድ ቀን ያልታሰበ ሁኔታ ገጠማቸው። ቤታቸው ከክብረ መንግስት ሰሜን ምስራቅ አቅጣጫ ከከተማው ወጣ ብሎ በሚገኝ ገጠራማ ሥፍራ ስለሆነ የሱቅ ዕቃ ሊገዙ ሔዋንን ታቅፈው ወደ ከተማ ሄዱ። ከአንድ ሱቅ ደርሰው የግዢ ወረፋ ሲጠብቁ ሔዋንን በሱቁ ባንኮኒ ላይ አስቀመጧት። ሔዋን ምንም እንኳ በህመም ምክንያት ሰውነቷ ቢጥመለመልም ነፍስ እያወቀችና አፏን እየፈታች በመሄዷ በሱቁ መደርደሪያ ላይ የሚታዩ የሸቀጥ ዓይነቶችን ለእናቷ እየጠቆመች 'ያ ምንድነው እማ? ያስ? ያኛውስ?... እያለች ትጠይቃቸዋለች። እሳቸውም ያወቁትን ያህል ያስረዷታል።

በሱቁ ውስጥ ዕቃ ሊገዙ የገቡ አንዲት ዕድሜያቸው ወደ ስልሳ የሚጠጋ ሴት አዛውንት ሔዋንና እናቷ የሚመላለሱትን እያዳመጡ በተለይ ሔዋንን እየት ያደርጓት ኖሯል። ጤነኛ እንዳልሆነች ከሁኔታዋ እየተረዱ ከንፈራቸውን እየመጠጡ

ሲያገኟት ቆይተው የገዙትን ዕቃ በመቀመጫቸው ላይ ከቆጣጠሩ በኋላ «ይቺ ልጅ ስንት ዓመቷ ነው የኔ እህት?» ሲሉ የሐዋንን እናት ጠየቋቸው።

«ድምጿ እንጂ ስድስት ዓመት ሞላት።»

«ጤና የላትም?»

«የላትም የኔ እናት! በጣም ተቸግሬያለሁ። ከሁለት ዓመቷ ጀምሮ ይኸው ትንገላታብኛለች። ይኸው አራት ዓመት ሙሉ እሷን አገዙ እኖራለሁ።»

«እምም...ም!» አሉና ሲትዮዋ «ቤትዎ የት ነው?» ሲሉ ጠየቋቸው። የሐዋን እናት በምልክት ሲነገሯቸው። «እስቲ አንድ ቀን ብቅ ብዬ አጠይቅዎታለሁ፤ ምናልባት መዳኒት ያገኙላት እንደሆን።» አሏቸው።

«ሆኖ ነው የኔ እናት!» ብለው የሐዋን እናት ፍንድቅድቅ እያሉ «አገርዎ የት ነው?» ሲሉ ጠየቋቸው።

«ቅርብ ነው። ተሲያት ላይ ብነሳ እርስዎ ቤት መድረስ እችላለሁ።»

«አደራ የኔ እናት፣ እንደው አደራ! እንደው አደራ!» በማለት የሐዋን እናት ሴትዮዋን አጥብቀው ተማፀኗቸው።

«አሳ ከፈቀደ ሳምንት እመጣለሁ።»

«እሺ የኔ እናት፣ እጠብቅዎታለሁ።»

ሴትዮዋ ቀጠሮአቸውን አክብረው ከሐዋን ወላጆች ቤት መጡና እዛውንቷ ሴት የባህል ህክምናቸውም ጀመሩ። ሐዋንን አካላቷን እንድትታጠብ ከአደረጉ በኋላ ራሳቸው ታቅፈው ትባት መሰል በሆነ ነገር መላ አካላቷን እየቀቡ ያሿት ጀመር። እምቢ ስትላቸው ያን ሲጨርሱ ሌላ መድሃኒት በማር እየበጠበጡ ያጠጧታል። በዚህ ዓይነት ለሰባት ቀናት እራሳቸው ከአከሟት በኋላ የግድ ይግቷታል። ለሚቀጥሉት ሰባት ቀናትም እናቷ እንዲያደርጉላት መክረዋቸው ወደ አገራቸው ተመለሱ። የሐዋን እናትም በተመከሩት መሰረት ፈፀሙ።

ዘመናዊ የህክምና ጠበብቶች እንዴት ሆኖ? ምኑ ከምን ተገናኝቶ? ስንት ዓይነት በሽታ ምን ዓይነት መድሃኒት? አወሳሰዱስ? መጠኑስ?... ወዘተ እያሉ አመክኒዮአቸውን እንደ ሰጋ እየዘለዘሉ ሊጠያየቁ ይችሉ ይሆናል፤ የሐዋን ጤንነት ግን ከዕለት ወደ ዕለት እየተሻሻለ ሄደ። የተሸበሸበ ቆዳዋ ወጠር፣ ፊቷ ፈካ፣ እያለ ከመምጣቱም በላይ መዳህ ጀመረች። ህክምና በተደረገላት በሁለተኛው ወር ቆማ መሄድ ቻለች። ሦስት ወር ሲሞላት ሙሉ ጤነኛ ሆነች።

የሐዋን እናትና አባት የተሰማቸው ደስታ ወሰን አልነበረውም። ሐዋን እንደገና እንደ ተፈጠረች ቆጠሯት። እየተመላለሱ የሚጠይቋትን ሀኪሟን ሴት ስጦታቸው አልረካ አሉ። አመስግነዋቸው አልጠግብ የሚያደርጋቸውን አጡት። ሁሉም ነገር ሳያረካቸው ቢቀር ቅድስት የነበረውን የሐዋን ስም 'ህዋ' ብለው አሉ። ነገር ግን በዘር ማንዘራቸው ክርስቲያን ስለሆኑ ከዚያው በአዛውንቷ ስም ቀየሩት። ነገር ግን በዘር ማንዘራቸው ... እነሆ ቋሚ ስሟ ሐዋን ሆኖ ቀረ።

ሳይርቁ «ሐዋን» በሚል ተኩት። እነሆ ቋሚ ስሟ ሐዋን ሆኖ ቀረ።

ዛሬ ታዲያ 'ልቤን' እያለች ስትሰቃይባቸው፣ ድካም እየተሰማት ድፍት ብላ ስትውልባቸው፣ ምግብ በአግባቡ መመገብ አቅቷት ሲያዩ፣ ፍዝዝ ትክዝ ስትል እየተመለከቱ አጀንን ይሰጉ ጀመር። ወደ እመት ሀዋ አይሮጡ ነገር እመት ሀዋ መሞታቸውን ከሰሙ ቆይተዋል። ወደ ዘመናዊ ሀኪም ቤት ወስደው

ሊያስመረምሯት ሀኪሞቹ የልብ ችግር እንዳለባት አረጋግጠው ከኪኒን ብቻ ሰጥተው ... ሀኪም ራሷ ናት። ሃሳብና ጭንቀት ካለባት ያንን ትታ መንፈሷን ... ሰፈፍት ማድረግ ይኖርባታል' አሏቸው። ይህ ደግሞ በሐዋን በኩል የሚሞከር አልሆነም። ከሀሳብ፣ ከትካዜና ከጭንቀት ማን ጎትቶ ያውጣት?

ከሀመሟ በተጨማሪ ያለባትን የውስጥ ችግር የሚያውቁላት እናቷ ግን ... አልቆረጡም፣ ሐዋንን የማረጋጋት ጥረታቸውን ቀጠሉ። መጀመሪያ ... አጠኑ። ሐዋን ቤት ውስጥ ከሆነች መደብ ላይ ጋደም ማለት ነው። ቤቱ ... ወደ ጓሮ ሄዳ ከዛፍ ሥር መቀመጥ ነው። ጓሮአቸው ደግሞ ሰፊና ... ዛፎች የተሞላ ነው። ሐዋን ከዚያ ውስጥ በአንዷ ዛፍ ስር መቀመጥ ... ያንንም አጠኑ። አቀማመጧ ይመቻት ዘንድ የዚያችን ዛፍ ዙሪያ ... ደለደሉ። በፀሃይ ጊዜ አሿራ፣ በዝናብ ጊዜ ጭቃ እንዳይሆንባት ሳር ተክለው ... እየጠጡ አለመለሙላት። ይበልጥ እየተመቻች ሲሄድ ተሰማቸው። ሐዋን ወደዚያ አካባቢ የምትሄደው ብዙ ጊዜ ከሰዓት በዚህ አላቆሙም። ... መሆኑን ተከታተሉ። እሳቸውም የቤት ስራቸውን ሲጨርሱ በዚያቸው ዛፍ ... ያጨዋውቷት ጀመር። ሁኔታው ለብዙ ጊዜ በዚሁ ቀጠለ። ... ስር ቡና እያፈሉ ... እያደር እያደር ሐዋን እስክሪብቶና ወረቀት መያዝ ጀመረች። ብዙ ጊዜ ... ያዩዋታል። ግን ደግሞ ስትጽፍ የዋለችውን ማታ ትተቀዋለች። ... ስትጽፍ የሚያዩባት ሁኔታ ያሳዝናቸዋል። ሰማይ ሰማይ ታያለች። ... ፍዝዝ ብላ መሬት መሬት። እንዳንዴ ብቻዋን የምታወራ ይመስል ... ሲንቀሳቀሱ፣ ሌላ ጊዜም ዓይኗ በእንባ ሲሞላ ያያሉ።

የሐዋን እናት ይኽን ሁሉ ሲከታተሉ ከቆዩ በኋላ በምትጽፈው ወረቀት ላይ ... የሚያገኙት እየመሰላቸው ይጓጉ ጀመር። የአስቸገራቸው ግን ስትጽፍ የዋለችውን ነገር ማታ ማታ መቅደዷ ነው። እንዴት አድርገው አግኝተው ሊያስነብቡት እንደሚችሉ ሲጨነቃቸው ቆይቶ ከመዋል ከማደር አንድ ብልሀት ... ቢሳካም ባይሳካም ብለው ሊሞክሩት አሰቡ። ሙከራቸውን ሊያደርጉ ... ሰባት ወትሮ እንደሚያደርጉት ሁሉ ከቀትር በኋላ እዚያው ሐዋን የምትቀመጥበት ዛፍ ስር የቡና ማፍላት ስራቸውን ጀመሩ። የዕለቱ ዋና ዓላማቸው ግን የሐዋንን ስሜት በዘዴ ለመመርመርና የምትጽፈውን ወረቀት አቀማመጥ ልብ ... መመልከት ስለነበር በተለይ የወረቀቱን ጉዳይ በዓይናቸው ሰረቅ እያረጉ ... ሲከታተሉ ቆዩ። በኋላም ቡናው ፈልቶ እየጠጡ ባሉበት ሰዓት፦

«ሕመቤ!» ሲሉ ጠሯት።

«አቤት እማ!» አለቻቸው ሐዋን ዓይን ዓናቸውን እያየች።

«ምንድነው የምትጥፊው?»

«ምንም እማ! ዝም ብዬ ነው።» አለቻቸውና ሐዋን እስኪርቢቶና ወረቀቱን በማስደገፊያ ደብተሯ ውስጥ ከትት አድርጋ ከአጠገቧ መሬት ላይ አስቀመጠችው።

እናቷ የደነገጡ መሰላቸውና «ጣፊ! ጣፊ የኔ ልጅ! የተማርሽውም እንዳይጠፋብሽ ጣፊ!» አሏት እንደ ማባበል ዓይነት።

«መጻፍ የተማሩትን ያስታውሳል ብለሽ ነው እማ?»

«ቢሆንም፣ ቢሆንም! መጣፉ ይሻላል። ጣፊ!»

ሒዎን ግን ጠዲያው ሀሳብ ውስጥ ገባች፡፡ ዓይኗ ሰማይ ላይ ተተከለ፡፡ ልቧ አድማስ ተሻግር ሄደ፡፡ አጠገቧ ያሉትን እናቷን ረሳቻቸው፡፡ በሆዷ እያወራች ከንፈሮቿም ይንቀሳቀሱ ጀመር፡፡

«እሙዬ!» ሲሉ እናቷ አሁንም ከሃሳቧ ቀሰቀሷት፡፡

«አቤት እማ!»

«አሊመ የነገረሽን ረሳሽው? ብዙ ማሰብና መጨነቅ እኮ ይቺን ልብሽን ታጣብስብሻለች ብሎሽ ነበር፡፡ እኔም ስታስቢ ሳይሽ እሰጋለሁ፡፡ ታዲያ አንዳንዴ እንዲ ተልብሽን ስብሰብ አድርገሽ፣ ሀሳብሽን መርሳት ብትሞክሪ ምናለበት የኔ ልጅ፡፡» እሷት በዘዘን አስተያየት መልከት እያሏት፡፡

«አይዞሽ እማ! አትጨነቂ፡፡ ብዙም አላስብ፡፡ አልጨነቅም» አለቻቸው እንገቷን ወደ መሬት ደፋ አድርጋ፡፡

«አየየ....እሙዬ! ሁኔታሽንማ እያየሁት አይደል! መጨነቱማ ምን ይቀራል ብለሽ የኔ ልጅ?» እሷት በትካዜ አነጋገር፦

«ተይ እማ! እንደዚያማ ከሆነ እኔም የባሰ እጨነቅብሻለሁ፡፡ ባይሆን እኔም ማሰቤን እተዋለሁ፡፡ አንቺም አትጨነቂብኝ፡፡» አለቻቸው ዓይን ዓይናቸውን እያየች፡፡

«እባክሽ እሙዬ እባክሽ! እንደው በአጠባሁሽ ጡት ገዝቼሻለሁና ይህን ሰላብና ትካዜ የሚባል ነገር እርግፍ አድርገሽ ተይልኝ! የኔ ልጅ እባክሽ!» እሷት እናቷ ዓይናቸው እንባ እስኪያቀር ድረስ ጭንቅ እያላቸው፡፡

«ተይ እማ! በጡትሽማ አትገዝችኝ! ጡትሽ እኮ ለኔ የእንቺነትሽ መገለጫ ነው፣ የኔነቴ መሠረትም ነው፡፡ ጡትሽ እኮ ሲጋና ደሜ ነው፣ ለዚያውም አስተዳደጌን እንደነገርሽኝ ለዚያን ያህል ዓመት የጠባሁት፡፡ ስለዚህ እማ፣ ግዝትሽን አውርጂልኝ፡፡ ድንገት ተሳስቼ ሀሳብ ውስጥ የገባሁ እንደሆን ግዝት መተላለፍ ሲሆንብኝ ይበልጥ እጨነቅብሻለሁ፡፡ እማ! አሁኑኑ ግዝትሽን አውርጂልኝ! እባክሽ የኔ እናት!» ስትል እጆቿን እያርገበገበች ተማፀነቻቸው፡፡

«እሺ የኔ ልጅ፣አውርጄለሁ፡፡» እሷት እንባቸው ከዓይናቸው ላይ እየወረደ፡፡

«እወድሻለሁ እማ!» አለችና ሒዎንም እንባዋን ከዓይኗ ላይ ትጠራርግ ጀመር፡፡ ለአፍታ ያህል በመሀላቸው ፀጥታ ሰፈነ፡፡

«ግን እሙዬ!» ሲሉ እንደገና ጠሯት፡፡

«አቤት እማ!»

«እንደው ለዚያ ለልጅ ደብዳቤ ጥፈሽለት ታውቂያለሽ?» ሲሉ ጠየቋት ወደ ዛሬው ዋና ጉዳያቸው ጠጋ ጠጋ ለማለት ፈልገው፡፡

«ለማ? ለእስቻለው?»

«ሆ»

«የት ብዬ እማ! አድራሻውን ባውቅማ ኖሮ ደብዳቤ ከመጻፍ ይልቅ...» ብላ ንግግሯን ቆም ስታደርግ እናቷ ቀጠሉ፡፡

«አዎ የኔ ልጅ! ሀሳብሽ ገብቶኛል፡፡ እንኳን አንቺ እኔ ራሴ ብርር.....ር! ብዬ ሄጄ የሆነውን ነገር እጠይቀው ነበር፡፡ ግን ምን ዋጋ አለው፣ የሄደበት አገር አጉል አጉል ሆነ፣ ምን ማድረግ እችላለሁ የኔ ልጅ!?» እሷት በሀሳብ ከጎኗ መሆናቸውን ለማረጋገጥ፡፡

«ኤርትራ ትሄጂ ነበር እማ?»

«ለምን አልሄድ እሙዬ! ለምን አልለፋ! ለምን አልንከራተት! እኔ እኮ ነገሩ ሁሉ ገብቶኛል፡፡ ሁሉን ነገር በእኛ ወርቆች ዓይን አይደል ያየሁት!» እሱ ታሪኩን ሲነግረኝ መርዕድን በማስታወስ፡፡ ቀጠሉና፡ «ያየሁት የልጁ ወተግራፍስ ቢሆን የሚረሳኝ ሆኖ ነው!! ባልወልደውም ልጄ ይመስለኛል፡፡ እንደ ወሰላ የረጋ መሆኑን አውቀዋለሁ፡፡» እሷትና እንባቸውን ከዓይናቸው ላይ ጥርግ አረጉት፡፡

በዚህ ጊዜ ሒዎን ያ ሸዋዬ ለአባትና ለእናቷ የጻፈችባት ደብዳቤ ትዝ አላት፡፡ በዚያ ምክንያት በእሷም ሆነ በእስቻለው ላይ አድሮ የነበረ ሲጋት ታወሳትና ... አለች በሆዷ፡፡ «ምነው ይኸን የእናቴን ሀሳብ አውቀኸው ቢሆን አስቻ! እንዲያ እየተጨነክኮ ሳስጨንቅህ! እንዲያ እያለቀስክ ሳስለቅስህ! ያን ያህል ስትጨነቅና ስትጠበብ ኖረህ ባሬ እናቴ ለአንተ ያላትን እምነትና ግምት አውቀኸው ቢሆን ኖሮ ምንኛ ደስ ባለህ ነበር? የቆሰለ መንፈስህ እንዴት በሻረልህ ነበር? ግን ምን ዋጋ አለው? ያ ሁሉ ሲሆን ቆየና የዛሬው ዕድልህ እንዲህ ሆኖ ቀረ አስቹ? የኔ ሆድ ምን ላርግህ! የኔ ፍቅር እንዴት ልሁንልህ!፣ በማለት ውስጥ ውስጧን ስታስብና ስትብሰለሰል ቆየችና ድንገት ለቅሶ ፈንቅሏት «እህህህ...» በማለት ተንሰፈሰፈች፡፡

«አንቺ እሙዬ!» አሉና እናቷ ድንግጥ ብለው ከመቀመጫቸው በመነሳት ወደ እሷ ሮጡ፡፡

«እማ ተይኝ!» አለች ሒዎን ፊቷን በጭኖቿ ላይ ድፍት አድርጋ እየተንሰቀሰቀች፡፡

«እባክሽ እሙዬ እባክሽ! የኔ ልጅ እባክሽ፣ ኧረ እንደው እባክሽ?» በማለት አንገቷን እቅፍ አድርገው እሳቸውም እያለቀሱ ይለምኗት ጀመር፡፡

ሒዎን ግን እሺ አላለችም፡፡ «እንቺ የማታውቂው ብዙ ነገር በሆዴ አለ እኮ እማ» አለች አሁንም እያለቀሰች፡፡ በዚያው ቀጠለችና «እስቻለው እኮ እብሮኝ የኖረው እያለቀሰ ነው እማ! ትቶኝም የሄደው እያዘነ ነው እማ! እስቻለው እኮ እኔን ሲል ያላየው መከራ የለም እማዬ! ያልቀመሰው አበሳ የለም እኮ! ወደ ኤርትራ እንዲሄድም ያደረኩት እኔ እራሴ ነኝ እማ! በዚያ ላይ የሄደበት አገር ጦርነት ነው፡፡ የዋይታና የኡኡታ ምድር ነው፡፡ እስቻለው እኮ የሚታየኝ በዚህ ሁሉ የሰው ልጅ አበሳና መከራ ውስጥ ሆኖ ነው፡፡ እስቻለው ሁልጊዜ ሲደማ ይታየኛል፡፡ ሁልጊዜ ሲቆስል ይሰማኛል፡፡ አንዳንዴማ ሞቶ ሬሳው በአውሬ ሲጎተት ይታየኛል፡፡ ይሄ መከራው ሁሉ ከአገዛ-ልቦናዬ ውስጥ አልጠፋ አለ እማ! ታዲያ እንዴት ላድርግ እማ? እንዴት ልሁነው እማ? እንዴትስ አይጨንቀኝ? እንዴትስ አይጠበኝ እማዬ!» አለችና አሁንም «እህህህ...» በማለት በለቅሶ ተንሰፈሰፈች፡፡

«እሱን ማሪያም ትጠብቀዋለች የኔ ልጅ! እሙዬ እባክሽ አታልቅሺብኝ! እባክሽ በአጠባሁሽ ጡት! እሙዬ አሁን ዝም በይ! በቃ ተይው የኔ ልጅ!» በማለት እናቷ እየተርገበገቡ ለመኗት፡፡

ሒዎን ግን ለቅሶዋ ሊበርድ እንባዋ ሊቆም አልቻለም፣ አሁንም እያለቀሰች «አት-አበባ እኮ፣ አት-አበባ እኮ....» ብላ ልትቀጥል ስትል ነገሩን ተወት አደረገችው፡፡ እንደበተ ቁጥቧ ሒዎን የቱንም ያህል ያስከፋቻት ቢሆን ሸዋዬን

በእናቷ ፊት መውቀስ አልፈለገችም፡፡ ብቻ አንጀቷ እስከሚንሰፈሰፍ ድረስ አሁንም በለቅሶ ተንሰቀሰቀች፡፡

እናቷ ግን ገብቷቸዋል፡፡ «አሷን ተያት እሙዬ! ያቺን አረመኔ ተያት የኔ ልዩ! ያችን ጨካኝ ተያት እሙ! እኔ ገብቶኝ የለ! ተረድቼው የለ! እባክሽ የኔ ልጅ ማልቀሱ አይጠቅምም፡፡ እባክሽ ዝም በይልኝ!!» ሲሉ ተማፀኗት እሳቸውም እያለቀሱ፡፡

«ኡ እሺ እማ፣ ዝ-ዝም እላለሁ፤ ቁጭ በይ!» አለቻቸው ድምጿ በሲቃ እየተቆራረጠና በእንባ የራስ ፊቷን እየጠራረገች፡፡

የሒዋን እናት እያለቀሱ አጠገቧ ቁጭ አሉና ዓይን ዓይኗን ያዩት ጀመር፡፡ ከትንሽ ቆይታ በኋላ ሒዋን በረድ እያለች መጣች፡፡ ለእፍታ ያህል ፀጥታ ሰፈነ፡፡ ግን ደግሞ ሒዋን ሀሳብ ውስጥ ገባች፡፡ ያን የሰሜን ኢትዮጵያ ክፍል በሀሳብ ትዳስሰው ጀመር፡፡ ወደዚያ ለመሄድ እንዲታሰብ እንኳ እንቅፋት የሆናትን ስለ አካባቢው ያላትን ግንዛቤ ሁሉ ታሰላስለው ጀመር፡፡

አዎ፣ ያ ሰሜን ኢትዮጵያ፣ የጥንት ስልጣኔ መነሻ፣ የውጭ ወራሪዎች መግቢያና መውጫ! በየዘመናቱ አንገታቸውን ብቅ እያረጉ ሲሰልሉት የኖረና እያወደሙም ቢሆን የወደሙበት የዘመናት የጦር አውድማ! ያ ሰሜን ኢትዮጵያ፣ የውጭ ወራሪዎች በፈጠሩት መዘዝ ወንድም ከወንድሙ እየተጋጨ 'አንተም ተው አንተም ተው' የሚል ጠፍቶ የእርስ በእርስ መጨራረሻ ሆኖ የቀረ የደም መሬት! ያ ሰሜን ኢትዮጵያ፣ ወንድ ልጇን ያላስገበረች ኢትዮጵያዊት እናት የለችምና የወላድ እርግማን የደረሰበት ይመስል ቦምብና መትረዬስ እየሰበሰበው የደጋ በረሃ ሲሆን የተቃረበ ምድር! ያ ሰሜን ኢትዮጵያ፣ ደም እንደ ውሃ እየወረደበት፣ አጥንት እየተከሰከሰበት፣ የሰው ልጅ አስከሬን በአውሬ እየተጎተተበት፣ የዋይታና ኡኡታ ጩኸት እያደነቆረው እራሱም ሲያለቅስ የሚኖር ያልታደለ ቦታ! ገና የወደፊት ዕጣ ፋንታው እንኳ በውል ያልታወቀ የሀገር ክፋይ!

ታዲያ በሒዋን አቅም እንዴት ይደፈር? ኩቶ በየት አድርጋ፣ እንዴት ብላ የአሰቻለውን ዱካ ለማነፍነፍ ትሂድ? ዙሪያው በእሳት የታጠረ ሲኦል፡፡ ገና ስታስበው ወላፈኑ ይገርፋታል፡፡ ገና ትዝ ሲላት ነበልባሉ ያቃጥላታል፡፡ አሰቻለውን በዚህ የመከራ ቦታ ላይ በሀሳብ ስታየው ትጨነቃለች፡፡ ትጠበባለች፡፡ እንባዋ ብቻ ሲረግፍ ይኖራል፡፡

ከቀኑ ከአሥር ሠዓት አለፍ እያለ ነው፡፡ ቡናው ሲያከትም ትንሽ ሲቀረው ሒዋንም ስትጽፍ የቆየችውን ወረቀት እጥፍ አድርጋ በማስደገፊያዋ ደብተር ውስጥ ከተተች፡፡ እናቷም ልብ ብለው ተመለከቷትና ብድግ ብለው ወደ ቤት አመሩ፡፡ የሒዋን ታናሽ ወንድም የሆነው አስራት ተስፋዬ መደብ ላይ ቁጭ ብሎ ሲያጠና አገኙትና «አስራቴ!» ሲሉም በሹክሹክታ ዓይነት ጠሩት፡፡

«አቤት!» አላቸው አስራት ቀና ብሎ እየተመለከታቸው፡፡ ወደ አሥራ ስድስት ዓመት የሚጠጋው ጠየም ያለ ለግላጋ ወጣት ነው፡፡

«እስቲ 'ሆዴን አሞኛል' ብለህ መደቡ ላይ ተኛ፡፡» አሉት፡፡

«ለምን?» አላቸው አስራት ደንገጥ እያለ፡፡

«እየሆን» አሉት ወደ ጆሮው ጠጋ በማለት «እሙዬን 'ራሴን አሞኛልና መድኃኒት ግዢልኝ' ብዬ ወደ ከተማ ልልካት ነው፡፡ እሷ ከሄደች በኋላ የምነግርህ ነገር አለኝ፡፡ በል ቶሎ ተኛ፡፡» አሉት እያቻኮሉ፡፡

«ምንድነው እሱ?» አላቸው አስራት ዓይኑን ዓይናቸው ላይ ትክል አድርጎ፡፡

«በኋላ እነግርሀ የለም! አሁን ተኛ፡፡» አሉትና ወደ ጓዳ ገባ ብለው ጋቢ አምጥተው ሰጡት፡፡ «በል ቶሎ በል!» ካሉ በኋላ አሁንም ወደ ጆሮው ጠጋ በማለት «እሙዬ 'ምን ሆንክ' ብላ ብትጠይቅህ 'ድንገት ቁርጠት ተነሳብኝ' ብለህ ትልስልስ እያልክ ንገራት፡፡» አሉት ጣደፍ ጣደፍ እያሉ፡፡

አስራት ግራ እየገባው ጋቢውን ለብሶ ቁጭ ብሎበት በነበረ መደብ ላይ ጥቅልል ብሎ ተኛ፡፡ በጆሮው ግን የእናቱን እንቅስቃሴ በጥንቃቄ ያዳምጣል፡፡

የሒዋን እናት የአስራትን አስተኛኘት ከአረጋገጡ በኋላ ወደ ጓሮ ዞሩ፡፡ ልክ እጓሮ ታመሙ ሁሉ ሰውነታቸውን ድክምክም፣ ዓይናቸውን ቅዝዝ! ፊታቸውንም ጭምድድ አድርገው ከሒዋን አጠገብ ደረሱና በቀስታ እየተቀመጡ «እንዴት ይሻለኛል እሙዬ፣ ስላለተስከበት ነው መሰለኝ ይኸ ራሴ ተነሳና ይፈልጠኝ ጀመር፡፡ ያንን ኪኒና የምትሉትን ነገር ግዢልኝ ልለው ወደ ቤት ብገባ አስራቴ ደሞ ሆዱን አመመኝ ብሎ ተኝቶ አገኘሁት፡፡» አሉና «ኧረ እዲያ!» በማለት ብስጭትና ምሬታቸውን ለመግለጽ ሞከሩ፡፡

«አመመሽ እማ?» አለቻቸው ሒዋን ሁኔታቸውን ሰለል እያደረገች፡፡

«ብታይ ጠሩን ይዞ! ሸቀሸቀኝ፡፡» አሏት ራሳቸውን በሁለት እጃቸው ይዘው ወደ መሬት በማቀንበስ፡፡

«ምን ዓይነት ኪኒን ይሆን?»

«ይኸ እምብር ነው ምንትስ የምትሉት!»

«አስፕሪን ይሆናል፡፡»

«ይሆናላ! እኔ አላቀው፡፡ አንዳንዴ ሲያመኝ ይኸው አስራቴ ነበር የሚገዛልኝ፡፡ እንግዲህ አባታችሁ እስከሚመጣ ልጠብቅና የሚያውቀው ተሆነ ይገዛልኛላ፡፡» አሏት በግማሽ ቀልባቸው ወደ ሒዋን ወረቀቶች ዓየት እያረጉ፡፡

«እኔ እገዛልሻለሁ እማ!» አለቻቸው ሒዋን፡፡

«እየ.... ልጄ! መንገዱ ይርቅሻላ፡፡ የኛ ሰፈር ደሞ ገጠር አይሉት ከተማ አትል ነው፡፡ ከሱቅ እስኪደርሱ ድረስ ያለው መንገድ መች ቀላል ነውና፡፡»

«ግድየለም እማ! መግገሩውን ስጪኝ፡፡» አለቻቸው፡፡

«ተበረታሽ ደግ የኔ ልጄ!» ብለው ከተቀመጡበት ተነሱና «ነይ ከቤት እሰጥሻለሁ፡፡» እያሉ ወደ ቤት አመሩ፡፡ አስራት ጥቅልል ብሎ እንደተኛ ነው፡፡ የእናቱንና የሒዋንን ወደ ቤት መግባት አውቆ የሚደረገውን ለመከታተል ጆሮውን አቁሞ ሳለ ሒዋን ተናገረችው፡፡

«አመመህ እንዴ አስራት!»

«ኧረ ቁርጠት ሊገለኝ ነው፡፡» አላት ገልበጥበጥ እያለ፡፡

የሒዋን እናት ፈጥነው ወደ ጓዳ ገብተዋል፡፡ «ቆይ ተኙ መድሃኒት እንገዛልሀለን፡፡ እስከዚያው ቻለው፡፡» እያሉ ይዘው የወጡትን ገንዘብ ለሒዋን ሰጧት፡፡ ተቀብላቸው ከቤት ስትወጣ እስከ ውጭ ድረስ ሸኟት፡፡

ጥቂት ርምጃዎች እስክትራመድ ድረስ በዓይናቸው ሲከታተሏት ከቆዩ በኋላ ፊታቸውን ወደ ግቢው በር ምልስ አድርገው እስከ ቁርጭምጭሚታቸው ይደርስ

የገበረ የአበሻ ቀሚሳቸውን እስከ ጉልበታቸው ድረስ ሰቀሰቁና ወደ ቤት ሳይገቡ ወደ ጓሮ በሚወስደው መተላለፊያ መንገድ ሮጡ። ከቦታው ሲደርሱ የሒዎንን የወረቀት አቀማመጥ ልብ ብለው ተመለከቱ፣ ወረቀቷን ሲመልሱ አቀማመጡ እንዳይጠፋባቸው ተጠንቀቁ። ከዚያም የጻፈችባትን ወረቀት ከማስደገፊያዋ ደብተር ውስጥ ቀስ ብለው መዝዘው አጠፏትና እሁንም በሩጫ ወደ ቤት ገሰገሱ።

«እስቲ ተነስ እስራቴ!» አሉት ቶሎ ቶሎ እየተነፈሱ።

እስራት ከተሸፈነበት ገለጥ ብሎ ከፊትለፊቱ የቆሙ እናቱንና በእጃቸው የያዟትን ወረቀት እየተመለከተ፦ «ምንድነው?» ሲል ጠየቃቸው።

«ቶሎ ተነስ! እሙዬ የጣፈችው ወረቀት ነው። ሳትመጣብን አንብበውና ከአስቀመጠችበት ቦታ ልመልስ።» አሉት በትንሹ እኒጋገር።

እስራት ከተኛበት ቀና ብሎ ወረቀቱን ተቀበለና አየት ሲያደርግ ግጥም ተደርድሮበታል። ከግጥሙ ጫርና ጫር ደግሞ የተለያዩ ቃላት ተሞንጫጭረውበታል። 'እስቹ! ሆዴ፣ የኔ ምስኪን...ጠዘተ የሚሉ። ወደ ዋናው ግጥም ከመግባቱ በፊት እነዚህን ቃላት አየት አየት ሲያደርግ ለካ ለሒዎን እናት ዘግይቶባቸው ኖሯል።

«እንብበው እንጂ! ኢቃተህ እንዴ?» ሲሉ ጮሁበት። እስራት ግጥሞቹን ማንበብ ጀመረ። እናቱም፣ ጆሮአቸውን አቁመው ያዳምጡ ጀመር።

«የኔ ሆድ አስቻለው አንተ የኔ ከርታታ!
ሳመንክው ለመሞት የማታመነታ።
አመጣለሁ ብለህ ሂደህ እንደ ዋዛ፣
አንተም በዚያው ቀረህ የኔም እሳር በዛ።
በእርግጥ ባትኖር እንጂ ፍጹም በህይወት፣
አይጨክንም ነበር ለስቹ የአንተ አንጀት።

የበላህን አውሬ ምነው ባገኘሁት፣
በውስጡ ባገኝህ እኔም በበላሁት።
ደምህን ከደሜ አጥንቱን ከአጥንትህ፣
አገናኝው ነበር ነፍስ እንዲዘራብህ።
የባምከው ከገሬሬ ደርቋል እንደ ከብት፣
ሕሀል ውሃ ጠልቶ አንተ እሊለህበት።

እንደው ሂጂ ሂጂ ብሪሪ ይለኛል፣
እልም ያለው ገደል ባህሩ ይታየኛል።
ዛሬ ነገ እሊሉ እንጂ ልብ እየዋለለ፣
ሰሚቱስ ይሙሀል በርቹ በርቹ እያለ።
ይጎትተኛል የናፍቆት ሰቀቀን፣
አንተን ካላገኘሁ አይቀርም እንድ ቀን።»

«ኧ! ኧ! እስቲ እስቲ ድገመው!» አሉ የሒዎን እናት አሁንም ጆሮአቸውን ወደ እስራት ጣል አድርገው። ዓይናቸው ፍጥጥ ማለት ጀምሯል።

እስራት ቀስ ረጋ ብሎ ደግሞ አነበበላቸው። አንብቦ ከጨረሰም በኋላ እናቱ የሚሆኑትን ለማየት ቀና ብሎ በስጋት ዓይን ያያቸው ጀመር።

የሒዎን እናት ድንገት ጥርሳቸውን ግጥጥ፣ ፊታቸውን ኩፍት እያረጉና እጃቸውን እያገሩ «እከከከከ ...! እከከከከ...! እከከከከ...!" አሉ አንዳች የህመም ስሜት ውስጣቸው ገብቶ በረበራቸውና። ቀጠሉ እሁንም እጆቻቸውን ወደ ላይ ሽፍነው በወገባቸው ላይ በማሳረፍ ቀሚሳቸው በአየር ተንሳፎ እስኪታይ ድረስ በቆመበት ላይ ወደ ግራ ወደ ቀኝ እየተወዛወዙ «እንቱ!» አሉ የጉሮሯቸው በረዘመ ድምጽ። ሟቿን የእስቻለውን እናት መጥራታቸው ነው። «የበጠት ጥዋ የለም? የካደሟት አድባር የለችም? የሳሙት ቤተክሲያን የለም? እረ እንድ በሉኝ! እረ በጡቃቢያ ድረሱልኝ! እረ ልጆቻ ልጄን በላብኝ! እረ እምነቶነብኝ! እረ ምን አባቴን ልሁነው! እያሉ ዓይንና አፍንጫቸውን ወጠሉቸው እየጠራረጉ ልክ ሞታ ቀብረዋት ሀዘናቸው ገና እንዳልወጣላቸው አይነት «ወይኔ ልጄን! ወይኔ ልጄን! እሙዬ ምንሳርግሽ? እንደው ምን ልሁንልሽ? ልጄ ልጄ! ልጄ ልጄ! ልጄ ልጄ!" አሉ በተከታታይ።

«ምንው እማዬ! ምን ሆንሽ?» አላቸው እስራት ደንግጦ።

«በቃ እኮ እንግዲህ እኔም ልጄ በህይወት እሰች ብዬ ተስፋ አላደርግም። አንተም እሁት አለችኝ ብለህ አታስብ! ልጄ ማምለጧ ነው። እሙዬ ተእንግዲህ ሰው አልሆንችም! በቃ በቃ! በቃ በቃ! እህህህ

«እረ ምንም አትሆን እማ!»

«አዲያ ወዲያ እሥራቴ! በቃ ቁርጡን ነገረችን እኮ! በቃ ተናዘዘች እኮ! እሙዬ ገደል መግባቷ ነው እኮ! እህህህህ...»

«እንጠብቃታለና!»

«እየየ... ጥበቃ! እየየ... ጥበቃ! ዋልኝ! የእሷ ነገር ተእንግዲህ አበቃ! እኔም አብሬ ወደ ገደል ነው! እኔም ከእሷ ጋር ወደ ባህር ነው! እህህህህ...» እስራት አጆቹን ከእናቱ ትከሻ ላይ አውርዶ ወደ መሬት በማጎንበስ አንገቱን ጠረግ ሲያደርግ እናቱም በቤቱ መሀል ወለል ላይ ቆመው እየየ ሲሉ ድንገት ከወደ ውጭ በር በሩል ድምጽ ሰሙ። የሒዎን እናት ያቺን ወረቀት ከቦታዋ ሳይመልሱላት ሒዎን የመጣች መስሏቸው በመደንገጥ ፈጥነው በበር በኩል አንገታቸውን መዘዝ አድርገው ሲያዩ ባለቤታቸው አቶ ተስፋዬ ሆነው አገኟቸው። ከብቶቻቸውን መስክ ይዘው ውለው ወደ ግቢ እያስገቧቸው ነው።

«አንተ ተስፋዬ!» ሲሉ የሒዎን እናት ከቤት በር ላይ ሆነው ግቢ ውስጥ ገብተው ያሉትን ባለቤታቸውን ተጣሩ።

«ወይ» አሏቸው አቶ ተስፋዬ ድንገጥ ብለው።

«ቶሎ ገባና ስልጅህ መላ ትፈልግ እንደሆን ፈልግ! እስበለዚያ ተእንግዲህ እንኳን እሷን እኔን አታገኘም!»

«የት ልትሄዱ አሰባችሁ?» አሉ አቶ ተስፋዬ ግራ ገባ እያላቸው።

«በቃ የትም! ሲያሻን ወደ ገደል፣ እሰያም ወደ ባህር። ቀልድ መስሎህ እንዳትቀልድ!» አሉና የሒዎን እናት ፊታቸውን ወደ ቤት ምልስ አደረጉ።

የሒዎን አባት በሁኔታው ተደናግጠው ፈጠን ብለው ወደ ቤት በመግባት ዙሪያውን በዓይናቸው ሲሰልሉ ሒዎንን አጧት። «ሒዎኔ የታለች?» ሲሉ ጠየቁ።

የሒዎን እናት ሒዎን የትና እንዴት እንደሄደች ከገለጹላቸው በኋላ በችኮላ እኒጋገር «ቁጭ በልና ጉድህን ልንገርህ!» አሏቸው።

የሒዎን አባት መደብ ላይ ቁጭ አሉና አፋቸውን ከፍተው ባለቤታቸው የሚነግሯቸውን ለመስማት በጉጉት ይጠብቁ ጀመር:: የሒዎን እናት ግጥሙ ሳለት ተስፋዬ እንዲነበቡላቸው አደረጉ:: ተነበቡላቸው::

«እንዴት እንዴት?» አሉና የሒዎን አባትም ንባቡ እንዲደገምላቸው ጠየቁ:: ተደገመላቸው::

«ምን ይሻላል ትላለህ ታዲያ?» አሏቸው የሒዎን እናት::

የሒዎን አባት ፍዝዝ አሉ:: አሰቡ አሰቡና «እንደው በእንቺ በኩል ምን ይታይሽ ይሆን ስንዴ? መላው የጠፋው ነገር ሆነ እኮ!» አሏቸው ጉንጫቸውን በመዳፋቸው ደገፈው ዘመም ብለው በመቆዘም::

«መላ አጣሁ! ግራ ገባኝ! የት ልግባው? እረ የት ልድረሰው!» አሉና የሒዎን እናት አሁንም ምርር ብለው አለቀሱ:: የሒዎን አባት እንደ ባለቤታቸው ባያለቅሱም ነገር ግን ጭንቅ አላቸው:: የልጃቸው ነገር አሳሰባቸው:: ችግሩን ያውቁታል፤ ያው የእስቻለው ጉዳይ ነው:: መንሻው ደግሞ የሆነውን ነገር ባለማወቁ ነው:: ይህን ሁሉ ሲያስቡ ቆዩና ቀደም ሲል እልፎ እልፎ ይታያቸው የነበረውን መላ በእናቷ ፊት መተንፈስ ፈለጉና፡-

«ስንዴ!» ሲሉ ጠሯቸው ባለቤታቸውን:: የሒዎን እናት ምድጃ አጠገብ ኩርምት ብለው ተቀምጠዋል::

«ወይ»

«ታልሆነ እንግዲህ መቸስ ቁርጥ አወቅ አትደንግጥ ይባል የለ! በአንድ ፊት ሞቷል ብለን እንንገራትና—» ብለው ሳይጨርሱ የሒዎን እናት ከተቀመጡበት ድንገት ብድግ እያሉ፡-

«ሆሆይ! እንዴት እንዴት በል! አበድክ እንዴ አንተ ሰው!» በማለት በአቶ ተስፋዬ ላይ አፈጠጡ:: «ዛሬውኑ ብርር ብላ እንድትጠፋልህ ፈልገሃላ!?»

«ግራ ገብቶኝ ነው እኮ ስንዴ!» አሉ አቶ ተስፋዬ:: እንደማፈርም አሉና ጎንበስ ብለው ነጩ በዛ ያለ ገብስማ ጺማቸውን ጎተት ጎተት ያደርጉ ጀመር::

«አንተን ግራ ስለገባህ እሙዬ አብዳ ትረፍ!?»

«እኔ እኮ ቁርጡን አውቃ ማረፏ__» ብለው ሳይጨርሱ የሒዎን እናት አሁንም አቋረጧቸው::

«ኧረ በወላዲቱ ይዝገሃለሁ!»

«እንቺንም እኔንም ባይልልን ነው እንጂ እሷስ ቢሆን ይኸን ያህል እየሆነች በሰው አፍ ልጃቸው ወንድ ወደዳ ባንባል—» ብለው አቶ ተስፋዬ ሳይጨርሱ የሒዎን እናት አሁንም ጮሁባቸው::

«ኧረ በሚካኤል! በምትጠጣው ጥዋ! ምናለ ልጅህን እንደ ባዳ ባታማት?» አሏቸው::

«ማማቴ እኮ አይደለም ስንዴ፣ ሰው እያውቅልንም ብየ ነው እንጂ እውነተኛውንማ ነገር አንቺ ነግረሽኝ የለም!» አሉና በዘንጋቸው መሬቱን መታ መታ ያደርጉት ጀመር:: አቶ ተስፋዬ ቀይ ናቸው:: ፊታቸው አነስ ብሎ ክብብ ያለ:: የታችኛው ፂማቸው ረዘም ያለና ገብስማ ነው:: አረንጓዴ ኮትና ሱሪ ለብሰዋል::ነጭ ጋቢ ደርበው ራሳቸው ላይ ነጭ ሻሽ ጠምጥመዋል:: ጥቁር ኮንጎ ጫማ ያለ ካልሲ አድርገዋል:: ጠንከር ያሉ የስልሳ ዓመት አዛውንት ይመስላሉ::

«ያልትስ የኔን ሀሳብ ስማኝ»

«እስቲ ምን? ከሆነማ ያንቺ ይበልጥ የለ::» አሉ የሒዎን አባት ጓጓ እያሉ::

«ለሽምዬ ደብዳቤ እንጣፍ::»

«ምን ብለን?»

«እሙዬን መጥታ ትውሰዳት::»

«እየ...ዬ! ያቺ ከይሲ ልጧ ይራራል ብለሽ ነው? ወስዳስ ሰላም ትሰጣታለች ብለሽ ገመትሽ?» አሏቸው የሒዎን አባት ቅር እያላቸው::

«ምን አስቤ መሰለህ አቶ ተስፋዬ?»

«ምን አስበሽ ይሆን?»

«ሽምዬ ለእሙዬ ትመቻቻለች ብዬ አይደለም:: ግን እሷን ሰበብ አድርገን እዚያ ነጋዴዎች ናቸው ብዬ ከነገርኩህ ልጆች ጋር ትቀላቀል ብየ ነው:: ተኛ እነሱ ይሸሏታል:: እነሱን ስታገኝ ትጥናናለች:: ሀሳብና ጭንቀቷ ከፊል ይልላት እንደሆን ብዬ ነው::»

«ከእህቷ የበለጠ ባዳ ይታመናል ብለሽ ነው?» አሉ ሒዎን አባት ፂማቸውን ጎተት እያረጉ ውጭ ውጭ በማየት::

«እማየ ያለችው ነገር ጥሩ ነው አባባ፤ ባይሆን እትአበባ እዚህ ድረስ እንድትመጣ ይደረግና እስታርቃችኋቸው ይዟት ትሂድ::» አለ አስራት ከእስከ አሁኑ የአባትና የእናቱ ምክክር ይኸኛው የተሻለ መሆኑን በማመን::

«ተሆነስ ሆኑና ደብዳቤውስ ቢጣፍ ማን ያደርስዋል? እሷ እንደሆነች ሰው ገደላ የሄደች ይመስል እኛንም ተወችን፤ ቀየውንም ጠላችው:: ባይሆን ስልክ ቢመታላት ይሻል እንደሆን እንጂ!» አሉ የሒዎን አባት አሁንም ውጭ ውጭ እያዩ::

«እንኳን ስልኩ ወረቀቱም የልብ አያደርስ:: ይልቅስ መሳፈሪያ ፈልጉልኝና እኔ ሄጄ ሁሉን ነገር ላስረዳትና ይዣት ልምጣ?» አለ አስራት አባትና እናቱን ተራ በተራ እየተመለከተ::

«እንዴት ታገኛታለህ አስራቴ!» አሉ የሒዎን እናት በሊያውም ሀሳቡን የደገፉት መሆኑን ለባለቤታቸው ለመግለፅ::

«ኢዲያ!» አለና አስራት እጁንም እያወናጨፈ «እንኳን እኔ አንቺስ አግኝተሻት የለ?» አላቸው::

«በያ ላይ ደግሞ ትምህርትህም ይቋረጣል ብዬ ነዋ!»

«ቅዳሜና እሁድን አስደግፌ ብሄድና ለአንድና ለሁለት ቀን ከትምህርት ብቀር ምን ያህል ይጎዳኛል?»

«የአስራቴ አሳብ ጥሩ ነው አቶ ተስፋዬ! ባይሆን ተጨማሪ እንዲሆን የኔና የአንተም ቃል ይጣፍና ይዞላት ይሂድ::» አሉ የሒዎን እናት::

«ይሁን ቃላችሁ ይሁን! በያ ላይ ፈጣሪ አምላክ ብላቱን ያምጣልን:: መቸስ ምን ይደረጋል?::» ብለው አቶ ተስፋዬ ከብቶቻቸውን ወደ በረት ሊያስገቡ ወደ ውጭ ወጣ አሉ:: በዚህ ጊዜ የሒዎን እናት አንድ ነገር ትዝ አላቸውና በድንጋጤ ብድግ አሉ:: «አንተ አስራቴ!» ሲሉ ጠሩት እየተጣደፉ::

«አቤት»

«የእሙዬን ወረቀት አምጣ! አደራህን! የተነካካት መስሏት ልጄ እንዳይከፋት ልክ እሷ አድርጋው እንደነበረ አድርገህ አጠፈው::» አሉት

አስራት ጠረቀቷን ቀድሞ በታጠፈችበት ሁኔታ አራት ቦታ አጣጥፎ ለጣቸውና ወደ ጓሮ ይዘው በመሄድ እንደነበረ አድርገው አስቀመጡላት።

ሸዋዬ በህዳር ወር የመጨረሻ ሳምንት ላይ ቆማ የመጀመሪያው መንፈቀ ትምህርት አልቆ ለአጭር ጊዜ ዕረፍት ትምህርት ቤት የሚዘጋበትን የጥርን ወር መጨረሻ በናፍቆት ትጠባበቃለች። ክብረ መንግስት የምትደርስበት ቀን ሳይቀር ተወስኗል። ዕቅዷ ከሔዋን ወይም ከወላጆቿ ተቃውሞ ቢገጥመው ማሳመኛ ይሆናል ብላ የምታስበውን እያዘጋጀች ነው። ዘዴና ብልሀት ሁሉ በልቧ ይጠነጠናል።

'ለሆዳም በሬ ጭድ ያገለታል' እንዲሉ ወንድሟ አስራት ተስፋዬ በአላሰበችው ቀንና ሰዓት ከቤቷ ከች ብሎ ያደረሳት ብሥራት ግን ስጋትና ፍርሀቷን ሁሉ ከልቧ ውስጥ እንደ ዕድፍ አጠበው። 'ሔዋን የልብ ህመምተኛ ሆናለች። በስሙ ላይ ክፉ ደግ አለና መጥተሽ እያት' ከማለት ውጭ ስለ ሔዋን ሁኔታ ምንም ዓይነት ፍንጭ ለሸዋዬ እንዳይሰጥ በተለይ በእናቱ አደራ የተባለው አስራት፣ የልጅ ነገር ሆኖበት አንዳንድ ነገሮችን ማፈንዳቱ አልቀረም። ሔዋን ዛፍ ስር ተተምጣ መዋል ማዘውተሯን! በሀሳብ እየተዋጠች ቤተሰቧንም ማሳሰቧንና በተለይ በህመሟ ምክንያት አገር ብትቀይር የተሻለ መሆኑ መታመኑን ሁሉ አልደበቃትም።

የሔዋን አገር መቀየር አስፈላጊነት የታመነበት ስለመሆኑ መስማቷ ሸዋዬን ከምንም ነገር በላይ አስፈነጠዛት። ሔዋን አገር መቀየር ካለባት ቀላሉ ከክብረ መንግስት ወደ ዲላ ነው። ይህ ደግሞ በቤተሰቦቿ ዘንድ ተፈጥሮ ይሆናል ብላ ከምታስበው ቅሬታ ነጻ የምትሆንበት አጋጣሚን ይፈጥራልና ወቅትና ጊዜ ያለ ሽማግሌ ሊያስታርቃት በመቅረቡ አምላኳን አመሰገነች። ወደ ክብረ መንግስት ልትሄድ በልቧ ይዛው የነበረውን የጊዜ ቀጠሮ አሳጠረችው። ወንድሟ አስራት ተስፋዬ ከቤቷ በደረሰ በአራተኛው ቀን እንዲሆን አደረገችው። በመሀል ያሉት ሁለት ቀኖችም የዝግጅት ጊዜ ሆኑ።

ብሥራቱን ያካፈለቻቸው በድሉና ማንደፍሮ በእነዚህ ሁለት ቀናት አልተለዩአትም። ወደ ክብረ መንግስት አካሄዷን ሊያሳምሩ ሽርጉድ አሉ። አብረዋት እየዋሉ አብረዋት አመሹ። በየገበያው ቦታ አብረዋት ዞሩ። አዘጋጇት! አዘገጃጇት። ጠዋት ወደ ክብረ መንግስት ልትሄድ ሻንጣዋ የያዘውን ይዞ ማታውኑ ተቆለፈ። የማግስቷ ጀምበር ክብረ መንግስት የምታደርስ የልቧ መብራት ሆነች።

ልክ በዚያው ዕለት ምሽት ላይ ክብረ መንግስትም ሌላ ዝግጅት በመደረግ ላይ ነው። የሔዋን አባትና እናት ሔዋን ወደ ዲላ መሄድ ያለ መሄድ ፍላጎቷን ለማወቅ ሊያነጋግሯት በተመካከሩበት መሠረት ውይይቱ ተጀመረ።

«እሙዬ!» ሲሉ ጠሯት እናቷ ለስለስ ባለ አነጋገር።

«አቤት እማ!» አለቻቸው ሔዋን ከአጠገባቸው መደብ ላይ ጋደም ብላ ሳለች። አባቷ ደግሞ ከባለቤታቸው ፊት ለፊት ምድጃው አጠገብ ተቀምጠው እሳት ይሞቃሉ።

«እንደው ይቺ ልብሽ ያስቸገረችሽ ይኸን አገር ጠልታብሽ ይሆን? እማስበው ምን ይሆን ነገር በአሉናዬ አውጠንጥኘው ጀመር ልጄ?» አሏት ጉልበታቸውን በሁለት እጆቻቸው ደገፍ በማድረግ ዓይን ዓይኗን እየተመለከቱ።

«አየ እማ! ቢቸግርሽ!»

«ቸገረኝ ልጄ! በጣም ቸገረኝ።»

«የት ልሄድ ታዲያ እማ?»

«እውነትሽ ነው። መሄጃማ ይቸግራል የኔ ልጅ!...» ካሉ በኋላ የሔዋን እናት ወደ አቶ ተስፋዬ ዞር በማለት «እንደው ወደ ዲላ ትሂድ ይሆን፤ አቶ ተስፋዬ?» ሲሉ ጠየቋቸው።

«ተሆነማ ወደዚያው ነው፤ ኋላማ ወዴት ትሄዳለች? ከዚያ ሌላ አገር አታውቅ!» አሉ አቶ ተስፋዬ አንገታቸውን ወደ እሳቱ ደፋ አድርገው።

«ከማን ጋር ልኖር?» ስትል ሔዋን ጠየቀቻቸው።

«በኔ ልብማ ከነዚያ ከንታፈሁ ጋር ትንሽ ተጫዋውተሽ ትመለሺ እንደሆን ብዬ ነዋ!» አሉ እናቷ ለስለስ ባለ አነጋገር።

«እህቷስ አለች አይደል!» አሉ አቶ ተስፋዬ ወደ እሳቱ እንዳቀረቀሩ።

«እንደገና ከእት አበባ ጋር?» አለች ሔዋን ደንገጥ ብላ።

«አዎን ለሰበብ! ተዚያ በኋላ ደግሞ ከእነዚያ ልጆች ጋር አንዳንድ ጊዜ መጫወቱ ትንሽ ያፍታታሽና ልብሽም እየተወችሽ ትሄድ እንደሆን ብዬ እኮ ነው።» አሉ እናቷ የሔዋንን ቁጣ ለመመለስ ረጋ ብለው።

«ተይ እማ! እንዲህማ አይሆንም።»

«ቀለብሽን ተሆነ እኔ እችላለሁ ሔዋኔ! ከቶ የአንቺ ጤና ይመለስ እንጂ፤ ደሞ ላንቺ ያልሆነ አዱኒያ ምን ሊያደርግልኝ! ላም ተሆነችም ላም፤ በሬ ተሆነም በሬ ይሸጣል። አይዞሽ!» አሉ የሔዋን አባት በቆራጥነት።

«እናንተ የማታውቁት ሌላም ችግር አለ።» አለች ሔዋን።

«ብትነግሪን አይፈታም?» አሏት እናቷ። ግን ትዝ ያላቸው ነገር አለ፤ ያኔ ታፈሁ '... በማትፈልገው ሰው ልታስደፍራት' ያሉቸው ነገር። ፊታ ብላ ቢታወጣውና ሁኔታውን በግልጽ ቢረዱት ፈለጉ።

«እኔና እት-አባበ አብረን መኖር አንችልም።» አለች ሔዋን ነገሩን ደፈንፈን አድርጋ።

«እረ ተይ ሔዋኔ፤ በእትማማቾች መካከል ቂም ተያይዞ አይኖርም!» አሉ አባቷ አሻግረው መልከት እያሏት።

«ከበድኳችሁ እንዴ አባዬ?»

«ለአንቺ ብለን ነው እንጂ እሙዬ! ደሞ አንቺ ምን ትከብጃናለሽ የኔ ልጅ?» አሏት እናቷ በማሳዘን ዓይነት አነጋገር።

«እንግዲያው እዚሁ ብሆን ይሻለኛል።» አለችና ሔዋን በረጅሙ ተነፈሰች።

የሒዋን እናትና አባት ግራ ተጋቡ:: ልጃቸው ወደ ዲላ ለመሄድ ፈቃደኛ አለመሆኗ ገባቸው:: ከዚያ በኋላ ምንም ሳይነጋገሩ ጊዜው መሸ:: እንደ ተዳፈጡ ተኙ:: ሌሊቱ በሀሳብ ነጉዶ ቀንም በትካዜ አለቀ::

የደስታ ፈረስ ጋልባ ሰምሰማ ስትጋልብ የዋለችው ሸዋዬ ከቤተሰቦቿ ቤት የደረሰችው ከአመሻሹ አሥራ አንድ ሰዓት አካባቢ ነው:: በዚያ ሠዓት አባቷ ከብቶቻቸውን ይዘው ከመስክ እየተመለሱ ነው:: እናቷ ደግሞ ምናልባት ሒዋን ሸዋዬ ስትመጣ ሀሳቧን የቀየረች እንደሆን ብለው ለወደፊቱ ግንኙነት እንዲያመች የዘመድ ስልክ ቁጥር ሊያመጡ ወደ ከተማ ሄደው እየተመለሱ ገና በመንገድ ላይ ናቸው:: ሸዋዬና አባቷ በር ላይ ተገናኝተው በመሳሳም ናፍቆታቸውን አውጥተው እየተነጋገሩ ወደ ቤት ሲገቡ ሒዋን በጓሮ በር በኩል ወደ ቤት ስትገባ ዓይን ለዓይን ግጥምጥም አሉ::

«አማይዬ!» አለች ሒዋን ሸዋዬን ስታይ ደንግጣ:: የትናንት ማታው ወሬ መሰረቱ ምን እንደነበረ ልቧ ጠረጠረ::

«እህትሽ መጣች ሒዋኒ!» አሉ አባቷ ተደስተው::

«ጠፋሁባት ይሆን?» በማለት ሸዋዬም ሳት እያለች ወደ ቤት ገባችና በሒዋን ላይ ጥምጥም ብላ ሳመቻት::

«አንቺ!» አለቻት አጠገቧ ቆማ ከእግር እስከ ራሷ እየተመለከተቻት::

«አቤት!» አለች ሒዋን ወደ መሬት እንዳቀረቀረች::

«ቤቱ! እንዲህ ሆንሽ ቀረሽ?»

ሒዋን ሸዋዬ ምን እያለች እንደሆነ አልገባትም:: ጠቁራባት ይሁን ከስታባት! ብቻ ያየችባትን አካላዊ ለውጥ ገና ትነግራት እንደሆን እንጂ ለጊዜው አለየላትም::

ሸዋዬ እንደ መናደድ ዓይነት እጆቿን ጨብ ጨብ ጨብ እያረገች «ዋይ-ዋይ-ዋይ-ዋይ......» አለች ደጋግማ:: በአባታቸው ግብዣ ሁሉም በመደብ ላይ ተቀመጡ::

«ሒዋኒ ክብረ መንግስት እንዳላደገችበት ሁሉ ዛሬ ዛሬ አልስማማት ብሏል የሸዋ!» አሉ የሒዋን አባት የሸዋዬ ቁጭት መነሻው የሒዋን መጎሳቆል መስሏቸው::

«ለመሆኑ ያምሻል?» ስትል ሸዋዬ ሒዋንን ጠየቀቻት::

«አልፎ አልፎ ልቤን ያመኛል::»

«ተመርምረሻል?»

«አዎ! መድሃኒትም እየወሰድኩ ነው::»

«ኡዲያ!» አለች ሸዋዬ በመመናጨቅ ዓይነት:: «ወጉ እንዳይቀር ነው እንጂ ቀድሞ ክብረ መንግስት ምን ሀኪም አለና!» አለች ውጭ ውጭ እያየች::

«እንደው ደህና ሀኪም የት ይገኝ ይሆን የሸዋ?» አሉ የሒዋን አባት በዓይንና በቀልባቸው ሒዋንን ሰለል እያደረጉ::

«ዘገያችሁ! በጣም ዘገያችሁ!» አለችና ሸዋዬ ከተቀመጠችበት ብድግ እያለች «ሰው የገዛ ልጁን አፍኖ ይገድላል እንዴ?» ብላ በጓሮ በር በኩል ወጣች::

[illegible] የጓደኞቿን ጋር ለመገናኘት ነበር:: ውስጥ ውስጡን ስትዘዋወር አስራት [illegible] የሒዋንን የዛፍ ሥር መጥያ መደብ አይታ በጣም ተገረመች::

የሒዋን እናት ከቤታቸው ሲገቡ ዓይናቸው በመጀመሪያ ያረፈው [illegible] የሸዋዬ ተሽከርካሪ ሻንጣ ላይ ነው:: ዋናው መልኩ ጥቁር ሆኖ [illegible] ብረት [illegible] ያበራል:: «ማ መጣ?» አሉ ገና በር ላይ ብቅ ብለው ፊት ለፊት መደብ ላይ ያን የልብስ ሻንጣ ሲያዩት::

«የሸዋ መጣች እኮ ስንዴ!» አሏቸው የሒዋን አባት እሳቸውም ያንኑ ሻንጣ እንደገና እየተመለከቱ:: የሒዋን እናት ወደ ቤት ገባ ብለው በግራ በኩል [illegible] አስራት ቁጭ ብሎ ፈገግ እያለ ያያቸዋል::

«[illegible] መጣህ እንዴ አስራቴ?» አሉና ለአራት ቀናትም ቢሆን ናፍቀውታልና ሲስሙት ጠጋ አሉ:: «የገና እና የጥምቀት ልብስ አስገዛልሁ ብለህ ሄደህ ራስህን ይዘህ መጣህ!» እያሉ ይስሙት ጀመር:: ይህ ዘዴ የአስራት ወደ ዲላ መሄጃ ሰበብ ተደርጎ ለሒዋን ሲነገር የሰነበተ ነበር::

«የታለች ታዲያ?» ሲሉ እንደገና ጠየቀው ገና መልስ ሳይሰጣቸው ራሷ ሸዋዬ በጓሮ በር በኩል ብቅ አለች:: የማይቀረው የእናትና ልጅ የናፍቆት ስሞሽና ጥይይት ተፈጸመ::

የሥራው ጉዳይ ውይይት የተጀመረው ማታ እራት ተበልቶ አብቅቶ ቡና እየተፈላና ሸዋዬ በሻንጣዋ ውስጥ ያጨቀቻቸውን የስጦታ ልብሶች ለየተመደበላቸው ሰዎች ማደል ስትጀምር ነው:: በመጀመሪያ ለአባትና እናቷ የገዛቻቸውን ነጠላና ኩታ እንዲሁም በልክ ተሰፍቶ የሚለበስ ብትን ጨርቅ አደለቻቸው:: ለሒዋን ደግሞ የተዘጋጁ ጉርድ ቀሚስና ማላበሻዎች እንዲሁም አረንጓዴ ዓይነት ስከርፍ ሰጠቻት:: ማሰሪያውን ጨምሮ በወርቅማ ቀለም ቅብ የሚያብረቀርቅ የእጅ ሰዓት ከእጅ ቦርሳዋ ውስጥ አውጥታና በሒዋን ግራ እጅ ላይ ማሰር ጀመረች::

በሁኔታው የተደነቁ እናቷ «ታዲያ እኮ ለእሙዬ ያረግሽው ብቻ በቂ ነበር የሸዋ! ለኛ ምን አሳሰበሽ?» አሉ ፈገግ ብለው ልጆቻቸውን ተራ በተራ እያዩ::

«ከሆነማ ቅድሚያ ለእናንተ ነው:: ሒዩ ልጅ ስለሆነች ገና ብዙ ይደረግላታል:: እናንተ ግን አሮጊትና ሽማግሌ ስለሆናችሁ...» ብላ ነገሯን ሳትጨርስ «ኪም-ኪም-ኪም-ኪም......» ብላ ሳቀች::

«እናንተ ሲያምርባችሁ እኮ እኛ እንዋባለን::» አሉ አቶ ተስፋዬ በተራቸው::

«ኧረ እኔ በጣም ያሳሰበኝ የሒዩ የልብ ህመም ነው::» አለችና ሸዋዬ በተለይ ወደ እናቷ በማተኮር «ለመሆኑ ታስባለች? ትጨነቃለች?» ስትል ጠየቀቻቸው::

«ኧረ እሷ እቴ! ደሞ እኔ እናቷ እያለሁ የምን ሀሳብ! የምንስ ጭንቀት?»

«ታዲያ እንዴት ጀመራት?»

«እንደው ተሚዱ::»

«ታዲያ ዲላ ሆስፒታል መኖሩን አታውቁም ወይስ...» ብላ ሸዋዬ ሁሉንም አየት አየት ስታደርጋቸው የሒዋን አባት ቀጠሉ::

«ተመካከሩበት አሁንም ይደርሳል::»

ሒዋን ግን ወደ መሬት አቀርቅራ ዝም አለች::

«ታውቂ ኖሯል እሙዬ?» ሲሉ እናቷ ጠየቋት፤ እሳቸውም የሚያውቁ ቢሆንም ስሜቷን መሰለያ መንገድ መፈለጋቸው ነበር ::

«አዎ::» አለች ሒዋን አሁንም እንዳቀረቀረች::

«ታዲያ ዝም ብለሽ መሞት ፈለግሽ?» ስትል ሸዋዬ ቆጣ ብላ ጠየቀቻት።
«እኔ ሐኪም አያድነኝም።» አለች ሑዋን እንዳቀረቀረች።
«እናስ? ጠንቋይ?» አለች ሸዋዬ በፌዝ አነጋገር።
«እስቲ እሙዬ ከእህትሽ ጋር ረጋ ብላችሁ ተመካከሩ።» አሉ የሑዋን እናት ጭንቅ ጥብብ እያላቸው። ሑዋን አቀርቅራ ዝም ስትል ልባቸው ፈራ።
«ሑዋኔ!» ሲሉ ጠሯት አባቷ።
«አቤት!»
«የሸዋ የምትለውን ተቀብለሽ መሞከሩ ይሻላል። ታልሆነ ታልሆን የአባትና የእናትሽን መደብ የሚከለክልሽ የለም የኔ ልጅ! ይኸን ነገር ችላ አትበይው።»
«ምናልባት እንደ ከዚህ ቀደሙ ጥት ወጣሽ? የት ገባሽ?፣ የምልሽ መስሎኝ እየሰጋሽ ይሆን?» አለችና ሸዋዬ አሁንም ቀጥላ «ያኔ እኮ ተማሪ ስለሆንሽ እንዳትዘናጊ ነው። ጭራሽ ዝም ካልኩሽ መረን እንዳትሄጂ የታላትነቴን ከአንገት በላይ ቆጣ ማለት እንዳለብኝ በማመን ነበር።» አለችና ሸዋዬ ወደ እናቷ እየተ እያረገች «እንደዚያ ማድረግ አልነበረብኝም እማዬ?» ስትል ጠየቀቻቸው።
«እንዴታ ልጄ! እንዴታ!» በማለት የሸዋዬን አነጋገር ያዳነቁ ከመሰሉ በኋላ «ምናልባት የልጅ ነገር ሆኖባት ሳታውቀው ቅሬታ ተሰምቷት ይመስለኛል።» አሉ ሸረፍ አድርገው ሑዋንን እየተመለከቷት።
«ዛሬ ግን በፈለገችው ሁዓት ወደ ፈለገችው ቦታ ብትሄድ በሰላም መመለሷን ከመመኘት በቀር ማን ይጠይቃታል።» አለች ሸዋዬ ፈገግ ባለ ሁኔታ።
«ተእንግዲህ ወዲያ እሷስ ሴትዮ እየሆነች አይደል!» አሉና የሑዋን እናት «ብትሄድም እኮ ወደነዚያ ታፈሡና በልሁ ወደሚባሉ ልጆች ነው፤ ሌላ የት ትሄዳለች!» አሉ የሑዋንንም የሸዋዬንም አስተያየት ለመሰለል ፈልገው።
«አንኳን እነሱ ጋ የትም ትሂድ አልኩሽ እማዬ! ቀና ብዬ ሳላያት ለእሷም ለእናንተም ቃል እገባለሁ!» አለች ሸዋዬ በተለይ እናቷን እያየች።
ሑዋን ድንገት ቀና አለችና በተለይ ሸዋዬን ትኩር ብላ ትመለከታት ጀመር። የሸዋዬን ንግግር ደግማ ደጋግማ ከጆሮዋ ላይ ትፈልገው ጀመር። ግን ደግሞ ማመኑም የቸገራት ትመስላለች።
«ትጠራጠሪያለሽ ሑዬ?» አለቻት ሸዋዬ ሑዋንን እየተ እያረገች።
ሑዋን መልስ ሳትሰጥ ወደ መሬት አቀረቀረች።
«እሙዬ፣ እህትሽን አነጋግሪያታ!» አሉ እናቷ።
«በርታ በርታ በይ ሑዋኔ!» አሉ አባቷ በበኩላቸው።
«የመጣሁት መታመምሽን ሰምቼ በችኮላ ነው። ፈቃድ እንኳ ስላላገኘሁ ነገውኑ እመለሳለሁና ቁርጡን ንገሪኝ።» አለች ሸዋዬ በሑዋን ላይ አተኩራ።
በዚህ ጊዜ የሑዋን እናት ድንገት ብድግ አሉና ወደ ሸዋዬ ጠጋ አሉ። ጡታቸውን እወጡና «በይ የሸዋ፣ እሙዬ ዲላ ሄዳ ከእነዚያ ልጆች ጋር መገናኘት ብትፈልግ ላትከለክያት በጠባሽው ጡት ቃል ግቢልኝ።» አሏት።
ሸዋዬ የእናቷን ጡት በእጇ ነካ አድርጋ መልሳ እጇን እየሳመች «ይኸው!» አለች።
«እልልልል...!» አሉ እናቷ።

ምዕራፍ አሥራ ሦስት

አሥራ ስድስት ወራትን በክብረ መንግስት አሳልፋ ወደ ዲላ የተመለሰችው ሑዋን ብዙ አካባቢያዊ ለውጥ ሊገጥማት እንደሚችል ገምታ ነበር። ነገር ግን ከሸዋዬ ቤት በዘመናዊ የቤት እቃዎች መሞላትና ወንድ ወንድ ከመሸተት በቀር ሌላው ነገር ያው ነው። በሸዋዬ ቤት የወንድ ኮትና ጃኬት ግድግዳ ላይ ተሰቅለው፣ የወንድ ጫማ በአልጋ ሥር ተቀምጦና ትልቅ የወንድ ፎቶ ግራፍ ብፌ ላይ ስታይ ሸዋዬ ባል ያገባች መሰላት። በእርግጥም ማንደፍሮን ገና የገባች እለት ተዋወቀችው። ማንደፍሮ መልኩ ጥቁር፣ ፊቱ ጉረድረድ ያለና አካሉ ግዙፍ ከመሆኑ ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ ሲጨብጣት የእጁ አከባበድ የሚያስፈራ ሆኖባት የነበረ ቢሆንም እያደር ስትግባባው ግን ባህሪው ቀላል የሆነ ሰው ነው። ይስቃል ይጫወታል። ቀልዶቹ ይጥማሉ። እየሰነበተች ስታየው እንዲያውም በእሱ መኖር ቤቱ ድምቀት ሲል መንፈሷም ዘና እያለ መጣ፤ «የኔ ፍልቅልቅ» በማለት እየጫወተችም ይበልጥ ያፍለቀልቃት ጀመር።
ዲላ እንደገባች በአፍንጫዋ የገባው አየር በእስቸለው የሰቀቀን ትዝታ የተሰወለ ነበር። ሆዷን ባር ባር እያሰው እንባዋም ያለ ገደብ ፈሰሷል። ቆም ሆና በተለይ ታፈሡን፣ በልሁን መርዕድንና ትርፌን አግኝታቸው በጋራ አልቅሰውና አንብተው እፎይ ካሉ ወዲህ ከፊል የመንፈስ መረጋጋትም እያገኘች ሄደ። ሸዋዬም ለአባትና ለእናቷ የገባችውን ቃል ያከበረች መሰለች፣ ሑዋን በማግኘቷም ሰዓት ወደ ታፈሡ ቤት ሄዳ የቱንም ያህል ጊዜ ቆይታ ብትመለስ የት ነበርሽ? ምን አስቆየሽ? አትላትም። ለሑዋን ከምንም በላይ የተመቻት ይህ የሸዋዬ ቃል ማክበር ነው።
ለአንድ አስራ አምስት ቀናት ያህል በዚህ አይነት አንፃራዊ የመንፈስ መረጋጋት ውስጥ የሰነበተችው ሑዋን ሦስተኛው ሳምንት ሲጀመር ግን ያ በሸዋዬ ቤት የመኖር ሥጋቷ የልቧን ግድግዳ ማንኳኳት ጀመረ፣ በድሉ አሸናፊ ማንደፍሮን እየተከተለ በዚያ ቤት ውስጥ ገባ ወጣ ማለት ጀመረ። ማንደፍሮ ስለ ሑዋን ብዙ ነገር ሲነገረው ከርሟል። ከእስቸለው ጋር የነበራት ግንኙነት፣ በድሉ ሑዋንን ለመቅረብ ያደረገው ጥረትና የሰጠችው ምላሽ፣ በአሁኑ ወቅት እስቸለው ስለሚገኝበት ሁኔታና ሌሎችም ሁኔታዎች በዝርዝር ተገልፀውለታል። ወደፊት በበድሉንና የሑዋንን ጉዳይ እንዲጨርስም አደራ ተጥሎበታል።
ምንም እንኳ በእስቸለውና በሑዋን መካከል የነበረው ግንኙነት በተዛባ ሁኔታ እየተነገረው የተሳሳተ መንገድ እንዲከተል የተገፋፋ ቢሆንም ማንደፍሮ ግን ሆዱን ፍርሃት ፍርሃት ይለው ነበር። ሁኔታው ምንም ይሁን ምን አንድ ነገር ተገንዝቧል። ሑዋን የምታፈቅረው ሰው አላት። ያ ሰው ለጊዜው በአካባቢው ባይኖርም በተስፋ እየጠበቀችው እንደሆነ ልብ ብሏል። የተጣለበት አደራ ደግሞ ይህን ተስፋ በጥሶ ሌላ እንዲቀጥል ነው። እናም ስህሊናው እየከበደው ውስጥ ውስጡን ይጨነቃል።
በሌላ በኩል ደግሞ ጉዳዩ የበድሉ ነው፣ የሥራ ዋስትናው። እንዲሁም የሸዋዬም ጥምር ነው፣ የአፍላ ፍቅረኛው። በዚህና በመሳሰሉት ሁኔታዎች እየተገፋፋ የተጣለበትን አደራ መወጣት የሚያስችሉ መላዎችን ሲፈጥር ሰንብቷል። አንድ ቀን በተለመደው ሁኔታ በድሉና ማንደፍሮ በሸዋዬ ቤት ጫት ለመቃም

አቅደው ከሸዋዬ ጋር በተደረገ ምክክር ቤቱ በልዩ ሁኔታ ተዘጋጅቷል። ከቀኑ ስምንት ሰዓት አካባቢ ከቤት ሲደርሱ ማንደፍሮ ከቤቱ ወለል ላይ ቆሞ ሰየት ያለ ሃሳብ አቀረበ። «ዛሬ ከምንም ነገር በፊት አንድ ነገር መፈፀም አለበት።» አለ በዚያ ሰዓት ጓዳ ውስጥ ለነበረችው ሑዋን በሚሰማ ሁኔታ ድምፁን ከፍ በማድረግ።

«ምን?» አለች ሸዋዬ ልክ እንደማታውቅ ሆና።

«ሑዩ የለችም እንዴ?» ሲል ማንደፍሮ እንደገና ጠየቃት።

«አለች። ጓዳ ውስጥ ናት።»

«እ ሁላችንም ወደ እሷ እንሂድ።» አለና ማንደፍሮ ቀድሞ ወደ ጓዳ ተራመደ። በድሉና ሸዋዬም ተከተሉት።

«የኔ ፍልቅልቅ!» ሲል ጠራት ማንደፍሮ ሑዋንን።

«አቤት!» አለች ሑዋን ድንግጥ እያለች። የቢያን ዕለት ደግሞ የልብ ህመሟ በጠር ብሶባት ፍራሽ ላይ ጋደም ብላለች።

«አንድ ጊዜ ብድግ ብትይ!»

ሑዋን በድንጋጤ ዓይኗ ፍጥጥ እንዳለ ተነስታ በዚያው በፍራሿ ላይ ቆመችና ከፊትለፊቷ የተኮለኮሉትን ሁሉ ተራ በተራ ታያቸው ጀመር።

«ዛሬ ዛሬ ሁሉም ነገር ገብቶኛል።» አለ ማንደፍሮ ሳቅ ብሎ። «ያ ሰውዬ!» ሲል ቀጠለ ወደ በድሉ እያመለከተ «ወደዚህ ቤት በመጣ ቁጥር ስሜትሽ ለምን እንደሚለዋወጥ ተረድቻለሁ። ያለ ፍላጎትሽ እየጎነተለ ሲያስቀይምሽ እንደቆየ ገብቶኛል። አሁን አሁን ጥፋት መሆኑን አምኖ ተቀብሏል። ይቅርታም ሊጠይቅሽ ተዘጋጅቷል። ይቅርታውን ተቀብለሽ እንድትታረቁና ልክ እንደ አንድ ቤተሰብ እየተያየን እንድንኖር ፈልጌአለሁ።» አላት።

ሑዋን ያሳሰበችውና ያልጠበቀችው አቀራረብ ነበር። ለጊዜው ግን ድንግጥ ብላ ወደ መሬት ከማቀርቀር በቀር ያለችው ነገር አልነበረም። ማንደፍሮ ወደ በድሉ ዞር አለና ቆጣ ባለ አነጋገር «ብል እግሯ ላይ ውደቅ!» ሲል አዘዘው። በድሉ ኩቱን ወደ ኋላ መለስ አድርጎ በሑዋን እግር ላይ ወደቀ።

«እልልልል...» አለች ሸዋዬ። ማንደፍሮም ብቻውን አጨበጨበ። ለሑዋን ግን ከትልቅ የእረብሻና የግርግር ጩኸት ውስጥ የገባች መሰላት። በድሉ በእግሯ ላይ ወደቆ ለአፍታ ሲቆይ ለመግደርደር ያህል እንኳ 'ብቃ ተነስ' አላለችውም። ሲበቃው ራሱ ተነሳ።

«ቀጥል!» አለ ማንደፍሮ ነገሩን በማሟሟቅ ዓይነት ፈንደቅ እያለ።

በድሉ ቀኝ እጁን በኮቱ ኪስ አስገብቶ አንዲት በብልጭልጭ ወረቀት የተጠቀለለች ነገር አወጣ። ወረቀቱን ቀዶ ጣለ። ከማይካ የተሰራች ነጭ ሙዳይ ብቅ አለች። እሷንም ከፈታት። በቅድሚያ ጥጥ መሳይ ነገር ታየ። ቀጠለና በግምት አሥራ አራት ግራም የሚሆን የክርስቶስ የስቅለት ተምሳሌት ማጫወቻ የተንጠለጠለበት የወርቅ ሀብል አወጣና በአንገት ውስጥ ለማስገባት የተዘጋጀ በሚመስል ሁኔታ ከያዘ በኋላ ፈገግ እያለ ማንደፍሮን አየት አደረገው።

«ቀጥል! ምን ታየኛለህ?» አለ ማንደፍሮ። በድሉ እነዚያን አራት ነጣጣ ጥርሶቹን ገልፈጥ አድርጎ ወደ ሑዋን ጠጋ ሲል ሑዋን ግን ድንገት ጮኸች።

«አልፈልግም!»

«ተይ እንጂ የኔ ፍልቅልቅ!» አለ ማንደፍሮ አሁንም ድንግጥ እያለ።

«እምቢ! አልፈልግም!» ሑዋን አሁንም። ፊቷን ኮስኮስ አድርጋ በድሉን በጥላቻ ዓይን ታየው ጀመር።

«እረ እንግዲህ!» አለና ማንደፍሮ ሑዋንን ወደ ራሱ ጎተት አደረገና ሁለት እጆቿን ያዝ በማድረግ «አጥልቅላት!» አለው በድሉን። በድሉ የሑዋን እጆች እንደተያያዙ ሀብሉን በአንገቷ ላይ የመጣል ያህል አስገብቶ ወደ ኋላው ፈገፈግ አለ። ማንደፍሮና ሸዋዬ አጨበጨቡ። ማንደፍሮ በሑዋን አንገት ላይ ያረፈውን ሀብል በእጁ ያዝ አድርጎ ወርቁንም ሑዋንንም ተራ በተራ እየተመለከተ «እንቺን መሰለች ቆንጆ የሚገባ ልዩ ስጦታ!» አላት።

ሑዋን ግን ዓይኖቿ በእንባ ሞሉ። ማንባሯን በክንዷ ጋርዳ ወደ መሬት በማቀርቀር ታለቅስ ጀመር።

«ሑዩ! እንዳንተያየም» አላት ማንደፍሮ። ሑዋን መልስ አልሰጠችውም። አሁንም አንገብሳ ታለቅስ ጀመር።

ትዳሯቸው እንዳልሞላ! ዓላማቸው እንዳልተሳካ በውል የተረዱት ማንደፍሮ፣ በድሉና ሸዋዬ ወደ ሳሎን ተመልሰው ፍራሻቸው ላይ ተኮለኮሉ። ሸዋዬ ተናዳለች። በድሉ አኩርፏል። ማንደፍሮም ቅስሙ ተሰብሯል።

በዝምታ የተጀመረው ጫት በኩርፊያ ጥቂት ተቃመ። አልፎ አልፎ አንዱ ወሬ ቢጀምርም እንኳ የሌላውን የሞቀ ምላሽ ሲያጣ ቶሎ ይቆርጠዋል። በየሆዳቸው ነገር ያስላስላሉ። ሸዋዬ ጎጆቷን እንዴት እንደምትወጣ፣ በድሉ በቀጣይ ምን ማድረግ እንዳለበትና ማንደፍሮ ደግሞ የተሰማውን ፀፀት እንዴት አድርጎ ከልቡ ሊያጠፋ እንደሚችል ያስባሉ።

ሑዋን ጓዳ ውስጥ ሆና በሌላ ሀሳብ ተውጣለች። ያን አንገቷ ላይ የተጣለባትን ሀብል አውልቃ ፍራሹ ላይ አስቀምጣ በጥላቻ ዓይን ታየዋለች። ወርቅ መሆኑ ቀርቶ ተገድሎ የተጣለ እውሬ ይመስላታል። 'ኤርትራ የሄደ ይመስለል ብለሽ...' በማለት መንፈሷን በአቆሰለ ሰው የተገዛ ነውና እርም ሆኖባታል። በዚያው ሰበብ አስቻለውን አስታወሰችው። ያኔ ለዝውውር ጥያቄ ወደ አዲስ አበባ ሲሄድ ሲል '...ምን ገዝቼልሽ ልምጣ?' ብሎ የጠየቃት ከአእምሮዋ ድቅን አለ። የሰጠችውም ምላሽ እንዲሁ። የመኪናው አደጋ ሰቀቀንም ትዝ አላት። ወደ ኤርትራ አካሄዱም በትዝታ መጣባት። 'አልሄድም' ብሎ የተከራከራትንም፣ ይሄድ ዘንድ ያባበለችበትንም ቃሎች አስታወሰቻቸው። ከአሁኑ የአስቻለው መቅረት ጋር እያገናዘበች በፀፀት እሳት ተቃጠለች። ተንገበገበች። አለቀሰችም። ሁሉም ነገር ተደማመረና ለአንድ ርምጃ አነሳሳት። ድንገት ከፍራሿ ላይ ብድግ አለችና ያንን የወርቅ ሀብል ይዛ ወደ ሳሎን ወጣች። ሁሉም ቀና ቀና ብለው ሲያዩዋት ሀብሉን በማንደፍሮ ጭኖች ላይ ውርውር አድርጋ ወደ ውጭ ገሰገሰች።

ሦስቱም በድንጋጤ ይተያዩ ጀመር። በየአፋቸው ውስጥ ያስገቡት ጫት እስከሚታይ ድረስ አፋቸው ተከፈተ። ዝም ዝም። ክው፣ ድርቅ በያሉበት።

«ምን መሆኗ ነው?» አለ ማንደፍሮ ከአፍታ ቆይታ በኋላ።

«ማንዴ፣ ዝም ትላለህ?» አለችው ሸዋዬ። ማንደፍሮ ጥቂት አሰበና አንድ ነገር በአዕምሮ ብልጭ ሲልለት ብድግ ብሎ በፍጥነት እየተራመደ ከቤት ወጣ። ከዚያም ወጥቶ ግራና ቀኝ ሲመለከት ሑዋንን ከሩቅ አያትና «ሑዩ!» ሲል ጠራት። እሷ ግን ዘወር አላለችም፣ ርምጃዋን ቀጠለች። ማንደፍሮ ሮጦ ደረሰባት።

ከፊትለፊቷ በረከክ ብሎ ተተምጦ ቀና ብሎ እየተመለከታት «የኔ ፍልቅልቅ፣ በእናትሽ!» አላት።

«ተወኝ ጋሽ ማንደፍሮ!» አለች ሒዋን እያለቀሰች።

«ለራሱ ነው የምለምንሽ የኔ ቆንጆ! አንዴ አዳምጭኝ!»

«ምን ላድርግልህ?»

«ለስራሁት ጥፋት ይቅርታ አድርጊልኝ፣ ሁለተኛ አልደግመውም።

«ይኸ ሰውዬ ዳግመኛ እዚህ ቤት እንዳይመጣ ታደርግልኛለህ?»

«ቢያንስ እኔን ተከትሎ እንዳይመጣ አደርጋለሁ። ስለ አንቺ ቢያወራልኝ መልስ አልሰጠውም። አንቺ የምታከብሪውን ሰው እኔም አከብራለሁ።»

«እሺ ጋሽ ማንደፍሮ! አሁን ልቀቀኝና ልሂድ»

ማንደፍሮ ቀሪውን የይቅርታ ልመና ወደፊት እንደሚቀጥል ተስፋ በማድረግ ከተንበረከከበት ብድግ ብሎ ሒዋንን ግንባሯ ላይ ሳም አድርጎ ለቀቃት። እሷም ወደ ታፈሡ ቤት ገሰገሰች። እሱም ወደ ጫቱ ተመለሰ።

«እምቢ አለችህ?» አለችው ሸዋዬ ዓይኗን ብልጥጥ አድርጋ እያየችው።

«ተዋት። ትረጋጋ!» አለ ማንደፍሮ የልቡን አድርሷልና ለራሱ ተረጋግቶ ወደ ፍራሹ አልፎ እየተቀመጠ።

«ምን ልሁን እያለች ነው?» አለ በድሉ ሸዋዬንም ማንደፍሮንም እየት እየት እያረገ።

«ፈርታ ይመስለኛል?» አለች ሸዋዬ።

«ማንን?» ሲል ጠየቃት በድሉ።

«ታስታውሰው የለም ያን በልሁ ተገኔ የሚባል ቀፈታም!» አለችና «ያለ እሱ በዚች ልጅ ህይወት ላይ ችግር የፈጠረ የለም። እሱ እያለ ከየት አመጣሁት ብላ ይህን ሁብል አንገቷ ላይ ታውሰው?» ብላ በቁጭት ዓይነት ራሷን ወዘወዘች።

«በልሁ የሚባለው ምኗ ነው?» ሲል ጠየቀ ማንደፍሮ።

«የዚያ የአሥመራ ሰውየዋ ጓደኛ ነኝ ባይ!» አለች ሸዋዬ አሁንም ውጭ ውጭ እያየች። በድሉ አንገቱን ነቅንቅ ነቅንቅ አድርጎ «የዘነጋሁት ነገር ገና አሁን ትዝ አለኝ።» አለ በተሰይ ሸዋዬን ትኩር ብሎ እየተመለከተ።

«እኔ ድሮም አውቀዋለሁ። ለአንተ ግልፅ ባደርግልህ አጉል በእልህ ተነሳስተህ አንድ ነገር ላድርግ ትላለህ ብዬ ፈርቼ ነው እንጂ!» አለችው።

በድሉ ድንገት ብድግ አለና ጫማውን አጠለቀ። አፉን ተጉመጥምጦ ኮቱንም ለበሰ። የዕለቱ የጫት ቅሞሽ ከራማው ተገፈፈና ማንደፍሮም ተከተለ። ሁለቱም ከቤት ሲወጡ ሲዘጋጁ «ወጣ አንልም የሸዋ!?» ሲል ማንደፍሮ ሸዋዬን ጠየቃት።

«አይ - አይ! የዛሬው ይለፈኝ፤ እናንተ ሂዱ።»

«ምነው? ደበረሽ?»

«ዛሬ ብርቱ ጉዳይ አለኝ፤ ከዚህ ቤት መውጣት አልፈልግም።» አለችው።

ማንደፍሮ የሸዋዬ ስሜት ገብቶት «በሒዋን ላይ አንድ ነገር ልትፈፅምባት ይሆናል» በማለት ልቡ እየሰጋ በድሉን ተከትሎ ከቤት ወጥቶ ሄደ።

ጊዜው መሸ። ከአሥራ ሁለት ሰዓት አልፎ ዓይን መያዝ ጀመረ። ሒዋን ወትሮ እንደምታደርገው ሁሉ ከታፈሡ ቤት አመሻሽታ ልክ ከምሽቱ አንድ ሰዓት

ላይ ከቤቷ ከች አለች። ሸዋዬ ግን ዓይኗን አፍጣ ጥርሷን አግጥጣ ጠበቀቻት። በዚያን ሰዓት የሸዋዬን ቤት ውስጥ መኖር ሒዋን ያልጠበቀችው ሁኔታ ነበር።

«ሰሚ አንቺ!» አለቻት ሸዋዬ ሒዋን ገና እግሯ ወደ ቤት ገባ እንዳለ።

«አቤት!» አለች ሒዋን።

«እስቲ ቁጭ በይና እንነጋገር።» አለቻት በዓይኗ ከፊትለፊቷ ያለችውን ዱካ እያሳየቻት። ሒዋን ቁጭ ስትል ሸዋዬ ራሷ «የት ነበር የሄድሽው?» አለቻት።

«እታፈሡ ጋ።»

«ዳግም ወደዚያ ቤት እንዳማትሄጂ ታውቂያለሽ!?»

«ለምን እት-አበባ? ለእማዬ የገባሽውን ቃል እረሣሽው?»

«አንቺ በሰው ሞራል ላይ ምን እየሰራሽ እንደሆነ እያየሁ እኔ ያረጀ ያፈጀ አደራ ላከብርልሽ ትፈልጊያለሽ!?» አለቻት።

«የእናት አደራ አያረጅም።»

«ለመሆኑ ቅድም ሰርተሽ የሄድሽው ነገር ትዝ ይልሻል?»

«የሰው ንብረት መለስኩ እንጂ ሌላ ምን አደረኩ?»

«የሰው ንብረት?» ስትል ሸዋዬ ቃሉን ደገመች።

«የኔ ያልሆነ ነገር ሁሉ የሰው ነው።»

«ትንሽ አታፍሪም?»

«ምንም እት አበባ!»

«ገልቱ! የሰው ገልቱ!!»

ሒዋን ወደ መሬት አቀረቀረች። እጆቿን በጡቶቿ ሥር አቆላልፋ መሬት መሬት ታይ ጀመር።

«ከወርቅ የበለጠ ምን እንድሰጥሽ ትፈልጊያለች?» አለቻት ሸዋዬ አሁንም በቁጣና በእልህ እንጋገር።

«ላጌጥበት ወይስ ልሸከመው?»

«ጤነኛ ነሽ ግን?»

«ለመሆንማ ታውቂው የለ እት- አበባ!!»

«ይሆሽ ይሂድ!»

ሒዋን እንባዋ በዓይኗ ሙሉ ግጥም አለ። ብድግ ብላ ወደ ጓዳ ገባችና ፍራሿ ላይ ድፍት አለች። ሸዋዬ ተፈናጥራ ተከተለቻትና ከፊቷ በመቆም «ትሰሚያለሽ? ለአንቺ ይብላኝልሽ እንጂ በድሉ አሸናፊ እንደሆን ስንቶች ስንት ነገር እናድርግልህ የሚሉት የተከበረ ልጅ ነው።» አለቻት።

«ታዲያ የሚሰጡት ካሉ መስጠት ለምን አስፈለገው?» አለቻት ሒዋን ፍራሿ ላይ ድፍት እንዳለች።

«የኛ ፈላስፋ!»

«እት-አበባ! በእናታችን ጡት ይዠሻለሁ፣ እያመመኝ ነው ተይኝ።»

«ለምን አያምሽ! አንቺ እንደሆንሽ ዱላ እየኖርሽ ሀሳብሽ ያለው ኤርትራ!» አለችና «አሁን ያን ሁብል ትመልሻለሽ ወይስ አትመልሺም?» ስትል ጠየቀቻት።

«እኔ የሰው ገንዘብ አልፈልግም።»

«ኧረ ወዲያ! ለካ አትፈልጊም?» በማለት ሸዋዬ ሒዋንን ካላገጠችባት በኋላ ወዲያው ደግሞ «ለመሆኑ የለበስሽውን ቀሚስና ያሰርሽውን ሰዓት የገዛችው ሸዋዬ

መስለችሽ? በድሉ እኮ ነው ሰው መስለሽው ሰው ሲያረግሽ እስቦ ያሸሞንሞነሽ፡፡ ካለቻት በኋላ «ደንቆሮ!» ብላት እየተፈናጠረች ወደ ሳሎን ሄዳ ፍሪጂ ላይ ቁጭ አለች፡፡ በእርግጥም ሔዋን በዕለቱ የለበሰችው ጉርድ ቀሚስ ባለፈው ጊዜ ከበረ መታገስት ሳለች ሸዋዬ የቀረበላት ስጦታ ነው፡፡ እንደገና እየት አረገችው፡፡ ወዲያው ሁለመናዋን ተንቀናች፡፡ ቶሎ አወልቃችና በሌላ ቀየረችው፡፡ ሰዓቱንም ከእጂ ላይ ፈታች፡፡ በትንሽ ፌስታል ውስጥ ሁሉንም አስገባችና ወደ ሳሎን በመሄድ «እንቺ ለባለቤቱ መልሺለት፡፡» ብላ ከሸዋዬ ጎን አስቀምጣ ወደ ጓዳዋ ተመለሰች፡፡ እት-አበባ ... አለች ሸዋዬ አሁንም በቁጣ፡፡ «ምን እያረግሽ ነው?» በንዴት

«እንቺ!» አለች አምኛል፡፡»

«ተይኝ እት አበባ እምኛል፡፡ እኮ እፈራለሁ ነው፡፡ ለምን ተጠቅልለሽ ሄደሽ አታርፊም፤

«ለሊሞሽ ያለው እኮ እፈራለሁ ነው፡፡ የነዶቷ ስት፣ የብሽቀት ኪኪኪ!!

ኪም-ኪም-ኪም...» የጎዱት ስት፣ የብሽቀት ኪኪኪ!!

ሔዋን ግን ዝም ብላ ጥቅልል ብላ ተኛች፡፡ የልብ ህመሟም ይሚጠናት ጀመር፡፡ እየጨነቃት ሄደ፡፡

«መልስ የለሽም?» አለች ሸዋዬ አሁንም ጮክ ባለ ድምጽ፡፡

«የሚሰማ ጆሮ የለማ!»

* * *

ጥቂት ቀናት አለፉ፡፡ አንድ ቀን ምሽት ላይ በልሁና መርዕድ በምህጻረ ቃል አማሆ ተብሎ በሚጠራው ሆቴል ውስጥ ከውጭ ወደ ቡና ቤቱ ሲገቡ በስተቀኝ በኩል በምትገኝ ብቸኛ ጠረጴዛ ላይ ቁጭ ብለው ከአንዲት የቡና ቤቱ አስተናጋጅ ጋር እየተቃለዱ ይጠጣሉ፡፡ ከጠረጴዛው ፊትለፊት ያለው ባንኮኒና የቡና ማሽን ብቻ ስለሆነ ቦታው እንደ ልብ ለመጫወት አመቺ ነው፡፡ የቀልዳቸውና የጭውውታቸው ማዕከልም የመርዕድ ዓይን አፋርነት ነው፡፡ አስተናጋጇ ባህሪውን ቀደም ብላ ስለምታውቅ በነገር እየነካካች ታሳፍረው ይዛለች፡፡

«መቼም የአንተን ድንግል የምወስደው እኔ ነኝ፡፡» ትለዋለች ጉልበቱንና ጭኖቹን እያሻሸች፡፡

«እስቲ እንደ ምንም ብለሽ ገላግይው፡፡» በልሁ እየሳቀ፡፡

«እቦ ተይኝና ስላ ወሬ አምጪ!» ይላል መርዕድ የአስተናጋጇን እጅ ከላዩ ላይ ለማንሳት እየሞከረ፡፡

«አይዞህ! ቦታውን እንደሆን እኔው ራሴ አሳይሃለሁ፡፡» አስተናጋጇ አሁንም፡፡

«እንዲህ ከመባል ሞት ይሻላል መርዕድ!» እያለ በልሁ ይስቃል፡፡

እንዲህና እንዲያ እያሉ በመጫወት ላይ ሳሉ ከምሽቱ አንድ ሰዓት ተኩል አካባቢ ሁለት ሰዎች ተከታትለው ወደ ቡና ቤቱ ገቡና ግራ ቀኝ ተመለከቱ፡፡ ከበሩ በስተግራ በኩል ያለው ዋናው ሳሎን በሰው ተሞልቷል፡፡ በቀኝ በኩል ያለችው ጠረጴዛ ደግሞ በእነበልሁ ተይዛለች፡፡ በቀጥታ ወደ ባንኮኒው በመጠጋት ጀርባቸውን ለእነበልሁ ሰጥተው ቆሙ፡፡ ወዲያው ደግሞ በድሉ አሸናፊ ከውጭ መጥቶ ተቀላቀላቸው፡፡ እሱ ከመሀል ሌሎቹ ግራና ቀኝ በመሆን ፊንጠር ፊጠር ብለው ተደረደሩና የሚጠጡትን አዘዙ፡፡ ለሁሉም አረቂ ቀረበላቸው ፡፡

በልሁ ግን ቅፍፍ ይለው ጀመር፡፡ እሱና በድሉ ቀድሞም ተደናቢው ነበር ... ግራ ድግሞ ግና ሲገባ ገልመጥ አድርጎት ... ከማያውቃቸው ሰዎች ጋር ገጥሟልና ጥርጣሬ ገባው፡፡ ... አሳምሮ አለው ግልብጥ ግልብጥ ያደርጉታል፡፡ ወደ ኋላቸው ዞር እያሉ ሲገላምጡት ያዩ ጀመር፡፡ ... የሚያወሩትን ትቶ እነበድሉን መከታተል ቀጠለ፡፡ መርዕድና በዚህ ሁኔታ ላይ ሳሉ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት አለፈ፡፡ የመጀመሪያ እድሉን እዚያው እተፈጠረበት አገር ረስቶ የመጣው የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን በቡና ቤቱ ውስጥ ተከፍቶ ያለ ምንም አድማጭ ለራሱ ይጮሀል፡፡ ዜና እወጃውን ዉርሶ የማስታወቂያ ፕሮግራም ማስተላለፍ ጀምሯል፡፡ የመኪና ስራ እንቅስቃሴ እያሳየ ... ያገኙትን ጠቀሜታ ይዘረዝራል፡፡

በድሉና ጓደኞቹ ከቴሌቪዥኑ ፕሮግራም ጋር የተያያዘ ወሬ ማውራት ጀመሩ፡፡ ያም ቢሆን ከበልሁ ጆሮ ደረሰና እሱም በጥንቃቄ ያዳምጥ ጀመር፡፡ ከበድሉ በስተቀኝ በኩል ከቡና ማሽኑ አጠገብ ቆሞ የሚጠጣው የበድሉ ጓደኛ «ስሚ አንቺ!» ሲል ጠራት ከባንኮኒ ውስጥ ቆማ የነበረችውን አስተናጋጅ፡፡

«አቤት!» አለችው፡፡

«የኢትዮጵያ ገበሬዎች ቴሌቪዥን ገዙ ወይስ እኔና አንቺን ገበሬ ለማድረግ ተፈልጎ ነው ይኸ ፕሮግራም የሚተላለፈው?» ሲል ጮክ ባለ ድምፅ ጠየቃት፡፡

«እኔ ምን አውቄ?» አለች አስተናጋጇ፡፡

«የከተማ ገበሬ ሞልቷል አትይውም!» አላት ሌላው የበድሉ ጓደኛ፡፡ ከግራ በኩል ሆኖ ወደ ኋላ ዘወር ብሎ በልሁንም እየት አደረገው፡፡

«ይኸ ከየገጠሩ ወፍ ዘራሽ ቡና የሚሰቅመው?» ሲል የመጀመሪያው ተናጋሪ ጠየቀ፡፡

«ሞፈርና ቀንበራቸውን ሰቅለው ወደ ከተማ የገቡ ገበሬዎች ስላሉ ታምርተው እንዲመለሱ ይሆናል፡፡» አለና በድሉ ወደ ኋላው ዞር ብሎ በልሁን ገልመጥ ሲያደርገው ዓይን ለዓይን ግጥምጥም አሉ፡፡

«አሃ!» አለ በልሁ፡፡ ነገሮች ሁሉ ደብልጥ እየገቡት ሄዱ፡፡ ሁኔታው የበለጠ ጆሮውን ጥሎ እንዲያዳምጥ አደረገው፡፡»

«ከተማ ውስጥ ገብቶ ማውደልደል የለመደ ገበሬ ምንም ቢሉት፣ ምን ቢያደርጉት ተመልሶ ገጠር አይገባም፡፡» አለ የመጀመሪያው ተናጋሪ የበድሉ ጓደኛ፡፡ እሱም በልሁን ዞር ብሎ ሲያየው አሁንም ከበልሁ ጋር ተገጣጠሙ፡፡

«ወዶ ነው! ተገዶ ይመለሳል፡፡» በማለት በድሉ ሲጨምር በልሁ ሁለመናውን ይነዝረው ጀመር፡፡ በልሁ ጠብ ጠብ ሲሸተው ትንፋሹ ያጥራል፡፡ እስኪጀምር ድረስ መላ ሰውነቱ ይንዘፈዘፋል፡፡ ዓይኑ ይፈጣል፡፡ ያ በሽታው ተነሳበት፡፡ በዚያው ስሜት ውስጥ ሆኖ ምልልሳቸውን ማዳመጡን ቀጠለ፡፡

«ስሚ አንቺ!» ሲል ተጣራ በድሉ አሁንም አስተናጋጇን፡፡

«አቤት!»

«ይህን ቴሌቪዥን ዝጊና ‹ቆይ ብቻ› የሚለውን ካሴት ክፈች፡፡ ይኸ ሴት እውል ሁሉ ልብ ቢገዛ!» አለና አሁንም ዞር ብሎ በልሁን ገላመጠው ፡፡

በዚህ ጊዜ በልሁ ለየለት፡፡ ተዘጋጅተው እንደመጡበትም በትክክል ተረዳ፡፡ ወዲያው በግራ ጣቱ ላይ ያጠለቃትን ባለ ፈርጥ ቀለበት ወደ ቀኝ ጣቱ አዛወራት፡፡

ጡንቻውን ማጠባበቅ ጀመረ። ከእንግዲህ አንዲት የትንኮሳ ቃልና ግልምጫ ቢቀረችው። ይጠባበቃትም ጀመር።

በድሉ አሁንም ቀጠለ። «እንኳን የግብርና ወሬ መስማት የግብርና ባለሙያ ነኝ ባይ በከተማ ውስጥ ማየት አስጠልቶናል።» አለና ብርጭቆውን ብድግ አድርጎ አረቄውን ጨለጠና ከመጠን በላይ ባንኮኒ እያንኳኳ «ቶሎ በይ! ነዳጅ ጨምሪ! ዛሬ የማነድደው አለኝ» አለና አሁንም ወደ በልሁ ዞር አለ።

«ስማ አንተ!» አለው በልሁ መርዕድን።

«ወይ» አለ መርዕድ። መርዕድ እየሆነ ያለውን ነገር ይከታተል ነበርና ደንግጦ መግቢያ ቀዳዳ አጥቷል።

«ለተቀመጥነበት ንቅንቅ እንዳትል እሺ!»

«ለምን ወጥተን አንሄድም?» አለ መርዕድ።

«ጉዳዩን እስከምፈጽም ጠብቀኝ።» አለና በልሁ ከወንበሩ ላይ ተነስቶ በቀጥታ ወደ ባንኮኒው አመራ። በበድሉ እና ከቀኙ በኩል ባለው ጓደኛው መካከል ባንኮኒ ተደግፎ ቆመና «ንበገዘ!» አላቸው ሦስቱንም ተራ በተራ እየተመለከተ። «ጨዋታችሁ ደስ አለኝና መጣሁ። እየጋበዛችሁኝ ወይ እየጋበዝኳችሁ እንጫወት ብዬ ነው።» አላቸው ዓይኑ ፈጠጥ ያለ ቢሆንም ነገር ግን ፈገግ ብሎ።

«ታውቀናለህ?» አለው በድሉ በቁመት የሚበልጠውን በልሁን አንጋጦ እየተመለከተ።

«ይመስለኝ ነበር። አሁን ግን እንደማንተዋወቅ ገባኝ። ግን ደግሞ ሳንተዋወቅ አንለያይም።» ሲል መለሰለት በልሁ ረጋ ብሎ። «ተገድጀ ወደ አገሬ ልመለስ ነውና የወጪ ልብልህ፣ ጠጣ!» አለው አሁንም እያፌዘ። እስከዚህ ወቅት ድረስ የበድሉ ጓደኞች ምንም ዓይነት እንቅስቃሴ አላደረጉም። ግን በልሁን በግርምት ዓይን ይመለከቱታል።

«ነገር ፈልገሃል እንዴ?» አለ በድሉ አሁንም በልሁን እየተመለከተ።

«ራሱ ፈልጎኝ ነው የመጣሁት። አሁን ጠጣ! ካልጠጣህ ግን እመታሃለሁ።»

«እ?» ብሎ በድሉ ቀስቀስ ሲል ሲል በልሁ ድንገት አንገቱን አነቀው። «ገበሬ አይደለሁ፣ ፊትህን ሳርሰው ነው።» አለና በመሀል ፊቱ ላይ ሀይለኛ ቡጢ አሳረፈበት። በፍጥነት ደገመው። ከቀኙ በኩል ያለውን የበድሉን ጓደኛ እንቅስቃሴ ይከታተል ነበርና እውነትም ሲንቀሳቀስ አይቶት ኖሮ በቃሪያ ጥፊ ዓይነት በሀይል ሲሰነዝርበት ጆሮ ግንዱን አገኘው። ሰውየው ባላሰበው ሁኔታና ሀይል ስለተመታ ከመርዕድ እግር ስር ወድቆ ጥቅልል አለ። መርዕድ በዚያው ጀመረው። በወደቀበት በእርግጫ ፊት ፊቱን ይለው ጀመር። ከበድሉ በስተግራ የነበረው ሰውዬ በልሁን ሊመታ ሲሞክር በልሁ ግን የበድሉን አንገት ይዞ ወዲያ ወዲህ እያሽከረከረ መመከቻ አደረገው። በዚህ አኳኋንም፣ አዘናግቶ በበድሉ ትከሻ ላይ አሻግሮ በመሰንዘር ከፊቱ ላይ ከባድ ቡጢ አሳረፈበት። ቀጠለና በድሉን ለሦስተኛ ጊዜ ከደገመው በኋላ አንገቱን ሲለቀው በድሉ ተዝለፍልፎ መሬት ላይ ተዘረጋ። በዚህ ጊዜ በልሁ ወደ ሰውዬው ሲሮጥ ሰውየው ግን ወደ ኋላው ዞሮ በቡና ቤቱ በር በኩል እግሬ አውጪኝ አለ። አመለጠው።

በልሁ የሮጠውን ሰውዬ ትቶ ወደ ቤት ምልስ በማለት በድሉን በወደቀበት ፊቱ ላይ እንዴ በእርግጫ ብሎት መጀመሪያ ወደ ጣለው ሰውዬ አለፈ። ሰውዬውና መርዕድ እየታገሉ ናቸው። እንደውም ሰውዬው መርዕድን አሸንፎ ሊነሳ ትንሽ

ቀርቶት ነበር። ነገር ግን በልሁ ደርሶ በክርኑ ወገቡ ላይ በሀይል ሲመታው ተመልሶ መሬት ላይ ተነጠፈ። ቀጥሎም በእርግጫ እንደ ስልቻ ያለፋው ጀመር።

እሪታና ጩኸቱ ቀለጠ፣ ቤቱ ተተረማመሰ። የበልሁን አስባቢር ያየ ማንም ወደ ሊይዘው ወይም ሊገላግለው አልሞከረም። ሁሉም አንገቱን ወደ ትከሻው ቀብሮ «አቤት ገደለው! ገደላቸው! ጨረሳቸው!» እያለ ከመሸማቀቅ በቀር ማንም ምንም አልሞከረም። የአስተናጋጆቹ ጩኸት ግን ምድሪቱን ቀውጢ አደረጋት። አስተናጋጅዋ ጠጪ ምስክርነት ፊርማ እያተፈተለች ከቡና ቤቱ ወጣ።

ጥሎ ገንድሶ ያለ ገላጋይ የተንጓለለው በልሁ ግን ድንገት ሳይታሰብ በገባለውን በቡጢ እየመታ «ዋይ! ዋይ! ዋይ! ዋይ!» ካለ በኋላ ቀጥሎም «ወንድሜ አጠፋሁ! ኧረ ምን በላሁ? ኧረ ምን ዋጠህ ወንድሜ? ትገዛ አልከኝ እኮ! ትገዛ አልከኝ እኮ ወንድሜ?!» እያለ ስትስት ብሎ ያለቅስ ጀመር። በዚያ ሰዓት ምን ትገዛ እንዳለው ከእሱ በቀር ማንም ያወቀ አልነበረም። ወዲያው ግማሹ አስተናጋጆች የወደቁትን ሰዎች ደም በውሃ ሲያጥቡ ሌሎቹ ደግሞ ከመርዕድ ጋር በመተባበር በልሁን ገፋፍተው በጓዳ በር በኩል ከቡና ቤቱ ውጪ ወሰዱት።

* * *

ሔዋን የልብ ህመሟ ከመቼውም ጊዜ ብሶባት ፍራሽ ላይ ድፍት ብላ መዋል አዘውትራለች። በበልሁ ቡጢ ፊቱ የተጠረማመሰው በድሉ አሸናፊ አልጋ ላይ ከዋለ አስራ አንድ ቀን ሆኖታል። እዚህ ቀን ላይ ሆኖ ሲቆጠር ማንደፍሮ ለአንድ ሳምንት ያህል ተረኛ ሆኖ በተመደበበት ከአዋሳ–ይርጋለም መስመር ላይ ለመስራት ከቤቱ ከወጣ ሶስት ቀናት አልፎታል።

እለቱ እሁድ ነው፣ ከሰአት በኋላ። ሸዋዬ ቤትዋ ውስጥ ሶብፏዋ ቁጭ ብላ ጫት ትቃማለች። ነገር ግን የጐረሰችውን ጫት ማላመጥ እስከምትረሳ ድረስ በሃሳብ ተውጣ ፍዝዝ ትክዝ ትላለች። በበድሉ ላይ የደረሰው ውርደት ከእሉ ይበልጥ እሷን አሳፍሯታል። ዛሬ በማውጠንጠን ላይ ያለችው ሃሳብም ይህንኑ ሀፍረትና ውርደት ስለምታካክስበት መንገድና ሁኔታ ነው።

መነሻ ያደረገችው ከራሱ ከበድሉ የመነጨ ሀሳብ ነው። ከጥቂት ቀናት በፊት በተኛበት አልጋ አጠገብ ቁጭ ብላ ስታፅናናው በነበረችበት ወቅት በድሉ አንድ ነገር ተናግሯታል ‹ሸዋዬ! በእህትሽ ምክንያት ደሜ ፈሰሷል። ቅሌትም ደርሶብኛል። መካሻዬም እሷው ናት። የመጣው ይመጣል እንጂ አልተዋትም። ወይ እንደኔ ትዋረዳለች። አለያም እስከ መጨረሻው በእጄ ትገባለች። ለዚህ ደግሞ የአንቺን የአሳስለስ ጥረት እጠብቃለሁ› የሚል። የዛሬው ሀሳብና ትካዜዋም በዚሁ ላይ የሚያጠነጥን ነው። ከበድሉ የዛቻ ቃሎች በተግባር ተፈጽሞ ማየት የምትፈልገው ሔዋን ጥቅልል ብላ በእሱ እጅ መግባቷን ብቻ ነው።

ሸዋዬ ያለማወላወል በአንድ ሀሳብ ፀንታለች። ሔዋን ከበድሉ እጅ እስከ ወዲያኛው ትገባ ዘንድ አንድ አጋጣሚ ተፈጥሮ ከእሱ መፀነስ ይኖርባታል። ይህ ዘሮን መንገዶች ሁሉ ያጥራሉ። ሔዋን እስቻለውን በተስፋ የመጠበቅ ሀሳቧ

ያሰበበሳ፣ ቢመሳ እንኳ መሸሹን ትመርጣለች። እስቻለው ራሱም ዘወር ብሎ ሊያያት አይሞክርም። እንዴ ከወለዳት የልጅ አባት ያስፈልጋታልና በድሉን መሪት አትፈልግም። ምርጫዋም እሱ ብቻ ይሆናል። ማርገዟ ያሳፍራትና ከነቀፈሥና ከነልሁም ትርቃለች። እንዲያውም ጭራሽ እንዳያውቁባት ወደ ቤተሰቦቿ ወደ ክፍለ መንግስት ልሂድ ልትል ትችላለች። ያኔ በድሉም ወደዚያው መመላለስ ይጀምራል። ወዲያው ከቤተሰቦቿ ይተዋወቅና እጁንም መጠርጋት ይጀምራል። ጀብ ይሆናል ድርብ ድል ይሆናል ሕጻም ለዚህ ብዙ ነበር ለማለት ያበቃታል። ብዙም ሰሸዋዬ ወርቃማው መሳ ብላ ሰይማዋለች።

ይህን ወርቃማ መሳ ሰፍራ ለማብቃት ግን በድሉ ከሔዋን ጋር የሚፈጽመው የጠቢብ ግንኙነት በተነበና ወትትና ሰዓት መሆን እንዳለበት ታምናለች። ለዚህ መሠረት የሆናት ደግሞ በወር አበባ አቆጣጠር የሚታወቅ የእርግዝና ወቅት ነው። እንደ ሔዋን ለመውለድ ሳይሆን ላለመውለድ ስትል ራሷ ስትጠቀምበት ኖራለችና እጡቱቱ አይቸግራትም። የሚያስፈልጋት የሔዋንን የወር አበባ ዙር ማወቅ ብቻ ነው፤ በየስንት ቀን እንደሚታያት ካወቀች በየትኛው ቀን ግንኙነት ብትፈጽም መፀነስ እንደምትችል ታውቀዋለች። በዚያ ሰዓት ሔዋን ወሲብ ይፈጸምባት ዘንድ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት ወስናለች። ሔዋን ጨሽት ብታሰማ እንኳ በተያያዥ ሊነሳባት የሚችለውን ውግዘት ጆሮ ዳባ ልበስ ልትለው ቆርጣለች።

የሔዋንን የወር አበባ ዙር ለማወቅ ግን ተቸግራለች። እሷን ራሷን አትጠይቃት ነገር ሰሞኑን ተኳርፈዋል። በሌላ በኩል በትክክል ላትነግራት ትችልና ጥረቷ ሊመክን ይችላል። አስተማማኝ እንዲሆንላት ሐኪም ማማከር እንደሚሻል ታይቷታል። ለዚህ ስኬት ደግሞ የሔዋንን የልብ ህመም መነሻ ማድረግ ፈለገች። ከዚህ ጋር ተያይዞ ባርናባስ ወየሰ ታወሳት። እሱ ደግሞ የውጭ ሀገር ትምህርቱን አጠናቆ ወደ ሥራው ከተመለሰ ሰንበቷል። ከመጣም ተገናኝተዋል። ባል ማግባቷን ሰምቶ ተነጋግረውበታል። ባርኔ አልተከፋም። እንዲያውም 'እንኳን ደስ ያለሽ' ብሏታል። በተገናኙ ቁጥር መቃለዳቸውን አልተውም። እናም የሔዋንን የልብ ህመም በማስመርመር ሂደት ምናልባት ከወር አበባሽ ጋር ግንኙነት ካለው በሚል ሰበብ በሚቀርበው ህኪም በኩል የወር አበባዋን መምጫ ዙር ሊያስጠናላት እንደሚችል ገመተች። ይህን ዘዴ ለራሱ ለበድሉ ብታካፍለው ከእሷ በተሻለ እንደሚችል ሲያስከው እንደሚችል አሰበች። የዚያኑ ዕለት ልትነግረው ከባርናባስ ጋር ተመካክሮ ሲያሳካው እንደሚችል አሰበች። የዚያኑ ዕለት ልትነግረው ወሰነች። ከምሽቱ አሥራ ሁለት ሰዓት ተኩል አካባቢ ከቤቷ ወጣች። በቀበሌ ዜሮ ሦስት የመጨረሻ ጫፍ ላይ ወደሚገኘው የበድሉ መኖሪያ ቤት ማምራት ጀመረች።

ቀኑ መሽት ብሎ ለዓይን መያዝ ጀምሯል። ወደ በድሉ ቤት በመሄድ ላይ ሳለች ልክ አስፋልቱ ላይ ስትደርስ ድንገት ሳታስበው ባርናባስን ከሩቅ አየችው። አስፋልቱን ይዞ ከታች ወደ ላይ ከሁለት ሰዎች ጋር በመሆን እሷ ወደነበረችበት አቅጣጫ ይመጣል። ከበድሉ በፊት ለእሱ ስለ ውስጥ አሳቧ በዚያ አጋጣሚ ትነግሽ ፍንጭ ልትሰጠው ወደደች። መንገድ ዳር ቆማ ጠበቀችው። ባርናባስ ልክ አጠገቧ ሲደርስ ከሰዎቹ ነጠል ብሎ ወደ እሷ እንዲመጣ በእጇ ጠቀሰችው። ባርናባስም ጥሪዋን ተቀብሎ ወደ እሷ ጠጋ እያለ

«የሸዋ፣ በጨለማ መንገድ ዳር ምን አቆመሽ?» ሲል ጠየቃት እጁን ለሰላምታ እየዘረጋ።

«ቸግሮኝ።» አለችው እንደመሽኮርመም እያለች።

«ምነው፣ ምን ገጠመሽ?» አላት ባርናባስ። ሞቅ ስላለው እፉ ተያይዟል።

«ከቸገረኝ እንኳ ቆይቷል። ድንገት በሩቅ ሳይህ ግን ላማክርህ ፈልጌ ነው።»

«ምንድነው ችግሩ?»

«በዛ ያቺን እህቴን ልቧን እያመማት ተቸግሬአለሁ። ምናልባት በደንብ ሊያስተካት የሚችል አንተ በተለይ የምትቀርበው ሐኪም ካለ እደራ ትልልኝ እንደሆን ብዬ ነው።»

«ሌላ ምን ይቸግራል! ይቻላት ነው!»

«ቢሮህ ውስጥ ምንጊዜም ትኖራለህ አይደል?»

«የት እሄዳለሁ።» ካለ በኋላ ባርናባስ እጇን ያዝ አድርጎ «ድሮ እንኳ ወደ ዘር አምስት ቀብሌ ጎራ አል ነበር፤ ባሬ ግን ወንዘረኛ አስለቀቀኝ» በማለት ሳቅ ብሎ ሸዋዬንም አሳቃት።

«ሁሉም በጊዜው ሆኗል በቃ!» አለች ሸዋዬ እንደ መሽኮርመም እያለች።

«በቃ! በቃ?» አላት ባርናባስ አሁንም ወልገድገድ እያለ።

«አብቅቶ!»

«ታዲያ ያቺን ቆንጆ እህትሽን እንኳ እንዴት አድርጌ ልጠይቃት?»

«እንዴ! እሷን መጠየቅ ማን ይከለክልሀል?»

«አሁን እችላለሁ? ወይስ ሰውየሽ ይኖር እንደሆን ...» ብሎ ነገሩን ተወት ሲያደርግ ሸዋዬ ቀጠለች።

«አሁን መሸ! ጓደኞችህም ጥለውህ ሄዱ!»

«እነሱን ተያቸው እባክሽ!» አለና «እውነት ሰውየሽ ከሌለ ልጠይቃት። በጣም በጣም ናፍቃኛለች።» አላት። ሸዋዬ የባርናባስ ሀሳብ አልከበዳትም። ማገደፍር የለምና ዓይን ለዓይን አይጋጩባትም። በሌላ በኩል እግረ መንገዷን ሔዋን ወደ ሐኪም ቤት እንድትሄድ ሊገፋፋት እንደሚችል ታያት።

«ከበረታህ እንሂድ። እንደውም ቀኑን ሙሉ እንደተኛች ነው የዋለችው።»

«ሰውየው ግን አይኖርም? አየሽ ምናልባት...» ብሎ እፍ እፏን ሲጠባበት ሸዋዬ ቀጠለች። «ለነገሩ ሰሞኑን አይኖርም፤ የስራ ተራው ከድርጋሰም-አዋሳ መስመር ላይ ነው።» አለችና «ግን ቢኖርስ የኔና የአንተን ጉዳይ የት ያውቃልና ይበራጠራል ብለህ ሰጋህ?»

«አለመኖሩ ጥሩ!»

ተያይዘው ሄዱ።

በግምት ለአስር ደቂቃ ያህል ተጉዘው ከቤት ሲደርሱ ቤቱ ተቆልፎ አገኙት። ሔዋን የለችም። የሄደችበትን ቦታ በመገመት ሸዋዬ ውስጧ እርር ድብን አለ። ሔዋን ሰሞኑን ወደ ታፈሥ ቤት ብቅ ብላ ስለማታውቅ ያቺን አጋጣሚ ተጠቅማ ወደዚያው እንደሾለከች ገባት። ውስጧ ብግን አለና በሆዷ «ቆይ እባቷ ትመጣታለች!» እያለች ባርናባስ ይቀመጥ ዘንድ ጋበዘችው።

ባርናባስ ወደ ውጭ አገር ለትምህርት ከሄደና ከተመለሰም ወዲህ በሸዋዬ ቤት ሲገባ የመጀመሪያ ጊዜው ነው። የቤቷ መሰዋወጥ ገረመው። ከሁሉም በላይ ያሉን ውስጥ የተዘረጋ አልጋ አማለለው።

«እውነትም ባል አግብተሻል የሸዋ።» አላት እንደ አዲስ።

«አይደል? ኪም-ኪም-ኪም-....»

ባርናባስ ከሞትታ ጋር ተቀላቅሎበት ሳይሆን አይቀርም ከቁጥጥሩ ውጭ በሆነ ስሜት አሊጋው ላይ ቁጭ አለና ክፊቱ የቆመችውን ሸዋዬ እንጋጠ ይመለከታት ጀመር ።

«እንዴ! ምን ነበር?» አለች ሸዋዬ እንደመሸበርመም እያለች። ባርናባስ ግን እንዲያውም ቀሚሷን ይዞ ጎተት ሲያደርጋት «ኧረ በህግ አምላክ?» አለችው።

ባርናባስ ጠንከር አለ። አሊጋው ላይ ጎትቶ እስተመጣትና «በህግ አምላክ መባል ያለበት ሌላ! እኔ እኮ የቀድሞ ባለይዞታ ነኝ።» አላት ደበስበስ እያደረገ።

«ያ እኮ ቀረ።»

«የሚቀረው እኔና አንቺ ስንቀር ብቻ ነው።» እያለ ትከሻዋን ይዞ ወደ አሊጋው ጋለል አደረጋት። በዚያው ቀጠለ። ሄዱ፣ ነጎዱ። ባላሰቡት መንገድ ጀወውወው.....!!

አጋጣሚ ሆኖ ማንደፍሮ ከሸዋዬ ቤት ሊደርስ ከአሥር ደቂቃ ያልበለጠ ጊዜ የሚወስድ መንገድ ብቻ ቀርቶታል። አስቦበት አልነበረም፣ ጠዋት ሰዎችን አሳፍሮ ከይርጋለም ወደ አዋሳ ሲሄድ ወደ አፖስቶ ኬላ ብቅ መበያ ዳገት ላይ መኪና ተበላሽቶበት ለመጠገን ሲለፋ ውሏል። የብልሽቱ መጠን ከባድ በመሆኑ ዕቃ ለውጦ መገጣጠም የሚችል ባለሙያ አስፈላጊ መሆኑን እምኖ ጉዳዩን ለተሽከርካሪው ባለቤቶች ሊያስረዳ ምሽቱን ዲላ ገብቷል። ዲላ ከተማ ከገባ በኋላ ቶሎ ወደ ቤቱ አልሄደም። ለውሃ ጥም መቁረጫ ያህል ሲጠጣ ቆይቷል። ከዚያም በኋላ በቅድሚያ ወደ በድሉ ነበር የሄደው። የገጠመውን ችግር አስረድቶ አስፈላጊውን ሁሉ ጠዋት ለመፈጸም ቀጠሮ ይዞ ወደ ቤቱ እየተመለሰ ነው።

ማንደፍሮ ከቤቱ ሲደርስ ቤት ውስጥ መብራት ሲበራ ከሩቅ ታየው። በር ከፍቶ ሊገባ እጁን ከመዝጊያው ላይ ጣል ሲያደርግ ሲል ድንገት አንድ ድምፅ ጆሮው ውስጥ ጥልቅ አለ። በሩን መግፋት ወይም መቆርቆር ትቶ ጆሮውን ወደ ውስጥ ጣል ሲያደርግ ያንን ድምጽ ደግሞ ሰማው። የሸዋዬ ድምጽ ነው። ሸዋዬ ወሲብ በምትፈጽምበት ጊዜ መለፍለፍ ትወዳለች። የወሲብ አጋሯን ስም ደጋግማ ካልጠራች አይሆንላትም። ይህን አመሏን ማንደፍሮም ያውቀዋልና አሁንም ሲያዳምጥ «ባርኒ! አንተ ባርኒ፣ እንዴት ነው እሱ? እኮ! እም... !» ስትል ሰማት።

«እ!» አለ ማንደፍሮ ድንግጥ ብሎ። ጆሮውን አሾልኮ ከእፏ ላይ ያደረሰው ይመስል በተዳዳው ላይ ለተመው። ሸዋዬ ልፍለፋዋን አሁንም ቀጠለች። በዚህ ጊዜ እንዲያውም የወንድ ወሲባዊ ድምፅ ጎረምረምረም ሲል ተሰማው። እየሆነ ያለው ነገር በትክክል ገባው።

ማንደፍሮ ልክ ከርቀት የሚጣራ ይመስል ድምፁን ከፍ አድርጎ «አንቺ!» ሲል ጮኸ። «ምን እየሰራሽ ነው በይ!?» አለና በዚያ በፈረጠመ ክንዱ ያን መዝጊያ ጓ! ጓ! ጓ! ጓ... ያደርገው ጀመር። ወዲያው ድምፅ ቆመ። መብራትም ጠፋ። ማንደፍሮ አሁንም በጩኸት ድምፅ «የትም አታመልጪ! እንደ መብራቱ አንችም ትጠፊያለሽ! በማንዴ ምትክ ያመጣሽው ባርኒም ዛሬ ይለይለታል!!» ካለ በኋላ አሁንም በሩን ጓ! ጓ! ጓ! እያደረገ «ክፈች! ክፈች! ክፈች!» እያለ ይጮኽ ጀመር። መልስ አጣ። መዝጊያውን ለመስበር ከማጠፊያው በኩል በእግሩም በእጁም መውገሩን ቀጠለ። ምናልባት ለእሱ አይታወቀው እንጂ ድምፁም ሆነ የበሩ ምት ጩኸት እስከ ውጭ ድረስ ይሰማል። ወይዘሮ ዘነቡና ሠራተኞቻቸው በጓሮ በር

ሙሉ ብቅ ብቅ ብለው ሁኔታውን ይመለከታሉ። ድምፅ ግን ቶሎ አላሰሙም፣ አሁንም ግን በተለይ ወይዘሮ ዘነቡ የቤታቸውም ደህንነት አስግቷቸው ሰራተኞቸው እንዳትል ሳያሊት አልቀሩም፣ ፋንትዬም ድምጿን ከፍ አድርጋ «እርርሪ» ብላ ጮኸች።

ማንደፍሮ በር መውገሩን ቀጥሏል። ከተደጋጋሚ ምት በኋላ የመዝጊያው ማጠፊያዎች ሁሉቱም ተንቀሉ። እልከፊት ወይም አልወድቅ አለው። ስካ ባርናባስ ከውስጥ ወደ ውጭ ጎትሮ ይዞበት ኖሯል። ለማንደፍሮም ምስጢሩ ገባው። ብቻ ጉልበቱን ተጠለ። ያ መዝጊያ ከውስጥና ከውጭ እየተገፋ ወዲያ ወዲህ በመዋለል ምላሱን አየ። ሁሉቱም ሀይላቸውን ለማጠናከር «እምምም...» ይተረመረማሉ። ባርናባስ ከውስጥ «እምምም...» ማንደፍሮ ከውጭ «እምምም...» እያሉ ትግሉ ቀጠለ። ማንደፍሮ ለመግደል፣ ባርናባስ ለመትረፍ።

የኋላ ኋላ ግን ባርናባስ ደክሞ ኖሯል። የጀርባው ላብ በመቀመጫው ፍንክት መሀል ሲንቆረቆር ተሰምቶታል። በትንፋሽ ብዛት ልቡም ልትፈነዳ ደርሳለች። ሸንቱም አምልጦታል። በዚህ ጊዜ መረታቱን አውቆ መዝጊያውን ትቶ ወደ አንድ በኩል ሸሸት ሲል ያለ የሌለ ሀይሉን ተጠቅሞ ይገፋ የነበረው ማንደፍሮ ወደ ውስጥ ተወርውሮ መሀል ወለሉ ላይ በደረቱ እርርረ...ብ አለ። በአፍጢሙ ተደፋ። እሱ ተድሞ ወለሉ ላይ ከተዘረጋ በኋላ በሀይል ሚዛን መዛባት ምክንያት ተንገጫግጮ የነበረው መዝጊያ ከላዩ ላይ ዞሮ ተጫነው።

ባርናባስ ይህን አጋጣሚ በመጠቀም ማንደፍሮን በተኛበት ላይ ለማዳከም አልቻለም። ፓንቱና ካኔትራውን እንዲሁም ጫማውን ጨምሮ ወንበር ላይ አስቀምጦት የነበረ ልብሱን በሙሉ በአንድ ላይ በሁለት እጆቹ እፍስ አድርጎ ደረቱ ላይ በመታቀፍ ማንደፍሮንና መዝጊያውን ተረማምዶ ከላይ እስከ ታች እርቃኑን እንደሆነ ወደ ውጭ ሮጠ። ከሙሉ ጨረቃ በሚፈልቀው ብርሃን ያን ቀይ ሰውነቱን እያብረቀረቀ ሲሮጥ ጩኸትና እሪታውን ሰምቶ ወደ ወይዘሮ ዘነቡ ግቢ ይጎርፍ የነበረው ሕዝብ «እብድ! እብድ! እብድ!» እያለ መንገድ ለቀቀለት። በርካቶች ከኋላ ለመከተል ቀልቀል ወደ እሮሬጣ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ሸመጠጠ።

ማንደፍሮ ከወደቀበት እንደ ምንም ተነስቶ መብራት ሲያበራ መጀመሪያ ያየው የተመሰቃቀለ አልጋውን ነው። ቆጨው። ወደ ውጭ ያመለጠ ሰው እንዳለ ተሰምቶታል። ግን ሊደርስበት እንደማይችል ገመተና ወደ ጓዳ እየት ሲያደርግ ሸዋዬ ርቃኗን እንስራ መስላ ከዕቃ መደርደሪያው ሥር ሽጉጥ ብላ አገኛት።

«ባርኒ?» አለችው ሸዋዬ በልመና ዓይነት እጆቿን በደረቷ ላይ ልጥፍ አድርጋ በመከራመት። በእሷ ቤት 'ማንዴ' ማለቷ ነበር። ደንግጣለችና ተሳሳተች።

«አይደለሁም!» አላት ማንደፍሮ በፈገግ እንጋገር።

«ብእናትህ ይገርሃለሁ»

«ባርኒ ሆኖ ቢሆን ይምርሽ ነበር! እኔ ግን ማንዴ ነኝ» አለና «እንዳትንቀሳቀሽ!» ሲል አስጠንቀቃትና ከኋላዋ በኩል ሆረና ቅልጥሟን፣ ጭኗንና ወገቧን አንድ ጋር አጣብቆ በመታቀፍ ብድግ አድርጎ እንደገና ወደ መሬት ወርውሮ እን...ዘጭ! አደረጋት።

ሸዋዬ ለአንዴ «አአአ...» ብላ ጮኸችና «ማንዴ ልተረተር እኮ ነው!» አለችው።

«የእኔስ ልፋት ለምንድን ነው? እንድትስነጣጠቱ አይደል!» አለና እንደገና ብድግ አድርጎ በሀይል ወረወረና ከግድግዳው ጋር ሲያላትማት አጠቃላይ ቤቱ ግውው የሚል ድምፅ አሰማ። ያቺ ሰርቪስ ቤት ከዳር እስከዳር ተንቃነቀች። ማገደፍር ደገመና ሸዋዬን ከጠደቀችበት አንስቶ እንደገና ከዕቃ መደርደሪያው ላይ ወርውሮ ሲያላትማት ራሱ የገዛቸው ብርጭቆዎችና ሸክላ ሳህኖች በሙሉ ክሽክሽክሽ...አሉና አመድ ሆኑ። ቤቱም እንደገና ተንቃነቀ።

«ኧረ ቤቴን! ኧረ ቤቴን! ያገር ያለህ!» የሚል ድምፅ ከውጭ ተሰማ፤ የወይዘሮ ዘነቡ ድምጽ። ሰው ሁሉ በር ላይ ተኮልኩሎ ይመለከታል። አንዳንዱ ይጮሀል፤ ጉብዙ ለመገላገል ግን ሁሉም ፈርቷል። ብቻ «ገደላት! ገደላት!» ይላል። ማገደፍር ሁሉንም ከቁብ አይቆጥረውም። የሸዋዬን እጅ ጥምዝዝ አደረገና ወገቧን ወደ ላይ አዙሮ በዘርጉ ሲደስቃት «ኣኣኣ ....» አለችና መሬት ላይ ተዘረጋች።

ከዚያ በኋላ ግን አልነሳ አለችው። ታግላ አሸንፋው አልነበረም፣ ከመድከሟ የተነሳ ሰውነቷ ስለተዝለፈለፈ ክብደቷ ጨመረበት። የእልሁን ያህል ወለል ላይ የተጋደመ ፊቷን በጫማው ረግጦ ድፍጥጥጥ ካደረጋት በኋላ እዚያው እንደተዘረረች ትቷት ወደ በር አመራ።

«ዘወር በል!» አለ ማገደፍር በር ላይ ተኮልኩሎ ሁኔታውን ይመለከት የነበረን ሰው ሁሉ። ሳሎን ውስጥ መግባት የጀመሩትም በር ላይ የተኮለኮሉትም ሰዎች ግርር.... ብለው ወደ ውጭ ወጡ።

ማገደፍር ግቢ ውስጥ እየተጧጧኸ ይርመሰመስ በነበረው ሕዝብ መሀል እየተራመደ «ማገደፍር ገና ዛሬ ተደፈረ! ተደፈረ! ተደፈረ!» ካለ በኋላ «ዋይ-ዋይ-ዋይ....» እያለ ከግቢ ውጭ ወጣ። ግራ ቀኝ ሳይመለከት ቀጥታ ወደ ከተማ ሄደ።

ያ በወይዘሮ ዘነቡ ግቢ ውስጥ ይተረማመስ የነበረ ሕዝብ ሁሉ እየተጋፋ ወደ ሸዋዬ ቤት ገባ። ርቃን ሥጋዋን ወለል ላይ ተጋድማ ስታለከልክ ላያት ሁሉ የምትተርፍ አትመስልም ነበር። የወሳንሳ ተሸክመው አልጋዋ ላይ አጋደሟት። ወይዘሮ ዘነቡ ከፊቷ ቆመው «ኧረ እስቲ ውሃ! ኧረ እስቲ ውሃ!» እያሉ ጮሁ። ውሃ በፍጥነት ተረበሳቸውና በአፍና በአፍንጫዋ ይወርድ የነበረ ደሟን ሲያጥቡ በነበረበት ወቅት ድንገት ሳትታሰብ ሐዋን ከተፍ አለች። በትርምስምሱ ደንግጣ እንዳልነበረ ሁሉ ጭራሽ ወደ ቤት ገብታ የሸዋዬን ሁኔታ ስታይ የባሰ በመረበሽ «ወይኔ ጉዴ! እትአበባ ምንድነው? እታበባ ምንድነው?» እያለች በድንጋጤ ትርገበገብ ጀመር።

በዚች ሰዓት ሸዋዬ በሌባ ጣቷ ወደ ሐዋን እየመለከተች ድክምክም ባለ ድምጿ «ያዙል...ኝ! ይቺን ሰው ያዙል...ኝ! ጎረምሳዋን ቤቴ ውስጥ ደብቃ ያስገደለችኝ እሷ ና...ት! ያዙል...ኝ!» እያለች ጥሪ ታስተላልፍ ጀመር።

ሐዋን ከው ብላ ደነገጠች። በአካባቢው የነበሩትን ሰዎች እየት እየት እያረገች ወደኋላዋ ታፈገፍግ ጀመር። ከሐዋን የበለጠ በውሃ ያጥቧት የነበሩት ወይዘሮ ዘነቡ ከመደንገጥ በተጨማሪ ንድድ አላቸውና:

«አ! ምን እያልሽ ነው አንቺ?» አሏት በቁጣ።

ሸዋዬ ግን አሁንም «ያዙል...ኝ! እሷ ናት ያስገደለች...ኝ! ያዙል...ኝ!» ማለቷን ቀጠለች።

ሐዋን ጉዳዩ ስላልገባት ይበልጥ እየደነገጠች ሄደች። ከቤት ወጣችና ግቢ ውስጥ ቆም ብላ ስታዳምጥ ሸዋዬ አሁንም ያዙልኝ እያለች ስትናገር ስትሰማ

[illegible] ከግቢም ወደ ውጭ ወጣች። ደግነቱ ማንም ሲይዛት አልቃጣም። እሷ ግን [illegible] ፈርታ ገልመጥ ገልመጥ እያለች በቀጥታ ወደ ታፈሡ ቤት ገሰገሰች።

ወይዘሮ ዘነቡ ጎዶ.ታቸው ባለ፡፡ ያጥቧት የነበረውን ትውት አደረጉና ወደ [illegible] እየተራመዱ በሁኔታው ለተሰበሰበው ሕዝብ በሚሰማ ድምፅ-

«ጎረቤቶቼ የሆናችሁ፣ ወገኖቼ የሆናችሁ ሁሉ፣ ይቺን መዘዘኛ ሴት [illegible] ከቤቴ አውጡልኝ! ቶሎ በሉ ዕቃዎን አውጡልኝ! ቶሎ በሉ! ለእናቷ ልጅ [illegible] ያልሆነች ነገ ለእኔም አትመለስ። ቀጣፊ ናት! ወስላታ ናት! የተረገመች!!» [illegible] ከዚያች ዕለት እንኳ ቢሰሙኝ አሻፈረኝ አሉ። በአካባቢው [illegible] ናቸውና ልመናቸው ተከበረ።

[illegible] በርካታ ወጣቶች ስለነበሩ የሸዋዬን ዕቃ አንድ ባንድ እያስቀሙ [illegible] ማውጣት ጀመሩ። ተባባሪው በርካታ ስለነበር የሸዋዬን ዕቃ የማውጣት [illegible] አላቆየም። ሁሉም ከአጥር ውጪ ወጣ። ወይዘሮ እልፍኝ ዕቃዎን [illegible] በመፍቀዳቸው ከእሳቸው ግቢ ውስጥ እየገባ ተቆለለ። ራሷ ሸዋዬም [illegible] ተይዛ ወደ እሳቸው ቤት ተወሰደች።

[illegible] ገትዝት የዶሮ ሽክም፣ እንዲሉ የሐዋንና የእስቻለውን ፍቅር አፍርሳ [illegible] ቤት ልትገነባ ደፋ ቀና ስትል የነበረች ሸዋዬ ህልሟ ሁሉ ከንቱ ሆነ። [illegible] የውሽት ቤት ነበርና እነሆ በአንድ ቀን ፈረሰ!!

ምዕራፍ አሥራ አራት

ከሶስት ወራት በኋላ ነው፤ የጥር እና የየካቲት ወራት መጋጠሚያ ሳምንት። ‹ብደንባሪ በቅሎ...› እንዲሉ ወትሮም ግርግር የማይለያት ዲላ ከተማ ሰሞኑን ደግሞ በባሰ ድንግርግር ውስጥ ሰንብታለች። የክፍለ ሀገሩ ስፖርት ሻምፒዮና ሲካሄድባት ሰንብቷል። ከመላ የሲዳሞ ክፍለ ሀገር በርካታ ስፖርተኞች መጥተው ይርመሰመሱባታል። በተለይ በፌስቲቫሉ ማጠናቀቂያ ቀናት ስፖርተኞች በቡድን በቡድን እየሆኑ የመደባደብ አዝማሚያ ስለጀመሩ የፀጥታ ጥበቃውም በዚያው ልክ ተጠናክሯል። በከተማዋ ውስጥ ያሉ ፖሊሶችና ሌሎች አጋዥ የፀጥታ ሀይሎች በተጠንቀቅ ሆነው የከተማዋን ፀጥታ ይጠብቃሉ።

ልክ ሻምፒዮናው በተጠናቀቀበት ቀን ከምሽቱ ሦስት ሰዓት አካባቢ የተፈራው ሁከት የተነሳ መሰለ። ከአንደኛ መንገድ በላይ ወደ አውራጃው አስተዳደር ፅህፈት ቤት መሄጃ አካባቢ ድንገት የእሪታና ኡኡታ ድምፅ ተሰማ። ወዲያው ደግሞ አንድ ጥይት ተተኮሰ። በርካታ የፀጥታ ሀይሎች ወደ አካባቢው መሮጥ ጀመሩ። ስፖርተኞች የተባሉ የመሰለው ህዝብና ሌሎች ስፖርተኞችም ወደዚያው ይጎርፉ ጀመር፤ ለዚያውም በሩጫና በጫጫታ ታጅበው።

በርካታ ሰው ከቦታው ሲደርስ ግን የጠቡ ዓይነትና መነሻው የተለየ ሆኖ ተገኘ፤ የተባሉት ስፖርተኞች ያልሆኑ ሁለት ሰዎች ናቸው። መነሻው በአንዲት ሴት ምክንያት መሆኑ ይወራል። ሰዎቹ ለድብድብ መጋበዛቸውን እንደ ቀጠሉ ናቸው። አንዲት በዕድሜ ጠና ያሉ ሴት ደግሞ ከአንድ ቤት በር ላይ ቆመው ይለፈልፋሉ። «ይቺ ነውረኛ! እኔ ደግሞ ደህና ሰው መስላኝ! ‹አንገት ደፊ አገር አጥፊ› አሉ! ሆሆይ! የድሀ ቤቱን ሊታስፈርሰው!» ይላሉ። ከሴትዮዋ አነጋገር በመነሳት አንድ ፖሊስ ጠጋ አላቸውና «ምንድነው ችግሩ የኔ እናት?» ሲል ጠየቃቸው።

«አረ በገዛ እጄ ጎትቼ ያመጣሁት ችግር ነው ልጄ! ከሁለት ወር በፊት ሳይሆን አይቀርም፤ አንዲት ሴትዮ መጥታ ቤት አከራይኝ ብላ መጣች። እኔ ደሞ ጨዋ መስላኝ አከራየኋት። ለካ ጋለሞታ ኖራ ይኸው ሁለት ወንዶችን በአንድ ጊዜ ቀጥራ ሰው ታፋጀለች።» አሉት እንደ እንዝርት በሚሾር ምላሳቸው እየተንጣጡ።

«ጋለሞታዋ የታለች?» ሲል ጠየቃቸው ፖሊሱ።

«ጋለሞታዋ የታለች?» ... ሴትዮዋ ከቆሙበት ቤት በታች ቀጥሎ ያለውን ክፍል በእጃቸው እየጠቆሙ «እዚህ ቤት ውስጥ ናት። ስራዋ አሳፍሯት ሳይሆን አይቀርም ቤት ዘግታ ትንፋረቅልሀለች።» አሉት። ፖሊሱ ወደ ተጠቆመው ቤት በር ጠጋ አለና እያንኳኳ

«ክፈች አንቺ!» አለ።

«እምቢ! አንከፍትም!» የሚል ምላሽ ከውስጥ ተሰጠው።

«ነገርኩሽ ብቻ! ፖሊስ ነኝ፤ ክፈች!»

«ነገርኩሽ ብቻ! ...» ሁለት ሴቶች ቆመው ያለቅሳሉ። ፖሊሱ በር ላይ ቆሞ ወደ ውስጥ እያየ «ማንኛሽ ነሽ ጋለሞታዋ?» ሲል ጠየቀ። በሩ ተከፈተ።

«እዚህ ጋለሞታ የለም» አለች ከሁለቱ አንዷ። ሌላዋ አሁንም አጎንብሳ ታለቅሳለች። እኒያ ለፍላፊዋ ሴትዮ ፖሊሱን ተከትለው ወደ በሩ ጠጋ ብለው ያዩ ነበርና ለፖሊሱ በእጃቸው እየጠቆሙ፡ «ይቺ አጎንብሳ የምትነፋረቀው ናት።» ካሉ በኋላ ወደ ኋላ መለስ እያሉ፡ «ይቺን ሁለት እጆቿን የማትረባ የቆንጆ በለል!»

የጥሏን እስር አርባ መግረፍ ነበር እንጂ...» እያሉ ወደ መጡበት አትጣጫ ተመለሱ። ሕዝቡ ከዚያም ከዚህም እየጎረፈ አካባቢው በመደበላለቅ ላይ ነው። ፖሊስ የተጠቆመችውን ጋለሞታ በቁጣ።

«ነይ ውጪ» አላት በር ላይ እንደ ቆመ።

«ለምን?» አለችው በፍርሀት እየተንቀጠቀጠች።

ፖሊሱ እንደ መናደድ አለና ገባ ብሎ በሀይለኛ ጥፊ እንዷ አጮላት። እንደገና ከኋላዋ ዞሮ ወደ በሩ ይገፈትራት ጀመር። የቤቱን በር ወጣ እንዳለች ፖሊሱ አሁንም በሀይለኛ እርግጫ መቀመጫዋ ላይ ሲያላርፍባት ወደ ላይ ነጥራ መሬት ላይ ተዘረጋች። «ወየው እኔ...!» ብላም ጮኸች።

«ስልደግምሽ ተነሽ!» ሲል ጮኸባት ፖሊሱ።

ተግተርትራ ተነሳች።

ለድብድብ ይጋበዙ የነበሩት ወንዶች ስብን ብለው ቆመው ስለነበር ጋለሞታዋ ከእነሱ ጋር እንድትቀላቀል ተደረገችና ገቢ ወደ ፖሊስ ጣቢያ ተጀመረ።

ታሳሪዎቹ ወደ ፖሊስ ጣቢያ ሲጓዙ በነበረበት ሰዓት አጀባቸው ይጓዝ የነበረ የሕዝብ ብዛት ሲታይ እውቅና ድንቅ ሽፍታ የተያዘ ይመስላል። ተጣዮቹ ስፖርተኞች አለመሆናቸው ቢታወቅም የአደባዳቢዎቹንና የተደባዳቢዎችን ማንነት ለማወቅ የነበረው እሽቅድምድምና ግፊያ ያስገርማል። ፖሊሶቹ ሕዝቡን ለማባረር ይሞክራሉ፤ ግን አልሆነላቸውም። ግፊያና ግርግሩ እንዲሁም ጫጫታው እንደቀጠለ ፖሊስ ጣቢያ ተደረሰና ታሳሪዎቹ እስር ቤት ሲገቡ ሁኔታዎች ቀስ በቀስ እየረገቡ ሄዱ።

ከጋለሞታዋ ጋር የነበረችው ልጅ ብቻ ከፖሊስ ጣቢያ በር ላይ ቀረች። ለትሰማን ታቀልጠዋለች። ቀኝ እጇን ግንባሯ ላይ አስደግፋ ትንሰቀሰቃለች።

«ምንድነሽ አንቺ?» ሲል አንድ ፖሊስ ጠየቃት።

«እህቱ እኮ ምንም አላደረገችውም።» አለችው አሁንም እያለቀሰች።

«ዝም ብለሽ ቅድም ትዬጃለሽ አትሄጂም?» አለና ፖሊሱ ሊመታት ጠጋ ሲል ልጅቱ ወደ ኋላዋ ሮጠች።

«ብይ በቀጥታ ወደ ቤትሽ! ቶሎ በይ!» ሲልም ጮኸባት።

ልጅቱ አማራጭ አልነበራትም፤ እያለቀሰች ወደ ቤቷ ተመለሰች።

በንጋታው ጠዋት ከመንበሩ ላይ የተሰየመው መርማሪ ፖሊስ የሌሊቱን የዕለት ሁኔታ መዝገብ ሲመለከት በርካታ ገጠመኞች ተመዝግበዋል። ከተራ ሌብነት ጀምሮ በስካር መንፈስ ጠብ የፈጠሩ፣ ለድብድብ የደሉቱ ስፖርተኞች፣ ሚስቱን የደበደበ ባል.... ወዘተ ይገኙበታል። ከዚያ ሁሉ የቀደመው ግን በአንዲት ሴት ምክንያት ሁከት የፈጠሩ ሰዎችና ሴትዮዋም ጭምር መታሰራቸውን የሚገልፀው ሪፖርት ነው። መርማሪው ፖሊስ በዚያው ቅደም ተከተል ስራውን ለማካሄድ ወረቀትና እስኪርቢቶውን አዘጋጅቶ የዕለቱን ረዳት ፖሊስ በጠረጴዛ ደወል ጠራ። ረዳት ፖሊሱ ወዲያው ቀረበ።

«እስቲ ዓለሙ መርጋ የሚባል እስረኛ አምጣልኝ።» አለው።

ረዳቱ ፖሊስ ወደኋላው ተመለሰና ዓለሙ መርጋን ከእስር ቤት በማምጣት ለምርመራ አቀረበው።

ዓለሙ ደንቦሸቦሽ ባለ ጠይም ፊቱ ላይ ክብ ዓይኖቹ የሚቁለጨለጩ ልጅ እግር ሰው ነው። ዕድሜው ከሰላሳ የሚዘለው አይመስልም። ነጣ ያለ ሸሚዝና ጥቁር ሱሪ ለብሷል።

መርማሪው ፖሊስ እንደተለመደው የተመርማሪውን ስም፣ ዕድሜ፣ አድራሻ፣ የሥራ ሁኔታ ጠይቆ ከመዘገበ በኋላ ወደ ዋናው የምርመራ ሥራ ገባ።

«ከመብራቱ ባዩ ጋር ምን አጣላህ?» ሲል ጠየቀው።

«በማይረባ ነገር ነው ጌታዬ!» አለ ዓለሙ መርማሪውን ፖሊስ በፍርሀት ዓይን እየተመለከተ።

«እንዴት ማለት?» አለው መርማሪው ፖሊስ።

«ሰው እንዴት በሴት ይጣላል?» አለ ዓለሙ እጆቹን በጉልበቶቹ ውስጥ አጣብቆ በመያዝ ዓይኖቹን በመርማሪው ፖሊስ ላይ እያቁለጨለጨ።

«ታዲያ አንተ ለምን ተጣላህ?» ሲል መርማሪው ፖሊስ ፈገግ በማለት ዓለሙን ጠየቀው።

መርማሪው ፖሊስ አሳ የመሰለ የጠይም ቆንጆ ነው፤ አፍንጫው ስልክክ ያለ ፀጉረ ለማ፣ የአሞራ ቅድ ቅርፅ ያላቸው ትላልቅ ዓይኖቹ ውትት ከመሰሉ ነጫጭ ጥርሶቹ ጋር ሲታዩ ውበቱን ያጎሉታል። ግርማ ሞገሱ ግጥም ያለና ዕድሜው በአርባዎቹ አጋማሽ የደረሰ የሚመስል ነው።

«ለነገሩ እልህ ይዞኝ ነው። ልጅቷን ከሁለትና ሦስት ወር በፊት አውቃታለሁ። ጥሩ ወዳጅነትም መስርተናል። እንደ ወትሮው መስሎኝ ከእሷ ጋር ላድር ወደ ቤቷ ጎራ ስል ቀድሞ ገብቶ ኖሮ ‹አትገባም› ብሎ ገፍትሮ ሊያስወጣኝ ሲል በዚያው ተያያዝን።» አለው ዘርዘር ባለ ሁኔታ።

«ሰውየውን ካሁን በፊት ታውቀው ነበር?»

«ኧረ የት ብዬ!»

መርማሪው ፖሊስ የዓለሙን ቃል መዝግቦ ካስፈረመው በኋላ «በል ሂድ! ምናልባት ካስፈለገ ሌላ ጊዜ ትጠራለህ።» አለው።

«ወደ ቤቴ?» ሲል ጠየቀ ዓለሙ።

«ወደ እስር ቤት ነው እንጂ! የምትለቀቀውማ እንደ ነገሩ ሁኔታ ዋስ ጠርተህ ነው።» አለው መርማሪው ፖሊስ፤ ነገሩ የዕለት ግጭት በመሆኑ ብዙም ርቀት በማይሄድ ምርመራ እንደሚጠናቀቅ መርማሪው ያስባል። የጠረጴዛ ደወል አቃጨለና ረዳቱ ፖሊስ ሲቀርብለት ዓለሙን ወስዶ መብራቱ ባዩ የተባለ ሌላ እስረኛ እንዲያቀርብለት አዘዘው።

ረዳቱም የተባለውን ፈፀመ።

መብራቱ ባዩም በዕድሜው ብዙ አልገፋም ፤ ከሠላሳ ብዙ አያልፈውም። ቀጠን ያለ ቀይ ዳማ ቢጤ ነው። መካከለኛ ቁመት አለው። ፀጉሩ አጠር፣ ከወደ አፉ ሞጥሞጥ፣ ዓይኖቹ አነስ አነስ ያሉ ናቸው። እሱም በተመርማሪ ወንበር ላይ ተቀምጦ መርማሪውን በፍርሀት ይመለከተው ጀመር።

መርማሪው ፖሊስ ልክ በዓለሙ ላይ እንዳደረገው ሁሉ መብራቱን መሠረታዊ መረጃዎችን እየጠየቀ ከመዘገበ በኋላ፡ «ከዓለሙ መርጋ ጋር ከአሁን በፊት ትተዋወቃላችሁ?» ሲል በቅድሚያ ጠየቀው።

«አይቸውም አላውቅ።»

«ምን አጣላችሁ ታዲያ?»

«እኔ ቀድሜ ገብቼ ባለሁበት ቤት መጥቶ ካልወጣህ ብሎ ሲያስገድደኝ ምክሬ፣ 'አልወጣም' ስለው በተቀመጥኩበት በጥፊ አቃጠለኝ። ከዚያ በኋላ ነው በርመ ነፍስ እጆቹን ይገፍ ድረሱልኝ ብዬ የጮኩት።» አለው ዓይኖቹን እያቁለጨለጨ።

«በተጣላችሁበት ቤት ውስጥ ለምን ነበር ቀድመህ የገባኸው?»

«ቤቴ ነዋ!»

«ቤቴ ስትል? ሴትዮዋ ሚስትህ ናት?»

«ቤቱ እንደ ሚስቴ ናት።»

«ለምን ያህል ጊዜ አብራችሁ ቆይታችኋል?»

«ኧረ ብዙ ነው።»

«እስኪ በግምት?»

«ከአሥራ አምስት ቀን በላይ አብረን አድረናል። ግን በተከታታይ አይደለም፣ አልፎ አልፎ ነው። ከተዋወቅን ግን ቆይተናል።»

«ወዳጅህ ስሟ ማን ይባላል?»

«ስሟ?» አለና መብራቱ ወደ ጣሪያ አንጋጠጠ። ግን ጠፋበት። ለማሰላሰል ሞከረና ሲያቅተው «ረሳሁት።» አለ የድንጋጤ ስሜት እየተነበበበት።

«አሥራ አምስት ቀን ሙሉ የአቀፍካት ወዳጅህን?» በማለት መርማሪው እየተገረመ ጠየቀው።

«ድንገት ስለሆነ የተገናኘነው ስሟ ይረሳኛል።»

መርማሪው ፖሊስ ጥርጣሬ ገባውና መብራቱን ትኩር ብሎ ተመለከተው። መብራቱ የበለጠ የእፍረትና የድንጋጤ ስሜት ይነበብበት ጀመር።

«ዋሽተሃል አይደል?» አለው መርማሪው በትኩረት እየተመለከተው።

«አጥፍቻለሁ ጌታዬ!» አለ መብራቱ ሽቁጥቁጥ እያለ።

የመርማሪው ፖሊስ ልብ አሁንም እየተጠራጠረ ሄደ። ሆኖም ቃል በማበት ወረቀት ላይ ከአስፈረመው በኋላ «የአንተንና የዓለሙን ጉዳይ በቀላሉ ላልፈው አስቤ ነበር። ነገር ግን ተጠራጥሬአለሁ። የሁለታችሁንም ጉዳይ እንደገና ሳላየው አልቀርም።» አለና ወደ እስር ቤት እንዲሄድ አሰናበተው።

የመርማሪው ፖሊስ ጥርጣሬ ቀላል አልነበረም። ዓለሙንም በሚጠይቅበት ወቅት ያየው የነበሩ ሁኔታዎች እንደገና ትዝ አሉት። በስካር መንፈስ በአንዲት ቤተኛ አዳሪ የተጣሉ መስለውት በእርግጥም ዋስ እያስጠራ በቀላሉ ሊለቃቸው ነበር አስቦ። አሁን ግን በጉዳዩ ላይ ጠለቅ ያለ ምርመራ ሊያደርግ ወሰነ። ‹ለማንኛውም፣ አለ በሆዱ 'እስቲ ጋለሞታ የተባለችው ሴት ሌላ አጠራጣሪ ፍንጭ የምታመጣ ከሆነ በቅድሚያ እሷን ላነጋግራት።' አለና በረዳቱ ፖሊስ እንድትጠራ አደረገ።

ጋለሞታዋ ተጠርታ ወደ መርማሪው ፖሊስ ቢሮ በር ላይ ስትደርስ ሁለመናዋ በፍርሀት ይንቀጠቀጣል። እንባዋ ከዓይኗ ላይ እንደ በረዶ ይረግፋል። መልኳ ደግሞ ይህ ቀረሽ የማትባል ውብ ናት። ዓይኖቿ እንደ ንጋት ኮከብ ያበራሉ። በዕድሜዋ ገና ወጣት ልጃገረድ ትመስላለች። 'ጋለሞታ' ለሚለው የሴትነት መገለጫ አንዳች አመልካች ነገር አይታይባትም። ከንፈሮቿ እምቦጦች ይመስላሉ። የአፍንጫዋ አቀማመጥ ለቁንጥ የተሰራ ይመስላል። የቀይና ነጭ ቡራቡሬ ድሪያ ለብሳ በጡቶቿ ተገትሮ የአንገቷን ድራሽ አጥፍቶታል። ከመርማሪው ቢሮ በር ላይ ደርሳ ምን እንደምትባል ትዕዛዝ እየጠበቀች ሳለች መርማሪው ፖሊስ ግን ይህንን ገፅታዋን ሲያይ ድንገት ተዝናግቶ ኖሮ 'ፐ! ይቺስ

ታደብድባለች፣ አለ በሆዱ። ወዲያው ደግሞ «ምን ያስለቅስሻል?» ሲል ፈገግ ብሎ ጠየቃት ሁኔታዋ ሁሉ እያስገረመው። ‹ግቢ! ቁጭ በይ› ማለቱን እንኳ እረሳው።

«ፈርቼ?» አለችው እንደተርበተበተች።

«የሰራሽው ስራ አሳፈረሽ?»

«ኧረ እኔ ምንም አልሰራሁም!»

«እስቲ ግቢና ቁጭ በይ!» አላት በእጁ አገጩን ያዝ አድርጎ አሁንም በትኩረት እየተመለከታት። ገለምታዋ ቁጭ አለችና አሁንም በፍርሀት ስሜት አቀርቅራ መሬት መሬት ታይ ጀመር።

«ምን አድርገሽ ነው የታሰርሽው?» ሲል ጠየቃት መርማሪው ፖሊስ ቀለ አያለ ሊያግባባት ፈልጎ።

«ምንም!» አለችና ለቅፅበት ያህል ቀና ብላ አየችው።

«ባለሙያና መብራቱን የት ነው የምታውቂያቸው?»

«እነማናቸው እነሱ?» አለች አሁንም። ለቅፅበት ያህል ቀና ብላ አይታው እንደገና አንገቷን ደፋች።

«ጭራሽ አታውቂያቸውም?»

«ኧረ እኔ እንደዚህ የሚባሉ ሰዎች አላውቅም።»

«ሁለቱም ወዳጆችሽ ናት እያሉ እኮ ነው።» አለና መርማሪው ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ ለምላሿ ጓጉቶ ይጠባበቃት ጀመር።

«ኣ!» አለችና አሁንም ቀና ብላ አየት አረገችው።

«ከማናቸውም ጋር አብረሽ አድረሽ አታውቂም?»

«እኔ ከወንድ ጋር ተኝቼ አላውቅም።»

«አንድም ቀን?»

«አንድ ቀን ብቻ ከምወደው ሰው ጋር አድሬ አውቃለሁ። ግን ከንፈሬን ስምቶል እንጂ ሌላ ምንም አላደረገኝም።»

«ማነው እሱ ደግሞ?» ሲል ጠየቃት መርማሪው።

«እሱ እዚህ አገር የለም! ኤርትራ እሚባል አገር ከሄደ ቆይቷል።»

«እ?» አለ መርማሪው ፖሊስ አንዳች የማያውቀው ስሜት መላ ሰውነቱን ድንገት ውርር እያረገው። «ማን ይባላል?» ሲል እንደገና ጠየቃት።»

«አስቻለው ፍሰሀ።»

«አስቻለው ፍሰሀ ?» ሲል ደግሞ ጠየቃት።

«አዎ።» አለችውና እሷም ድንግጥ ብላ ቀና ብላ ታየው ጀመር።

«እንዴ!» አለና መርማሪው እንደገና አትኩሮ ያያት ጀመር። ስሜቱ እያደር ተለዋወጠ። «አንቺ ስምሽ ማን ይባላል?» ሲል ጠየቃት የምትሰጠው መልስ ቀድሞ እያስፈራው።

«ሒሩት ተስፋዬ።»

«ምን?» ሰምቶ እንዳልሰማ።

«ሒሩት ተስፋዬ እባላለሁ።»

መርማሪው ፖሊስ ፍዝዝ ብሎ ቀረ። የያዘው እስኪርቢቶ ከእጁ ላይ ሾልኮ ሲወድቅ ፈጽሞ አልታወቀውም። ዲላ ከተማ እየኖረ ስለመሆኑ እንደ አዲስ ታወቀው። በሀሳብ ጥቅልል ብሎ አስመራ ከተማ ገባ።

መርማሪው ፖሊስ የሀምሣ አለቃ መኮንን ዳርጌ ይባላል። በሲዳሞ ክፍለ ሀገር በሀገረ ማሪያም ከተማ ተወልዶ ያደገ ነው። እዚያው በፖሊስነት ተቀጥሮ

እስከ ምክትል አ/ሥር አለቅነት የደረሰና እሱም እንደ አስቻለው ፍሰሀ የዘመቻ ግዳጅ ተመድቦበት ወደ ግንባር ዘምቶ በኤርትራ ምዕራባዊ የጦር ግንባሮች ለተከታታይ ሦስት ዓመታት ሲዋጋ የቆየ ነው። በጦር ግንባር በፈጸመው ጀብዱ የሀምሣ አለቅነት ማዕረግ ካገኘ በኋላ በተጣይ የውጊያ ወቅት በደረሰበት ቁስለት የተዋጊነት ብቃቱ ቀንሶ ወደነበረበት የፖሊስ ሰራዊት አባልነቱ እንዲመለስ ተወስኖለት ወደ ሲዳሞ የተመለሰና በጌዴዎ ምደባ ዲላ ውስጥ በመርማሪነት እየሰራ ያለ ፖሊስ ነው።

ከሁለት ዓመት በፊት ወደ ሲዳሞ ሊመለስ በተነሳበት ወቅት በአስመራ ከተማ ለጥቂት ቀናት ቆይቶ ነበር። በእነዚያ ቀናት ውስጥ ከአንድ ቀደም ብሎ ከሚያውቀው የአስመራ ነዋሪ ከሆነ ሰው ጋር ‹ሰራዬ መናፈሻ› ተብላ በምትታወቅ ቡና ቤት ቀጠሮ ይይዛሉ። በቀጠሮ ቀን የሀምሣ አለቃ መኮንን ዳርጌ ከቀጠሮው ቦታ ቀድሞ ይደርሳል። ጓደኛውን ለመጠበቅ እዚያው ቡና ቤት ውስጥ ብቻውን ይቀመጣል።

እሱ በተቀመጠበት ጠረጴዛ ማዶ ብቻውን የተቀመጠ ሰው ከዓይኑ ይገባል። ያ ሰው የአካል ጉዳተኛ ነው። የግራ እግሩ ተቆርጦ ሰው ሰራሽ እግር ተተክቶለታል። ቀኝ እጁም እንዲሁ ከእምባር መዋያው በታች ተቆርጦ በፕላስቲክ ጣቶች የተተካ ነው። ከአጠገቡ ደግሞ ክራንች ግድግዳ ተደግፎ ቆሟል። የሰውዬው ፊት በእሳት የተለበለበ ይመስላል። ግራ ዓይኑም የጠፋች ያህል ሆናለች። ግራ ጆሮው በጉዳት ምክንያት የተሰጠፈች ስጋ እንጂ በእርግጥ ጆሮ አትመስልም። በዚሁ ላይ ውስጡም ሰላም ያለው አይመስልም። የሀምሣ አለቃ መኮንን ዳርጌ አትኩሮ ሲመለከተው ያ ሰው የሚያስብ የሚተክዝ ይመስለዋል። ፊቱ ቶሎ ቶሎ ይለዋወጣል። ብቻውን እንደሚያወራ ሁሉ ከንፈሮቹን ያንቃንቃል።

የሀምሣ አለቃ መኮንን ዳርጌ ያን ሰውዬ አከታትሎ እያየው ሳለ ያ የቀጠረው ሰው ድንገት ይመጣል። ያ አካል ጉዳተኛ ከበሩ ፊትለፊት ተቀምጦ ነበርና የሀምሣ አለቃው ጓደኛ ቡና ቤቱ ውስጥ እንደገባ በቀጥታ ወደ ጉዳተኛው ሰው በመሄድ ሰላም ይለዋል። ትንሽ ከተጠያየቁ በኋላ አዲስ መጪው ሰውየ ወደ ሀምሣ አለቃው ይመለሳል። እነሱም ሰላምታ ተለዋውጠው አብረው ቁጭ ይላሉ። መጠጥ አዝዘው መጠጣት ይጀምራሉ። በመሀል ሀምሣ አለቃው ስለዚያ አካል ጉዳተኛ ሰው ጓደኛውን ይጠይቀዋል።

«ያ ሰውየ ምን ሆኖ ነው? ከአካሉ መጎዳት በተጨማሪ ውስጡም ሰላም ያለው አይመስልም።» ሲል ጓደኛውን ይጠይቀዋል።

«እንደውም እኮ የአገርህ ሰው ነው።»

«የሲዳሞ?»

«አዎ፣ እንዳትው ለዘመቻ ተልኮ ነው የመጣው። በሙያው ሀኪም ነው። ጉዳት የደረሰበት ደግሞ በፈንጂ ነው፣ በአንድ ወቅት ያውም አስመራ ገብቶ ወር እንኳ ሳይሞላው በተንቀሳቃሽ ክሊኒክ ወደ አንድ የጦር ግንባር ከሌሎች የሥራ ባልደረቦቹ ጋር ሲሄድ።»

«ማን ይባላል?»

«ነርስ አስቻለው ፍሰሀ ይባላል።»

የሃምሣ አለቃ መኮንን ዳርጌ ከንፈሩን መጠጠና «ሳነጋግረው ይሆን?»

«በእናትህ እስቲ አነጋግረው።»

የሀምሣ አለቃ መኮንን ዳርጌ አላመነታም፤ ብድግ ብሎ ወደ እስቻለው ሄደ። እጁን ለሰላምታ እየዘረጋ «የሀምሣ አለቃ መኮንን ዳርጌ እባላለሁ።»

«እስቻለው ፍሰሀ» በማለት እስቻለውም ጨበጠው። የሀምሣ አለቃው ከእስቻለው አጠገብ ቁጭ እያለ «ይቅርታ እስቻለው፤ የሀገሬ ልጅ መሆንህን ለማረጋገጥ ፈልጌ ነው።» አለው

«የት አገር?»

«የሲዳሞ ልጅ አይደለህም?»

እስቻለው ትንሽ ፈገግ ብሎ መሬት መሬት ካየ በኋላ፤ «በእርግጥ ሲዳሞ ውስጥ አልወለድም። ነገር ግን ወደዚህ የመጣሁት ለሥራ ከሄድኩበት ከዲላ ሆስፒታል ነው።» ካለ በኋላ የሀምሣ አለቃውን ቀና ብሎ እያየ «አንተ ሲዳሞ የት ላይ ነህ?» ሲል ጠየቀው።

«ውልደቴም ዕድገቴም በሀገረ ማሪያም ከተማ ነው።»

«እእእ» አለና እስቻለው «በእርግጥም ዲላና ሀገረ ማርያም ቅርብ ለቅርብ ናቸው።» አለው።

«ወዲህ ከመጣህ ቆየህ?» ሲል የሀምሣ አለቃው ጠየቀው።

«አዎ፤ ቆየት አልኩ።»

«በግዳጅ እንደ መጣህ ሰማሁ። አልጨረስክም?»

«አሁንም በግዳጅ ላይ ነኝ።»

«መቼ ነው የምትጨርሰው?»

«ዕድሜ ልክ ሳይሆንብኝ አይቀርም።»

የሀምሣ አለቃው በእስቻለው መልስ ተጠራጠረና እየቀለደ ስለመሰለው ፈገግ እያለ «እንዴት?» ሲል ጠየቀው። ወዲያው ደግሞ አንድ አስተናጋጅ ጠራና ቀድሞ ከነበረበት ጠረጴዛ ላይ የጀመረውን የቢራ ጠርሙስ እንዲያመጣለት አዘዘው።

«ምነው ጓደኛህን ትተህ?» አለው እስቻለው ቀና ብሎ እያየው።

«ከሀገሬ ልጅ ጋር መጫወት ፈለኩ።» አለና የሀምሣ አለቃ «እስቲ ምናምን ውሰድ። ከነገ ወዲያ ወደ ሀገሬ ልመለስ ነውና የወጪ ልበልህ።» ሲል ጋበዘው።

«ይኸው! ጠጣሁ እኮ!» አለ እስቻለው ቀደም ሲል አጠገቡ የነበረ የለስላሳ ጠርሙስ እያሳየው።

«ሌላ ነገር፡

«ምንም አልጠጣም»

«ቢራ ጠጣ።»

«አልኮልማ ጭራሽ አልጠጣም። ሻይ ቡናም ቀድም ብዬ ጠጥቻለሁ። አመሰግናለሁ።» አለ እስቻለው በማከታተል።

የሀምሣ አለቃው ወደ ጨዋታው ተመለሰ። «ወደ ሲዳሞ የመመለስ ዕቅድ የለህም?» ሲል ጠየቀው።

«የለኝም»

«ለምን?»

«ቢታ ስላልፈለኩ ብቻ ነው»

«እስከ መጨረሻው?»

በዚህ ጊዜ እስቻለው ፊቱን ወደ ጣሪያ መለሰና ዓይኑን በኮርኒስ ላይ ሰካ። ፍዝዝ ትክዝ አለ። ደስ የማይል ስሜት በፊቱ ላይ መነበብ ጀመረ። በዚያው ልክ የሃምሣ አለቃውም በእስቻለው ሆድ ውስጥ የተቀበረ አንድ ነገር እንዳለ ገባውና፡-

«ችግር አለ እንዴ የኔ ወንድም?» ሲል ትኩር ብሎ እያየ ጠየቀው። እስቻለው ድንገት ወደ ቀልቡ እንደመመለስ አለና፣ «አይ አይ፤ ችግር የለም። ወደ ሲዳሞም በስተርጅና ዕድሜዬ ብቅ ማለት አስባለሁ።» ካለ በኋላ ወደ ሀምሣ አለቃው ቀና በማለት ፈገግ እያለ «ግን ደግሞ ከሀገሬ በፊት እኔ ቀድሜ ከአረጀሁ» አለው።

«አልገባኝም።»

«ምኑ?»

«የሀገር እርጅና።»

እስቻለው ወደ መሬት አቀረቀረና ራሱን ወዘወዘ። አውቆም ይሁን ሳያውቅ ከንፈሩን ነከሰ። ስሮቹ በግንባሩ ላይ ተገተሩ። ፊቱ ተከፋ።

«አስረዳኝ የኔ ወንድም!» አለው የሃምሣ አለቃ ክንዶቹን አቅልሎ ጠረጴዛውን በመደገፍ እስቻለውን እየተመለከተ።

«ሀገር በገዳዮቿ መዳፍ ውስጥ እስከ ገባች ድረስ ምናልባት እንደ ሰው አትቀበር እንደሆን እንጂ ማርጀት ቀርቶ ልትሞትም ትችላለች።» አለ እስቻለው ፊቱን ነፍትት እያለውና ጣሪያ ጣሪያ እያዩ።

«ስትል?» ሲል ጠየቀው የሀምሳ አለቃ መኮንን ዳርጌ፣ የእስቻለው አነጋገር ምስጢሩ ለጊዜው ባይገባውም ግን ደግሞ በውስጡ ብዙ ነገር ያዘለ ስለመሆኑ ከወዲሁ ገምቷል።

«አየህ ሃምሳ አለቃ!» ሲል ቀጠለ እስቻለው። «በአንድ ሀገር ውስጥ ያሉ ህዝብና መንግስት ከተኮራረፉ ምድርና ሰማይ ይቀያየማሉ። ያኔ ከዜጎቿ ልብ ውስጥ ተስፋ ይጠፋል። ተስፋ የሌለው ሕዝብ ጭካኔ ይወልዳል። ሲጨክን ጠላት የሚያደርገው የገዛ ሀገሩን ነው። አምባገነኖች የቱንም ያህል ጡንቻቸው ቢፈረጥም ድሀን ማስተዳደርና መቆጣጠር አይችሉም። እንዲያውም በቀጣው እነሱንም ያጠፉቸዋል። ያኔ ገዥና ተገዥ አይኖርምና ጥፋት ይነግሳል። በዚህ ጊዜ ሀገር መቃመም ትጀምራለች። ታዲያ ይህ ከሆነ ሀገር አልሞተችም? የሀምሣ አለቃ!» ሲል ጠየቀው።

የሃምሣ አለቃ መኮንን ዳርጌ በአላሰበውና አስቦትም በማያውቅ የተለየ ሐሳብ ውስጥ ገባ። አንዳች አስፈሪ ስሜት ወጣበት። እስከ ዛሬም እንደ ሰው እያሰበ ስለመኖሩ ተጠራጠረ። ፍርሀትና ጭንቀትም አደረበት። በረጅሙ ተነፈሰና፡-

«አስደነገጥከኝ እስቻለው!» አለው።

«ሊያስፈራም ሊያስደነግጥም ይችላል ሃምሣ አለቃ። በአሁኑ ወቅት ሀገራችን ታማለች። ህመም ደግሞ በቶሎ ያስረጃል። ከሀገሬ በፊት እኔ ከአረጀሁ ያልኩህም በዚህ ምክንያት ነው።» አለና እስቻለው የሃምሳ አለቃን ትኩር ብሎ ተመለከተው።

«ይህ ገባኝ እስቻለው» አለና የሃምሣ አለቃ መኮንን ዳርጌ «እንቆቅልሽ የሆነብኝ ግን ለምን ከዚያ ወዲህ ወደ ዲላ ላለመሄድ እንደወሰንክ ነው። ምናልባት ይህም ምስጢር ይኖረው?» ሲል ፈራ ተባ እያለ ጠየቀው።

«ምስጢር የለውም። እኔ ግን መሄድ አልፈልግም።»

«አይመስለኝም እስቻለው! ይህ ውሳኔህ ምስጢር ሳይኖረው አይቀርም። አይበህ ምስጢር ቢኖረውም በበኩሌ እጠብቅልሃለሁና ንገረኝ።» አለው።

«ወታደር አይደለህ! ለምስጢርማ ማን ብሎህ» አለና እስቻለው ፈገግ አለ።

«ሙያዬ ስለሆነ ሳይሆን ለአንተ በመታመን።»

እስቻለው ጭንቅ አለው። የሀምሣ አለቃው ጥያቄ ከልብ የመነጨ መሆኑ ይገባዋል። ግን ደግሞ የሆዱን ምስጢር ለማንም ላለመናገር ወስኗል ! የሀምሣ አለቃው ልመና ግን መንፈሱን ወጥሮ ያዘው። ወደ ጣሪያ ወደ መሬት ካየ በኋላ በቅድሚያ በረጅሙ ተነፈሰ። የሀምሣ አለቃውንም አየት ሲያደርገው በፊቱ ላይ የጭንቅ ስሜት አነበበበት። መጨነቁም ስለ እሱ መሆኑ ገባው። ከዚያ በኋላ ፍንጭ ሊሰጠው ፈለገ።

«አየህ ሃምሳ አለቃ! እኔ በአሁኑ ሰዓት ወደ ዲላ ብሄድ ያለ ጊዜዋ የምትረግፍ አበባ አለች።» አለና እንባው ከዓይኑ ላይ ዝርግፍ አለ።

«እንዴት?»

«አበባ የምልህ በእርግጥ ተክል አይደለችም። ሔዋን ተስፋዬ የምትባል የሰው ልጅ ናት። የምወዳት የምትወደኝ፣ የምሳሳላት የምትሳሳልኝ፣ የመጀመሪያ ፍቅረኛዬና እጮኛዬ ነበረች። ልንጋባ ሁለት ወር ሲቀረን ነበር እኔ ድንገት ወደ አስመራ የመጣሁት። አሁን ግን ይኸው እንደምታየኝ ግማሽ አካሌ ከጥቅም ውጭ ሆኗል። ያለ ጊዜዋ ትረግፋለች የምልህም ያቺ አበባ እንዲህ ሁኜ ብታየኝ የሚፈጠርባትን የስሜት ስቃይ ስለማውቀው ነው። እንደኔ እግሯ ባይቆረጥ፣ ብታየኝ እንደኔ ፊቷ ባይጠበስ! እንደኔ ጀርባዋ ባይበላሽ፣ እንደኔ ዓይኗ ባይጠፋ እኔን በዚህ ሁኔታ ካየች ግን በንዴት! በቁጭት በብስጭትና በፀፀት የአዕምሮ ህመምተኛ ትሆንብኛለች ብዬ እሰጋለሁ። ታዲያ ይህን እያወኩ ሄጄ የዚያችን አበባ ህይወት ላበላሸው ሀምሣ አለቃ?» አለውና በጉንጩ ላይ ይንቆረቆር የነበረ እንባውን በእጁ መዳፍ ሙሉ ሙዥቅ አድርጎ ጠረገው።

«አታልቅስ የኔ ወንድም!» አለው ሃምሣ አለቃ እሱም ዓይኑ በእንባ እየሞላ።

«እኔማ ገና ብዙ ብዙ አለቅሳለሁ ሀምሳ አለቃ! እኔ ዕድለ ቢሱ ያቺን አበባ ዕድለ ቢስ አድርጌያት ቀርቻለሁ። ስለ ሔዋን ተስፋዬ ገና ብዙ አለቅሳለሁ። በህይወት እስካለሁ ልረሳት አልችልምና ሳለቅስ እኖራለሁ።» አለና እስቻለው አሁንም «እህህህህ ...! በማለት መላ ሰውነቱ እስኪንቀጠቀጥ ድረስ በለቅሶ ሲቃ ተርገፈገፈ።

«ምናልባት ትጠየፊኛለች ብለህ ሰግተህ ይሆን የኔ ወንድም?» ሲል ሃምሣ አለቃ የራሱንም ዓይን እየጠረገ ጠየቀው።

«ፍጹም ሀምሳ አለቃ! የኔዋ ሔዋን መልኳ አበባ እንደሚመስል ሁሉ ውስጧም ውብ ነውና ትጠየፊኛለች ብዬ አይደለም። የኔዋ ሔዋን እንዲህ ያለ ተፈጥሮ የላትም። በራሴ በኩል ግን ከእንግዲህ እኔ ለእሷ አልገባም ብዬ ወስኛለሁ።» አለ እያለቀሰ።

«ታዲያ እሷ እየጠበቀችህ ቢሆንስ?»

«ተስፋ እንድትቆርጥ ብዬ የበኩሌን አንድ ርምጃ ወስጃለሁ። የምትኖረው በኔ ደመወዝ ስለነበር እንዲቋረጥባት ብዬ የመንግስት ስራ ለቅቄ በአንድ የፈረንጆች ግብረ ሰናይ ድርጅት ክሊኒክ ውስጥ በአስተርጓሚነት ተቀጥሬአለሁ።»

«ምናልባት ርሀብ ላያሸንፋት ቢችልስ?»

«ምናልባት ርሀብ ... ግን ልጅ ናትና ከመቆየት ህሳቧን ብትቀይር «ይህ እኔንም ያሰጋኛል። ግን ልጅ ናትና እኔ እዚያው እያለሁ ሊድሯትና እያልኩ እንገላለሁ። በዚያ ላይ ደግሞ ገና እኔ እዚያው እያለሁ ሊድሯትና ሊያገቧትም እያሰቡ የሚያንገዋብቡ ሰዎች ነበሩና በእነሱ ጫና ተሸንፋ አዲስ ህይወት ብትጀምር እያልኩም እፀልያለሁ።»

የሃምሣ አለቃ መኮንን ዳርጌ የእስቻለውን ምክንያት ሀሳብ ሲሰማ ቆይቶ ወደ ዲላ ላለመሄድ የወሰነበት ምክንያት ሲገባው በራሱ ውስጥ ያለው የመንፈስ ቀስል እመመዉና ለእስቻለው ይገልጽለት ዘንድ ከማሌቱ ገፋፋው።

«ስማ እስቻለው።» አለው ፍንዝዝ ትክዝ ብሎ ከቆየ በኋላ። «እንዳንተው ተገድጄ ወደዚህ አገር የመጣሁ ነኝ። መጥቶ የፈፀምኩት ሰው መግደል ነው። እሳዬ ላይ የምታየው የሀምሳ አለቃነት ማዕረግ የተሰጠኝም ሰው በመግደሌ ነው። የገደልኩት ደግሞ የሀገሬን ልጆች ወንድሞቼን ነው። ቀድሞ ኤርትራ ገድዬ ከሆን በዚያው መጠን በርካታ ዘመድ አዝማዶቻቸውን አስዝኛለሁ። በዚህ ሥራዬ ደግሞ ተሸልሜበታለው። ታዲያ እኔ ይህን ያህል የሀገሬ ልጆች ተሸክሜ ወደ ሀገሬ ልገባ ከቶ በምን አንተ ልታየኝ መጥተህ ራስህ በተጎዳህ! ልትጠፍን መጥተህ ራስህ በተሰበርክ በሰለለህ! ልትረዳ መጥተህ ራስህ በተጎዳህ! ምን የሚያሳፍር ነገር ሰርተሃልና ከዚህ ዓይንት አለም ውስጥ ላይ ልትደርስ ቻልክ?» ሲል ጠየቀው።

«ሀሳብህን አደንቃለሁ ሀምሳ አለቃ!» ሲል ጀመረ እስቻለው። «ልዩነቱ ግን አንተ የገደልካቸው ኢትዮጵያውያን ሞተው አርፈዋል። ቤተሰቦቻቸውም እርማቸውን አውጥተው ተገላግለዋል። በፀሎት ያለው በአንተ ልብ ብቻ ነው። ምናልባት ራስህን ይፈጅህ እንደሆን እንጂ የሞቱትና ያሉት ግን ሁሉንም ተጠናቀውታል። የኔ መሄድ ግን ወዳጆቼን እንደ እሳት ያቃጥላቸዋል። ትቼም እንዳልኩህ በተለይ የኔዋ አበባ ትረግፍብኛለች። የህይወትን ጣዕም ታጣብኛለች። የልጅነት ህይወቷ የስቃይና የመከራ ይሆንብኛል። እሷ ከእንግዲህ እኔን እንዲት የዚያ የቆራጣው! የዚያ የእውሩ! የዚያ የደንቆሮው ሚስት እያተባለች እንድትኖር አልፈልግም። 'ሞቷል' ብላ እንድትረሳኝ ብቻ ነው የምፈልገው። ይህን መስዋዕትነት እከፍልላት ዘንድ ይገባኛል። እወዳታለሁና በቁሜም አልፈልግም። አፈትራታለሁና የህይወቷን መበላሸት አልሻም።» አለና እስቻለው አሁንም እንባውን በጉንጩ ላይ አንቆረቆረው።

የሀምሣ አለቃ መኮንን ዳርጌ የእስቻለውን አኳኋን እየተመለከተ የእሱም ዓይን ያነባ ጀመር። አንድ ነገር ትዝ አለውና እስቻለውን ደግሞ ጠየቀው።

«ለመሆኑ ከልጅቷ ሌላ ዲላ ውስጥ የሚኖር ዘመድ የለህም?»

«እህትም ከወንድምም የሚበልጡ ጓደኞች ነበሩኝ፣ ናፍቆትና ትዝታቸው ዕድሜ ልክ የማይረሳ። እዎ እነሱንም ሳስባቸውና ሳስታውሳቸው እኖራለሁ።»

«ታዲያ ከእነሱ ዕድሜ ልክ ተለያይተህ መኖሩ አይቆጭህም?»

«ይበልጥ የሚያንገበግበኝ ግን ቀድሞ ነገር ከእነሱም ከሔዋንም ተለይቼ ወደዚህ ቦታ መምጣቴ ነው። ወዲህ እንድመጣ የተደረኩት በተንኮልና በደባ ነው። በሀይልና በተፅዕኖ ነው። ዛሬ ላይ ሆኜ ሳስበው ምነው ግፈኞች ሲያነቁኝ እዚያው ተናንቄአቸው ቢሆን! ምነው አሻፈረኝ ብዬ ቃታ ስበውብኝ ቢሆን! ምነው እስረው በገረፉኝ ወይ ከሥራ ተባርሬ እንደ ሌላው ወኔ በርሃብ ሞቼ ቢሆን፥ እያልኩ ሳስብ ነው የሚቆጨኝ። ላይቀርልኝ ነገር ሽሽቼ መሞቴ ነው የሚያቃጥለኝ። የእውነት ውሳኔማ የራሴ ስለሆነ ለምን ይቆጨኛል? የሁሉንም ናፍቆት፣ የሁሉንም ትዝታ እችለዋለሁ። ገፍቶ ቢመጣብኝ ህዘንና ለቅሶ ነው። እያዘንኩና እያለቀስኩ እኖራለሁ። እነሱን ግን መልካም እንዲገጥማቸው እመኛለሁ።» አለና ዓይኑን በመዳፉ አበሰ አደረገ።

«በእርጅና ዘመንህስ ጊዜ ለመሄድ ለምን አስብክ?»

«ምናልባት ለኔዋ ሒዋን የማስበውና የምመኘው ሁሉ ተሳክቶላት ማየት
የቻልኩ እንደሆነ ብዬ። በእርግጥም እኩያዋን አግብታ፣ ልጆች ወልዳ፣ ማን
ማሰሪያ አድርሳ ባያት፣ የሕሷን ክንፈር እንደ ሳምኩት ሁሉ የልጆቿን ጉንጮች
ስሚያቸው ብሞት አጥንቴ በሰላም የሚተኛ፣ አፈሩም የሚቀለኝ ይመስለኛል።»
የሀምሳ አለቃ መኮንን ዳርጌ የአስቻለው የፍቅር ዕናት፣ መልካም ምኞቱ
አርቆ አስተዋይነቱ እጅጉን ገርሞት ትኩር ብሎ ሲመለከተው ድንገት ከ[illegible]
ቴፕ አንድ ሙዚቃ ተለቀቀ።

ጊዜው ይርዘም እንጂ ማየት አይሻለሁ፣
ጊዜው ይርዘም እንጂ ማየት አይሻለሁ፣
ሞት ካለየኝ በቀር በህይወት እያለሁ፣
ሞት ካለየኝ በቀር በህይወት እያለሁ።

አስቻለውና የሃምሣ አለቃ መኮንን ዳርጌ እርስ በእርስ ተያዩ። ነገ
ኢጋጣሚ እንደሆነ ሁለቱም ገብቷቸዋል። ግን ደግሞ ረዘም ላለ ጊዜ እንባ
እንዲያራጩ አደረጋቸው።
የሀምሣ አለቃ መኮንን ዳርጌ ዛሬ በዲላ ፖሊስ ጣቢያ ውስጥ ሒዋንን ከፊቱ
አስቀምጦ በሀሳብ ወደ ኋላ በመኮብለል ይህ የተመለሰው የትዝታ ጓዝ ይዞ
ነበር። ደግነቱ ትዝታ የእውናዊ ክንውን ያህል ጊዜ አይወስድምና በትንሽ ደቂቃዎች
ውስጥ ይህን ሁሉ ሲያስብ ቆይቶ ያነቃውም የራሱ ለቅሶ ነው። ድንገት «ሀሌ»
የሚያሰኝ የለቅሶ ትንታ ተናነቀው። እንባውም በጉንጮቹ ጉ ብሎ ወረደ። ስሚቋን
ከሒዋን ለመደበቅ አሰበና ወዲያው ቀልጠፍ ብሎ፦
«ምን እንዳስለቀሰኝ ታውቂያለሽ?» አላት።
«ኧረ አላወኩም።» አለችው ሒዋን እንባ ባቀረሩ ዓይኖቿ እየት
እያረገችው።
«ልክ እንደ አንቺ ከፍቅረኛዬ ተለይቼ ስለምኖር እሷ ትዝ ብላኝ ነው።»
አላት እንባውን በመሀረብ እየጠራረገ። ሒዋን ‹ለምን አትሄድላትም› ልትለው ነበር።
ግን ፈራችና ወደ መሬት አቀርቅራ እሷም አስቻለውን እስታወሳ ታለቅስ ጀመር።
«ለመሆኑ አሁን እንዴት እየኖርሽ ነው?» ሲል ጠየቃት ሀምሳ አለቃ።
የጓለሙንና የመብራቱን ነገር እርግፍ አድርጎ ተወና ከአስቻለው ምኞትና ተስፋ
አኳያ በምን ሁኔታ ላይ እንዳለች ለማወቅ ጓጓ።
«ቀድሞ የአስቻለው ሰራተኛ፣ ዛሬ ደግሞ ለኔ ጓደኛ ከሆነች ትርፌ ቢጋሻው
ከምትባል ልጅ ጋር ቤት ተከራይተን አብረን እየኖርን ነው።»
የሃምሳ አለቃ ያኔ አስቻለው ‹ሞቷል› ብላ ተስፋ እንድትቆርጥና ደግሞ
ሌላ አማራጭ እንድትፈልግ ብዬ የመንግስት ስራ ለቅቂያለሁ' ያለውን
አስታውሶ «በምን ትተዳደራላችሁ?» ሲል ጠየቃት።
«በልሁ ተገኔ የሚባል የአስቻለው ጓደኛ እኔን በአውራጃው ግብርና ጽህፈት
ቤት ውስጥ በተላላኪነት አስቀጥሮኛል። ለትርፌ ደግሞ መንቀሳቀሻ ወረት ሰጥቷት
ሻይና ዳቦ እየሸጠች እየተረዳዳን አብረን እንኖራለን።»
«በዚህ ሁኔታ ለምን ያህል ጊዜ ቆያችሁ?»

«ሁለት ወር ይሆነናል። ትርፌ እስጤ ቤት ተቀጥራ ትሰራ ነበር። እኔ
ደግሞ ከሕሁቴ ጋር እኖር ነበር። ግን ከሕሁቴ ጋር ሳንስማማ ቀረንና በልሁ ትርፌን
ከስጤ ቤት አውጥቶ አብረን እንድንኖር አደረገን።»
«ባል ለማግባት አልሞከርሽም?»
«አስቻለውን ትቼ?» አለችው ዓይኖቿን በዓይኖቹ ላይ ክላት አድርጋ።
«ምናልባት ባይመጣስ?»
«ባይመጣም አላገባም።»
«ጭራሽ?»
«ዕድሜ ልኬን።»
ሀምሳ አለቃ አሁንም እንባው በዓይኑ ሞላ። የአስቻለው ተስፋና ምኞት
የመረብን ወንዝ አልተሻገረም፤ በኤርትራ ሰማይ ላይ ተንሳፎ ቀርቷል። ሃምሳ አለቃ
እንባውን ጠርጎ ምራቁን ዋጥ አደረገና «ለመሆኑ ይኸ በልሁ የሚባል የአስቻለው
ጓደኛ እዚህ ከታሰርሽ ወዲህ ጠይቆሽል?» ሲል ጠየቃት።
«አልሰማሁም መሰል፤ እስከ አሁን አልመጣም።»
ሃምሳ አለቃ መኮንን ከዚህ በኋላ ጊዜ ማጥፋት አልፈለገም። ረዳቱን
በደመል ጠራና ሒዋንን ወደ እስር ቤት አስመለሰ። ረዳቱን እንደገና ጠራውና ቀጭን
ትዕዛዝ ሰጠው። «ይቺን ልጅ ሊጠይቅ በልሁ ተገኔ የሚባል ሰው ቢመጣ ከልጅቱ
ጋር ከመገናኘቱ በፊት ወደኔ አምጣልኝ።» አለው።

እንደ ሀምሳ አለቃ መኮንን ዳርጌ ከትዝታ ጋር የተቀላቀለ እይታን እንጂ
መርሰድ እሸቴም በደረቅ ጭንቀት ተወጥሮ ነው ያረፈደው። የጀመረው ደግሞ ገና
ጠዋት ከሁለት ሰዓት በፊት። መኖሪያው በዜሮ ሁለት ቀበሌ የታችኛው ጥግ ሲሆን
የሚያስተምረው ደግሞ የዲላ ከተማ የላይኛው ጫፍ በሆነ ቀበሌ ውስጥ የሚገኘው
የአዲ ዳዊት ትምህርት ቤት ውስጥ ነው። ሒዋንና ትርፌ የተከራዩት ቤት መንገዱ
ላይ በመሆኑ ሲወጣም ሲወርድም ጎራ እያለ ይጠይቃቸው ነበር። ዛሬ ጠዋት ግን
ወደ ሥራው ሲሄድ ያ ቤት በጠዋት ከውጭ ተቆልፎ አየው። ወዲያው እንደነገሩ
የጎረቤት ሰዎችን ሲጠይቅ ማታ ሲሆንና ሲባል የመሸው ሁሉ በዝርዝር ተነገረው።
በሰማው ወሬ የተሰማው ድንጋጤ ጭራሽ ራስ ምታት ለቀቀበት።
ቢቸግረው ወደ በልሁ ቢሮ ሮጠ። ነገር ግን ዘግይቶ ነበር እንጂ በልሁ ለመስክ ስራ
ወጥቷል። መስሪያ ቤት ደርሶ ይኸው ሲነገረው ያለ ውጤት ተመለሰ።
እንደገና ወደ ታፈሡ ቤት ሲሮጥ አሰበ። ግን ከአንደኛ እስከ ሦስተኛ ክፍለ
ጊዜ አስተምሮ ሌሎቹን ክፍለ ጊዜያት ነፃ እንደሆነ አስታወሰና በሰንድ ፊት ስራውን
አጠናቆ ለመሄድ ወስኖ እየተጨነቀም ቢሆን ወደ ትምህርት ቤት አመራ።
ልክ ከጠዋቱ አራት ሰዓት ላይ ሥራውን ጨርሶ ወደ ታፈሡ ቤት
በመገስገስ ላይ ሳለ አስፋልቱን አቋርጦ ሊያልፍ ሲል ከይርጋ ጨፌ አቅጣጫ
ትመጣ የነበረች ቶዮታ መኪና ድንገተኛ ክላክስ ስታደርግ ሰማ። ዞር ብሎ ሲመለከት
የበልሁ የመስክ መኪና ናት። በክላክስ ያስጠራውም ራሱ በልሁ ኖሯል። በአስፋልት
ላይ ቆሞ መኪናዋን ጠበቀ።

«ዛሬ ስራ የለም እንዴ?» ሲል ጠየቀው በልሁ ከአጠገቡ ሲደርስ አንገቱን በመስበር አቀርቅሮ መርዕድን እየተመለከተ።

«እስቲ ና ውረድ!» አለ መርዕድ ፊቱ በድንጋጤ ጭምትርትር እንዳለ።

በልሁም የመርዕድ ሁኔታ ገና ሲያየው አስደንግጦታል። «ምነው? ምን ሆንሀል?»

«ችግር አለ።»

በልሁ ከመኪናዋ ላይ ዱብ ብሎ ወደ መርዕድ በመጠጋት «ምንድነው ችግሩ?» ሲል ጠየቀው።

«ሔዋን ታስራለች!»

«ምን አድርጋ?»

መርዕድ ከሰው የሰማውን በሙሉ ነገረው።

«ያምሀል እንዴ አንተ ሰው?»

«የነገሩኝን ነው እኮ የምነግርህ?»

«ከታሰረች ጠይቀሃታል?»

«አሁን ወደዚያው እየሄድኩ ነበር።»

ለነበሩበት ቦታ ፖሊስ ጣቢያው ቅርብ ነው። በልሁ ሾፌሩን ወደ ቤቱ እንዲሄድ አሰናበተውና ከመርዕድ ጋር ወደ ፖሊስ ጣቢያው ገሰገሱ። ርምጃቸው ፈጣን ስለነበር ከአምስት ደቂቃ ባላይ አልወሰደባቸውም ።

ትርፌ ገና በጠዋት ለሔዋን ቁርስ ይዛ እንደሄደች አልተመለሰችም ኖሯል። እንዲያውም በእስረኞች ግቢ እንድትገባ ተፈቅዶላት ኖሮ ፊት ለፊት ከሔዋን ጋር አብረው ተቀምጠው በልሁና መርዕድን ከሩቅ ሲያዩአቸው ተንጫጩ። «በልሁ መርዕድ! በልሁ መርዕድ!» በማለት።

በልሁና መርዕድ ከጣቢያው በር ላይ እንደ ደረሱ አንድ ፖሊስ ጠጋ አላቸውና «ከእናንተ ውስጥ በልሁ ተገኔ የሚባል ማነው?» ሲል ጠየቃቸው።

«እኔ!» አለው በልሁ በሌባ ጣቱ ወደ ራሱ እያመለከተ።

«ሀምሳ አለቃ ይፈልጉሃል።»

«በሰላም?»

«አላውቅሁም» አለና ፖሊሱ ወደ እነሔዋን ዞር ብሎ አየት አደረገና ፊቱን ወደ በልሁ በመመለስ «ከልጅቷ ጋር ሳይገናኝ ወደኔ አምጡት ነው ያሉት» አለው።

«ቢሮው የት ነው?» አለ በልሁ ቁና ቁና እየተነፈሰ።

«ተከተለኝ!» አለና ፖሊሱ በልሁን ከፊት ከፊት እየመራ ወስዶ ከሃምሳ አለቃው ቢሮ አስገባው።

የሃምሳ አለቃ መኮንን ዳርጌ ጆሮግንዶቹን በእጆቹ ይዞ ጠረጴዛው ላይ በማቀርቀር ሀሳብ ውስጥ ገብቶ ሳለ ፖሊሱ በልሁን ይዞ በመድረስ «አቶ በልሁ እኒህ ናቸው» አለው። ሃምሳ አለቃ መኮንን ዳርጌ ለካ በልሁን ከተማ ውስጥ በዓይን ያውቀው ኖሯል። እንዲያውም በአለባበሱ፣ በተክለ ሰውነቱና አጠቃላይ አቋሙ ያደንቀው የነበረ ሰው ሆኖ ሲያገኘው «በልሁ ተገኔ ማለት አንተ ኖረሀል እንዴ?» እያለ ብድግ ብሎ ጨበጠው።

«አዎ ነኝ» አለ በልሁ ቁና ቁና እየተነፈሰ።

«ቁጭ በል እስቲ!» ሁለቱም ፊት ለፊት ተቀመጡና ተፋጠጡ።

«የተበሳጨህ ትመስላለህ!» አለው የሃምሣ አለቃ።

«አዎ! እጅግ በጣም ተናድጃለሁ።

«ምነው?»

«የማትታሰር ሰው አስራችኋል!» አለው በልሁ ቁጭ እንዳለ በቀኝ እጁ ሽንጡን በመያዝ ሃምሳ አለቃውን እየተመለከተ።

«ወንጀል ፈጽማ እንደሆነስ?» አለ ሃምሳ አለቃው ፈገግ እያለ።

«የተባለው ከሆነ አላምንም።» አለና በልሁ የሃምሳ አለቃውን ጠረጴዛ መታ መታ እያረገ «ቀድሞ ነገር የታሰረ ሁሉ ወንጀለኛ፣ የአዘዘ ሁሉ ጻድ ነው ብዬ ማመን ከተውኩኝ ቆይቻለሁ።» አለው።

«አይፈረድብህም!»

«አሁን ለምን ፈለከኝ?» ሲል በልሁ ዓይኑን ፈጠጥ አድርጎ ጠየቀው።

«ለብርቱ ጉዳይ!» አለና ሃምሳ አለቃው በረጅሙ ተንፍሶ «ግን አቶ በልሁ፣ አሁን የምነግርህ ጉዳይ ሔዋን ለምትባል ልጅ ፈጽሞ መንገር የለብኝም፣ ባይሆን ለአንተና ለቅርብ ጓደኞችህ ከነገርኳችሁ በኋላ አስፈላጊውን የሚሆን ነገር ነው።»

«ምንድነው እሱ?»

«አስቻለው ፍሰሀ የሚባል ጓደኛ እንደ ነበረህ ሰማሁ።»

«አሁንም አለኝ።»

«አብራችሁ ያላችሁ አይመስለኝም።»

«ከልቤ አይወጣምና ምንጊዜም አብረን የምኖር ይመስለኛል።»

«በአካል ማለቴ ነው።»

«ከተፉዎች አለያይተውናል። አሁን የትና በምን ሁኔታ ላይ እንዳለ ግን አላውቅም።» ካለ በኋላ በልሁ «ለአንተ ማን ነገረህ?» ሲል ጠየቀው።

«በህይወት አለ ብልህ ታምናለህ?»

«የት አገር?»

«እዚሁ ኢትዮጵያ ውስጥ።»

«እ?» በልሁ አፉ ተከፍቶ ቀረ። ዓይኖቹ በሃምሳ አለቃው ላይ ተተከሉ።

«እስቲ ከሚቀርቡህ ሰዎች ጋር በመሆን ተሰባሰቡልኝና ስለ እሱ ሁኔታ በጋራ ላነጋግራችሁ። እኔ የማውቀው ነገር አለኝ።»

«ዛሬ ማታ ቢሆንስ?»

«ይቻላል።»

ቦታና ሰአት ወስነው ተለያዩ።

* * *

የሃምሳ አለቃ መኮንን ዳርጌ ፖሊስ ሆኖ ከተቀጠረ ጀምሮ አሁን ያጋጠመውን ዓይነት አስደሳች ሥራ አግኝቶ አያውቅም። የሔዋንና በሷ ምክንያት ተጣሉን ያሉ ሰዎችን ጉዳይ እንደ የመንግስት ተቀጣሪነቱ ሳይሆን ልክ እንደ ራሱ ጉዳይ በተለየ ስሜትና ትኩረት ሲከታተለው ወሰነ።

የስራው የመጀመሪያ ዕቅድ የሔዋንን ድንግልና በሐኪም ማረጋገጥ ነበር። በእርግጥም ፈፀመው! ሔዋን ያልተሟሸ ገላ ባለቤት ሆና አገኛት። የምስክር ወረቀቱንም በእጁ ያዘ። ለምርመራው የሚያመቹ በርካታ ፍንጮችን ከአካባቢው አግኝቷል። የምርመራው ሂደት በዚያው አቅጣጫ እንዲጓዝ አድርጎ ዕቅድና ስልቱንም ቀይሶታል። ስለ አስቻለው ሁኔታ ታፈሡ! በልሁና መርዕድን

ሲያንጋግር ባመሸበት ሦስተኛ ቀን ላይ ዓለሙ መርጋንና መብራቱ ባዩን ሁለቱንም በአንድ ጊዜ ከቢሮው አስቀረባቸውና «ልብ ብላችሁ አዳምጡኝ» ሲል ሀምሳ አለቃ እስጠንቀቃቸው:: ዓለሙና መብራቱ ከፊቱ ተቀምጠው የሚሆኑት ሁኔታ በሩስ ውስጣቸውን ያስነብበዋል::

«ሒዋን ተስፋዬ የምትባል ሴት ወዳጃችሁ እንደሆንች ቃል በሰጣችሁበት ወረቀት ላይ ፊርማችሁን አኑራችኋል፣ ነው ወይስ አይደለም?» ሲል ጠየቃቸው::

«ነው! ነው!» አሉ:: በፍርሀት ስሜት ይቁነጠነጡ ጀመር::

ሃምሳ አለቃ አንዲት ወረቀት ከጠረጴዛው ላይ ብድግ አድርጎ እያሳያቸው «ይቺ ወረቀት ግን ቅጥፈታችሁን እረጋግጣባችኋለች:: ሒዋን ድንግል ስለመሆኗ የምታረጋግጥ የሐኪም ወረቀት ናት::» ብሎ ወረቀቱን ጠረጴዛ ላይ በክብር ከአስቀመጠ በኋላ እንደገና አየት እያረጋቸው «ዋሽታችኋል ወይስ አልዋሻችሁም?» ሲል ጠየቃቸው:: ዓለሙና መብራቱ እርስ በእርስ ተያዩ:: ከንፈራቸውን በምላሳቸው እያራሱ ይትበጠበጡ ጀመር::

«ተናገሯ!»

ዓለሙ መርጋ ድንገት ብድግ አለና «እውነቱን አወጣለሁ ጌታዬ!» አለ እጆቹን ወደ ኋላ አቆላልፎ እጅ እየነሳ::

«አንተስ?» አለና ሀምሳ አለቃ በመብራቱ ላይ አፈጠጠ:: መብራቱም ልክ እንደ ዓለሙ ብድግ ብሎ «ግልጥ አድርጌ አወጣለሁ ጌታዬ!» አለና እጅ ነሳ::

ሀምሳ አለቃ መኮንን ዳርጌ ከመቀመጫው ብድግ አለ:: ከጠረጴዛው ላይ ሁለት ንፁህ ወረቀቶችን አነሳ:: ወደ ሁለቱም ጠጋ በማለት እንዳንድ እያደላቸው «አንተ በዚህ፣ አንተ ደግሞ በዚህ፣ ይህን ጉዳይ ትፈጽሙ ዘንድ ማን እንደላካችሁና ምን ዓይነት ውለታ ሊከፈላችሁ ቃል እንደተገባላችሁ፣ እንዲሁም በዚህ ጉዳይ ላይ የት፣ መቼና ከማን ጋር እንደተነጋገራችሁ በራሳችሁ እጅ ጽፋችሁ ታመጣላችሁ::» ካለ በኋላ በማስጠንቀቂያ ዓይነት ሴባ ጣቱን ቀስሮ «ልብ በሉ! በሁለታችሁ ጽሁፍ ላይ አንዲት ልዩነት ብትገኝ ሁለታችሁም ዕዳ ትገባላችሁ::» አለና ወደ በሩ ራመድ እያለ «ኑ ተከተሉኝ::» አላቸው:: ይዟቸው ወጣ:: በፖሊስ ጣቢያው ግቢ ውስጥ በሚገኙ ሁለት የተለያዩ ክፍሎች ውስጥ ለየብቻ አስገብቶ ቆለፈባቸው:: በግምት ከአንድ ሰዓት በኋላ የተከፈተላቸው ዓለሙና መብራቱ ያቀረቡለት ፅሁፍ ለሃምሳ አለቃ መኮንን ዳርጌ ለከሰዓት በኋላ ስራው ምቹ ሁኔታ ፈጠረለት:: በዚያው አለቃ መኮንን ዳርጌ ለከሰዓት በኋላ ስራው ምቹ ሁኔታ ፈጠረለት:: በዚያው

ዕለት ከሰዓት በኋላ ከኢየሱብት እየለቀመ ለዚያውም እንዱ ስለሌላው መሰረት ሸዋዬንና በድሉን ከኢየሱብት እየለቀመ ለዚያውም አንዱ ስለሌላው በማያውቁበት ሁኔታ ለየብቻ እስር ቤት ከቷቸው አደረ:: በነጋታው ጠዋት በቅድሚያ ዓለሙንና መብራቱን ወደ ቢሮ አስጠራና ጎን ለጎን አስቀምጦ:

«ስሙ!» አላቸው ተራ በተራ እየተመለከተ::

«አቤት! አቤት!» አሉ በየተራ::

«እቤት! አቤት!» አሉ በየተራ::

«ከጻፋችሁት ወረቀት ለይ እንደተረዳሁት፣ ዓለሙ የመኪና ሾፌር፣ መብራቱ ደግሞ ረዳትና ገንዘብ ያዥ ሆናችሁ ልትቀጠሩ በበድሉ አሸናፊ በተገባላችሁ ቃል መሰረት በንጹህ ሰው ላይ አሳፋሪ የስም ማጥፋት ወንጀል ፈጽማችኋል:: ከእንግዲህ እናንተን ነጻ ሊያደርጋችሁ የሚችለው በዋና ጠንሳሾቹ ላይ ቋሚ ምስክር ሆናችሁ ስትገኙ ብቻ ነው::» አለና «አሁን ዋናዎቹን ወንጀለኞች እዚሁ አላችሁበት ላቀርባቸው ነው:: እናንተም ከፊታቸው ቆማችሁ ወንጀሉን ትፈጽሙ ዘንድ በእነሱ የተነገራችሁን ሁሉ በዝርዝር ስለመናገራቸው ቀድማችሁ

ልትገልጹላቸው ይገባል::» አለና «ታደርጋላችሁ ወይስ አታደርጉም?» ሲል ቆጣ ብሎ ጠየቃቸው::

«እናደርጋለን::» አሉ ሁሉቱም በአንድ ላይ::

ሃምሳ አለቃው ሸዋዬና በድሉን ወዲያው አስወረዷቸው:: እነሱን በአንድ በኩል ዓለሙና መብራቱን ደግሞ በሌላ በኩል አስቀምጦ ፊት ለፊት አፋጠጣቸው:: ትናንት በዓለሙና በመብራቱ ተጽፈው የቀረቡትን ወረቀቶች በእጁ ጠልጠል አድርጎ ያዘና «ዓለሙና መብራቱ!» ሲል ጠራቸው::

«አቤት! አቤት!» አሉ በተከታታይ::

«እነዚህ ወረቀቶች እናንተ በሒዋን ተስፋዬ ላይ እንድትፈጽሙ በሸዋዬና በድሉ የታዘዛችሁትን ሁሉ የዘረዘራችሁባቸው ናቸው::» አለና «ዋሸሁ?» ሲል ጠየቃቸው::

«እውነት ነው! ትክክል ነው!» አሉ ዓለሙና መብራቱ::

ሃምሳ አለቃው ወደ ሸዋዬና በድሉ ዞር ብሎ «ትቃወሙ ይሆን? አመታችሁ?» ሲል ጠየቃቸው::

ሁለቱም አንገታቸውን ደፉ::

ሃምሳ አለቃው የጠረጴዛ ደወል አቃጨለና ረዳቱ ፖሊስ ሲመጣለት ሸዋዬን፣ ዓለሙንና መብራቱን ወደ እስር ቤት አስመለሳቸው:: በድሉ አሸናፊ ብቻውን ተገኘ::

«አቶ በድሉ!» ሲል ጠራው የሀምሳ አለቃ መኮንን ዳርጌ::

«አቤት!»

«ሒዋን ተስፋዬ ምን ዓይነት በደል ብትፈጽምብህ ነው የዚህ ዓይነት መንገድ ያዘመትክባት?» ሲል ረጋ ብሎ ጠየቀው::

«አስደብድባኛለች»

«በማን?»

«በልሁ ተገኙ በሚባል ጥጋበኛ!»

«ሥነ-ሥርዓት!» ሲል ጮኸበት ሀምሳ አለቃ ዓይኑን አፍጥጦ እያየውና ጣቱንም ቀስሮ:: «በልሁ ተገኙ በጡጫ ያተረፈህን እምቢ ማለቷን ትተህ ደግሞ በህግ ቦታ ላይ ተቀምጠህ ልትዘልፈው ትሞክራለህ?» አለው እልህ እየተናነቀውና በንዴት ፊቱ ልውጥውጥ እያለ::

በድሉ ከመደንገጡ የተነሳ በዓይኑ መግቢያ ቀዳዳ የሚፈልግ ይመስል ወደ ላይ ወደ ታች፣ ወደ ቀኝ ወደ ግራ ዓይኑን እያማተረ ይቁነጠነጥ ጀመር::

«በምን ተገናኝታችሁ ነው ያስደበደበችህ?»

«እወዳታለሁ!»

«ለምን ወደድከኝ ብላ አስደበደበችህ?»

«መሰለኝ::»

«ስለዚህ ልትበቀላት ፈለክ?»

«የራሷ እህት ናት የገፋፋችኝና መላውን የፈጠረችልኝ::»

«ስሟን ጥራታ!»

«ሸዋዬ::» አለና በድሉ እነዚያን ገጣጣ ጥርሶቹን የባሰ ግጥጥ አደረጋቸው::

ላብ ላብ ብሎት ጭንቀቱ ይታወቅበታል::

«የተደበደበ ሰው ቢደበድብ ወይም ቢያስደበድብ ድርጊቱ ወንጀል ቢሆንም፣ ነገር ግን ስም አለው። ግን ‹ወንድ አደባደበች› ብሎ ማስጠራቱ ምንድነው ዓላማው?» ሲል ጠየቀው።

«ስሜን ለማጥፋት።»

«ማለት?»

«ልጅቷ አስመራ ሄዶ የቀረ እጮኛ አላት።»

«እሺ!»

እዚህ ያሉት ጓደኞቼ ግን ከማንም ጋር እንዳትገናኝ ይጠብቁታል። እሷም ትፈራቸዋለች። ወንድ አደባደበች ተብሎ ከተወራባት ግን እነሱ ያርቋታል። እሷም ተስፋ ትቆርጥና የኔን ጥያቄ ትቀበላለች ብዬ በማሰብ ነው።» አለና በድሉ በተቀመጠበት ላይ ተቁነጠነጠ።

«ስማ!» አለው የሃምሳ አለቃ መኮንን ዳርጌ ቁጣ በተቀላቀለበት አነጋገር።

«አቤት!»

«እዚሁ እንዳለህ የሲራ መሀንዲስህን አስጠራታለሁ። እጥር ምጥን ባለ ቃል ሁሉን ነገር እንደተናገርከኝ ትነግራታለህ። ነገር አደፋፍናለሁ ካልክ ጠብህ ከመንግስት ጋር ብቻ ሳይሆን ከኔም ጋር በግል እንደሚሆን እወቅ!!»

«እሺ እነግራታለሁ!»

ሃምሳ አለቃ ረዳቱን በደወል ጠራና እንደቀረበለት ሸዋዬን እንዲያመጣ አዘዘው። ረዳቱ ሸዋዬን ወዲያው አቀረባት። በበድሉ ፊትለፊት እንድትቀመጥ ታዝዛ አለፍ ብላ ተቀመጠች። ከመርማሪው ፖሊስ ይልቅ በድሉን በፍርሀት ዓይን ታየው ጀመር።

«ተጥላ!» አለ ሃምሳ አለቃው በድሉ ላይ በማፍጠጥ።

በድሉ ከተቀመጠበት ብድግ አለና ወደ ሸዋዬ ጣቱን ቀስሮ «የቀይ ሽብሩን ጉዳይ ሙሉጭ አድርጌ ተናግሬያለሁ። ብትዋሺ ውርድ ከራሴ!» አላትና ተመልሶ ቁጭ አለ። የሃምሳ አለቃ መኮንን ዳርጌ ‹ቀይ ሽብር› የሚለውን ቃል ሲሰማ ሰውነቱን እንቀጠቀጠው። አጠገቡ ያሉት ሰዎች ነፍሰ ገዳዮች መስለው ታዩት። ልክ በቀይ ሽብር ጊዜ እንደተፈጸመው ሁሉ እሱም እነዚህን ሰዎች ዘቅዝቆ ቢሰበልባቸው ደስ ባለው ነበር። ግን ደግሞ ጨካኞች የፈጸሙትን የጭካኔ ተግባር መድገም የባለ አረመኔነት መሆኑን ይገነዘባልና በቁጭት ራሱን ወዘወዘ ተወው። ወዲያው ረዳቱን በደወል ጠራ። በድሉን ወደ እስር ቤት አስወሰደና ሸዋዬን ብቻዋን አገኛት።

ሸዋዬ በዕለቱ አጠር ያለ ሰማያዊ ጉርድ ቀሚስና ቡናማ ሹራብ ለብሳለች። ሸዋዬ በዕለቱ አጠር ያለ ሰማያዊ ጉርድ ቀሚስና ቡናማ ሹራብ ለብሳለች። ሳታስበው ታስራ በማደሯ ፀጉሯን ቀላ ያለች ስከርፍ አንገቷ ላይ ጣል አድርጋለች። አመዷ ወጥቷል። ማንደፍሮ ሜዳ ላይ የደፈጠጠው አላበጠረችም፣ አልተቀባባችም። ተኮሳትሮ በጉሯ ተንጨፍሯል። ፊቷ ጠባሳው አልጠፋም። ተኮርኩራለች። ያ አጭር ፀጉሯ ተንጨፍሯል። ፊቷ ጠባሳው አልጠፋም። ጥርስ መስመር ሰርተዋል። በድንጋጤ ዓይኗ ቀጫጭን እግሮቿን ስታነካካቸው አድራ መስመር ሰርተዋል። በድንጋጤ ዓይኗ ፍጥጥ ብሎ የሲትነት ጥላዋ ተገፏል። ታስጠላለች።

«መምህርት ሸዋዬ!» ሲል ጠራት የሀምሳ አለቃ መኮንን ዳርጌ ሁለት እጆቹ ላይ አገጩን አስደግፎ ዘንበል ብሎ እየተመለከታት።

«አቤት!»

«ሙያሽን ምን ያህል ትወጅዋለሽ?»

«ብጣም እወደዋለሁ፣ አከብረዋለሁ፣ ተማሪዎቼም በጣም ይወዱኛል።»

«ምን እያስተማርሻቸው እንደሆነ ስለሚገባቸው ይሆናላ!» አላት በምፀት።

«ትንትን ብትንትን አድርጌ ነው የማስተምራቸው።»

የሃምሳ አለቃው በረጅሙ ተነፈሰና ወደ ጠረጴዛው ጎበጥ አለ። ራሱን ወዘወዘ አድርጎ ብዕርና ወረቀቱን ከአመቻቸ በኋላ «እስቲ እኔም እንደተማሪዎችሽ እንደምድሽ ስለ ቀይ ሽብሩ ጉዳይ ትንትን ብትንትን አድርገሽ ንገሪኝ።» አለ።

ሸዋዬ የደረቀ ከንፈሯን በምላሷ እያራሰች ወደ ላይ ወደ ታች በማየት ከተብለጨለጨች በኋላ «ቀይ ሽብሩ....» ብላ ልትጀምር ስትል እንደገና ወደ ሃምሳ አለቃው ቦር ብላ «በድሉ ነግሮህ የለ?» አለችው።

ሃምሳ አለቃው በሸዋዬ አስተሳሰብ እንደ መገረም ብሎ ድንገት ፈገግ እንደ ማለት አለና «እሱ ብቻ ሳይሆን ኀለሙም መብራቱም ባሰፈው ዘርዝረውታል። ግን መጀመሪያ ሀሳቡን ያፈለቅሽው አንቺ ስለሆንሽ ከባለቤቷ መስማት ፈልጌ ነው። እንዲ መንገዱን ምን ያህል እውነተኛ እንደሆንሽ ለማወቅ ፈልጌ ነው።» ብሎ አፉን ሲያደርጋት ሸዋዬ ቀጠለች ።

«እኔ እኮ ውሸት አላውቅም!» አለችው ቀበጥበጥ እያለች።

«እኔስ መች ወጣኝ? በይ እውነቱን ንገሪኝ።»

«ቀይ ሽብር ማለት ያው ቀይ ሽብር ነው።» አለችው ዓይኖቿን ወዲያና ወዲህ ላይ እያርገበገበች።

«ነገርኩሽ አንቺ ሴትዮ!» አላት ተናዶ። ምን ደንዝ ናት በሆዱ።

«ምን ልበል ታዲያ?» ሸዋዬ ድንገጥ አለች። ተጨነቀችም።

«ዝርዝር ሂደቱን ንገሪኝ ነው ያልኩሽ!» አለና «ቀይ ሽብር ለምን አስፈለገ?» ሲል ጠየቃት።

«ሒዋን አስቸገረችኝ።»

«ምን አድርጊኝ ብላ?»

«በቃ፣ እሷ እያለች ባልም ትዳርም ሊኖረኝ አልቻለም።»

«ነጠቀችሽ ወይስ አፋታችሽ?»

«ሁለቱንም።»

«እንዴት እያረገች?»

«መጀመሪያ በልቤ የወደድኩትን ሰው ውስጥ ለውስጥ ገፋ ብላ ጠለፈችብኝ። እንደገና——» ብላ ልትቀጥል ስትል ሃምሳ አለቃ ቀደማት።

«የነጠቀችሽ ሰው ማን ይባላል?»

«አስቻለው ፍሰሀ ይባል ነበር።»

«እንዴ!» አለ ሃምሳ አለቃ በመገረምም በመደነቅም ዓይነት። ትኩር ብሎ ሸዋዬን ሲመለከታት ከቆየ በኋላ «አስቻለውን ትወጂው ነበር?» ሲል ጠየቃት።

«ነፍሴ እስክትወጣ!»

ሃምሳ አለቃ ግራ ገባው። ልክ ሒዋንን ያነጋገረ ዕለት እንደሆነው ሁሉ እስኪርብቶውን ወረቀት ላይ ጣል አደረገና ጉንጮቹን ደገፍ ወደ ጠረጴዛው አቀረቀረ። በዚያው ሀሳብ ውስጥ እንዳለ ሸዋዬ ‹በልቤ የወደድኩትን...› ያለችውን አስታወሰና ቅናት እንደነበረባት ተረዳ። ራሱን ወዝውዞ ከአጎበሰበት ቀና በማለት-

«እሺ፣ ደግሞ ከማን አፋታችሽ?» ሲል ጠየቃት።

«ያን እንኳ ባናወራው ይሻላል።»

«ለምን?»

«ደስ አይልማ!»

ሀምሣ አለቃው የሸዋዬ ባዶነት አስገረመውና አሁንም ጎንበስ ብሎ እንደ መሳቅ አለ፡፡ እንደገና ቀና ብሎ «ታዲያ ለኔ የሚያስደስተኝ ደስ የሚያሰኘውን ነገር ማወቅ መሆኑን አጣሽው? ወይስ ፖሊስ ጣቢያ ውስጥ መሆንሽን ረሳሽውን» ወረቀቶች ብድግ አድርጎ «ታሪክሽ ሁሉ እኮ እዚህ ላይ ተዘርዝሯል፡፡ መደበቁ ያዋጣሽ መስለሽ?» አላት፡፡ በእርግጥ ስለ ፍቺ ነገር የተጠቀሰ ነገር አልነበረም፡፡ ነገር ግን ሸዋዬን ለማስፈራራትና ለማስጠንቀቅ ተጠቀመበት፡፡

«ሰዎቹ ያንንም አውቀዋል?» አለች ሸዋዬ ደንግጣ፡፡

«በእነሱ ላይ ተጨምሮ በድሉ አጋልጦሻል፡፡»

«ቅሌታም ነው፡፡»

የሀምሣ አለቃ መኮንን ዳርጌ ድንገት «ቂቂቂቂ......» ብሎ ሳቀ፡፡ ሸዋዬ ፊደል ከመቁጠሯ በቀር ምንም እንዳልተማረች ታሰበው፡፡ እውቀትም ሥርዓትም አጣባት፡፡ በዚያ ምትክ የክፋትና የተንኮል ሰው መሆኗን በውል ተገነዘበ፤ «ጊዜዬን አትግደይ መምህርት ሸዋዬ!» ሲል ቆጣ ብሎ ተናገራት፡፡ በዚያው ልክ ሸዋዬም በድንጋጤ ሽምቅቅ አለች፡፡

«የነገሩህ ሁሉ ልክ ነው፡፡» አለችው በአቋራጭ የተገላገለች መስሏት፡፡

«ዝርዝሩን ከአንቺም እፈልጋለሁ፡፡ ቀጥይ!»

ሸዋዬ እንደማይቀርላት ተረዳች፡፡ በሒዋን ላይ ልትፈጽም የነበረውን የማስደፈርና የማስረገዝ ዕቅድ ሳይቀራት ቤቷ ውስጥ ባርናባስና ማንደፍሮ የተዳረጉትንና ከማንደፍሮ ጋር ተለያይታ መቅረቷን በዝርዝር ተናገረች፡፡

የሃምሣ አለቃ መኮንን ዳርጌ ፀጥ ብሎ ሲያዳምጣት ከቆየ በኋላ በረጅሙ ተነፈሰና ሁኔታው ገርሞት ራሱን ወዘወዘ፡፡ በተለይ ባርናባስና ማንደፍሮ ከመዝጊያ ጋር ያደረጉትን ትንቅንቅና የመጨረሻውንም ሁኔታ በነገረችው ጊዜ ሁኔታው ሁሉ በእዝነ-ልቦናው ታየውና ድንገት «ቂ.ቂ.ቂ.ቂ...»ብሎ ሳቀና «ለመሆኑ ባርናባስ የተባለው ሰው እዚሁ ዲላ ውስጥ አለ?» ሲል ጠየቃት፡፡

«የታለና! ስራው አሳፍሮት ‹ገር እልም ብሎ ጠፍቶ!» አለችው፡፡

«እናም ይህን ሁሉ ውርደት ለማካካስና ሒዋንን ለመበቀል ተነሳሽና የቀይ ሽብር ዕቅድ አወጣሽ?»

«ስታናድደኝ ታዲያ ምን ላርጋት?»

ሃምሣ አለቃ መኮንን ዳርጌ ሁሉም ነገር በትክክል ገባው፡፡ ዋናውን የምርመራ ሥራ ስለማጠናቀቁ እርግጠኛ ሆነ፡፡

ምዕራፍ አሥራ አምስት

'መወለድ ቋንቋ ነው' ይላሉ አበው ሲተርቱ፡፡ በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ተደጋግሞ እንደታየው ሰዎች አብረው እስካልበሉና እስካልጠጡ፣ ክፉ ደጉን በጋራ እስካልተካፈሉ እንዲሁም እስካልተረዳዱና እስካልተደጋገፉ ድረስ የዘር ግንድና የደም ትስስርን ብቻ መሰረት በማድረግ እህቴ፣ ወንድሜ፣ አክስቴ፣ አጎቴ...ወዘተ መባባል ብቻ ከሆነ በእርግጥም 'መወለድ' የሚለው ቃል ለወንድነት ያለፈ ፋይዳ ሲኖረው አይታይም፡፡ በተቃራኒው እንኳንስ መወለድ፣ የአንድ ወንዝ ውሃ እንኳ አብረው ሳይጠጡ፣ ነገር ግን በአንድ ከተማ ወይም በአንድ አካባቢ አብረው በመኖራቸው ብቻ ሰሚት፣ ፍላጎታቸውና አመለካከታቸው ተገጣጥሞ ጥብቅ ቤተሰባዊ ትስስርን ሲፈጥሩ ይታያሉ፡፡ ለዚህ ደግሞ የአስቻለው፣ የበልሁ፣ የታፈሡና የመርዕድ ከልብ የመነጨ ፍቅር ዓይነተኛ ምስክር ነው፡፡

ለእነዚህ የፍቅር ቤተሰቦች ትውውቅ መሰረት የሆነው የታፈሡና የባለቤቷ ጋብቻ ነበር፡፡ ታፈሡ በወሎ ክፍለ ሀገር በወረኢሉ አውራጃ ውስጥ ከዘቢ እስከ ጃማ ድረስ በተዘረጋው ወይናደጋማ ቦታ ላይ ከተመሰረተ ሰፊ ቤተሰብ ትወለዳለች፡፡ ባለቤቷ ደግሞ በጎጃም ክፍለ ሀገር ደጀን አካባቢ የተወለደ ቢሆንም አባቱ መምህር ስለነበሩ በሥራ ምክንያት ብዙ በቆዩበት በመሀል ሜዳ ከተማ ለብዙ ዓመታት የቆየ ነው፡፡ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን በዚያው ከተማ አጠናቆ በኋላም በተግባረ-ዕድ ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ቤት በምህንድስና ሙያ ሰልጥኖ ትምህርቱን ሲጨርስ ለስራ ተመድቦ ወደ ዲላ ነበር የሄደው፡፡

በዚሁ ጊዜ ተይዩ ታፈሡ እንግዳሰው የአንደኛና የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን በወረኢሉ ልዕልት የሺመቤት ትምህርት ቤት አጠናቃ ለከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ደሴ በሚገኘው ወይዘሮ ስሂን ትምህርት ቤት ለመማር ትሄዳለች፡፡ ሁለቱ በአንድ ሰፈር ያድሩ ነበርና በዚያው ሰበብ ይተያያሉ፡፡ በሂደት ይተዋወቃሉ፡፡ ቀስ በቀስ ይቀራረባሉ፡፡ የኋላ ኋላ ይዋደዱና በመጨረሻም ይጋባሉ፡፡

ታፈሡ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን ጨርሳ አዲስ አበባ በሚገኘው የኮተቤ የመምህራን ትምህርት ኮሌጅ ትገባለች፡፡ ከጥቂት ወራት በኋላ ደግሞ ባለቤቷ በዝውውር ወደ ዲላ ይሄዳል፡፡ ታፈሡም የኮሌጅ ትምህርቷን ስታጠናቅቅ በጋብቻ ሰበብ ወደ ባለቤቷ እንድትሄድ ተደርጎ እሷም በዲላ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በመምህርነት ትመደባለች፡፡

አስቻለው ተወልዶ ያደገው በመሀል ሜዳ ከተማ እንደ መሆኑ የተማረውም እዚያው ነው፡፡ እሱ ልጅ በነበረበት ወቅት የታፈሡ ባለቤት በዚያው ከተማ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ሲከታተል ያውቀው ነበር፡፡ እሱ ራሱም በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል በነርስነት ሙያ ሰልጥኖ ሲመረቅ ለስራ ተመድቦ ወደ ዲላ ሆስፒታል ይሄዳል፡፡ ገና ዲላ ከተማ የገባ ዕለት የታፈሡን

ባለቤት መንገድ ላይ ያየዋል፡፡ ፈራ ተባ እያለ ያናግረዋል፡፡ የትና እንዴት እንደሚያውቀው ያስረዳዋል፡፡ የታፈሡ ባለቤት የአስቻለውን ለአገሩ እንግዳ መሆን በመረዳት ወደ ቤቱ ይወስደዋል፡፡ ከታፈሡ ጋር ያስተዋውቀዋል፡፡ ታፈሡ ለአስቻለው ትመቸዋለች፡፡ አዘውትሮ ወደ ቤቷ እንዲመጣ ታደርገዋለች፡፡ እሱም እየተመላለሰ መጠየቁን ይቀጥላል፡፡ በዚያው እየተግባቡና እየተዋደዱ ይሄዳሉ፡፡ ታፈሡ የመጀመሪያ ልጇን ስትወልድ ክርስትናውን ለአስቻለው ትሰጠዋለች፡፡ አበ ልጅችም ይሆናሉ፡፡

በሌላ መንገድ ደግሞ በልሁና መርዕድ ትውውቅ እየፈጠሩ ነበር፡፡ መርዕድ ወደ አጼ ዳዊት ትምህርት ቤት ከመዛወሩ በፊት ከዲላ በስተደቡብ በሚገኘው በጨጨ ገብርኤል አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ያስተምር ነበር፡፡ በልሁ ደግሞ አዘውትሮ ወደ መስክ ስራ የሚሄደው በዚያ መስመር ስለነበርና መርዕድም ብዙ ጊዜ ከዲላ ከተማ ወደ ስራው የሚሄደው በእግሩ ስለነበር፣ በልሁ መርዕድ መምህር መሆኑን ስለሚያውቅ በአጋጣሚው ጊዜ ሁሉ ለመስክ ስራ በሚጠቀምባት መኪና ላይ ያሳፍረዋል፡፡ በዚያው እየተግባቡ ይሄዳሉ፡፡ መርዕድ በተፈጥሮው ተጫዋች በመሆኑ ለበልሁ በጣም እየተመቸው ይሄዳል፡፡ ጫትም አብረው መቃም ይጀምራሉ፡፡

በልሁና አስቻለው በከተማ ውስጥ በዓይን ይተዋወቁ ነበር፡፡ አንድ ቀን ደግሞ አስቻለው ከአንድ የዲላ ከተማ ነዋሪ ጋር ሆኖ በአንድ ቡና ቤት ውስጥ ሻይ እየጠጡ ሳሉ በልሁ ድንገት ይደርሳል፡፡ ያ ከአስቻለው ጋር የነበረ ሰው በልሁን በደንብ ያውቀው ኖሮ ቁጭ ብሎ ሻይ እንዲጠጣ ይጋብዘዋል፡፡ በልሁም ቁጭ ይላል፡፡ ከአስቻለው ጋር የነበረው ሰው ‹ሊመሆኑ ሁለታችሁ በዓይን ትተዋወቃላችሁ?› ሲል ሁለቱንም ተራ በተራ እያየ ይጠይቃቸዋል፡፡ ‹በዓይን› ይሉታል፡፡ ሰውየው አስቻለውና በልሁን በቅደም ተከተል እየጠራ ‹እንተ መንዜ፣ አንተ ቡልጌ፣ በትውልድ ስፍራ እኮ ጎረቤቶች ናችሁ› ይላቸዋል፡፡ በልሁና አስቻለው ፈገግ ፈገግ በማለት እንደገና እየተጨባበጡ እንደ አዲስ የስም ትውውቅ ያደርጋሉ፡፡ ከዚያ በኋላ፣ መንገድ ላይ በተገናኙ ቁጥር ጠበቅ ያለ ሰላምታ መለዋወጥ ይቀጥላሉ፡፡ አንዳንዴም ሻይ ቡና መገባበዝ ይጀምራሉ፡፡

ከወራት በኋላ ሁለቱን የበለጠ የሚያቀራርብ አጋጣሚ ተፈጠረ፡፡ አንድ ምሽት ላይ በልሁ በአንድ ቡና ቤት ውስጥ በተለምዶ ባለጌ ወንበር ተብላ በምትጠራ መቀመጫ ላይ ቁጭ ብሎ ይጠጣል፡፡ አንዲት የቡና ቤቱ አስተናጋጅ አጠገቡ ቆም እያለች ታጫውተዋለች፡፡ በቡና ቤቱ ውስጥ ቁጭ ብለው ይጠጡ የነበሩ አራት ጎረምሶች ልጅቷን እየፈለጉ በልሁን መተናኮል ይጀምራሉ፡፡ በልሁ ግን ንቋቸው ዝም ብሎ ልጅቷን ያጫውታል፡፡ ቆየት ብሎ ከጎረምሶቹ መሀል መስከር የጀማመረው አንዱ ልጅቷን በሀይል ጎትቶ ሊወስድ ይደርሳል፡፡ ሲጀምር ድንገት አስቻለው ይደርሳል፡፡ ወደ ልጅቷና በልሁ መራመድ ሲጀምር ድንገት አስቻለው ይደርሳል፡፡ ጎረምሳውን ሊመታ ሲል

በልሁ ከተቀመጠበት ባለጌ ወንበር ላይ ወርዶ ጎረምሳውን ሊመታ ሲል አስቻለው ይይዘውና ወደ ጎረምሳው ዞር ብሎ ‹አንተ እረፍ እንጂ› ይለዋል፡፡ ጎረምሳው ግን ‹ምን አገባህ› ብሎ በአስቻለው ላይ ያፈጣል፡፡ አስቻለው

ደግሞ ሲያስጠነቅቀው ያ ጎረምሳ ጭራሽ ሊመታው ይጠጋዋል፡፡ በዚህ ጊዜ ጎረምሳው የተማመነባቸው ጓደኞቹ አስቻለውንና በልሁን ሊመቱ ግርር ብለው ወደ እነሱ ይመጣሉ፡፡ ድብድብ ይጀመራል፡፡ አስቻለውና በልሁ ከወንበር ወደ ወንበር፣ ከጠረጴዛ ወደ ጠረጴዛ እየዘለሉ አራቱን ጎረምሶች እመድ ያደርጓቸዋል፡፡ ሁሉንም ይዘርሯቸዋል፡፡ በድብድቡ ምክንያት የቡና ቤቱ ዕቃዎች እንዳሉ ይሰባበራሉ፡፡ ወንበሮች ይሰባበራሉ፡፡ ይሆማሉ፡፡ ፖሊስ ይደርሳል፡፡ በልሁና አስቻለው ታስረው ያድራሉ፡፡ በፖሊስ ጣቢያ ውስጥ ሲያድሩ እንትልፍ አልወሰዳቸውም ነበር፡፡ ሲያወሩና ሲጫወቱ ያጋልጣሉ፡፡ ጠዋት በዋስ ሲለቀቁ ሁለቱም ወደ አስቻለው ቤት ነበር የሄዱት፡ በእንቅልፍ እረፍ ሲሉ፡፡ በልሁ ከአስቻለው ቤት ሲገባ በቅድሚያ ዓይኑ ያረፈው በአስቻለው አልጋ ፊትለፊት ለጫት መቃሚያ የተነጠፈች በምትመስል ፍራሽ ላይ ነበር፡፡

«ጫት ትቅማለህ እንዴ?» ሲል አስቻለውን ይጠይቀዋል፡፡

«እንዲያውም»

«ፍራሿ ታዲያ…»

«ባልቅምም ሲቃም ደስ ስለሚለኝ አንዳንዴ የሥራ ባልደረባዬ እየመጣ ይቅምባታል፡፡»

«መርዕድ የሚባል ጓደኛ አለኝ፡፡ እኔና እሱም እንቅምባታለን፡፡»

«ትችላላችሁ፡፡»

በልሁ ብዙም ሳይቆይ መርዕድን አምጥቶ ከአስቻለው ጋር ያስተዋውቀዋል፡፡ ከዕለቱ ጀምሮ በዚያች ፍራሽ ላይ ተቀምጠው ይቅሙባታል፡፡ ይቀጥላሉ፣ ያዘወትራሉ፡፡ ይስማማሉ፡፡

አንድ ቅዳሜ ቀን በልሁና መርዕድ አስቻለውን ከነናቸው አስቀምጠው ጫት ደመት ባለ ሁኔታ ጫት እየቃሙ በመጫወት ላይ ሳሉ ታፈሡ ወትሮም እንደምታደርገው ሁሉ ወደ አስቻለው ቤት ጎራ ትላለች፡፡ የዕለቱ አለባበሷ እጅግ ያማረና ፈገግታዋ የተለየ ነበር፡፡ ነጫጭ የሀገር ልብስ ለባለ እንቁጣጣሽ መስላለች፡፡ የሦስቱ ጓደኛሞች አቀማመጥ አስደስቷት ይበልጥ ፈገግ ብላ አየቻቸውና «እቤት ደስ ስትሉ…» እያለች ወደ ውስጥ ትገባለች፡፡ ሁሉም ብድግ ብለው ይቀበሏታል፡፡ ይጨባበጣሉ፡፡ አስቻለው ከበልሁና ከመርዕድ ጋር ያስተዋውቃታል፡፡ ለትንሽ ሰዓት አብራቸው ትቆያለች፡፡ ይጫወቷታል፡፡ በልሁና መርዕድ የታፈሡን ቁንጅና፣ የአነጋገር ለዛዋንና ፈገግታዋን እያዩ ሲደነቁ ይቆያሉ፡፡

ታፈሡ ወደ ቤቷ ልትመለስ ከቤት እንደወጣች በልሁ አስቻለውን «ይቺ ሴት ምንህ ናት?» ሲል ይጠይቀዋል፡፡

አስቻለው የበልሁ ስሜት ገብቶት ሳቅ ፈገግ እያለ ‹ምነው ምን ፈለክ?» ይለዋል?፡፡

«አቦ ቆንጆ ናት»፡፡

«የተከበረች ባለ ትዳር ናት»

«ባሏ ዕድለኛ ነው፡፡»

«እንዴት?»

«እንኳን ለአልጋው ለሳሎኑም ጌጥ ናት።» ይሳሳቃሉ።

የታፈሡ የበልሁና የመርዕድ ግንኙነት በእስቻለው ጥግ ይጥባባሉ። ይዋደዳሉ። በልሁ ታፈሡን ያየት ዕለት የስሜት ህዋሳቱ ተንቃንቀው የነበረ ቢሆንም ውሎ እያደረ ግን በእህትነት እቅፏ ውስጥ ይገባል። ሁሉን ነገር እርግፍ አድርጎ በመተው ያከብራታል። የእህትና የወንድምነት ግንኙነታቸው ይጠነክራል። በክፉ በደግ ሳይለያዩ በቤተሰባዊነት ፍቅር ይቀጥላሉ።

ይህ የባዕድ ዝምድና መሠረት በተጣለ በሶስተኛው ዓመት ገደማ ነበር ሔዋን መጥታ ከመሀላቸው የተቀላቀለችው። ታፈሡ፣ በልሁና መርዕድ በእስቻለውና ሔዋን ፍቅር የተደሰቱትን ያህል ስቃያቸውንም አብረው ተሰቃይተዋል። መከራቸውንም ተካፍለዋል። ለቅሷቸውንም አብረው አልቅሰዋል። በሁሉም ነገር ዛሬም አብረው ናቸው።

የሆምሳ አለቃ መኮንን ዳርጌ ድንገት በመሀላቸው ተገኝቶ ስለ እስቻለው ያየውንና የሚያውቀውን ሁሉ ከነገራቸው በኋላ በተለይ በልሁ የእስቻለውን ዱካ እንፍንፎ ለማግኘት ወደ አስመራ ኤርትራ ለመሄድ ሲወስን ውሎ አላደረም፤ አንድ ሳምንት ባልሞላው ጊዜ ውስጥ ዝግጅቱን አጠናቆ ተነሳ። አዎ፣ ወደ አስመራ በረረ።

ዕለቱ እርብ ነው፣ ከቀኑ አሥር ሠዓት አካባቢ። በልሁ ከአስመራ የአይሮፕላን ማረፊያ ክልል ወጥቶ በሩ አካባቢ ተኮልኩለው መንገደኞችን ይጠባበቁ ከነበሩ ታክሲዎች መካከል ተረኛውን ጠየቀና ወደተጠቆመበት ታክሲ አመራ። አንድ ቀጠን ያለ መልከ መልካም የታክሲ ሾፌር የመኪናውን በር ከፍቶ በእጁ ጠቀሰው።

«የት መሄድ ፈለጉ?» አለ ሾፌሩ በልሁን አስገብቶ በሩን ከዘጋ በኋላ።

«ሰራዬ መናፈሻ»

«መናፈሻውን ነው ወይስ አካባቢውን የሚፈልጉት?» ሲል ጠየቀው ሾፌሩ ወደ ኋላው ዞር ብሎ በልሁን እየተመለከተ።

«ራሱን መናፈሻውን።»

«ማረፊያ አለ ብለው ነው?»

«የለውም እንዴ?»

«መኖር ነበረው፣ ነገር ግን መናፈሻው በአሁኑ ጊዜ ዝግ ነው።»

«ለምን ተዘጋ?» አለ በልሁ ደንግጦ።

ሾፌሩ አንገቱን ወዲያ ወዲህ መለስ ቀለስ አደረገና «ምክንያቱን እንኳ እንጃ! ከተዘጋ ግን ከዓመት በላይ ሆኖታል።» አለው

«እና እዚያ ውስጥ ሰው ፈልጌ ማግኘት አልችልም?» አለ በልሁ አንገቱን ወደ ሾፌሩ ሰገግ አድርጎ።

«ምን ሰው አለና!»

በልሁ ቅስሙ ስብር አለ። ከሆምሳ ዓለቃ መኮንን ዳርጌ የተሰጠው ምልክትና አድራሻ ያ መናፈሻ ብቻ ነበር። የሆምሳ አለቃ ራሱ በአስመራ ከተማ ውስጥ ከዚያ መናፈሻ በስተቀር ሌላ አካባቢ ብዙም አያውቀውም። የአስመራ ቆይታው አጭር ስለነበር ተዘዋውሮ አላየውም።

«ምን ይሻለኛል ታዲያ የኔ ወንድም?» ሲል በልሁ ጭንቅ እያለው ሾፌሩን ጠየቀው።

«እኔ እንጃ!» አለና ሾፌሩ ለአፍታ ያህል ቆየት ብሎ ወደ በልሁ ዞር በማለት «እዚያ የሚሰራ ሰው ነበር የሚፈልጉትን?» ሲል ጠየቀው።

«እዚያ አዘውትሮ የሚገባ ወንድሜን ነበር።»

«ታዲያ እንዱ ጋ አረፍ ብለው ያፈላልጉታላ»

በልሁ ለአፍታ ያህል ፀጥ ብሎ ሲያሰላስል ቆየና «እስቲ ጥሩ ማረፊያ ወደምትለው ሆቴል ውሰደኝ።» አለው። የበልሁ ተክለ ሰውነታዊ ገፅታና በራሱ አንደበት ‹ጥሩ ማረፊያ› በማለት በተናገረው ቃል መሰረት ጥሩ ኗሪ እንደሆነ የገመተው ሾፌር «ወደ ኮምፒሽታቶ ይሻልዎታል» አለው።

«ኮምፒሽታቶ ምንድነው?» ሲል ጠየቀው በልሁ ቃሉ የተለየ ትርጉም ካለው ብሎ በማሰብ።

«መሀል ከተማ ላይ የሚገኝ ቦታ ነው። ጥሩ ጥሩ ሆቴሎችም የሚገኙት በዚያው አካባቢ ነው።» አለ ሾፌሩ።

«እሺ እንሂድ!»

በእርግጥ በልሁም የገንዘብ ችግር የለበትም፣ እንደ አጋጣሚ ሆኖ ከሞቱት ወራት በፊት ወላጅ አባቱ ‹እስቲ ብትኖርበትም፣ ብትሸጠውም ቦታ መያዝ ደግ ነውና ቤት ለመስራት ሞክር› በማለት ከሰጡት በርካታ ገንዘብ ላይ ግማሽ ያህሉን በመንገድ ሻንጣው ውስጥ አድርጎ ይዞት ሄዷል።

እስቻለውን በመፈለግ ሂደት ታሪካዊቷን የአሥመራ ከተማ ለማየት ይጓጓ የነበረው በልሁ ገና ከጅምሩ መንፈሱ በስጋት በመወጠሩ በሚጓዝበት ጎዳና ግራና ቀኙ ያሉትን የከተማዋን ገፅታዎች እንኳ ልብ ብሎ ሳያይ የ ባለ ታክሲ ተጉዞ ተጉዞ ከአንድ አካባቢ ሲደርስ ዳር ይዞ በመቆም «ኮምፒሽታቶ ማለት ይህ ነው!» አለው።

«ወደ አንዱ ሆቴል ጠጋ ብታደርገኝ»

«ይቻላል» አለና ሾፌሩ ከመንታ መንገዱ ወደ ቀኝ ታጠፈና ‹ኒያላ ሆቴል› ከተባለ ሆቴል በር ላይ አደረሰው።

በልሁ የታክሲ አገልግሎት ክፍያውን ከምስጋና ጋር ከፈለና የልብስ ሻንጣውን ትከሻው ላይ አንግቶ ወደ ሆቴሉ የእንግዳ መቀበያ ክፍል አመራ። አልጋ ሲጠይቅ መኖሩ ተነገረው። አንድ አስተናጋጅ ከፊት ከፊት እየመራ ወሰደውና ክፍሉን አሳየው። ክፍሉ ንፁህና ግሩም የሚባል አልጋ አለው። በልሁ የክፍሉን በር ዘግቶ አልጋው ላይ አረፍ በማለት ስለገጠመው ችግር ያሰላስል ጀመር። ማሰቡ ግን መላ አላስገኘለትም። ይልቁንም የባሰ ጭንቅ ጭንቅ ይለው ጀመር።

በመሀል አንድ ነገር ትዝ አለውና ከዚያው ጋር በተያያዘ ሌላም ነገር ቆጨው፡፡ በመሠረቱ አስቻለው አካል ጉዳተኛ ነው፡፡ ብዙ መጓዝ ስለማይችል ቤት የሚከራየው በሚሰራበት አካባቢ ሊሆን ይችላል፡፡ ስራዬ መናፈሻ ውስጥ የሚያዘወትር ከሆነም ቤቱም ሆነ መሥሪያ ቤቱ በዚያው አካባቢ ከመሆን እንደማያልፍ ገመተና ያንን ባለ ታክሲ ብመናፈሻው አካባቢ ማረፊያ ካለ ወደዚያ አድርሰኝ፣ ሳይለው በመቅረቱ ነበር ቁጭቱ፡፡ ሆኖም አሁንም ሳይዘገይ ጥሩ ሀሳብ እንደ መጣለት አስቦ ጭንቀቱ ከፊል ሲለለት ሀሳቡን ሰብስቦ አደረገና ወደ መታጠቢያ ክፍል ሊገባ ፈለገ፡፡ የሚለብሰውን ፒጃማ አዘጋጅቶ ሊታጠብ ገባ፡፡

ታጥቦ አበጥሮ ሲያበቃ ምግብ አሰኘው፡፡ ወደ ሆቴሉ ሬስቶራንት ጊዜ ከበላ በኋላ በቀጥታ ከሆቴሉ ቅጥር ግቢ ወጣ፡፡ ሰዓቱ ከአስራ ሁለት አልፍ ብሏል፡፡ የመንገድ መብራቶች በርተዋል፡፡ ከሆቴሉ በስተግራ አቅጣጫ ተራመደና መንታውን መንገድ አቋርጦ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ ያራመድ ጀመር፡፡ የምሽት የአስመራ ውበት ማራኪ ነው፡፡ እየሩም ሞቅ ያሉ መብራቶች የደመቁ፡፡ የከተማዋ አቀማመጥ ማራኪ፡፡ መንገዶች ንፁህና የተስተካከሉ፡፡ በልሁ በሁሉም የአስመራ ገፅታ እየተደሰተ በግምት እስከ ሶስት መቶ ሜትር ከተጓዘ በኋላ በስተቀኙ በኩል አንድ በበረንዳው ላይ በርካታ ወንበሮች የተደረደሩበት፣ በሰው ብዛት ሞቅ ደመቅ ያለ ሆቴል አየና ጎራ አለበት፡፡ ሰው አልባ የነበረች ጠረጴዛ አግኝቶ ቁጭ እንዳለ አንዲት ወፈር ያለች ጠይም ጎፈሬ አስተናጋጅ ቀረብ አለችውና፡-

«እንታይ ክዕዘዝ» አለችው፡፡

«ትግሪኛ አልችልም፡፡» አላት በልሁ ቀና ብሎ በፈገግታ እያያት፡፡

«ሞይ! ይቅርታ የኔ ወንድም!» ብላ አስተናጋጇ በፈገግታ አየት ካደረገችው በኋላ «ምን ሊታዘዝ ማለቱ እኮ ነው፡፡» አለችው፡፡

በልሁ በልጅቷ ትህትናና ፈገግታ ደስ ብሎት እሱም ፈገግ በማለት «ቢራ አምጭልኝ» አላት፡፡

አስተናጋጇ ቢራውን ይዛ መጥታ በብርጭቆ ሞላችለትና ከአጠገቡ ራቅ ብላ የግድግዳ ጥግ ደገፍ ብላ ቆመች፡፡ በልሁ ልጅቷ ያሳየችውን ትህትና እስታውሶ ሁኔታዋ ደስ ስላለው በልቡ ስላለው ጉዳይም ሊያወያያት ፈልጎና ሊጠራት አሰበ፡፡ ነገር ግን በዚያች ቅጽበት ማጣደፉ ለሌላ ነገር ይመስላታል በማለት ለጊዜው ተወት አረገው፡፡ የመጀመሪያውን ቢራ ጨርሶ ሁለተኛውን ስታቀርብለት ግን እንደ ምንም ጨከነና፡-

«የኔ እህት ላነጋግርሽ እፈልግ ነበር!» ሲል ጠየቃት፡፡

«ምን?» አለችው አስተናጋጇ ጠጋ ብላ፡፡

«ቁጭ ማለት አትችይም?»

«እችላለሁ፡፡» ብላው ቁጭ ልትል ወንበር ሳብ ስታደርግ በልሁ «እየጠጣሽ ነዋ» ቀደማት፡፡

አስተናጋጅዋ ሳቅ እያለች ወደ ውስጥ ገባችና ለራሷም ቢራ ይዛ በመምጣት ከፊትለፊቱ ቁጭ አለች፡፡

«አስመራ፡ ከተማዋም ሰዎቿም በጣም ደስ ትላላችሁ፡፡» አላት በልሁ ፈገግ ብሎ እየተመለከታት፡፡

«አይደል?» አለች አስተናጋጇም እንደ መሽኮርመም እያረጋት፡፡

«በእውነት ታምራላችሁ፡፡»

«እናመሰግናለን፡፡»

በልሁ አስተናጋጇን እያጫወተ ትንሽ ሲያሳስቃት ከቆየ በኋላ ወደ ዋና ጉዳዩ ተመለሰ፡፡ «አንድ ነገር ብጠይቅሽ ታውቂ ይሆን?» ሲል ጠረጴዛውን ደገፍ ብሎ ዓይን ዓይኗን እያየ ጠየቃት፡፡

«ምን?»

«እዚህ አስመራ ውስጥ ብሩዬ ሞናፊኝ የሚባል ሆቴል እንዳለ ሰምቻለሁ፡፡ የት አካባቢ ይሆን?»

«ያ የተዘጋው?»

«ሲሉ ሰማሁ፡ ግን ለምን እንደተዘጋ ታውቂያለሽ?»

«ኧረ እኔ አላውቅም!» አለችና አስተናጋጇ በልሁን ለየት ባለ አስተያየት ታየው ጀመር፡፡ በእርግጥ በልሁም የአስተያየቷ መለወጥ ገብቶታል፡፡

«ምነው? መጠየቁ ቅር አለሽ እንዴ?» ሲል ጠየቃት፡፡

«አይ...እሱ እንኳ...» ብላ ንግግሯን ቆረጥ ስታደርገው በልሁ ጣልቃ ገባ፡፡

«ቅር ካለሽ ጥያቄዬን እንሳለሁ፡፡» አለና ብርጭቆውን ብድግ አድርጎ ቢራውን ተጎነጨ፡፡

«የሸዋ ሰዎች እኮ አትታመኑም፡፡» ብላ አስተናጋጇ በቅንድቧ ስር አሾልካ በልሁን አየት አደረገችው፡፡

«የሸዋ ሰው መሆኔን በምን አወቅሽ?» አላት በልሁ እንደመገረም ብሎ፡፡ ለነገሩ አልተግባባውም፤ በልሁ የሸዋ ሰው ስትለው የደብረ ብርሃን ተወላጅ መሆኑን ያወቀች መስሎት ነው፡፡ እሷ ግን ቀደም ሲል 'ትግሪኛ አልችልም' ስላለትና ለበርካታ የአስመራ ሰው ትግሪኛ የማይችል ሁሉ የሸዋ ሰው እንደሆነ ተደርጎ ስለሚገመት ነው፡፡

«ትግሪኛ አልችልም አላልከኝም?» አለችው ፈገግ እያለች፡፡

«ትግሪኛ የማይችል ሁሉ የሸዋ ሰው ነው እንዴ?» ሲል ጠየቃት፡፡

«ታዲያ ከየት ሊባል ነው?»

«ብዙ አገር አለ እኮ!»

«ለእኛ ግን ትግሪኛ የማይችል ሰው የሸዋ ወይም የመሀል አገር ሰው ነው የሚባለው፡፡»

በልሁ ምስጢሩ ገባው፡፡ እንደ መሳቅ አለና «ጥሩ እሺ» ካለ በኋላ «ግን ለምን አንታመንም?» ሲል ጠየቃት፡፡

«እኔ እንጃ! ግን የሸዋን ሰው አትመኑ ሲባል እሰማለሁ፡፡» አለችው የቢራዋን ጠርሙስ አንገት ይዛ ሽክርክር ሽክርክር እያረገች፡፡

በልሁ ስሜቷን እየተረዳ ሲሄድ ራሱንም ወዝወዝ ወዝወዝ አደረገና ትኩር ብሎም ተመለከታት፡፡ ሆድ ሆዱንም ይቆጨው ጀመር፡፡ ከአፍታ ዝምታ በኋላ «ለነገሩ እኮ እኛም እናንተን እናምናችሁም» አላት የምትመልሰውን ለመስማት ጓጓ ብሎ እየጠበቃት፡፡

«ደሞ እኛ ምን አደረግን?»

«ማድረጉን ምንም አላደረጋችሁም፡፡ እኛም ብንሆን ምንም አላደረግንም፡፡ ግን ገገሮቻችን ብዙ ሊያደራርጉን ስለሚፈልጉ እንዳንተማመንና እርስ በእርሳችን እንድንጠራጠር ያደርጉናል፡፡ ይህ የኔና የአንቺ አለመተማመን እንኳ በመጠኑም ቢሆን እየተሳካላቸው መሆኑን የመለከታል፡፡» ካለ በኋላ እጆቹን አቆላልፎ ጠረጴዛው ደገፍ በማለት «አያሳዝንም?» ሲል ጠየቃት፡፡

«እጅ እንጃ!» አለችና አስተናጋጇ ቢራዋን ጎንጨት እያለች አካባቢዋን ቃኘት ቃኘት ታደርግ ጀመር፡፡

«አንድ ነገር ልንገርሽ!» አላት በልሁ አሁንም ትኩር ብሎ እያያት፡፡

«ምን?»

«የለ መተማመናችን ምስጢር ምንም ይሁን ምን፣ እንዳንተማመን ያደረጉን ወገኖች ዓላማቸው ምንም ይሁን ምን፣ ውጤቱም የቱንም ያህል የከፋ ይሁን፣ ነገር ግን የአንዲት አገር ልጆች ነን፡፡ ዘመን በዘመን ተሸሮ ጊዜን ጊዜ ሲተካው ዞሮ ዞሮ አንድ መሆናችን አይቀርም፡፡» አላት፡፡

«ሊሆን ይችላል»

«አትጠራጠሪ፡፡» አላትና በልሁ ስለዛሬው ጉዳዩ ሊያወያያት በማሰብ

«እስቲ ለዛሬ እንኳ ታምኚኝ ከሆነ ስለ ሰራዬ መናፈሻ የጠየኩበትን ምክንያት ዝርዝር አድርጌ ልንገርሽ፡፡» አላት፡፡

«ምንድነው እሱ?» ብላ ጓጓ አለችና ትመለከተው ጀመር፡፡

በልሁ ወዲያው ጀመረ፡፡ በቅድሚያ ለአስመራ እንግዳ መሆኑን ነገራት፡፡ ወደ አስመራ የመጣበትን ምክንያት አስከተለ፡፡ ስለ አስቻለው ሁኔታ ገለጸላት፡፡ የአስቻለውንና የመናፈሻዋን ቁርኝት አስረዳት፡፡ የመናፈሻዋ መዘጋት ያስከተለበትን ስጋት አብራራላት፡፡

አስተናጋጇ በፅሞና ነበር ያዳመጠችው፡፡ ከልቡ እየተናገረ መሆኑን ከአጠቃላይ ገፅታው ትረዳ ነበር፡፡ በተለይ ስለ አስቻለው ሁኔታ ሲተርክላት ፊቷ በሀዘን ስሜት ይሞላ ነበር፡፡ በልሁ ነገሩን ሲያጠቃልል ራሷን ለብዙ ጊዜ ወዘወዘች፡፡ በመጨረሻም በረጅሙ ተነፈሰችና፡-

«ያሳዝናል» አለችው፡

«ፈቃደኛ ከሆንሽ እርጂኝ!»

«መናፈሻው የተዘጋው ባለቤቱ የሻቢያ አባል ሆኖ ስለተገኘ ነው፡፡» አለችው፡፡

«እ!» አላት በልሁ ይበልጥ እንድታብራራለት ፈልጎ፡፡

«ለሰበቡ አንድ የጦር ሜዳ ተዋጊ የነበረ ሰው በዓልቤርጎው ውስጥ ... የጦር መሳሪያዎችም አብረውት ነበሩ፡፡ ሰውየው ግን እጅ እርፎ ተገኘ፡፡

... ብሎ ተዋግቶ እዚያው ሞተ፡፡ የመናፈሻዋ ባለቤትና ሰራተኞችም ... እየተያዙ ታሰሩ፡፡ ብቻዬ የዚያን ዕለት መላ አስመራ ከተማ ቀውጢ ... የሆነችው፡፡ በርካታ ወጣቶች መንገድ ላይ ተገድለዋል፡፡ ... ከመናፈሻው ባለቤት ጋር ግንኙነት አላቸው ተብለው የተጠረጠሩ ... ቀናት ሲለቀሙ ዋሉ፡፡ ስለዚህ ስለዚያ መናፈሻ ማውራት ራሱ ... ነው፤ እኔም ትድም ችላ ያልኩህ፡፡» አለችው፡፡

«ደንበኞችም ሞተው ይሆን?» ሲል በልሁ እየፈራ ጠየቃት፡፡

«እሱን እንኳ እርግጠኛ አይደለሁም፡፡»

በልሁ ጥርጣሬ ገባው፡፡ መንፈሱ ተጨነቀ፡፡ በረጅሙ ተነፈሰና ወደ ... ትርትር ብዙ ከአሰበ በኋላ እንደገና ወደ አስተናጋጇ ቀና በማለት «... መናፈሻዋ የምትገኝበት አካባቢ የት ነው?» ሲል ጠየቃት፡፡

አስተናጋጇ በእጇ ወደ ምዕራባዊ አስመራ አቅጣጫ እያመለከተች «... በኩል ነው፤ ወደ አባ ሻውል ሲሄዱ ወደ ግራ ወረድ ሲሉ የሚገኝ አካባቢ፡፡» አለችው፡፡

«ታክሲ ይገባዋል?»

«በእግርም ይቻላል፡፡»

«አመሰግናለሁ የኔ እመቤት!» አለና በልሁ ከኪሱ ገንዘብ እያወጣ «... ስንት ይሆን?» ሲል ጠየቃት፡፡

«ሦስት ቢራ አይደል፤ ሦስት ብር ብቻ፡፡» አለችው፡፡

በልሁ አስር ብር ሰጣትና «በተረፈው አንቺ ጠጪ፡፡ እኔ ግን መንገድ ... ስለዋልኩ ይከዋኛልና ወደ ማረፊያዬ ልሂድ፡፡» አላት፡፡

... በጥሩ ስሜትና ፈገግታ ተሰነባበቱ፡፡

የበልሁ የማግስቱ የመጀመሪያ ስራ አስተናጋጇ በጠቆመችው አቅጣጫ ሄዶ ያቺን መናፈሻ ማግኘት ነበር፡፡ በእርግጥም ብዙ ሳይቸገር አገኛት፡፡ ሲያዩዋት ደስ የምትል መናፈሻ የነበረች ትመስላለች፡፡ ግቢዋ በልዩ ልዩ ተክል ያሸበረቀ ነው፡፡ ዋናው ቡና ቤት መሀል ላይ ይገኛል፡፡ በአራት ማዕዘን ቅርፅ ጥርብ ድንጋይ የተሰራ ነው፡፡ በየአትክልቱ መሀል አልፎ አልፎ ... መዝናኛ ጎጆዎች ይታያሉ፡፡ ከአንዱ ወደ ሌላው መተላለፊያ መንገድ ... የተሰራ ነው፡፡ አሁን ግን የዛፎቹ ቅርንጫፍ ስለማይከረከም እየተዝ... ይመስላሉ፡፡ በዚያ ላይ የወፎች ኩስ ተንጠባጥቦባቸው ተዥጎርጉረዋል፡፡ ... ዙሪያ አጥር ከታች አንድ ሜትር ያህል በግንብ፤ ከላይ ደግሞ የዚያን ... በብረት ፍርግርግ የታጠረ ነው፡፡ ዋና መግቢያው በር በብረት መዝጊያ ... ተከርችሟል፡፡ አንድ ሰው ብቻ ይጠብቀዋል፡፡

በልሁ የዚያች መናፈሻ የቀድሞ ገፅታ በእዝነ-ልቦናው ታየውና እንባ ... አስቻለውን በዚያ ውስጥ አስታወሰው፡፡ አስቻለው አሁን እዚያ ... እያለ፤ ነገር ግን ቢጠራው አልሰማ፤ እጁን ቢዘረጋ አልደርስበት ያለው ... ሆዱ ባባ፡፡ እንባውም ፈሰሰ፡፡ መሀረቡን አውጥቶ አይኑን ጠረግ ... ሲያደርግ ድንገት ድምፅ ሰማ፡፡ ከመናፈሻዋ በር ጠባቂ በኩል ነበር፡፡

«ምን አሉኝ ጌታዬ?» ሲል በልሁ ወደ ሰውየው እያየ ጠየቀው፡፡

ሰውየው አሁንም ተናገሩ። ነገር ግን በትግሪኛ ስለነበር ለበልሁ አልገባውም።

ሰውየው ከስልሳ አለፍ የሚሉቸው ይመስላሉ። የሰማያዊ ካኪ ኮታ ለብሰው ራሳቸው ላይ የዘበኛ ቆብ አድርገዋል። እላቸውም አማርኛ በደንብ አይችሉ ናር በእጃቸው እያመለከቱ «ወዲያ ወዲያ...» አሉት። በልሁም ከዚህ አካባቢ ሂድ ማለታቸው እንደሆን ገብቶት ከቦታው መራቅ ጀመረ።

ከአባ ሻውል በስተደቡብ አቅጣጫ በሚወስደው አጧራማ መንገድ ላይ ዝም ብሎ ይራመድ ጀመር። ያ አካባቢ ከሌላው የአስመራ አካል ጋር ሲነጻጸር ደከም ያለ ነው። ሰው ግን ይበዛበታል። በየመንገዱ ዳር ያሉት ቤቶችም ደከም ያሉ ናቸው። ሞቅ ደመቅ ያሉ ቡና ቤቶች አይታዩበትም፤ ትንንሽ ግሮሰሪዎች፣ ጠላና እንዲሁም አረቄ ቤቶች ይበዙበታል።

በልሁ ድንገት በል በል አለውና ከአንድ ጠላ ቤት ውስጥ ገባ። ሰዓቱ ገና ከአራት ብዙም አላለፈም። ነገር ግን በርካታ ጠጪዎች ቤቱ ውስጥ አሉ። ባለ ጠላ ቤቷ ሳይሆኑ የማይቀሩ አንዲት ወደ ሃምሳ የሚጠጋቸው ቀይ ረጅም ዘንካታ የሆኑ ሴት ወይዘሮ ወንበር ላይ ጉብ ብለው በየመደቡ ላይ ተቀምጠው ከሚጠጡ ሰዎች ጋር ይጫወታሉ። ቋንቋቸው ትግሪኛ ነው።

በልሁ ገብቶ ሲቀመጥ ምን ልታዘዝ የሚል አስተናጋጅ አልቀረበም። ጠላ ቤት ነውና መስተንግዶው የታወቀ ነው። አንዲት ከፊቱ ጎስቆል ያለች ልጅ እግር ሴት በጣሳ ጠላ ይዛለት ቀረበች። በእጁ ሰጠችው። በልሁ ጠላውን ቀመስ ሳያደርግ ወለል ላይ ቁጭ አደረገው።

እኒያ ነጫጭ የሀገር ልብስ ለብሰው ወንበር ላይ ቁጭ ያሉት ቀይ መልከ መልካም ሴት በልሁን አየት አደረጉና «ብርጭቆ ከህበካ?» አሉት በትግሪኛ።

«ምናሉኝ እማማ?» አለና በልሁ «ትግሪኛ አልችልም» አላቸው።

«ዋይ!» አሉና ሴትዮዋ «ብርጭቆ ይሰጥህ ወይ ማለቴ እኮ ነው።» አሉት።

«አያስፈልግም እማማ! አመሰግናለሁ!» አለና ጣሳውን አንስቶ ፉት አለ።

«የሸዋ ሰው ነህ?» ሲሉ ጠየቁት ሴትየዋ ፈገግ እያሉ።

«አዎ» አላቸው። በልሁ ያቺንም የማታውን አስተናጋጅ አስታወሳት።

«አይዞህ የኔ ልጅ! በል ጠጣ!» አሉትና ሴትዮዋ ወደ ሌሎች ጠጪዎች ዞር በማለት ጨዋታቸውን ቀጠሉ።

በልሁ አልፎ አልፎ ጠላውን ፉት እያለ የሚያወሩት ነገር ባይገባውም የጠጪዎችን ወሬ ሲያዳምጥ ብዙ ቆየ። በየመሀሉ ግን ልቡን ዳዳ የሚያሰኘው ነገር አለ። ሊናገር ከአሁን አሁን ሲል ድንገት ሴትዮዋ ቀድመው አናገሩት።

«ተጫወት የኔ ልጅ!።» አሉት በልሁን ፈገግ ብለው እያዩ። በልሁ ጣሳውን እያነሳ ሳለ ሴትዮዋ ቀጠሉ። «ቋንቋችንን አታውቀው፤ እንዴት እናናግርህ?» አሉት እጆቻቸውን በጉልበቶቻቸው ስር አጣምረው ፊት ለፊት እየተመለከቱት።

«ኧረ ይሁን፤ ምንም አይደል!» ብሎ በልሁ ወዲያው ደግሞ «በዚህ አካባቢ የሚያውቋቸው የሚሲዮናች ሀኪም ቤት ይኖር ይሆን እማማ?» ሲል ጠየቃቸው።

ሴትዮዋ ትንሽ አሰብ አደረጉና «እነዚያ ጥሊያኖቹ?» ሲሉ ጠየቁት።

«ይሆናሉ። በእርግጥ ፈረንጆች ናቸው።»

«ከዚህ ወደታች በኩል ነበሩ። ነገር ግን አሁን እኮ ከዚያ ቦታ ለቀዋል።» አሉት።

«ለቀዋል?» በልሁ አሁንም ደንገጥ እያለ።

«ቆዩ እኮ!»

«ምን ያህል ጊዜ ሆናቸው?»

ሴትዮዋ በቀጥታ ለበልሁ ምላሽ ሳይሰጡ ወደ ጠጪዎቹ ዞር በማለት በትግሪኛ ያነጋግሯቸው ጀመር። ደግመው ደጋግመው ከተመላለሱ በኋላ ሴትዮዋ ፊታቸውን ወደ በልሁ መለስ አድርገው «ከዓመት በላይ ይሆናቸዋል ነው የሚሉኝ» አሉት።

በልሁ እንደገና ወሽመጡ ቁርጥ አለ። አጋጣሚዎች ለምን እንደሚደጋገሙበት ግራ ገባው። እዝን ባለ ፊት፣ ትክዝ ባለ አነጋገር «በቃ ይተውት እማማ!» አላቸውና ጣሳውን አንስቶ ፉት ካለለት በኋላ መልሶ አስቀመጠው። ወደ መሬት አጎንብሶ ራሱን ደጋግሞ ወዘወዘው።

«ልትታከም ኖሯል?» ሲሉ ሴትዮዋ ጠየቁት።

«አይደለም። እነሱ ጋር ይሰራ የነበረ ሰው እፈልግ ነበር።» አላቸውና አሁንም ወደ መሬት ጎንበስ አለ።

«አየየ.... ለቀዋላ!» ብለውት ሴትዮዋ ወደ ጨዋታቸው ተመለሱ።

በልሁ ከዚያ በኋላ ብዙ መቆየት አልፈለገም። እስከ አሁን ባገኘው መረጃ የእስቻለው ዱካ በቀላሉ እንደማይገኝ፣ ምናልባትም ጭራሽ ሳይገኝም እንደሚችል ፈራ። ውስጡም ተናደደ። ተስፋው እየጨለመ ሄደ።

ወዲያው አንድ ነገር ታየው፤ ወደ አረፈበት ሆቴል መብረር። እዎ ሄደ። በጠራራ ፀሐይ በእንሶላና ብርድ ልብስ ጥቅልል ብሎ ተኛ፤ እስቻለውን እንዳያገኝ ከጋረደው የጭንቅ ጉም ያመለጠ መሰለው።

የሰው ልጅ የቱንም ያህል ቢያስብ፣ ቢጨነቅ ወይም ቢናደድ፣ ቢበሳጭ አሊያም ቢፈራ፤ በአጠቃላይ በየትኛውም ስሜት ውስጥ ቢሆን በህይወት ለመሰንበት የግድ የሚያስፈልገው አንድ ነገር አለ፤ ምግብ። በልሁ በእንሶላና በብርድ ልብስ ውስጥ ቢደበቅም አላመለጠውም፤ እጅሬ ርሀብ ከውጭ ሳይሆን ከውስጥ የሚነሳ እሳት ነውና አንጀቱን ይሞረሙረው ጀመር። ከአንድ ጣሳ ጠላ ሌላ የቀመሰው ነገር ባለመኖሩ ከቀኑ ዘጠኝ ሰዓት አካባቢ ከተኛበት ስቅስቆ አስነሳው። ምሣ አይሉት ራት አደባልቆ ሊበላው ወደ ሆቴሉ ሬስቶራንት ወረደ። ሚሲዮኖቹ ሀኪሞች ይሰሩ ከነበሩበት አካባቢ በመልቀቅ ዜና ተበሳጭቶ ሳይበላ ሳይጠጣ በመዋሉ መንፈሱ ድክምክም ብሎበት የነበረው በልሁ ምሳ በልቶ ቀዝቀዝ ያለ ለስላሳ ከውሃ ጋር እየቀላቀለ ሲጠጣ በዚያው ልክ ተነቃቃ። ረጋ ብሎ ማሰብም ጀመረ።

አንድ ነገር ታየው፡፡ ሚሲዮናቹ ሃኪሞች እንደ መሆናቸው መጠን ከክፍለ ሀገሩ ጤና ጥበቃ ጽህፈት ቤት ጋር በአንድ ወይም በሌላ መንገድ ግንኙነት ሊኖራቸው እንደሚችል ታሰበው፡፡ ምናልባትም የስራ ፈቃድ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ያ ከሆነ ደግሞ ወቅታዊ ሪፖርቶች ይጠበቁባቸው ይሆናል፡፡ በዚያው መጠን በሁለቱ አካላት መካከል መተራረብና የአድራሻ ልውውጥ ሊኖር ይችላል፡፡ ሚሲዮናቹ እዚያው አስመራ ካሉም እዚያው ሊፈልጋቸው፣ ወደ ሌላ ክፍለ ሀገርም ተዛውረው ከሆነ በአሉበት ቦታ መሄድ እንዲችል በትድሚያ ወደ ክፍለ ሀገሩ ጤና ጥበቃ ጽህፈት ቤት ሄዶ አድራሻቸውን ሊጠይቅ ወሰነ፡፡ በእርግጥም ጥሩ ሀሳብ የመጣለት መሆኑ ተሰማውና ልቡን ደስ አለው፡፡

ማግስቱ እሁድ ስለሆነ የመንግስት መስሪያ ቤት አይከፈትም፡፡ ዕለቷን ግን በከንቱ ማሳለፍ አልፈለገም፡፡ ወዲያው ትዝ ያለው ያንኑ የተዘጋ የሚሲዮናች የቀድሞ መስሪያ ቤት መፈለግና በዚያው ዙሪያ የእስቻለውን ዱካ ማነፍነፍ ነበርና ትናንት ወደ ሰራየ መናፈሻ የሄደበትን መንገድ ይዞ ተጓዘ፡፡ ከጠዋቱ ሶስት ሰዓት አለፍ ብሏል፡፡ ጠላ የጠጣባትን ቤት ሳይቸገር አገኛት፡፡ ሴትዮዋ የጠቆሙትን አቅጣጫ በመያዝ ቁልቁል ወደ አስመራ ከተማ ደቡባዊ ምስራቅ አቅጣጫ ተጓዘ፡፡ በየመንገዱ የሚጠይቃቸው ሰዎች እያመላከቱት ትክክለኛውን አቅጣጫ ይዞ እንዲጓዝ ረዱት፡፡

በግምት ከተኑ አራት ሰዓት አካባቢ ያን ቀድሞ የሚሲዮናች መስሪያ ቤት አገኘው፡፡ ዙሪያው በረጅም ግንብ የታጠረ ሰፊ ግቢ ነው፡፡ ቤቱ በርካታ ክፍሎች ያሉት ባለ አንድ ፎቅ ነው፡፡ በሩ ግን የመደበኛ ወታደር መለዮ በለበሰ ሰው ይጠበቃል፡፡ በልሁ ለመጠጋት ፈራ፡፡ በዓይኑ ስረት እያረገ እያየው ፊትለፊት ባለው መንገድ ላይ ሲዘዋወር ከቆየ በኋላ አንድ ብቻውን የሚሄድ ወጣት ቢጤ አገኘና «የኔ ወንድም!» አለው በአጠገቡ አለፍ ሲል ሲል::

«አቤት!»

«ይሄ ቤት ቀደም ሲል ሃኪሞች ይሰሩበት እንደነበር አውቃለሁ፡፡ አሁን ግን በሩ ላይ ወታደር ሳይ ጊዜ ለመግባት ፈራሁ፡፡ ሌላ መስሪያ ቤት ሆኖ ይሆን?» ሲል ጠየቀው::

«የአንድ የጦር ጀኔራል መኖሪያ ሆኗል!» አለው ወጣቱ በልሁን አየት እያረገ፡፡

«ከመቼ ጀምሮ?»

«ከዓመት ያልፈዋል፡፡»

«ሃኪሞቹ የት ሄደው?» አለ በልሁ ትናንት ተናድዶ ሳይጠይቅ የቀረውን ጥያቄ ማንሳት ፈልጎ፡

«አላውቅም፡፡» ብሎት ወጣቱ ርምጃውን ሊቀጥል ሲል፡፡ «ሰፈርህ እዚሁ ነው የኔ ወንድም?» ሲል ጠየቀው ወጣቱ ሳይሄድበት ፈጠን ብሎ::

«አዎ»

«ይህ ቤት ሃኪም ቤት በነበረበት ወቅት ከሰራተኞቹ መሀል ለየት ያለ ሰው ታውቅ ነበር?» ሲል ጠየቀው ፈራ ተባ እያለ፡፡

«በምን የሚለይ?»

«አካል ጉዳተኛ የሆነ፡፡»

«ብዙ አካል ጉዳተኞች ነበሩ፡፡ ግን የማናቸውንም ስም አላውቅም፡፡ ሲወጡ ሲገቡ ብቻ ነበር የማያቸው፡፡» አለው ወጣቱ አሁንም ርምጃውን ሊቀጥል ዳዳ እያረገው፡፡

«እግሩ ተቆርጦ ሰው ሰራሽ እግር የተተካለት ታውቅ ነበር?» አለው በልሁ አሁንም ፈጠን ፈጠን ባለ አነጋገር፡፡

«አዎ፡፡ ስሙን ግን አላውቀውም፡፡»

«ፊቱም ላይ ጠባሳ ነበረው፡፡»

«ያውም እስከ ጆሮው ድረስ፡፡» አለው ወጣቱ የበለጠ ገፋ አድርጎ፡

«የት አካባቢ ይኖር እንደነበር የምታውቀው ነገር ካለ የኔ ወንድም?»

«ብዙ ጊዜ ሰራተኞች በመኪና ስለሚገቡና ስለሚመጡ መኖሪያቸው ራት ሳይል አይቀርም፡፡» ካለ በኋላ ወጣቱ «ግን ለምንድን ነው ይኸን ያህል የምትመረምረኝ?» ሲል ኮስተር ብሎ በልሁን ጠየቀው፡፡

በልሁ ዛሬም ያቺን መጀመሪያ ያነጋገራትን የቡና ቤት አስተናጋጅ አስታወሰ፡፡ ከእሷ ይበልጥ ይኼኛው ወጣት ብዙ እንደታገሰው ተረዳና «ይቅርታ የኔ ወንድም» ብሎ ጉዳዩን አጠር አድርጎ አስረዳው፡፡

ወጣቱ ርምጃውን ቀጠለ፡፡ በልሁ ግን እዚያው ባለበት አቀርቅሮ ቆመ፡፡ ወጣቱ አስቻለውን በዓይን እንደሚያውቀው ተረድቷል፡፡ ነገር ግን የሰራተኞች በመኪና መግባትና መውጣት ጉዳይ መኖሪያቸው የግድ በዚያ አካባቢ ላይሆን እንደሚችል አመለከተው፡፡ በዚያው ልክ በልሁ ተስፋ ቆረጠ፡፡ በንገው ዕትዱ ላይ ብቻ አተኮረ፡፡ ሲያስብበት ውሎ ሲያስብበትም አደረ፡፡

ሰኞ ዕለት ጠዋት አረፋፍዶ ከመኝታው ተነሳ፡፡ አለባበሱንም ለየት አደረገው፡፡ ዲላ ውስጥ ለሰርግ ወይም ለየት ላለ ድግስ ካልሆነ በቀር አዘውትሮ የማይለብሰውን ደብዘዝ ያለ ሰማያዊ ሙሉ ልብስ ለብሶ የጥቁርና የነጭ ቡራቡሬ ክራባት አሰረ፡ ጥሩ ቁርስ በላ፡፡ ትናንት ቦታውን አጥንቶት ወደነበረው የክፍለ ሀገሩ ጤና ጥበቃ ጽህፈት ቤት አመራ፡፡ ከጠዋቱ ሶስት ሠዓት አካባቢ ከቅጥር ግቢው ውስጥ ገባ፡፡ ‹የአስተዳደር ምክትል ስራ አስኪያጅ› የሚል ጽሁፍ ወዳለበት ቢሮ ልቡ አደላ፡፡ በፀሐፊዋ በኩል አመራና በር ላይ ቆሞ፡-

«ጤና ይስጥልኝ!» አላት፡፡

«አብሮ ይስጠን» አለችና ፀሃፊዋ ከመቀመጫዋ ብድግ አለች፡፡ አጠር ብላ ወፈር የምትል፣ የቀይ መልክ መልካም የሆነች፣ ዕድሜዋ ወደ አርባ የሚጠጋት ሴት ወይዘሮ ናት፡፡ አጠር ያለ ፀጉሯን ጆንትራ አበጥራለች፡፡

«ሃላፊውን ማነጋገር እችላለሁ?»

«ስለምን ጉዳይ?»

በልሁ የልቡን መዘርዝር አልፈለገም፡፡ ያን ጉዳይ ከእንባ ጋር አይመለከቷቸውም ልትለው እንደምትችል አሰበና «የግል ጉዳይ ነው፡፡» ካላት በኋላ፣ የምታዝንለት መስሎት «የመጣሁትም ከሲዳሞ ነው» ሲል ገለጸላት፡፡
ቡሉፋዋ ወንበር እያሳየችው «ይቀመጡ» ብላው ወደ አስታዋ ቢሮ ገባች፡፡ ብዙ፣ ሳትቆይ ወዲያው ተመለሰችና «ይግቡ» አለችው፡፡
የሃላፊው ቢሮ ሰፊት ያለ ነው፡፡ መጠን ሰፊ ወለሉ በአረንጓዴ ቀለም ምንጣፍ የተሸፈነ፣ መስኮቱ በነጭ ስስ እና ቀይ ወፍራም መጋረጃ የተከለለ፣ ከስድስት የማያንሱ ወንበሮች ያሉት ትልቅ የእንግዳ ጠረጴዛ የተንግለለበት፣ ግድግዳው ሹሯሯግ ቀለም የተቀባና ደስ የሚያሰኝ ገፅታ ያለው ነው፡፡
ሃላፊው አቶ ካሀሳይ ገብሩም መልክ መልካም ነው፡፡ ድምቅ ያለ ቀይ ሆኖ ፊቱ ረጅም፣ ፀጉሩ እስከ መሀል እናቱ ተመልጦ ወዙ የሚያጥበረብር፣ ጥቁር ሰማያዊ ሙሉ ልብስ በነጭ ሸሚዝና ጥቁሩ በዛ ያለበት ቡራቡሬ ከረባት ያደረገ፣ አፍንጫው ሰልከክ፣ ዓይኖቹ ጎላ ያሉና ዕድሜው ከአርባ አምስት ዓመት የማያንሰው ጎልማሳ ነው፡፡
«ጤና ይስጥልኝ!» አለ በልሁ ወደ ውስጥ ገብቶ ሃላፊውን እጅ እየነሳ፡፡
«አብሮ ይስጥልን!» ብሎ ካሀሳይ ከወንበሩ ብድግ ብሎ ተቀበለው፡፡ ሰማቸውን በመለዋወጥ እጅ ለእጅ ተጨባበጡና በካሀሳይ ግብዣ በልሁ ከእንግዳ መቀበያ ወንበር ላይ ተቀመጠ፡፡
«ምን ልርዳዎት አቶ በልሁ?» ሲል ካሀሳይ በልሁን ጠየቀው፡፡
«ችግር ገጥሞኝ ነው አቶ ካሀሳይ»
«ምን ዓይነት ችግር?»
በልሁ የመጣበትን አገርና ለምን ወደ አስመራ እንደመጣ በአጭሩ ከአስረዳ በኋላ «ወንድሜ በሚሲዮናች ክሊኒክ ውስጥ ይሰራ እንደነበር ተጠቁሚ ነበር፡፡ የሚሲኒዮቹን የስራ ቦታ አጠያይቄ ባገኘውም ነገር ግን ከአንድ ዓመት በፊት ከዚያ ቦታ እንደለቀቁ ሰማሁ፡፡ ምናልባት ከሙያ አንጻር የምታውቋቸው ከሆነና አሁን የሚገኙበትን ቦታ ትጠቁመኝ ከሆነ ብዬ ነበር፡፡» አለና በልሁ ካሀሳይን ቀና ብሎ ተመለከተው፡፡
«የት አካባቢ የነበሩት ናቸው?» ሲል ካሀሳይ በልሁን ጠየቀው፡፡
«ቀበሌውን በትክክል አላወኩትም፡፡ ነገር ግን አባ ሻውል ከሚባለው ቦታ ወረድ ብሎ በምዕራባዊ የከተማዋ ዳርቻ የሚገኝ ክሊኒክ እንደ ነበር ማወቅ ችያለሁ፡፡»
ካሀሳይ ሚሲዮኖቹን ያወቃቸው ይመስላል፡፡ አንገቱን ነቅነቅ ነቅነቅ ካደረገ በኋላ «ታዲያ እነ እነሱ አስመራ ውስጥ አይደለም ቦታ የቀየሩት፣ ጠቅላላ ከሀገር ተባረረዋል» አለው፡፡
«ተባረረዋል?» ሲል ጠየቀ በልሁ፡፡ ዓይኖቹ ፍጥጥ ብለው በካሀሳይ ላይ ተተከሉ፡፡
«ከዓመት በላይ ሆናቸው»

«በምን ምክንያት ተባረሩ አቶ ካሀሳይ? ምናልባት ወንድሜም አብሮ ተባረረ ይሆን?» ሲል በስጋት ስሜት ውስጥ ሆኖ ጠየቀው፡፡
«ወንድምህ እንኳ አብሮ ሊባረር የሚችልበት ሁኔታ የለም፡፡ እነሱ የተባረሩት ከሀገር ውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ገቡ ተብሎ ነው፡፡»
«በፖለቲካ?»
«መሆኑ ነዋ! ለነገሩ እነርሱም አያርፉ፣ ነገሮች ሁሉ እንደ ራሳቸው ሀገር እየመሰላቸው የኛ መንግስት አካሄድ ሳይጥማቸው ሲቀር በአገኙት አጋጣሚ ሁሉ ወጋ ማድረግ ይወዳሉ፡፡» አለ ካሀሳይ ፈገግ ብሎ የበልሁን ምላሽ እየጠበቀ፡፡
በልሁ ፈጥኖ ለካሀሳይ መልስ መስጠት አልፈለገም ወይም አልቻለም፡፡ ዓይኑን ብቻ ትክል አድርጎ ካሀሳይን ያየው ጀመር፡፡ እንዲያውም ቀስ በቀስ ዓይኖቹ በእንባ ይሞሉ ጀመር፡፡
«ምነው አቶ በልሁ?» ሲል ካሀሳይ የበልሁ ስሜት መለዋወጥ አስገርሞት ጠየቀው፡፡
በልሁ አሁንም መልስ ከመስጠት ይልቅ ፊቱን ከካሀሳይ ላይ መልሶ ወደ ጠረጴዛው በማጎንበስ በእንባ የሞላውን ዓይኑን በመሀረብ ይጠርግ ጀመር፡፡
«አቶ በልሁ!» አለ ካሀሳይ ይበልጥ እየደነገጠ፡፡
«ሆዴ አዘነ አቶ ካሀሳይ!»
«ምነው? ወንድምህ አብሮ የተባረረ መሰለህ?»
«አይደለም አቶ ካሀሳይ፣ የዕድሉ ነገር አሳዝኖኝ ነው፡፡» አለና ንግግሩን በማራዘም «አዬ አቶ ካሀሳይ፣ ወንድሜ የጤና ባለሙያ እንጂ ፖለቲከኛ አልነበረም፡፡ ነገር ግን በሄደበት ቦታ ሁሉ የፖለቲካ መዘዝ አልለቀው አለ፡፡» አለው አሁንም የዓይኖቹን እንባ እየጠራረገ፡፡
«ማለት?»
«ወንድሜ ገና ልጅ ሳለ የሚረዳው ወንድሙ በፖለቲከኞች ተገድሎበት በችግር ተማረ፡፡ በስንት ስቃይ ትምህርቱን ጨርሶ ስራ ከያዘም በኋላ አሁንም ፖለቲከኞች ሰላም ነስተው ሲያዋክቡት ኖሩ፡፡ የኋላ ኋላም በግፍና በተፅዕኖ ወደዚህ ክፍለ ሀገር በ እናት ሀገር ጥሪ ሽፋን አስገድደው ላኩት፡፡ በእነሱ ጦስ አካሉን አጣ፡፡ እዚሁ ከተማ ውስጥ አዘውትሮ ያርፍባት የነበረችው ሰራዬ መናፈሻ ደግሞ ከፖለቲካ ጋር በተያያዘ መዘጋቷን ሰማሁ፡፡ እነሆ አሁን ደግሞ አርስዎም አሰሪዎቹ በፖለቲካ ጉዳይ ከሀገር መባረራቸውን እየነገሩኝ ነው፡፡ ይህ የፖለቲካ ጉዳይ እኔም እንዳሳገኘው ምክንያት ሊሆን ነው፡፡ ታዲያ ይሄ አያሳዝንም አቶ ካሀሳይ?» ሲል በልሁ የተሰማውን ጥልቅ ሀዘን ለካሀሳይ ገለፀለት፡፡
ካሀሳይ ገብሩ በሰማው ታሪክ፣ በበልሁ አለቃቀስና የነገሮች አገላለፅ የእሱም ልብ ተነካ፡፡ በልሁን ያህል ግርማ ሞገሱ ግጥም ያለ የወጣት ጠንበለል ከፊቱ ቁጭ ብሎ እንባውን እያፈሰሰ ብሶቱን ሲገልጽለት የእሱም አንጀት ተላወሰ፡፡ ወንድ ልጅ ሲከፋው እንባው ምን ያህል ቅርብ እንደሆነ ከመቼውም

ጊዜ በዓይ ሲረዳ ሆዱ ተንቦጫቦጨ፡፡ በሀዘን ስሜት ራሱን ደጋግሞ ወዘወዘና በልሁን ትኩር ብሎም ተመለከተው፡፡ በልሁ አሁንም ንግግሩን ቀጠለ፡፡

«በቃ እኮ አቶ ካህሳይ፣ ከእንግዲህ ወንድሜን ላላገኘው ነው፡፡» አለው እንባው በዓይኖቹ ላይ ተቋጥሮ ሰማይ እየመሰለ፡፡

ካህሳይ ገብሩ አሁንም ለአፍታ ያህል በሀዘን ዓይን ከተመለከተው በኋላ ራሱን ለረጅም ጊዜ ወዝውዞ በረጅሙ ተንፈሰና «ለመሆኑ የወንድምህ ስም ማን ይባላል?» ሲል ጠየቀው፡፡

«አስቻለው ፍሰሀ፡»

«እዚያ አልዘኝ ቦታ ላይ ይሰሩ ከነበሩ ሚሲዮኖች ጋር ይሰራ እንደነበረ እርግጠኛ ነህ?»

«በቂ የሆኑ አመልካች ምልክቶችን አግኝቻለሁ፡፡ በአመዛኙም እርግጠኛ ሆኛለሁ፡፡»

ካህሳይ ገብሩ በልሁን እየተመለከተ ትንሽ ከቆየ በኋላ ፈጠን ባለ ሁኔታ የስልክ እጀታ አነሳ፡፡ ቁጥሮችን አዙሮ ያዳምጥም ጀመር፡፡ ከትንሽ ቆይታ በኋላ መናገር ጀመረ፤ በስልክ፡

«ሄሎ አቶ ሀይለአብ... የእነዚያ ባለፈው ዓመት ከሀገር የተባረሩ የማሊያን ሚሲዮኖች ፋይል በቅርብ ይገኝልሀል... እስቲ ያቀርቡት በነበረው ዓመታዊ የስራ ሪፖርት ላይ በሰው ሀይል ዝርዝራቸው ውስጥ የስራ ማዕረጉ ነርስ የሆነ አስቻለው ፍሰሀ የሚባል ሰው ተመዝግቦ ከሆነ አይተህ ብትነግረኝ.... ጎሽ የኔ ወንድም ደውልልኝ እጠብቅሀለሁ፡፡» አለና ስልኩን ዘጋው፡፡ ወዲያው ወደ በልሁ ዞር ብሎ ሲመለከት በረጅሙ ሲተነፍስ አየው፡፡

«ሰማህ አቶ በልሁ!» ሲል ጀመረ ካህሳይ ገብሩ በሁለት ክንዶች ጠረጴዛ ተደግፎ ፊት ለፊት በልሁን እየተመለከተ፡፡

«አቤት አቶ ካህሳይ!»

«ስሜትህ ሁሉ ገብቶኛል፡፡ አሳዝነኸኛልም፡፡ ግን አንድ ነገር እንድትረዳልኝ እፈልጋለሁ፡፡ ትቀበለኝ ይሆን?»

«ምን ይሆን አቶ ካህሳይ?»

«የወንድምህ በፖለቲካ መዘዝ መሰቃየት የዕድሉ ወይም የዕድለ ቢስነቱ ውጤት አይደለም፤ ኢትዮጵያዊ በመሆኑ ብቻ የሚጠብሰው እሳት ነው፡፡ ይህ ደግሞ ምናልባት ልክ እንዳንተ ወንድም ጠባሳው ጎልቶ አይታይብን እንደሆነ እንጂ እኔም አንተም በአጠቃላይ ኢትዮጵያውያን ሁሉ በፖለቲካ እሳት የተቃጠልንና በመቃጠል ላይ የምንገኝ አሳዛኝ ፍጡራን ነን፡፡ እንዲያውም ነደን ነደን እንዳናልቅ መሰጋትና መፍራት ያለብን ዜጎች ነን፡፡» ካለ በኋላ ካህሳይ ምራቁን ዋጥ አድርጎ ለአፍታ ያህል ካሰላሰለ በኋላ ንግግሩን ቀጠለ፡፡

«እየህ አቶ በልሁ! ለዚህ ደግሞ ምክንያቷ ሀገራችን ኢትዮጵያ አይደለችም፡፡ ምናልባት እኛ ዜጎቿና ይበልጥ ግን ፖለቲከኞቻችን ናቸው፡፡ የሀገራችን ፖለቲከኞች የሚመሩበትና የሚያራምዱት የፖለቲካ አስተሳሰብ ከራሳቸው ጥቅም ባለፈ ለሀገርና ለወገናቸው ምንም እንደማይጠቅም ራሳቸው ጠንቅቀው ያውቁታል፡፡ ይህም ስለሆነ ሕዝባችን ተቀብሎናል ብለው

ስለማያምኑ እንዲያውስ የእያንዳንዱ ግለሰብ ወይም ማህበረሰብ የተቃውሞ ኮሽታ ዝምታው ራሱ ያስፈራቸዋል፡፡ ኮሽታውን ለማምከን በሃይል ይመቱታል፣ ዝምታውንም ትኩሳት ለማዳመጥ ሆን ብለው ራሳቸው ይቀሰቅሱታል፡፡ በአጠቃላይ ስለሚፈሩ ሕዝባቸውን ማሳረፍ አይፈልጉም፡፡ ለዚህም ሲባል የሚደገፉበት የእንቅስቃሴ ዘርፍ የለም፣ ከግለሰብ ህይወት ጀምሮ በዕድሩ፣ በትዳሩ ፣ በእርሻው በንግዱ፣ በእምነት በሃይማኖት... ወዘተ፡፡ ከዚያም ባለፈ የእያንዳንዱን ግለሰብ የየዕለት እንቅስቃሴ ካልተከታተሉ አይሆንላቸውም፡፡ ፈሪዎች ናቸውና ማስፈራራት የወገብ ቀበቷቸው ነው፡፡ በዚህ መሀል ተጎጂው እያንዳንዱ ግለሰብ ነው፡፡ እያንዳንዱ ማህበረሰብ ነው፡፡ የዚህ ሁሉ ጠቅላላ ድምር ውጤት ደግሞ የመላ የሀገራችን ሕዝብ ጉዳትና ስቃይ ነው፡፡» ካለ በኋላ ካህሳይ ገብሩ ንግግሩን ጠበቅ በማድረግ «ታዲያ በእንዲህ ያለ መከራ ውስጥ ከተዘፈቀ ማህበረሰብ ውስጥ የተወለደው የአንተ ወንድም የፖለቲካና የፖለቲከኞች ሰለባ ቢሆን ምን ያስደንቃል?» ሲል ጠየቀና ወደ ኋላ ወንበሩን ደገፍ በማለት የበልሁን ምላሽ ይጠባበቅ ጀመር፡፡

በልሁ ፍዝዝ ብሎ ካህሳይን እየተመለከተ በፅሞና ያዳምጥ ነበርና ካህሳይ ንግግሩን ለጊዜው ቆም ሲያደርግ እስከ አሁን አምቆ ይዞት የነበረውን ትንፋሽ «እሁሁ.....» በማለት በረጅሙ ተንፍሶ አወጣው፡፡ በካህሳይ አነጋገር ተደንቆም ለረጅም ጊዜ ራሱን ወዘወዘ፡፡

«ተሳሳትኩ አቶ በልሁ?» ሲል ጠየቀው ካህሳይ የበልሁን አኳኋን ፊት ለፊት እየተመለከተ፡፡ በልሁ ግን ለካህሳይ ጥያቄ ቀጥተኛ መልስ ከመስጠት ይልቅ ሀሳቡ በትክክል የገባው መሆኑን በሚገልጽ አነጋገር

«የመጨረሻው ነገር አያስፈራም አቶ ካህሳይ?» ሲል ጠየቀው፡፡

ካህሳይ አሁንም በሁለት ክንዶች ጠረጴዛውን ተደግፎና «ያስጨንቃል!» ሲል ቀጠለ፡፡ «እንደምታውቀው ሀገሪቱ ዳር እስከዳር በጦርነት እየታመሰች ነው፡፡ ሁሌም እየደማች ነው፡፡ በየቀኑ እየቆሰለች ነው፡፡ ከተፋላሚ ወገኖች የሚሰማው ሁሉ የጀግንነት ወሬ እንጂ የተለየ የፖለቲካ አመለካከት ወይም የተለየ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ፍልስፍና አይደለም፡፡ በተቃውሞ ወገን የተሰለፈው ቡድን እሸንፎ ስልጣን ቢይዝ እንኳ የሀገራችንና የህዝቦቿ ዕጣ ፈንታ ምን ሊሆን እንደሚችል በግልጽ አይታወቅም፤ ምናልባት ሰዎች በሰዎች ተለውጠው የጭቆና አገዛዙ መልክና ባህሪ ይለወጥ እንደሆነ እንጂ!! እንዴት ብትለኝ ድሉ የጠመንጃ እንጂ የአዲስ ሀሳብና አመለካከት ስለማይሆን፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ከዚህ ጦርነት በኋላ ሌላ ጦርነት ላለመነሳቱ እንዳች ዋስትና ሊኖር አይችልም፤ ሌላ የተከፋ ቡድን መሸመቁ አይቀርምና፡፡» ካለ በኋላ ካህሳይ ንግግሩን በባሰ እልህና ስሜት ቀጠለ፡፡

«ያ ከሆነ የባሰ ችግር ሊያስከትል ይችላል አቶ በልሁ፡፡ እየህ፣ አንድ ጦርነት ወደ ሌላ ጦርነት እየተሸጋገረ የሕዝብ ስቃይና መከራ በተራዘመ ቁጥር ሕዝብም ከሕዝብ እየተለየና እየተከፋፈለ ይሄዳል፤ በዘር፣ በሃይማኖት፣ በቋንቋ፣ በጎሳ...ወዘተ፡፡ ምናልባት ገዢዎች በስልጣን ላይ የመቆያ ዘዴ ይሆናቸው ዘንድ ይህን የሕዝብ የመከፋፈል እዝማሚያ ለራሳቸው ሲሉ

ያበረታቱትም ይሆናል፡፡ በህዝብ መካከል ጠብና ጥላቻ፣ ጥርጣሬና ፍርሀት በማስፈን እነሱ ከሌሉ አደጋ ሊፈጠር እንደሚችል እስመስለው ለማውራት ይችሉ ዘንድ የከፋ ውጥረትን ሊፈጥሩ ይችላሉ፡፡ ያም ሆኖ የተወጠረ ነገር ውሎ አድሮ መበጠሱ አይቀርምና የከፋ አደጋ የሚፈጠረውም ያኔ ነው፡፡»

«ይታይህ አቶ በልሁ! ሁለት የፖለቲካ ቡድኖች ተፋልመው ሊላውን አሸንፎ ስልጣን ቢይዝ ቢያንስ አንፃራዊ ሰላምና መረጋጋት እንኳ ይችላል፡፡ ነገር ግን በዘር፣ በሃይማኖት፣ በጎሳና በቋንቋ ተከፋፍሎ የተፋጠጠ ሕዝብ ባለበት አገር ውስጥ ድንገት አንድ ቀን የሽብር ፊሽካ የተነፋች እንደሆን ማነው ያንን እሳት የሚያጠፋው? ማነው ያን የመከራ ሌሊት የሚያነጋው? ማነው ያን ጨለማ የሚገፈው?» ካለ በኋላ ካህሳይ ፊቱን ላብ ላብ እያለው፣ የእፍንጫው ቀዳዳዎች ሳብ ገተር እያሉና ዓይኑንም ፍጥጥ አድርጎ በልሁን እየተመለከተ «በኔ እምነት ፈንድቶ ፈንድቶ የማያልቅ የበቀል ቦንብ፣ መግለ የማይጠግግ የሀገር ቁስል፣ ወርዶ ወርዶ የማይቆም የሕዝብ እንባ ያስከትላል ብዬ እፈራለሁ፣ ኢትዮጵያውያን እርስ በእርሳችን እየተረጋገጥን በራሳችን ላይ የምናመጣው ምፅዓት!!» አለና ዓይኖቹን በበልሁ ላይ ተከላቸው፡፡

በልሁ ተገኔ በሕይወቱ ለመጀመሪያ ጊዜ ፈራ፡፡ በተፈጥሮው ጀግና ነበር፣ በግሉ፣ እንኳን አንድ ሰው አስር ሆነው ቢከብቡት ጭራሽ የማይደነግጥ ልበ ሙሉ፣ ቢሰነዝር ከመሬት የሚደባልቅ፣ ቢሰነዘርበት በእስተማማኝ የሚመክት፡፡ ዛሬ ግን ጉዳዩ የሀገርና ሕዝብ ሆነበትና ልቡ ራደ፡፡ መላ ሰውነቱን የቀውስና የሽብር ሹክሹክታ ተሰራጨበት፡፡ ብቻ በረጅሙ ተነፈሰና በወትቱም ያቺን መጀመሪያ አስመራ ከተማ የገባ ዕለት ያነጋገራትን የቡና ቤት አስተናጋጅ ስሜት አስታውሶ፡-

«እንዲያውም እኮ ያ ጊዜ የደረሰ መሰለኝ አቶ ካህሳይ?» አለው ዓይኖቹን ፍዝዝ አድርጎ ካህሳይን እየተመለከተ፡፡

«በጣም ተቃርቧል፡፡ በመገስገስ ላይ ነው፡፡ ይቆም ዘንድ መላ ካልተበጀለት በቀር!! በአጠቃላይ እኛ ዜጎቿ፣ በተለይ በተለይ ገዥዎች ሆድና ስልጣናቸውን ወደ ጎን ትተው ፊጥነው ወደ ህሊናቸው ካልተመለሱ በቀር አደጋው የከፋና አስቃቂ ነው፡፡» ያ አደጋ ከተከሰተ ደግሞ የኔ ስጋት ምን እንደሆነ ታውቃለህ?» አለና በልሁን አከታትሎ ተመለከተው፡፡

«እ» አለ በልሁ ካህሳይ ቀጥሎ ለሚናገረው ነገር በጣም እየጓጓ፡፡

«ወደፊት የዚች ሀገር ታሪክ ሲጻፍ ‹ኢትዮጵያ የምትባል አንድ ሀገር ነበረች› ተብሎ እንዳይጀመር!!»

ከዚህ በኋላ በልሁና ካህሳይ እንዱ የሌላውን ውስጣዊ ስሜት የበለጠ ለመረዳት በመናበብ ላይ ያሉ በሚመስል ሁኔታ እርስ በእርስ በመተያየት ላይ ሳሉ ድንገት ስልክ ጮኸ፡፡ ካህሳይ ስልኩን አነሳና በጆሮው ላይ ለትሞ «ሄሎ... አቶ ሀይለአብ፣ እህ ከምን ደረስክ?... ተገኘ?.... አመሰግናለሁ የኔ ወንድም!» አለና ስልኩን ዘግቶ ወደ በልሁ እየተመለከተ «በእርግጥም የወንድምህን አድራሻ በትክክል ደርሰህበት ኖሯል፡፡» አለው፡፡

«አዎ አቶ ካህሳይ፡ እኔም አልተጠራጠርኩ ነበር፡፡» አለና በልሁ ስለ ...ምክር የፈለገ በሚመስል ዓይነት «ታዲያ እንግዲህ ምን ባደርግ የሚሻል ይመስልዎታል?» ሲል ካህሳይን ጠየቀው፡፡

«በኔ በኩል አንድ ነገር ላደርግልህ የምችል ይመስለኛል፡፡»

«ምን ይሆን አቶ ካህሳይ?» አለ በልሁ ቀልቡ ጓጓ እያለ፡፡

«እነዚህ ሚሲዮን የሚባሉ ነገሮች እኛ መንግስታዊ ያልሆኑ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ወይም በተለምዶ ኤን.ጂ.ኦ የምንላቸው ናቸው፡፡ አስራ አንድ ያህል ድርጅቶች አሁን በአስመራ ከተማ ውስጥ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛሉ፡፡ ብዙ ጊዜ በአንድ ኤን.ጂ.ኦ ያገለገለ ሰራተኛ ያ ድርጅት ሲፈርስ ወይም ሲዘጋ አሊያም በሌላ ሁኔታ ስራ ሲያቆም ሰራተኛው ያለውን የስራ ልምድ በመጠቀም ወደ ሌላው ሄዶ የመቀጠር ልምድ አለ፡፡ የአንተም ወንድም ከነዚያ ከተባረሩት ሚሲዮናዊ ድርጅት ውስጥ እንደ ወጣ ምናልባት በሌላ ድርጅት ውስጥ ተቀጥሮ ከሆነ ልክ ዛሬ አቶ ሀይለአብ እንዳደረገው ሁሉ እኔም ከእሱ ጋር በመተባበር የሌሎቹን ድርጅቶች ሪፖርቶች በመመርመር የወንድምህ ስም ከተገኘ ውጤቱን በአንድና በሁለት ቀን ውስጥ ልገልጽልህ እችላለሁ» አለው፡፡

«አመሰግናለሁ አቶ ካህሳይ!» አለ በልሁ በአክብሮትና በትህትና እጅ እየነሳ፡፡

«የት ነው ያረፍከው?» ሲል ጠየቀው ካህሳይ፡፡

«ኒያላ ሆቴል ሃያ አራት ቁጥር፡፡»

«ጥሩ አቶ በልሁ! በተረፈ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ይሁን፡፡» ብሎ በልሁን በሰላምታ ለመሸኘት ከወንበሩ ላይ ብድግ አለ፡፡ በልሁም ብድግ አለና ለሁለተኛ ጊዜ የከበረ ምስጋናውን አቅርቦ ተጨባብጠው ተሰነባበቱ፡፡

* * *

ስድስት ቀናት አለፉ፣ እንዲያውም በልሁ አስመራ ከገባበት ቀን ጀምሮ ሲቆጠር አሥረኛ ቀን፡፡ የእስቻለው ዱካ ግን አልተገኘም፣ ጭራሽ እየራቀ ሄደ፡፡ የካህሳይ ገብሩ ጥረትም አልተሳካ፣ የእስቻለው ስም በየትኛውም ኤን.ጂ.ኦ የሰው ሀይል ሪፖርት ውስጥ ተካትቶ አልተገኘም፡፡ በልሁ በቀጠሮው ቀን ወደ ካህሳይ ቢሮ ብቅ ባለበት ወቅት የተነገረው ይኸው መጥፎ ዜና ነበር፡፡

በልሁ ከዚያ በኋላ ማድረግ የፈለገው አንድ ነገር ብቻ ነበር፡፡ ሳይታክት ሳይሰለች በአስመራ ከተማ ውስጥ በሚገኙ ቡና ቤቶች ሁሉ እየተዘዋወረ ስለ እስቻለው ወሬ መጠየቅ፡፡ የበልሁ ሀሳብ በየቡና ቤቱ እየተዘዋወረ አስተናጋጆችን በማነጋገር ምናልባት እስቻለው ያዘወትርባት በነበረችው ሰራዬ መናፈሻ ውስጥ ይሰሩ የነበሩ የሆቴል ሰራተኞችን ከአገኘሁ የሚል ነበር፡፡ በእርግጥም አነስተኛ ሻይ ቤቶችና ኬክ ቤቶች ሳይቀሩ በአስመራ ዋና ዋና መንገዶች ላይ የተኮለኮሉትን ቡና ቤቶች ሁሉ ጎበኛቸው፡፡ ከቀትር በፊት ሲሆን ሻይ ቡና፣ ወደ አመሻሹ ላይ ደግሞ ቢራ ወይም ሌላ ዓይነት መጠጥ

እየያዘ በመቀመጥ ብዙዎቹን አነጋገረ፡፡ ሆኖም ፍንጭ እንኳ ሊያገኝ አልቻለም፡፡ እንዲያውም ከሚጠጣው ሻይና ቡና ብዛት የተነሳ ሊያገኝ ተቃጠለ፡፡ ቢራና የአልኮል መጠጡም በተለይ ሌሊት ሌሊት እንጂ እየነሳው ተቸገረ፡፡

በዚህ ሁኔታ ላይ ሰንብቶ ልፋቱ ሁሉ መና ሲቀርበት ሌላ ሙከራ ሊያደርግ አሰበ፡፡ በቀጥታ ወደ ዲላ ስልክ መደወልና ታፈሡን ማግኘት፡፡ በእሷ በኩል የሀምሳ አለቃ መኮንን ዳርጌን ለማግኘት መሞከር፡፡ ሀሳቡም፣ ምናልባት የሀምሳ አለቃ መኮንን ዳርጌ ያን ከአስቻለው ጋር ለመገናኘት ምክንያት የሆነውን የአስመራ ኗሪ ጓደኛውን አድራሻ የሚያቀው ከሆነ ሊጠይቀውና በእሷ እየታገዘ ወደ አስቻለው ለማምራት ነበር፡፡ በልሁ ይህን ያሰበው አስመራ በእሷ በአሥራ አንደኛው ቀን በዕለተ ዕሁድ ላይ ሆኖ ነው፡፡ ታፈሡንም ሆነ የሀምሳ አለቃ መኮንን ዳርጌን በቀላሉ በስልክ ሊያገኝ የሚችለው በመስሪያ ቤት በኩል ስለሆነ ስልክ የመደወል ሙከራውን በማግስቱ ሰኞ ሊያደርግ ወሰነ፡፡

ይህን ሀሳብ ያሰላሰለው በኒያላ ሆቴል ውስጥ አልጋ ላይ ጋደም ብሎ ነው፡፡ ከሙሳኒ ላይ የደረሰውም በዕለቱ ወደ አስር ሰዓት አካባቢ ነው፡፡ በዚያ አልጋ ላይ ለብዙ ጊዜ ቆይቶ ስለነበር ከውሳኔ በኋላ በአስመራ መንገዶች ላይ ጥቂት ሊዘዋወር ፈለገ፡፡ ለባብሶ ወጣ፡፡ ጥቂት ሲዘዋወር ከቆየ በኋላ ሳያስበው ከዚያ አስመራ የገባ ዕለት ጎራ ባለበትና ስለ አስቻለው ለመጀመሪያ ጊዜ የጠየቀት የቡና ቤት አስተናጋጅ በምትሰራበት ሆቴል እግሮቹ አደረሱት፡፡ ጥቂት ለማረፍና ከልጅቷም ጋር ጥቂት ሊጫወት አስቦ ጎራ አለ፡፡ ቁጭ አለና ቢራ አዘዘ፡፡ ልጅቷን ግን በዓይኑ ቢፈልጋትም ሊያያት አልቻለም፣ ወይ የጠዋት ተረኛ ሆና አሊያም በሌላ ምክንያት በእለቱ በሆቴሉ ውስጥ የለችም፡፡ እሱ ግን ብቻውን ቁጭ ብሎ ሲጠጣ አመሸ፡፡ ከምሽቱ ሁለት ሠዓት አካባቢ ሂሳቡን ከፈለና ወደ ማረፊያው ኒያላ ሆቴል አመራ፡፡

ልክ እንደደረሰ የአልቤርጎውን በር ከፍቶ ወደ አልጋው ሊራመድ ሲል አንዲት ለሁለት የታጠፈች ወረቀት ወለሉ ላይ ታየችው፣ በበሩ ስር ወደ ውስጥ የተወረወረች ትመስላለች፡፡ ልቡ ደንገጥ አለና ተኩር ብሎ ተመለከታት፡፡ ወዲያው ብድግ አድርጎ ሲያያት አጭር መልዕክት ይዛለች፡፡

«አቶ በልሁ፣ ከዚህ በታች በተገለጸው ስልክ ቁጥር 'ስዩም' ብለው ይደውሉ፡፡» ይላል የያዘችው መልዕክት፡፡

«አ!» አለ በልሁ ሁለመናውን ነዘር እያደረገው፡፡ «ማነው ስዩም ማለት?» አለ ብቻውን እየተነጋገረ፡፡

ጉዳዩ ከአስቻለው ጋር የተያያዘ መልዕክት ካለው ብሎም ጓጓ፡፡ ቀስ እያለ ሲያስበው ግምቱ ይበልጥ ጠነከረ፡፡ ጭራሽ ስልክ ለመደወል ቸኮለ፡፡ ያቺ ወረቀት ከእጁ ሾልካ የምትጠፋበት መስሎት በመዳፉ ውስጥ ጭብጥ አደረጋትና በችኮላ የአልቤርጎውን በር ዘግቶ ወደ ውጭ በረረ፡፡ ከኒያላ ሆቴል አጥር ግቢ ወጥቶ መንገዱ ላይ እንደ ደረሰ በመንገድ ላይ በቡድን ሆነው እየሄዱ የነበሩ ሰዎችን በጅምላ ጠየቃቸው፡፡

«ስልክ በቅርብ የት አገኛለሁ ወንድሞቼ?»

«በዚያም በዚህም ሞልቷል!» አለው ከመንገደኞች አንዱ፡፡ በልሁ ወደ አትጣጤ መሮጥ እንዳለበት ሲያስብ አሁንም ከመንገደኞች አንዱ ወደ ያን አትጣጤ እያመለከተ «በዚህ በኩል በቅርብ ታገኛለህ፡፡» አለው፡፡

በልሁ በዚያው አትጣጤ ሮጠ፡፡ አንድ ሁለት ሱቆች ውስጥ ሲጠይቅ አንዱ ጋር ስልክ አያስደውሉም፣ ሌላኛው ደግሞ ለጊዜው ስልኩ ተበላሽቶ ኖሮ «አይሰራም» አለችው ሱቅ ጠባቂዋ፡፡ በጠየቀበት በአምስተኛው ሱቅ ውስጥ አገኘና ደወለ፡፡

«ሄሎ!» አለችው አንዲት ሴት፡፡

«አቶ ስዩምን ፈልጌ ነበር የኔ እመቤት!»

«ይጠብቁ!» ብላው ሴትዮዋ የስልኩን እጀታ በሆነ ነገር ላይ ስታስቀምጥና በርቀት አጠራር «ስልክ ይፈልግሀል ስዩም» ስትል በስልኩ ውስጥ ተሰማው፡፡ በልሁ ከስዩም ድምጽ በፊት ወደ ስልኩ እየቀረበ ስለመሆኑ ለማወቅ ኮቴውንም በጥንቃቄ ያዳምጥ ጀመር፡፡ በእርግጥም ተሰማው፡፡

«ሄሎ!» አለ ወንድ ሰው፡፡

«አቶ ስዩም ነዎት ጌታዬ?»

«አዎ ነኝ»

«በልሁ እባላለሁ፡፡ አልቤርጎ ውስጥ መልዕክትዎን አግኝቼ ነው፡፡»

«አ፣ ነዎት? አስቻለው ፍሰሀ የሚባል ሰው በመፈለግ ላይ ያሉት?»

«አዎ ጌታዬ!» አለ በልሁ፡፡ ልቡ በድንጋጤ ትርትር ሊል የደረሰ መሰለው፡፡

«ታዲያ ለምን አመሹ? በጊዜ አይደውሉም ነበር? እኔ እኮ አስር ሠዓት አካባቢ ነበር መልዕክቱን ያስቀመጥኩልዎት፡፡» አለ ስዩም፡፡

«እኔም እኮ በዚያው አካባቢ ነው ከክፍሉ የወጣሁት፣ ለጥቂት ተላልፈን እንደሆነ እንጂ!» አለና በልሁ አጋጣሚው እንዳያመልጠው በመስጋት «ወይ እኔ ወደ እርሶ ልምጣ?» ሲል ጠየቀው፡፡

«መቼ? አሁን?»

«ምንም ችግር የለብኝም ጌታዬ!»

«ቸኩለዋል ማለት ነው?»

«በጣም አቶ ስዩም፣ እጅግ በጣም!»

«በቃ እኔ እመጣለሁ፡፡ ባይሆን እንዳንጠፋፋ ከክፍልዎ ይጠብቁኝ፡፡»

«ንቅንቅ አልልም ጌታዬ!»

«እሺ መጣሁ፡፡»

ለበልሁና ለስዩም መተዋወቂያ አስቻለውን የመፈለግ ስራ እንደ ምልክትነት የመውሰዱ ጉዳይ ነገሩ ከአስቻለው ጋር የተያያዘ ስለመሆኑ የበለጠ ተስፋ አደረበት፡፡ ግን አስቻለውን የሚያስገኝ ይሆን ወይስ ሌላ ሁኔታውን የሚያውቅበት አጋጣሚ? የበልሁ የዚያች ቅፅበት ሀሳብና ስጋት ሆነ፡፡ ግን የሆነው ይሁን፣ በልሁ ዛሬ ስዩምን ማግኘት አለበት፡፡ ስዩም ደግሞ 'መጣሁ'

አለው እንጂ በምን ያህል ደቂቃ ከኒያላ ሆቴል ሊደርስ እንደሚችል አልገለጸለትም፡፡ በስልክ ያነጋገረው ከሩቅ ይሁን ከቅርብ ቦታ ሆኖ ይሁን አይሁን አያውቅም፡፡ ለማንኛውም ከተጠሮው ቦታ ቀድሞ መድረስ ነበረበትና ስልክ ከደወለበት ሰዓት ጀምሮ እስከ ኒያላ ሆቴል የመኝታ ቤት ቁጥር ሃያ አራት ድረስ ያለውን መንገድ በሩጫ ጨረሰው፡፡ የፎቁን ደረጃዎች እንኳ በሩጫ ነው የረመረማቸው፡፡ ከክፍሉ ደርሶ በሩ ላይ ሰው ያለመቆሙን ሲያረጋግጥ ነው እፎይ አለ፡፡ ወደ ክፍሉ ከመግባቱ በፊት ሽንጥና ሽንጡን ይዞ በመቆም የሩጫ ትንፋሹን ጨረሰና በሩን ከፍቶ ወደ ውስጥ በመግባት አልጋው ላይ ቁጭ አለ፡፡ ቁና ቁና እየተነፈስ በር በሩን ይመለከት ጀመር፡፡ በኮሪደሩ ውስጥ ኮቴ በሰማ ቁጥር ቀልቡ እየተበተነ ደቂቃዎች አለፉ፤ ምናልባት በግምት አሥራ አምስት ደቂቃዎች፡፡

ድንገት አንድ ወፈር ያለ ጠይም ሰው የቤት ውስጥ ነጣ ያለ ቲታውን በነጭ እስኪከር ሜማ ለብሶ በሩ ላይ ከች አለ፡፡ በሩ አካባቢ ቆም ብሎ ፈገግ እያለ ወደ ውስጥ በልሁን እየት ሲያደርገው «አቤት!» አለ በልሁ ከአልጋው ላይ ብድግ በማለት፡፡

«አቶ በልሁ?»

«ነኝ፡፡ አቶ ሰዩም ነዎት?»

«አዎ»

ተጨባበጡ፡፡ በዕድሜ ተመሳሳይ ናቸውና 'አንቱ' መባባሉን ትተው «ታዲየስ- ታዲየስ! ደህና ነህ-ደህና ነህ!» ተባብለው ትከሻ ለትከሻ ተሳሳሙ፡፡

«ወደ ቡና ቤት እንውረድ ይሆን የኔ ወንድም?» ሲል በልሁ ሰዩምን ጠየቀ፡፡

«እዚያም እዚህም ቢሆን ይቻላል!» አለ ሰዩም፡፡

«እዚያም እዚህም ቢሆን ይቻላል!» አለ ሰዩም፡፡

በልሁ ብዙ ጉዳይ አለውና እያዝናና ብዙ ሊያነጋግረው ፈልጎ «የለም ወደ ቡና ቤት ሄደን ሻይ ቡና ብንል ይሻላል፡፡» እያለ በሩን ቆላለፈና ተከታትለው ወደ ቡና ቤት በመሄድ አንዲት ባዶ ጠረጴዛ አግኝተው በመቀመጥ ቢራ አዘዙ፡፡

«የአስቻለው ወንድም ነህ?» ሲል ሰዩም ቀድሞ ጠየቀው፡፡

«አዎ! ግን እንዴት አገኘኸኝ አቶ ሰዩም?» ሲል በልሁ ቀጥሎ ጠየቀው፡፡

«በአጋጣሚ ነው፡፡ አቶ ካሀሳይ ገብሩ የሚባሉ ሰው አነጋግረሃል፡፡ እኔና እሳቸው ደግሞ በቅርብ እንተዋወቃለን፡፡ ትናንትና አብረን ቁጭ ብለን ሳለን በሆነ አጋጣሚ ወሬ ተነሳና አንተ አስቻለው የሚባል ሰው በፍለጋ ላይ እንዳለህ ጠቀሱ፡፡ እኔ ደግሞ አስቻለውን አውቀው ነበርና ‹ነርሱ አስቻለው ፍሰሀ?› ብዬ ስጠይቃቸው ‹ታውቀዋለህ እንዴ?› ሲሉ ጠየቁኝና እንደማውቀው ስነግራቸው ከተቀመጡበት ተነስተው ሳሙኝ፡፡ ከዚያም የአንተን አድራሻ ሰጡኝና አንተንና አስቻለውን እንዳገናኛችሁ ከባድ አደራ ጣሉብኝ፡፡» አለው ሰዩም በማከታተል፡፡

በልሁ «እሁሁ...» ብሎ በረጅሙ ተነፈሰ፡፡ ካህሳይ ገብሩን በሌለበት ክልቡ አመሰገነው፡፡ ወዲያው «አስቻለውን ታውቀው ኖሯል?» አለው በልሁ ለዳርዳርታው፡፡

«አዎ! በአንድ ኤን.ጂ.ኦ ውስጥ የስራ ባልደረባዬ ነበር፡፡»

«አሁንስ?»

«የነበርንበት ኤን.ጂ.ኦ ፈርሶ እኔ በሌላ ኤን.ጂ.ኦ ውስጥ ተቀጥሬአለሁ፡፡ አስቻለው ግን ለጊዜው ስራ አልያዘም፡፡»

«ሥራ አጣ?»

«አጥቶ አይደለም፤ ግን ትንሽ እያመመው ስለሆነ ጤና አጥቶ ነው፡፡...» ብሎ ሰዩም ሊቀጥል ሲል ድንገት አንድ ሰው ከኋላው መጣና ትከሻውን መታ አድርጎ፦

«ደሞ ቴታ ለብሰህ መጠጣት ጀመርክ?» እያለ ከፊት ዞሮ ጨበጠው፡፡ ያው ሰውዬ በልሁንም እየጨበጠ ሳለ ሰዩም፦

«ተዋወቀው፤ የአገር ወዳድ ወንድም ነው፡፡» አለው፡፡

«ክፍሌ—በልሁ» ተባብለው ተዋወቁ፡፡

ክፍሌ እነበልሁ በነበሩበት ጠረጴዛ ላይ ቁጭ እያለና በተለይ ሰዩምን እየተመለከተ «ግን እሱ ልጅ እንዴት ሆነ እባክህ? ሰሞኑን ጠይቄው አላውቅም፡፡ ሻል አላለው ይሆን?» ሲል ጠየቀው፡፡

«ምንም አይለው!» አለና ሰዩም በልሁን አየት አደረገው፡፡

በልሁ ሁለት አዳዲስ ነገሮች በሀሳቡ ገቡ፤ በአንድ በኩል የአስቻለው መታመም፤ በሌላ በኩል ደግሞ አስቻለው ‹አገር ወዳድ› ተብሎ የመጠራቱ ነገር፡፡ በእርግጥ የስሙ ነገር አሳሳቢ አልነበረም፤ አስቻለው የዘመቻ ግዳጁን ከአጠናቀቀ በኋላ ወደ ሀገሩ የመመለስ ፍላጎት ስላልነበረውና ለምን እንደሆነ ጓደኞቹ በጠየቁት ጊዜ የሆዱን በሆዱ እያደረገ ‹ለምን እሄዳለሁ? እዚሁ ሆኜ ሀገሬን ባገለግል አይሻልም!› በማለት ስለሚመልስላቸው ጓደኞቹም ከዚሁ በመነሳት ያወጡለት የቀልድና የምፀት ቅፅል ስም ነው፡፡ ለጊዜው ግን ሁኔታው የበልሁን ልብ ዱ! ማድረጉ አልቀረም፤ አሳሰበው፡፡

«ግን ያመዋል?» ሲል በልሁ ጠየቀ፡፡ የስሙን ጉዳይ ለጊዜው ማንሳት አልፈለገም፡፡

«አዎ! አልፎ አልፎ ቢሻለውም ብዙ ጊዜ ግን ያመዋል፡፡» አለና ሰዩም ጠርሙሱን አንስቶ ቢራውን ተጎነጨ፡፡

«እኔ ግን የእሱ ልጅ ህመም አካላዊ ብቻ አይመስለኝም፤ የመንፈስ ችግርም ያለበት ይመስላል፡፡» ካለ በኋላ ክፍሌ በተለይ ወደ በልሁ ዞር ብሎ «ግን እንዴት ነው የኔ ወንድም፤ አስቻለው ከሀገሩ ወዲህ ወደ አስመራ ሲመጣ በመልካም ማህበራዊ ሁኔታ ውስጥ አልነበረም?» ሲል ጠየቀው፡፡

በልሁ ከምንም በፊት እንባ ቀደመው፡፡ የክፍሌ ግምት ትክክል መሆኑን እሱ ይበልጥ ያውቀዋልና ሁሉንም የአስቻለውን ሁኔታዎች በማስታወስ «አዎ የኔ ወንድም፤ በአስቻለው ሆድ ውስጥ ብዙ ጣጣ አለ፡፡» አለና በዓይኑ ላይ የተንጠለጠለውን እንባ በመዳፉ ሙሉ ጥርግ አደረገው፡፡

ሰዩምና ክፍሌ የበልሁን አኳኋን ሲያዩ ልባቸው ድንገት ድንገት ትኩር ትኩር እያሉ ተመለከቱት፡፡ ሰዩም ቀደም አለና በልሁን ለማፅናናት ያክል «አይዞህ! ያሲጋህ መታመሙ ከሆነ ይህን ያህል በጣና የተጋነነ እንዳይመስልህ፡፡» አለና አሁንም የበለጠ ለማበረታታት ያህል «ነገ ልታገኘው ልታየው አይደል?» አለው፡፡

‹መገኘቱ ጥሩ› አለ በልሁ በሆዱ፡፡ ወዲያው ደግሞ «ብቻ በእጠቃላይ የአስመራ ሰዎች እግዚአብሔር ይስጣችሁ፡፡ ለፍቼ ደክሜ በከንቱ እንዳልቀር ተባብራችሁኛል፡፡» አለና ጣእሙ ምንም ምንም ባይሰውም የቢራ ጠርሙሱን አንስቶ ተጎነጨ፡፡

በመሀል ክፍሌ ከተቀመጠበት ብድግ አለና «ሰዩም እስቲ ባአንድ ጉዳይ ፈልጌሀለሁ፡፡ አንዴ እናግረኝና ትመለሳለህ፡፡» አለው፡፡

«እሬ እኔም ልሄድ ነው ጠብቀኝ፡፡ ይቺን ልጨልጥና አብረን እንወጣለን፡፡» ካለ በኋላ ሰዩም ወደ በልሁ ዞር ብሎ «በቃ የኔ ወንድም፤ ነገ በፈለከው ሰዓት እስቻለው ቤት ወስጄ አገናኝችኋለሁ፡፡» አለው፡፡

«ከቻልክማ በጠዋት ነው አቶ ሰዩም!» አለው በልሁ፡፡

«ችግር የለም፣ በጠዋት ተነስተህ ጠብቀኝ፡፡ እዚሁ ድረስ መጥቼ ይዤህ እሄዳለሁ፡፡» አለና ሰዩም የያዛትን የጠርሙስ ቢራ በአንድ ትንፋሽ ጨልጦ ተነሳ፡፡ ተመሰጋግነው ተለያዩ፡፡

በልሁ አስቻለውን በማግስቱ እንደሚያገኘው እርግጠኛ ሆነ፡፡ ግን ደግሞ በምን ሁኔታ እንደሚያገኘውና እሺ ብሎ ወደ ዲላ የመሄድ ያለመሄዱ ጉዳይ እንደ አዲስ ያስጨንቀው ጀመር፡፡ የህመሙም ሁኔታ በእጅጉ አሳሰበው፡፡ ለስሙ አንሶላና ብርድ ልብስ ለብሶ አልጋ ላይ ተኛ፡፡ ይሁን እንጂ ቀልቡ ሊያርፍ አልቻለም፡፡ መኝታ እንዳልተመቸው ሁሉ ቶሎ ቶሎ ይገላበጣል፡፡ እየጨነቀው ቁና ቁና ይተነፍሳል፡፡ የአስቻለው አጠቃላይ ሁኔታ በእዝነ-ልቦናው እየመጣበት በሀዘን ስሜት አሁንም አሁንም ከንፈሩን ይመጥጣል፡፡ አልፎ አልፎ እንባ እንባም ይለዋል፡፡

ከዚህ ዓይነት አስጨናቂና የተደበላለቀ ስሜት ለአንዴም ሳይላቀቅ የ ሌሊት ተጋመሰ፡፡ እንዲያውም ሊነጋ ጥቂት ሠዓታት ብቻ ቀሩት፡፡

ከጥቂት ቆይታ በኋላ በአላሰበው ሁኔታ ከአስቻለው ጋር ተገናኙ፡ ለዚያውም ያ ሊጠፋ ተቃርቧል የተባለ የግራ ዓይኑ ከጓደኛው እኩል ልክ እንደ ድሮው የባቄላ አበባ እንደመሰለ፡ ያ በቦምብ ፍንዳታ አደጋ ተጠባብሶ ያብለጨልጫል የተባለ የግራ ፊቱ ልክ እንደ ቀድሞው ወዙ እየተቀዳ፡ ያ በእሳት ተጨራምቶ የተቆረጠ ይመስላል የተባለ የግራ ጆሮው ከጓደኛው እኩል ተስተካክሎ እንደ ቆመ ፣ ያ በሰው ሰራሽ አካል ተተክቷል የተባለ እጅና እግሩ የፕላስቲክ ቅጥያ ሳይኖረው፡ ክራንች አጠገቡ ሳይቆም፤ ብቻ በሁሉም ነገር የ የድሮው አስቻለው፡ አካሉ የተሟላ ፣ አቋሙ የተስተካከለ፡ ጤንነቱ የተጠበቀ፡ በፈገግታ የተሞላ አስቻለው ፍሰሀ፡፡

«ስለ አንተ የሰማሁት ነገር ሁሉ ሀሰት ነው እንዴ አስቻለው?» የሚል ነበር የበልሁ የመጀመሪያ ጥያቄ፡፡

«በዚህ ዘመን እውነት ትጠብቃለህ እንዴ በልሁ? ሀሰት በነገሰበት በሰፈነበትና ትጥፋት ዓይን በእወጣበት ዘመን?» አለው አስቻለውም ፈገግ ብሎ እየተመለከተው፡፡

«ምነው ግን ጭከን ብለህ ጠፋህ?»

«የጨካኞች ዘመን አይደል! እኔም እንደ ዘመኑ ልሁን ብዬ!»

«ብትጨክን ብትጨክን በሔዋን መጨከን ነበረብህ?»

«ሔዋን ለኔ ምኔ ናት?»

«ፍቅርህ!»

«ፍቅር ቀረ እኮ! መውደድና መዋደድ ተረሳ እኮ!»

«እይ አንተን እምና እየኖረች? በናፍቆት እየጠበቀችህ?»

«ደሞ የምን ማመንና መተማመን አመጣህ? እምነት በክህደት ተተክቶ! ጥርጣሬ ተስፋፍቶ! ሰው እንኳን ሌላውን ራሱን በካደበት ዘመን? ሔዋን እኔን እምና ተቀምጣ ከሆነ በእውነት ተሳስታለች፤ የዋህ ወይም ጂል አትሁኚ ብለህ ልትመክራት ይገባል፡፡»

«ሔዋን ጂልም የዋህም አይደለችም፣ ብልህና አስተዋይ የሕይወት ጓደኛህ ናት አስቻለው፡፡»

«ብልህና አስተዋይ ብትሆን ኖሮ እስከ አሁን በሕይወት ልትኖር አትችልም ነበር፡፡ ‹ወደፊትም ቢሆን በዚህ ባህሪሽ በምድር ላይ መቆየት አትችይም› ብለህ ንገራት»

«እንዴት አስቻለው?»

«አብሪተኞች ያጠፏታል!»

«አብደሀል እንዴ አስቻለው?»

«አዎ በልሁ፤ ማበድ ስላለብኝ አብጃለሁ»

«መመርመር አለብህ!»

«መመርመር ካለባቸው የአባበዱ ሰዎች ናቸው፡ በሚያሳብድ ዘመን ካላበዱ ቀድሞም ቢሆን ጤነኛ ሆነው አልተፈጠሩምና፡፡»

«ነገርህ ሁሉ ግራ ሆነብኝ አስቻለው!?»

«ሁሉም ነገር ግራ ሆኗላ በልሁ! ሁሉም ነገር ተጣሟል! ሁሉም ነገር ከመሠረቱ ተናግቷል!»

በልሁ የአስቻለው ሁኔታና አነጋገር ግራ አጋብቶት ፀጥ ረጭ ብሎ በግርምት ዓይን እየተመለከተው ሳለ ድንገት የአልቤርጎው በር ተንኳኳ፡፡ በልሁ ድንግጥ ብሎ ከእንቅልፉ ብንን ሲል ሁሉም ነገር ቅዠት ሆኖ አገኘው፡፡ አስቻለውም በቅፅበት ከፊቱ ተሰወረ፡፡ ራሱም ያለበት ቦታ ጠፋበት፡፡ ከድንጋጤ ወጥቶ ወደ ቀልቡ መለስ ሲል ከወገቡ ቀና ብሎ «በስመ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ....» ብሎ በማማተብ ወደፊት እግሩ ላይ ድፍት አለ፡፡

በሩ ግን አሁንም ተንኳኳ፡፡

«አቤት! ማነው?» እያለ በልሁ በፈጣን እንቅስቃሴ አንሶላና ብርድ ልብሱን ከላዩ ላይ ያሽቀንጥረው ጀመር፡፡

«እረፍዷል እኮ! አልተነሳህም እንዴ?» አለ ሰዩም ከውጭ ሆኖ፡፡

«ተነስቻለሁ» አለ በልሁ የመንተ-እፍረቱን፤ ወዲያው ፒጃማውን እንደለበሰ ከአልጋ ላይ ወረደና በሩን ከፈተው፡፡

«እንቅልፍ ላይ ነበርክ መሰለኝ፡፡»

በልሁ ዓይኖቹን በጣቶቹ እየጠራረገ «ይገርምሃል! ያለ እንቅልፍ ከቆረ ሲንጋጋ ሲል ወስዶኝ ኗራል፡፡ እስከምለባብስ ግባና ወንበሩ ላይ አረፍ በል፡፡» ሲል ስዩምን ጋበዘው፡፡

«እታች ቡና ቤት ውስጥ ሻይ እየጠጣሁ እጠብቅሃለሁ፡፡ ቶሎ ለባብስና ና፡፡»

በዚሁ ተስማምተው ስዩም ከፎቁ ላይ ወደ ታች ወደ ቡና ቤቱ ወረደ፡፡ ትረጋግቶ በልሁ ግን ከመደንገጡና ከመቸኮሉ የተነሳ የአለባበስ ትድም ተከተሎ ጠፋበት፡፡ ሳይፀዳዳና ሳይተጣጠብ ልብሱን ለባበሰ፡፡ ሲያስታውስ የሚቀሩት ነገሮች አሉ፤ እንደገና ወደ መፀዳጃ፤ ከዚያም ወደ ፀጉር ማበጠር፡፡ ግን ሁሉም ነገር በችኮላና በጥድፊያ ነው፡፡

ሁሉንም ነገር እንደምንም ጨራርሶ ወደ ሆቴሉ ተንደርድሮ ሲወርድ ስዩም ያዘዘውን ሻይ ጠጥቶ ጨርሷል፡፡ በልሁም እንዲጠጣ ጋበዘው፡፡ ግን እሺ አላለም፤ ይልቁንም የስዩምን የሻይ ሂሳብ ለመክፈል ተሽቀዳደመ፡፡ ከፈለ፡፡ ከቡና ቤቱ ወጡና በስተግራ በኩል ወደ አባ ሻውል በሚወስደው የአስፋልት መንገድ ላይ ወደ እስቻለው ቤት ጉዞ ተጀመረ፡፡ ከጠዋቱ ሁለት ሰዓት ተኩል አካባቢ ሆኗል፤

በልሁ ከስዩም ጋር አብሮ እየተራመደ ሳለ እግሮቹ በፍርሀት ይንቀጠቀጣሉ፡፡ ከንፈሮቹ እየደረቁ ደጋግሞ በምላሱ ያርሳቸዋል፡፡ ጭራሽ ከስዩም እኩል ከጎኑ ሆኖ ለመራመድ እየፈራ ወደ ኋላ ቀረት ቀረት ይላል፡፡ ብዙ ከተጓዙ በኋላ አባ ሻውል ከመድረሳቸው በፊት ወደ ግራ በሚወስደው ኮረንኮች መንገድ ላይ ቁልቁል ወረዱ፡፡ ብዙ ከተጓዙ በኋላ አንዲት የሀገር ልብስ የለበሱ ሴት ወይዘሮ አንዲት ልጅ እግር ቢጤ ሴት ዘንቢል አሲዘው ከፊትለፊት ሲመጡ አዩአቸው፡፡ ከጥቂት ርምጃዎች በኋላ ይበልጥ ተቀራረቡ፡፡ በኋላም ተገናኙ፡፡

«በጠዋት ወዴት እማማ አብረኸት?» ሲል ስዩም ቀድሞ ጠየቃቸው፡፡

«ለገበያ ወደ አባ ሻውል፡፡» አሉት ወይዘሮ አብረኸት በእጃቸው ስዩምን ሰላም እያሉ በዓይናቸው ደግሞ በልሁን እየተመለከቱ፡፡ የት እንደሚያውቁት የሚያስታውሱ ይመስላሉ፡፡

«ተዋወቁት፤ የአገር ወዳድ ወንድም ነው፡፡» አላቸው ስዩም ፊቱን ብሎ ሁለቱንም ተራ በተራ እየተመለከታቸው፡፡

«አገር ወዳድ የኛ?» አሉ ወይዘሮ አብረኸት አሁንም በልሁን ትኩር ብለው እያዩት፡፡

«አዎ፡፡»

«ከአሁን ቀደም አላየሁህም እንዴ የኔ ልጅ?» ሲሉ ጠየቁት በልሁን፡፡

«አይተውኛል፡፡ ከጥቂት ቀናት በፊት ከቤትዎ ጠላ ጠጥቻለሁ፡፡»

«እኮ የሚሲዮኖችን ሀኪም ቤት የጠየክኝ?»

«ኧረ ያሁን፤ ምንም አይደል!» ብሎ በልሁ ወዲያው ደግሞ «በዚህ የሚያውቋት የሚሲዮኖች ሀኪም ቤት ይኖር ይሆን እማማ?» ሲል አከለ፡፡ ጠየቃቸው፡፡

ሴትዮዋ ትንሽ አሰብ አደረጉና «እነዚያ ጥሊያኖቹ?» ሲሉ ጠየቁት፡፡

«ይሆናሉ፡፡ በእርግጥ ፈረንጆች ናቸው፡፡»

«በዚህ ወደታች በኩል ነበሩ፡፡ ነገር ግን አሁን እኮ ከዚያ ቦታ ለቀዋል፡፡» አሉት፡፡

«ለቀዋል?» በልሁ አሁንም ደንገጥ እያለ፡፡

«ቆዩ እኮ!»

«ምን ያህል ጊዜ ሆናቸው?»

ሴትዮዋ በተጥታ ለበልሁ ምላሽ ሳይሰጡ ወደ ጠዉዎቹ ዞር በማለት በትግሪኛ ያነጋግሯቸው ጀመር፡፡ ደግመው ደጋግመው ከተመላለሱ በኋላ ሴትዮዋ ፊታቸውን ወደ በልሁ መለስ አድርገው «ከዓመት በላይ ይሆናቸዋል ነው የሚሉኝ» አሉት፡፡

በልሁ እንደገና ወሸመጡ ቁርጥ አለ፡፡ ኢጋጣሚዎች ለምን እንደሚያጋጥሙበት ግራ ገባው፡፡ እዝን ባለ ፊት፤ ትክዝ ባለ አነጋገር «በቃ ይተውት እማማ!» አላቸውና ጣሳውን አንስቶ ፉት ካለለት በኋላ መልሶ አስቀመጠው፡፡ ወደ መሬት አቀንብሶ ራሱን ደጋግሞ ወዘወዘው፡፡

«ልትታከም ኖሯል?» ሲሉ ሴትዮዋ ጠየቁት፡፡

«አይደለም፡፡ እነሱ ጋር ይሰራ የነበረ ሰው እፈልግ ነበር፡፡» አላቸውና አሁንም ወደ መሬት ጎንበስ አለ፡፡

«እየየ.... ለቀዋል!» ብለውት ሴትዮዋ ወደ ጨዋታቸው ተመለሱ፡፡

በልሁ ከዚያ በኋላ ብዙ መቆየት አልፈለገም፡፡ ውስጡም ተናደደ፡፡ እስከ አሁን ባገኘው መረጃ የእስቻለው ዱካ በቀላሉ እንደማይገኝ፤ ምናልባትም ጭራሽ ላይገኝም እንደሚችል ፈራ፡፡ ተስፋው እየጨለመ ሄደ፡፡

ወዲያው አንድ ነገር ታየው፤ ወደ አረፈበት ሆቴል መብረር፡፡ አዎ ሄደ፡፡ በጠራራ ፀሐይ በእንሶላና ብርድ ልብስ ጥቅልል ብሎ ተኛ፤ እስቻለውን እንዳያገኝ ከጋረደው የጭንቅ ጉም ያመለጠ መሰለው፡፡

የሰው ልጅ የቱንም ያህል ቢያስብ፤ ቢጨነቅ ወይም ቢናደድ፤ ቢበሳጭ አሊያም ቢፈራ፤ በአጠቃላይ በየትኛውም ስሜት ውስጥ ቢሆን በህይወት ለመሰንበት የግድ የሚያስፈልገው አንድ ነገር አለ፤ ምግብ፡፡ በልሁ በእንሶላና በብርድ ልብስ ውስጥ ቢደበቅም አላመለጠውም፤ አንጀቱ ርሀብ ከውጭ ሳይሆን ከውስጥ የሚነሳ እሳት ነውና አንጀቱን ይሞረሙረው ጀመር፡፡ ከአንድ ጣሳ ጠላ ሌላ የቀመሰው ነገር ባለመኖሩ ከቀኑ ዘጠኝ ሰዓት አካባቢ ከተኛበት ሰቅስቆ አስነሳው፡፡ ምሣ አይሉት ራት አደባልቆ ሊበላው ወደ ሆቴሉ ሬስቶራንት ወረደ፡፡ ሚሲዮኖቹ ሀኪሞች ይሰሩ ከነበሩበት አካባቢ በመልተት ዜና ተብሳጭቶ ሳይበላ ሳይጠጣ በመዋሉ መንፈሱ ድክምክም ብሎበት የነበረው በልሁ ምሳ በልቶ ቀዝቀዝ ያለ ለስላሳ ከውሃ ጋር እየቀላቀለ ሲጠጣ በዚያው ልክ ተነቃቃ፡፡ ረጋ ብሎ ማሰብም ጀመረ፡፡

አንድ ነገር ታየው፡፡ ሚሲዮናቹ ሃኪሞች እንደ መሆናቸው መጠን ከክፍለ ሀገሩ ጤና ጥበቃ ጽህፈት ቤት ጋር በአንድ ወይም በሌላ መንገድ ግንኙነት ሊኖራቸው እንደሚችል ታሰበው፡፡ ምናልባትም በሌላ መንገድ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ያ ከሆነ ደግሞ ወቅታዊ ሪፖርቶች የስራ ፈቃድ ይሆናል፡፡ በዚያው መጠን በሁለቱ አካላት መካከል መተራረቢና የእድሳት ልውውጥ ሊኖር ይችላል፡፡ ሚሲዮናቹ እዚያው አስመራ ካሉም እዚያው ሊፈልጋቸው፣ ወደ ሌላ ክፍለ ሀገርም ተዛውረው ከሆነ በአሉበት ቦታ እዚያው እንዲችል በትድሚያ ወደ ክፍለ ሀገሩ ጤና ጥበቃ ጽህፈት ቤት መሄድ አድራሻቸውን ሊጠይቅ ወሰነ፡፡ በእርግጥም ጥሩ ሀሳብ የመጣለት ቢት ኗ ተሰማውና ልቡን ደስ አለው፡፡

ማግስቱ እሁድ ስለሆነ የመንግስት መስሪያ ቤት አይከፈትም፡፡ ማግን ግን በከንቱ ማሳለፍ አልፈለገም፡፡ ወዲያው ትዝ ያለው ያንኑ ስለነጋ የሚሲዮናች የቀድሞ መስሪያ ቤት መፈለግና በዚያው ዙሪያ የእስቻለውን ዱካ ማነፍነፍ ነበርና ትናንት ወደ ስራፍ መናፈሻ የሄደበትን መንገድ ይዞ ተጓዘ፡፡ ከጠዋቱ ሶስት ሰዓት አለፍ ብሏል፡፡ ጠላ የጠጣባትን ቤት ሳይቸገር አገኘ፡፡ ሴትዮዋ የጠቆሙትን አቅጣጫ በመያዝ ቁልቁል ወደ አስመራ ከተማ ደቡባዊ ምስራቅ አቅጣጫ ተጓዘ፡፡ በየመንገዱ የሚጠይቃቸው ሰዎች እያመላከቱት ትክክለኛውን አቅጣጫ ይዞ እንዲጓዝ ረዱት፡፡

በግምት ከተን አራት ሰዓት አካባቢ ያን ቀድሞ የሚሲዮናች መስሪያ ቤት አገኘው፡፡ ዙሪያው በረጅም ግንብ የታጠረ ሰፊ ግቢ ነው፡፡ ቤቱ በርካታ ክፍሎች ያሉት ባለ አንድ ፎቅ ነው፡፡ በሩ ግን የመደበኛ ወታደር መለዮ በለበሰ ሰው ይጠበቃል፡፡ በልሁ ለመጠጋት ፈራ፡፡ በዓይኑ ሰረቅ እያረገ እያየው ፊትለፊት ባለው መንገድ ላይ ሲዘዋወር ከቆየ በኋላ አንድ ብቻውን የሚሄድ ወጣት ቢጤ አገኘና «የኔ ወንድም!» አለው በአጠገቡ አለፍ ሊል ሲል።

«አቤት!»

«ይሄ ቤት ቀደም ሲል ሃኪሞች ይሰሩበት እንደነበር አውቃለሁ፡፡ አሁን ግን በሩ ላይ ወታደር ሳይ ጊዜ ለመግባት ፈራሁ፡፡ ሌላ መስሪያ ቤት ሆኖ ይሆን?» ሲል ጠየቀው።

«የአንድ የጦር ጀኔራል መኖሪያ ሆኗል!» አለው ወጣቱ በልሁን አየት እያረገ፡፡

«ከመቼ ጀምሮ?»

«ከዓመት ያልፈዋል፡፡»

«ሃኪሞቹ የት ሄደው?» አለ በልሁ ትናንት ተናድዶ ሳይጠይቅ የቀረውን ጥያቄ ማንሳት ፈልጎ፡

«አላውቅም፡፡» ብሎት ወጣቱ ርምጃውን ሊቀጥል ሲል፡፡ «ሰፈርህ እዚሁ ነው የኔ ወንድም?» ሲል ጠየቀው ወጣቱ ሳይሄድበት ፈጠን ብሎ።

«አዎ»

«ይህ ቤት ሃኪም ቤት በነበረበት ወቅት ከሰራተኞቹ መሀል ለየት ያለ ሰው ታውቅ ነበር?» ሲል ጠየቀው ፈራ ተባ እያለ፡፡

«በምን የሚለይ?»

«አካል ጉዳተኛ የሆነ፡፡»

«ብዙ አካል ጉዳተኞች ነበሩ፡፡ ግን የማናቸውንም ስም አላውቅም፡፡ ሲወጡ ሲገቡ ብቻ ነበር የማያቸው፡፡» አለው ወጣቱ አሁንም ርምጃውን ሊቀጥል ዳዳ እያረገው፡፡

«እግሩ ተቆርጦ ሰው ሰራሽ እግር የተተካለት ታውቅ ነበር?» አለው በልሁ አሁንም ፈጠን ፈጠን ባለ አነጋገር፡፡

«አዎ፡፡ ስሙን ግን አላውቀውም፡፡»

«ፊቱም ላይ ጠባሳ ነበረው፡፡»

«ያውም እስከ ጆሮው ድረስ፡፡» አለው ወጣቱ የበለጠ ገፋ አድርጎ:

«የት አካባቢ ይኖር እንደነበር የምታውቀው ነገር ካለ የኔ ወንድም?»

«ብዙ ጊዜ ሰራተኞች በመኪና ስለሚገቡና ስለሚመጡ መኖሪያቸው ራቅ ሳይል አይቀርም፡፡» ካለ በኋላ ወጣቱ «ግን ለምንድን ነው ይሄን ያህል የምትመረምረኝ?» ሲል ኮስተር ብሎ በልሁን ጠየቀው፡፡

በልሁ ዛሬም ያቺን መጀመሪያ ያነጋገራትን የቡና ቤት አስተናጋጅ አስታወሰ፡፡ ከእሷ ይበልጥ ይኼኛው ወጣት ብዙ እንደታገሰው ተረዳና «ይቅርታ የኔ ወንድም» ብሎ ጉዳዩን አጠር አድርጎ አስረዳው፡፡

ወጣቱ ርምጃውን ቀጠለ፡፡ በልሁ ግን እዚያው ባለበት አቀርቅሮ ቆመ፡፡ ወጣቱ አስቻለውን በዓይን እንደሚያውቀው ተረድቷል፡፡ ነገር ግን የሰራተኞች በመኪና መግባትና መውጣት ጉዳይ መኖሪያቸው የግድ በዚያ አካባቢ ላይሆን እንደሚችል አመለከተው፡፡ በዚያው ልክ በልሁ ተስፋ ቆረጠ፡፡ በነገው ዕቅዱ ላይ ብቻ አተኮረ፡፡ ሲያስብበት ውሎ ሲያስብበትም አደረ፡፡

ሰኞ ዕለት ጠዋት አረፋፍዶ ከመኝታው ተነሳ፡፡ አለባበሱንም ለየት አደረገው፡፡ ዲላ ውስጥ ለሰርግ ወይም ለየት ላለ ድግስ ካልሆነ በቀር አዘውትሮ የማይለብሰውን ደብዘዝ ያለ ሰማያዊ ሙሉ ልብስ ለበሶ የጥቁርና የነጭ ቡራቡሬ ክራባት አሰረ፡፡ ጥሩ ቁርስ በላ፡፡ ትናንት ቦታውን አጥንቶት ወደነበረው የክፍለ ሀገሩ ጤና ጥበቃ ጽህፈት ቤት አመራ፡፡ ከጠዋቱ ሶስት ሠዓት አካባቢ ከቅጥር ግቢው ውስጥ ገባ፡፡ «የአስተዳደር ምክትል ስራ አስኪያጅ» የሚል ጽሁፍ ወዳለበት ቢሮ ልቡ አደላ፡፡ በፀሐፊዋ በኩል አመራና በር ላይ ቆሞ፡-

«ጤና ይስጥልኝ!» አላት፡፡

«እብሮ ይስጠን» አለችና ፀሃፊዋ ከመቀመጫዋ ብድግ አለች፡፡ አጠር ብላ ወፈር የምትል፣ የቀይ መልከ መልካም የሆነች፣ ዕድሜዋ ወደ አርባ የሚጠጋት ሴት ወይዘሮ ናት፡፡ አጠር ያለ ፀጉሯን ጆንትራ አበጥራለች፡፡

«ሃላፊውን ማነጋገር እችላለሁ?»

«ስለምን ጉዳይ?»

በልሁ የልቡን መዘርዝር አልፈለገም፡፡ ያን ጉዳይ ከእነሳ 'ይህ አይመለከታቸውም' ልትለው እንደምትችል አሰበና «የግል ጉዳይ ነው፡፡» ካላት በኋላ፣ የምታዝንለት መስሎት «የመጣሁትም ከሲዳሞ ነው» ሲል ገለጸላት፡፡

ፀሐፊዋ ወንበር እያሳየችው «ይቀመጡ» ብላው ወደ አለቃዋ ቢሮ ገባች፡፡ ብዙ፣ ሳትቆይ ወዲያው ተመለሰችና «ይግቡ» አለችው፡፡

የሃላፊው ቢሮ ለየት ያለ ነው፡፡ መጠኑ ሰፊ ወለሉ በአረንጓዴ ቀለም ምንጣፍ የተሸፈነ፣ መስኮቱ በነጭ ስስ እና ቀይ ወፍራም መጋረጃ የተከለለ ከስድስት የማያንሱ ወንበሮች ያሉት ትልቅ የእንግዳ ጠረጴዛ የተንጣለለበት ግድግዳው ሹሩማ ቀለም የተቀባና ደስ የሚያሰኝ ገፅታ ያለው ነው፡፡

ሃላፊው አቶ ካህሳይ ገብሩም መልከ መልካም ነው፡፡ ድምቅ ያለ ቀይ ሆኖ ፊቱ ረጅም፣ ፀጉሩ እስከ መሀል እናቱ ተመልጦ ወዙ የሚያጥበረብር፣ ጥቁር ሰማያዊ ሙሉ ልብስ በነጭ ሸሚዝና ጥቁሩ በባ ያለበት ቡራቡሬ ክራባት ያደረገ፣ አፍንጫው ሰልከክ፣ ዓይኖቹ ጎላ ያሉና ዕድሜው ከአርባ አምስት ዓመት የማያንሰው ጎልማሳ ነው፡፡

«ጤና ይስጥልኝ!» አለ በልሁ ወደ ውስጥ ገብቶ ሃላፊውን እጅ እየነሳ፡፡

«እብር ይስጥልኝ!» ብሎ ካህሳይ ከወንበሩ ብድግ ብሎ ተቀበለው፡፡ ስማቸውን በመለዋወጥ እጅ ለእጅ ተጨባበጡና በካህሳይ ግብዣ በልሁ ከእንግዳ መቀበያ ወንበር ላይ ተቀመጠ፡፡

«ምን ልርዳዎት አቶ በልሁ?» ሲል ካህሳይ በልሁን ጠየቀው፡፡

«ችግር ገጥሞኝ ነው አቶ ካህሳይ»

«ምን ዓይነት ችግር?»

በልሁ የመጣበትን አገርና ለምን ወደ አስመራ እንደመጣ በአጭሩ ከአስረዳ በኋላ «ወንድሜ በሚሲዮኖች ክሊኒክ ውስጥ ይሰራ እንደነበር ተጠቁሚ ነበር፡፡ የሚሲኒዮቹን የስራ ቦታ አጠያይቄ ባገኘውም ነገር ግን ከአንድ ዓመት በፊት ከዚያ ቦታ እንደለቀቁ ሰማሁ፡፡ ምናልባት ከሙያ አንጻር የምታውቋቸው ከሆነና አሁን የሚገኙበትን ቦታ ትጠቁመኝ ከሆነ ብዬ ነበር፡፡» አለና በልሁ ካህሳይን ቀና ብሎ ተመለከተው፡፡

«የት አካባቢ የነበሩት ናቸው?» ሲል ካህሳይ በልሁን ጠየቀው፡፡

«ቀበሌውን በትክክል አላወኩትም፡፡ ነገር ግን አባ ሻውል ከሚባለው ቦታ ወረድ ብሎ በምዕራባዊ የከተማዋ ዳርቻ የሚገኝ ክሊኒክ እንደ ነበር ማወቅ ችያለሁ፡፡»

ካህሳይ ሚሲዮኖቹን ያወቃቸው ይመስላል፡፡ አንገቱን ነቅነቅ ነቅነቅ ካደረገ በኋላ «ታዲያ እኮ እነሱ አስመራ ውስጥ አይደለም ቦታ የቀየሩት፣ ጠቅላላ ከሀገር ተባርረዋል» አለው፡፡

«ተባርረዋል?» ሲል ጠየቀ በልሁ፡፡ ዓይኖቹ ፍጥጥ ብለው በካህሳይ ላይ ተተከሉ፡፡

«ከዓመት በላይ ሆናቸው»

«በምን ምክንያት ተባረሩ አቶ ካህሳይ? ምናልባት ወንድሚም አብሮ ተባርሮ ይሆን?» ሲል በስጋት ስሜት ውስጥ ሆኖ ጠየቀው፡፡

«ወንድምህ እንኳ አብሮ ሊባረር የሚችልበት ሁኔታ የለም፡፡ እነሱ የተባረሩት 'በሀገር ውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ገቡ' ተብሎ ነው፡፡»

«በፖለቲካ?»

«መሆኑ ነዋ! ለነገሩ እነርሱም አያርፉ፣ ነገሮች ሁሉ እንደ ራሳቸው ሀገር እየመሰላቸው የኛ መንግስት አካሄድ ሳይጥማቸው ሲቀር በአገኙት አጋጣሚ ሁሉ ወጋ ማድረግ ይወዳሉ፡፡» አለ ካህሳይ ፈገግ ብሎ የበልሁን ምላሽ እየጠበቀ፡፡

በልሁ ፈጥኖ ለካህሳይ መልስ መስጠት አልፈለገም ወይም አልቻለም፡፡ ዓይኑን ብቻ ትክል አድርጎ ካህሳይን ያየው ጀመር፡፡ እንዲያውም ቀስ በቀስ ዓይኖቹ በእንባ ይሞሉ ጀመር፡፡

«ምነው አቶ በልሁ?» ሲል ካህሳይ የበልሁ ስሜት መለዋወጥ አስገርሞት ጠየቀው፡፡

በልሁ አሁንም መልስ ከመስጠት ይልቅ ፊቱን ከካህሳይ ላይ መልሶ ወደ ጠረጴዛው በማጎንበስ በእንባ የሞላውን ዓይኑን በመሀረብ ይጠርግ ጀመር፡፡

«አቶ በልሁ!» አለ ካህሳይ ይበልጥ እየደነገጠ፡፡

«ሆዬ አዘነ አቶ ካህሳይ!»

«ምነው? ወንድምህ አብሮ የተባረረ መሰለህ?»

«አይደለም አቶ ካህሳይ፣ የዕድሉ ነገር አሳዝኖኝ ነው፡፡» አለና ንግግሩን «አይደለም አቶ ካህሳይ፣ ወንድሜ የጤና ባለሙያ እንጂ ፖለቲከኛ በማራዘም «አዩ አቶ ካህሳይ፣ ወንድሜ የጤና ባለሙያ እንጂ ፖለቲከኛ አልነበረም፡፡ ነገር ግን በሄደበት ቦታ ሁሉ የፖለቲካ መዘዝ አልለቀው አለ፡፡» አለው አሁንም የዓይኖቹን እንባ እየጠራረገ፡፡

«ማለት?»

«ወንድሜ ገና ልጅ ሳለ የሚረዳው ወንድሙ በፖለቲከኞች ተገድሎበት በችግር ተማረ፡፡ በስንት ስቃይ ትምህርቱን ጨርሶ ስራ ከያዘም በኋላ አሁንም ፖለቲከኞች ሰላም ነስተው ሲያዋክቡትኖሩ፡፡ የኋላ ኋላም በግፍና በተፅዕኖ ወደዚህ ክፍለ ሀገር በ እናት ሀገር ጥሪ ሽፋን አስገድደው ላኩት፡፡ በእነሱ መስ አካሉን አጣ፡፡ እዚሁ ከተማ ውስጥ አዘውትሮ ያርፍበት የነበረችው ሰራዬ መናፈሻ ደግሞ ከፖለቲካ ጋር በተያያዘ መዘጋቷን ሰማሁ፡፡ እነሆ አሁን ደግሞ ይህ እርስዎም አሰሪዎቹ በፖለቲካ ጉዳይ ከሀገር መባረራቸውን እየነገሩኝ ነው፡፡ ታዲያ ይሄ የፖለቲካ ጉዳይ እኔም እንዳላገኘው ምክንያት ሊሆን ነው፡፡ ታዲያ ይሄ አያሳዝንም አቶ ካህሳይ?» ሲል በልሁ የተሰማውን ጥልቅ ሀዘን ለካህሳይ ገለፀለት፡፡

ካህሳይ ገብሩ በሰማው ታሪክ፣ በበልሁ አለቃቀስና የነገሮች አገላለፅ የእሱም ልብ ተነካ፡፡ በልሁን ያህል ግርማ ሞገሱ ግጥም ያለ የወጣት ጠንበለል ከፊቱ ቁጭ ብሎ እንባውን እያፈሰሰ ብሶቱን ሲገልጽለት የእሱም አንጀት ተላወሰ፡፡ ወንድ ልጅ ሲከፋው እንባው ምን ያህል ቅርብ እንደሆነ ከመቼውም

ጊዜ በላይ ሲረዳ ሆዱ ተገቦጫቦጨ፡፡ በዚህን ስሜት ራሱን ይጋግሞ በልሁን ትኩር ብሎም ተመለከተው፡፡ በልሁ አሁንም ንግግሩን ቀጠለ፡፡

«በታ እኮ አቶ ካህሳይ! ከእንግዲህ ወንድሜን ላላገኘው ነው፡፡» እሰጠማጨ እንባው በጓደኞቹ ላይ ተቋጥሮ ሰማይ እየመሰለ፡፡

ካህሳይ ገብሩ አሁንም ለአፍታ ያህል በዚህን ዓይን ከተመለከተው በኋላ ራሱን ለረጅም ጊዜ ወዝውዞ በረጅሙ ተንፈስና «ለመሆኑ የወንድምህ ስም ማን ይባላል?» ሲል ጠየቀው፡፡

«እስቻለው ፍሰሀ፡፡»

«እዚያ አልከኝ ቦታ ላይ ይሰሩ ከነበሩ ሚሊዮኖች ጋር ይሰራ እንደነበረ እርግጠኛ ነህ?»

«በቂ የሆኑ አመልካች ምልክቶችን አግኝቻለሁ፡፡ በእመነትም እርግጠኛ ሆኛለሁ፡፡»

ካህሳይ ገብሩ በልሁን እየተመለከተ ትንሽ ከቆየ በኋላ ፊጠን ባለ ሁኔታ የስልክ እጀታ አነሳ፡፡ ቁጥሮችን አዙሮ ያዳምጥም ጀመር፡፡ ከትንሽ ቆይታ በኋላ መናገር ጀመረ፡ በስልክ፡፡

«ሄሎ አቶ ሀይለአብ... የእነዚያ ባለፈው ዓመት ከሀገር የተባረሩ የጣሊያን ሚሊዮኖች ፋይል በቅርብ ይገኝልሀል... እስቲ ያቀርቡት በነበረው ዓመታዊ የስራ ሪፖርት ላይ በሰው ሀይል ዝርዝራቸው ውስጥ የስራ ማዕረጉ ነርስ የሆነ እስቻለው ፍሰሀ የሚባል ሰው ተመዝግቦ ከሆነ አይተህ ብትነግረኝ.... ጎሽ የኔ ወንድም ደውልልኝ እጠብቅሀለሁ፡፡» አለና ስልኩን ዘጋው፡፡ ወዲያው ወደ በልሁ ዞር ብሎ ሲመለከት በረጅሙ ሲተነፍስ አየው፡፡

«ስማሀ አቶ በልሁ!» ሲል ጀመረ ካህሳይ ገብሩ በሁለት ክንዶች ጠረጴዛ ተደግፎ ፊት ለፊት በልሁን እየተመለከተ፡፡

«አቤት አቶ ካህሳይ!»

«ስሜትህ ሁሉ ገብቶኛል፡፡ አሳዝነኸኛልም፡፡ ግን አንድ ነገር እንድትረዳልኝ እፈልጋለሁ፡፡ ትቀበለኝ ይሆን?»

«ምን ይሆን አቶ ካህሳይ?»

«የወንድምህ በፖለቲካ መዘዝ መሰቃየት የዕድሉ ወይም የዕድለ ቢስነቱ ውጤት አይደለም፣ ኢትዮጵያዊ በመሆኑ ብቻ የሚጠብሰው እሳት ነው፡፡ ይህ ደግሞ ምናልባት ልክ እንዳንተ ወንድም ጠባሳው ጎልቶ አይታይብን እንደሆነ እንጂ እኔም አንተም በአጠቃላይ ኢትዮጵያውያን ሁሉ በፖለቲካ እሳት የተቃጠልንና በመቃጠል ላይ የምንገኝ አሳዛኝ ፍጡራን ነን፡፡ እንዲያውም ነደን ነደን እንዳናልቅ መስጋትና መፍራት ያለብን ዜጎች ነን፡፡» ካለ በኋላ ካህሳይ ምራቁን ዋጥ አድርጎ ለአፍታ ያህል ካሰላሰለ በኋላ ንግግሩን ቀጠለ፡፡

«አየህ አቶ በልሁ! ለዚህ ደግሞ ምክንያቷ ሀገራችን ኢትዮጵያ አይደለችም፡፡ ምናልባት እኛ ዜጎቿና ይበልጥ ግን ፖለቲከኞቻችን ናቸው፡፡ የሀገራችን ፖለቲከኞች የሚመሩበትና የሚያራምዱት የፖለቲካ አስተሳሰብ ከራሳቸው ጥቅም ባለፈ ለሀገርና ለወገናቸው ምንም እንደማይጠቅም ራሳቸው ጠንቅቀው ያውቁታል፡፡ ይህም ስለሆነ ሕዝባችን ተቀብሎናል ብለው

ስለማያምኑ እንኳንስ የእያንዳንዱ ግለሰብ ወይም ማህበረሰብ የተቃውሞ ኮሽታ ምንጊዜም ራሱ ያስፈራቸዋል፡፡ ኮሽታውን ለማምከን በሃይል ይመቱታል፡ የሥልጣናቸውም ትኩሳት ለማዳመጥ ሆን ብለው ራሳቸው ይቆሰቁሱታል፡፡ በሥልጣናቸው ስለሚፈሩ ሕዝባቸውን ማሳረፍ አይፈልጉም፡፡ ለዚህም ሲባል በሕዝቡ ላይ የእንቅስቃሴ ዘርፍ የለም፡ ከግለሰብ ህይወት ጀምሮ በዕድሩ፣ የማይገቡበት ፣ በእርሻው በንግዱ፣ በእምነት በሃይማኖት... ወዘተ፡፡ ከዚያም ባለፈ በትዳሩ ግለሰብ የየዕለት እንቅስቃሴ ካልተከታተሉ አይሆንላቸውም፡፡ የእያንዳንዱን ፈሪዎች ናቸውና ማስፈራራት የወገብ ቀበቷቸው ነው፡፡ በዚህ መሀል ተጎጂው እያንዳንዱ ግለሰብ ነው፡፡ እያንዳንዱ ማህበረሰብ ነው፡፡ የዚህ ሁሉ ጠቅላላ ድምር ውጤት ደግሞ የመላ የሀገራችን ሕዝብ ጉዳትና ስቃይ ነው፡፡» ካለ በኋላ ካህሳይ ገብሩ ንግግሩን ጠበቅ በማድረግ «ታዲያ በእንዲህ ያለ መከራ ውስጥ ከተዘፈቀ ማህበረሰብ ውስጥ የተወለደው የአንተ ወንድም የፖለቲካና የፖለቲከኞች ሰለባ ቢሆን ምን ያስደንቃል?» ሲል ጠየቀና ወደ ኋላ ወንበሩን ደገፍ በማለት የበልሁን ምላሽ ይጠባበቅ ጀመር፡፡

በልሁ ፍዝዝ ብሎ ካህሳይን እየተመለከተ በፅሞና ያዳምጥ ነበርና ካህሳይ ንግግሩን ለጊዜው ቆም ሲያደርግ እስከ አሁን አምቆ ይዞት የነበረውን ትንፋሽ «እሁሁ....» በማለት በረጅሙ ተንፍሶ አወጣው፡፡ በካህሳህይ አነጋገር ተደንቆም ለረጅም ጊዜ ራሱን ወዘወዘ፡፡

«ተሳሳትኩ አቶ በልሁ?» ሲል ጠየቀው ካህሳይ የበልሁን አኳኋን ፊት ለፊት እየተመለከተ፡፡ በልሁ ግን ለካህሳይ ጥያቄ ቀጥተኛ መልስ ከመስጠት ይልቅ ሀሳቡ በትክክል የገባው መሆኑን በሚገልጽ አነጋገር

«የመጨረሻው ነገር እያስፈራም አቶ ካህሳይ?» ሲል ጠየቀው፡፡

«ያስጨንቃል!» ካህሳይ አሁንም በሁለት ክንዶች ጠረጴዛውን ተደገፎና ሲል ቀጠለ፡፡ «እንደምታውቀው ሀገራቱ ዳር እስከዳር በጦርነት እየታመሰች ነው፡፡ ሁሌም እየደማች ነው፡፡ በየቀኑ እየቆሰለች ነው፡፡ ከተፋላሚ ወገኖች የሚሰማው ሁሉ የጀግንነት ወሬ እንጂ የተለየ የፖለቲካ አመለካከት ወይም የተለየ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ፍልስፍና አይደለም፡፡ በተቃውሞ ወገን የተሰለፈው ቡድን አሸንፎ ስልጣን ቢይዝ እንኳ የሀገራችንና የህዝቦቿ ዕጣ ፈንታ ምን ሊሆን እንደሚችል በግልጽ አይታወቅም፣ ምናልባት ሰዎች በሰዎች ተለውጠው የጭቆና አገዛዙ መልክና ባህሪ ይለወጥ እንደሆን እንጂ!! እንዴት ብትለኝ ድሉ የጠመንጃ እንጂ የአዲስ ሀሳብና አመለካከት ስለማይሆን፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ከዚህ ጦርነት በኋላ ሌላ ጦርነት ላለመነሳቱ እንዳች ዋስትና ሊኖር አይችልም፣ ሌላ የተከፋ ቡድን መሸመቁ አይቀርምና፡፡» ካለ በኋላ ካህሳይ ንግግሩን በባሰ እልህና ስሜት ቀጠለ፡፡

«ያ ከሆነ የባሰ ችግር ሊያስከትል ይችላል አቶ በልሁ፡፡ አየህ፣ አንድ ጦርነት ወደ ሌላ ጦርነት እየተሸጋገረ የሕዝብ ስቃይና መከራ በተራዘመ ቁጥር ሕዝብም ከሕዝብ እየተለየና እየተከፋፈለ ይሄዳል፤ በዘር፣ በሃይማኖት፣ በቋንቋ፣ በጎሳ...ወዘተ፡፡ ምናልባት ገገርዎች በስልጣን ላይ የመቆያ ዘዴ ይሆናቸው ዘንድ ይህን የሕዝብ የመከፋፈል አዝማሚያ ለራሳቸው ሲሉ

ያበረታቱትም ይሆናል። በህዝብ መካከል ጠብና ጥላቻ፣ ጥርጣሬና ፍርሀት በማስፈን እነሱ ከሌሉ አደጋ ሊፈጠር እንደሚችል አስመስለው ለማሳመን ይችሉ ዘንድ የከፋ ሁኔታን ሊፈጥሩ ይችላሉ። ያም ሆኖ የተጠናከረ ውሎ አድሮ መበጠሱ አይቀርም፣ የከፋ አደጋ የሚፈጠረውም ያኔ ነው።» ነገር

«ይታያል አቶ በልሁ! ሁለት የፖለቲካ ቡድኖች ተፋለመው ሊጎዱን አሸንፎ ስልጣን ቢይዝ ቢያንስ እንጻራዊ ሰላምና መረጋጋት እንኳ ይችላል። ነገር ግን በዘር፣ በሃይማኖት፣ በጎሳና በቋንቋ ተከፋፍሎ የተፋጠጠ ሕዝብ ባለበት አገር ውስጥ ይህንን አንድ ቀን የሽብር ፈሽ፣ የተጋፋጭ እንዲሁ ማንው ያንን እሳት የሚያጠፋው? ማንው ያን የመከራ ሌሊት የሚያነጋው? ማንው ያን ጨለማ የሚገፈው?» ካለ በኋላ ካሀሳይ ፊቱን ላብ ላብ እያለው የአፍንጫው ቀዳዳዎች ሳብ ጥብቅ እያሉና ዓይኑንም ፍጥጥ አድርጎ በልሁን እየተመለከተ «በጌ እምነት ፈንድቶ ፈንድቶ የማያልቅ የበቀል ቦንብ፣ መገለ የማይጠግን የሀዘር ቁስል፣ ወርዶ ወርዶ የማይቆም የሕዝብ እንባ ያስከትላል ብዬ እፈራለሁ። ኢትዮጵያውያን እርስ በእርሳችን እየተፈጋገምን በራሳችን ላይ የምናመጣው ምፅዓት!» አለና ዓይኖቹን በበልሁ ላይ ተከላቸው።

በልሁ ተገኔ በሕይወቱ ለመጀመሪያ ጊዜ ፈራ። በተፈጥሮው ጀግና ነበር፤ በግል፣ እንዲያ አንድ ሰው እስር ሆነው ቢከብቡት ጭራሽ የማይደናገጥ ልበ ሙሉ፣ ቢሰነዝር ከመሬት የሚደባልቅ፣ ቢሰነዝርበት በአስተማማኝ የሚመክት፣ ዛሬ ግን ጉዳዩ የሀገርና ሕዝብ ሆነበትና ልቡ ራደ። መላ ሰውነቱን የቀውስና የሽብር ሽክሽክታ ተሰራጨበት። ብቻ በረጅሙ ተነፈሰና በውቅቱም ያቺን መጀመሪያ አስመራ ከተማ የገባ ለለት ያነጋገራትን የቡና ቤት አስተናጋጅ ስሚት አስታወሰ።

«እንዲያውም እኮ ያ ጊዜ የደረሰ መሰለኝ አቶ ካሀሳይ?» አለው ዓይኖቹን ፍዝዝ አድርጎ ካሀሳይን እየተመለከተ።

«በጣም ተቃርቧል። በመገስገስ ላይ ነው። ይቆም ዘንድ መላ ካልተበጀለት በቀር!! በአጠቃላይ እኛ ዜጎች፣ በተለይ በተለይ ገዥዎች ሆድና ስልጣናቸውን ወደ ጎን ትተው ፊታቸውን ወደ ህሊናቸው ካልተመለሱ በቀር አደጋው የከፋና አስቀቂ ነው።» ያ አደጋ ከተከሰተ ደግሞ የኔ ስጋት ምን እንደሆነ ታውቃለህ?» አለና በልሁን አከታትሎ ተመለከተው።

«ኧ» አለ በልሁ ካሀሳይ ቀጥሎ ለሚናገረው ነገር በጣም እየጓጓ።

«ወደፊት የዚች ሀገር ታሪክ ሲጻፍ ‹ኢትዮጵያ የምትባል አንድ ሀገር ነበረች› ተብሎ እንዳይጀመር!!»

ከዚህ በኋላ በልሁና ካሀሳይ አንዱ የሌላውን ውስጣዊ ስሜት የበለጠ ለመረዳት በመናበብ ላይ ያሉ በሚመስል ሁኔታ እርስ በእርስ በመተያየት ላይ ሳሉ ድንገት ስልክ ጮኸ። ካሀሳይ ስልኩን አንስቶ በጆሮው ላይ ለጥፎ «ሄሎ… አቶ ሀይለአብ! እህ ከምን ደረስክ?… ተገኘ?…. አመሰግናለሁ የኔ ወንድም!» አለና ስልኩን ዘግቶ ወደ በልሁ እየተመለከተ «በእርግጥም የወንድምህን አድራሻ በትክክል ደርሰህበት ኖሯል።» አለው።

«እም አቶ ካሀሳይ፣ እኔም አልተጠራጠርኩ ነበር።» አለና በልሁ ስለ ...ኛትም ምክር የፈለገ በሚመስል ዓይነት «ታዲያ እንግዲህ ምን ባደርግ የሚሻል ይመስልዎታል?» ሲል ካሀሳይን ጠየቀው።

«በኔ በኩል አንድ ነገር ላደርግልህ የምችል ይመስለኛል።»

«ምን ይሆን አቶ ካሀሳይ?» አለ በልሁ ቀልቡ ጓጓ እያለ።

«እነዚህ ሚሲዮን የሚባሉ ነገሮች እኛ መንግስታዊ ያልሆኑ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ወይም በተለምዶ ኤን.ጂ.ኦ የምንላቸው ናቸው። አስራ እንደ ያህል ድርጅቶች አሁን በአስመራ ከተማ ውስጥ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛሉ። ብዙ ጊዜ በአንድ ኤን.ጂ.ኦ ያገለገለ ሰራተኛ ያ ድርጅት ሲፈርስ ወይም ሲዘጋ አሊያም በሌላ ሁኔታ ስራ ሲያቆም ሰራተኛው ያለውን የስራ ልምድ በመጠቀም ወደ ሌላው ሄዶ የመቀጠር ልምድ አለ። የአንተም ወንድም ከዚያ ከተባረሩት ሚሲዮናዊ ድርጅት ውስጥ እንደ ወጣ ምናልባት በሌላ ድርጅት ውስጥ ተቀጥሮ ከሆነ ልክ ዛሬ አቶ ሀይለአብ እንዳደረገው ሁሉ እኔም ከእሱ ጋር በመተባበር የሌሎቹን ድርጅቶች ሪፖርቶች በመመርመር የወንድምህ ስም ከተገኘ ውጤቱን በአንድና በሁለት ቀን ውስጥ ልገልጽልህ እችላለሁ» አለው።

«አመሰግናለሁ አቶ ካሀሳይ!» አለ በልሁ በአክብሮትና በትህትና እጅ እየነሳ።

«የት ነው ያረፍከው?» ሲል ጠየቀው ካሀሳይ።

«ኒያላ ሆቴል ሃያ አራት ቁጥር።»

«ጥሩ አቶ በልሁ! በተረፈ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ይሁን።» ብሎ በልሁን በሰላምታ ለመሸኘት ከወንበሩ ላይ ብድግ አለ። በልሁም ብድግ አለና ለሁለተኛ ጊዜ የነበረ ምስጋናውን አቅርቦ ተጨባብጠው ተሰነባበቱ።

* * *

ስድስት ቀናት አለፉ፤ እንዲያውም በልሁ አስመራ ከገባበት ቀን ጀምሮ ሲቆጠር እሥረኛ ቀኑ። የአስቻለው ዱካ ግን አልተገኘም፤ ጭራሽ እየራቀ ሄደ። የካሀሳይ ገብሩ ጥረትም አልተሳካ፤ የአስቻለው ስም በየትኛውም ኤን.ጂ.ኦ የሰው ሀይል ሪፖርት ውስጥ ተካትቶ አልተገኘም። በልሁ በቀጠሮው ቀን ወደ ካሀሳይ ቢሮ ብቅ ባለበት ወቅት የተነገረው ይኸው መጥፎ ዜና ነበር።

በልሁ ከዚያ በኋላ ማድረግ የፈለገው አንድ ነገር ብቻ ነበር። ሳይታክት ሳይሰለች በአስመራ ከተማ ውስጥ በሚገኙ ቡና ቤቶች ሁሉ እየተዘዋወረ ስለ አስቻለው ወሬ መጠየቅ። የበልሁ ሀሳብ በየቡና ቤቱ እየተዘዋወረ አስተናጋጆችን በማነጋገር ምናልባት አስቻለው ያዘወትርባት በነበረችው ሰራዬ መናፈሻ ውስጥ ይሰሩ የነበሩ የሆቴል ሰራተኞችን ካገኘሁ የሚል ነበር። በእርግጥም አነስተኛ ሻይ ቤቶችና ኬክ ቤቶች ሳይቀሩ በአስመራ ዋና ዋና መንገዶች ላይ የተኮለኮሉትን ቡና ቤቶች ሁሉ ጎበኛቸው። ከቀትር በፊት ሲሆን ሻይ ቡና፣ ወደ አመሻሹ ላይ ደግሞ ቢራ ወይም ሌላ ዓይነት መጠጥ

እየያዘ በመቀመጥ ብዙዎቹን አነጋገረ፡፡ ሆኖም ፍንጭ እንኳ ሊያገኝ አልቻለም፡፡ እንዲያውም ከሚጠጣው ሻይና ቡና ብዛት የተነሳ እንቅልፍ ተቃጠለ፡፡ ቢራና የአልኮል መጠጡም በተለይ ሌሊት ሌሊት እንቅልፍ እየነሳው ተቸገረ፡፡

በዚህ ሁኔታ ላይ ስንብቶ ልፋቱ ሁሉ መና ሲቀርበት ሌላ ሙከራ ሊያደርግ አሰበ፡፡ በተጥታ ወደ ዲላ ስልክ መደወልና ታፈሡን ማግኘት፣ በእሷ በኩል የሆምሳ አለቃ መኮንን ዳርጌን ለማግኘት መሞከር፡፡ ሀሳቡም፣ ምናልባት የሆምሳ አለቃ መኮንን ዳርጌ ያን ከአስቻለው ጋር ለመገናኘት ምክንያት የሆነውን የአስመራ ኗሪ ጓደኛውን አድራሻ የሚያቀው ከሆነ ሊጠይቀውና በእሱ እየታገዘ ወደ አስቻለው ለማምራት ነበር፡፡ በልሁ ይህን ያሰበው አስመራ በገባ በአሥራ አንደኛው ቀን በዕለተ ዕሁድ ላይ ሆኖ ነው፡፡ ታፈሡንም ሆነ የሆምሳ አለቃ መኮንን ዳርጌን በቀላሉ በስልክ ሊያገኝ የሚችለው በመስሪያ ቤት በኩል ስለሆነ ስልክ የመደወል ሙከራውን በማግስቱ ሰኞ ሊያደርግ ወሰነ፡፡

ይህን ሀሳብ ያስላሰለው በኒያላ ሆቴል ውስጥ አልጋ ላይ ጋደም ብሎ ነው፡፡ ከሙሳኑ ላይ የደረሰውም በዕለቱ ወደ አስር ሰዓት አካባቢ ነው፡፡ በዚያ አልጋ ላይ ለብዙ ጊዜ ቆይቶ ስለነበር ከሙሳኔ በኋላ በአስመራ መንገዶች ላይ ጥቂት ሊዘዋወር ፈለገ፡፡ ለባብሶ ወጣ፡፡ ጥቂት ሲዘዋወር ከቆየ በኋላ ሳያስበው ከዚያ አስመራ የገባ ዕለት ጎራ ባለበትና ስለ አስቻለው ለመጀመሪያ ጊዜ ያወያየት የቡና ቤት አስተናጋጅ በምትሰራበት ሆቴል እግሮቹ አደረሱት፡፡ ጥቂት ለማረፍና ከልጅቷም ጋር ጥቂት ሊጫዋወት አስቦ ጎራ አለ፡፡ ቁጭ አለና ቢራ አዘዘ፡፡ ልጅቷን ግን በዓይኑ ቢፈልጋትም ሊያያት አልቻለም፣ ወይ የጠዋት ተረኛ ሆና አሊያም በሌላ ምክንያት በእለቱ በሆቴሉ ውስጥ የለችም፡፡ እሱ ግን ብቻውን ቁጭ ብሎ ሲጠጣ አመሸ፡፡ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት አካባቢ ሂሳቡን ከፈለና ወደ ማረፊያው ኒያላ ሆቴል አመራ፡፡

ልክ እንደደረሰ የአልቤርጎውን በር ከፍቶ ወደ አልጋው ሊራመድ ሲል አንዲት ለሁለት የታጠፈች ወረቀት ወለሉ ላይ ታየችው፣ በበሩ ስር ወደ ውስጥ የተወረወረች ትመስላለች፡፡ ልቡ ደንገጥ አለና ተኩር ብሎ ተመለከታት፡፡ ወዲያው ብድግ አድርጎ ሲያያት አጭር መልዕክት ይዛለች፡፡

«አቶ በልሁ፣ ከዚህ በታች በተገለጸው ስልክ ቁጥር 'ስዩም' ብለው ይደውሉ፡፡» ይላል የያዘችው መልዕክት፡፡

«አ!» አለ በልሁ ሁለመናውን ነዘር እያደረገው፡፡ «ማነው ስዩም ማለት?» አለ ብቻውን እየተነጋገረ፡፡

ጉዳዩ ከአስቻለው ጋር የተያያዘ መልዕክት ካለው ብሎም ጓጓ፡፡ ቆሞ እያለ ሲያስበው ግምቱ ይበልጥ ጠነከረ፡፡ ጭራሽ ስልክ ለመደወል ቸኮለ፡፡ ያቺ ወረቀት ከእጁ ሾልካ የምትጠፋበት መስሎት በመዳፉ ውስጥ ጭብጥ አደረጋትና በችኮላ የአልቤርጎውን በር ዘግቶ ወደ ውጭ በረረ፡፡ ከኒያላ ሆቴል አጥር ግቢ ወጥቶ መንገዱ ላይ እንደ ደረሰ በመንገድ ላይ በቡድን ሆነው እየሄዱ የነበሩ ሰዎችን በጅምላ ጠየቃቸው፡፡

«ስልክ በቅርብ የት አገኛለሁ ወንድሞቼ?»

«በዚያም በዚህምሞልቷል!» አለው ከመንገደኞች አንዱ፡፡ በልሁ «በዚያም» መሮጥ እንዳለበት ሲያስብ አሁንም ከመንገደኞች አንዱ ወደ በየት አቅጣጫ እያመለከተ «በዚህ በኩል በቅርብ ታገኛለህ፡፡» አለው፡፡

በልሁ በዚያው አቅጣጫ ሮጠ፡፡ አንድ ሁለት ሱቆች ውስጥ ሲጠይቅ አንዱ ጋር ስልክ አያስደውሉም፣ ሌላኛው ደግሞ ለጊዜው ስልኩ ተበላሽቶ ኖሮ «አይሰራም» አሉት፡፡ ሦስተኛው ሱቅ ጠባቂዋ፡፡ በጠየቀበት በአምስተኛው ሱቅ ውስጥ አገኘና ደወለ፡፡

«ሄሎ!» አለችው አንዲት ሴት፡፡

«አቶ ስዩምን ፈልጌ ነበር የኔ እመቤት!»

«ይጠብቁ!» ብላው ሴትዮዋ የስልኩን እጀታ በሆነ ነገር ላይ ስታስቀምጥና በርቀት አጠራር «ስልክ ይፈልግሀል ስዩም» ስትል በስልኩ ውስጥ ተሰማው፡፡ በልሁ ከስዩም ድምጽ በፊት ወደ ስልኩ እየቀረበ ስለመሆኑ ለማወቅ ኮቴውንም በጥንቃቄ ያዳምጥ ጀመር፡፡ በእርግጥም ተሰማው፡፡

«ሄሎ!» አለ ወንድ ሰው፡፡

«አቶ ስዩም ነዎት ጌታዬ?»

«አዎ ነኝ»

«በልሁ እባላለሁ፡፡ አልቤርጎ ውስጥ መልዕክትዎን አግኝቼ ነው፡፡»

«እ፣ ነዎት? አስቻለው ፍሰሀ የሚባል ሰው በመፈለግ ላይ ያሉት?»

«አዎ ጌታዬ!» አለ በልሁ፡፡ ልቡ በድንጋጤ ትርትር ሊል የደረሰ መሰለው፡፡

«ታዲያ ለምን አመሹ? በጊዜ አይደውሉም ነበር? እኔ እኮ አስር ሠዓት አካባቢ ነበር መልዕክቱን ያስቀመጥኩልዎት፡፡» አለ ስዩም፡፡

«እኔም እኮ በዚያው አካባቢ ነው ከክፍሉ የወጣሁት፣ ለጥቂት ተላልፈን እንደሆን እንጂ!» አለና በልሁ አጋጣሚው እንዳያመልጠው በመስጋት «ወይ እኔ ወደ እርሶ ልምጣ?» ሲል ጠየቀው፡፡

«መቼ? አሁን?»

«ምንም ችግር የለብኝም ጌታዬ!»

«ቸኩለዋል ማለት ነው?»

«በጣም አቶ ስዩም፣ እጅግ በጣም!»

«ቢቃ እኔ እመጣለሁ፡፡ ባይሆን እንዳንጠፋፋ ከክፍልዎ ይጠብቁኝ፡፡»

«ንቅንቅ አልልም ጌታዬ!»

«እሺ መጣሁ፡፡»

ለበልሁና ለስዩም መተዋወቂያ አስቻለውን የመፈለግ ስራ እንደ ምልክትነት የመውሰዱ ጉዳይ ነገሩ ከአስቻለው ጋር የተያያዘ ስለመሆኑ የበለጠ ተስፋ አደረበት፡፡ ግን አስቻለውን የሚያስገኝ ይሆን ወይስ ሌላ ሁኔታውን የሚያውቅበት አጋጣሚ? የበልሁ የዚያች ቅፅበት ሀሳብና ስጋት ሆነ፡፡ ግን የሆነው ይሁን፣ በልሁ ዛሬ ስዩምን ማግኘት አለበት፡፡ ስዩም ደግሞ 'መጣሁ'

አለው እንጂ በምን ያህል ደቂቃ ከኒያላ ሆቴል ሊደርስ እንደሚችል አልገለጸለትም፡፡ በስልክ ያነጋገረው ከሩቅ ይሁን ከቅርብ ቦታ ሆኖ ይሁን አይሁን አያውቅም፡፡ ለማንኛውም ከቀጠሮው ቦታ ቀድሞ መድረስ ነበረበትና ስልክ ከደወለበት ሱቅ ጀምሮ እስከ ኒያላ ሆቴል የመኝታ ቤት ቁጥር ሃያ አራት ድረስ ያለውን መንገድ በሩጫ ጨረሰው፡፡ የፎቁን ደረጃዎች እንኳ በሩጫ ነው የረመረማቸው፡፡ ከክፍሉ ደርሶ በሩ ላይ ሰው ያለመቆሙን ሲያረጋግጥ ነው እፎይ ያለ፡፡ ወደ ክፍሉ ከመግባቱ በፊት ሽንጥና ሽንጡን ይዞ በመቆም ብቻ ትንፋሹን ጨረሰና በሩን ከፍቶ ወደ ውስጥ በመግባት አልጋው ላይ ቁጭ አለ፡፡ ቁና ቁና እየተነፈሰ በር በሩን ይመለከት ጀመር፡፡ በኮሪደሩ ውስጥ ኮቴ በሰማ ቁጥር ቀልቡ እየተበተነ ደቂቃዎች አለፉ፤ ምናልባት በግምት አሥራ አምስት ደቂቃዎች፡፡

ድንገት አንድ ወፈር ያለ ጠይም ሰው የቤት ውስጥ ነጣ ያለ ቲታውን በነጭ እስኒከር ጫማ ለብሶ በሩ ላይ ከች አለ፡፡ በሩ አካባቢ ቆም ብሎ ፈገግ እያለ ወደ ውስጥ በልሁን አየት ሲያደርገው «አቤት!» አለ በልሁ ከአልጋው ላይ ብድግ በማለት፡፡

«አቶ በልሁ?»

«ነኝ፡፡ አቶ ሰዩም ነዎት?»

«አዎ»

ተጨባበጡ፡፡ በዕድሜ ተመሳሳይ ናቸውና 'አንቱ' መባባሉን ትተው «ታዲየስ- ታዲየስ! ደህና ነህ-ደህና ነህ!» ተባብለው ትከሻ ለትከሻ ተሳሳሙ፡፡

«ወደ ቡና ቤት እንውረድ ይሆን የኔ ወንድም?» ሲል በልሁ ሰዩምን ጠየቀ፡፡

«እዚያም እዚህም ቢሆን ይቻላል!» አለ ሰዩም፡፡

በልሁ ብዙ ጉዳይ አለውና እየዘናና ብዙ ሊያነጋግረው ፈልጎ «የሰም ወደ ቡና ቤት ሄደን ሻይ ቡና ብንል ይሻላል፡፡» እያለ በሩን ቆላለፈና ተከታትለው ወደ ቡና ቤት በመሄድ አንዲት ባዶ ጠረጴዛ አግኝተው በመቀመጥ ቢራ አዘዙ፡፡

«የእስቻለው ወንድም ነህ?» ሲል ሰዩም ቀድሞ ጠየቀው፡፡

«አዎ! ግን እንዴት አገኘኸኝ አቶ ሰዩም?» ሲል በልሁ ቀጥሎ ጠየቀው፡፡

«በአጋጣሚ ነው፡፡ አቶ ካህሳይ ገብሩ የሚባሉ ሰው አነጋግረሃል፡፡ እኔና እሳቸው ደግሞ በቅርብ እንተዋወቃለን፡፡ ትናንትና አብረን ቁጭ ብለን ሳለን በሆነ አጋጣሚ ወሬ ተነሳና አንተ አስቻለው የሚባል ሰው በፍለጋ ላይ እንዳለህ ጠቀሱ፡፡ እኔ ደግሞ አስቻለውን አውቀው ነበርና ‹ጎርሱ አስቻለው ፍሰሀ?› ብዬ ስጠይቃቸው ‹ታውቀዋለህ እንዴ?› ሲሉ ጠየቁኝና እንደማውቀው ስነግራቸው ከተቀመጡበት ተነስተው ሳሙኝ፡፡ ከዚያም የአንተን አድራሻ ሰጡኝና አንተንና አስቻለውን እንዳገናኛችሁ ከባድ አደራ ጣሉብኝ፡፡» አለው ሰዩም በማከታተል፡፡

በልሁ «እሁሁ...» ብሎ በረጅሙ ተነፈሰ፡፡ ካህሳይ ገብሩን በሌለበት በልቡ አመሰገነው፡፡ ወዲያው «እስቻለውን ታውቀው ኖሯል?» አለው በልሁ ለማረጋገጥ፡፡

«አዎ! በአንድ ኤን.ጂ.ኦ ውስጥ የስራ ባልደረባዬ ነበር፡፡»

«አሁንስ?»

«የነበርንበት ኤን.ጂ.ኦ ፈርሶ እኔ በሌላ ኤን.ጂ.ኦ ውስጥ ተቀጥሬአለሁ፡፡ እስቻለው ግን ለጊዜው ስራ አልያዘም፡፡»

«ሥራ አጣ?»

«አጥቶ አይደለም፤ ግን ትንሽ እያመመው ስለሆነ ጤና አጥቶ ነው፡፡» ብሎ ሰዩም ሊቀጥል ሲል ድንገት አንድ ሰው ከኋላው መጣና ትከሻውን መታ አድርጎ፦

«ደሞ ቴታ ለብሰህ መጠጣት ጀመርክ?» እያለ ከፊት ዞሮ ጨበጠው፡፡ የሰውዬውን በልሁንም እየጨበጠ ሳለ ሰዩም፦

«ተዋወቀው፤ የአገር ወዳድ ወንድም ነው፡፡» አለው፡፡

«ክፍሌ---በልሁ» ተባብለው ተዋወቁ፡፡

ክፍሌ እነበልሁ በነበሩበት ጠረጴዛ ላይ ቁጭ እያለና በተለይ ሰዩምን እየተመለከተ «ግን እሱ ልጅ እንዴት ሆነ እባክህ? ሰሞኑን ጠይቄው አላውቅም፡፡ ሻል አላለው ይሆን?» ሲል ጠየቀው፡፡

«ምንም አይለው!» አለና ሰዩም በልሁን እየት አደረገው፡፡

በልሁ ሁለት አዳዲስ ነገሮች በሀሳቡ ገቡ፤ በአንድ በኩል የእስቻለው መታመም፤ በሌላ በኩል ደግሞ እስቻለው ‹አገር ወዳድ› ተብሎ የመጠራቱ ነገር፡፡ በእርግጥ የስሙ ነገር አሳሳቢ አልነበረም፤ እስቻለው የዘመቻ ግዳጁን ከአጠናቀቀ በኋላ ወደ ሀገሩ የመመለስ ፍላጎት ስላልነበረውና ለምን እንደሆነ ጓደኞቹ በጠየቁት ጊዜ የሆዱን በሆዱ እያደረገ ‹ለምን እሄዳለሁ? እዚሁ ሆኜ ሀገሬን ባገለግል አይሻልም!› በማለት ስለሚመልስላቸው ጓደኞቹም ከዚሁ በመነሳት ያወጡለት የቀልድና የምፀት ቅፅል ስም ነው፡፡ ለጊዜው ግን ሁኔታው የበልሁን ልብ ዷ! ማድረጉ አልቀረም፤ አሳሰበው፡፡

«ግን ያመዋል?» ሲል በልሁ ጠየቀ፡፡ የስሙን ጉዳይ ለጊዜው ማንሳት አልፈለገም፡፡

«አዎ! አልፎ አልፎ ቢሻለውም ብዙ ጊዜ ግን ያመዋል፡፡» አለና ሰዩም ጠርሙሱን አንስቶ ቢራውን ተጎነጨ፡፡

«እኔ ግን የእሱ ልጅ ህመም አካላዊ ብቻ አይመስለኝም፤ የመንፈስ ችግርም ያለበት ይመስላል፡፡» ካለ በኋላ ክፍሌ በተለይ ወደ በልሁ ዞር ብሎ «ግን እንዴት ነው የኔ ወንድም፤ እስቻለው ከሀገሩ ወዲህ ወደ አስመራ ሲመጣ በመልካም ማህበራዊ ሁኔታ ውስጥ አልነበረም?» ሲል ጠየቀው፡፡

በልሁ ከምንም በፊት እንባ ቀደመው፡፡ የክፍሌ ግምት ትክክል መሆኑን እሱ ይበልጥ ያውቀዋልና ሁሉንም የእስቻለውን ሁኔታዎች በማስታወስ «አዎ የኔ ወንድም፤ በእስቻለው ሆድ ውስጥ ብዙ ጣጣ አለ፡፡» አለና በዓይኑ ላይ የተንጠለጠለውን እንባ በመዳፉ ሙሉ ጥርግ አደረገው፡፡

ስዩምና ክፍሌ የበልሁን አኳኋን ሲያዩ ልባቸው ድንግጥ ድንግጥ ትኩር ትኩር እያሉ ተመለከቱት፡፡ ስዩም ቀደም አለና በልሁን ለማፅናናት ያክል «አይዞህ! ያሲጋህ መታመሙ ከሆነ ይህን ያህል በጤና የተያዘ እንዳይመስልህ፡፡» አለና አሁንም የበለጠ ለማበረታታት ያህል «ነገ ልታገኘውና ልታየው አይደል?» አለው፡፡

መገኘቱ ጥሩ፡ አለ በልሁ በሆዱ፡፡ ወዲያው ደግሞ «ብቻ በአጠቃላይ የአስመራ ሰዎች እግዚአብሔር ይስጣችሁ፡፡ ለፍቼ ደክሜ በከንቱ እንዳልቀር ተባብራችሁኛል፡፡» አለና ጣእሙ ምንም ምንም ባይለውም የቢራ ጠርሙሱን አንስቶ ተጎነጨ፡፡

በመሀል ክፍሌ ከተቀመጠበት ብድግ አለና «ስዩም አስቲ ለአንድ ጉዳይ ፈልጌሀለሁ፡፡ እንዴ እናግረኝና ትመለሳለህ፡፡» አለው፡፡

«እረ እኔም ልሄድ ነው ጠብቀኝ፡፡ ይቺን ልጨልጥና አብረን እንወጣለን፡፡» ካለ በኋላ ስዩም ወደ በልሁ ዞር ብሎ «በቃ የኔ ወንድም፤ ነገ በፈለክው ሰዓት አስቻለው ቤት ወስጄ አገናኛችኋለሁ፡፡» አለው፡፡

«ከቻልክማ በጠዋት ነው አቶ ስዩም!» አለው በልሁ፡፡

«ችግር የለም፤ በጠዋት ተነስተህ ጠብቀኝ፡፡ እዚሁ ድረስ መጥቼ ይዤህ እሄዳለሁ፡፡» አለና ስዩም የያዛትን የጠርሙስ ቢራ በአንድ ትንፋሽ ጨልጦ ተነሳ፡፡ ተመሰጋግነው ተለያዩ፡፡

በልሁ አስቻለውን በማግስቱ እንደሚያገኘው እርግጠኛ ሆነ፡፡ ግን ደግሞ በምን ሁኔታ እንደሚያገኘውና እሺ ብሎ ወደ ዲላ የመሄድ ያለመሄዱ ጉዳይ እንደ አዲስ ያስጨንቀው ጀመር፡፡ የህመሙም ሁኔታ በእጅጉ አሳሰበው፡፡ ለስሙ አንሶላና ብርድ ልብስ ለብሶ አልጋ ላይ ተኛ፡፡ ይሁን እንጂ ቀልቡ ሊያርፍ አልቻለም፡፡ መኝታ እንዳልተመቸው ሁሉ ቶሎ ቶሎ ይገላበጣል፡፡ እየጨነቀው ቁና ቁና ይተነፍሳል፡፡ የአስቻለው አጠቃላይ ሁኔታ በእዝነ-ልቦናው እየመጣበት በህዘን ስሜት አሁንም አሁንም ከንፈሩን ይመጥጣል፡፡ አልፎ አልፎ እንባ እንባም ይለዋል፡፡

ከዚህ ዓይነት አስጨናቂና የተደበላለቀ ስሜት ለአንዴም ሳይላቀቅ ያ ሌሊት ተጋመሰ፡፡ እንዲያውም ሊነጋ ጥቂት ሠዓታት ብቻ ቀሩት፡፡

ከጥቂት ቆይታ በኋላ በአሳሰበው ሁኔታ ከአስቻለው ጋር ተገናኘ፤ ለዚያውም ያ ሊጠፋ ተቃርቧል የተባለ የግራ ዓይኑ ከጓደኛው እኩል ልክ እንደ ድሮው የባቄላ አበባ እንደመሰለ፡ ያ በቦምብ ፍንዳታ አደጋ ተጠባብሎ ያብለጨልጫል የተባለ የግራ ፊቱ ልክ እንደ ቀድሞው ወዙ እየተቀዳ፣ ያ በእሳት ተጨራምቶ የተቆረጠ ይመስላል የተባለ የግራ ጆሮው ከጓደኛው እኩል ተስተካክሎ እንደ ቆመ ፣ ያ በሰው ሰራሽ አካል ተተክቷል የተባለ እጅና እግሩ የፕላስቲክ ቅጥያ ሳይኖረው፣ ክራንች አጠገቡ ሳይቆም፣ ብቻ በሁሉም ነገር ያ የድሮው አስቻለው፣ አካሉ የተሟላ ፣ አቋሙ የተስተካከለ፣ ጤንነቱ የተጠበቀ፣ በፈገግታ የተሞላ አስቻለው ፍሰሀ፡፡

«ስለ አንተ የሰማሁት ነገር ሁሉ ሀሰት ነው እንዴ አስቻለው?» የሚል ነበር የበልሁ የመጀመሪያ ጥያቄ፡፡

«በዚህ ዘመን እውነት ትጠብቃለህ እንዴ በልሁ? ሀሰት በነገሰበት፣ ሸፍጥ በዘመነትና ቅጥፈት ዓይን በአወጣበት ዘመን?» አለው አስቻለውም ፈገግ ብሎ እየተመለከተው፡፡

«ምነው ግን ጭክን ብለህ ጠፋህ?»

«የጨካኞች ዘመን አይደል! እኔም እንደ ዘመኑ ልሁን ብዬ!»

«ብትጨክን ብትጨክን በሔዋን መጨከን ነበረብህ?»

«ሔዋን ለኔ ምኔ ናት?»

«ፍቅርህ!»

«ፍቅር ቀረ እኮ! መውደድና መዋደድ ተረሳ እኮ!»

«እሷ አንተን አምና እየኖረች? በናፍቆት እየጠበቀችህ?»

«ደሞ የምን ማመንና መተማመን አመጣህ? እምነት በክህደት ተተክቶ! ጥርጣሬ ተስፋፍቶ! ሰው እንኳን ሊላውን ራሱን በካደበት ዘመን? ሔዋን እኔን አምና ተቀምጣ ከሆነ በእውነት ተሳስታለች፤ የዋህ ወይም ጂል አትሁኚ ብለህ ልትመክራት ይገባል፡፡»

«ሔዋን ጂልም የዋህም አይደለችም፤ ብልህና አስተዋይ የሕይወት ጓደኛህ ናት አስቻለው፡፡»

«ብልህና አስተዋይ ብትሆን ኖሮ እስከ አሁን በሕይወት ልትኖር አትችልም ነበር፡፡ ‹ወደፊትም ቢሆን በዚህ ባህሪሽ በምድር ላይ መቆየት አትችይም› ብለህ ንገራት»

«እንዴት አስቻለው?»

«አብራተኞች ያጠፏታል!»

«አብደሀል እንዴ አስቻለው?»

«አዎ በልሁ፤ ማበድ ስላለብኝ አብጃለሁ»

«መመርመር አለብህ!»

«መመርመር ካለባቸው የአላበዱ ሰዎች ናቸው፤ በሚያሳብድ ዘመን ካላበዱ ቀድሞም ቢሆን ጤነኛ ሆነው አልተፈጠሩምና፡፡»

«ነገርህ ሁሉ ግራ ሆነብኝ አስቻለው!?»

«ሁሉም ነገር ግራ ሆኗላ በልሁ! ሁሉም ነገር ተጣሟል! ሁሉም ነገር ከመሠረቱ ተናግቷል!»

በልሁ የአስቻለው ሁኔታና አነጋገር ግራ አጋብቶት ፀጥ ረጭ ብሎ በግርምት ዓይን እየተመለከተው ሳለ ድንገት የአልቤርጎው በር ተንኳኳ፡፡ በልሁ ድንግጥ ብሎ ከእንቅልፉ ብንን ሲል ሁሉም ነገር ቅዠት ሆኖ አገኘው፡፡ አስቻለውም በቅፅበት ከፊቱ ተሰወረ፡፡ ራሱም ያለበት ቦታ ጠፋበት፡፡ ከድንጋጤ ወጥቶ ወደ ቀልቡ መለስ ሲል ከወገቡ ቀና ብሎ «በስመ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ....» ብሎ በማማተብ ወደፊት እግሩ ላይ ድፍት አለ፡፡

በሩ ግን አሁንም ተንኳኳ፡፡

«አቤት! ማነው?» እያለ በልሁ በፈጣን እንቅስቃሴ አንሶላና ብርድ ልብሱን ከላዩ ላይ ያሽቀነጥረው ጀመር፡፡

«እረፍዷል እኮ! አልተነሳህም እንዴ?» አለ ስዩም ከውጭ ሆኖ፡፡

«ተነስቻለሁ!» አለ በልሁ የመንተ-እፍረቱን፡፡ ወዲያው ፒጃማውን እንደለበሰ ከአልጋ ላይ ወረደና በሩን ከፈተው፡፡

«እንቅልፍ ላይ ነበርክ መሰለኝ፡፡»

በልሁ ዓይኖቹን በጣቶቹ እየጠራረገ «ይገርምሀል! ያለ እንቅልፍ አድሮ ሊነጋጋ ሲል ወሰደኝ ፍራል፡፡ እስከምለባብስ ግባና ወንበሩ ላይ አረፍ በል፡፡» ሲል ስዩምን ጋበዘው፡፡

«እታች ቡና ቤት ውስጥ ሻይ እየጠጣሁ እጠብቅሀለሁ፡፡ ተረጋግተህ ለባብስና ና፡፡»

በዚህ ተስማምተው ስዩም ከፎቅ ላይ ወደ ታች ወደ ቡና ቤቱ ወረደ፡፡ በልሁ ግን ከመደንገጡና ከመቸኮሉ የተነሳ የአለባበስ ቅደም ተከተሉ ሁሉ ጠፋበት፡፡ ሳይፀዳዳና ሳይተጣጠብ ልብሱን ለባበሰ፡፡ ሲያስታውስ የሚቀሩት ነገሮች አሉ፤ እንደገና ወደ መፀዳጃ፤ ከዚያም ወደ ፀጉር ማበጠር፡፡ ግን ሁሉም ነገር በችኮላና በጥድፊያ ነው፡፡

ሁሉንም ነገር እንደምንም ጨራርሶ ወደ ሆቴሉ ተንደርድሮ ሲወርድ ስዩም ያዘዘውን ሻይ ጠጥቶ ጨርሷል፡፡ በልሁም እንዲጠጣ ጋበዘው፡፡ በልሁ ግን እሺ አላለም፤ ይልቁንም የስዩምን የሻይ ሂሳብ ለመክፈል ተሽቀዳደመና ከፈለ፡፡ ከቡና ቤቱ ወጡና በስተግራ በኩል ወደ አባ ሻውል በሚወስደው ሰፊ የአስፋልት መንገድ ላይ ወደ አስቻለው ቤት ጉዞ ተጀመረ፡፡ ከጠዋቱ ሁለት ሰዓት ተኩል አካባቢ ሆኗል፤

በልሁ ከስዩም ጋር አብሮ እየተራመደ ሳለ እግሮቹ በፍርሀት ይንቀጠቀጣሉ፡፡ ከንፈሮቹ እየደረቁ ደጋግሞ በምላሱ ያርሳቸዋል፡፡ ጭራሽ ከስዩም እኩል ከጎኑ ሆኖ ለመራመድ እየፈራ ወደ ኋላ ቀረት ቀረት ይላል፡፡ ብዙ ከተጓዙ በኋላ አባ ሻውል ከመድረሳቸው በፊት ወደ ግራ በሚወስደው ኮረንኮች መንገድ ላይ ቁልቁል ወረዱ፡፡ ብዙ ከተጓዙ በኋላ አንዲት የሀገር ልብስ የለበሱ ሴት ወይዘሮ አንዲት ልጅ እግር ቢጤ ሴት ዘንቢል አሲዘው ከፊትለፊት ሲመጡ አዩአቸው፡፡ ከጥቂት ርምጃዎች በኋላ ይበልጥ ተቀራረቡ፡፡ በኋላም ተገናኙ፡፡

«በጠዋት ወዴት እማማ አብረኸት?» ሲል ስዩም ቀድሞ ጠየቃቸው፡፡

«ለገበያ ወደ አባ ሻውል፡፡» አሉት ወይዘሮ አብረኸት በእጃቸው ስዩምን ሰላም እያሉ በዓይናቸው ደግሞ በልሁን እየተመለከቱ፡፡ የት እንደሚያውቁት የሚያስላስሉ ይመስላሉ፡፡

«ተዋወቁት፤ የአገር ወዳድ ወንድም ነው፡፡» አላቸው ስዩም ፈገግ ብሎ ሁለቱንም ተራ በተራ እየተመለከታቸው፡፡

«አገር ወዳድ የኛ?» አሉ ወይዘሮ አብረኸት አሁንም በልሁን ትኩር ብለው እያዩት፡፡

«አዎ፡፡»

«ከአሁን ቀደም አላየሁህም እንዴ የኔ ልጅ?» ሲሉ ጠየቁት በልሁን፡፡

«አይተውኛል፡፡ ከጥቂት ቀናት በፊት ከቤትዎ ጠላ ጠጥቻለሁ፡፡»

«እኮ የሚሲዮኖችን ሀኪም ቤት የጠየከኝ?»

«አዎ»

«ዋይ! የአገር ወዳድ ወንድም ኖረህል እንዴ?»

«አዎ እሱን በመፈለግ ላይ ነበርኩ፡፡»

«ታዲያ ገልፀህ አትነግረኝም ኖሯል እንዴ ልጄ! ቤቱን እኮ አሳይህ ነበር፡፡ ከእም ጋር ብዙም አንራራቅ፣ ያው የጎረቤት ያህል ነን፡፡»

«አላወቅሁማ የኔ እናት!»

ወይዘሮ አብረኸት ወደ ስዩም ፊታቸውን መለስ አድርገው «ግን አገር ወዳድ ከእ ቤት እልም ብሎ መጥፋቱ ምን ሆኖ ይሆን ስዩሜ? ለወትሮው እንኳ እኔ ጋ ብቅ ሳይል እይውል አያድርም ነበር፡፡ ወይስ ያ ያመኛል የሚለው ነገር አየጠናበት ሄደ? ይኸው ዓይኑን ከአየሁት ሶስት ወይም አራት ወር ሊሞላኝ ነው፡፡» አሉት፡፡

«እያመመው ነው እማማ አብረኸት፡፡»

«ብታ ደከመው?»

«መሰለኝ፡፡» አለ ስዩም በዓይኑ ሰረቅ አድርጎ በልሁን እያየ፡፡

የወይዘሮ አብረኸትና የስዩም ቃለ ምልልስ ለበልሁ የመርዶ ያህል አስደንጋጭ ነበር፡፡ ብቻ ጣልቃ መግባት አልፈለገም፡፡ የሆዱን በሆዱ አምቅ አድርጎ የመጨረሻውን ለማየት በፍርሀት ይጠብቃል፡፡

ወይዘሮ አብረኸት ደረታቸውን በቡጢ መታ መታ እያደረጉ «ልጄን! ልጄን! ልጄን!» ካሉ በኋላ «እስኪ ከተመቸኝ ዛሬ ከሠዓት በኋላ ብቅ እላለሁ፤ እሊያም ነገ ጠዋቱ እየዋለሁ፡፡» ብለው ተሰናብተዋቸው ወደ ገበያቸው አመሩ፤ ስዩምና በልሁም መንገዳቸውን ቀጠሉ፡፡

በልሁና ስዩም የያዙትን የኮረንኮች መንገድ በመቀጠል ወደ ታች ሲወርዱ ከወይዘሮ አብረኸት ቤት መድረሳቸውን በልሁ ልብ አለ፡፡ በዚያው ልክ ወደ አስቻለው ቤት መቃረባቸውን ተረዳና ልቡ የድንጋጤና የፍርሃት ከበሮ ይመታ ጀመር፡፡ የወይዘሮ አብረኸትን ቤት አልፈው ጥቂት ከተጓዙ በኋላ ስዩም በግራ በኩል የሚገኝ አንድ አቋራጭ መንገድ ይዞ ታጠፈ፡፡ በልሁም ተከተለ፡፡ ጥቂት ከተራመዱ በኋላ ስዩም አሁንም በሌላ የግራ አቅጣጫ በሚወስድ መንገድ ይዞ ወደ ላይ ታጠፈ፡፡ በልሁ አሁንም ተከተለ፡፡ በጥላን የተሰሩ አምስት ቤቶችን አልፈው ስዩም የስድስተኛውን ቤት የውጭ በር አንኳኳ፡፡

በዚህ ጊዜ በልሁ ሁለመናውን ላብ አጠለቀው፡፡ ትንፋሹ በረከተ፡፡ ደረቱ ወጣ ገባ ሆዱ ሞላ ሞሸሸ ይል ጀመር፡፡ በሩ እስኪከፈት ድረስ ሽንጥና ሽንጡን ይዞ በመቆም እንዴ ወደ መሬት ሌላ ጊዜ ወደ ሰማይ እያየ ተቅበጠበጠ፡፡ የአስቻለው መገኘት ነገር እንደ ህልም እልም ብሎ ይጠፋ እየመሰለው ልቡ ቷ ቷ ቷ ይል ጀመር፡፡

የውጪው በር ተከፈተ፡፡ ፊትለፊት ከጥርብ ድንጋይ የተሰራ ዘመናዊ ቪላ ቤት ለዓይናቸው ገጭ አለ፡፡ በረንዳው በብረት ፍርግርግ ተሰርቶ ነጭ ቀለም የተቀባ፤ የበርና መስኮቶቹ መስታወት ነጣ ባለ መጋረጃ አሸብርቀው የጥሩ

ኗሪዎች መኖሪያ የሚመስል ነው፡፡ ግቢው ተስተካክሎ የተደለደለ፣ በየአጥሩ አጠገብ የአበባ ተክሎች የሚታዩበት እምር ድምቀት ያለ ነው፡፡

ስዩም ወደ ቪላው አላመራም፡፡ በስተግራ በኩል ወደ ጓሮ በሚወስደው የእግር መንገድ ይዞ ተራመደ፡፡ በልሁም ተከተለው፡፡ በጓሮ በኩል አራት ክፍሎች ያሉት ረጅም የሰርቪስ ቤት አለ፡፡ የተሰራው ከጥርብ ድንጋይ ቢሆንም ነገር ግን ሲሚንቶ የሌለው ደረት ካብ ነው፡፡ የአራቱም ሰርቪስ ክፍሎች በር መዝጊያቸው የቆርቆሮ ነው፡፡ ስዩም መካከል ላይ ከሚገኙት ክፍሎች ወደ አንዱ ተራመደና ገና በሩ ላይ እንደደረሰ «እንዴት አደርክ አገር ወዳድ?» ሲል ወደ ውስጥ ተናገረ፡፡ ቤቱ ገርበብ ብሎ ተከፍቷል፡፡

ከውስጥ በኩል ለስዩም ሰላምታ የተሰጠው የምላሽ ድምጽ ግን በተለይ ለበልሁ እጅጉን አስደንጋጭ ነበር፡ እጅግ የደከመ፣ እጅግ የሰለለና የእስቻለው ሊሆን ይችላል ብሎ ለማመን በጣም የሚያስቸግር ነበር፡፡ «ይመስገነው፡፡ ደህና ነኝ ስዩሜ!» የሚል ድምፅ ወጣ ከውስጥ በኩል፡ ግን ደግሞ ድምጽ እንደሚወጣ ባይቆም ሳልጠበቀ ሰው ፍጹም ሊሰማ በማይችል ሁኔታ፡፡ የበልሁ ጆሮ ቀድሞ ባይቆም ኖሮ ሰው የተናገረ ስለመሆኑ ባልታወቀው ነበር፡፡

«እንዴት ነው፣ ሻል አላለህም?» እያለ ስዩም ወደ ውስጥ ገባ፡፡ በልሁ ግን በድንጋጤ ድርቅ ብሎ በሩ ላይ እንደ ቆመ ቀረ፡፡

«ምንም አልተሻለኝም ስዩሜ፣ አሁንማ ከመኝታዬም ለመነሳት ሰው ሊያስፈልገኝ ነው፡፡ እየደከመኝና እየቃተተኝ ሄደ፡፡» የሚል ድምጽ ከውስጥ ተሰማ፡፡ በዚህ ሰዓት በልሁ በር ላይ ቆሞ በፍርሀት ዓይን ወደ ውስጥ እየተ ያደርግ ጀመር፡፡ ከራስጌው በኩል ከራንች ግድግዳ ተደግፎ እየ፡፡ በራስጌ ከመደሩ ላይ የምግብ ሳህኖች ይታያሉ፡፡ ቀጥታ ወደ ታማሚው ሲያይ በግራ ፊቱ ላይ ጠባሳ ታየው፡፡ ነገር ግን ትራስ ላይ ካረፈው የታማሚው ጭንቅላት በቀር ወደ ታች ያለው ሰውነቱ ፍጹም ያለ አይመስልም፡፡ ከድምጹ መድከምና መስለል በተጨማሪ የታማሚው ሰውነት አልቆ ከአልጋው ላይ የመጥፋቱ ነገር ያ ሰው በእርግጥ እስቻለው ስለመሆኑ የበልሁ ልብ ሊያምን አልቻለም፡፡

«ስማ አገር ወዳድ! ዛሬ ደግሞ ዘመድ ወዳድ ይዤልህ መጥቻለሁ፣ እስቲ እንደ ምንም ብለህ ቀና በል፡፡» አለ ስዩም አልጋው ስር ቆሞ ታማሚውን በተኛበት ቁልቁል እያየ፡፡

«የኔ ዘመዶች እዚህ ድረስ አይመጡም፡፡» አለ ታማሚው ከውስጥ፡፡

«እንዴት?» ሲል ጠየቀው ስዩም፡፡

«በስቀቀን እንባ የሞላ ወንዝ መንገድ ዘግቶባቸዋል!»

«እውነቱን ነው፣ ቀና ብለህ እየው፡፡» አለና ስዩም ወደ በሩ ፊቱን መለስ አድርጎ በልሁን «ገባ በል እንጂ የኔ ወንድም!» ሲል ጋበዘው፡፡ በልሁ ወደ ውስጥ ገባ፡፡

ምናልባት የሰው ጥላ ውልብ ሲል ተሰምቶት ሳይሆን አይቀርም ታማሚውም ፊቱን በቀስታ ወደ በሩ መለስ አደረገ፡፡ ነገር ግን በበር በኩል የሚገባው ብርሃን ዓይኑን ስለሰበረው ያን እንግዳ አጢኖ ለማየት አልቻለም፡፡

«ይህ ሰው ዘመድህ አይደለም?» ሲል ጠየቀው ስዩም፡፡

ሀመምተኛው ግን አሁንም አጢኖ ለማየት አልቻለም፡፡ በልሁ ደግሞ የሀመምተኛውን የፊት ገፅታ እያየ የዚያን ሰው ማንነት ለይቶ ለማወቅ የሚጥር ይመስላል፡፡ የዚያ ሀመምተኛ ፊት አጠቋቆር፣ ከስቶ ከስቶ የፊቱ አጥንቶች እንደ ጦር መሾል፣ ድዱ አልቆ የጥርሶቹ መግጠጥና አጠቃላይ የመዘናው መጥፋት እስቻለው ነው ብሎ ለማመን ተቸገረ፡፡ ግን ደግሞ ሳይወድ በግድ መታከል እንዳለበት አመላካች ነገሮች ታዩትና የግዱን አመነ፡፡ ከግርጌ በኩል አልጋው ላይ ቁጭ በማለት ያን ሀመምተኛ ፊትለፊት እየተመለከተ፡፡

«አላወከኝም እስቻለው?» ሲል ጠየቀው፡፡

እስቻለው በልሁን ለጥቂት ሴኮንዶች ያህል ሲያይ ከቆየ በኋላ እሱም በሙሉ ሊያምን የማይችለውን ነገር የግድ ለማመኑ የቃል ምልክት ሰጠ፡፡

«እንዴ! እንዴ! እንዴ!» አለ ደጋግሞ፡፡ አሁንም ጥቂት ሲያየው ከቆየ በኋላ «የኔ በልሁ?» ሲል ጠየቀ፡፡

«አዎ የኔ እስቻለው፣ የአንተ በልሁ ነኝ፡፡»

«እኔ አላምንም! እኔ አላምንም! እኔ አላምንም!» አለ እስቻለው ዓይኑን ኮርኒስ ላይ ሰክቶ እያሰቀሰ፡፡

«እመን እስቻለው፣ በልሁ ተገኜ ነኝ፡፡» አለና በልሁም ስቅስቅ ብሎ እያለቀሰ በእስቻለው ደረት ላይ ልጥፍ አለ፡፡ ከሁለቱም በኩል የሰቀቀን ለቅሶ ደወል አስተጋባ፡፡ ከሁለቱም ዓይን የእንባ ቦይ ተቀደደ፡፡ ናፍቆትና ሰቀቀን እየታጨዱ በእንዲት የታጣፌ አልጋ አውድማ ላይ ይበራዩ ጀመር፡፡

በመሀል ስዩም መገላገል ጀመረ፡፡ በልሁን ከእስቻለው ደረት ላይ ለማንሳት እየታገለ «ተው እንጂ የኔ ወንድም! ለምን እያለቀስክ ታስለቅሰዋለህ? ሀመምተኛ መሆኑን እያወቅክ?» ይለው ጀመር፡፡

በስንት ልመናና ማባበል በልሁ ከእስቻለው ደረት ላይ ቀና ብሎ ተደላድሎ ተቀመጠ፡፡ ግን የሁለቱም ለቅሶ አሁንም ቀጠለ፡፡ በልሁ ወደ መሬት አጎንብሶ እስቻለው ደግሞ ዓይኑን ጣሪያ ላይ ሰክቶ ይንሰቀሰቁ ጀመር፡፡

የመጀመሪያ ዙር የሰቀቀን እንባቸውን አፍስሰው በረድ ረጋ ማለት ሲጀምሩ እስቻለው ቀድሞ ተናገረ፡፡ «ግን እዚህ ድረስ እንዴት ልትመጣ ቻልክ በልሁዬ?» ሲል ጠየቀው እንባውን በጆሮ ግንዶቹ ላይ እያንቆረቆረ፡፡

«አገሩ የቱንም ያህል ቢርቅ፣ መንገዱ የቱንም ያህል አስቸጋሪና ጠመዝማዛ ቢሆን ኤርትራ ወይም አስመራ ኢትዮጵያ ውስጥ መሆኑን አትዘንጋ፡፡» አለው በልሁም አጎንብሶ እንባውን እያንጠባጠበ፡፡

«እኔ እኮ ረስቻችኋለሁ በልሁዬ!»

«እድለኛ ነሃ!»

«እንዴት በልሁዬ?»

«በሔዋን የሚጨክን አንጀት አምላክህ ስለ ሰጠህ፡፡»

እስቻለው የሔዋን ድምፅ ሲነሳ አንጀቱ ብቻ ሳይሆን ሆድ ዕቃው በሙሉ የተላወሰ መሰለው፡፡ ሁለመናው ተናወጠ፡፡ «ህእ!» ብሎ የሰቀቀን ድምፅ በማውጣት ለአፍታ ያህል በልሁን አየት አደረገና የደከመና የሰለለ ድምፁን ሲቃ እየቆራረጠበት «ሔ-ሔዋን ግን እ-አለች?» ሲል ጠየቀው፡፡

«መኖሩን አለች፡፡»

«ጉግን ምንምን ሆንች?»

«እንተን ፍለጋ ካልሄድኩ፣ ካጣሁትም ገደል ወይም ባህር ውስጥ ካልገባሁ ብላ በማስቸገሯ እግርና እጇን ታስራ ስታለቅስ ነው የምትኖረው፡፡» አለው በልሁ እውነትም በዚሁ ሁኔታ እንዳያት ሁሉ ዓይኑ በእንባ እየሞላ፡፡

በዚህ ጊዜ ከአስቻለው አንደበት የተለየ ድምፅ ተሰማ፡፡ ለቅሶ አይሉት ጩኸት፣ ግን በስለታማ ጩቤ እንጀቱን የወጉት ይመስል በረጅሙ «እእእእእ...» ሲል ጮኸ፡፡

በልሁም ልክ ቀደም ሲል እንዳደረገው ሁሉ በአስቻለው ደረት ላይ እንደገና ድፍት በማለት ፊቱን በአስቻለው አንገት ውስጥ ሸጉጦ «ጨክንክብን እኮ አስቻለው! በሆነብና በናፍቆት ፈጀኸን እኮ አስቻለው! ዱካህን አጠፋህብን እኮ አስቻለው!» በማለት ተንሰቅስቆ ያለቅስ ጀመር፡፡ ሁለተኛው ዙር የናፍቆትና የስቃቃን ለቅሶ ከሁለቱም ዓይን እንባ እንደ ውሃ ያወርድ ጀመር፡፡

በመሀል የተቸገረውና የተጨነቀው ስዩም ነው፡፡ ሁኔታቸው ሁሉ አንጀቱን በላው፡፡ አስቻለው ስንትና ስንት ጉድ በሆዱ አምቆ ይኖር እንደነበረ ይበልጥ እየገባው ሲሄድ ያለፈውም የአስመራ ውስጥ ኑሮው ክፉኛ አሳዘነው፡፡ ያም ሆኖ አሁንም ወደ ግልግሉ ገባ፡፡ በልሁን ከአስቻለው ደረት ላይ ለማንሳት እየታገለ፡

«ተው እንጂ የኔ ወንድም፣ ለዚህ ነው እንዴ ‹አስቻለው አስቻለው› እያልክ ስታጣድፍ የነበረው? ተው እንጂ! ፀና ብለህ እሱንም አፅናናው፡፡» እያለ ይለምነው ጀመር፡፡ በልሁ ከአስቻለው ደረት ላይ በግድ ተነሳ፡፡ እንባው ግን ሊቆምለት አልቻለም፡፡

አስቻለውም እያለቀሰ በሀሳብ ደግሞ ወደ ዲላ ነጎደ፡፡ የሒዋንን አኳኋን በእዝነ-ልቦናው ይመለከተው ጀመር፡፡ ከዓይኗ የሚፈሰው እንባዋ በስሜት ቆጠቆጠው፡፡ የታሰረችበት እግር ብረት የእሱን እጅና እግር ሲከረክረው ተሰማው፡፡ በዚህ ጊዜ አንዳች እንግዳ ስሜት ተፈጠረበትና ‹ተነስ! ሂድ! ብረር ወደ ሲዳሞ!› አለው፡፡

ምዕራፍ አሥራ ስድስት

ታፈሡ እንግዳሰው ከተፈጠረች ጀምሮ እንደ ሰሞኑ በሀሳብና በጭንቀት መንፈሷ ተናውጦ አያውቅም፡፡ ችግሩ የጀመራት የሀምሣ አለቃ መኮንን ዳርጌ ስለ አስቻለው አጠቃላይ ሁኔታ በዝርዝር ከገለፀላቸው ጊዜ ጀምሮ ነው፡፡ በልሁ አስቻለውን ፍለጋ ወደ አስመራ ከሄደ በኋላ ደግሞ ብሶባት ሰንብታለች፡፡ ሲጓዝም በልሁ አስቻለውን ያገኘው ይሆን ወይስ ያጣው ይሆን? ቢያገኘውስ እሺ ብሎ ይመጣለት ይሆን? ቢመጣስ የሒዋን ስሜታዊ ምላሽ ምን ሊሆን ይችል ይሆን? ከሚል ስጋትና ፍርሀት የሚመነጭ ነው፡፡

ለእነዚህ አሳሳቢ ጉዳዮች በቂ ምላሽ ሳታገኝላቸው ውስጥ ውስጡን ሲበሏት፣ ሲያስጨንቋትና ሲያሳስቧት ድፍን አሥራ ሰባት ቀናት አለፉ፡፡ ዛሬ ግን ከሁሉም ነገር መቋጫ ቀን ላይ ደርሳለች፣ በልሁ አስቻለውን ፍለጋ ወደ አስመራ ከሄደበት ቀን ጀምሮ ሲቆጠር አሥራ ስምንተኛ ቀን፣ በእለተ ቅዳሜ፡፡

በተለይ ሒዋን በማታውቀው ሁኔታ ታፈሡ ‹እንግዶች አሉብኝ› በማለት ማለዳ ተነስታ የድግስ ስራ ጀምራለች፡፡ ስጋና የመጠጥ ዓይነቶችን ጨምሮ በርካታ የምግብ ሸቀጦችን ገዝዝታ ሒዋንና ትርፌን በስራ ወጥራቸዋለች፡፡ ከአንድም ሁለትና ሦስት ምድጃዎችን በመጠቀም ይከትፋሉ፣ ያቁላላሉ፣ ይቀቅላሉ፡፡

የታፈሡ እጆች በስራ ይጠመዱ እንጂ ቀልቧ በቤት ውስጥ ወይም በስራው ላይ አልነበረም፡፡ ሀሳቧ ሁሉ ይበታተናል፡፡ ከሒዋንና ከትርፌ ጋር የምትለዋወጠውን ጭውውት ከልቧ አታዳምጠውም፡፡ ብትስቅ እንኳ ሳቋ ለዛ የለውም፡፡ ለጭውውቱ የምትሰጠው ምላሽ ከርእስ ጉዳዩ ጋር ብዙም አይጣጣምም፡፡ አልፎ አልፎ ከሀሳቧ ብንን ስትል ብቻ ጭውውቱን እንደ አዲስ ትጀምረዋለች፡፡

በግምት ከቀኑ አምስት ሠዓት አካባቢ ሳይሆን አይቀርም ታፈሡ ሌላ አስፈሪና አስደንጋጭ ክስተት ተፈጠረባት፡፡ ነገሩ የመነጨው ከወደ ሒዋን አካባቢ ነው፡፡

ሒዋን በልሁ አስቻለውን ፍለጋ ወደ አስመራ ስለመሄዱ አታውቅም፡፡ ምናልባት አስቻለው ወደ ዲላ ባለመመለስ አቋሙ የፀና እንደሆን፣ ወይም ጭራሽ ያልተገኘ እንደሆነ ደስታ በሽታ ሆኖ እንዳያሳቅቃት ሁኔታው ለእሷ ድብቅ ነበር፡፡ በልሁ ቤተሰብ ሊጠይቅ ወደ ደብረ ብርሃን እንደ ሄደ ነው የተነገራት፡፡ እናም የበልሁን መምጣት የምትጠብቀው ከደብረ ብርሃን እንደሚሆን አድርጋ ነው፡፡ ታፈሡን እናግራ ያስደነገጠቻትም ከዚሁ ጋር በተያያዘ ነው፡፡

«ታፈሡዬ!» ስትል ጠራቻት ሒዋን ትርክክ ባለ የከሰል ፍም ላይ የተጣደ ድስት በረጅም ማማሰያ እያማሰለች፡፡

«ወይ የኔ ወርቅ!» አለቻት ታፈሡ ወደ ሔዋን ዞር በማለት፡፡ በዚያች ሰዓት የሶፋ ጌጦች እያስተካከለች ነበር፡፡

«ዛሬ ሕልም አየሁ፡፡»

«ምን ዓይነት ሕልም ሔዩ?»

«በልሁ ከደብረ ብርሃን የመጣ ይመስለኛል፡፡ መንገድ ላይ ከረሜላ ገዝቶ ሲያላምጥ ቆይቶ ኖሮ ልክ እዚህ ሲደርስ የከረሜላውን እላቂ ከአፉ አውጥቶ ይሰጠኝ ይመስለኛል፡፡ ግን እጄ ላይ ሊያስቀምጣት ሲል ድንገት አምልጣኝ መሬት ላይ ትወድቅብኛለች፡፡ ብፈልጋትም አጣታለሁ፡፡ ወዲያው ደግሞ እኔም ያለሁበት ቦታ ይጠፋኛል፡፡» አለችና «ፍችው ምን ይሆን ታፈሡዬ?» ስትል ጠየቀቻት፡፡

«እ!?» አለች ታፈሡ ድንገት ሳታስበው፡፡ በሁለት እጇቿ ሸንኮና ሽንጧን በመያዝ ቆማ ሔዋንን አተኩራ ታያት ጀመር፡፡

«መጥፎ ህልም ነው እንዴ ታፈሡዬ»

ታፈሡ እንደገና ወደ ቀልቧ መለስ ብላ ራሷን ለማረጋጋት እየሞከረች «ለነገሩ የህልም ጥሩና መጥፎ የለውም፣ 'ህልም እንደ ፈቺው ነው' ይባል የለ» አለችና አሁንም ስሜቷን እፍን አድርጋ ወደ ሶፋ ማስጌጥ ስራዋ ተመለሰች፡፡ ግን ደግሞ ሃሳቧ ሁሉ ጥቅልል ብሎ ወደ ትናንት ምሽት ሁኔታዋ ነጎደ፡፡

የታፈሡ እንግዳሰው የትናንት ምሽት ሁኔታ የተለየ ነበር፡፡ በልሁ አስቻለውን ይዞ ዲላ ከተማ መግባቱ ነው፡፡ በልሁ አስቻለውን ይዞ ከቀኑ ስምንት ሠዓት አካባቢ ዲላ እንደገባ በቀጥታ ወደ ታፈሡ ቤት ይዞት መሄድ አልፈለገም፡፡ አማሆ ተብሎ በሚጠራው ሆቴል ውስጥ አሳረፈው፡፡ ለዚህ ምክንያቱ አስቻለው አሁን በሚገኝበት ሁኔታ ላይ ሔዋን ብታየው ሊደርስባት የሚችለውን የመንፈስ ስብራት በምን መልኩ መቀነስ እንደሚቻል ከታፈሡም ሆነ ከሌሎች ጋር መመካከር የሚያስችል ጊዜ ለመግዛት ነበር፡፡

በዚሁ መሠረት በዕለቱ ከአመሻሹ አስር ሰዓት አካባቢ ታፈሡ ወደ ሆቴሉ ጎራ እንድትል በሚስጥር ላከባት፡፡ እሷም ጥሪውን ስትሰማ ከመደንገጧ የተነሳ ምን እንዳደረገች ሳይታወቃት የቤት ልብሷን እንደለበሰች፣ ነጠላ ሜማዋን እንዳደረገች ብፌ ላይ ጣል አድርጋት የነበረች የአንገት ልብሷን ብድግ አድርጋ ነበር ወደ ሆቴሉ የበረረችው፡፡ 'ሰዎች ተጣልተው ድረሽልኝ ብለውኝ ነው' ብላ ባትናገር ኖሮ ያበደች መስሏቸው ሔዋንና ትርፌም በተከተሏት ነበር፡፡ ብቻ ወደተነገራት ሆቴል ሮጣ ስትደርስ ወደ አልቤርጎው ማለፊያ አቅጣጫ እንኳ ጠፍቷት ነበር፡፡ በአመላካች እርዳታ እንደ ምንም ገባች፡፡ ፊትለፊት ወደ አልጋ ክፍሎች ስትመለከት በልሁ፣ መርዕድና የሃምሳ

አለቃ መኮንን ዳርጌ ከአንድ የአልቤርጎ ክፍል በር አጠገብ በረንዳ ላይ ቆመው አየች፡፡ እጅግ በሚያስገርም ጩኸት «በልሁዬ... !» ስትል ከርቀት ተጣራች፡፡

«ረጋ በይ ታፊሎ፡፡» አላት በልሁ ከአሯሯጧ በተጨማሪ የጥሪዋ ድምፀት ውስጣዊ ስሜቷን አስረድቶት፡፡

ታፈሡ የበልሁን ማሳሰቢያ ከቁብ አልቆጠረችውም፡፡ ጆላላ የቤት ቀሚሷን ወደ ጉያዋ ሰብሰብ አድርጋ በመሮጥ ከመሀላቸው ጥልቅ አለች፡፡ ወዲያው በበልሁ አንገት ውስጥ ተሸጉጣ ገና የአስቻለውን ሁኔታ ሳታውቀው በመባባት ስሜት ስቅስቅ ብላ ታለቅስ ጀመር፡፡

«አይዞሽ ታፊሎ!» አላት በልሁ እሱም ፊቱን በትከሻዋ ላይ አስደግፎ በእጁ ጀርባዋን እያሻሸ፡፡

«እናስ በልሁ?» አለችው ታፈሡ፡፡ የአስቻለውን ሁኔታ በድፍኑ መጠየቋ ነው፡፡ አስቻለውን አገኘኸው? ይዘኸው መጣህ? ብላ በዝርዝር ብትጠይቀው ምናልባት ምላሹ አሉታዊ ቢሆን ብላ ሰጋች፡፡

«እስቲ ነይ ወደ ውስጥ ግቢ፡፡» አለና በልሁ ወደ አልቤርጎው ክፍል ፊቱን መልሶ ወደ ውስጥ ተራመደ፡፡ ታፈሡ ከፍርሀቷ የተነሳ በጥንቃቄ እርምጃ ከኋላው ተከተለች፡፡ የሀምሣ አለቃ መኮንን ዳርጌና መርዕድም ወደ ክፍሉ ገቡ፡፡

ታፈሡ ከክፍሉ ውስጥ ገብታ ወደ አልጋው ስትመለከት አንድ ሰው ተኝቶ አየች፡፡ ከአንገቱ በታች ያለው ሰውነቱ አልጋው ላይ የሚታይ አይመስልም፡፡ የድዱ ስጋ አልቆ ጥርሶቹ ገጥጠዋል፡፡ የፊቱ ላይ አጥንቶችም እንደዚሁ፡፡ ዓይኖቹ እንባ አቅርረው ሲያዩዋት አየች፡፡ የግራ ፊቱ ጠባሳ ያ የሀምሳ አለቃ መኮንን ዳርጌ የገለጸውን መልክ ያንፀባርቃል፡፡ ታፈሡ ያ ሰው አስቻለው ስለመሆኑ ማመን ቢያዳግታትም በተለይ የፊቱ ጠባሳ፣ የግራ ዓይኑ ልትጠፋ የደረሰች መሆኗ፣ የግራ ጆሮው ልጣፊ ስጋ መስላ መታየቷና ከራስጌው በኩል ግድግዳ ተደግፎ የቆመ ክራንች መታየቱ የግዱን እንድትቀበለው አደረጋት፡፡ ብቻ አሁንም ጨርሳ ላለማመኗ ምስክር የሚሆን ቃል ተናገረች፡፡ ያን የተኛ ሰው ማየት ትታ ወደ በልሁ ዓይኗን በማፍጠጥ፦

«እ! አስቻለው?» ስትል በቁጭት ስሜት ጠየቀችው፡፡

«ተቀያየረብሽ አይደል?»

«አስቻለው ነው ብለኸኝ እረፋ!»

«አማራጭ የለኝም!»

ታፈሡ ብርክ እንደያዛት ሁሉ ቀስ ብላ ከአስቻለው ጎን አልጋው ላይ ተቀመጠችና ቁልቁል ፊቱን እየተመለከተች «በእርግጥ የኔ አስቻለው ነህ?» ስትል ጠየቀችው፡፡

አስቻለው ከራሱ ሁኔታ ይበልጥ የታፈሡ ስሜት አንጀቱን በላው፡፡ እንባው በዓይኑ ሙሉ ጢም ብሎ ሞላና በዚያው በደከመና በሰለለ ድምፁ ለዚያውም በለቅሶ እየተቆራረጠበት «ያንቺ ባልሆን ነበር ደስታዬ ታ-ታፊሎ! የ-እንቺ መሆኔ የድሮው ይበቃ ነበር፡፡ በ-በልሁ ግን ዛሬም የእሷ ካልሆንክ ብሎ ጎትቶ አመጣኝ፡፡» አላት አሁንም እያለቀሰ፡፡

ታፈሡ ሁለት እጆቿን ወደ ላይ ዘርግታ፡፡ «ኡ-ኡ-ኡ-ኡ ...!» ካለች በኋላ እንደገና «እኔ አላምንም! እኔ አላምንም! እኔ አላምንም!» እያለች በአስቻለው ደረት ላይ ድፍት አለች፡፡ መላ ሰውነቷ በሲቃ እስከሚርገፈገፍ ድረስ ትንሰቀሰቅ ጀመር፡፡ በዚህ ጊዜ በቦታው የነበሩ ሁሉ ዓይኖቻቸውን ይጨምቁ ጀመር፡፡ በተለይ በልሁ አስቻለውን ከአስመራ አስነስቶ ለማምጣት ሲሞክር ሁለቱ የተለዋወጡት ቃል ትዝ አለውና የባሰ ሆዱ ባባ፡፡

አስቻለውን ለመጀመሪያ ጊዜ አስመራ ከተማ ውስጥ በአገኘበት ዕለት በተለይ የሔዋን ጉዳይ በተነሳበት ወቅት አስቻለውን 'ሂድ! ተነስ ብረር! ወደ ሲዳሞ' የሚል ስሜት መጥቶበት የነበረ ቢሆንም በማግስቱና በሳልስቱ ግን ወደ ዲላ የመሄዱ ጉዳይ ጭንቅ ጭንቅ ብሎት፡-

‹በልሁዬ! አሁን እኔን ከዚህ ይዘህ ሄደህ ለሔዋን ገፀ-በረከት ማቅረቡ ያስደስትሀልን? እኔ ከእንግዲህ ወዲያ ለሔዋን የምሆን ሰው ነኝን? ምናለ እዚሁ ቀርቼ የሆንኩትን ብሆን! ምናለ ዖቺ እመቤት በኔ ምክንያት የሰቀቀን እሳት ባይነድባትና የወደፊቱ ህይወቷ ጎደሎ ሆኖ ባይቀር! ምናለ ይህን ሁሉ ነገር አውጥተህ አውርደህ ጥቅምና ጉዳቱን እመዛዝነህ የኔን ውሳኔ ምክንያትና ዓላማ ብትረዳልኝ የኔ በልሁ!› በማለት በእፅንኦት ለምኖት ነበር፡፡

በልሁ በበኩሉ ‹እውነቱን ልንገርህ አስቻለው፣ ሔዋን በአሁኑ ሰዓት ከምንም በላይ የምትናፍቀውና የምትጓጓለት ነገር ቢኖር የአንተን የሚናገር እንደበት ነው፡፡ ይህ ብቻ ለእሷ አዲስ የህይወት ምዕራፍ ይከፍትላታል፡፡ ያን ያህል ስለ አንተ ስትጨነቅና ስትሳቀቅ፣ ስትናፍቅህና የሆንከውን ነገር ባለማወቋ መንፈሷ ሲረበሽ ኖራ የመጨረሻህን ሳታይ ሳትሰማ ብትሞት አጥንቷስ እርፍ ይተኛላታል አስቻለው?› ካለ በኋላ ‹ታምነኛለህ አስቻለው፣ ሔዋን 'አስቻለው ሞቶ እንደሆነ ንገሩኝ:: መቃብሩንም አሳዩኝ:: አጥንቶቹን ለቃቅሜ በጨርቅ ቋጥሬ በሕይወት እስካለሁ ድረስ ጡቶቼ ሥር አቅፌአቸው ልኑር::' ያለች እውነተኛ አፍቃሪህ ናት:: ስለዚህ እባክህ እሺ በለኝ! እባክህ አታሳፍረኝ! እባክህ ቁረጥና ተነሳ፣ ወደ ዲላ፣ ወደ ሲዳሞ እንሂድ!› በማለት ተማፅኖት ነበር፡፡

እነዚህ የልመና ቃሎች ነበሩ አስቻለውን ከአስመራ እንዲነሳ ለመጨረሻ ጊዜ የቀሰቀሱት፡፡ የአይሮፕላን ቲኬት ቆርጠው ከአራት ቀናት በኋላ የደረሳቸውን ወረፋ ተጠቅመው ቦሌ ዓለም አቀፍ አይሮፕላን ማረፊያ ሲደርሱ በልሁ ለአስቻለው አንድ ሀሳብ አቅርቦለት ነበር፣ ወደ ዲላ ከመሄዳቸው በፊት አዲስ አበባ ከሚገኙ ትላልቅ ሆስፒታሎች በአንዱ አስመርምሮ ሊያሳክመው መፈለጉን፡፡ አስቻለው ግን አልተቀበለውም፡፡ ‹በልሁዬ፣ ለኔ ብለህ ብዙ አትልፋ፡፡ የእስከ ዛሬው ልፋትህም ከልክና ከመጠን በላይ ነው፡፡ በምድርም በሰማይም ስለ ክባዱ ውለታህ እግዚአብሔር ያስብህ፡፡ አሁን ዝም ብለህ ወደ ዲላ ይዘኸኝ ሂድ፡፡ ከመጣሁ አይቀር ሳልሞት የሔዬን ዓይን ልየው፡፡ ምናልባት ከእሷም ከታፈሡም ጋር ስገናኝ የህክምናውን ነገር ካመናችሁበት

ከሔዋን ጋር ይዘኸኝ ትመጣና እዷም ከጎኔ ሆና ታስታምመኛለች፡፡› ብሎት ነበር፡፡

በዚሁ መሠረት አዲስ አበባ ከአንድ ቀን በላይ አላደሩም፤ በማግስቱ ነበር ወደ ዲላ የገሰገሱት፡፡ በልሁ ታዲያ አሁን በዚያ አልቤርጎ ውስጥ ታፈሡ የአስቻለውን ሁኔታ ዓይታ እየሆነች ያለችውን ነገር ሲመለከት ‹ሔዋንስ ስታየው ምን ዓይነት ስሜት ይፈጠርባት ይሆን?› ከሚል ስጋት በመነጨ ጭንቀት ነው ሆዱ ከፉኛ የባባውና ምርር ብሎ ያለቀሰው፡፡

በዚሁ ሁኔታ በርካታ ደቂቃዎች አለፉ፡፡ ከቆይታ በኋላ የሀምሳ አለቃ መኮንን ዳርጌ የታፈሡና የአስቻለው የሰቀቀን ለቅሶ ትንቅንቅ አሳሰበውና ከተቀመጠበት ብድግ ብሎ ወደ አልጋው ተጠጋ፡፡

«ወይዘሮ ታፈሡ!» አላት አጠገቧ ቆሞ ቁልቁል እየተመለከታት፡፡

እሷ ግን ምላሽ አልሰጠችውም፡፡ ይልቁንም የአስቻለውን የፊት ጠባሳ እየሳመች «መልክህን አጠፉት አስቹ? ወዝህን አደረቁት የኔ ወንድም? ከሰውነት አወጡህ የኔ ወንድም?» እያለች በፕላስቲክ የተበየዱ እጁንና እግሩን እየደባበሰች «የአንተን ወስዱና የእነሱን ተኩልህ የኔ ሆድ፣ እነዚያ ጨካኞች! እነዚያ አረመኔዎች! እህህህ....» አለች አሁንም፡፡ በዚህ ጊዜ አስቻለውም ተናገረ፡፡

«እንዲህ እንድሆን የተፈረደብኝ እኮ ገና እዚሁ ሳለሁ ነው ታፈሡ! እዚያ ሄጄ የገጠመኝ አፈጻፀሙ ነው፡፡ እኔ እኮ ዕድለ ቢስ ነኝ ታፈሡዬ!» አለና በደህነኛው እጁ እንባውን ለመጥረግ ፊቱን ሙሉ በመዳፉ ሙዥርት አደረገው፡፡

በአነጋገሩ አንጀቷ የተላወሰው ታፈሡ ከተቀመጠችበት ድንገት ብድግ አለች፡፡ እንደ ማበድ እንደ መሰከር አደረጋትና አሁንም ሁለት እጆቿን ወደ ላይ ዘርግታ ሰማይ ሰማይ እያየች «እየየ...! እየየ...! እየየ...!» ብላ እንደገና ደግሞ «እየየ ሸዋዬ! እየየ ባርናባስ! የእናንተን ነገር እግዚአብሔር አይርሳው!! በምድር ለሰራችሁት ሁሉ በሰማይ ይጠይቃችሁ! እንድየ ይፋረዳችሁ!» እያለች አልጋው ላይ ቁጭ ብላ በሁለት እጆቿ ፊቷን በመሸፈን አቀርቅራ ታለቅስ ጀመር፡፡

«ወይዘሮ ታፈሡ!» አላት የሀምሳ አለቃ መኮንን ዳርጌ አሁንም ከፊቷ ቆሞ፡፡ ምላሿን ሳይጠብቅ ንግግሩን ቀጠለ፡፡ «ያለፈው አለፈ በቃ! ከእንግዲህ ማሰብ ስለወደፊቱ ነው፡፡ ይህ አለቃቀስሽ ደግሞ የልጁን ሆድ የባሰ ከማማባት በቀር ሌላ ጥቅም የለውም፡፡ ደግሞም አንቺ ብዙ የምታውቂው ትልቋ ወይዘሮ እንዲህ የምትሆኚ ከሆነ ያቺማ የዋኋ ሔዋን እንዴት ትሆነው ይሆን? ስለዚህ እባክሽ የኔ እመቤት፣ አሁን እሷን እንዴት ማረጋጋት እንደምንችል በእርጋታ ብንነጋገር» ሲል ተማፀናት፡፡

«ይሻላል ታፈሡ! ሁሉን ተይውና ረጋ ብለሽ እንነጋገር» አላት በልሁም እንባውን ከዓይኑም ከፊቱም ላይ በመሀረብ እየጠራረገ፡፡ ደቂቃዎችን ፈጀች እንጂ በእርግጥም ታፈሡ ተረጋጋች፡፡ በልሁም ሆነ የሀምሳ አለቃ መኮንን ዳርጌ ያቀረቡት ሀሳብ ወሳኝ መሆኑን ታምናለች፡፡ ተቀበለችውም፡፡ በጉዳዩ ላይ ብዙ ተነጋገሩ፡፡ ሔዋንና አስቻለውን የማገናኛውም ቀን ተወሰነ፣

ለማግስቱ፡፡ ሰዓቱ ደግሞ ምግብ ተሰራርቶ ካለቀ በኋላ ወደ ሰባት ወይም ስምንት አካባቢ፡፡ በሚገናኙም ጊዜ የሔዋንን ልቦና ማደንጋገሪያ ዘዴ ተፈጠረ፡፡ ከዚህ በኋላ ነበር ታፈሡ ወደ አሥራ ሁለት ሠዓት አካባቢ ወደ ቤቷ የተመለሰችው፡፡

የዛሬው የድግስ ሽርጉድም የዚሁ ዕቅድና ፕሮግራም አንዱ አካል መሆኑ ነው፡፡ የሔዋን ህልም ግን የታፈሡን ልብ የባሰ አሸበረውና በባስ ስጋት ውስጥ ገባች፡ ‹ይቺ ልጅ የዋህ ናትና አምላኳ ምን እየነገራት ይሆን?› በማለት፡፡

ያም ሆኖ የድግሱ ስራ ቀጠለ፡፡ በያይነቱ ተከፋፍለው ይሰሯቸው የነበሩ የወጥ ዓይነቶች ሁሉ ደረሱ፡፡ ቤት ተወለወለ፡፡ መቀመጫ ወንበሮች ተስተካከሉ፡፡ ጊዜውም ደረሰ፡፡ ልክ ከቀኑ ሰባት ሠዓት ተኩል፡፡

የሚመጡትን እንግዶች በውል የምታውቀው ታፈሡ ብቻ ናት፡፡ ትርፌም ዋናው እንግዳ አስቻለው መሆኑን ታውቃለች፡ ታፈሡ ትናንት ማታ በሆነ ሰበብ ወደ ውጭ ጠርታ ለሔዋን ፍንጭ እንዳትሰጥ አስጠንቅቃ የአስቻለውን መምጣት በጆሮዋ ሹክ ብላታለችና፡፡ ሔዋን ግን ምንም ዓይነት ፍንጭ አልነበራትም፡፡ እሷ የምትጠብቀው የማታውቃቸውን የታፈሡን እንግዶች ብቻ ነው፡፡ ነገር ግን ድንገት ከሁሉም ቀድማ ዓይኗን ወደ ውጭ በር ጣል ስታደርግ የምታውቀውና የምትናፍቀው፣ ነገር ግን በዚያ ሠዓት ይመጣል ብላ ያላሰበችው እንግዳ ብቅ ሲል አየችው፤ በልሁ፡፡ ሁላማ ሱሪ በነጭና ሰማያዊ ሁራሁሬ ሸሚዝ ለብሶ ነጣ ያለ ጃኬቱን ትከሻው ላይ አንጠልጥሎ በፍጥነት ርምጃ እየገሰገሰ ወደ ታፈሡ ቤት መጣ፡፡

«እንዴ! ታፈሡዬ! በልሁዬ መጣ!» አለች ሔዋን በልሁን ፍልቅቅ ብላ እያየችና ጆሮዋን እንታፈሡ ለሚሰጧት መልስ አቁማ፡፡

«መጣ?» ብላ ታፈሡ ቶሎ ብላ ወደ በሩ በመራመድ ላይ ሳለች በልሁ ወዲያው ከቻ አለ።

«ታዲያስ! እንደምናችሁ?» እያለ እንደ አዲስ ሊስማት ወደ ታፈሡ ተጠጋ፡፡

«እንኳን ደህና መጣህ በልሁዬ?» አለች ታፈሡም አንገቱን እቅፍ አድርጋ እየሳመችው፡፡

«ሔዬ?» አለ በልሁ ወደ ሔዋን እየተመለሰ፡፡

«አቤት በልሁዬ!»

ደጋግመው ተሳሳሙ፡፡ በልሁ ልክ እንደ ታፈሡና ሔዋን ትርፌንም ከሳማት በኋላ ወዲያው ንግግር ጀመረ፡፡ የሮጠና የቸኮለም ይመስል እንደ ማለከለክ ይቃጣዋል፡፡ «እንዴት ነው፣ አዲስ ስሜት አይነበብብኝም?»

«ይመስላል፡፡ ግን ምንድነው?» አለችው ታፈሡ ዓይኖቿ በፍርሀት እየተርገበገቡና ልቧ ከወትሮው እጥፍ እየመታ»

«አስመራ ደርሼ መጣሁ፡፡»

«አ!» አለች ታፈሡ የደነገጠች መስላ ለመታየት እየሞከረች፡፡

«አስቻለውን አግኝቼ ይገርው መጣሁ፡፡»

«ምን?» ታፈሡ አሁንም በድንጋጤ ዓይነት፡፡

በልሁና ታፈሡ እርስ በርስ የሚተያዩ ይምሰሉ እንጂ በዓይናቸው ሰረቅ አድርጎ በማየት የሚሰልሉት የሔዋንን ስሜት ነው፡፡ ሔዋን የበልሁን አስቻለውን አግኝቼ ይገርው መጣሁ፣ የሚል ቃል ስትሰማ ልክ ሳያስብ ሳይጠረጥር በኃይለኛ ጥፊ ድንገት ጆሮውን እንደተመታ ሰው ሰማይና ምድሩ ተቀላቀለባት፡፡ ዓይኗ ፈጠጠ፡፡ ጥርሷ ገጠጠ፡፡ አፏም ያለ ፍላጎቷ ፏ ብሎ ተከፈተ፡፡ በአጠቃላይ የአንጎሏ የማሰብ ሥርዓት ተዛባ፡፡ በድን ሆነች፡፡

በልሁ ለጥያቄ ፋታ በማይሰጥ ፍጥነት ቶሎ ቶሎ ይናገር ጀመር «ግን አንድ ነገር ልንገራችሁ፡ አስቻለው በድንገተኛ አደጋ ምክንያት አንዳንድ የአካል ጉዳቶች ደርሰውበታል፡፡ በእጅና በእግሩ ላይ የፕላስቲክ ልጣፎች ይታያሉ፡፡ ለጊዜው የሚሄደውም በክራንች ነው፡፡ ፊቱም ላይ ትንሽ ተጎድቷል፡፡ ነገር ግን ‹የፕላስቲክ ቆዳ ጥገና› በተባለ የህክምና ጥበብ በአጭር ጊዜና በአስተማማኝ ሁኔታ ሁሉም ነገር ወደነበረበት ሁኔታ እንደሚመለስ ሀኪሞች አረጋግጠውልናል፡፡» አለና አሁንም ፈጥኖ በመቀጠል «ልብ በሉ! ከዚሁ የህክምና ጥበብ አጠቃቀም ጋር በተያያዘ ህክምናውን በተሟላ የሰውነት ስጋ ላይ ማድረግ ስለማይቻል አስቻለው በጣም በጣም እንዲከሳ ተደርጓል፤ ለህይወት ማቆያ ብቻ እንጂ በቂ ምግብ አይወስድም፡፡ የመከሳቱም ምክንያት ይኸው ብቻ ነው፡፡ ከስቶ ስታዩት ሌላ ነገር መስሏችሁ እንዳትደነግጡ፡፡ እሺ!» ብሎ ፊቱን ወደ ውጭ በር መለስ ሲያደርግ አስቻለውና አጃቢዎቹ ተከታትለው ብቅ ሲሉ አያቸው፡፡ ወዲያው ደግሞ «ያው! አስቻለው እየመጣ ነው፡፡ ወጣ በሉና በእልልታ ተቀበሉት፡፡» አላቸው፡፡

በእርግጥም ሰዎች አስቻለውን አጅበው ከውጭ በር ላይ ደርሰዋል፡፡ ታፈሡና ትርፌ እልልታውን እያቀለጡ ወደ እንግዶቹ ሮጡ፡፡ ሔዋን ግን ከቆመችበት ንቅንቅ አላለችም፡፡ እንደ እንጨት ደርቃ ቀረች፡፡ በልሁ ከተናገረው ቃል አንዱንም አልተረዳችም፡፡ ቀድሞ ነገር ጆሮዋ እንኳ ስለመስማቱ ማንም እርግጠኛ አይደለም፡፡

«ሔዬ» ሲል ጠራት በልሁ ሁኔታዋን ተጠራጥሮት ለመሰለል ያህል፡፡

ሔዋን ልክ እንደ አዕምሮ ዘገምተኛ ሰው የቂለና የጅል በሚመስል ድምጽ «እ» አለችው በደመ ነፍስ፡፡

«ብቅ ብለሽ አስቻለውን አትቀበይውም እንዴ?»

ሔዋን ግን አሁንም ዝም፡፡ በልሁ ራሱ ከንዷን ያዝ አድርጎ የመጎተት ያህል ወስዶ በር ላይ ቢያደርሳትም ከዚያ ማለፍ አልቻለችም፡፡ እንዲያውም የቤቱን በር የግራ በኩል መቃን ሙጥኝ አለች፡፡ ዓይኗ ከውጭ ከሚመጡት ሰዎች ላይ አልተነቀለም፡፡ ታፈሡና ትርፌ አስቻለውን በመሳም ላይ ናቸው፡፡ የአስቻለው ነገር ግን ምን እየተደረገ እንዳለ ለሔዋን አይታወቃትም፡፡ የአስቻለው አጃቢዎች ከሀምሳ አለቃ መኮንን ዳርጌና መርዕድ ሌላ ሦስት የቀድሞ የስራ

ባልደረቦቹ ናቸው፤ ከእስቻለው ጋር ስድስት፡፡ ታፈሡና ትርፌ ቢጨመሩ ስምንት ሆነዋል፡፡ ለሒዋን ግን የሰዎቹ ብዛት የአንድ ከተማ ነዋሪ በሙሉ ሰላማዊ ሰልፍ የወጣ መስሎ ነው የሚታያት፡፡ ሰዎች ስለመሆናቸው በሙሉ በሙሉ አይታወቃትም፤ በሰመመን ውስጥ የሚታይ የእንዳች እንኳ ትርምስምር መስሎ እንጂ፡፡ በሀልም ይሁን በእውን ባለየላት ሁኔታ ፍጡራን ሊመስላት ያልቻለ አንድ ፍጡር በዙሪያዋ የሚንተተ መስሎ ይታያታል፡፡ ሰው ጤነኛው እግሩ እንኳ በሙሉ እግር አይመስልም፤ ሱሪው ብቻ ይወዛወዛል፡፡ የፊቱም አጠቃላይ ገፅታ አስፈሪ ጭምብል ያጠለቀ መሰላት፡፡ ሰው ስለመሆኑ እንኳ እርግጠኛ ሳትሆን እስቻለው አጠገቧ ደረሰ፡፡

«ሒዩ» አላት እስቻለው ከጤነኛውም ከጉዳተኛውም ዓይኖቹ እንባውን እያፈሰሰ፡፡ ለሒዋን ግን ድምጹ እንኳ የሰው አልመሰላትም፡፡ ስልል ያለና በጣም የደከመ ነው፡፡ መልስ ሳትሰጠው ፍጥጥ ብላ ብቻ ትመለከተው ጀመር፡፡

«አላወቅሽኝም ሒዩ?»

ሒዋን አሁንም ዝም፡፡

«ባሚው እንጂ ሒዩ!» አለች ታፈሡ እስቻለውን ደገፍ አድርጋ ከጎኑ በመቆም፡፡ በአሁን ሠአት ከታፈሡ በኩል ለቅሶ የለም፡፡ በሒዋን አኳኋን ደንግጣ ሁለመናዋ ደርቋል፡፡ በልሁም ሆነ ሌሎቹ በትኩረት የሚከታተሉት የሒዋንን ስሜት ነው፡፡ ያስጋቸውም የልብ ህመምተኛ መሆኗ ነው፡፡

ሒዋን አሁንም በዚያ በተረበሸ ስሜት ውስጥ ሆኗ ልትገደል የተከበበች አውሬ ይመስል ዓይኗን በሁሉም ላይ ከማንከራተት በስተቀር ምላሽ መስጠት አልቻለችም፡፡ እስቻለው ራሱ «ተድሞም እኮ የፈራሁት ይህንኑ ነበር ዘመዶቼ!» አለና እያለቀሰ ፊቱን በሒዋን ትከሻ ላይ አሳረፈው፡፡ እዚያው ላይ ተደፍቶ ይንሰቀሰቅ ጀመር፡፡

«ወደ ቤት ቢገቡ አይሻልም?» አለ በሁኔታው ራሱም የተደናገጠው የሃምሳ አለቃ መኮንን ዳርጌ፡፡

እስቻለውን ከሒዋን ትከሻ ላይ አላቅቀው ወደ ቤት አስገቡት፡፡ በትልቁ ሶፋ ላይ ጋለል ብሎ እንዲተኛ ከአደረጉት በኋላ በተለይ ታፈሡ ፣ በልሁና የሃምሳ አለቃ መኮንን ዳርጌ ወደ ሒዋን ተመለሱ፡፡

«ሒዩ» አለቻት ታፈሡ በቅድሚያ፡፡

ሒዋን ግን አሁንም ዝም! ግን ደግሞ በአልታሰበ ሁኔታ ቤት ውስጥ ወለል ላይ በቆሙ ሰዎች ውስጥ አሾልካ እስቻለው ወደተኛበት ሶፋ ዓይኗን ስትወረውር አዩዋት፡፡

«ወደ ውስጥ ትግባ» አለ በልሁ፡፡

ታፈሡ የሒዋንን ክንድ ያዝ አድርጋ «እስቲ ግቢ» በማለት ወደ ውስጥ መራቻት፡፡ ሒዋን ተራመደች፡፡ ከእስቻለው ራስጌ በኩል ባለው ሶፋ ላይ አስቀመጧት፡፡ ወዲያው ዓይኖቿን በእስቻለው ላይ ተከለች፡፡ ዓይኗን በፕላስቲክ በተቀጠለው የእስቻለው ግራ እጅ ላይ ያነጣጠረች ትመስላለች፡፡ ሁኔታዋን ይከታተሉ የነበሩ ሁሉ የመጨረሻው ነገር እስፈርቷቸው በጥ ረጭ ብለው ይመለከቷታል፡፡

ከደቂቃዎች በኋላ ሒዋን እንቅስቃሴ ጀመረች፡፡ ሰው አየኝ አላየኝ ብሎ የመደቀ ዕቃ ሊያነሳ እንዳሰበ ሌባ ዓይኗን በሰዎቹ ላይ እያንከራተተች እጇን ወደ እስቻለው የፕላስቲክ እጅ ሰደድ አደረገች፡፡ ብድግ አድርጋ አየት ከአደረገችው በኋላ መልሳ ጣል አደረገችው፡፡ ወዲያው ደግሞ ዓይኖቿ የእንባ በረድ ሰሩና በዓይኖቿ ሽፋሽፍት ጨለመት ስታደርጋቸው ጉንጮቿን ሳይነኩ ወደ መሬት ረገፉ፡፡

በዚህ ጊዜ ታፈሡ ፈጥና ተጠጋቻት፡፡ የሶፋውን የሻይ ጠረጴዛ ገፋ አድርጋ ቦታ ካስፋች በኋላ ከሒዋን ፊትለፊት በርከክ ብላ በመቀመጥ «ሒዩ! ምነው ዝም አልሽ? ለቅሶውንስ ምን አመጣው? እስቻለው እንዲሁ እንደሆን የሚቀር መሰለሽ እንዴ?» አለቻት፡፡

በዚህ ሰዓት ማንም ባላሰበውና ባልጠበቀው ሁኔታ ሒዋን ድንገት «ዋ...ይ!» በማለት በረጅሙ ጮኻ ወደፊቷ ግንብር በማለት በታፈሡ አንገት ላይ ተጠመጠመች፡፡ ቤቱ በለቅሶ ታመሠ፡፡ የሁሉም አንጀት ተላወሰ፡፡ ሶፋ ላይ ጋለል ብሎ ተኝቶ ግራና ቀኝ በጉንጮቹ ላይ እንባውን ያንቆረቆር የነበረው እስቻለውም ያንኑ የደከመና የሰለለ ድምጹን ባለ በሌለ ሃይሉ በመጠቀም «በልሁ!» ሲል ተጣራ፡፡

«ወይ እስቻለው» ሲል መለሰለት፡፡ እስቻለው ግን እንደገና «ታፈሡ!» ሲል ደግሞ ተጣራ፡፡

«ምነው እስቹ?»

«ቦታ ከዚህ ቤት አውጡኝ! ቦታ ወደ አንድ ቦታ ወስዳችሁ ደብቁኝ! እኔ አልሆንልኝም፡፡ አታስቃዩኝ! ሒዩም አትስቃይባችሁ፡፡ እናንተም አትስቃዩ! እባካችሁ! ስለ ነፍስ ይገርችኋለሁ፡፡» አለ በተከታታይ፡፡ በልሁና ታፈሡ የሚሉት ጠፍቷቸው አቀርቅረው እንባቸውን ሲያፈሱ በመሀል የሃምሳ አለቃ መኮንን ዳርጌ ጣልቃ ገባና «የት ትሄዳለህ እስቻለው?» አለው፡፡

«ቦታ! የትም! እያስለቀስኩ በማላስለቅስበት ቦታ! የትም ይሁን፤ ብቻ ከዚህ ቦታ ሰውሩኝ፡፡» አላቸው፡፡ ለጊዜው ማንም መልስ የሰጠው የለም፡፡ ሁሉም መንፈሳቸው ተረብሾ ሆዳቸው ባባ፡፡ ግራ ተጋቡ፡፡ ተጨናነቁ፡፡

«እዚህ ቤት ባታሳድሩኝ ደስ ይለኛል፡፡» አለ እስቻለው ዓይኑንም አፍንጫውንም እየጠራረገ፡፡

«የትም አትሄድም፤ የትም ተወስደህ አትደበቅም፡፡ ነገር ግን ነገውኑ ለህክምና ወደ አዲስ አበባ ትሄዳለህ» አለው በልሁ። ሒዋን ይህን የቃል ምልልስ ስሚቷ ይከታተል ኖሯል፡፡ ምልልሱ ምን ዓይነት ስሜት ያሳድረባት መሆኑ ለማንም ግልጽ ባይሆንም ባልተጠበቀ ሁኔታ ነቃ በማለት፡-

«እእስ በልሁዬ!» ስትል ጠየቀችው፡፡

«ከእንግዲህ አትለያዩም፤ አንቺም አብረሽን ትሄጂና ከጎኑ ቁጭ ብለሽ ታስታምሚዋለሽ፡፡ እኔንም ትረጅኛለሽ፡፡» አላት በልሁ፡፡

ሒዋን ድምጿ እየተቆራረጠ «እ-እሺ!» አለችና ከታፈሡ አንገት ላይ ቀና ብላ ራሷን ችላ ሶፋው ላይ ቁጭ አለች። በእንባዋ ሙላት ስማይ የመሰሉ ዓይኖቿን ወደ እስቻለው ወርወር እያደረገች እከታትላ ትመለከተውም ጀመር፡፡

ምዕራፍ አሥራ ሰባት

በቀድሞው የዴሳ ከተማ አውቶብስ መናኸሪያ ፊትለፊት በሀምሳ ሜትሮች ርቆ ከታች በስተምዕራብ በኩል የሚገኘው ‹አባይ ፏፏቴ› ሆቴል በዕለተ እሁድ ምሽት ለዘጠትር ደንበኞች ዝግ ሆኖ ለየት ያሉ እንግዶች ሊስተናገዱበት ተዘጋጅቷል፡፡ ለክብር እንግዶች የተዘጋጀው መድረክ የተለያዩ ቀለማት ባሏቸው መብራቶች አጊጧል፡፡ የድግሱ ታዳሚዎች ከመድረኩ ፊትለፊት በተዘጋጀላቸው ወንበርና ጠረጴዛ ላይ ተቀምጠዋል፡፡ ከታዳሚዎቹ መሀል የሚበዙት የፖሊስ ሰራዊት አባላት ናቸው፡፡ መለዮ የለበሱት ይበልጣሉ፡፡ ጠረጴዛዎቻቸው በነጭ ጨርቅና በላስቲክ ተሸፍነው ያልተከፈቱ የቢራ ጠርሙሶች ተደርድረውባቸዋል፡፡ አስተናጋጆች የመስተንግዶ ስራቸውን ለማከናወን ጥግ ጥግ ይዘዋል፡፡ በትላልቅ ድምጽ ማጉያዎች የሚለቀቀው ሙዚቃ አዳራሹን ያንቀጥቀዋል፡፡ የድግሱ ታዳሚዎች ፊትለፊት በመድረኩ ላይ የተዘረጋውን ልዩ ሶፋ እየተመለከቱ የክብር እንግዶችን ይጠባበቃሉ፡፡

ልክ ከምሽቱ አስራ ሁለት ሠዓት ተኩል ላይ ሙዚቃው ድንገት ቆመ፡፡ በሙዚቃው ፉጨት ውስጥ እየተጫዋወቱ ይሳሳቁ የነበሩ እንግዶች ዝም ዝም አሉ፡፡ ቤቱ ፀጥ ረጭ አለ፡፡ ወዲያው አንድ የዝግጅት አስተባባሪ ኮሚቴ ሰብሳቢ ሳይሆን የማይቀር ጠየም ያለ ልጅ እግር ሰው ከሆቴሉ ጓዳ በኩል መጥቶ ወደ መድረኩ ወጣ፡፡

«እንዴት ዋላችሁ እንግዶቻችን?» አለ ፈገግ ባለ ሁኔታ እጆቹን እያፍተለተለና በሆቴሉ ውስጥ የታደሙ እንግዶችን በሙሉ በዓይኑ እየቃኘ፡፡

«እግዚአብሔር ይመስገን!» የሚል ምላሽ ተሰጠው ከታዳሚዎቹ፡፡

«በቅድሚያ ጥሪያችንን አክብራችሁ፣ ጊዜያችሁን መስዋዕት አድርጋችሁ በዚች ሰዓትና ቦታ ስለተገኛችሁልን በዕለቱ የክብር እንግዳና በዝግጅት አስተባባሪ ኮሚቴ ስም ምስጋናዬን ማቅረብ እወዳለሁ፡፡»

ከታዳሚዎቹ በኩል ሞቅ ያለ ጭብጨባ ተቀበለው፡፡

«አመሰግናለሁ፡፡» አለና «ዛሬ በዚች ሠዓትና ቦታ የመገናኘታችን ዓላማ ለሁላችንም ግልጽ ነው፡፡ እንደሚታወቀው ሰዎች በአንድ ወይም በሌላ አጋጣሚ ይተዋወቃሉ፡፡ የትውውቁ መሰረት በአንድ አካባቢ መኖር፣ የስራ ባህሪና ቦታ፣ ወይም ሌላ ሌላም ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን መተዋወቅና መግባባት ወይም መዋደድ እንዳለ ሁሉ በሆነ አጋጣሚ መለያየትም ይኖራል፡፡ የመለያያው መንገድና ዓይነትም እንደዚሁ ብዙ ነው፡፡ በጠብና በጥላቻ፣ በሞት፣ በስራ ዝውውር.... ወዘተ ሊሆን ይችላል፡፡ በአጠቃላይ በደስታም በሀዘንም የተዋወቁና የተዋደዱ ሰዎች ሊለያዩ ይችላሉ፡፡

«ዛሬ ልናከብረው የተዘጋጀነው የመለያየት በዓል ግን የሰላምና የደስታ ነው፡፡ አንድ የስራ ባልደረባችን ዕድገትና ሹመት አግኝቶ ከመካከላችን በመለየት ወደ ሌላ አካባቢ ሊሄድ ስለመሆኑ ሁላችንም እናውቃለንና እስቲ

...መገርማችን ደስታ መግለጫ ይሆን ዘንድ ሁላችንም እንደ እናጨብጭብ»
...ለ በፈገግታ ዓይን እያየ ታዳሚዎቹን ጠየቃቸው፡፡
አሁንም ሞቅ ያለ ጭብጨባ ተቀበለው፡፡

«አመሰግናለሁ፡፡ ከዚህ ቀጥሎ የክብር እንግዳችን ከቅርብ ዘመድ ...ዶቹ ጋር በመሆን እየመጣ ስለሆነ ወደ መድረኩ በሚያልፍበት ሰዓት ...ሁላችንም ከተቀመጥንበት ብድግ በማለት በጭብጨባ እንድንቀበለው እያሳሰብኩ በኋ በኩል የመክፈቻ ንግግሩን እዚህ ላይ አበቃለሁ፡፡ አመሰግናለሁ፡፡» በማለት እጅ ነስቶ ወደ መጣበት አቅጣጫ ተመለሰ፡፡

የድግሱ ታዳሚዎች የክብር እንግዳውን በዓይናቸው የሚጠብቁት ...ሁ በር በኩል ነበር፡፡ ነገር ግን ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ በዚያ የመክፈቻ ንግግር ባደረገው ሰው እየተመራ ከወደ ጓዳ በኩል ድንገት ብቅ አለ፡፡ የክብር እንግዳው የሀምሳ አለቃ መኮንን ዳርጌ ነው፡፡ የምክትል መቶ አለቅነትና የወላይታ አውራጃ ፖሊስ አዛዥነት ሹመት አግኝቶ ሊሄድ ነው፡፡ ድግሱም አሱኑ ለመሸኘት ነው፡፡

የቀድሞው የሀምሳ አለቃ፣ ዛሬ ግን የምክትል መቶ አለቅነት ማዕረጉን መለዮ ለብሶ ከአስተባባሪ ኮሚቴ ሰብሳቢው ኋላ ተከትሎ ብቅ ሲል ታዳሚዎች በሙሉ ከተቀመጡበት ብድግ በማለት በማያቋርጥ ጭብጨባ ተቀበሉት፡፡ ከእሱ ኋላ ነጫጭ የሀገር ልብሷን ለብሳ እንቁጣጣሽ የመሰለችው ታፈሡ እንግዳሰው፣ ቀጥላ ሒዋን፣ ከእሷ ኋላ ደግሞ መርዕድ እሸቴ በመሆን ተከታተሉ፡፡ ሁሉም ለታዳሚዎች የጭብጨባ አቀባበል እጅ እየነሱ ወደ መድረኩ አመሩ፡፡ ምክትል የመቶ አለቃ መኮንን ዳርጌ እና ታፈሡ ጎን ለጎን፣ እንዲሁም ሒዋን ከታፈሡ ቀኝ በኩል፣ መርዕድ ደግሞ ከምክትል መቶ አለቃ መኮንን ዳርጌ ግራ ጎን በመቆም ታዳሚዎች እንዲቀመጡ ጋበዙ፡፡ ታዳሚዎች ጭብጨባቸውን አቁመው ሲቀመጡ የክብር እንግዶችም በየቆሙበት አቅጣጫ ተቀመጡ፡፡ ሙዚቃው ተለቀቀ፡፡ አስተናጋጆችና የድግሱ አስተባባሪዎች በታዳሚዎች ፊት ተቀምጠው የነበሩ ጠርሙሶችን መክፈት ጀመሩ፡፡ መስተንግዶው ጦፈ፡፡

በርካታ የድግሱ ታዳሚዎች ታፈሡንና መርዕድን በከተማ ውስጥ ያውቋቸዋል፡፡ ሒዋንን ግን እንኳንስ በውል የሚያውቃት በዓይኑም ዓይቷት የሚያውቅ ስለመሆኑ አንድም ታዳሚ እርግጠኛ አልነበረም፡፡ ከሁሉም በላይ ታዳሚዎቹን ያስደነቃቸው በምን ምክንያትና ሰበብ ታፈሡና መርዕድ የምክትል መቶ አለቃ መኮንን ዳርጌ የቅርብ ዘመድ ወዳጆች ሊሆኑ እንደቻሉ ነው፡፡ ያም ሆኖ ሁሉም በየሆዳቸው ‹ወይ ጉድ! የሰው ዘሩና የግንኙነት መስመሩ እኮ አይታወቅም› በማለት በግርምት አለፉት፡፡

የግብዣው ሥነ-ሥርዓት ቀጠለና በምክትል መቶ አለቃ መኮንን ዳርጌ ቀዳሚነት፣ በእነታፈሡ ቀጣይነት የብፌ ምግብ መነሳት ጀመረ፡፡ ታዳሚዎችም በየአቀማመጥ ቅደም ተከተላቸው ተከታትለው ምግብ አነሱ፡፡ እራት መበላት ተጀመረ፡፡ የመጠጡ ግብግብም ተከታተለ፡፡ ምግብ ተበልቶ አብቅቶ፣ ሳህኖች ከየጠረጴዛው ላይ ተነስተው፣ ጠረጴዛዎች በአስተናጋጆች ተወልውለው ካበቁ

በኋላ መጠጡ ጭውውቱና የሙዚቃው ጨኸት በቀጠለበት ሰዓት አሁንም ለሁለተኛ ጊዜ ሙዚቃው ድንገት ቆመ። የታዳሚዎችም ወሬና ጫጫታ ወዲያው ቆመና አዳራሹ ፀጥ ረጭ አለ። ሰዓቱ በግምት ከምሽቱ ሁለት ተኩል አካባቢ ይሆናል። አሁንም ያ የመክፈቻ ንግግር ያደረገው ሰው ወደ መድረኩ ሲራመድ ታየ። ቀድሞ እንዳደረገው ሁሉ ከታዳሚዎች ፊትለፊት በመቆም ታዳሚዎቹን በፈገግታ እያየ፡

«የተከበራችሁ እንግዶቻችን» ሲል ጀመረ። «ቀደም ሲል በመክፈቻ ንግግሬ ላይ እንደጠቀስኩት የዛሬው ጉዳያችን የስራ ባልደረባችን የሆነው የቀድሞው የሃምሣ አለቃ ዛሬ ደግሞ...» ብሎ ንግግሩን ጎተ...ት በማድረግ ወደ ጎኑ ዞሮ ምክትል መቶ አለቃን ሳቅ እያለ ሲያይ ታዳሚውም ምክትል መቶ አለቃ መኮንን ዳርጌና እንታፈሱም ሳቁ።

«አፍሬም ፈርቼም ነው እኮ!» አለ በመቀለድ ዓይነት።

ሳቅና ጭብጨባ ከታዳሚዎች ተቻረው።

«አመሰግናለሁ።» ብሎ እጅ ከነሳ በኋላ «በቀጣይ ሁለት ፕሮግራሞች አሉን። በመጀመሪያ የምንወደውና የምናከብረው ጓደኛችንና የስራ ባልደረባችን ከመካከላችን ተለይቶ ሲሄድ ማስታወሻችን ያድርጋት ዘንድ ያዘጋጀንለትን ስጦታ ማበርከትና ከዚያ ቀጥሎም ምክትል መቶ አለቃ መኮንን ዳርጌ ስለ ስጦታ የማዕረግ ዕድገትና ሹመት እንዲሁም ከእኛ ከወዳጆቹ በመለየቱ ያደረበትን ስሜት አጠር ባለ ሁኔታ የሚገልጽበት ፕሮግራሞች ናቸው። በዚሁ ቅደም ተከተል ማከናወን እንዲቻል የአውራጃችን ፖሊስ አዛዥ የሆኑት መቶ አለቃ ብዙአየሁ አስራት ስጦታዋን እንዲያበረክቱልንና ምክትል መቶ አለቃም ወደ መድረኩ ጫፍ ቀረብ ብሎ እንዲቀበልልን ሁለቱንም እጋብዛለሁ። አመሰግናለሁ።» ብሎ ከመድረኩ ወረደ።

መቶ አለቃ ብዙአየሁ ከታዳሚዎች መሀል ብድግ ብሎ ወደ መድረኩ አመራ። ማዕረጉን የሚገልጽ መለዮ ለብሷል። ከአርባ ዓመት እስፍ ያለው የሚመስል ጎልማሳ ነው። ወፈር ያለና ቀይ መልከ ቀና ብጤ ነው። መድረኩ ላይ እንደ ወጣ በቅድሚያ ለምክትል መቶ አለቃ መኮንን ዳርጌ፣ ቀጥሎ ደግሞ ለድግሱ ታዳሚዎች የፖሊስ ሰላምታ ሰጠ።

ወዲያው ምክትል የመቶ አለቃ መኮንን ዳርጌ ከተቀመጠበት ሶፋ ላይ ብድግ ብሎ ወደ መድረኩ ጫፍ ተራመደ። መቶ አለቃ ብዙአየሁ የግራ እጁን ወደ ግራ የሱሪው ኪስ አስገብቶ አንዲት በብልጭልጭ ወረቀት የታሸገች የማይካ ብልታጥ አወጣ። ወረቀቱን ቀዶ ከጣለ በኋላ ብልቃጧን ከፈተና አንድ ረዘም ወፈር ያለ የወርቅ ሀብል አወጣና ለታዳሚው ዘርግቶ አሳየ።

ተጨበጨበለት።

ወደ ምክትል መቶ አለቃ መኮንን ዳርጌ ጠጋ አለና ምክትል መቶ አለቃ መኮንን ዳርጌ ፈገግ ብሎ ጎንበስ በማለት አንገቱን ሲሰጠው አጠለቀለት። ሞቅ ያለ ጭብጨባ ተሰማ። ወዲያው ሁለቱ የፖሊስ መኮንኖች የፖሊስ ሰላምታ ተሰጣጡ። ቀጥለውም ተቃቀፉ።

አሁንም ተጨበጨበ።

የመቶ አለቃ ብዙአየሁ ወደ ቦታው ሲመለስ ምክትል የመቶ አለቃ መኮንን ዳርጌ ባለበት ላይ እንደ ቆመ ፊትለፊት ታዳሚውን ይመለከት ጀመር። ፕሮግራሙ ተረም ብሎ ተዋውቆ ነበርና ተጨማሪ ማስተዋወቅ አላስፈለገም። መቶ አለቃ ብዙአየሁ ከቦታው ደርሶ እንደተቀመጠ ምክትል መቶ አለቃ መኮንን ዳርጌ ንግግሩን ጀመረ። «በቅድሚያ ለተደረገልኝ የሽኝት ድግስና ለተበረከተልኝ ስጦታ ወሰን የሌለው ምስጋናዬን አቀርባለሁ።»

ተጨበጨበለት።

ምክትል መቶ አለቃ መኮንን ዳርጌ ንግግር ለመቀጠል እየፈለገ ነገር ግን መናገር ያቃተው መሰለ። ሆዱ ባብቶ እንባ ተናነቀው። ለታዳሚዎች በሀዘን ስሜት ከንፈራቸውን ሲመጡ ተሰማው። በዚህ ጊዜ የባሰውኑ እንባው ዝርግፍ አለ። ሁለቱንም ዓይኖቹን በሁለት እጅ ጣቶቹ ጠራረገና «በእኔ እምነትና ግምት በዲላ የአንድ ዓመት ቆይታዬ ይህን ያህል ዘመድ ወዳጅና የሰው ፍቅር ያፈራሁ አይመስለኝም ነበር። ሁኔታው ግን ከእምነቴና ከግምቴ በላይ ሆኖ ሳገኘው ሁሉም ነገር ተአምር ነው የሆነብኝ።» አለና አሁንም ዓይኖቹን ጨመቀ።

«መቼም በአገኘሁት የማዕረግ እድገትና ሹመት እልተደሰትኩም አልላችሁም። ግን ደግሞ ከዲላና ከእናንተ መሀል መለየቴ የደስታ በሽታ እንደሆነብኝ ማናችሁም የምትገነዘቡልኝ ይመስለኛል።» አለና መላ ታዳሚውን በዓይኑ ይቃኘው ጀመር። ከአፍታ ዝምታ በኋላ እንደገና ንግግር ጀመረ። «ለዚህ ዓይነቱ ስሜት መፈጠር ምክንያቱ ብዙ ነው። እናንተ መቸም እናንተ ናችሁ፣ የምወዳችሁና የምትወዱኝ የሥራ ባልደረቦቼና የግል ወዳጆቼ። በኔ በኩል ግን ራሷ ዲላ ከተማ የተለየና የሕይወት ሙሉ ትዝታ በሚሆን ገጠመኝ የተጠመድኩባትና የተለየ ፍቅርም እንዲያድርብኝ ያደረገችኝ ከተማ በመሆኗ ከእሷም ከእናንተም መለየቱ የዳገት ያህል ከብዶኛል።»

ታዳሚዎች ከንፈራቸውን መጠጡ። ምክትል መቶ አለቃ መኮንን ዳርጌ ቀጥሎ ለሚናገረው ነገር የበለጠ ጓጉ። እሱ ግን አሁንም እንባ ይተናነቀው ጀመር።

«የተከበራችሁ ወንድሞቼና እህቶቼ!» አለ እንደምንም። «መቼም የፖሊስነት ስራ ብዙ ጊዜ የሚያውለው ከወንጀልና ከወንጀለኞች ጋር ስለመሆኑ ሁላችንም የምናውቀው ነው። ፖሊስ ቢሰራም፣ ቢያወራም ስለ ወንጀልና ስለአፈጻጸሙ እንዲሁም ስለምርመራ ሂደትና ስለ ውጤቱ ነው። የወንጀል ዓይነቶችና የአፈጻጸማቸውም መንገድ ብዙ ነው። የሚያስቁ፣ የሚገርሙና የሚያስቆጩም አሉ። እኔ በፖሊስነት ስራ ለሃያ አምስት ዓመታት ያህል ስሰራ በእነዚህ ሁሉ ስሜቶች ውስጥ አልፌአለሁ። በዚህ ረገድ ለዲላ የተለየ ትዝታ እንዲኖረኝና የተለየ ፍቅር እንዲያድርብኝ ያደረገኝ የስራ ገጠመኝ ግን በማገኛውም ጊዜና ቦታ ከገጠመኝ ፍጹም የተለየ በመሆኑ ነው፤ ስለ ዲላ ከተማ ለማውራት የተገደድኩት።» አለና በትካዜ ስሜት ውስጥ ገብቶ መሬት መሬት ያይ ጀመር።

በዚህ ወቅት አንድ ነገር በሆዱ ያሰላስላል፣ ሸዋዬና በድሉ በሔዋን ላይ የፈጸሙትን ወንጀልና የወንጀል ድርጊቱን ዓላማ። ያን ጉዳይ በዚያ መድረክ ላይ ቢተርከው ከግብረ ገባዊ መለኪያ አንጻር ትክክል የመሆኑና አለመሆኑ ጉዳይ አስጨነቀው። ስሜቱ ተናገር ተናገር ይለዋል። የቦታው ትክክለኛነት ደግሞ

አልዋጥለት ይለዋል። በመሀል እንባ ተናንቀውና ዓይኑን ይጨምቅ ጀመር። በተለይ ሔዋንን በልቡ ሲያስባት ባንዳች ስሜት ተሸንፎና ‹ሰዎች ስለ ሰዎች ለመናገርና ስማቸውን ለማጥፋት ጊዜና ቦታ እንመርጥም፣ ግን ደግሞ ከፋት በተለይም የሰዎችን መልካም ስብእናና ክብራቸውን የሚያጎላ ነገር ለመናገር ለምን እናመነታለን?› አለ በሆዱ። አልሆም ተናነቀው። እናም ወደዚያው አመራ።

«ትዝ ይላችሁ ይሆናል ወንድሞቼ!» አለና ፊትለፊት እየተመለከተ «ምናልባት ከሁለት ወር በፊት ሲሆን ይችላል፣ ታዳሚዎችን የስፖርት ፌስቲቫል ተካሂዶ በተጠናቀቀበት ዕለት ምሽት ላይ ‹አንዲት ከተማ ሁለት ወንዶችን በተመሳሳይ ሰዓት ቀጥራ አደባደበች› በሚል ሰበብ ግርግር የተፈጠረበት ዕለት?» ሲል ጠየቀና ታዳሚዎችን ለረጂም ጊዜ ተመለከታቸው። ታዳሚዎች በአዎንታ አንገታቸውን ሲነቀንቁ አየና በበለጠ ቁጭት ተገፋፍቶ ድንገት ወደ ሔዋን ዞር በማለት «ነይ ወደኔ ሔዋን!» ሲል ጮክ ባለ ድምጽ ጠራት።

ሔዋን ያላሰበችውና ያልጠበቀችው ሁኔታ በመሆኑ በድንጋጤ በእስቸበት ድርቅ ብላ ቀረች። ዓይኗን ፍጥጥ አድርጋ ምክትል መቶ አለቃን ትመለከተው ጀመር።

«ነይ ወደኔ፣ ትመለሽለሽ!» አላት አሁንም።

«ታፈሡዬ!» አለችና ሔዋን ከምክትል መቶ አለቃ ጥያቄ ታድናት ዘንድ የታፈሡን ቀሚስ ጭምድድ አድርጋ ያዘች።

«አይዞሽ ሔዩ! ተነሽ! ምክትል መቶ አለቃን አታስቀይሚው።» አለቻት ታፈሡ የሔዋንን ጉንጭ ደበስበስ እያረገች።

ሔዋን ስትፈራ ስትቸር፣ በጭንቀት ፊቷ እንደተኮማተረ፣ ዓይኗ ግን በምክትል መቶ አለቃ መኮንን ዳርጌ ላይ እንደተሰካ ብድግ ብላ ቆመች። ወደ እሱ ለመራመድ ግን ፈራች። በዚህ ጊዜ ራሱ ምክትል መቶ አለቃ ክንዷን ያዝ አድርጎ ወደ መድረኩ ጫፍ ወሰዳትና ንግግሩን ጀመረ።

«ይቺ ቆንጆ ልጅ ነበረች ወንድሞቼ ጋለሞታ የተባለችው።» አለ በጣቱ ወደ ሔዋን እያመለከተ። ሔዋን ግን አንገቷን ደፍታ አቀረቀረች። ታዳሚዎች ሔዋንን ትኩር ብለው ያዩዋት ጀመር። ለምስጢሩ ከመጓጓቱ የተነሳ ሁሉም ፀጥ ረጭ ብሎ የምክትል መቶ አለቃን ንግግር ይጠብቅ ጀመር።

«ኢያችሁ ወንድሞቼ 'ጋለሞታ' የሚለው ቃል የሴትነት መግለጫ ጭራሹን ለዚች ቆንጆ ወጣት ልጃገረድ አያገለግልም። ከዚያም አልፎ በምርመራ ሂደት እንደተጣራው ይህቺ ልጅ ማንም ያልነካት ድንግል ናት። አደባደበቻቸው የተባሉትንም ሰዎች ጭራሹን አታውቃቸውም። ነገር ግን ቃል ገብታለት በአጋጣሚ የተለያትን ፍቅረኛዋን ቃሏን አክብራ በመጠበቅ ላይ ሳለች ለራሱ የፈለጋት ሰው፣ ለራሷ ጥቅም ከቆመች እህቷ ጋር ተመሳጥሮ የዚችን ልጅ መልካም ስም ለማስጠፋትና ከሚወዳትና ከምትወደው ፍቅረኛዋ ጋር ለማለያየት በማሰብ ያሴሩባትና የፈጸሙባት የስም ማጥፋት ወንጀል ሆኖ ተገኘ። እውነት ግን በራሷ ላይ ነፍስ ዘራች። የፖሊስነት ሙያ ይህቺን ልጅ ነጻ አወጣት። አጋጣሚ ሆነና በእኔው ምክንያት ከዚያ ተለይታው ከምትኖረው ፍቅረኛዋም ጋር ተገናኘች። ልጁ

ለሶስት ሰዓት ትንሽ የጤንነት ችግር ገጥሞት አዲስ አበባ በሚገኘው ቅዱስ [illegible] ሆስፒታል ተኝቶ እየታከመ ሲሆን ይህቺም ልጅ ከጎኑ ቁጭ ብላ [illegible] ይዛለች። ዛሬ እዚህ ቦታ የተገኘችውም በእኔ ጥሪና ግብዣ ነው። [illegible] ነበር የመጣችው። ነገ ደግሞ ወደዚያው ተመልሳ ትሄዳለች።» ሲል በዚያ [illegible] አዳራሽ ውስጥ የተገኘ ታዳሚ ሁሉ ሞቅ ባለ ጭብጨባ ቤቱን አንቃነቀው።

«ግን ግን» ሲል ቀጠለ ምክትል መቶ አለቃ መኮንን ዳርጌ «ይቺ ልጅ መልካም ስሟ በከንቱ ጠፍቶ አልቀረም፣ በአስተማማኝ ነጻ ወጥታለች። በአንጻሩ ደግሞ ያቺ ሴረኛ እህቷና ተባባሪዋ ከነወንጀላቸው ተደብቀው አልቀሩም። ከሰጡት [illegible] ቃል በተጨማሪ በሰውና ቴክኒካዊ ማስረጃዎች ድርጊታቸው [illegible] እነሆ ሁለቱም በህግ ቁጥጥር ስር ውለው ፍርዳቸውን በመጠባበቅ ላይ ናቸው።»

ታዳሚው አሁንም አጨበጨበ። እንደውም ጆሮ የሚበጠስ ፉጨት ተሰማ።

«አመሰግናለሁ።» ካለ በኋላ ምክትል መቶ አለቃ መኮንን ዳርጌ ሔዋንን ትከሻ ላይ ሳም አድርጎ ወደ መቀመጫዋ እንድትመለስ አመለከታት።

ሔዋን የሩጫ ያህል ተራምዳ ሶፋው ላይ ቁጭ በማለት ከፍርሀትና ከድንጋጤ ትድብታት ይመስል በታፈሡ ጡቶች መሀል ሽጉጥ አለች። ታለቅስም ጀመር። የሸዋዬንና የበድሉ አሸናፊን ተንኮል እንዲሁም የወደፊት እጣ ፋንታቸውን ከምክትል መቶ አለቃ መኮንን ዳርጌ እንደበት የሰማችው እንደ ሰመመን ነበር። እያደር ስታሰላስለው ግን ቁጭቱም ንዴቱም ተደማምሮ ምርር አድርጎ አስለቀሳት።

«እናም ወንድሞቼ» ብሎ ምክትል መቶ አለቃ መኮንን ዳርጌ ንግግሩን ሊያጠቃልል ሲል ድንገት ዓይኑን ወደ ሆቴሉ መግቢያ በር ላይ ጣል ሲያደርግ የጥድፊያ ዓይነት እንቅስቃሴ ተመለከተና ቀልቡንም ሰረቅ አደረገበት። በእርግጥም በር አካባቢ ቁጭ ብሎ የነበረ አንድ የድግስ ታዳሚ ወደ መድረክ ሲገሰግስ አየው። ሰውየው ከምክትል መቶ አለቃ መኮንን ዳርጌ አጠገብ ደረሰና ወደ ጆሮው ጠጋ ብሎ «ታፈሡና ሔዋን የሚባሉ ካሉ በአስቸኳይ ቤት ድረስ ይምጡ። የሚል መልዕክተኛ መጥቶ ነው።» አለው።

ምክትል መቶ አለቃ መኮንን ዳርጌ መልዕክቱን እንደሰማ ወደነታፈሡ ዞር ብሎ ሲያይ ለካ የተነገረውን መልዕክት እነሱም ሰምተውት ኖሮ አቀብቁበው እያዩት ኖሯል። «ምንድነው ሃምሳ አለቃ?» በማለት ታፈሡ ከተቀመጠችበት ተስፈንጥራ ተነሳች። ከመደንገጧ ብዛት የቀድሞውን ሃምሳ አለቃ በቀድሞ ማዕረጉ ጠራችው።

«'በአስቸኳይ ቤት ድረስ ኑ ተብለዋል' ይላል።» አላት ራሱም የድንጋጤ ስሜት እየተነበበበት።

«ኧረ ፍጠኑ ብለዋችኋል!» አለ መልዕክተኛው።

ታፈሡ፣ሔዋንና መርዕድ የምክትል መቶ አለቃውንም ሆነ የድግሱ ታዳሚዎችን ፈቃድ መጠየቅ የሚያስችል ፋታ እና ጊዜ አላገኙም። በታፈሡ መሪነት የእሽቅድምድም ያህል ተከታትለው ከአዳራሹም ወጡና ወደ ታፈሡ ቤት ሮጡ።

በዚህ ጊዜ የድግሱ ድባብ ፍጹም ተሰጠጠ። ምክትል መቶ አለቃ መኮንን ዳርጌ ራሱ ግራ ገብቶት በአለበት ቆሞ ቀረ። ታዳሚዎችም እንዲሁ በር በሩን፣ ሌላ ጊዜ ምክትል መቶ አለቃ መኮንን ዳርጌን በመመልከት ዓይናቸው ይንከራተት ጀመር። ከጥቂት ቆይታ በኋላ ግን ጥቂት ፖሊሶች ወደ ታሬሌ ቤት ሄደው የሆነውን ነገር እንዲያጣሩ ታዘዙና የእንታፈሡን ዱካ ተከትለው ገሰገሱ።

* * *

በዕለተ ረቡዕ ከማለዳ ጀምሮ የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ቅጥር ግቢ ቀውጢ ሆኗል። ሰበቡ የመኪና አደጋ ነው። አንዲት በተለምዶ ‹ውይይት› በመባል የምትታወቅ ታክሲ በርካታ የመድሐኒዓለም አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎችን አሳፍራ ከትምህርት ቤቱ በር ላይ በመድረስ ቆማ በማራገፍ ላይ ሳለች አንድ የፍሬን ችግር የነበረበት የከተማ አውቶቡስ ከታክሲዋ ላይ በመውረድ ላይ የነበሩ ተማሪዎችን ጨፍልቋቸው ነው። በርካታ ሞተዋል። ሌሎች ከፍተኛ የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል። ከአደጋ ተረፉ የሚባሉ ተሳፋሪዎች ብዙ አልነበሩም። ከተማሪዎቹ በተጨማሪ ሌሎች መንገደኞችም የሞትና የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል።

የሞቱትም ሆኑ የቆሰሉት ወደ ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ነው የተወሰዱት። ይህ አደጋ ከጠዋቱ ሁለት ሠዓት አካባቢ ደርሶ አረፈደ እያለ ሲሄድ ደግሞ የአደጋ ሰለባዎች ዘመድ አዝማዶች ከቦታው እየደረሱ የሆስፒታሉን ቅጥር ግቢ በለቅሶ፣ በጩሀትና በጩኸት እያደበላለቁ የጩበጣ ውጊያ የሚካሄድበት ጦር ሜዳ አስመስለውት አርፍደዋል። ሕይወታቸው ያላለፈ የአደጋው ሰለባዎች የስቃይ ጩኸት ከቤተሰቦቻቸው ሎሎታ ጋር ተዳምሮ ያ ግቢ ግብዓተ መሬት የሚፈጸምበት የመቃብር ቦታ መስሏል። የሆስፒታሉ ሐኪሞችና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ለሥራቸው የሚያደርጉትና የሚጨብጡትን አጥተው ተዋክበዋል። ቀደም ሲል አሉጋ ያዘው ተኝተው ይታከሙ የነበሩ ህሙማን ጨርሶ ተረስተዋል። ችግሩ ለአስታማሚዎቹ ተርፎ እነሱም በጭንቀት ወለሉ ያለሉ።

ከዚህ ችግር ተካፋይ አንዱ በልሁ ተገኔ ነው። አስቻለው ደግሞ ከለም ጀምሮ ህመሙ ፀንቶበት ሰንብቷል። በዚያው ልክ በልሁ አጠገቡ በመቆም የሚንከራተቱ የአስቻለውን ዓይኖች አስታትሎ ማየት የዘወትር ስራው ሆኗል። ሐኪም ዓይኖቹ በሰጠ ቀጥር ለውጥ ያመጣለት እየመሰለው ቢጓጓም ነገር ግን የአስቻለው ሁኔታ ከዕለት ወደ ዕለት እያሽቆለቆለ ሄዷል።

አደጋው በደረሰበት ዕለትም የአስቻለው ነፍስና የበልሁ ዓይኖች ተፋጥጠው አደሩ። ውትሮም እንደሚያደርገው ሁሉ በልሁ አስቻለው በተኛበት አልጋ አጠገብ ቆሞ ቁልቁል እየተመለከተው ሳለ ከውራደር ነቃበት ድንገተኛ ጩኸት ተሰማ። በአደጋው ከፍተኛ ጉዳት ደርሶባት የነበረች ልጅ ብዙም ሳትቆይ ሕይወቷ አልፏ ኖሯል። አልፊታ የተባለችው በመሆኗ በዚያው አስቻለው በተኛበት ክፍል በር ላይ ጩኸታቸውን ያሰሙ። የሟቿ ስም ‹ሐሊን› ኖሯል። አልቃሾቹም «ሐሊን ሐሊንዬ... ሐሉ...» እያሉ ያለቅሱ ጀመር።

ይህን የለቅሶ ጩኸትና የሟቿን ስም አስቻለው በሰመመን ውስጥ ሆኖ ሰምቶት ኖሯል። በልሁ ጠጋ ብሎ እጁን እንዲይዘው ጠቀሰው። በልሁ ጠጋ እንዳለለት አስቻለው እጁን ያዝ አደረገና፦

«ሒዋን ምን ሆና ሞተች በልሁ?» ሲል ዓይኑን እያንከራተተ ጠየቀው።

«ምን?» አለ በልሁ ድንግጥ በማለት። «ስለየትኛዋ ሒዋን ነው የምታወራው አስቻለው?» ሲል መልሶ ጠየቀው።

አስቻለው ልክ እንደ ጃጀ ሽማግሌ የበልሁን እጅ ጥብቅ አድርጎ በመያዝ ዓይኖቹን እያንከራተተ «አትዋሸኝ በልሁ፤ ሒዋን ሞታለች።» አለው።

በልሁ የባሰ ተረበሸ። እሱ በጤናማ ስሜቱ የሟቿ ስም ሐሊን ስለመሆኑ እርግጠኛ ቢሆንም ለአስቻለው ግን ‹ሒዋን› የተባለ እንደሚመስለው ሲረዳ ስለ አስቻለው የአሉ መንፈስ ተሰቃየ። ግን ብቻ ያልተማመነኩ መሰሉት፦

«ሒዋን እኮ በአሁኑ ሠዓት ያለችው ዲላ ነው። ለህምሳ አለቃ መኮንን ዳርጌ ሸኛት እንደ ሄደች ገና አልመጣችም። ምናልባት ዛሬ ወደ ማታ ላይ ትመጣና ታያታለህ። አሁን የሚያለቅሱት ሰዎች ‹ሐሊን› የምትባል ልጅ ሞታባቸው ነው። ‹ሒዋን› አይደለም የሚሉት።» አለው በማከታተልና ሽብር በተቀላቀለበት አነጋገር።

አስቻለው የበልሁን ንግግር ከቁብ አልቆጠረውም። ምናልባትም በትክክል እየሰማው ላይሆን ይችላል። የራሱን ንግግር ብቻ ቀጠለ።

«እኔንም እሷ በተቀበረችበት ቤተክርስቲያንና መቃብር ውስጥ ቅበረኝ።»

«ቀድሞ እሷ መች ሞተችና?»

አስቻለው አሁንም የራሱን ቀጠለ። «በመቃብራችን ላይ ‹እኛ በሰንቱ ሞተናል፤ እናንተ ግን አደራ፣ ብለህ ጻፍበት።» አለው የበልሁን እጅ ጭምድድ አድርጎ እንደያዘ።

የበልሁ ጭንቀት ከመጨረሻው ጫፍ ላይ ደረሰ። ከአስቻለው ጋር መነጋገሩ ዋጋ እንደሌለው አመነ። ቢሆንም ባይሆንም ሐኪም መጥራት እንዳለበት ታየው። እጁን ከአስቻለው እጅ ውስጥ እንደምንም ፈልቅቆ አላቀቀና በፍጥነት በሩን ከፍቶ ወጣ። ከነርሶቹ ክፍል በር ላይ እንደደረሰ አስቻለውንና በአካባቢው የተኙ ህሙማንን የምትከታተለዋን ነርስ ከውስጥ ወደ ውጭ ስትወጣ አገኛት። የተለያዩ መድሐኒቶችን ይዛ ወደ ድንገተኛ ክፍል በመሄድ ላይ ነበረች።

«እመቤት፣ ልጁ እኮ ያክመዩኝ» አላት በልሁ ትንፋሹ በርክቶ እያለከለከ። ነርሷን ‹ሲስተር› ብሎ መጥራት ሲገባው ‹እመቤት› ማለቱ መለማመዱና አክብሮት ማሳየቱ ነበር።

«ከወትርው የተለየ ምን ለውጥ አየህበት?» ስትል ነርሷም አእርምጃዋም ብላ ጠየቀችው። የበልሁ ሁኔታ ትኩረቷን ስቦታል።

«ይቃዥ ጀመር።»

«ምን እያለ?»

«ዘምባሎ የሆነ ያልሆነውን።»

«እሺ፤ ቆይ ይህን መድሐኒት ድንገተኛ ክፍል ላድርስና መጥቼ አያለሁ።» ብላው ወደ ድንገተኛ ክፍል ለመሄድ ከፎቅ ወደ ምድር ቤት ወረደች።

በልሁ ከስጋቱና ከፍርሀቱ የተነሳ ነርሷን ሊያምናት አልቻለም። እንዳይጠፋበት ለመከታተል ተከትሏት ወረደ። የጣቸበትን ክፍል እስከምትመለስ ድረስ እዚያው በገባችበት ክፍል በር ላይ ቆሞ ይጠብቃት ጀመር። አድራሻዋ አረጋገጠ

ነርሷ ብዙም ድንገተኛ ክፍል ውስጥ ብዙ አልቆየችም። መድሐኒቶችን አድርሳ ወዲያው ከክፍሉ ወጣች። በሩ ላይ በልሁን ስታገኘው በሚቴ ገብቷት ፈገግ አለችና «የምቀር መስሎህ ነው አይደል!» አለችው።

«አልዋሽም ሲስተር፣ ሰግቼ ነው።»

ነርሷ ከፊት፣ በልሁ ከኋላ በመሆን ተከታትለው ሶስተኛ ፎቅ ላይ ሲደረሱ በቀጥታ ወደ አስቻለው ክፍል አመሩ። ነርሷ ክፍሉን ከፍታ ስትገባ ብዚያ ሰዓት የአስቻለው ዓይኖች በር ላይ ተሰክተው ኖሯል። ልክ ነርሷ ገባ፣ በልሁ ከተል ሲል ፍጹም በአልጠበቀው ጩኸትና ጠንካራ ድምጽ አስቻለው፡-

«ሔዋን!» አለ ጭራሽ ከአንገቱ ቀና ብሎ ዓይኑን ፍጥጥ በማድረግ።

«አይደለሁም።» አለችው ነርሷ። አስቻለው ያቺ ነርስ ሔዋን ያለመሆኗን አውቆ ይሁን አሊያም በነርሷ ምላሽ ተስፋ ቆርጦ ብቻ ተመልሶ ወደ ትራሱ ጋለለ አለ።

«ሔዋን ምን ናት?» ስትል ነርሷ በልሁን ጠየቀችው።

«እህቱ።» አላት ድንገት አፉ ላይ የመጣለትን።

«እኔን ትመስላለች?»

«ኧረ በፍጹም!»

ነርሷ አስቻለውን እጅ ዘርግታ የመዳፉን ማጠፊያ ትስልል ጀመር። በያዘችው የማዳመጫ መሳሪያ የልቡን ምት አዳመጠች። መጨረሻ ላይ «አይዞህ ደህና ነው፣ እስቲ ለማንኛውም ዶክተሩንም ልጥራው።» በማለት በልሁን አፅናንታው ከክፍሉ ወጣች።

በልሁ የዶክተሩ መጠራት በአንድ በኩል እፎይታ ቢሰጠውም በሌላ በኩል ደግሞ አስቻለው አንድ ችግር እንደታየበት ጠረጠረና በተደበላለቀ ስሜት በክፍሉ ውስጥ ይንቆራጠጥ ጀመር። ቁና ቁና እየተነፈሰ አንዳንዴ አስቻለውን ይስልላል። ሌላ ጊዜ በጆሮው ኮቱ ከውጭ ያዳምጣል፣ የዶክተሩን መምጣት በመጠባበቅ።

ብዙም ሳይቆዩ ያቺ ነርስና የአስቻለው ዶክተር ተከታትለው መጡ። ልክ ነርሷ እንዳደረገችው ሁሉ ዶክተሩም አስቻለውን ከደባበሰ በኋላ በልሁ ከክፍሉ ውስጥ እንዲወጣ አዘዘው። በልሁ ወጣ። ነርሷና ዶክተሩ ክፍሉ ውስጥ እንደሆኑ እሱ በኮሪደሩ ውስጥ ይንቆራጠጥ ጀመር።

ወዲያው ነርሷ ከክፍሉ ወጣችና በቀጥታ ወደ አንድ ክፍል ውስጥ ገብታ የመድሐኒት ዓይነቶች ይዛ ተመለሰች። ከጥቂት ቆይታ በኋላ አሁንም ተመልሳ ወጣች። በሁለተኛው ጊዜ ግን እንደ በፊቱ መድሐኒት ሳይሆን ሌላ ዶክተር ይዛ ወደ አስቻለው ክፍል አመራች። ሁለቱም ክፍሉ ውስጥ ገቡ።

የበልሁ የኮሪደር ላይ የቆይታ ጊዜ በረከተ። ሁለት ዶክተሮች መሆናቸው በመረዳዳት የአስቻለውን ሕይወት የመታደግ ዕድል ሊኖር እንደሚችል ቢገምትም በሌላ በኩል ደግሞ ‹ይህ ነገር የአስቻለው ህመም መጥናት ምልክት ነው› በሚል

የሀሳብ አጣብቂኝ ውስጥ ገባ። ከዚሁ ጋር ተያያዘና አስቻለው የኑዛዜ ቃል በአእምሮው መጣበት። ይመራመርበትም ጀመር።

ከሁሉም በፊት ግን የሔዋን የደህንነት ጉዳይ አሳሰበው። የምክትል መቶ አለቃን የሽኘት ስነ-ሥርዓት እሁድ አከብራ ሰኞ ዕለት ከመርዕድ ጋር አዲስ አበባ ሊገቡ ቀጠሮ ነበራቸው። ነገር ግን ሰኞና ማክሰኞንም አልፈው እነሆ ዛሬ ዕረቡ ላይ ተደርሷል። እነሱ ግን አልመጡም።

«እና» አለ በልሁ ለብቻው እየተነጋገረ «ይቺ ልጅ ያ የልብ ሕመሟ ምን ዓይነት ችግር ፈጥሮባት ይሆን? አስቻለው የሔዋን ሞት የታየው ከዚሁ ጋር የተያያዘ አደጋ ደርሶ ይሆን እንዴ?» አለና ጭንቅ ጥብብ ሲለው ወደ ላይ አንጋጦ እጆቹን ወደ ላይ በመዘርጋት «ጌታ ሆይ! ይህንንስ አታድርግ! ይህንንስ አታምጣ!» በማለት አምላኩን ተማፀነ። ቀጠለ አሁንም በአስቻለው የኑዛዜ ቃል ዙሪያ መመራመሩን። «ለመሆኑ» አለ አሁንም እጆቹን በደረቱ ላይ አቆላልፎ ጎንበስ ብሎ በኮሪደሩ ላይ ራመድ ራመድ እያለ። «እኛ በከንቱ ሞተናል፣ እናንተ ግን አደራ ብለህ ጻፍበት ሲል ምን ማለቱ ይሆን? ምን ዓይነት መልዕክት ማስተላለፍ ፈልጎ ይሆን?» እያለ ሲያስብ በራሱ በበልሁ አዕምሮ ውስጥ ብዙ ሀሳቦች ተመላለሱበት። ‹ሳንወልድ ሳንከብድ በከንቱ ስንነፋፈት ኖረን ልፋታችን ሁሉ ከንቱ ሆነ። እናንተ ግን እንዲህ ዓይነት ፍሬ አልባ ፍቅር ተጠንቀቁ ማለቱ ይሆን?› ካለ በኋላ ግን ደግሞ ወዲያው ሀሳቡን ለወጠ። ‹የለም፣ አስቻለው እንዲህ ዓይነት መልዕክት ለትውልድ ማስተላለፍ አይፈልግም። እንዲያውም ‹በሕይወት እስካላችሁ ድረስ በፍቅር ኑሩ› ይላል እንጂ!» በሚል እሳቤ ተካው።

አሁንም ቀጠለ መመራመሩን። «የአስቻለው አዕምሮ እኮ መስኮቱ ብዙ ነው፤ የማያይበት አቅጣጫ የለም። ምናልባት ሞት ሞት ሸተተውና ለሞት ያበቃውን የህይወት ጉዞ መርምሮት በሂደት በተፈጠረ ስህተት ለዚህ ተዳርገአለሁና በእናንተ እንዳይደገም ማለቱም ይሆናል።» አለና በእርግጥም የአስቻለውን የሕይወት ውጣ ውረዶች ያስባቸው ጀመር።

አዎ! አስቻለው በሽታ ላይ ለመውደቁ ሰበቡ ወደ ኤርትራ መሄዱ ነው። ወደ አስመራ እንዲሄድ የተደረገው በግፍ ነው። የግፍ ዕዳ እንዲጫንበት ያደረገውም የራሱ ተፈጥሮአዊ ባህሪ ነው። ሁል ጊዜ እውነትን ይፈልጋል፣ ይናገራልም። ዘመኑ ደግሞ የውሸት ነው። ሁለቱ ተጋጩና መጋኛ ፈጠሩበት። ከዚህም በተጨማሪ አስቻለው በተፈጥሮው የተዕዕና ሽንፈት አይቀበልም። የግል ነጻነቱን አያስደፍርም። የዜግነት መብቱን ማጣት አይፈልግም። ሰውየው ክብር ሟች ነው። ሁሉን በቀጥታ ሁሉን በፊትለፊትና ሁሉን በግልፅነት መፈፀምና እንዲፈፀምም ይፈልጋል። ግን ደግሞ ይህ በሚቻልበት ዘመን አልተወለደም። ወይ ቀድሟል ወይ ዘግይቷል። የዚህ ሁሉ ጣጣ ወደ አስመራ እንዲገፋተር አድርጎታል። ወደ ኤርትራ ከመሄድ ይልቅ ባለ መሄዱ የሚደርስበትን መከራ ሁሉ ለመሸከም ቁርጠኛ ነበር። ነገር ግን ከስራ እንዳይባረር፣ ወይም የእናት ሀገር ጥሪ ባለመቀበል ‹ወንጀል› እንዳይታሰር፣ በዚህና በዚያ ምክንያት ፍቅሩ የሆነችውን ሔዋንን እንዳያጣ በማሰብ ራሱ በልሁ፣ ታፈሡና መርዕድ እንዲሁም ሔዋን ተባብረው በፈጠሩበት ጫና

ተገደዶ ነበር የሄደው። ይህን ነገር አስቻለው እንደ ሸንፈት ነበር የቆጠረው። እነሆ ውጤቱ ደግሞ አሳዛኝ ሆኖበታል።

በልሁ ይህን ሁሉ ነገር ካወጣ ካወረደ በኋላ «ይህ ሰው ሕኖ በከንቱ ሞተናል…፣ ማለቱ ሕኛ ግፍን ስንሸሽ ኖረን ነገር ግን ግፍ አስገበት ድረስ መጥቶ ለሞት ዳርጎናል። ይህ ከንቱ ሞት ነው። እናንተ ግን ግፍና ተስፋንን በበታው ታገሉት እንጂ አትሸሹት። ግፈኞች እስካሉ ድረስ ግፍ አሳችሁበት ድረስ ይመጣባችኋል። ስትታገሉ ሙቱ እንጂ ስትሸሹ አትሙቱ። አደራ!» ማለቱ ይሆናል።» በማለት አስበና የንግዜሉን ምስጢር እንዳገኘው ሁሉ የልብ እርዳታ ተሰማው። በረጅሙ ተንፍሶ ራሱን ወዘወዘ።

ወዲያው የሰው ኮቴ ተሰማው። ወደ አስቻለው ክፍል ዞር ብሎ ሲመለከት ሁለቱ ዶክተሮች ተከታትለው ሲወጡ አየ። ምን ሊሉት እንደሚችሉ በመጓጓት ትኩር ብሎ ሲመለከታቸው ያ የአስቻለው ዶክተር በእጁ ጠቀስ አደረገውና በልሁም ጠጋ ብሎ ጆሮውን ሲሰጠው «እይዞህ ደህና ነው። በተረፈ ነርሷ የምትሰጥህን ትዕዛዝ ተቀበል።» ብሎት ወደ ቢሮው አመራ። በልሁ ከነርሷ የሚሰጠውን ትዕዛዝ ለመስማት ዓይኑ ከክፍሉ የምትወጣበትን ጊዜ በመጠባበቅ ላይ ሳለ ነርሷ ወዲያው ወጣች። በሩን መልሳ ዘጋችና እንዲያውም ቆለፈችው። በልሁ ወደ እሷ ሲራመድ ማሰቡን አውቃ «እዚያው ጠብቀኝ።» አለችው።

በልሁ ቀጥ ብሎ ቆመ። ዓይኖቹ ግን በነርሷ ላይ ትክል አሉ። ልቡ ደንግጥ አለና ከንፈሮቹን በምላሱ ያርስ ጀመር። ነርሷ ግን ወደ በልሁ ስትጠጋ ፈገግ ብላ ነው። በዚያው ፈገግታ በተላበሰ ሁኔታዋ የበለጠ ጠጋ አለችውና፡-

«ደነገጥክ እንዴ?» ስትል ጠየቀችው።

«ፈራሁ»

«አይዞህ! ምንም አይለው። አሁን አንድ ለየት ያለ መድሐኒት ሰጥተነዋል። መድሐኒቱ ግን የህመምተኛውን እንቅስቃሴና የትኩረት መስዋወጥ አይፈልግም። ቢያንስ ለግማሽ ሰዓት ዕረፍትና የሀሳብ መረጋጋትን ይጠይቃል። ስለዚህ አንተም እንዳትገባ ብዬ በሩን ቆልፌዋለሁ። እኔ እስከምጠራህ ድረስ ዘወር ዘወር እያልክ ራስህን አዝናና። እንዲያውም እታች ወርደህ ወደ ክበብ አረፍ ብትል ጥሩ ነው። እኔም ስፈልግህ በቀላሉ አገኝሀለሁ።» አለችው ረጋ ባለ መንፈስ።

በልሁ አሁንም በረጅሙ ተነፈሰ። ምራቁንም ዋጥ አደረገ። የነርሷን ትዕዛዝ መቀበል እንዳለበት ከዶክተሩም ተነግሮታል። የነርሷም አነጋገር ለዛ የተላበሰ ነው። ነርሷ ወደ ቢሮዋ ስታመራ እሱም ከሶስተኛ ፎቅ ምድር ላይ ወደሚገኘው የሻይ ክበብ አመራ።

ግማሽ ሰዓት ለበልሁ የግማሽ ዓመት ያህል ረዘመበት። ለነገሩ ከጠዋት ጀምሮ ምንም ነገር በአፉ አልገባምና ርሀብም ተሰማው። ሰዓቱ ደግሞ ወደ ስድስት ተኩል ተጠግቷል። ሻይና ኬክ አዘዘ። ፉት ፉት፣ ጎረስ ጎረስ አደረገ። ቡናም አዘዘ። ሲቀርብለት አሁንም ፉት ፉት አለ። ግን የሁሉም ነገር ጣዕም እህል ውሃ አይለውም። ማጣፈጫው ስኳር ይሁን ጨው አይለይለትም። ትክክስ ይሁን ቀዝቃዛ አይሰማውም። ስሜቱ ሁሉ በአስቻለውና በሁኔታው ዙሪያ ብቻ ሆነ። በመሀል የሒዋንና የመርዕድ ጉዳይ ትዝ አለው። «ዛሬም ላይመጡ?» አለ ለብቻው

አየተነጋገረ። «ትንሽ ልጠብቃቸውና ስልክ ደውዬ ችግራቸውን ማወቅ አለብኝ። ብቻ ነርሷ ስለ አስቻለው የምትነግረኝ ነገር ሰላም ይሁን!» እያለ በማሰብና በማሰላሰል ላይ ሳለ ሠዓቷ ደርሶ ኖሮ ያቺ ነርስ ድንገት ከፊቱ ከች አለች።

«ሻይ ቡና አልክ?» አለችውና ወንበር ሳብ አድርጋ ከአጠገቡ ቁጭ አለች።

«ሁሉንም አደረኩ።» አላት በልሁ በፍርሀት ዓይን እየተመለከታት።

ነርሷ ቡና አዘዘች። እስከሚቀርብላትም ድረስ ከበልሁ ጋር ጭውውት ጀመረች። ተነጋገሩ። በእርግጥም ብዙ ተወያዩ። ተግባቡም። ከዚያች ሠዓት ጀምሮ በልሁ ወደ ዲላ ስልክ ለመደወል ቁርጥ ሀሳብ ላይ ደረሰ። ከነርሷ ጋር ተሰነባበቱና እሷ ወደ ስራዋ ስትመለስ በልሁ ደግሞ ከሆስፒታሉ ቅጥር ግቢ ወጥቶ ስልክ ፍለጋ ኪዎስኮችን ይፈልግ ጀመር።

ስልክ እንዳገኘ በቀጥታ መርዕድን ለማግኘት ወደ የአፄ ዳዊት ትምህርት ቤት ደወለ። ለጊዜው መርዕድን አላገኘውም። ስልኩን ያነሳው ሰው ግን መርዕድን ከአ/ሥር ደቂቃ በኋላ ሊያቀርብለት እንደሚችል ነገረው። «ለካ ዛሬም ወደ አዲስ አበባ ጉዞ አልጀመሩም» አለ በልሁ። ዲላ ውስጥ አንድ ችግር እንዳለ ገመተ። የሆዱን በሆዱ አድርጎ ወደ አውራጃው ግብርና ጽህፈት ቤት ደወለ። በጓደኞቹ አማካይነት ለታፈሡ ሊደርስለት የሚፈልገውን መልዕክት አስተላለፈ። ይህ ሁሉ እስከሚሆንበት ድረስ መርዕድን የቀጠረበትም ሰዓት ደረሰና እንደገና ወደ አፄ ዳዊት ትምህርት ቤት ደወለ። መርዕድን አገኘው።

«ሀሎ መርዕድ!»

«አቤት!»

«አንተና ሒዋን እንመጣለን ያላችሁት ባለፈው ሰኞ አልነበረም እንዴ? ነገር ግን ይኸው እስከዛሬ አልተነሳችሁም፤ ችግሩ ምንድነው?» ሲል ጠየቀው።

መርዕድ ለበልሁ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት የተቸገረ በሚመስል አኳኋን ትንፋሹ ቁርጥ ቁርጥ እያለና እንደ መርበትበትም እያደረገው «እ…እ…» ካለ በኋላ «ግን እኮ ነገ ልንመጣ ተነስተናል።» አለው።

«ሒዋን ግን ደህና ናት?»

«ደህና ናት።»

«በእርግጥ ነገ ወደዚህ ወደ አዲስ አበባ ጉዞ ትጀምራላችሁ?»

«አዎ፣ ወስነናል።»

«ጥሩ እሺ! እንዳትቀሩ፣ እጠብቃችኋለሁ።»

ስልኩ ከሁለቱም በኩል ተዘጋ።

የዕረቡ ቀትር ተጠናቀቀ። ፀሐይ ወደ ምዕራብ አዘቀዘቀች። አድማሱን አቅልታ ጨረሯን ወደ ላይ በመዘርጋት እሷ ግን ቁልቁል ሸሸች። ብላ ብላም ጠለቀች። ለዓይን መያዝም ጀመረ። የመንገድ መብራቶች ሁሉ በሩ። ክዋክብትና ጨረቃ የሰማይ ቦታቸውን ተረከቡ። ሌሊቱም ተጀመረ።

ለበልሁ ግን ሁሉም ነገር ያው የቀን ያህል ነው። እንቅልፍ አላስፈለገውም፤ በንቃት ያስባል። ዕረፍትም አላገኘም፤ የዘመኑን የሰዓት እላፊ አላስፈለገውም፤ በንቃት ያስባል። ነወዲያ ወዲህ ገደብ በራሱ ጥሶ በአዲስ አበባ አውራ መንገዶች ላይ ይሯሯጣል። በሀሳቡ ሒዋንና መርዕድ ወደ አዲስ አበባ ሊመጡ ስንቅና

ልብሳቸውን ሲያዘጋጁ እየታየው እሱ ደግሞ ማለዳ ተነስቶ ወደ ዲላ ለመብረር የኮንትራት መኪና ለማግኘት ይለፋል፡፡

ወደ እኩለ ሌሊት ላይ የሚፈልገውን የመኪና ዓይነት አገኘ፤ ፈጣንና ጠንካራዋን ባለ አንድ ጋቢና ቶዮታ መኪና፡፡ በእርግጥም ገና ጎህ ሳይቀድ ተሳፈረባት፤ ከጨለማው ቅልቅል ጉዞ ወደ ዲላ ጀመረ፡፡

ከአፍንጫው መተተር የተነሳ "መጥረቢያ ፊት" ሊባል በሚችል ባለሙያ ሾፌር የምትነዳው ቶዮታ መኪና ማልዳ በመነሳት የአዲስ አበባ መንገዶችን በግላጭ አግኝታ እንደ ንስር ትወረወርባቸው ጀመር፡፡ ከአዲስ አበባ ወጥታ ሊቃቂን፣ ዱከምን ደብረዘይትንና ሞጆን አቆራርጣ ወደ ሲዳሞ መስመር መታጠፊያውን መንገድ ስትይዝ ገና ከጠዋቱ አንድ ሰዓት እንኳ በወጉ አልሞላም፡፡ ከፍተኛ የተነሳ ከነመድ የተረፈው የሸራ ሸፍኗ እንደ እየተርገበገበ ሲጮህ የእውቅ ዜመኛ ቀጨጨ ይመስላል፡፡ ጋቢናዋ በንፋስ ተሞልቶ ከኋላ በኩል ግን ድንቅ የተፈጥሮ ሙዚቃ እየተሰማባት ቶዮታዋ ወደ ፊት ተጠጋች፡፡ የእዋሽ ወንዝንም ገና በጠዋቱ ተሻገረችው፡፡ ከዚያም እልፍ ወደ አለም ጤና፡፡ ሾፌሩና በልሁ ለመጀመሪያ ጊዜ የተነጋገሩት ዝዋይ ከተማ ሊደርሱ ሲሉ ነው፡፡

«ስማ ሾፌር! ቁርስ ያስፈልግህ ከሆነ ዝዋይ ከተማ ላይ አረፍ ብንል፤ እሱን ካለፍን ዲላ ሳንደርስ የረባ ነገር አይገኝም፡፡» አለው በልሁ፡፡

«ለኔ ሳይሆን ለአንተ ያስፈልግሃል፡፡ እኔ በጠዋት መብላት ብዙም አልወድም፡፡ አንተ ቁርስ የምታደርግ ከሆነ ልቁም፡፡» አለው ልክ እንደ አፍንጫው ትንፋሹም ወጣ ወጣ ብሎ አስፈሪ ግርማ ሞገስ የተላበሰው ሾፌር፡፡

«የለም! አንተ የማትበላ ከሆነ ዝም ብለን እንሂድ፡፡» አለ በልሁ በመኪናዋ የፊት መስታወት ወደፊት እያየ፡፡

«ቀመስ ብታደርግ አይሻልም የኔ ወንድም?»

«በፍጹም! ሂድ ቀጥል!»

መሪና ማርሹን፣ እንዲሁም ፍሬሲዮንና ፍሬኑን በአንድ እጁ የሚቆጣጠረው ይመስል ሁሉን ነገር በፍጥነትና በቅልጥፍና እያስተካከለ ያ ሾፌር ያቺን ቶዮታ መኪና ነዳጅ እስከ አፍንጫዋ እየጋተ ያበርራት፣ ያከንፋት ጀመር፡፡ ከዝዋይ ከተማ ወጣ ብለው አዳሚ ቱሉን በማለፍ በግምት አስር ኪሎ ሜትር ከተጓዙ በኋላ በልሁ ድንገት ስቅስቅ ብሎ ያለቅስ ጀመር፡፡ ሰበቡ ያ ቦታ ያኔ እስቻለው በከባድ የመኪና አደጋ የተጎዳበት ሥፍራ መሆኑ ነው፡፡ የበልሁ ለቅሶ ያንን አሰቃቂ ሁኔታ በማስታወስና ከዓመታት በኋላ ደግሞ እስቻለው ያለበት ሁኔታ መንፈሱን ረብሾት አንጀም ስለተንሰፈሰፈበት ነው፡፡

በበልሁ አለቃቀስና እኳኋን ልቡ የተነካው ሾፌር አየት መልከት ካደረገው በኋላ «ተው እንጂ የኔ ወንድም! ምን ነካህ? ወንድ ልጅ እኮ እንዲህ አድርጎ አያለቅስም፡፡» አለው ረጋ ባለ አነጋገር፡፡

በልሁ ግን አሁንም እንባውን በጉንጮቹ ላይ እያንቆረቆረ «በአሁኑ ጊዜ ማልቀስ ያለበትማ ወንድ ልጅ ነው ሾፌር! ወንድ ልጅ ዛሬ ያላለቀሰ መቼ

ሊያለቅስ?» አለ ስሜቱ የባሰ እየተለዋወጠ፡፡ እንዲያውም ፊቱን ከፍ፣ ቀና አድርጎ «ጉብዋ! ሰውነቱንም ጥብቅ በማድረግ በባሰ የእልህና የቁጭት አነጋገር «ቆራጡ ያለች ቀን ቀና እልል ብላው የመከራ ሸክም የከበደው ወንድ ልጅ! ዛሬ ላይ ቆሞ የነገ ተስፋውን እንዳያይ በጭፍን ፖለቲካ ዓይኑን የተጋረደ ወንድ ልጅ! በተንኮልና በደባ መረብ ተይዞ ያለ ተፈጥሮው ወኔውን የተሰለበ፣ እገር ከወርቅ ታስሮ በማይፈልገው ጉዳና እንደ በግ በመነዳት ያለ ወንድ ልጅ!» በማለት እንባውን እያፈሰሰና ድምፁም እየተቆራረጠ «ዛሬ ነው አሁን ነው እንጂ፣ ወንድ ልጅማ ማ-ማልቀስ ያለበት!» አለና ሲቃ እንደ ሰውነቱን እስኪያርገፈግፈው ድረስ «ሀሀሀሀ...» በማለት ተንሰቅስቆ አለቀሰ፡፡

«ቢሆንም፣ ቢሆንም» አለና ሾፌሩ ወዲያው ደግሞ «አይዞህ! የጊዜ ጉዳይ ነው እንጂ ከፉዎች ለከፋ ዓላማቸው ሲሉ የፈተሉትን ማግ ራሳቸው ይገነዙበታል፡፡» አለው፡፡

በልሁ በረጅሙ ተንፍሶ «እስቲ ይሁን!» አለና ዓይኑን ጠራርጎ ወደፊቱ ይመለከት ጀመር፡፡ እንባው አሁንም በጉንጮቹ ላይ ይንቆረቆራል፡፡

የዝዋይን የሚዳ በረሃ ጨርሰው ቡልቡላን አለፍ በማለት ወደ አርሲ ነገሌ በመቃረብ ላይ ሳሉ በልሁ አሁንም ሾፌሩን አናገረው፡፡ «ስማ ሾፌር!»

«አቤት!»

«ከፊትለፊታችን «ዲላ-አዲስ አበባ» የሚል ታፔላ የለጠፈ አውቶቡስ ስናገኝ ትቆምልኛለህ፤ አውቶቡሱንም ታስቆምልኛለህ፤ ከዚያ ወደዚህ የሚመጡ ሰዎችን ማግኘት እፈልጋለሁ፡፡» አለው፡፡

«እሺ የኔ ወንድም!» ሲል ሾፌሩም በትህትና መለሰለት፡፡

መኪናዋ በረረች፡፡ ሻሸመኔ ከተማ ደረሰች፡፡ ሰዓቱም ወደ ሶስት ተጠጋ፡፡ በልሁ ከፊትለፊቱ አውቶብስ ይጠብቃልና ማንኛውም ዓይነት የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ከፊትለፊቱ ከሩቅ በታየው ቁጥር አውቶቡስ እየመሰለው ልቡ ስንጥቅ ስንጥቅ፣ ትንፋሹ ቁርጥ ቁርጥ ማለት ጀመረ፡፡ ያ ከርቀት የታየው መኪና አጠገቡ ሲደርስና መለስተኛ አውቶቡስ መሆኑን ሲያውቅ እንደገና ልቡ መለስ ይላል፡፡ ብቻ ልቡ ሲወጣ ሲላላ ከሻሸመኔ እስከ አዋሳ ድረስ ያለው ሚዳማው የሃያ ኪሎ ሜትር መንገድ እንደ ምንም አለቀ፡፡

ልክ ሶስት ሰዓት ተኩል ሆነ፡፡ ቶዮታዋም ከጥቁር ውሃ ድልድይ ላይ ከች አለች፡፡ በልሁ ፊትለፊት ሲመለከት በጥቁር ውሃ ፍተሻ ጣቢያ ላይ ሁለት እንበሳ አውቶቡሶች ቆመው ሲፈተሹ አየ፡፡ መኪኖቹ እያንዳንዳቸው እስከ ስልሳ ሰው የሚጭኑ በመሆናቸው የሁለቱም መኪና ተሳፋሪ ወርዶ መንገድ ላይ ሲርመሰመስ የፍተሻውን ቦታ ከሩቅ ሲያዩት ገበያ ይመስላል፡፡ በዚያ ሰው መሀል መርዕድና ሔዋን ሊኖሩ እንደሚችሉ ገመተና «ድልድዩን አለፍ ብለህ ትቆምልኛለህ ሾፌር! የምፈልጋቸው ሰዎች እዚህ ሕዝብ ውስጥ ሳይኖሩ አይቀሩም፡፡» አለው፡፡

ሾፌሩ በታዘዘው መሰረት ድልድዩን ተሻግሮ ዳር ይዞ ቆመ፡፡ በልሁ ከመኪናዋ ላይ ወረደና በቀጥታ ወደ ሕዝቡ አመራ፡፡ ልክ ወደ ሕዝቡ መሀል ገብቶ ፍለጋውን ሊቀጥል ሲል የሚያውቀውን ድምጽ ከሩቅ ሰማ፡፡

«በልሁ!» የመርዕድ ድምጽ ነው፡፡

በልሁ ድምጹን ወደሰማበት አቅጣጫ ዞር ሲል አውነትም መርዕድን አየው፡፡ ቀጥሎ ደግሞ ሒዋንን፡፡ እሱም ወደ እነሱ እነሱም ወደ እሱ በመራመድ ተገናኙና ተሳሳሙ፡፡

በልሁ በተለይ ሒዋንን አተኩሮ ሲመለከታት ከአጠቃላይ ሁኔታዋ አንድ ዓይነት ችግር ይነበብባታል፡፡ ሰውነቷ ጥውልግልግ ብሏል፡፡ ራሷን በጥቁር ሻሽ ግጥም አድርጋ አስራለች፡፡ ነጠላዋን ዘቅዝቃ ለብሳለች፡፡ ዓይኖቿ ሙጭሙጭ ብለው ቀልተዋል፡፡ ከንፈሮቿም ደራርተዋል፡፡ 'በእርግጥም ችግር አለ' አለ በልሁ በሆዱ፡፡ ከምንም በላይ ስለ ታፈሡ አሰበ፡፡ እሷ ደህና ብትሆን በልጆቿ ላይ አደጋ ደርሶ ሊሆን እንደሚችል ልቦናው አሰበ፡፡ ግን የሆዱን ሁሉ በሆዱ አደረገና፡-

«እንኳንም አልተላለፍን፡፡ እኔ ደግሞ መሥሪያ ቤቴ ውስጥ ያለኒ የማይፈታ ችግር ተፈጥሮ ለዚያው ጉዳይ ተጠርቼ ነው ዛሬ የመጣሁት፡፡» ካለ በኋላ ከመንገድ ማዶ የቆመችውን ቶዮታ መኪና በእጁ እያመለከተ «በዚያች መኪና ነው የመጣሁት፡፡ አሁን እናንተ ብቻችሁን አዲስ አበባ ብትሄዱ ምንም ስለማታደርጉ ወደ ዲላ እንመለስና ነገ በዚችው መኪና ወደ አዲስ አበባ እንሄዳለን፡፡» አላቸው፡፡

«የቆረጥነውስ ቲኬት» አለ መርዕድ፡፡

«ቢቃ ይክሰር፣ ነገ ወጪ ሳናወጣ ስለምንሄድ ምንም አይደል፡፡» በማለት እቃ ይዘው ከሆነ እንዲያወርዱ ነገራቸው፡፡ መርዕድ ወደ አውቶቡሱ ፈጥኖ ገባና ዕቃውን ሁሉ አወራርዶ ከበልሁ ጋር ተከፋፍለው በመያዝ ወደ ቶዮታዋ አመሩ፡፡ ሒዋን በዛሬው ቀን ከእስቻለው ጎን መቆም ባለመቻሏ ውስጥ ውስጧን ቅር እያላት ከቶዮታዋ ደረሱና መርዕድ ከሾፌሩ ጎን፣ ሒዋን ከመሀል በልሁ ደግሞ ከዳር በኩል በመሆን እንደ ምንም ተጨናንቀው ተቀመጡ፡፡ ጉዞውም ቀጠለ፤ ወደ ዲላ፡፡

ቶዮታዋ አዋሳ ከተማን አልፋ ወደ አቤላ ከተማ የሚያደርሰውን ቁልቁለታማ ረጅም መንገድ እስከምትጨርስ ድረስ ማንም ምንም ቃል አልተነፈሰም፤ ሁሉም ዝም፡፡ ሁሉም ፀጥ፡፡ በየሆዳቸው 'ማን ይጀምር ማን ይቅደም' የሚል ፉክክር ላይ ናቸው፡፡ ወደ ከተማዋ ዳርቻ ሲደርሱ ግን በልሁ ተሸነፈ፡፡ «ለመሆኑ እስከ ዛሬ የቆያችሁት በሰላም ነው?» ሲል ለሁለቱም ጥያቄ አቀረበ፣ የሆነ ችግር ካለም ልስማውና ልረፍ በሚል ስሜት፡፡

መርዕድና ሒዋን ግን ዝም ዝም አሉ፡፡ መርዕድ ደንግጦ በሾፌሩ በኩል ባለው መስታወት ውስጥ ውጭ ውጭ ይመለከት ጀመር፡፡ ሒዋን ደግሞ ዓይኖቿ እንባ እያቀረሩ ፊትለፊት ትመለከታለች፡፡ ይህ ሁኔታ በልሁን የበለጠ አሳሰበውና ቁርጡን ማወቅ ፈለገ፡፡

«ታፈሡ ደህና አይደለችም እንዴ?» ሲል በተለይ ሒዋንን እያየ ጠየቃት፡፡

«እሷ ደህና ናት፡፡» አለች ሒዋን እንባዋ ድንገት ዝርግፍ እያለ፡፡

«ታዲያ ማ ምን ሆነ?» አለ በልሁ ጠንከር ባለ አነጋገር፡፡ ሁለቱም የተጨነቁ መስለው ታዩት፡፡

«ት-ትርፌ» አለች ሒዋን ቃሏ እየተቆራረጠ፡፡

«አ!» አለ በልሁ በድንጋጤ፡፡ ትርፌ ፍፁም በሀሳቡ ውስጥ አልነበረችም፡፡ ስሟ ሲነሳ ግን ቀልቡ ብትን አለና «ትርፌ ምን ሆነች?» ብሎ መልስ ሳይጠብቅ «ሞተች?» ሲል ወዲያው ጠየቀ፡፡

ሒዋን ድንገት ሰቅሶ ፈነቀላት፡፡ ፊቷን ከበልሁ ክንድ ላይ ልትም አደረገችና «አ-አዎ በልሁዬ!» አለች ድምጿ በለቅሶ እየተቆራረጠ፡፡

«ምን ሆና?»

«ሕ-ሕሳት ነው በ-በልሁዬ!»

«ተቃጠለች?»

«አ-አዎ!»

«በስመ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ...!» ብሎ በልሁ ከአማተበ በኋላ ግንባሩን ይዞ በማቀርቀር አሰቀሰ፡፡ ሾፌሩ ራሱ በሁኔታው ተገረመና 'ምን ዓይነት መከራ የወረደበት ቤተሰብ ነው!' አለ በሆዱ፡፡

በልሁ ትንሽ አለቃቅሶ እንባውን ከአፈሰሰ በኋላ ወደ ጥያቄው ተመለሰ፡፡ «ምን ስታደርግ ተቃጠለች?» ሲል በተለይ ሒዋንን እያየ ጠየቃት፡፡

«በሀምሳ አለቃ መኮንን ዳርጌ ሸኚት ማግስት እኔና መርዕድ ወደ አንተና እስቻለው ጋ ለመምጣት ቀጠሮ ይዘን አልነበር?»

«እሺ!»

«ለአንተና ለእስቻለው የሚሆን ምግብ ማዘጋጀት አሰብንና እኔና ታፈሡዬ በሸኙቱ ላይ ተገኝተን እስከምንመለስ ድረስ ትርፌ በምድጃና በኬሮሲን ምድጃ ጥምር ወጥ እያቁላላች እንድትጠብቀን ነግረናት ሄድን፡፡ ምናልባት የኪሮሲን ምድጃ ነዳጅ አልቆባት እጨምራለሁ ስትል እዳር ፈስሶባት ሳይሆን አይቀርም ምድጃው እንዳለ ይነዳል፡፡ በነበልባሉ ሀይል ቀሚሷ ይያያዛል፡፡ በዚያው...» ብላ ሳትጨርስ በልሁ አቋረጣት፡፡

«ሞታ አገኛችኋት?»

«ሸኙቱ ላይ እንዳለን የታፈሡ ጎረቤቶች ሰው ልከውብን ሮጠን ስንደርስ ቀሚሷ በላይዋ ላይ ነዶ ነዶ አልቆ በቃጠሎ ስቃይ ላይ እንዳለች ደረስን፡፡»

«ሐኪም ቤት አልወሰዳችኋትም ነበር?»

«ወስደናት ሐኪሞችም ሊረዷት ተሯሩጠው ነበር፡፡ ነገር ግን ሳይሆን ቀረና የዚያኑ ሌሊት ሞተች፡፡ ሰኞ ዕለት ነው የተቀበረችው፡፡»

በልሁ ክፉኛ አዘነ፡፡ የትርፌ ስቃይ ውስጡን ተሰማው፡፡ ከንፈሩን ነክሶ ራሱን ደጋግሞ ወዘወዘና «ያሳዝናል! በጣም ያሳዝናል!» አለ ደጋግሞ፡፡

ሒዋን እያለቀሰች፣ በልሁ ሆዱ እያዘነና መርዕድ ተጨንቆ መውጫ መግቢያ እንዳጣ መኪናዋ ብዙ ተጓዘች፡፡ አቤላን፣ ለኩንና አፖስቶን አልፋ ወደ ጩኮ ከተማ ተጠጋች፡፡ ሰዓቱም ወደ አራት ሰዓት አካባቢ ተጠጋ፡፡ ሒዋን በልሁን ስለ እስቻለው ሁኔታ ለመጠየቅ ፈራች፡፡ በአንድ በኩል ምላሹን ስትፈራ በሌላ

ቤኩል ትዝታለችውን ሁኔታ ሳይነግረኝ ይቾላል የሚል ሲንት ያዛት። ነገር ግን ነገሩን ለማንሳት አንድ መላ መሞከትና ወዲያው ተጠቀመችበት።

‹አሁን ነገ ወደ አዲስ አበባ ስንሄድ የትርፌን መሞት ለእስቾለው እንነግረዋለን ወይስ...› ብላ ነገሯን ቢአንፓልፓል ተወችው።

በልሁ በፍጥነት መለሰላት። ‹ይኖደዱ አልነበር፤ እስከ አሁን ሆዱ ነገርት ይሆናል።› እሱና ዝም ብሎ በመኪናውት ውስጥ ውጭ ውጭ ያይ ጀመር።

‹ምናልባት ይደነግጥና አንድ ነገር የሆነ እንደሆነ ብዬ ፈርቼ እኮ ነው።› አለቻው ሒዋን ስለ አስቸለው ሁኔታ ምርመራዋን ለመቀጠል።

‹እስቲ እዚያው ስንደርስ እንደ ሁኔታው እናደርገዋለን።›

እንደገና ፀጥታ። መኪናዋ ግን ሄደች፤ ነጎደች። ጨለን አልፋ የዲላን መዳረሻ ጠመዝማዛ መንገድ ተያያዘችው። የዲላ ከተማ መዳረሻ ታየ። አንዳንድ ቤቶችም ብቅ ብቅ አሉ። አንዳንድ ልቦች የፍርሀት ከበሮ ይመቱ ጀመር። መኪናዋ ግን ያለ ሁካብ ፍጥነትዋን እየጨመረች በረረች። የመጨረሻውን የለገዱራ ወንዝ ድልድይ ተሻግራ ከዲላ መውጫ የመጀመሪያ ፍተሻ ኬላ ላይ ደረሰች። ደግነቱ ከአዲስ አበባ ወደ ዲላ ሲሄዱ ፍተሻ የለም። ያም የፍተሻ ኬላ ታለፈ። ዲላ ከተማን በሰሜንና በደቡብ ለሁለት የሚከፍለው ዳገታማ የአስፋልት መንገድ ተጀመረ። ያም ቢሆን ከደቂቃዎች የበለጠ ጊዜ አልወሰደም። ልክ ‹ሰባተኛ መንገድ› ተብሎ በሚጠራው የጠጠር መንገድ ላይ ሲደርሱ በበልሁ አመልካችነት ቀዮታዋ ወደ ቀኝ ታጠፈች። ያ መንገድ በሲቃስተኛ ተሞልቷል። ነጠላቸውን ያሸረጡ ሴቶችና ጋቢ የለበሱ ወንዶች አጥለቅልቀውታል። አንዳንዶቹ ወደ ታፈሡ ቤት አቅጣጫ ይሄዳሉ። አንዳንዶቹ ደርሰው የሚመለሱ ይመስላሉ። ሾፌሩ የገባው ነገር ነበርና የመኪናዋን ጡሩንባ ደጋግሞ ሲያንባርባው ደርሰው ተመላሽ የነበሩ ለቃስተኞች ፊታቸውን ወደ ታፈሡ ቤት አቅጣጫ ይመልሱ ጀመር።

መኪናዋ ከታፈሡ ቤት የሚያደርሰውን የመጨረሻ መንገድ ስትጀምር የታፈሡ ቤት አካባቢ ከነጉድጓዱ ብቅ አለ። ሁለት ድንኳን ተተክሎበታል። የሰው ጉጭ ይርመሰመሳል። መኪናዋ ወደ ድንኳኑ ስትጠጋ ትልቅ ፎቶ ግራፍ ይዛ እንደ አብደት እንደ ስካር በሚያደርጋት ሴት እየተመራ ያ ሁሉ ሰው ወደ መኪናዋ ተንቀሳቀሰ። ሕዝቡና መኪናዋ ሲገናኙ ሴትዮዋ ታፈሡ እንግዳሰው፤ የያዘችው ፎቶ ግራፍ ደግሞ የእስቻለው ፍስሀ። ነገሮች ሁሉ ግልፅ ሆኑ፤ መርዕድ ድንግጥ ሲል ሒዋን ደግሞ ሁለመናዋ ደነዘዘ። መኪናዋ ከሕዝቡ አጠገብ ስትደርስ ቀጥ ብላ ቆመች። ታፈሡ ወደ መኪናዋ የዕቃ መጫኛ ስትዞር በልሁ የጋቢናውን በር ከፈተና ዱብ አለ። በሩ ላይ ቆሞ ፈዝዛ ደንግዛ መንቀሳቀስ ያቃታትን ሒዋን እየተመለከተ «ሒዋን! ፅኚ እንግዲህ! እስቻለው ሞቷል!» አላት።

ሒዋን ግን የሰማችው አትመስልም፤ ፍጥጥ ብላ ቀረች። በልሁ ትናንት መርዕድን በስልክ ባነጋገረበት ሰዓት ‹ነገ ልንመጣ ተነስተናል› ሲለው ‹እሺ ኑ› ብሎ

የመለሰለት በእርግጥም እንዲመጡና ልበ በሽተኛዋ ሒዋን መርዶዋን ከመስማቷ በፊት በእጁ እንድትገባለትና ሊፈጠር የሚችለውን አደጋ በእሱ እገዛ ለማስቀረት አስቦ ነበር። አሁን ግን ከዚያ አደጋ የሚያመልጥ አልመስል አለውና ደነገጠ።

ሒዋን ፈዝዛ መትረት አስፈራው። ብቻ የተቻለውን ያህል ለመሞከር በማሰብ መሪዋር ገፋ እንዲያደርግለት ጠየቀውና ደብልቡን ግን እሱ ራሱ ሰቅስቆ አድርጎ እንደ ወደ መሬት አወረዳት።

«ሒዩ!» ሲል ጠራት ወደ ታች አዘቅዝቆ እያያት።

ሒዋን ግን ዝም። ይልቁንም ዓይኖቿ ስልምልም እያሉ ከአትቶ ውስጥ ወደ ታች ወደ ታች ትንሸራተትበት ጀመር። በልሁ ግራ ሲገባው ትትፍ አላትና ራርፊል ወዳለ ቦታ ላይ ወስዶ አስቀመጣት። ቢደገፋትም አልሆነለትም፤ ልክ ጠትልሰው እንደጣሉት ኅማ ትዘረጋጋበት ጀመር።

በልሁ ፈራና በጩኸት «ታፈዎ! ታፈዎ ድረሺ! ታፈዎ ድረሺ!» እያለ ይጣራ ጀመር። በቃል ታፈሡን እየተጣራ በእጁ ደግሞ ሒዋንን ለማቃናት ይጥራል። ታፈሡ አልሰማችም። እሷ ራሷ በእስቻለው አስከሬን ሳጥን ላይ ትንፈራፈራለች። ሒዋንን የሰው መዓት ከበባት። እየሆነች ያለችውን ነገር ለማየት አንዱ በሌላው ትከሻ ላይ ሲንጠራራ አንዳንዱ ደግሞ «ዘጠር በሉ! ገለል በሉ! አየር ስጧት! አየር...አየር...» እያለ ይጮሀል። ነገር ግን ሁሉም ነገር ምንም አልፈየደም። ሒዋን ሳትመለስ እየሄደች ስለመሆኑ ምልክቶች ታዩ። እንቅስቃሴዋ ሁሉ ቆመ።

መርዕድ ለታፈሡ መልዕክት አድርሶ ኖሯል። ታፈሡ ያንን ሰው ሁሉ እየገፈታተረች ከመሀል ስትገባ በልሁ ቁጭ ብሎ በሁለት እጆቹ መሬት እየመታ ሲጮህ ሒዋን ደግሞ ዝርግትግት ብላ አገኘቻቸው።

«ኣ!» አለች አፏ ትድኀድ መስሎ እስኪከፈት ድረስ። «እኮ ምንድን ነው!?» ካለች በኋላ ሜዳ ላይ ዝርር ያለችውን ሒዋንን ልክ እንደ ልጅዋ ችፈረሲ ጨዋታ ጋለበችና የሒዋንን አንገጭ ወዲያ ወዲህ እያገላበጠች «አንቺ ሒዩ! አንቺ የኔ! አንቺ ሒዩ! ሐዩ! ሒዩ!» ትላት ጀመር። ጆሮዋን በአፍና በአፍንጫ ላይ ብትለትምም ምንም ትንፋሽ አጣች። ጭራሽ እየቀዘቀዘች ሄደችባት።

ታፈሡ እንደዚያው ችፈረሲ እንደጋለበቻት በሁለት እጆቿ ግራና ቀኝ መሬት እየመታች «ዋይ! ዋይ! ዋይ! ዋይ!» አሁንም ደግሞ «ዋይ! ዋይ! ዋይ! ዋይ!» ለሶስተኛ ጊዜ «ዋይ! ዋይ! ዋይ! ዋይ!...» በዙሪያው ያለው ሕዝብ ሁሉ በለቅሶ ተንጫጫ።

የሆነው ሁሉ ሆኗልና ቀጥሎ መሆን ያለበት መሆን ጀመረ። የሒዋን አስከሬን ከበልሁና ከታፈሡ እጅ ወጣ። የመጨረሻ ዝግጅት ለሚያደርጉላት ለገናገሯ ተላልፎ ተሰጠ። በታፈሡ ቤት በር ፊትለፊት በሚገኘው ስፊ መንገድ ላይ የሚደረገው ረግዶ ግን ነዷጅ እንደተጨመረበት እሳት ይብሷ ተቀጣጠለ።

ከቀኑ ወደ ስድስት ሰዓት አካባቢ ሌላ አዲስ ክስተት ታየ። ትናንት በልሁ በመስሪያ ቤት ጓደኞች በኩል የእስቻለውን ሕይወት ማለፍ ለታፈሡ እንዲነገራት አድርጎ ነበርና ታፈሡም በተሰማት መራር የሀዘን ስሜት መሀል የሒዋን አባትና እናት ትገ ብለዋት ልጃቸውን ያላቅሷት ዘንድ በሒዋን በኩል ታውቀው በነበረ የስልክ አድራሻ መልዕክቱ እንዲደርሳቸው አድርጋ ኖሯል። የሒዋን እናትና አባት ‹ሀዘኑን እንዴት መርዶውን እንደሰሙ ይበልጥ ያዘኑት ለልጃቸው ነበር፤ መርዶውን ማታ እንደ ሰሙ ወደ ዲላ ለመብረር ሲዘጋጁ ትችለዋለች› በማለት።

አድረው ከክብረ መንግስት ወደ አለታ ወንዶ፣ ከዚያም ወደ ዲላ በመጓዝ ስድስት ሰዓት አካባቢ በታፈሡ ደጅ ከሚወርደው ሙሾ መሀል ገቡ። የሔዋን እናት ከንፋቸውን ዘርግተው እየሮጡ ወደ ሕዝቡ ሲቀላቀሉ የሚያስሙት ጩኸት «ልጄስ...! ልጄስ...! ልጄን አሳዩኝ! እሙዬን አገናኙኝ!...» እያሉ ነው።

ምን እያሉ እንደሆንና ለጊዜው የራሳቸውን ማንነት ሕዝቡ ያልተረዳላቸው ቢሆንም ነገር ግን ቆየት እያለ ምስጢሩ ሲታወቅ የታፈሡ ጎረቤቶች ጠጋ ጠጋ አሏቸው። ክንዳቸውን ከወዲያና ከወዲህ በመያዝ «ቀስ ይበሉ! ረጋ ይበሉ!» ይሏቸው ጀመር። እሳቸው ግን አሁንም «ልጄ የታለች? እሙዬ የታለች!» ማለታቸውን ቀጠሉ። ባለቤታቸው አቶ ተስፋዬም ከኋላ ከኋላቸው እየተከተሉ ልክ እንደ ሔዋን እናት ይጮሀሉ። ያለቅሳሉ።

የታፈሡ ጎረቤቶች ሰብሰብ አሉና የሔዋንን እናት ወደ አንድ ገለጥ ወዳለ ቦታ ወስደው ትንሽ ለማረጋጋት ከሞከሩ በኋላ ስለሆነው ነገር ፍንጭ ሰጧቸው።

የሔዋን እናት የተሰጣቸውን ፍንጭ የብዥታ ያህል የሰሙ ቢሆንም ሊቀበሉት የፈለጉ አልመሰሉም፤ አሁንም ልክ እንደ በፊቱ «ልጄስ! እሙዬስ! አሳዩኝ እንጂ!» እያሉ ይጮሁ ጀመር። ባለቤታቸው አቶ ተስፋዬ ግን የተሰጣቸውን ፍንጭ ስምተዋልና በድንጋጤ በእስብት ድርቅ አሉ።

የታፈሡ ጎረቤቶች የሔዋንን እናት ሙሉ ለሙሉ ማሳመን ፈለጉ። ከወዲያና ከወዲህ ክንዳቸውን እንደያዙ የሔዋን አስከሬን ወዳለበት ክፍል ይዘዋቸው ገቡ። ግልጥ ግልጥልጥ አድርገው የማይለወጠውን እውነት አሳዩአቸው።

የሔዋን አባት አቶ ተስፋዬ በዓይናቸው ያዩትን ነገር አምነው በመቀበል ቤቱን በጩኸት ሲያደባልቁት የሔዋን እናት ግን ለየት ያለ ስሜት ታየባቸው። ድንገት ከት-ከት-ከት-ከት ብለው ሳቁ። ሳታቸው ግን ድርቅ ያለ ሳቅ። ምንም ለዛ የሌለው ሳቅ። በዚያ ላይ ጥርሳቸውን ግጥጥ፣ ዓይናቸውን ብልጥጥ አድርገው በቅዠት ውስጥ እንዳሉ ሁሉ የቤቱን ጣሪያና ግድግዳ ይቃኙት ጀመር።

የሴትዮዋ ስሜትና ሁኔታ የገባቸው የታፈሡ ጎረቤቶች ሌላ ርምጃ ወሰዱ። የሔዋንን እናት እጆች ጥብቅ አድርገው ያዙ። ከራሳቸው ወገብ ላይ መቀነታቸውን ፈቱ። በዚያ መቀነት ሁለት እጆቻቸውን ግጥም አድርገው አሰሯቸው። ይህ ሁሉ ሲሆን የሔዋን እናት ምንም ዓይነት ድምጽና የእንቢታ እንቅስቃሴ አላሳዩም። የታፈሡ ጎረቤቶች ይህም ሁኔታ የጤንነት አልመሰላቸውም፤ ትቅፍ አደረጉና ወደ ሌላ ክፍል ወስደው አስተመጧቸው። እሳቸውም እርፍ ብለው ተቀመጡ። ድምጽ የለም። እንቅስቃሴ የለም። ዓይናቸውን ብቻ ማንከራተት። ጠባቂ ተመደበላቸው።

የአስቻለው የቀብር ሥነ-ሥርዓት ከቀኑ ስድስት ሠዓት አካባቢ ይፈጸማል ተብሎ ሠዓቱ ለታፈሡ አድርተኞች ተገልጾ ነበር። ነገር ግን ሳይታሰብ ደባል አግኝቷልና መቃብሩ መስፋት ስለነበረበት በዚሁ ምክንያት ለአስር ሰዓት ተላልፏል። ያም ሰዓት ደረሰ። መቃብሩ በእንግዶቹ ልክ ተዘጋጅቶ አልቆ ኖሮ መልዕክቱ መጣ። አስከሬን ሳይሆን አስከሬኖች መኪና ላይ ተጫኑ።

በሀዘን ብዛት ስትዘል ስትፈርጥ የዋለችው ታፈሡ በአስከሬን መጫኛ መኪና ጋቢና ውስጥ ትገባ ዘንድ ብዙ ተለመነች። እሷ ግን እሺ አላለችም። በእሷ ምትክ በልሁ ገባና እሷ በአስቻለውና በሔዋን አስከሬን መሀል ቆማ የመኪናዋን

ጋርቶ መጋለያ ተደግፋ መጓዙን መረጠች። ወጣችና ጉዞ ወደ ቤተክርስቲያን ተጀመረ፤ ወደ መቃብር ቦታ!!

የታፈሡ እንግዳሰው በአስከሬን መጫኛ የመኪና ቋሚ ላይ መውጣት በዚያን ሁሉ አስከሬን አጀቢ ትኩረት ሳበ። ታፈሡ ወትሮም ቢሆን በብዙዎች በጎድ የምትታወቅ ብትሆንም በዕለቱ ደግሞ ለማያውቋት ሁሉ ግልጽ ሆነች። ለቀቅ ያለ የጉጉና የጥቁር ቡራቡሬ ድሪያ ለብሳ በዚያ ላይ በመርፌ ቁልፍ የታሰረች ቢጫ ፎጣ ትከሻዋ ላይ ጣል አድርጋ፣ ያን ክቅላቱ የተነሳ ብርቱካናማ ቀለም ያለውን ጨሌታ የመሰለ ክንዷን ወደ ላይ እየዘረጋች በሀዘን ስትርገበገብ፣ አልፎ አልፎም ደረቷን ስትደቃውና በጉንጯ ሙሉ የሚወርደው እንባዋ ሲታይ ውበቷም የሀዘኗም ጥልቀት፣ የሰውነቷም እንቅስቃሴ ያን አስከሬን አጃቢ ሁሉ ያስደምመው ጀመር።

አስከሬኑ ጥቂት እንደ ተጓዘ ታፈሡ በግራ እጇ የመኪናዋን ጋርቶመጋለያ በመያዝ፣ ቀኝ እጇን ወደ ላይ እየዘረጋች ሌባ ጣቷን ቀስራ በማወዛወዝ ተወልዳ በአደገችበት በወረኢሉ አውራጃ የብቻ የሀዘን እንጉርጉሮ ዘይቤ አልቅሳ ማስለቀስ ጀመረች፣ ለዚያውም በሚያምር ቅላፄና እንደ መረዋ በሚስረቀረቅ ውብና ማራኪ ድምጿ። እንዲህም አለች።

«ላይበላ ነገር ተፈተፈተና፣
ላይጠጣ ነገር ተጠነሰሰና፣
ሁሉም ከንቱ ሆነ አፍ ተለጎመና።»

«ምዎምዎም...» የሚል ድምጽ ተቀበላት ከሕዝቡ በኩል። ከሚኞቹ ታሪክ በመነሳት ሳይሆን እይቀርም ያሰማችው ግጥምና ዜማ የሁሉንም አንጀት በላውና ማልቀስ ያልፈለገውን ሁሉ ያስለቅሰው ጀመር። ታፈሡ የምትጨምረው የእንጉርጉሮ ግጥምና ዜማ ካለ ብሎ ሲጠብቅ ታፈሡም ቀጠለች።

«ምንኛ ችሎት ነው የበየነባችሁ፣
ምን አይነት ዳኛ ነው የወሰነባችሁ፣
በመቃብር እንጂ በምድር ላይቀናችሁ።

ሕዝቡ አሁንም «ምዎምዎ....» በማለት እንደ ንብ መንጋ አስገመገመ። ሁሉም በለበሰው ጋቢና ነጠላ ዓይንና አፍንጫውን ይጠርግ ጀመር። ታፈሡም ሶስተኛውን የእንጉርጉሮ ዜማ ቀጠለች።

«የመከራ ሌሊት አልነጋ ቢላቸው፣
የዚች ምድር ስቃይ ለቅሶ ስልችቷቸው፣
በደል የሌለበት ሌላ ዓለም ታያቸው።»

የሕዝቡ አቀባበል አሁንም ተመሳሳይ ሆነ። የሞቱትን እያስታወሰ ሀዘኑን ከመግለጽ በተጨማሪ ታፈሡ ደግማ የምትለው ነገር በማለት ይጓጓ ጀመር።

ታፈሡ ዲላ ውስጥ ለዓመታት ያህል ስትቆይ በዚያ ቤተክርስቲያን ውስጥ ብዙ የቀብር ሥነ-ሥርዓቶችን ተካፍላለች። እዚያ በተገኘች ቁጥር የምታየው ነገር አለ፣ በአመለካከታቸው ልዩነት ምክንያት ልጆቻቸው የተገደሉባቸው ወላጆች ሁሉ የዕለቱን ሬሳ እየተዉ በልጆቻቸው መቃብር ላይ ሁሉ ሲንፈራፈሩ ብዙ ጊዜ

ተመልክታለች። ምናልባት ያ ሁኔታ ትዝ ብሏትና የዛሬዎቹም የመቃብር እንግዶች መልኩን በተኖረ የፖለቲካ ሰለባዎች መሆናቸው ተሰምቷት ሳይሆን አይቀርም ልክ የቤተክርስቲያኑ ጫፍና የመቃብር ቦታው መታየት ሲጀምር ታፈሡ ጣቷን ወደ ቤተክርስቲያኑ ቀስራ እንዲህ አለች።

«ስማ አንተ ቤተስኪያን ስማ አንተ ደብር፣
አደራ አንተ ጉድጓድ አንተ መቃብር፣
ስንቱን እንደበላህ እንድትመሰክር።»

ታፈሡ በዚህ አላቆመችም፤ ምናልባት ድህነት ምንጊዜም የበደልና የመገፋት መንስዔ እንደሚሆን ተገንዝባ ሳይሆን አይቀርም፣ እንዲሁም የእስቻለውና የሔዋን ዕጣ ፋንታ የዚሁ ማህበራዊ ገፅታ ውጤት መሆኑ አሳዝኗት ሊሆን ይችላል፣ብቻ እንዲህ ስትል አንጎራጎረች።

«እኔ አልኮነንም ሀሰት ተናግሬ፣
እኔ አልታመም ውሸት ተናግሬ፣
ድሃ አልኖረብኝም ድሃዋ ሀገሬ።

ታፈሡ ምንም ፋታ ሳትሰጥ ወዲያው በመቀጠል ደግማ አንጎራጎረች።

«ሰዎች ኡኡ በሉ ምነው ዝም አላችሁ፣
ወገኖቼ ጩኹ ምነው ፀጥ አላችሁ፣
ግፍ ራስ አዙሮ ሲጥል እያያችሁ።»

ሕዝቡ አሁንም እንደ ቀድሞው የታፈሡን እንጉርጉሮ ተከትሎ አለቀሰ። እያደር ደግሞ የታፈሡ ስሜት እየገባው ሄደ። ለካ ታፈሡ የምታለቅሰው ለሞቱት ብቻ አልነበረም፣ የሕዝብ ስሜት ነው የምታንፀባርቀው። ያ ሕዝብ የታፈሡ የእንጉርጉሮ ምስጢር ገባውና ሁሉም ለየራሱ ያለቅስ ጀመር።

ለነገሩማ 'የአሳ ግማቱ ከጭንቅላቱ' ይባል የለ! የተዛባ ሀገራዊ ሥርዓተ-አስተዳደር በሰፈነበት ጊዜና ቦታ ሁሉ ግፍና ጭካኔ፣ እብሪትና ጀብደኝነት መንገሱ አይቀርምና፤ ይህ ደግሞ ወደ ማህበረሰቡ ውስጥ እየተስፋፋ ክፋትና ተንኮል፣ ቅናትና ምቀኝነት እንዲሁም ራስ ወዳድነት ስር እየሰደደ መሄዱ ተፈጥሮአዊ ነውና፤ በዚህ ዓይነት ማህበራዊ ቀውስ ውስጥ በተዘፈቀ ማህበረሰብ ውስጥ የሚኖር ግለሰብም ይሁን ቤተሰብ በአንድ ወይም በሌላ መንገድ መጎዳቱ አይቀሬ ነውና፤ ውድ ከውዱ እየተለየ፣ ቤተሰብ እየተበተነ፣ ለሀዘንና ፀፀት መዳረጉ አይቀርምና ለዚህ ደግሞ የእስቻለውና ሔዋን ዕጣ ፈንታ ምስክር ነውና፤ የታፈሡ እንጉርጉሮ ትርጉም ግልጽ ነው። ሕዝቡም የራሱን ኑሮና ሕይወት ሲመረምር ሁሉም ነገር ስለገባው ሁሉም በየበኩሉ ዘለሳ ዘለሳ ያነባ ጀመር። በእርግጥም ተንሰቅስቆ አለቀሰ።

ቀጣዩ ሥነ-ሥርዓት ሰውን ለመሬት መስጠት ነው። አዎ መሬት፤ የጥቂቶች መጠቀሚያ፤ ነገር ግን የሁሉም ቀበኛ! የእድለኞች መደሰቻ፤ ነገር ግን የእድለ ቢስ ሁሉ መካተቻ! የሰጧትን ቢሰጧት በቃኝን የማታውቅ ግዑዝ ፍጡር፣ መሬት! የዛሬዎቹንም እንግዶቿን አፏን ከፍታ ጠበቀቻቸው። አዎ ገቡላት። ልክ

አፈር መመለስ ሲጀመር ከጉድጓዱ አጠገብ ቆማ ስትንሰቀሰቅ የነበረችው ታፈሡ ሁለት እጆቿን ወደ ሰማይ ዘረጋች። ሁለት ሌባ ጣቶቿን ቀሰረች። ደግማ ልታንጎራጉር እንደሆነ የገባው ሕዝብ የእንጉርጉሮ ግጥሞቹን ለመስማት በጉጉት ፀጥውን አቆመ። እሷም በዚያው በሚሰረቀረቅ ድምጿና በሚያሳዝን ዜማዋ፦

«ደህና ሁኑ እንግዲህ አፈር ይቅለላችሁ፦
ለእውነት ሞታችኋል ገነት ትመቻችሁ፦
ወዮ ለጨካኞች ለገዳዮቻችሁ።»

ስትል ያ ሁሉ ሕዝብ «ዎዎዎዎ....» በሚል የእሮሮ ድምፅ ሲቀባላት ሰማይ ያጉረመረመ መሰለ። ታፈሡ እንደገና ፊቷን ወደ ሕዝቡ መለሰች። የመቃብሩ ቦታ ከፍታ መሬት ላይ ስለነበር እሷ ወደ ታች ስትመለከት ሕዝቡ ሁሉ ይታያታል። ሕዝቡም ከታች ሆኖ ወደ ላይ ሲመለከት ታፈሡን በግልፅ ያያታል። አሁንም ሁለት እጆቿን ወደ ሰማይ ዘርግታ ሌባ ጣቶቿን ቀስራ እንባዋ በጉንጮቿ ላይ በአራት ማዕዘን እየወረደ እንጉርጉሮዋን ቀጠለች፦

«ብዙ አስበው ነበር ከሞት አፋፍ ወዲህ፦
ብዙ ሆነው ነበር ከመቃብር ወዲህ፦
እነሱስ አረፉ ቀሪ አልቅስ እንግዲህ።»

ካለች በኋላ ደረቷን እየደለቀች፣ የእንጉርጉሮዋን የመጨረሻ ቃሎች እየደጋገመች፣ ሁለት እግሮቿን ነቅላ እየዘለለች በማርገድ «ኗሪ አልቅስ እንግዲህ...! ቀሪ አልቅስ እንግዲህ...! ቋሚ አልቅስ እንግዲህ!.. ድሃ አልቅስ እንግዲህ...!» እያለች ታረግድ ጀመር።

በዚህ ጊዜ ከአሁን ቀደም በመቃብር ቦታ ላይ ታይቶ የማይታወቅ ለየት ያለ ሁኔታ መታየት ጀመረ። በዚያ ቦታ የነበረች ሴት ሁሉ ልክ እንደ ታፈሡ ደረቷን እየደለቀች፣ በዚያ ቦታ ላይ የነበረ ወንድ ሁሉ እጆቹን ወደ ውስጥና ወደ ውጭ እያወዛወዘ በመዝለል በድምፅም «ዋይ ዋይ...ዋይ ዋይ! ዋይ ዋይ...ዋይ ዋይ! ዋይ ዋይ...ዋይ ዋይ!» በማለት ታፈሡን ተከትሎ ለረጅም ጊዜ አረገደ።

በዝላዩ መሬት ተንቀጠቀጠች። አባሯው ተነሳ። ሰማዩና ምድሩ አነገነገ። ሳር ቅጠሉ አለቀሰ። የቤተክርስቲያኑ ታቦት ራሱ መቋሚያ ይዞ በማጎንበስ የሚተክዝ መሰለ። ያን አካባቢ የሀዘን ድባብ አጨለመው። ዲላ ከተማ ሆድ እቃዋ ተንቃነቀ።

የረግዶው ማሳረጊያ ደግሞ መራር ለቅሶ። አዎ ዓይኖች ሁሉ ያለ ገደብ አነቡ። አንጀቶች ሁሉ ተንሰፈሰፉ። ሆዶች ሁሉ ተንቦጫቦጩ። በሁሉም ዘንድ ሀዘን፣ በሁሉም ዘንድ ምሬት፣ በሁሉም ዘንድ ቁጭት ሆነ። ሁሉም ስሜት ተቀላቀለና ያን ሁሉ ሕዝብ እንደ ጉብስ አመሰው፤ እንደ ጥሬ ቆላው፤ እንደ ዱቄት ፈጨው! ንፁሀን ስለ ቅን ሀሳባቸው የሞት ዕድል ቢገጥማቸውና በእንባና በሀዘን ብዛት ከሞት ሊነሱ የሚችሉ ቢሆን ኖሮ እስቻለውና ሔዋን የመጀመሪያዎቹ በሆኑ ነበር። ነገር ግን ሊሆን አይችልምና ሳይሆንም ቀረ። አይምሬ መሬት ዋጥ ስልቅጥ አድርጋቸው ዝም ፀጥ አለች። ዓለም እንደ ክፉ እናት ያለ ቀናቸው የሕይወት ጡት

ያስጣለቻቸው አስቻለውና ሒዋን በመሬት አደሩ። የእነሱ ነገር በሁሉም መልኩ አከተመ። በቃ ተደመደመ።

በመቃብር ቦታ የሚፈጸመው ሁሉ ተፈጽሞ ቀባሪና ሀዘንተኛ ወደ ኋላ መመለስ ሲጀምር በርሀብና በሀዘን ብዛት መላ ሰውነቱ የዛለው በልሁ በሁለት የስራ ባልደረቦች ግራና ቀኝ ተደግፎ ይራመዳል። ግን ደግሞ ከጥቂት ርምጃዎች በኋላ ድንገት ሳይታሰብ መላ ሰውነቱን እንደ ብረት የሚያጠነክር ስሜት ሲፈጠርበት ታዩ። እንባ ያፈዘዛቸው ዓይኖቹን ፈትሶፈት ሲወረውር መምህርት ሸዋዬ እህቷን ትቀብር ዘንድ ከእስር ቤት ተፈትዶላት በአንዲት ሴት ፖሊስ እየተጠበቀች ከሕዝብ ፊንጠር ብላ በመቆም ስታለቅስ ዓይቷት ኖሯል።

«ልቀቁኝ!» አላቸው ግራና ቀኝ የደገፉትን የስራ ባልደረቦቹን። እነሱም ስሜቱን አልተረዱምና ምናልባት መደገፉ ለእርምጃ ሳይመቸው ቀርቶ ሊሆን ይችላል በሚል ለቀት ለቀት ሲያደርጉት በልሁ ለማዘናጋት ያህል ሁለትና ሶስት ርምጃዎችን በቀስታ ተራመደ። ቀጥሎ ርምጃውን ፈጠን ፈጠን አደረገ። መጨረሻ ላይ ግን ሮጠ። ሸመጠጠ! ወደ ሸዋዬ። ስሜቱን የተረዳ ማንም አልነበረምና ድርጊቱን በግርምትና በድንጋጤ ከመመልከት በቀር ‹ምነው? ወዴት?› ያለው የለም። እሱ ግን በቅፅበት ከሸዋዬ አጠገብ ደረሰ።

የበልሁን ትክክለኛ ስሜት የተረዳችው ሸዋዬ ናት። «ገደለኝ! አድኑኝ!» እያለች በፍርሃትና በድንጋጤ በመጮህ አጠገቧ ቆማ ትጠብቃት በነበረችው ፖሊስ ላይ ተጠመጠመች። በልሁ ከፖሊሷ ላይ እንደ ሰርዱን ጣላ ፈልቅቆ አላቀቃት። ወዲያው አንገቷን በሁለት እጁ አንቆ ወደ ላይ በማንጠልጠል መልሶ መሬት ላይ ዘረጋት። አንገቷን እንዳነቀ በላይዋ ላይ ተኛባት። በዚህ ጊዜ ሕዝቡ በድንጋጤ ተጯጯኸ። በርካታ ሰው ሊገላግል ትንቅንቁን ቀጠለ። ሴቷ ፖሊስ በእቅሟ በያዘቻት አጭር ዱላ የበልሁን ጀርባ እየደበደበች «ተነስ! ልቀቅ! ልቀቅ!» እያለች ትጮህ ጀመር።

በልሁ ግን ወይ ንቅንቅ! ይልቁንም ከታነቀችው ሸዋዬ ይልቅ የማነቅ ሀይሉን ለማጠንከር እሱ የበለጠ በላይዋ ላይ ይንፈራፈር ጀመር። ማንም ሳያስለቅቀው የልቡን ስለ ማድረሱ እርግጠኛ ሲሆን ብቻ ለቅቋት ተነሳ። በእርግጥም ሸዋዬ መሬት ይዛ ቀረች። ሌላ ጩኸት! ሌላ ዋይታ!

በልሁ ሁለት እጆቹን ወደ ሴቷ ፖሊስ በመዘርጋት «ያውልሽ! ወደሚገባኝ ቦታ ውሰጅኝ!» አላት። ፖሊሷ ለራሷም ፈርታ መላ ሰውነቷ እየተንቀጠቀጠ «ሂድ ቅደም! ወደ ጣቢያ!» አለችው።

በልሁ አላመነታም፣ ወደ ታዘዘበት አቅጣጫ ርምጃ ጀመረ። ሴቷ ፖሊስና የበልሁን መጨረሻ ለማየት የጓጉ በርካታ ሰዎች አጅበውት መጓዝ ጀመሩ።

የሸዋዬን እጣ ፈንታ የተረዳችውና የበልሁን የጉዞ አቅጣጫ ያወቀችው ታፈሡ ግን ስሜቷ እንደ ሌላው ሰው የግርምትና የድንጋጤ አልነበረም፤ በሀዘን ላይ የተጨመረ ሌላ ጥልቅ ሀዘን። ይህንኑ ስሜቷን በቃልና በድርጊት ገለጸችው።

«ኡኡኡኡ...» ስትል ጮኸች ሁለት እጆቿን ወደ ሰማይ ዘርግታ። በልሁን በዓይኗ እየተከተለች በጩኸት አነጋገር «በልሁዬ! አንተም ወደ እስር ቤት? በልሁዬ! የአንተም እጆች ለሰንሰለት? የአንተም እግሮች ለእግር ብረት? ከንደኝ

ሲዝሉ! ያ ወኔህ ሊሟሽሽ!?» በማለት ልክ እንደ አጀማመሯ «ኡኡኡኡ...» እያለች ስትሽከረከር ራሷን አዙሯት ይሁን ወይም ሌላ የመንፈስ ችግር ገጥሟት ብቻ መሬት ላይ ውድቅ አለች። ወድቃም አልበቃት፣ ዝልፍልፍ ዝርግትግት አለች።

ሕዝቡ እየተጯጯኸ ከበባት። ቀና ሊያደርጓት ቢሞክሩም አልቻሉም። በርካታ ሰዎች «መኪና! መኪና! መኪና! ቶሎ በሉ!» እያሉ ጮሁ። አስከሬን ይዛ ወደ ቤተክርስቲያን ሄዳ የነበረችው ፒክአፕ መኪና በዚያው አካባቢ ስለነበረች ወዲያውኑ ቀረበች። ሕዝቡ በመተባበር ታፈሡን እንደ ምንም የወሳንሳ አንስቶ መኪናዋ ላይ አወጣት። ወደ ዲላ ሆስፒታል ይዘዋት በረሩ። የታፈሱን መጨረሻ ለማየት የጓጓ እጅግ በርካታ ሕዝብ መኪናዋን ተከትለው ወደ ዲላ ሆስፒታል ይጉርፍ ጀመር፣ የቻለ በሩጫ፣ ሌላው ደግሞ እያለከለከም ቢሆን በፍጥነት ርምጃ።

በዚህ ጊዜ ለማይድና ምድሩ የተደበላለቀበት መርዕድ እሸቴ ነው። የአስቻለውንና የሒዋንን እጣ ፋንታ፣ የበልሁን ዕድልና የታፈሡን ሁኔታ ሲያይ በምድር ላይ ብቻውን የቀረ መሰለው። ጨነቀው። ከማን እና እንዴት ማምለጥ እንዳለበት ባይገባውም ግን ‹ሂድ ሂድ! ሩጥ ሩጥ!› የሚል ስሜት መጣበት። እዎ ሮጠ፣ ቁልቁል ወደ አንደኛ መንገድ። እዚያም ሲደርስ አልቆመም፣ ቀኙን ይዞ አሁንም ሸመጠጠ። መንገድ ላይ የነበሩ ሰዎች በአግራሞት እየተገረሙ ሲመለከቱት ከዲላ ወደ አለታ ወንዶ የሚወስደውን መንገድ ይዞ ሩጫውን ቀጠለ። ቁልቁለቱን ጨርሶ ወንዙን ተሻገረ፣ በዚያው ፍጥነት ዳገቱንም ተያያዘው። ያንንም በአፍታ ጨረሰው። ለአንዴም ዞር ሳይል ጋራውን ዞረ። እነሆ ከዚያች ዕለት ወዲህ በዲላ ከተማ ውስጥ ታይቶ አያውቅም።

ምሽቱን የሒዋን አባት አቶ ተስፋዬ የመከራ ጉድ ተሸክመው ዲላ ውስጥ ብቻቸውን ቀሩ፣ በአንድ በኩል የልጅ አስከሬን፣ የሸዋዬን። በሌላ በኩል ደግሞ በድንጋጤ ምክንያት ምንኛ የእስትንፋስ አካላቸው እንደ ተጎዳ ሳይታወቅ ዝም ፀጥ ብለው የቀሩ ዱዳ ባለቤታቸውን። ደግነቱ ያዚያኑ እለት ምሽት ሕዝቡ ገንዘብ በማውጣት ሬሳቸውንም ዱዳቸውንም በኮንትራት መኪና አስጭኖ በጠዋት በማለዳ ወደ ክብረ መንግስት ሸኛቸው። ጥቂት ሰዎችም አብረዋቸው ሄዱ።

ሸዋዬን ቀበሩ። የሒዋን እናት ግን የእልጋ ቁራኛ ሆነው ቀሩባቸው። ዛሬም አይናገሩም። እንባቸው ግን ሁሌም በጉንጫቸው ላይ ሲንቆረቆር ይኖራል።

ጊዜ ሄደ፣ ነጎደ። ቀናት በቀናት ሳምንታት በሳምንታታ እንዲሁም ወራት በወራት እየተቀየሩ ያ ዓመትም በሌላ ዓመት ተተካ። በዚህ ጊዜ ውስጥ መርዕድ እሸቴ በዚያው ተወልዶ ባደገበት ሐረርጌ ክፍለ ሀገር ውስጥ እየኖረ ስለመሆኑ ተሰማ። በድሉ አሸናፊ የተፈረደበትን የአንድ ዓመት እስራት ጨርሶ እንንቱን ደፍቶ ዲላ ውስጥ ይኖራል።

በልሁ የፍርድ ሂደቱ ተጠናቆ የአሥራ ሰባት ዓመት እስራት ተፈርዶበት በአዋሳ ወህኒ ቤት ገብቷል። የአስቻለውን የኑዛዜ አደራ ግን ፈጽሟል። እዚያው ዲላ ከተማ ውስጥ በፖሊስ ምርመራ ላይ እንዳለ በሚቀርቡት የመስሪያ ቤት ባልደረቦቹ አማካይነት የአስቻለውና የሒዋን ሐውልት አሰርቷል። በሐውልቱ ላይ አንድ ሜትር ብረት አስቁሞ በዚያም ላይ ስፋቱ እስራ አምስት፣ ቁመቱ ሰባ አምስት ሳንቲ ሜትር የሆነ ላሜራ አስሰጥሮ ጥቁር ቀለም ከአስቀባ በኋላ በዚያ ላይ

የአስቻለውን የኑዛዜ ቃል በነጭ ቀለም በራሱ እጅ ጽሑፍ ዕሯታል። ያ ዕሑፍ ዛሬም ይነበባል፤ ‹እኛ በከንቱ ሞተናል! እናንተ ግን እደራ ራ ራ ራ ራ...› እያለ ያስተጋባል፤ ለሀያው ትውልድ የሚሰማ የሟች ድምፅ!!

ታፈሡ በደረሰባት የመንፈስ መረበሽ ምክንያት ለሁለት ሳምንታት ያህል በዲላ ሆስፒታል ስትታከም ከቆየች በኋላ አገግማ ወጥታለች። ነገር ግን የሥነ-ልቦና ችግር ተፈጥሮባት ብቸኛ ሆናለች። አልቃሻ ሆናለች። ደግነቱ የከፍተኛ ህክምና አገልግሎት ማግኘት ትችል ዘንድ ሐኪሞች በጻፉላት የድጋፍ ደብዳቤ መሰረት የስራ ዝውውር አግኝታ አዋሳ ገብታለች። ለበልሁም ቀርባዋለች። ዘወትር ትጠይቀዋለች። ትክስ ወጥም ታቀምሰዋለች።

ሁለቱ በተገናኙ ቁጥር የጭውጡት ርእሳቸው የፈረሰው የፍቅር ቤተሰባቸው ጉዳይ ነው። በትዝታ እያነሱት ሁል ጊዜ ያለቅሳሉ። ሁልጊዜም ያነባሉ። የዘወትር ፀሎታቸው ደግሞ ‹ምናለ ይቺ መሬት፣ ምናለ ይቺ ምድር፣ ምናለ ይቺ ኢትዮጵያ፣ ለአዘኑ ሁሉ፣ ለተከዙ ሁሉ፣ ለተገፉና ለተነሳቁሉ ዜጎቿ ሁሉ የምህረት አዋጅ አውርዶ ‹በቃ!› ይላቸው ዘንድ ፈጥና እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ብትዘረጋ!!› የሚል ሆኗል።

ተ ፈ ፀ መ

ሌሎች የደራሲው ሥራዎች፡-

- ምዕራባዊት
- አፈላማ

በየመፃሕፍት መደብሩ ይገኛሉ፡፡



አዲስ ሰው ሲፈጠር አዲስ ሀሳብ ይፈልቃል። አዲስ ሀሳብ ጎልቶ ሲወጣ አዲስ ማህበረሰብ ይፈጥራል። አዲስ ማህበረሰብ ደግሞ አዲስ ሀገር ይገነባል።

እነሆ ይህም መጽሐፍ ተረኛዋን 'አዲስ ሰው' ሰንቋል።

እሷም ምዕራባዊት!

የሰው ልጅ ልቡ ሲሰበር የመንፈስ ስቃዩ እስከ ምን ድረስ እንደሆነ በታላቁ ትራጄዲያዊ መጽሐፍ 'ያልታበሱ ዕንባዎች' እይታችኋል። የተሰበሩ ልቦችን ለመጠገን የሚያስከፍለውን መስዋዕትነት ደግሞ ከ 'ምዕራባዊት'

እነሆ ከእኔ እጅ ወጥቷልና ከእንግዲህ የእናንተ ነው። አንብቡት፣ ትደመማላችሁ! አስነብቡት፣ ትመሰገኑበታላችሁ!!

ለማከፋፈልም ሆነ ለአስተያየት
0911 66 69 55

International Leadership Institute Printing Press 0111 22 03 61

ዋጋው 45.25 ብር

እነሆ፣ ነፍሴን ከሥጋዬ ነጥዬ
ከህዝብ ጋር ቀላቀልኳት!

ደራሲው

ከውስጥ ገጾች

«... ያ ሰሜን ኢትዮጵያ፤ የጥንታዊ ስልጣኔ መነሻ፣ የውጭ ወራሪዎች በየዘመናቱ እንገታቸውን ብቅ እያረጉ ሲሰልሉት፣ እየወደሙም ቢሆን ሲወድሙበት የኖረ የዘመናት የጦር አውድማ! ያ ሰሜን ኢትዮጵያ፤ የውጭ ወራሪዎች በፈጠሩት መዘዝ ወንድም ከወንድሙ እየተጋጨ ሲተራረድ፤ አንተም ተው አንተም ተው የሚል ጠፍቶ የእርስ በእርስ መተራረጃ የሆነ የደም መሬት! ያ ሰሜን ኢትዮጵያ፣ ወንድ ልጁን ያላስገበራት ኢትዮጵያዊት እናት የለችምና የወላድ እርግማን የደረሰበት ይመስል ቦምብና መትረየስ እየለበለበው የደጋ በረሀ ሊሆን የተቃረበ ምድር! ያ ሰሜን ኢትዮጵያ፤ ደም እንደ ውሃ እየወረደበት፤ አጥንት እየተከሰከሰበት፣ የሰው ልጅ አስከሬን በአውሬ እየተንተተበት፣ የዋይታ እና ኡኡታ ጩኸት እያደነቀረው ራሱም ሲያለቅስ የሚኖር ያልታደለ ቦታ! ያ ሰሜን ኢትዮጵያ፣ የወደፊት ዕጣ ፋንታው እንኳ ገና በውል ያልታወቀ የሀገር ክፋይ! ታዲያ . . . እንዴት ሆኖ. . .»

★ ★ ★

«. . . ማስተዋል የጎደላቸው አብሪተኞች ስልጣን በያዙበት ጊዜና ቦታ ሁሉ አውቆ መኖርን ያህል የማይድን በሽታ የለም። መስሪ አካሄዳቸው በገባህ ቁጥር ልብህ ይደማል። ሲዋሹና ሲቀጥፉ በሰማህ ቁጥር አንጀትህ ይቆስላል። ዖቍካኔ ተግባራቸውን በምታይበት ጊዜ ውስጥህን ይኮሰኩሰዋል። ያኔ መንፈስህ ይረበሽና አካላዊ ጤናም ታጣለህ፤ ያልታደለች ሀገር ዜጋ ከመሆን የሚመነጭ አለመታደል! ስለዚህ. . .»

"እኔ አልኮነንም ሀሰት ተናግሬ!
እኔ አልታመም ውሸት ተናግሬ!
ድሃ አልኖረብሽም ድሃዋ ሀገሬ።

ሰዎች ኡኡ በሉ ምነው ዝም አላችሁ!
መገኖቹ ጩኹ ምነው ፀጥ አላችሁ!
ግፍ ራስ አዙሮ ሲጥል እያያችሁ።

እኛ በከንቱ ሞተናል፣
"እናንተ ግን አደራ ራራራራ......"

ለአስተያየትዎ
0911 66 69 55

ዋጋው ብር 65.72 ብቻ